ትንቢተ ኢሳይያስ

ከቀድሞ አባቶች ሲወርድ ሲዋረድ የመጣው

ንባቡና ትርጓሜው (በአንድምታ)

ኢትዮጵ ረታና ቤተሰቡ
ማስ ቤተ መጻሕፍት

«ውእቱሰ ነሥአ ደዌነ ወፆረ ሕማመነ»

ኢሳ. ፶፫ ፡ ፬

በሊቃውንት ጉባኤ ተመርምሮ የታተመ ::

አሳታሚ :- ትንሣኤ ማሳተሚያ ድርጅት

አዲስ አበባ
፲፱፻፺፯ ዓ.ም.

www.ethiopianorthodox.org

መግለጫ

አገራችን ኢትዮጵያ መጽሐፍተ ብሉያትን ከምንጫቸው መቀበሏ በታሪክ ሲወሳ፣ ሲነገርም ይኖራል፤ በመሆኑም ሰማይና ምድርን፣ ማለትም የሚታዩትንና የማይታዩትን የፈጠረ እግዚአብሔር መኖሩን በሕገ ልቦና አምና በእውነት ስታመልከው መኖሯ እሙን ነው።

ከተቀበለቻቸው መጽሐፍተ ብሉያት ውስጥ አንዱ ትንቢተ ኢሳይያስ ነው። ትንቢቱን የተናገረውና የጻፈው የአሞጽ ልጅ ኢሳይያስ መሆኑ የታወቀና የታመነ ሲሆን እርሱም በነቢይነት የነበረውና የተናገረው በይሁዳ ነገሥታት በአዝያን፣ በኢዮአታም በአካዝና በሕዝቅያስ ዘመነ መንግሥታት ከ፯፻፶ አስከ ፮፻፹ ከክርስቶስ ልደት በፊት ሲሆን ከተናገራቸው ቃላት ከብዙው በጥቂቱ

1ኛ. ልዑል እግዚአብሔር ከዙፋኑ ላይ ተቀምጦ ሱራፌል ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ ብለው ሲያመሰግኑት ማየቱን (6.5-8)

2ኛ. ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከቅድስት ድንግል ማርያም እንደሚ ወለድ በትንቢት መናገሩን (7፣14)

3ኛ. በድንግልና ተፀንሶና ተወልዶ ወንጌልን ዞሮ ማስተማሩን፣ ም.61፣1-4

4ኛ. በዕለተ ዓርብ ለሰው ልጆች ሁሉ መከራን ተቀብሎ ከዘለዓለም ፍርድና ኩነኔ ነፃ ማውጣቱን፣ ምዕ 53፣1-12 ግልጽ አድርጎ በመናገሩ ከነቢያት ሁሉ በአማኞች ዘንድ ተደናቂነትን ያገኘ ታላቅ ነቢይ ነው።

ከዚህም በመነሳት ሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያን ይህን ትንቢት ደረቅ ሐዲስ ይሉታል ። በዘመኑም ለነበሩ የይሁዳ ነገሥታትና የእስራኤል ሕዝብ ሁሉ በአንድ ልብ ሆነው በእግዚአብሔር ላይ ብቻ እምነት እንዲኖራቸው፣ ጠላት በሚነሳባቸውም ጊዜ ሌላ የጎረቤት እርዳታ እንዳይጠይቁ በጽኑእ ይመክራቸው እንደነበረ ተጽፏል ። (31፣1-3)

ከዚህ በላይ እንደተገለጸው በዘመኑ ሲደረግ የነበረውና በኋላም በዘመነ ሐዲስ የሚደረገውን አምላካዊ ሥራ የተረጎመ የትንቢት መጽሐፍ ነው።

www.ethiopianorthodox.org

በመሆኑም ቀደም ሲል በዳግማዊ አፄ ሚኒሊክ መታሰቢያ በኣታ ለማርያም ገዳም የመጻሕፍተ ብሉያት መምህር የነበሩት መጋቤ ምሥጢር ጌራ ወርቅ ጥበቡ ያስተምሩበት የነበረው ትንቢተ ኢሳይያስ አንድ ምታ ትርጓሜ ቢታተም ለሚያስተምሩ መምህራን፣ ለሚማሩ ደቀ መዛሙርትና ለመላው ሕዝበ ክርስቲያን ጠቃሚ እንደሚሆን አምነንበታል።

እንዲሁም ከላይ ስማቸው የተጠቀሰው የመጻሕፍተ ብሉያት ሊቅ መጋቤ ምሥጢር ጌራ ወርቅ ጥበቡ በሕይወተ ሥጋ ባይኖሩም ድካማቸውና ጥረታቸው በከንቱ እንዳ ይቀር፣ ለመጪውም ትውልድ በቤተ ክርስቲያናችን ቅርስ ሁኖ እንዲኖር በማሰብ በሙሉ የመጻሕፍተ ብሉያትን አንድምታ ትርጓሜ ለማሳተም ካለን ዕቅድ አኳያ በመጀመሪያ መጽሐፈ ኢሳይያስ አንድምታ ትርጓሜ በሊቃውንት ጉባኤ ታይቶና ተመርምሮ በትንሣኤ ማሳተሚያ ድርጅትታችን አሳታሚነት ታትሞ ለሊቃውንቱ፣ ለደቀ መዛሙርቱና ለምእመናኑ እንዲደርስ አድርገናል። በቀጣይም ሌሎቹ መጻሕፍተ ብሉያት በቅደም ተከተል እየታተሙ በሥራ ላይ እንደሚውሉ ስናበሥር መንፈሳዊ ደስታ ይሰማናል።

«ስብሐት ለእግዚአብሔር ከያነ ዘፈጠረ ከመ ናምልኮ »

አባ ጳውሎስ
ፓትርያርክ ርዕሰ ሊቃነ
ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳስ ዘአክሱም
ወእጨጌ ዘመንበረ ተክለ ሃይማኖት

፲፱፻፺፯ ዓ.ም
አዲስ አበባ ኢትዮጵያ

መቅድም

ዘኢሳይያስ ነቢይ በረከተ እግዚአ ብሔር አምላኩ የሃሉ ምስሌነ ለዓለመ ዓለም አሜን፣

ኢሳይያስ ማለት ቅቡዕ እምቅብዓ ትንቢት ማለት ነው፤

ትንቢት የሚገልጥ መንፈስ ቅዱስ ስላደረበት ቅቡዕ እም ቅብዓ ትንቢት ተባለ፤

አንድም መድኃኒት ማለት ነው፤

ኢያሱ ሆሴዕ ኢየሱስ ማለት መድኃኒት ማለት እንደሆነ መድኃኒት መባሉም እንደ ኢያሱ ወልደ ነዌ ባጭር ታጥቆ ጋሻ ነጥቆ ዘገር ነቅንቆ አማሌቃውያንን አጥፍቶ እስራኤልን አድኖ እንደ ኢየሱስ ክርስቶስም ሥጋውን ቆርሶ ደሙን አፍስሶ ሕማማተ መስቀልን ታግሦ፣ አጋንንትን፣ መናፍቃንን አጥፍቶ ምዕመናንን አድኖ፣ መድኃኒት የተባለ አይደለም፤

አባት እናቱ ደጋጎች ናቸውና በትንቢቱ፣ በትምህርቱ እንዲ ያድን አውቀው ኢሳይያስ ብለውታል፣

አንድም ዛሬ እኛ ወንድ በተወ ለደ በአርባ ቀን፣ ሴት በተወለደች በሰማንያ ቀን፣ ከቤተ ክርስቲያን አግብተን፣ አጥምቀን ስም እንድናወጣ፣ እነዚያም በስምንት ቀን ከቤተ ግዝረት ገብተው ስም ያወጣሉና ያንጊዜ አባት እናቱ በትንቢቱ በትምህርቱ እንዲ ያድን አውቀው ኢሳይያስ ብለውታል፤

አንድም ወንድ ልጅ ሲወልዱ ሂደው ደጋጎች ሰዎችን ስሙን ማን እንበለው ይሏቸዋል፣ እነሱም የበቁ ያወቁ ናቸውና ዕገሌ በሉት ይሏቸዋል፣ በትንቢቱ በትምህርቱ እንዲያ ድን አውቀው ኢሳይያስ ብለውታል መድኃኒት ማለት ነው፤

ይህም ኢሳይያስ በእስራኤል ስለ ሦስት ነገር በአሕዛብ ስለ አራት ነገር ተናግሯል። በእስራኤል ስለ ሦስት ነገር እንደ ምነው ቢሉ እስራኤል በደብረ ሲና የተሠራላቸውን ሕግ ቢያፈርሱ በሀገራቸው ሳሉ አባር ቸነፈርእንዲመጣባቸው፣ ቄዋቄ እንዲደረግባቸው፣ ሚጠት እንዲደረግላቸው ተናግሯልና። ለዚህም ለሦስቱ ሥጋዊ መከራ ሦስት መንፈሳዊ አምላል መርገፍ ይሰጡታል፤ እንደ አባር እንደ ቸነፈር ርኀብ እም እግዚአብሔር አግኝቷቸዋል፤

www.ethiopianorthodox.org

መቅድም

ጥቅስ ሞታ ለነፍስ ርኂቅ እም እግዚአብሔር እንዲል ፊልክ ተሰእ ፶፬ እንደ ዔዋዌ ሥጋ ዔዋዌ ነፍስ ተደርጐባቸዋል፣ እንደ ሚጠተ ሥጋ ሚጠተ ነፍስ ተደርጐላቸዋል፤ አባር ቸነፈርና ዔዋዌስ አንድ ወገን ናቸው፤ ይጎራበታሉ ብሎ ሦስተኛ ሰው ሁኖ ሥጋ ለብሶ እንዲያድን አውቆ ሥጋዌ ወልደ እግዚአብሔርን ተናግ ሯል፤ ይወርዳል፤ ይወለዳል፤ ይሰቀላል ይሞታል ብሎ ተናግሯልና፤

በአሕዛብስ ስለ አራት ነገር እንደምነው ቢሉ አሕዛብ አምላከ ሕዝብ ነው እንጂ አምላከ አሕዛብ አይደለም ይላሉ፤ ግድ አምላከ አሕዛብ ወሕዝብ እንደሆነ ተናግሮባ ቸዋልና፣ ሁለተኛ በደበያት እንዲጠፉ ተናግሮባቸዋል፤ በፍዳ ማለት ነው፤ በደበያት አለ እስራኤልን እያጋደሙ ኮር ይወጡባቸዋል፤ ፈረፈር ይሻገሩ ባቸዋል፣ ቢዘህ ፍዳ ይጠፋ ሉና፤ ሦስተኛ አፍርሆ እስራ ኤል በአሕዛብ መከራ ሲያጸና ባቸው አይተው ሕግ ባልተሠ ራላቸው በአሕዛብ እንዲህ መከራ ያጸናባቸው እኛ በደብረ ሲና የተሠራልንን ሕግ ብናፈር ስማ መከራውን እንዴት ያጸናብን ይሆን እያሉ ይፈራ ሉና፤ አራተኛ ትእምርት ነቢዩ ሕዝቡም አሕዛቡም ይጠ ፋሉ ብሎ ይናገራል፤ «ያስተም ራልም ብትል ይሆናል» ኋላም እስራኤል አሕዛብ ሲጠፉ አይተው ያ ነቢይ የተናገረው ነገር አልቀረም፣ እሊያ አሕዛብ ጠፉ እኛም እንጠፋ ይሆናል ብለው ምልክት ያደርጓቸዋልና እንዲህ አለ:: ይኸስ አይደለም አፍርሆና ትእምርትስ አንድ ወገን ናቸው ይጎራበታሉ ብሎ፣ አራተኛ በነቢይ በካህን ሳያናግር እንዳያጠፋቸው ተና ግሮባቸዋልና፤ ጥቅስ ሠረይነ ሰብአ ወኢያሕየውነ (ኤር.ጸ ፶፩÷፱)፤

ወኮነ ጽድቅነ ከመ ፀርቀ ትክቶ:: (ኢሳ.ም. ፷፬ ÷ ፮)፣

ፈወስናሃ ለባቢሎን ወኢተፈወሰት እንዲል፤ (ኤር.ም. ፶፩ ÷ ፱፣

ይኸም ተጽፎ ሲነበብ ሲተረ ጐም ከነቢያት እስከ ሐዋርያት ደረሰ፣ ሐዋርያትም ለቀሌምን ጦስ ሰማንያ አንዱን መጻሕ ፍት ቆጥረው ሲሰጡ አንድ መጽሐፈ ኢሳይያስ ብለው ቆጥረው ሰጥተውታል፣ ይኸም ለከንቱ አልተጻፈም፣ እኛ ልን መከርበት እኛ ልንገሠጽበት

ተጽፎልናል፤ ወኵሉ ዘተጽሕፈ ለተግሣጸ ዚአነ ተጽሕፈ ከመ በትዕግሥትነ ወበተወክሎ መጻ ሕፍት ንርከብ ተስፋነ እምኀበ እግዚአብሔር እንዲል፤ ሮሜ ምዕ. ፲፭ ቍ ፬፤ ይኸ አርእስት ነው፣ ሠለስቱ ምእት ለመጻሕ ፍት አርእስት ሲሰጡ አርአስት ሰጥተውታል፤ እሱ ግን ነገሩን ራዕይ ዘርእየ ኢሳይያስ ብሎ ያመጣዋል::

ምዕራፍ ፩

፩፣ ራእይ ዘርእየ ኢሳይያስ ወልደ አሞፅ፣

ትንቢት ዘተነበየ ነገር ዘተና ገረ ሲል ነው፤ የአሞፅ ልጅ ኢሳ ይያስ ያስተማረው ትምህርት የተናገረው ነገር ይኸ ነው፤

ዘርእየ በእንተ ይሁዳ ይህ በእንተ ያለስፍራው የገባ ነው የክፉ ነው ሰዎች እንዲማረኩ፤

ወበእንተ ኢየሩሳሌም፣

ሀገሪቱ እንድትጠፋ አይቶ የተናገረው ነገር ይኸ ነው ፤

አንድም ዘርእየ በእንተ ይሁዳ ጥቃቅኑ አህጉር ኢየሩሳሌም መዲናይቱ እንድትጠፋ አይቶ የተናገረው ነገር ይኸ ነው፤

በመዋዕለ ኦዝያን ወኢዮአታም፣ ወአካዝ ወሕዝቅያስ እለ ነግሡ በይሁዳ፣

እለነግሡ ለይሁዳ እለ ነግሡ በይሁዳ ነገሥታተ ይሁዳ ይላል፣ ሦስቱም አብነት ነው፤

በይሁዳ በነገሡ በነዚህ ዘመን አይቶ የተናገረው ነገር ይኸ ነው፤

እነዚህንስ ለምን ለይቶ አነሣ ቸው ቢሉ በእነዚህ ዘመን ብመክራቸው ባስተምራቸው አንሰማም ብለው ጠፉ ለማለት፣ አንድም አሁን ወደፊት እየተ ረተረ የሚያመጣቸው ነውና እንደ አርእስት አነሣቸው::

፪፣ ስማዕ ሰማይ፣

እስከዚህ አርእስት ነው፣ ነገሩን ከዚህ ይጀምራል፣ ሰማይ የእስራ ኤልን ነገር ስማ ማለት ዝናም ለዘር ጠል ለመከር አትስጥ::

ወአፅምዒ ምድር፣

ምድርም የእስራኤልን ነገር ስሚ ማለት የዘሩብሽን አታብ ቅዪ፣ የተከሉብሽን አታጽ ድቂ፣ አንድም ስማዕ ሰማይ ሰማይ ልዑላኑ፣ ወአጽምኢ ምድር፣ ምድር ትሑታኑ የእስ ራኤልን ነገር ስሙ፤

www.ethiopianorthodox.org

አንድም ሰማይ መላእክት፣ ምድር ደቂቀ አዳም፣ የእስራኤልን ነገር ስሙ፣ እስራኤልን በተጣላበት ወራት በጎ በጎዎችን አታማልዱኝ ይላቸዋልና፤

አንድም ሰማይ የእስራኤልን ነገር መስክር፣ ምድርም የሰማይን ምስክርነት አድምጪ፤ እግዚአብሔር በተጣላበት ወራት ሰማይን ዝናም ለዘር ፣ ጠል ለመከር፣ አትስጥ ይለዋል፣ ይሽን ይነሳል፤

ምድርንም የዘሩብሽን አታብቅዪ፣ የተከሉብሽን አታጽድቂ ይላታል፣ ይሽን ትነሳለችና፤

እስመ እግዚአብሔር ነበበ ከመዝ፡

እግዚአብሔር እንዲህ ብሎ ተናግሯልና፤

ወይቤ ውሉደ ወለድኩ፣

በሕገ ልቡና ልጅ ወለድሁ፤

ወአልሐቁ ፣

በሕግ መጽሐፋዊ ልጅ አሳደግሁ ብሏልና፤

አንድም ውሉደ ወለድኩ በፍቅር በሃይማኖት ልጅ ወለድሁ ብሏልና፤

ወአልሐቁ፣

በመና በደመና ልጅ አሳደግሁ ብሏልና፤

እሙንቱሰ ዐለዉኒ፣

እነሱ ግን በኃጢአት በክህደት ጸንተው ወነጀሉኝ ብሏልና፤

አንድም ኃጢአት ሠርተው፣ ጣዖት አምልከው ወነጀሉኝ ብሏልና ፤

ፒ፣ ላህምኒ አእመረ ዘአጥረዮ፣

ዘቀነዮ ዘኩነኖ ሲል ነው ላምስ እንኳ የገዛውን ጌታውን ያውቃል፤ ትች::

ወአድግኒ ምቅማሐ ወቤተ እግዚኡ፡

አህያም ገለባ የሚቅምበትን የጌታውን ቤት ያውቃል፤ ትች፤

አንድ ገዝ የሆነ እንደሆነ ከዋለበት ሲመጣ ከብዙ መንጋ ተለይቶ ወደ ጌታው ቤት ይሄዳልና፤

እስራኤልሰ ኢያእመሩኒ ወሕዝብየኒ ኢጠየቁኒ፡

አሥሩ ነገድ፣ ሁለቱ ነገድ አላወቁኝም፣ አልተረዱኝም፤

አንድም አላወቁኝም አልተረዱኝምና ሰማይ የእስራኤልን ነገር ስማ፤

እነዚያ ከላሙ ከአህያው አንሰው እኔን ከባለ ላሙ ከባለ አህያው አሳንሰው አላወቁኝም አልተረዱኝምና፤

ዐይኑ ዐነው ቢሉ፡ ስማ አልፋው፣ አነው ቢሉ መስክር ሲል ነው፤

አንድም ያዘዋውሩታል ዐይኑ ዐነው ቢሉ መስክር አልፋው አነው ቢሉ ስማ፤

አንድም ስማዕ ሰማይ፣ ሰማይ የአይሁድን ነገር ስማ ማለት ዝናም ለዘር ጠል ለመከር አትስጥ፤

ወአዕምዓ ምድር፣

ምድርም የአይሁድን ነገር አድምጪ ማለት የዘሩብሽን አታብቅዪ የተከሉብሽን አታጽድቂ፣ አንድም ሰማይ ልዑላኑ ምድር ትሑታኑ የአይሁድን ነገር ስሙ፤

አንድም ሰማይ መላእክት ምድር ደቂቀ አዳም የአይሁድን ነገር ስሙ በተጣላበት ወራት አታማልዱ ይላቸዋልና፤ አንድም ሰማይ የአይሁድን ነገር መስክር ወአዕምዓ ምድር፣ ምድርም የሰማይን ምስክርነት አድምጪ፣ እግዚአብሔር በተጣላበት ወራት ሰማይን ዝናም ለዘር፣ ጠል ለመከር አትስጥ ይለዋል፣ ይሽን ይነሣል፤

ምድርንም የዘሩብሽን አታብቅዪ፣ የተከሉብሽን አታጽድቂ ይላታል፣ ይሽን ትነሳለችና፤

አንድም ስማዕ ሰማይ ብለህ መልስ፣ አብ የክርስቶስን ነገር መስክር፤

ወአዕምዓ ምድር ፣

ቤተ ክርስቲያንም በዮርዳኖስ የመሰከረውን የአብን ምስክርነት አድምጪ፤

እስመ እግዚአብሔር ነበበ ከመዝ፣

እግዚአብሔር እንዲህ ብሎ ተናግሯልና፤

ወይቤ ውሉደ ወለድኩ፣

በትንቢት ልጅ ወለድሁ፤

ወአልሐቁ፣

በሱባዔ ልጅ አሳደግሁ ማለት ሱባዔ እያስቈጠርሁ፣ ትንቢት እያናገርሁ አሳደግሁ ብሏልና::

እሙንቱሰ ዐለዉኒ፣

እነሱ ግን ወነጀሉኝ ማለት ሩቅ ብእሲ ወልደ ዮሴፍ አሉኝ፤ ላህምኒ አእመረ ዘአጥረዮ ዘፈጠሮ ሲል ነው ላምስ እንኳ የፈጠረውን ጌታውን ያውቃል፤

www.ethiopianorthodox.org

አንድም ለሰው ጥሪት አድርጎ የሰጠውን ጌታውን ያውቃል፤

ወአድግኒ ምቅማሐ ወቤተ እግዚኡ፣

አህያም ገለባ የሚቅምበትን የጌታውን ቤት ያውቃል፤ ቤተ እግዚኡ ያለው ባለቤት የሌለው ዝርዝር ነው፤ ሀገሩ እንዲህ ሆነ፣ ጌታው እንዲህ አደረጉ እንደ ማለት ያለ ነው፤

እመቤታችን ለመቄጠር በወጣች ጊዜ ከባለላሙ፣ ከባለ አህያው ቤት ደርሳ ወለደችው፤ ከዚያ አግኝተው አሚሙቀውታል፤ ወአስተማወቅዎ እስ ትንፋሰ አድግ ወላህም እንዲል ቅዳሴ ማርያም፤

አንድም ቤት ያለው አምቦ ነው እመቤታችን ለመቄጠር በወጣች ጊዜ ከዚህ ደረሰች፣ ዮሴፍ ጎጆም እንደሆነ ሠርቶ ላት፣ ዳስም እንደሆነ ጥሎላት ከዚያ ወለደችው፤ በዚያ ልማድ አምቦውን ሲሉ መጥተው አማ ሙቀውታል፤

አንድም ቤት ያለው የነዳዊት፣ የነሰሎሞን፣ የነኢዮስያስ ቤት ነው፤ የቀደሙ ነገሥታት ቤታ ቸውን በጨው መሸጋ ይሠሩ ታል፤ በሜዋፄ ፈርሶ እንስሳት እየጋጡ አጐድጕደውታል፤

እመቤታችን ለመቄጠር በወጣች ጊዜ ከዚያ ደረሰች፤ ዮሴፍ ጎጆም እንደሆነ ሠርቶ ላት፣ ዳስም እንደሆነ ጥሎላት ከዚያ ወለደችው፤ ከዚያ አግኝ ተው አሚሙቀውታል::

አንድም ቤት ያለው ጎል ነው፤ የጌታውን ቤት ጎልን አወቀ::

እስራኤልሰ ኢያእመሩኒ፣ አይ ሁድ አምላክ ወልደ አምላክ መሆኔን አላወቁኝም፡

ወሕዝብየኒ ኢጠየቁኒ፣

ሐና ቀያፋም አልተረዱኝም፡ አላወቁኝም፣ አልተረዱኝምና፤

ስማዕ ሰማይ ብለህ እሠር፤

፬፣ አሌሎ ለሕዝብ ኃጥእ ዘምሉዕ ዓመፃ፣

ዓመፅን ለተመላ ለኃጥእ ወገን ወዮለት፤

ዘርዕ እኩያን፤

አዝርዕተ እኩያን ሲል ነው፤ ለክፉዎች ልጆች ወዮላቸው፤

አንድም እንዳለ ይሆናል፣ ክፉዎች ለሆኑ ልጆች ወዮላ ቸው፤

ወውሉድ ጽልሕዋን፣

ውሉደ ጽልሕዋን ይላል፣ ለከዳ ተኞች ልጆች ወዮላቸው፤

አንድም እንዳለ ይሆናል፣ ከዳተ ኞች ለሆኑ ልጆች ወዮላቸው፤

እፎ ኀደግምዎ ለእግዚአብሔር፣

እግዚአብሔርን እንዴት ተዋ ችሁት፣ እንዴት ተዋችሁት፣ እንዴት ተዋችሁት፤

ወአመዓዕክምዎ ለቅዱሰ እስራኤል፣

ጽንዐ እስራኤል ክብረ እስራ ኤል እግዚአብሔርን እንዴት አሳዘናችሁት፣ እንዴት አሳዘ ናችሁት፣ እንዴት አሳዘናች ሁት፡

፭፣ እፎ እንከ ትቄስሉ እንዘ ትዌስኩ ኃጢአተ በዲበ ኃጢአት፣

በኃጢአት ላይ ኃጢአት እየሠ ራችሁ በመከራ ላይ መከራ እንዴት ትቀበሉ ይሆን፤

አንድም በኃጢአት ላይ ኃጢ አት እየሠራችሁ እንዴት በመከራ ላይ መከራ ትቀበላ ላችሁ፡

ኵሉ ርእስ ለሕማም፣

ይከውን ያለበት ነው፤ ካልተ መለሳችሁስ የሰው ሁሉ ራስ ለመገጠብ ይሆናል፤

ትብትብ ምንጣፍ በመሸከም፤

ወኵሉ ልብ ለኃዘን፣

የሰው ሁሉ ልቡና ለኃዘን ይሆናል፤

አንድም ኵሉ ርእስ ለሕማም ንጉሡ ለመከራ ይሆናል፤ ርእስ አለው ከሁሉ በላይ ነውና፤

ወኵሉ ልብ ለኃዘን ሊቀ ካህናቱ ለኃዘን ይሆናል፣ ልብ አለው ለባዊ ነውና፤

አንድም ኵሉ ርእስ ለሕማም ንጉሡ ለመከራ ይሆናል፣ ርእስ አለው ራስ በጠጉር ተከቦ እንዲኖር ንጉሡም በሠራዊት ተከቦ ይኖራልና፤

ወኵሉ ልብ ለኃዘን፣ ነቢዩ ለኃዘን ይሆናል፤ ልብ አለው የልቡን ምሥጢር አውጥቶ የሚናገር ስለሆነ፤

አንድም ኵሉ ልዑላኑ ወኵሉ ልብ አዋቆች ለኃዘን ይሆናሉ፤

፮፣ እምእግር እስከ ርእስ ዘኢኮነ ቍስለ፣

ከእግር ጀምሮ እስከ ራስ ድረስ ያልቈሰለ የለም፣ ራሳቸው ትብትብ ምንጣፍ በመሸከም ይመለጣል፣ እግራቸውን እሾሁ እንቅፋቱ ያቈስለዋል፤ የቀረ ሰውነታቸውን ለፈለማ እያሉ ይወጓቸዋልና፤

ወኢኮነ ፍቅወተ፣

ያልተገመሰ የለም፤

www.ethiopianorthodox.org

ወኢኮነ ጸልዐ ዘይመግል፡

የሚመግል ቍ ስ ል ባይደለ ቍስል ያልቈሰለ የለም፡

ወአልቦ ከመ ይጠይዕዎ ሥራየ ወኢይፀምምዎ ወኢይቀብዕዎ፡

ወ. ዘ. ነው፡ አልቦ አኮ ነው፡ ይቀብዕዎ ወይፀምምዎ ሲል ነው፡

መድኃኒት ቀብቶ የሚያሽሩት ቍስል ባይደለ ቍስል ያልቈሰለ የለም፡ እንዲህ ማለት ማርከው ወስደው አያሳርፉ ቸውምና፡

አንድም እ ን ዳ ለ ይሆናል፡ ቍስሉ ሲሽር ለምዕ ይሆናል፡ ያንን የሚያድን መድኃኒት ይቀቡታልና፡

አንድም ኢይቀብዕዎ ወኢ ይፀምምዎ ይላል፡ ይኸውም መድኃኒት ቀብቶ የሚያሽ ሩት ቍስል አይደለም፡

አንድም እምእግር እ ስ ከ ርእሰ ዘኢኮነ ቍስለ፡

ከእግር ጀምሮ እስከ ራስ ድረስ የዘመድ ቍስል ባይደለ በባዕድ ቍስል ያልቈሰለ የለም፡

ወኢኮነ ፍቅዓተ፡

የዘመድ ግ ም ሳ ች ባይደለ በባዕድ ግምሳች ያልተገመሰ የለም፡

ወኢኮነ ፀልዐ ዘይመግል፡

የሚመግል የዘመድ ቍስል ባይደለ በ ባ ዕ ድ ቁስል ያልቈሰለ የለም፡

የዘመድ ቍስል የሆነ እንደሆነ ቀቅ ተፍቶ አነክሶ ያሽሩታል ለእስራኤል ግን ይኸን ሁሉ የሚያደርግላቸው የለምና፡

አንድም የዘመድ ቍስል የሆነ እንደሆነ ፀቡን አስክሰው ያስታ ርቁታል ቍስሉን መድኃኒት ቀብተው ያድኑታል፡ እሊኸን ግን ወግተው ገምሰው ጥለ ዋቸው ይሄዳሉ እንጂ ይኸን ሁሉ አያደርጉላቸውምና፡

አንድም እፎ እንከ ትቈስሉ እንዘ ትዌስኩ ኃጢአተ በዲበ ኃጢአት ብሎ ነበርና እምእግር እስከ ርእስ ዘኢኮነ ቍስለ አለ፡ ከቋሚ ከሰንሚ ጀምሮ እስከ ንጉሡ ድረስ አፍአዊ ቍስል ባይደለ በውስጣዊ ቍስል ያልቈሰለ የለም፡

ወኢኮነ ፍቅዓተ፡

አፍአዊ ግምሳች ባይደለ በውሳ ጣዊ ግ ም ሳ ች ያልተገመሰ የለም፡

ወኢኮነ ጸልዐ ዘይመግል፡

የሚመግል አፍአዊ ቍስል ባይ ደለ በውሳጣዊ ቍስል ያልቈ ሰለ የለም፡

ወአልቦ ከመ ይጠይዕዎ ሥራየ ወኢይፀምምዎ ወኢይቀብዕዎ፡

መድኃኒት ቀ ብ ቶ የሚያሽ ሩት አፍአዊ ቍስል ባይደለ በውሳጣዊ ቍ ስ ል ያልቈሰለ የለም ምሥጢሩ ኃዘን ዔዋቂ ነው፡

አንድም ከሰባ ዘመን አስቀድሞ መድኃኒት ሚ ጠ ት ን ሰጥቶ የሚያሽሩት አ ፍ አ ዊ ቍስል ባይደለ በውሳጣዊ ቍስል ያልቈሰለ የለም፡

አንድም ኵሉ ርእስ ለሕማም ርእስ ክርስቶስ ለመከራ ይሆ ናል። (ጥቅስ) ንሕነ አባል ወውእቱ ርእስ እንዲል አፈ. ወ. ድ. ፮፡

ወኵሉ ልብ ለኃዘን የሰው ሁሉ ልቡና አምስት ሺህ ከአምስት መቶ ዘመን ለኃዘን ይሆናል፡

ከዚህ በታች ያለው ከፊተኛው ትርጓሜ ጋራ አንድ ነው፡ አንድም ኵሉ ርእስ ለሕማም ወኵሉ ልብ ለኃዘን እምእግር እስከ ርእስ ዘኢኮነ ቍስለ ወኢኮነ ፍቅዐተ ወኢኮነ ፀልዐ ዘይመግል ወአልቦ ከመ ይጠ ይዕዎ ሥ ራ የ ወኢይፀምምዎ ወኢይቀብዕዎ እፎ እ ን ከ ትቈስሉ እንዘ ትዌስኩ ኃጢ አተ በዲበ ኃጢአት ብሎም ይጽፋል፡

፮ ምድርከሙኒ በድወ፡

ትከውን ያለበት ነው፡ አገራችሁ ምድረ በዳ ትሆናለች፡

አንድም እንዳለበት ይሆናል አገራችሁ ምድረ በዳ ሆነ፡

ወአህጉሪከሙኒ ው ዕ ያ በእሳት፡ አገራችሁ በእሳት ተቃጠለ፡

ለበሐውርቲከሙኒ ፀር ይበልዖ በቅድሜከሙ፡

አገራችሁን እያያችሁ ስልም ናሶር ናቡከደነፆር ያጠፋዋል፡ አገር እያዩት ሲጠፋ ያሳዝ ናልና በቅድሜክሙ አለ፡

አንድም ፀር ዘበቅድሜክሙ ይላል፡ ስልምናሶር በፊታችሁ ያጠፋዋል፡

ያማስኖ ወያመዘብሮ ፀር፡

ስልምናሶር ናቡከደነፆር ፈጽሞ ያጠፋዋል፡

አንድም ያማስኖ ወያመዘብሮ ነኪር፡

ልዩ ጠላት ስልምናሶር ናቡከ ደነፆር ያጠፋዋል፡

አንድም ያማስኖ ወያመዘብሮ ፀር ነኪር ይላል፡ ትርጓሜው አይለወጥም፡

www.ethiopianorthodox.org

አንድም ፀር ነኪር ባዕድ ጠላት ያጠፋዋል፣ የዘመድ ጠላት የሆነ እንደሆነ የጓመት ልብስ የዕለት ጉርስ ይተዋል፤

የባዕድ ጠላት ግን አይተው ምና፡

፮፣ ወትትነደግ ወለተ ጽዮን ከመ ልገተ ዐቃቢ ቀምሐ፣

የጽዮን ልጅ እንደ ፍሬ ጠባቂ ጎጆ ትጠፋለች፡

ፍሬ ጠባቂ ፍሬውን ለቅሞ ጎጆውን አ ፍ ር ሶ እንዲሄድ ሰዎችን ማርከው ገንዘባቸውን ዘርፈው አገራቸውን ተኩሰው ሂደዋልና ወለተ ጽዮን ያላቸው መላውን ቤተ እስራኤልን ነው፡ የአማራ ልጅ፣ የሳሻም ልጅ፣ የሸዋ ልጅ እንዲሉ፡

አንድም ጽዮን ያላት የዳዊት ከተማ ናት፣ ጽዮን አላት ትተድግለችና ወለት ያላት የሰሎሞን ከተማ ናት፣ ወለት አላት በኋላ ናትና፡

አንድም ጽዮን ያላት የሰሎሞን ከተማ ናት፣ ጽዮን አላት ትባልጣለችና፡

ወለት ያላት የዳዊት ከተማ ናት፣ ወለት አላት ታንሳለችና፡ አንድም ወለተ ሕማ ይላል፡ ሕማ የምትጠብት ምዕመን ሲለ ነው፡

ወከመ ዳሰ ዐቃቢ ወይን፣

እንደ ፍሬ ጠባቂ ጎጆ ትጠ ፋለች፣

አንድም ወከመ ዳሰ ዐቃቢ ወይን፣ ወ ይ ኑ ን ከመውደቅ እንደሚጠብቀው እንደ ዳሱ ትጠፋለች በ ክ ረ ም ት ግዘፍ እንዲነሣ ብለው ከመሬት ጥለውት ይከርማሉ፣ ኋላ በበጋ ያነሡታልና፡

አንድም ፍሬውን ከመርገፍ እንደሚጠብቀው እንደ ዘለላው እንደ ጎረጉ ትሆናለች፡

ወከመ ዘገር ኀዕርት፣

በጦር ታጥራ እንደነበረች፡

ቅትልት እ ስ ራ ኤ ል እንደወ ንት፡

ትጽርት ሰባት ቅጽር እንደ ነበራት፡

ንሕልት እንደ ፈረሰች እንደ ኢያሪኮ ትሆናለች፡

ገባዔ

፱፣ ወሶበ አኮ እግዚአብሔር ዐባያት ዘአትረፈ ለነ ዘርዐ፡

አሸናፊ እግዚአብሔር አሥሩን ነገድ አስማርኮ ሁለቱን ነገድ፣ ሁለቱን ነገድ አ ስ ማ ር ኮ ትሩፋንን ያስተረፈልን ባይሆን።

ከመ ሰዶም እምኮነ ወከመ ገሞራ እመሰልነ፣

እንደ ሰዶም በሆነ ነበር፣ ገሞራ ንም በመሰልነ ነበር፣ እነዚያ ዘር ም ክ ን ያ ት አጥተው እንደጠፉ እኛም ዘር ምክንያት አጥተን በጠፋነ ነበር፡

አንድም ወ ሶ በ አ ኮ ብ ለ ህ መልስ ፡

አሸናፊ እግዚአብሔር ዐበይት ነቢያትን አጥፍቶ ደቂቅ ነቢያ ትን፣ ደቂቅ ነቢያትን አጥፍቶ ካህናትን መዘምራንን ያስቀረ ልን ባይሆን እንደ ሰዶም በሆነ ነ በ ር ፣ ገሞራንም በመሰልነ ነበር ፡

እነዚያ የሚመክራቸው፣ የሚያ ስተምራቸው አጥተው እንደ ጠፉ እኛም የሚመክረን የሚያ ስተምረን አጥተን በጠፋነ ነበር፡

አንድም ወ ሶ በ አኮ ብ ለ ህ መልስ፡

አሸናፊ እግዚአብሔር ዐበይት ነቢያትን ደቂቅ ነቢያትን ፣ ካህናትን ፣ መ ዘ ም ራ ን ን አጥፍቶ፣ አሳልፎም ብትል ይሆናል፣ ሐዋርያትን ሰብዓ አርድእትን ቅዱሳት አንስትን ከእምቢታ ከክህደት ያስቀ ረልን ባይሆን እንደ ሰዶም በሆንነ ነ በ ር ገሞራንም በመሰልነ ነበር፡

እነዚያ መምህር አብነት አጥ ተው እንደጠፉ እኛም መምህር አብነት አጥተን በጠፋን ነበር፡ አንድም ካ ህ ና ት መዘምራን ካለፉ በኋላ ሐ ዋ ር ያ ት ን፣ ሐዋርያት ካለፉ በኋላ ሰብዓ አርድእትን፣ ሰብዓ አርድእት ካለፉ በኋላ ሊ ቃውንትን ያስነሣልን ባይሆን ሃይማኖት አጥተው እ ን ደ ጠ ፉ እንደ ሰዶም እንደ ገሞራ ሰዎች በሆንነ ነበር እነሱንም በመሰልነ ነበር፡

አንድም አ ሸ ና ፊ እግዚአብ ሔር እመቤታችንን ከመርገመ ሥጋ ከመርገመ ነፍስ ያስቀ ረልን ባይሆን እንደ ሰዶም በሆነ ነበር ገሞራንም በመሰልነ ነበር፣ እነዚያ የነፍስ አማላጅ አጥተው እንደጠፉ እኛም የነፍስ አማላጅ አጥተን በጠ ፋን ነበር፡

፲፣ ስምዑ ቃለ እግዚአብሔር መላእክተ ሰዶም፣

ከመ ሰዶም እምኮነ ብሎ ነበርና

የሰዶም አለቆች የእግዚአብ ሔርን ነገር ስሙ፡

www.ethiopianorthodox.org

ወአፅምዑ ሕገ እግዚአብሔር ሕዝበ ገሞራ፣

ወከመ ገሞራ እመሰልነ ብሎ ነበርና፤

የገሞራ ወገኖች የእግዚአብሔርን ሕግ ስሙ፤

መላእክተ ሰዶም ሕዝበ ገሞራ ማለቱ፤

የትውልድ አይደለም የግብር ነው፤

፲፩፣ ለምንት ሊተ ብዝኀ መሥዋዕቲክሙ ይቤ እግዚአብሔር፣

መሥዋዕቱን እያቀረብንልህ መላእክተ ሰዶም ሕዝበ ገሞራ ትለናለህ ትሉኝ እንደሆነ በኃጢአት ሳላችሁ የምታቀርቡት የመሥዋዕቱ ብዛት ለምኔ ነው፤

ጽጉብ አነ እመሥዋዕተ ሐራጊት ወስብሐ አባግዕ፣

የጊደሩን የበጉን መሥዋዕት የጠገብሁ ነኝ ማለት የበጎ የበጎዎችን መሥዋዕት የጠገብሁ ነኝ፤

አንድም ሐራጊት የሙሴ የአሮንን መሥዋዕት፣ ወአልህምት ይላል፣ የዳዊት የሰሎሞንን መሥዋዕት፣ አባግዕ የኢዮስያስን መሥዋዕት የጠገብሁ ነኝ ኢዮስያስ ለፋሲካ እልፍ በግ ሠውቷል፤

አንድም ዘይኤይስ ያለበት ነው፣ ከዚህ ሁሉ የሚበልጥ ቅዳሴ መላእክትን የጠገብሁ ነኝ፤

አንድም የልጄን መሥዋዕ ትነት የጠገብሁ ነኝ፤

ኢይፈቅድ ደመ ላህም ወጠሊ፣

የላሙን የበጉን መሥዋዕት አልሻም ምነው ሠዉልኝ ብሏቸው የለምን ቢሉ በግብዕ ሳሉ ላም ያመልኩ ነበርና በለመዱት ለመሳብ ነው እንጂ ለጌታ የሚረባው የሚጠቅመው ሁኖ አይደለም፤

አንድም ጥንቱንም አልሻ፤

አንድም የልጄን መሥዋዕ ትነት ነው እንጂ የላሙን የበጉን መሥዋዕት አልሻም፤

፲፪፣ ወእመኒ አምጻእክሙ ኢታስ ተርእዩኒ፣

መሥዋዕቱንም ብታመጡ በባለ ሟልነት አትታዩኝም፤

አንድም ዛሬ አምጥታችሁ እንደሆነ ነገ አታሳዩኝም ወደቤተ ጣዖት ትወስዱታላችሁ፤

አንድም ኢታርእዩኒ አታሳዩኝ ይላል፣ የቁጣ አነጋገር ነው፤

መኑ ጎሠሦ ለዝንቱ እምእዴክሙ፣

መሥዋዕታችሁን ከእጃችሁ ማን ሻው፣ ኢይፈቅድ ደመ

ላህም ወጠሊ ያለውን ያስተረጐማል፤

ወኢትደግሙ እንከ ከይደ ወወድየ፣

ዳግመኛ ወደ ቤተ መቅደስ አትገቡም ማለት ቤተ መቅደስን አትረግጧትም፣ ተማርካችሁ ትሄዳላችሁ፣ አንድም ዛሬ መጥታችሁ እንደሆነ ነገ አትደግሙም ወደ ቤተ ጣዖት ትሄዳላችሁ፤

አንድም ኢትድግሙ አትድገሙ ይላል የቁጣ አነጋገር ነው፤

፲፫፣ ወእመኒ አምጻእክሙ ስንዳሌ ከንቱ፤

ልጠ ጐርዶ የወጣ ስንዴም ብታመጡ በኃጢአት ሳላችሁ ከንቱ ነው፣ አልቀበለውም::

ወዕጣንክሙኒ ርኩስ፣

ዕጣናችሁም ርኩስ ነው አልቀበለውም፤

አስሕርቲክሙኒ፣

ሠርቀ ወርኃችሁ አስርሕቲ ክሙኒ ቢል እሸት ነዶአችሁ ርኩስ ነው፣ አልቀበለውም፤

ወሰንበታቲክሙኒ፣

የዓመቱን ቅዳሜ ቈጥሮ ሰንበታት ብሎ አበዛ፤ አንድም እሑድን በትንቢት ጨምሮ ቈጥሮ፤

ወዕለተክሙኒ ዐባየ ኢይፈቅድ፣

በዐለ ፋሲካን አልሻም፤

ወጸመክሙኒ ፣

ጾማችሁንም አልሻም፣ ያንጊዜ ምን ጾም አላቸውና እንዲህ አለ ቢሉ እኛ ዛሬ ዓርብና ረቡዕን እንድንጾም እነዚያም እሑድንና ማክሰኞን፣ ማክሰኞንና ሐሙስን ይጾሙ ነበርና፤

አንድም በጥቅምት ባሥር ቀን ዕለተ ዮሴፍን ይጾማሉና አባቶቻቸው ዮሴፍን በግፍ ሸጠውት ነበርና ዕዳ አታድርግባቸው ሲሉ ይጾሙ ነበር፤

ዕረፍተክሙኒ ወጽርዓተክሙኒ፣

አንድ ወገን ዓመተ ኀድገትን አልሻም፤

አንድም ዕረፍተክሙኒ ዓመተ ኀድገትን፤

ወጽርዓተክሙኒ በኢዮቤልዩ በአርባ ዘጠኝ በአርባ ዘጠኝ ዘመን የሚያከብሯትን አምሳኛይቱን ዘመን ወቀድስዋ ለይእቲ ዓመት ዘኃምሳ ኵላ ክረምታ የሚላትን፤

አሪት ዘሌ. ምዕ. ፳፭ ቁ. ፲፤

፲፬፣ ወሠርቀ ወርኀክሙኒ፤

የላይኛውን እሸት ነዶ ቢሉ ይኸነን የአሥራ ሁለቱ ሠርቀ

www.ethiopianorthodox.org

ወርኅ የ ላ ይ ኛ ው ን የአሥራ አንድ ሠርቀ ወርኅ ቢሉ ይህ የሚያዝያ ሠርቀ ወርኅ ማለት ነው፤

(ጥቅስ) ወ ዝ ን ቱ ይኩንክሙ ቀዳማየ አውራኅ ብሏቸዋልና፤ አሪት ዘዘ.ምዕ.፲፪ ቁ. ፪፤

የአሥራ አንዱን ሠርቀ ወርኅ የሚያዝያን ሠርቀ ወርኅ አልወድም፤

ወበዕላተክሙኒ ጸልዑት ነፍስየ፣

በዐለ ሰዊትን በዐለ መጸለትን ሰውነቴ ጠላች፤

ሰቈራረ ኮንክሙኒ፣

የምታጸይፉኝ ሆናችሁ ማለት ር ኒ ቅ እምእግዚአብሔር አገኛችሁ፤

ወጠለቁክሙ፣

ሰለቸኋችሁ፣ ፈ ታ ኋ ች ሁ፣ ጌታን በመርዓዊ፣ ቤተእስራኤልን በመርዓት ይመስላቸዋልና፣ ፈታኋችሁ አለ፤

ወኢይሠረ ለክሙ ኃጢአተክሙ፣

ኃጢአታችሁን ይቅር አልላች ሁም ንስሓ ከገቡ ይቅር የማይላ ቸው ሁኖ አይደለም፣ አይገ ቡም ሲል ነው፤

፲፩፣ ወሶበ ታነሥኡ እደዊክሙ ኀቤየ እመይጥ ገጽየ እምኔክሙ፣

እጃችሁን ለመሥዋዕት ቃላች ሁን ለጸሎት ወደኔ ብታነሡ ገጸ ረድኤቴን ከናንተ እመል ሳለሁ፤

ወእመኒ አብዛኅክሙ ምህላክሙ ኢይሰምዐክሙ፣

ምህላችሁንም ብታበዙ አልሰ ማችሁም ብቻ ለ ብ ቻ ሁኖ የሚጸልዩት ምህላ ተሰብስቦ የሚጸልዩት ምህለላ ይባላል፤

እስመ ደመ ምሉዕ እደዊክሙ፣

እጃችሁ ደምን ተመልታልና፤ አንድም እስመ ደም ምሉዕ ውስተ እደዊክሙ፣ በእጃችሁ ደም ተመልታልና፤

አንድም የድህውን ገንዘብ ቀም ታችሁበእጃችሁ ተመልታልና፣ ደክሞ ሠርቶ የሚያገኘው ስለሆነ ደም አለው፣ ደመወዝ እንዲሉ፤

፲፮፣ ተሐፀቡ ወንጹሐነ ኩኑ፣

ይስማንስ ካላችሁ ንስሓ ገብታ ችሁ ከኃጢአት ንጹሓን ሁኑ፤

ወአዕትቱ እከየ እምነፍስክሙ፣

ቂምን ተንከልን ከልቡናችሁ አርቁ፤

እምቅድመ አ ዕ ይ ን ት የ ሕድጉ እከየክሙ፣

ክፉውን ኃጢአት ሁሉ ከፊቴ አርቁ፣ ኃ ጢ አ ት እየሠሩ

አያውቅብንም ብለዋልና፤ እም ቅድመ አዕይንትየ አለ፤

፲፯፣ ወተመህሩ ገቢረ ሠናይ፣

በጎ ሥራ መሥራትን ተማሩ፤

ጎሥዋ ለጽድቅ፣

አሠርቱ ቃላትን ሺት፤

አንድም እውነት ፍርድን ሺት፣

ወአድኅኑ ግፉዐ፣

የተበደለውን እውነት ፈርዳ ችሁ አድኑ፤

ፍትሑ ለዕጓለማውታ፣

እናት አባቱ ጥለውት ለሞቱ ፍረዱ ማለት ችግረኛ መሆኑን አይታችሁ ርዱት፤

ወአጽድቁ ዕቤረ፣

ባልቴቲቱን እውነተኛ በሏት፣ ሐሰት ይዛ ብትመጣ ማለት አ ይ ደ ለ ም ፤ እውነት ይዛ ብትመጣ አታድሉባት፤

፲፰፣ ንዑ ንትዋቀስ ይቤ እግዚአ ብሔር፣

እግዚአብሔርኑእንዋቀስ አለ፣ ሰውና እግዚአብሔርማ ተዋቅሶ ይሆናልን ኑ እንታረቅ ሲል ነው፤ ሲታረቁ ከሆድ፣ ሲታ ጠቡ ከክንድ ነውና፤

እመኒ ኮነ ኃጢአትክሙ ከመ ኪኪ፣

ኃጢአታችሁ እ ን ደ ሱፋላ በርኖስ ቢጠቁር ፣

አፀዓድዎ ከመ በረድ ፣

እንደ በረድ ነጭ አደርገዋለሁ፤

ወእመኒ ቈሐ ከመ ለይ አነጽሖ ከመ ፀምር፣

እንደ ጁኽ ግምጃ ቀይ ቢሆን እንደ ብዝት አነጻዋለሁ፤ ኃጢ አቱን አ ነ ጻ ዋ ለ ሁ ማለት አይደለም፤ ኃጢአቱን አርቄ እናንተን አነጻችኋላሁ ሲል ነው፤ አንድም እመኒ ኮነ ኃጢ አትክሙ ከመ ኪኪ አጸአድዎ ከመ በረድ ንስሐስ ከገባችሁ ኃጢአታችሁ እንደ ቁራ ቢጠ ቁር እንደ በረድ ነጭ አደር ገዋለሁ፤ ወእመኒ ቈሐ ከመ ለይ አነጽሖ ከመ ፀምር፣ እንደ ጁህ ግምጃ ቀይ ቢሆን እንደ ብዝት አነጻዋለሁ ማለት አስተ ሠርይላችኋለሁ፣ አንድም ከመ ኪኪ ባለው ከመ ቀርመዝ ይላል፣ እንደ ቀደመው ሁለቱ ንም ያስተረጕማል ፤ አንድም ኪኪ በርኖስ ቀርመዝ ቁራ ኃጢአታችሁ እንደ በርኖስ አንድም እንደ ቁራ ቢጠቁር እንደ በረድ ነጭ አደርገዋለሁ፤ እንደ ጁኽ ግምጃ ቀይ ቢሆን

www.ethiopianorthodox.org

እንደ ብዝት አነፃዋለሁ፤ ኃጢ
አቱን አነጻዋለሁ ማለት አይ
ደለም፤ ኃጢአታችሁን አርቄ
እናንተን አነጻችኋለሁ ሲል
ነው፤

፲፱፣ ወእመሰ ፈቀድክሙ ወሰማዕ
ክሙኒ በረከተ ምድር ትበልዑ፣

የምመክራችሁን ምክር ወዳ
ችሁ ብ ት ሰ ሙ ኝ የኢየሩሳ
ሌምን ድልብ ትበላላችሁ፤

፳፣ ወእመሰ አበይክሙ ሰሚያትየ
መጥባሕትየ ትበልዓክሙ፣

መስማቱን ግን እምቢ ብትሉ
ሥልጣኔ ታጠፋችኋለች፣ መጥ
ባሕትየ ማለቱ ባርበኛ ግሥ
ነው፤

አንድም ሾተሌ ታጠፋችኋ
ለች፣ የስልምናሰር የናቡከደ
ነፆር ሾተል በተፈጥሮ ገንዘቡ
ናትና የኑርሱን ሰርሰ ሰጥቶ
ተናገረ፤

አስመ ከማሁ ነበበ አፉሁ ለእግዚአ
ብሔር፣

እግዚአብሔር ይጥፉ ብሎ
አዟልና፤

፳፩፡ እፎ ኮነት ዘማ ሀገረ ጽዮን
ማእምንት፣

የታመነች የጽዮን መዲና ኢየሩ
ሳሌም እንዴት ዘማ ሆነች
ዝሙት የሴትና የወንድ ብቻ
አይደለም፣ እግዚአብሔር ያላዘ
ዘውን ሁሉ መሥራት ዝሙት
ነውና እንዲህ አለ፤

(ጥቅስ) እስመ ዘማዊ ዲያብሎስ
ዘአኀዘክሙ ኢ ክ ህ ለ ይዕቀ
ብክሙ እንዲል፤

እንተ ምልዕት ፍትሐ፣

እውነት ፍርድ ይፈረድባት
የነበረ፤

ወኀደረ ውስቴታ ጽድቅ፣

ምግባር ትሩፋት ይሠራባት
የነበረች አ ን ድ ም አሠረቱ
ቃላት ይነገሩባት የነበረች
የጽዮን መዲና ኢየሩሳሌም
እንዴት ዘማ ሆነች፤

ወይእዜሰ ፈያት ወቀተልት፣

መልዕዋ ያለበት ነው፤ ዛሬ
ግን ነፍሰ ገዳዮች ወንበዴዎች
መሉባት፤

፳፪፡ወርቅኪኒ ወብሩርኪኒ ተምያን፣

ወርቅሽ ብርሽ ግብዝ ነው፤
በወርቁ ናስ፣ በብሩ ቆርቆሮ
ይጨምሩበታልና፤

ወመያስያንኪኒ ይቶስሑ ማየ
በውስተ ወይን፣

መሸተኞችሽም በወይኑ ውሀ
ይቀላቅሉበታል፣ ባለወይን ባለ
ዋጋ ብትልም ይሆናል፣ ባለ
ጊዜ ሽሌውን በርደዴውን
ታቀምሰዋለች፤ ዘወር ሲል፣
አንድ ዋንጫ ሁለት ዋንጫ
ውሀ ቀድታ ትለቅበታለች፤

አንድም ወርቅኪኒ ወብሩር
ኪኒ ብለህ መልስ፣ ሕግሽ
ሕገ አሪት ግብዝ ነው፤ ሕጎ
ጣያት የተቀላቀለበት ነው፣

ወመያስያንኪኒ ይቶስሑ ማየ
በውስተ ወይን ነቢያተ ሐሰት፣
ካህናተ ጣያትም በነቢያት
በካህናት ት ም ህ ር ት ላይ
ሐሰተኛ ት ም ህ ር ት ይቀላ
ቅላሉ ማለት ነቢያት ምግባር
ትሩፋት ሥሩ ትማ ረካላችሁ
ብለው ካስተማሩ በኋላ ሰላም
ሰላም አይሏችሁ ዔዋቄ የለም
እያሉ ያስተምራሉና፤

አንድም ሕግሽ ሕገ አሪት
ግብዝ ነው፤ ድኅነተ ነፍስ
አያሰጥም፣ እለፈ ካላት በኋላ
ሲሠሯት ቢገኙ ግብዝ የምታ
ሰኝ ስለሆነች፤

ወመያስያንኪኒ ይቶስሑ ማየ
በውስተ ወይን፣

መምህራኖችሽ ጸሐፍት ፈሪሳ
ውያንም በሕገ ወንጌል ላይ
ሐሰተኛ ትምርትን ይቀላ
ቅላሉ፣ ወንጌል እንበለ አሪት፣
ጥምቀት እ ን በ ለ ግዝረት
አይረባም፣ አይጠቅምም እያሉ
ያስተምራሉና፤

፳፫፡ መላእክትኪኒ ሐያድያን፣

አለቆችሽ ቀ ማ ኞ ች ናቸው፤
አንድም፣ ዳ ኞ ች ሽ ቀማኞች
ናቸው፤ ቀማኞች የሚሆኑ እሊህ
ሱቱፋኑ ስረቅት ከሌቦች ጋራ
የሚተባበሩ ናቸው፤ ከሌቦች
ጋራ የሚተባበሩ እሊህ፤

መስተናድአን፣

አንዱ በ ፊ ት አ ን ዱ በኋላ
እየሆኑ የሚኼዱ ናቸው፤

አንድም መስተንዕዳን ይላል
ዛሬማ እንጂ ከ እ ገ ሌ ቤት
ሂጂ ውሻ ሳይጮኽብኝ ሰው
ሳይነቃብኝ እንዲህ ያለ ገንዘብ
አመጣሁ ባለ ጊዜ ምን አቦ
ጐልማሳ እያሉ የሚያደናንቁ
ናቸው፤

አንድም መስተፋጥናን ይላል፣
ሰውን የሚያፋጥኑ ናቸው፤
አንተ ስረቅ እኔ ላጥልቅ (ልጠ
ብቅ) እያሉ፤

አንድም መስተናሥአን ይላል፣
ሰው አንገቱን ደፍቶ ባዩት
ጊዜ ምን ሁህ አንገትኽን
ደፍተኻል ይሉታል፣ ቢርበኝ
ቢጠማኝ ይላቸዋል፤ ምነው
እንደኛ ሰ ር ቀ ኽ ቀምተህ
አ ት በ ላ ም እያሉ ሰውን
የሚያነሣሡ ናቸው፤

ወያፈቅሩ ሕልያነ ወይፈቅዱ
ይሚጡ ፍትሐ፤

መማለጃ ተ ቀ ብ ለ ው ፍርድ
ሊለውጡ ይወዳሉ፤

www.ethiopianorthodox.org

ወኢያየምው ዕቤረ ብእሲተ፣

ባልቴቲቱን ሴት አይሰሚትም፣

ወኢይፈትሑ ለዕንለ ማውታ፣

እናት አባቱ ጥለውት ለሞቱ አይፈርዱም ማለት ችግረኛ መሆኑን አ ይ ተ ው አይረዱ ትማና፣

፳፱፡ በእንተዝ ከመዝ ይቤ እግዚ አብሔር ጸባአት፣

ወያፈቅሩ ሕልያነ ወይፈቅዱ ይሚጡ ፍትሐ ብሎ ነበርና፣

መማለጃ ተ ቀ ብ ለ ው ፍርድ ሊለውጡ ስለሚወዱ አሸናፊ እግዚአብሔር እንዲህ አለ፡

አሌ ሎሙ ለኃያላነ እስራኤል፣

ለመኳንንተ እ ስ ራ ኤ ል ሲል ነው፣

ለኃያላነ ፈርያን እንዲል ለእስራ ኤል አለቆች ወዮላቸው፡

ኢይቈርር መዓትየ እምኀዕለ ዐርየ፣

መዓቴ መቅሠፍቴ ከጠላቶቼ አይርቅም፡

አንድም ኢ ያ ቈ ር ር ይላል መዓቴን መ ቅ ሠ ፍ ቴ ን ከጠ ላቶቼ አላርቅም፡

ወእትቤቀሎሙ ለጸላእትየ፣

ጠላቶቼን ተ በ ቅ ዬ አጠፋቸ ዋለሁ፡

፳፭፡ ወአመጽእ እዴየ ላዕሌኪ፣

እደ መዓቴን ባንች አመጣለሁ፡

ወአረስነኪ፡

ቤተ እ ስ ራ ኤ ል በመከራው አግልሻለሁ

ወእፈትን ዛኀለኪ በከውር፡

ዝገትሽን በከውር እፈትነዋለሁ ማለት ክፉ ክፉውን ለይቼ አጠፋለሁ፡

ወአሴስል ኵሉ ናዕከኪ፣

ቅልቅሉን ኃጢአትሽን፡

አንድም ናሕከኪ ይላል ጽኑዕ ኃጢአትሽን አርቃለሁ፡

ወአውዕዮሙ ለከሀድያን፣

ከሀድያንን አጠፋቸዋለሁ፡

ወአዐትቶሙ እምኔኪ ለኵሉሙ ዐማዕያን፣

ዐመፀኞችን ሁሉ ከ አ ን ቺ አርቃቸዋለሁ፣

፳፮፡ ወእሠይም ለኪ መኳንንተኪ ከመ ትካት፣

አለቆችሽን እንደ ዳዊት እንደ ሰሎሞን ጊዜ እሾማቸዋለሁ፡

ወመመኅከርተኪ ከመ ቀዲሙ፣

መማክርቶችሽንም እንደ ሙሴ እንደ አሮን ጊዜ እሾማቸዋለሁ፡

ወእምዝ ትሰመዪ ሀገረ ጽድቅ ደብረ አህጉረ ጽዮን ማእምንት፣

ከሚጠት በኋላ የታመንሽ የጽዮን መ ዲ ና ኢየሩሳሌም አሠርቱ ቃ ላ ት የሚነገሩባት አገር ትባያለሽ፡

፳፯፡ እስመ በጽድቅ ይድኅኑ ዒዉዋንኪ፣

ምርኮኞችሽ እስራኤል በእው ነት ይድናሉና፣ (ጥቅስ) ውነሊቆ ሰብዓ ዓመት ባለው ኤር. ፳፭÷፲፱ ወእምድኅረ ሰብዓ ዓመት ይሔውፀክሙ እግዚአ ብሔር በሣህል ባለው ይድ ናሉና፡

ወበምጽዋት፡

ቸርነቱን ምጽዋት አድርጎ ሰጥቷቸው፡

አንድም በጽድቅ በሃይማኖት ወበምጽዋት በምግባር ይድ ናሉ፡

አንድም ወእሰይም ለኪ፣ ስለዓበ ይት ነቢያት ፈንታ ሐዋር ያትን፣ ስለ ደቂቅ ነቢያት ፈንታ ሰባ አርድዕትን እሾም ልሻለሁ፡

ወእምዝ ትሰመዪ ሀገረ ጽድቅ ደብረ አህጉረ ጽዮን ማእምንት፣

የታመንሽ የምእመናን መዲና ቤተ ክርስቲያን ከአምስት ሺህ አምስት መቶ ዘመን በኋላ ወንጌል የ ሚ ነ ገ ር ባ ት አገር ትባያለሽ፣ እ ስ መ በጽድቅ ይድኅኑ ዒ ዉ ዋ ን ኪ፣ ምርኮ ኞችሽ፣ ነፍሳት በሐሙስ ዕለት ወበመንፈ ቃ ለዕለት እትወለድ እምወለተ ወ ለ ት ከ፣ ባለው ይድናሉና ፡

ወበምጽዋ ት፣ ሥጋውን ደሙን ምጽዋት አድርጎ ሰጥቷቸው፡

አንድም በጽድቅ በሃይማኖት ወበምጽዋት በምግባር ይድ ናሉ፡

፳፰፡ ወይትቀጠቀጡ ኃጥኣን ወዐማዕያን ኀቡረ፣

ኃጥአን ዐማዕያን አንድ ሁነው ይጠፋሉ፡

ኃጥአን ያ ላ ቸ ው ሃይማኖት ያላቸው ም ግ ባ ር የሌላቸው እንደኛ ያሉ ናቸው፡ ዐማዕ ያን ያላቸው ሃይማኖትም ምግባርም የሌላቸው ናቸው፡

ወይጠፍዉ ኵሎሙ እለ ኀደግዎ ለእግዚአብሔር፣

እግዚአብሔርን በሕግ በአም ልኮት የተዉት ሁሉ ይጠ ፋሉ፡

፳፱፡ ወይትኀፈሩ በአማልክቲሆሙ በዘመከሩ ለሊሆሙ፣

እሳቸው በሠሯቸው በጣዖታቱ ያፍራሉ፡

www.ethiopianorthodox.org

ወይትኀፈሩ በ ም ሕ ራ ማ ቲ ሆ ሙ ዘፈተዉ፣

በወደዱት በመስገጃቸው ያፍ ራሉ፤

፴፣ ወይከውኑ ከመ ዕፀ ጠርቤንቶስ እንተ ነገፈት ቈጽላ፣

ቅጠሏ እንደ ረገፈ እንደ ቡጥም (ደረቅ) እንጨት ይሆናሉ፣ ቅጠሉ ረግፎ ግንዱ እንዲቀር ገንዘባቸው አልቆ ያለ ገንዘብ ባዶዋችን ይቀራሉ፤

ወከመ ገነት እንተ አልባቲ ማይ፣

ውሀ እ ን ደ ሌ ለ ባ ት ተክል ይሆናሉ፤ ያች ከሥሯ ተነቃቅላ እንድትወድቅ ሥር መሠረታ ቸው ይጠፋል፤

፴፩፣ ወይከውን ኃይሎሙ ከመብርዐ ባሕሩስ፣

የእስራኤል ኃይላቸው ሠራዊ ታቸው እ ን ደ መቃ መስዬ ገለባ ይሆናል፤

ወምግባራቲሆሙ ከመ አፍሐመ እሳት፣

ኃጢአታቸውም እንደ እሳት ይሆናል ማለት አጥፊ ይሆናል፤

አንድም ወይከውን ኃይሎሙ ብለህ መ ል ስ፤ የእስራኤል ኃይላቸው እንደ መቃ መስዬ ገለባ ይሆናል፤ ያ ደካማ ነው፤ ኃይላቸውም ደካማ ነውና፤

ወምግባራቲሆሙ ከመ አ ፍ ሐ መ እሳት፣

የእስራኤል ኃጢአታቸው እንደ እሳት ፍም ነው ማለት አጥፊ ይሆናል፤ የ እ ሳ ት ፍህም ቢቆሙበት እ ን ዲ ጎ ዳ ኃጢአ ታቸውም ይጎዳቸዋልና፤

አንድም ወይከውን ኃይሎሙ ከመ ብርዐ ባሕሩስ፣ የእስራኤል ኃይላቸው ሠራዊታቸው እንደ መቃ መስዬ ገለባ ይሆናል፣ ያ እንዲሰበር ድል ይነሣሉና፤

ወምግባራቲሆሙ ከመ አፍሐመ እሳት፣

የነስልምናሶር የነናቡከደነፆር መድፋቸው ነፍጣቸው መርቡ ጣቸው እ ን ደ እሳት አጥፊ ይሆናል ፤ አንድም የነስልም ናሶር የነናቡከደነፆር ኃይላቸው ሠራዊታቸው እ ን ደ መቃ መስዬ ገለባ ይሆናል፤

ወምግባራቲሆሙ ከመ አፍሐመ እሳት፣

የነቂሮስ የ ነ ዳ ር ዮ ስ መድፋ ቸው ነፍጣቸው መርቡጣቸው እንደ እሳት አጥፊ ይሆናል፤

ወይውዕዩ ኃጥአን ወዐማፅያን ኀቡረ፣

ኃጥአን ዐማፅያን አንድ ሁነው ይጠፋሉ፤

ወየኃጥኡ ዘያጠፍእ ሎሙ እሳቶሙ፣

መዓቱን መቅሠፍቱን የሚያር ቅላቸው ያ ጣ ሉ፣ መዓት መቅሠፍት በ ብ ዙ ወገን ይርቃልና፤ እንደ ሙሴ ያለ ነቢይ የተገኘ እንደሆነ መዓት መቅሠፍት ይርቃል፤ ጠስየኒ እመጽሐፈ ሕይወትከ እምት ጥ ስ ዮ ሙ ለእሎንቱ ብሎ መዓቱን መቅሠፍቱን እንዳ ራቀ፤ ዘፀ.ም ፴፪ ቁ.፲፤ እንደ ኢያሱ ያለ መስፍን የተገኘ እንደሆነ መዓት መቅሠፍት ይጠፋል፤

ለምንት አ ዕ ድ ዎ አእደውኮ ለገብርከ ወ ና ሁ እስራኤል ሜጠ ዘባኖ ቅድመ ፀሩ ብሎ መዓቱን መቅሠፍቱን እንደ መለሰ፤ ኢያ ም.፯ ቁ.፯፤ እንደ ዳዊት ያለ ንጉሥ የተገኘ እንደሆነ፤ መዓት መቅሠፍት ይመለሳል፤ ምንተ ገብሩ እሉ አባግዕ እንዘ አነ ኖላዊሆሙ ዘአበስኩ ዛቲ ኃጢአት ትኩን ላዕሌየ ወ ላ ዕ ለ ቤተ አቡየ ብሎ መዓቱን መቅሠፍቱን እንደመለሰ፤ ነገ. ካልዕ ም.፳፬ ቁ. ፲፯ ፤ እንደ ሕዝቅያስ ያለ የተገኘ እ ን ደ ሆ ነ መዓት መቅሠፍት ይመለሳል፣ ርኢ ትዕይርቶ ለ ሰ ና ክ ሬ ም ብሎ መዓቱን መ ቅ ሠ ፍ ተ ን እንደ መለሰ፤ ኢሳ.ም ፴፯ ቁ. ፲፯፤ እንደ ሰብአ ነነዌ ያለ የተገኘ እንደሆነ መዓት መቅሠፍት ይመለሳል፤ ን ስ ሓ ገብተው መዓቱን መ ቅ ሠ ፍ ቱ ን እንደ መለሱ::

ምዕራፍ ፪

፩፣ ቃል ዘኮነ ኀበ ኢሳይያስ ወልደ አሞፅ፣

ዘመጽአ ዘተነግረ ሲል ነው፣

ከአሞፅ ልጅ ከኢሳይያስ ዘንድ የመጣ የተነገረ የእግዚአብሔር ቃል ይህ ነው፤

ዘርእየ በእንተ ይሁዳ ፣

ይህ በእንተ በስፍራው የገባ ነው፤ የበጎ ነው ሰዎች እንዲ መለሱ፤

ወበእንተ ኢየሩሳሌም፣

ሀገሪቱ እንድትቀና አይቶ የተናገረው ነገር ይህ ነው፤

አንድም በእንተ ይሁዳ ሁለቱ ነገድ፣

ወበእንተ ኢየሩሳሌም፣

አሥሩ ነ ገ ድ እንዲመለሱ አይቶ የተናገረው ነገር ይህ ነው፤

www.ethiopianorthodox.org

አንድም በእንተ ይሁዳ ጥቃቅኑ አህጉር፤ ወበእንተ ኢየሩሳሌም መዲናይቱ ኢየሩሳሌም እንድትቀና አይቶ የተናገረው ነገር ይህ ነው፤

፪፡ ወይከውን በደኃሪ መዋዕል፣

በኋላ ዘመን እንዲህ ይሆናል፣ አለ፣ በሕዝቅያስ፣ በዘሩባቤል ዘመን እንዲህ ይሆናል፤

ያስተርኢ ቤተ እግዚአብሔር ውስተ አርእስተ አድባር ወይትሌዐል መልዕልተ አውግር፣

ይከውን ያለውን ያስተርኢ ብሎ አመጣው፤ በሕዝቅያስ ዘመን ያሉ እንደሆነ ቤተ መቅደስ፣ በኪዳነ አብርሃም በኪዳነ ይስሐቅ በኪዳነ ያዕቆብ ጸንቶ ይታያል፤

በዘሩባቤል ዘመን ያሉ እንደሆነ በአምስቱ ቆመ ብእሲ በስድስቱ ቆመ ብእሲ በሰባቱ ቆመ ብእሲ ተሠርቶ ይታያል፤

ወየሐውሩ ኀቤሁ ኵሉሙ አሕዛብ፣

በሚጠት ያመኑ አሕዛብ ሁሉ ወደቤተ መቅደስ ይሄዳሉ፤

፫፣ ወይመጽኡ ብዙኃን አሕዛብ፣

ብዙ አሕዛብ ወደ ቤተ መቅደስ ይመጣሉ፤

ወይብሉ ንዑ ንዕርግ ውስተ ደብረ እግዚአብሔር፣

ከመሄዳቸው አስቀድመው ኑ ወደቤተ እግዚአብሔር እንሂድ ይላሉ፤

ወውስተ ቤተ አምላክ ያዕቆብ፣

ወደያዕቆብ ፈጣሪ ማደሪያ ወደቤተ መቅደስ እንሂድ ይላሉ፤

ወየሐውሩ ኀቤሁ፣

በዘመነ ሐዲስ ያመኑ አሕዛብ ወደ ቤተ ክርስቲያን ይሄዳሉ፤

ይንግሩነ ፍኖቶ ወንሑር በአሠሩ ለእግዚአብሔር፣

ዘጠኙን ቃላት ያስተምሩን ዘንድ በኢታምልክም ጸንተን እንኖር ዘንድ ኢታምልክን አሠር አላት፣ ፍለጋ ከአገር ከመንደር እንዲያደርስ ኢታምልክም ከዘጠኙ ታደር ሳለችና፤ ይንግሩነ ፍኖቶ ወአሠሮ ኢታምልክን ዘጠኙን ቃላት ይነግሩን ዘንድ፤ አንድም ንሑር በአሠሩ ወበፍኖቱ ይላል፤ በኢታምልክ በዘጠኙ ጸንተን እንኖር ዘንድ፤

እስመ እምጽዮን ይወጽእ ሕግ ወቃለ እግዚአብሔር እምኢየሩሳሌም፣

ከነቢያት ትንቢት ከካህናት ትምህርት ይገኛልና እንሂድ ይላሉ፤ አንድም ከነቢያት ትንቢት ከካህናት ትምህርት ይገኛልና ኑ ወደቤተ እግዚአብሔር እንሂድ ይላሉ ይላል ነቢዩ፤

አንድም ወይከውን በደኃሪ መዋዕል ብለህ መልስ፤ ከአምስት ሺህ አምስት መቶ ዘመን በኋላ በዘመነ ሐዲስ እንዲህ ይሆናል፤ ይከውን ያለውን ያስተርኢ ብሎ አመጣው፤ በወርቅ በብር ከተሠራ ከነገሥታቱ ቤት ይልቅ በጭቃ በኖራ የተሠራ ቤተ ክርስቲያን በመዐርግ በልጦ ይታያል፤

ወይመጽኡ ብዙኃን አሕዛብ፣

ብዙ አሕዛብ ወደ ቤተ ክርስቲያን ይመጣሉ፤

ወደቤተ ክርስቲያን ከመሄዳቸው አስቀድመው ኑ ወደቤተ ክርስቲያን እንሂድ ይላሉ፤ አሠርቱ ቃላትን ይነግሩን ዘንድ፣ በስድስቱ ቃላተ ወንጌልም ጸንተን እንኖር ዘንድ፤

አንድም ይንግሩነ ፍኖቶ ወአሠሮ፤ አሠርቱ ቃላተ አሪትን ስድስቱ ቃላተ ወንጌልን ይነግሩን ዘንድ፤

አንድም ንሑር በፍኖቱ ወበአሠሩ ይላል፣ በአሠርቱ፣ ቃላተ አሪት በስድስቱ ቃላተ ወንጌል ጸንተን እንኖር ዘንድ፣ ሕግ ጌታ ከእመቤታችን ይወለዳልና፤ (ጥቅስ) አንሶሰወት ሕማ ወአስተርአየት ውስተ ዓለም እንዲል። አንድም ሐጋጌ ሕግ ጌታ ከእመቤታችን ይወለዳልና ጽዮን አላት፣ ፀወነ ሥጋ፣ ፀወነ ነፍስ ናትና አካላዊ ቃል እርሱ ከእመቤታችን ይወለዳልና ኢየሩሳሌም እንጂ ማለት መካነ ሰላም ማለት ነው፤ እሷንም ብኪ ድኅነ ዓለም ወበወልድኪ ኮነ ሰላም ይላታልና፤ አንድም ሕገ ወንጌል በቤተክርስቲያን ይነገራልና አካላዊ፣ ቃል እርሱ በሥጋነት በደምነት በቤተክርስቲያን ይገኛልና፣ ኑ ወደቤተክርስቲያን እንሂድ ይላሉ፤

፬፡ ወይኴንን በማዕከለ አሕዛብ፣

ሕዝቅያስ ዘሩባቤል በአሕዛብ መካከል ሁኖ ይፈርዳል።

ወይዛለፎሙ ለብዙኃን አሕዛብ፣

ብዙ አሕዛብን ይዘልፋቸዋል፣ ብትገብሩ ገብሩ ብትቀቅሉ

www.ethiopianorthodox.org

ቀቅሉ ያለዚያ እወጋችኋለሁ እያለ፤

ወይመትሩ መጣብሒሆሙ ለምሳር፣

ሾተላቸውን ምሳር አድርገው ያሠሩታል፤

ወኵያንዊሆሙ ለማዕፀድ፣

ጦራቸውን ማጭድ አድርገው ያሠሩታል፤

ወኢያነሥእ እንከ ሕዝብ ዲበ ሕዝብ መጥባህተ፣

አንዱ ባንዱ ላይ ጠብ አያነሣም፤

ወኢይትሜሐሩ እንከ ቀትለ፣

እንግዲህ ሰልፍ አይማሩም፤

በሀገራቸው ወርኀ ፀብ ሲሆን ሰልፍ መማር አለና፣ በፈረስ እየጋለቡ የአንዱን እግር ሰናፊል በአንድ እግር ማግባት በአረቄ መ ር ፌ ፈትል ማግባት፣ ዘ ን ግ ወርውሮ መቅለብ፣ አለንጋ ማንሣት አለና በሕዝቅያስ በዘሩባቤል ጊዜ ዘመኑ ዘመነ ሰላም ሁኖ እስራኤል ጠላት ጠፍቶላቸው በወይኑ በበለሱ ሥር ድንኳ ናቸውን ተክለው ጃንጥላቸውን ጥለው ሲበሉ ሲጠጡ ይውሉ ነበርና፤

(ጥቅስ) ይ በ ል ዑ ወይሰትዩ ታሕተ ወይኖሙ ወበለሶሙ ወይነብሩ ተአሚኖሙ እንዲል ፩:ም ነገ. ፬÷፳፯

፭፤ ወይእዜኒ ቤተ ያዕቆብ ንዑ ንሑር በብርሃነ እግዚአብሔር፣

አሁንም የ ያ ዕ ቆ ብ ወገኖች በብርሃነ ረ ድ ኤ ቱ ጸንተን እንኖር ዘንድ ኑ፤ አንድም ኑ በብርሃነ ረ ድ ኤ ቱ ጸንተን እንኑር፣ አንድም በብርሃነ ረድኤቱ ጸንተን የምንኖር በትን ሥራ እንሥራ፤

አንድም ጸንተን እንድንኖር እንሁን፤ አንድም ወይኳንን በማዕከለ አሕዛብ ብለህ መልስ፣ ጌታ በአሕዛብ መካከል ሁኖ ይ ፈ ር ዳ ል፤ ያስተምራልም ብትል ይሆናል፣ ተኀድገ ለከ ኃጢአትከ (ማቴ. ፱÷፪) ተኀድገ ለኪ ኃጢአትኪ (ሉቃ. ፯÷፵፰) ፈቀድኩ ንጻሕ ተንሥእ ንሣእ ዓራተከ (ማቴ. ፱÷፪) እያለ ይፈርዳል፤

ወይዛለፎሙ ለብዙኃን ሕዛብ፣

ጸሐፍት ፈሪሳውያንን ያዋት ታቸዋል፤

አሌ ለክሙ ጸሐፍት ፈሪሳ ውያን መደልዋን እለ ትበልዑ አብያተ መበለታት ወዕጓለ ማውታ እያለ ማቴ.፳፬÷፲፬፣ ሰይፋቸውን መቆፈሪያ አድር ገው ያሠሩታል ጦራቸውንም

ሠቅ መ ስ ቀ ል አድርገው ያሠሩታል፤ እንግዲህ አንዱ ባንዱ ላይ ጠብ አያነሣም፤ እንግዲህ ሰልፍ አይማሩም፤ በጌታ ዘመን ሥጋዊ ጠላት ቅሉ ጠፍቶላቸዋልና፤

ጥቅስ ወያጠፍእ ሠረገላ እምኤ ፍሬም ወአፍራሰ እምይሁዳ ወይከውን ሰላም በመዋዕሊሁ እንዲል፤ ዘካ. ፱÷፲፤ አሁንም የያዕቆብ ዘ ነ ፍ ስ ወገኖች በብርሃነ ረ ድ ኤ ቱ ጸንተን እንኖር ዘንድ ኑ፤ አንድም በብርሃነ ረድኤቱ ጸንተን እንኑር፤

አንድም ጸንተን የምንኖር በትን ሥራ እንሥራ፤ አንድም ጸንተን እንድንኖር እንሁን፤

እስመ ተረስዐ ሕዝበቶሙ ለእስራ ኤል፣

ሕ ዝ ብ ና ሆ ሙ ሲል ነው፣ የአሥሩ ነገድ ወገንነታቸው ተዘንግቷልና፤ እንደነዚያ እንዳ ንዘነጋ ንዑ ንሑር ኑ እንሔድ፤

፮፣ እስመ መልዐ በሐውርቲሆሙ ከመ ትካት ዘ ያ ስ ግ ሉ ከመ ኢሎፍሊ፣

መልዐ ከመ ኢሎፍሊ ዘያስግሉ ከመኢሎፍሊ ብለህ ግጠም፣ አ ገ ራ ቸ ው ኢሎፍላውያን ቀድሞ ይጠነቍሉት እንደ ነበረ ያለ ጥንቈላ ስለ መላ፤

ወከመ ትውልደ ነኪር ኮኑ፣

የ ከ ነ ዓ ን ልጆች ያመልኩት እንደ ነበረ ያለ ጣዖት አገራቸው ስለመላ ወገንነታቸው ተዘንግቷ ልና እንደ ነዚያ እንዳንዘነጋ በብርሃነ ረ ድ ኤ ቱ ጸንተን እንኖር ዘንድ ኑ፤

ወተወልዱ ሎሙ ብዙኅ ደቂቅ ካልዕ ሕዝብ ፣

ለናት ላባታቸው ሁለተኛ የሚ ሆኑ ብዙ ል ጆ ች ተወለዱ ላቸው፤ አንድም የልጅ ልጆች ተ ወ ለ ዱ ላ ቸ ው ፤ አንድም እምካልዕ ሕዝብ ከራቀ ወገን ከአሕዛብ ብዙ ልጆች ተወለዱ ላቸው፤

፯፣ ወመልዐ ብሔሮሙ ወርቀ ወብሩረ፣

አገራቸው ወርቁን ብሩን መላ ትች፤ ወ አ ል ቦ ኍ ል ቍ ለመዛግብቲሆሙ፤

ለገንዘባቸው ስፍር ቍጥር የለውም፤ ትች፤

ወመልዐት ምድሮሙ አፍራሰ፣

ምድራቸው ፈረሶችን መላች፣ ወአልቦ ኍልቍ ለሠራዊቶሙ፤

www.ethiopianorthodox.org

ለሠራዊታቸውም ስፍር ቍጥር የለውም፤ ትኾ፤

፳፣ ወመልዐት ምድሮሙ ጣዖተ፣ ዘገብሩ በእደዊሆሙ፣

ወርቁ ብሩ በዛባቸው፣ ምን እ ና ው ለ ው ብለው ጣዖት አድርገው ሠርተውት አገራ ቸው በ እ ጃ ቸ ው የሠሩት ጣዖትን መላ፤

ወሰገዱ ለዘገብሩ በአፃብኢሆሙ፣

በእጃቸው ለሠሩት ለጣዖቱ ሰገዱ፤

፱፣ ወተቀጽዐ ሰብእ ውኀረ ዕጓለ እመሕያው፣

ሰው ሁሉ በመከራው ጐበጠ፤ ሰውም ሁሉ ጐሰቈለ፤ አንድም መከራ ተቀበለ፤

ወኢይስሕቶሙ ሞት፣

የተወረወረ ጦር አይስታቸ ውም፤ አንድም ኢያሴሕቶሙ ሞት፣ ሞት አያሳርፋቸውም ዛሬም ነገም ይሞታሉ፤

፲፣ ወይእዜኒ ባእ ውስተ ኰኮሕ፣

አሁንም ይሆንላችሁ እንደሆነ ወደዋሻው ግቡ ይላቸዋል፣ ፍና ተሳልቆ፤

አንድም መከራ እንዳለባቸው መናገር ነው፤

ወተነብዑ ውስተ ግበበ ምድር እምፍርሀተ ገጸ እግዚአብሔር፣

የእግዚአብሔር ገጸ መዐቱን ከመፍራታቸው የተነሣ በጕድ ጓድ ውስጥ ተሠወሩ፤

ወእምግርማሁ፣

ከግርማ መዓቱ የተነሣ፤

ወእምስብሐተ ኃይሉ፣

ከሀሊነቱን ከሚገልጥበት ከተ አምራቱ የተነሣ፤

አመ ተንሥአ ይቀጥቅጣ ለምድር፣

ኢየሩሳሌምን ያጠፋት ዘንድ በተነሣ ጊዜ፣ አንድም ኢየሩሳ ሌምን እንደ ሰም ያቀልጣት እንደገል ይቀጠቅጣት ዘንድ፤ በመዓት በተነሣ ጊዜ፤ አንድም እስመ ተ ን ሥ አ በመዓት ተነሥቷልና፤ አንድም አመ ተንሥአ በመዓት በተነሣ ጊዜ ይቀጠቅጣ ይላል፣ እንደ ሰም ያቀልጣታል፣ እንደገል ይቀጠ ቅጣታል፤

፲፩፣ እስመ አዕይንተ ልዑላን ሰብእ የኀስራ፣

የልዑላን ሰዎች ዐይን በሞት ይፈስሳልና፤

ወየኀስር ል ዕ ል ና ሁ ለዕጓለ እመሕያው፣

የሰው ክ ብ ሩ ይዋረዳልና ተነብዑ ብለህ እሠር፤

ወይትሌዐል እግዚአብሔር ባሕቲቱ ይእተ አማረ፣

ያንጊዜ እግዚአብሔር ብቻ እለሳቸውን አ ጥ ፍ ቶ ልዕልና ውን ይገልጣል፤

፲፪፣ እስመ ዕለተ እግዚአብሔር ዐባያት ላዕለ ኵሉ ፀር ወጻላኢ፣

አሸናፊ እግዚአብሔር የሚፈ ርድባት ዕለተ ፄዋዌ በጠ ላቶች ላይ ትመጣለችና፤ ፀር የዕለት ጠላት፣ ጸላኢ ጥንተ ጠላት ነው፣

ዝኩ ፀላኢ ሐማ አማሌቃዊ እንዲል፤ አስ.ቴ. ፯ ÷ ፮፣

ወዝኑር፣ በትዕቢተኛው ላይ፣

፲፫፣ ወላዕለ ኵሉ ዕፀ ሊባኖስ ነዋህ ወልዑል፣

ነዋህ ልዑል አንድ ወገን ነው፤ ዕለተ ፄዋዌ በባለጸጋው ትመጣለችና፤

ወጸቢ ኵሉ ወግር ልዑላት፣

በመኪንንቱ ትመጣለችና፤

፲፬፣ ወላዕለ ኵሉ ማኅፈድ ነዋህ ወልዑል፤

ልዑል ክቡር በሚሆን በንጉሡ ላይ ትመጣለችና፤

፲፭፣ ወላዕለ ኵሉ አረፍት ቀዋም፣

በአርበኛው ላይ ትመጣለችና፤

፲፮፣ ወላዕለ ኵሉ አሕማር ዘውስተ ባሕር፣

በደሴት በሚኖሩ በነጋድያን።

አንድም በ ደ ሴ ት የሚኖሩ ነጋድያንን በሚገዙ በነገሥ ታቱ ላይ ትመጣለችና፤

(ጥቅስ) አሌሉን ለአሕማር እለ ቦን ክንፍ እንዲል፤ ኢሳ ፲፰÷፩፤

ወላዕለ ኵሉ ጣዖተ አማልክት፤

አማልክት በ ሚ ገ ሉ በጣዖ ታቱ፤ አ ን ድ ም ካህናት ባሏቸው በጣዖታቱ፤ አንድም አማልክተ ጣዖት ይላል ጣዖት ባላቸው ጣ ዖ ት ን በሚያ መልኩ በካህናቱ ትመጣለችና፤

፲፯፣ ወይቴሐት ኵሉ ሰብእ፣

ሰው ሁሉ ይዋረዳል፤

ወአዕይንተ ዕቡያን ሰብእ ይቴሐታ፣

የክፉዎች ሰዎች ዓይን በሞት ይፈስሳልና፤

ወየኀስር ል ዕ ል ና ሁ ለዕጓለ እመሕያው፣

የሰው ሁሉ ልዕልናው ክብሩ ይዋረዳል፤

ወይትሌዐል ይእተ አሚረ እግዚአ ብሔር ባሕቲቱ፣

ያንጊዜ እግዚአብሔር ብቻ ልዕልናውን ይ ገ ል ጣ ል ና፣ ወይትሌዐል ብለህ እሠር፤

www.ethiopianorthodox.org

፲፰፣ ወየኀብኡ ኵሎ ጣዖቶሙ ዘገብሩ በእደዊሆሙ፣

በእጃቸው የሠሩትን ጣዖታቸ ውን ሁሉ ይሠውራሉ፣ የወርቅ የብር ነ ው ና ይወስዱብናል ብለው፤

፲፱፣ ወያበውእዎሙ ውስተ በአታት፣

ወደዋሻ ያገቧቸዋል፤

ወውስተ ንቅዐታተ ኰኵሕ፣

ወደተከፈለው ድንጊያ ያገቧቸ ዋል፤

ወውስተ ግበበ ምድር፣

ወደ ጕድጓድ ያገቧቸዋል፣

እምቅድመ ገጸ ግርማሁ ለእግዚ አብሔር፣

ከእግዚአብሔር ከግርማ መዐቱ የተነሣ፤

ወእምስብሐተ ኃይሉ፣

በከሀሊነቱ ከሚያደርገው ከተ አምራቱ የተነሣ፤

አመ ተነሥአ ይቀጥቅጣ ለምድር፣

ኢየሩሳሌምን ያጠፋት ዘንድ በመዓት በተነሣ ጊዜ፣ አንድም ኢየሩሳሌምን እንደ ሰም ያቀልጣት፣ እንደ ገል ይቀጠቅጣት ዘንድ በመዓት በተነሣ ጊዜ፣ አንድም እስመ ተንሥአ ኢየሩሳሌምን እንደ ሰም ያቀልጣት እንደ ገል ይቀጠቅጣት ዘንድ በመዓት ተነሥቷልና፤

አንድም በመዓት በተነሣ ጊዜ ይቀጠቅጣ ይላል፤ እንደ ሰም ያቀልጣታል እንደ ገል ይቀጠ ቅጣታል፤

፳፣ ውእተ አሚረ ያወፅእ ሰብእ ርኩሰ ጣዖተ ዘወርቅ ወዘብሩር፣

ያንጊዜ ሰው የወርቅ የብር የሚሆን ጣዖትን ያወጣል፣ ለማሸሽ፤

ዘገብሩ በእደዊሆሙ ከመ ይስግዱ ለከንቱ፣

ለከንቱ ጣዖት ይሰግዱ ዘንድ፤ አንድም ከንቱ ሊሆንባቸው ይሰግዱ ዘ ን ድ በእጃቸው የሠሩት፤

፳፩፣ ከመ ያብኡ ውስተ ግበበ ምድር፣

ያወፅኡ ከመ ያብኡ ብለህ ግጠም ንቀውት፣ አንድም ኋላ ሊያወጡት፣ ወደ ጕድጓዱ ያገቡት ዘንድ ካስቀመጡበት ያወጡታል፤

ወውስተ ንቅዐታተ ኰኵሕ፣

ወደተከፈለው ምድር ያገቡ ታል፤

እምቅድመ ገጸ ግርማሁ ለእግዚ አብሔር፣

ከእግዚአብሔር ከግርማ መዐቱ የተነሣ፤

ወእምስብሐተ ኃይሉ፣

በከሃሊነቱ ከ ሚ ያ ደ ር ገ ው ከተአምራቱ የተነሣ ፤

አመተ ን ሥ አ ይቀጥቅጣ ምድር፤ እንዳለፈው ተርጕም ሦስት ጊዜ ይ ቀ ጥ ቅ ጣ ይቀጥቅጣ ይቀጥቅጣ እያለ ተናገረ፣ ሦ ስ ት ጊዜ ተማር ከዋልና በ ኢ ኮ ን ያ ን፣ በኤልያቄም ፣ በሴዴቅያስ፤

፳፪፣ ወኀደጉ ኵሉ ዕጓለ እመሕ ያው ዘነፍስ ውስተ ገጹ፣

ሥጋዊ ደማዊ የሚሆኑ ሰዎች ሁሉ በጣዖቱ ግንባር ጉድፉን፤ ትቢያውን ጣሉ፤ የሠወርነ መስሏቸው፤

ምንተ ይሔሊ ውእቱ፡

አያድናቸው ፤ አይራዳቸው ፤ አይታደጋቸው፤ ምን ያደርግ ላቸዋል ይላል ነቢዩ፤ አንድም ዕጓለ እ መ ሕ ያ ው ዘነፍስ፣ ባለአእምሮ ሰ ዎ ች በሚጠት ጣዖቱን በግንባሩ ደፍተው ጥለውት ይ ሄ ዳ ሉ፣ ምንተ ይሔሊ፣ አያድነን፣ አይራዳን አይታደገን ምን ያደርግልናል ብለው::

ጉባዔ፣

ምዕራፍ ፫

፩፣ ናሁ እግዚአብሔር ፀባዖት ያአትት እምኢየሩሳሌም ወእም ይሁዳ ኀያላነ ወጽኑዓነ፣

እነሆ አሸናፊ እግዚአብሔር ከአሥሩ ነገድ ከሁለቱ ነገድ ፅኑዓኑን ኃያላኑን ያርቃል፤

ወፅንዐተ ኃይለ እክል

እህሉን በልተውት እንዳያ ጸናቸው ያደርገዋል፤ አንድም የእህሉን ኃይል ያርቃል ማለት የእህል ኃ ይ ሉ በልተውት ማጥገብ ነው፣ በ ል ተ ው ት እንዳያጠግባቸው ያደርጋል፤

ወኃይለ ማይ፣

ውሀውን ጠጥተውት እንዳያረ ካቸው ያደርገዋል፤ የውሀ ኃይሉ ጠጥተውት ጥም መቁረጥ ነው፤ ጠጥተውት ጥማቸውን እንዳይ ቆርጥ ያደርገዋል ፤ አንድም ናሁ እግዚአብሔር ፀባዖት ያአትት እም ኢየሩሳሌም ወእምይሁዳ ብለህ መልስ፤

እነሆ አሸናፊ እግዚአብሔር ከአሥሩ ነገድ ከሁለቱ ነገድ ጽኑዓነ አ እ ም ሮ፣ ኃያላነ አእምሮ የሚሆኑ ሐዋርያትን ያርቃል፤ ቢመክሯቸው ቢያስተ ም ሯ ቸ ው የማይሰሟቸው ቢሆኑ፤ እ ን ከ ሰ ንትመየጥ

www.ethiopianorthodox.org

እስመ አልብየ እክል ውስተ ቤትየ ወኢልብስ፣

በቤቴ እህል የለምና ልብስም የለምና፣

ወኢይክውን መልአከ ለዝ ሕዝብ፡

ይህ ሰው ጎጆ የወጣ ነው፤ እንኪንስ ጎጆ ለወጣኸው ላንተ ጎጆ ላልወጣው ለዚህ ገዢ አለቃ አልሆነውም፤

፰፣ እስመ ኀለፈት ኢየሩሳሌም፣

ተነልፍ ሲል ነው፤ ኢየሩሳሌም ታልፋለች ትጠፋለችና፤

ወይሁዳኒ ወድቀት፣

ትወድቅ ሲል ነው፤ ይሁዳም ታልፋለች ትጠፋለችና ማለት አሥሩ ነገድ ሁለቱ ነገድ ይጠፋሉና

በእንተ ልሳኖሙ ዘዐመፃ፣

በአንደበታቸው በሥሩት በነገር ሥራቸው ይጠፋሉና፣ ስንኪንስ ጎጆ ለወጣኸው ላንተ ጎጆ ላልወጣው ለዚህ ገዢ አለቃ አልሆነውም ይላል፤ አንድም እንዳለ ኀለፈት ወድቀት ብሎ ኢየሩሳሌም አልፋለች ጠፍታለችና ይሁዳም አልፋለች፣ ጠፍታለችና ስንኪንስ ጎጆ ለወጣኸው ላንተ ጎጆ ላልወጣው ለዚህ ገዢ አለቃ አልሆነውም ይለዋል ይላል ነቢዩ፤ አንድም

ያ አባት ልጁን እንዲህ እንዲለው፣ አንሰ ኢይክውን መልአከ ለዝ ሕዝብ ይላል፤ ጌታ ለወገኔ ለእስራኤል ገዢ አለቃ አልሆነውም፣ ኢየሩሳሌም ጠፍታለችና ይሁዳም ጠፍታለችና፤

ወይክህድዎ ለእግዚአብሔር፣

እግዚአብሔርን ስለካዱት፤

፱፣ እስመ ይእዜ ኀስረ ክብሮሙ፣

ባለጸግነታቸው ጠፍቷልና ፤ አንድም ክብራቸው ተዋርዷልና፤

ወተነፍረ ገጸሙ፣

ፊታቸውም በመከራ አፍሯልና፤

ወተቃወመቶሙ ኃጢአቶሙ ከመ ኃጢአተ ሰዶም ወገሞራ፣

እንደ ሰዶም እንደ ገሞራ ሰዎች ኃጢአት ኃጢአታቸው ተቃወመቻቸው፤

አስተርአየት ወተዐውቀት ላዕሌ ሆሙ፣

አስተርአየት ማንሻ ነው፣

አንድም እንደ ሰዶም እንደ ገሞራ ሰዎች ኃጢአት ኃጢአታቸው አስተርአየት ወተዐውቀት እስራኤልን በማጥፋት ታወቀች፤ ተገለጠች፤

አንድም የሰዶም የገሞራ ኃጢአት ፍዳን በማምጣት እነሱን በማጥፋት እንደተገለጠች በቃል አምጥቶ አስተርአየት ወተዐውቀት፣ የእስራኤልም ኃጢአት እነሱን በማጥፋት ፍዳን በማምጣት ተገለጠች፤

አንድም አስተርአየት ወተዐውቀትን በቃል አምጥቶ ከመ ኃጢአተ ሰዶም ወገሞራ የሰዶም የገሞራ ኃጢአት ፍዳን በማምጣት እነሱን በማጥፋት እንደተገለጠች የእስራኤልም ኃጢአት ፍዳን በማምጣት እነሱን በማጥፋት አስተር አየት፣ ወተአውቀት ታወቀች፣ ተገለጠች፤

አንድም ማካፈል ነው፤ የሰዶም የገሞራ ኃጢአት እነሱን በማጥፋት አስተርአየት፣ እንደተገለጠች የእስራኤልም ኃጢአት እነሱን በማጥፋት ታወቀች፡

አሌ ላ ለነፍሶሙ፣

ለሰውነታቸው ወዮላት፤

እስመ መከሩ እኩየ ምክረ ላዕለ ነፍሶሙ፣

በሰውነታቸው መከራ ቢመጣባቸው ክፉ ምክር መክረዋልና፤

፲፣ ወመከሩ እንዘ ይብሉ፣

እንዲህ ብለው መከሩ፡

ንሥዐሮ ለጻድቅ፣

ድህውን እናጥፋው አሉ፤

እስመ ዕፁብ ወክቡድ ውእቱ ለነ፣

ማለዳ ማለዳ እየመጣ ተበደልሁ ፍረዱልኝ ማለቱ ለእኛ ጭንቃችን ነውና፤ አንድም ንሥዐሮ ለጻድቅ ብለህ መልስ፤ ነቢዩን እናጥፋው አሉ፤ ሕግ እግዚአብሔርን ጠብቁ ትማረ ካላችሁ ማለቱ ለእኛ ጭንቃችን ነውና፤ አንድም ጻድቀ ባሕርይ ወልደ እግዚአብሔርን እናጥፋው አሉ፤ እስመ ዕፁብ አሌ ለክሙ ጸሐፍት ፈሪሳውያን መደልዋን እለ ትበልዑ አብያተ መበለታት ወዕንለ ማውታ እንዲል፤ማቴ፡፳፫÷፲፫፣ ማለቱ ለእኛ ጭንቃችን ነውና፤

አንድም ሐዋርያውን እናጥፋው አሉ፤ በነፍስ አውታር መስቀሉ በሌጌዎን መንጻቱ (መጣሉ) ለእኛ ጭንቃችን ነውና፤

ወይእዜኒ ይብልዑ ማዕረረ ምግባሮሙ፣

አሁንም ፍዳቸውን ይቀበሉ ይብልዑ ማዕረረ ግሥ ነው፤

አንድም ምግባር ኃጢአት፣ ማዕረር ፍዳ፣ የኃጢአታቸውን ፍዳ ይቀበሉ፤

www.ethiopianorthodox.org

፲፭፣ አሌ ሎ ለኃጥአ በእከይ፣

በኃጢአቱ ሰ ኃ ጥ እ ሰው ወዮለት፣ አንድም ዘበእከዩ ይላል፤ በ ኃ ጢ አ ቱ ጸንቶ ለሚኖር ሰው ወዮለት፤

በከመ አከየ ግብረ እደዊሆሙ ይረክቡ ሕዝብየ፣

ወገኖቼ እስራኤል እንደ እጃቸው ሥራ መጠን መከራውን ይቀበላሉ፤

፲፮፣ እለ ያስተበዕዉክሙ ያስሕቱክሙ፣

ሰላም ሰላም አይሂችሁ ፄዋዌ የለም እያሉ የሚያደናንቋችሁ ነቢያተ ሐሰት ካህናተ ጣዖት ያስታችሁ ዘንድ ነው፤

አንድም ያስሕቱክሙ ያስታችኋል፤

ወይደምስሱ አሠረ እገሪክሙ፣

ፍለጋችሁን ያጠፉ ዘንድ ነው፤ አንድም ይደመስሱ ይላል፤ ፍለጋችሁን ያጠፋሉ፤

፲፫፣ ወባሕቱ ይእዜ ይትነሣእ እግዚአብሔር ለኵንኖ፣

ነገር ግን እግዚአብሔር ለመፍረድ ይነሣል፤

ወያቀውሞሙ ለ ሕ ዝ ቡ ከመ ይትዋቀሰሙ፣

ይወቅሳቸው ዘንድ ወገኖቹን ያቆማቸዋል፤

፲፬፣ ወይመጽእ እግዚአብሔር ለሊሁ ምስለ ሊቃውንተ ሕዝቡ፣

እግዚአብሔር በአለቆች አድሮ ይመጣል፤

ወምስለ መላእክቲሁ፣

አንድ ወገን በአለቆች አድሮ ይመጣል፤

ሊቃናት የነገር ፣ መላእክት የሀገር ነው፤

ወይብል አንትሙ አውዐይክሙ ወይንየ፣

ሕዜን አፈረሳችሁ፤

ወበርበረ ነዳይ መላዕክሙ ውስተ አብያቲክሙ፣

የድሀውንም ገንዘብ እየበዘበዛችሁ በቤታችሁ መላችሁ ይላቸዋል፤ አንድም ወይመጽእ እግዚአብሔር ለሊሁ ምስለ ሊቃውንተ ሕዝቡ ብለህ መልስ፤ እግዚአብሔር ካለቆች ጋራ ለመወቃቀስ ይመጣል፤

ወይብል አንትሙ አውዐይክሙ ወይንየ፣

ወገኖቼ እስራኤልን በደላች ኋቸው፤ ወ በ ር በ ረ ነዳይ የድሆችንም ገንዘብ እየበዘበዛችሁ በቤታችሁ መላችሁ ብሎ ለመወቃቀስ ይመጣል፤

፲፭፣ ለምንት ትገፍዕዎሙ ለሕዝብየ፣

ከእንጨት መ ር ጠ ለታቦት ከሰው መ ር ጠ ለሸመት፣

እንዲሉ መርጩ ብሾማችሁ ወገኖቼ እስራኤልን ለምን ትበድሏቸዋላችሁ ብሎ ከአለቆች ጋራ ለመወቃቀስ ይመጣል፤

ወታስተነፍሩ ገጸ ነዳይ፣

የድሀውን ፊት ለምን ታሳፍራላችሁ፣ ድሀው፣ ባለፀጋው፣ በድሎት ዳኛው እውነት ይፈርድልኛል ብሎ ይሄዳል፣ ዳኛውም አድልቶ ሐሰት ይፈርድበታል፣ ይህን ጊዜ ያፍራልና፤

፲፮፣ ከመዝ ይቤ እግዚአብሔር፣

እግዚአብሔር እንዲህ አለ፤

እስመ ተዘነራ አዋልደ ጽዮን፣

ተዝናራ ሲል ነው፣ ተከዐውኩ ከመ ማይ ያለውን ተክዕውኩ ብለው እንዲተረጉሙ የጽዮን ልጆች ታብየዋልና፣

ወየሐውራ እንዘ ያገዝፋ ክሣኗን፣

አንገታቸውን እየነቀነቁ ይሄዳሉ፤

አንድም ይሄዳሉና፤

ወይትቃፀባ በአዕይንቲሆን፣

በዐይናቸው ይጠቃቀሳሉ፣ አንድም ይጠቃቀሳሉና፤

ወያጽሕሳ በእገሪሆን፣

በእግራቸው ያሸበሸባሉ የእግር አታሞ ይመታሉ፤

አንድም ይመታሉና፣

ወይስሕባ አዝፋረ አልባሲሆን፣

የልብሳቸውን ጫፍ ይጐትታሉ፣ ልብስ መጐተት የትዕቢት ምልክት ነው ፤ አንድም የልብሳቸውን ጫፍ ይጐትታሉና፤

ወይዘፍና፣

ይዘፍናሉ፤ አንድምይዘፍናሉና፤

፲፯፣ ወየኀሰሮን እግዚአብሔር ለሊቃናተ አዋልደ ጽዮን፣

ለአዋልደ ሊቃናተ ጽዮን ሲል ነው፤ የጽዮንን አለቆች ልጆች እግዚአብሔር ያጐሰቍላቸዋል፤

አንድም እንዳለ ይሆናል የሴት አለቆች አሉና፤

ወይቀፍጸን እግዚአብሔር አልባ ሲሆን ይእተ አሚረ፣

ያንጊዜ እግዚአብሔር ልብሳቸውን ይገፍፋቸዋል፤

፲፰፣ ወይሰልቦን አልባሰ ክብሮን፣

የሚከበሩበትን ልብሳቸውን ይገፍፋቸዋል፤

ወሠርጓቲሆን፣

ሽልማታቸውን፤

፲፱፣ ወሐብለታቲሆን፣

ሠርጓቲሆን ያለውን ይተረትራል እንጥልጥላቸውን፤

www.ethiopianorthodox.org

ወአውቃፊሆን፣
አምባራቸውን፡
ወአዕኑቂሆን፣
ንፎ መንደልቷቸውን፡
ወጎልቀታቲሆን፣
ተርታ ቀለበታቸውን፡
፴፣ ወባዝግናቲሆን፣
ዝርግፋቸውን፡ (የወርቅ ማርዳ)
ወቀፀላቲሆን፣
የወርቅ ከለቻቸውን፡
ወባሕርያቲሆን፣
የዕንቁሩ ከለቻቸውን፡
ወክብሶሆን፣
ሰርሜዳቸውን (የራስ ጌጥ ነው)፡
፴፩፣ ወአልባሲሆን ዘሜላት፣
ነጭ ሐር የሚሆን ልብሳቸውን፡
ወዘሲራይ፡
ቀይ ሐር የሚሆን ልብሳቸውን፣
ወዘሰግላጥ፣
ብጫ የሚሆን ፣ አንድም ልብሰ ፀሐይ ነው፡
፴፪፣ ወአልባሰ ክብር ዘወርቅ፣
የሚከበሩበት ወርቀ ዘቦ ቀሚሳ ቸውን፡
ወአልባሰ አሥቅ፣
ከአራት ጎ ብ ር ከአምስተኛ ወርቅ የተሠራውን፡

ወአራዙን፡
ቀሚሳቸውን፣
፴፫፣ ወመዋጥሒሆን ዘሰንሰሪቀ ፣
ሰማያዊ ሐር የሚሆን መጐናጸ ፊያቸውን ይሽን ሁሉ ይገፍ ፉቸዋል፡
፴፬፣ ወሀየንተ መዓዛ ዕፍረትኪ ፀበል ይኩንኪ፣
ሽቱ ትቀቢ ስለ ነበረ ፈንታ ትቢያ ይብነንብሽ፡
ወሀየንተ ቅናትኪ ዘወርቅ ሐብለ ቅንቲ፣
የወርቅ ዝናር ትታጠቂ ስለነበረ ፈንታ ኖሪት (ጉንጉን) መታ ጠቂያ ታጠቂ፡
ወሀየንተ ቀፀላኪ ዘወርቅ ዘውስተ ርእስኪ ብርሐት ትባእኪ፡
በራስሽ የወርቅ ቀፀላ ታደርጊ ስለነበረ ፈንታ ቡህነት ትው ጣብሽ፡ ትብትብ ምንጣፍ በመሸከም፡
በእንተ እከየ ምግባርኪ፣
ስለ ክፉ ሥራሽ፣
ወሀየንተ ልብስኪ ዘሜላት ልበሲ ሠቀ፣
ነጭ ሐር ትለብሺ ስለነበረ ፈንታ ምንጣፍ ልበሺ፡

፴፭፣ ወወልድኪ ዘይልሕቅ ዘታ ፈቅሪ ይወድቅ በኲናት፣
የምትወጂው ታላቁ ልጅሽ በጦር ተደብድቦ ይወድቃል፡
አንድም የምትወጂው ታላቁ ንጉሥሽ በጦር ተደብድቦ ይወድቃል፡
ወኃያላንኪ በፀብእ ይትጎፈሩ፣
አርበኞችሽም በሰልፍ ይጐሰ ቍላሉ፡
፴፮፣ ወይላህዉ አስከሬናተ ሠርገኪ፣
የሽልማትሽ ሣጥኖች ማለት ጌጥሽ የሚቀመጡባቸው ሣጥ ኖች ያለቅሳሉ፡ የሰዎችን ግዕዛን ለሣጥኖች ሰጥቶ ተናገረ፡
ወትተርፊ ባሕቲተኪ፣
ገንዘብሽ ሂዶ ሂዶ አልቆ ብቻሽን ትቀሪአለሽ፡
አንድም ወይላህዉ በአስከሬናተ ሠርገኪ ሶበ ይተርፍ ባሕቲቶ ይላል፡
ገንዘቡ ሂዶ ሂዶ አልቆ ብቻውን በቀረ ጊዜ በሽልማቶችሽ ሣጥኖች ያለቅሳሉ፡ ዛሬ ካህን የሞተ እንደሆነ፣ መቋሚያውን፣ ጸናጽሉን፣ ቋዱን፣ ቀሽመሬውን ይዘው እንዲያለ ቅሱ፡ ወታደር የሞተ እንደሆነ ጋሻውን፣ ጦሩን፣ ጐራዴውን ይዘው እንዲያለቅሱ፡
ወይነጽሑኪ ውስተ ምድር፣
በጦር እየወጉ ከምድር ይጥሉ ሻል።

ምዕራፍ ፬

፩፣ ወይእኅዛሁ ሰብኡ አንስት ለአሐዱ ብእሲ፣
በዜዋዜ ወንድ ወንዱ አልቆ ሴት ሴቱ ቀርቶ ሰባት ሴቶች አንዱን ወንድ በነገር ይይዙታል ማለት ባል ሁነን ይሉታል፡
ወይብላሁ እክለ ዚአነ ንሴሰይ ወልብሰ ዚአነ ንትኤረዝ፣
ለናንተ ሁሉ ልብስ ቀለብ ወዴት አገኛለሁ ቢላቸው ገንዘባችንን በልተን ገንዘባችንን ለብሰን እንኖራለን ይሉታል፡
ዳዕሙ ይሰመይ ስምከ በላዕሌነ፣
ባል አላቸው ተባልልን እንጂ አንድም ስምህ በእኛ ይጠራ እንጂ፡
ወአኀድጎ ጽዕለተ፣
ጽዕልት እምንእሳ (ጋለሞታ) መባልን አስተወን እንጂ ገንዘባችንን በልተን፣ ገንዘባ ችንን ለብሰን እንኖራለን ይሉታል፡ አንድም ወይእኅዛሁ

www.ethiopianorthodox.org

ሰብዑ አንስት ለአሐዱ ብእሲ ብለህ መልስ፡ ሰባቱ ከዋክብት፣ ሰባቱ ዕለታት ጌታን በነገር ይይዙታል፣ ሰባቱ ከዋክብት ሰባቱን ዕለታት ፈጠሩ የሚሉ መናፍቃን ነበሩና ከዋክብቱ፣ ሸምሸ ፣ ቀ መ ር ፣ መሪህ መሸተሪ፣ ዙሐል፣ አጣርድ ዝሑራ ናቸው፡ እክለ ዚአነ ንሴሰይ ወልብሰ ዚአነ ንትኤረዝ በ ተ ፈ ጥ ሮ አ ች ን ጸንተን እንኖራለን፡

አንድም በፍጡርነታችን ጸን ተን እንኖራለን ይሉታል፡

ዳዕሙ ይሰመይ ስምከ በላዕሌነ፡

ፈጣሪ አላቸው ተባልልን እንጂ በተፈጥሮአችን፡ አንድም በፍ ጡርነታችን ጸንተን እንኖራለን ይሉታል፡

ወአኀድገነ ጽእለተ ከዋክብቱ ፈጣሪያነ ፍጥረት መባልን፣ ዕለታቱ ፍ ጡ ራ ነ ፍጥረት መባልን አ ስ ተ ወ ን እንጂ ይሉታል፡ አ ሁ ን እነዚያ እንዲህ ተባብለው አይደለም የሚያሰኝ ስ ለ ሆ ነ እንዲህ አለ፡

አንድም፣ ወይእኅዛሁ ሰብዑ አንስት ለአሐዱ ብእሲ ብለህ መልስ፡ ፍጹማን ምእመናን ጌታን በሃይማኖት ይይዙታል፡

ጥቅስ እስመ ጎልቈ ሳብዕ ፍጹም ውእቱ በነበ ዕብራ ውያን እ ን ዲ ል ሃይ አበ እክለ ዚአነ ንሴሰይ፡ ልጅነትን ሥጋህን፣ ደምህን ተቀብለን እንኖራለን፡ (ጥቅስ) ነዐ ብላዕ ኅብስተከ በፍሥሓ ወስተይ ወይነከ በልብኀ እንዲል፡ መክ. ፱÷፯፡ እክለ ዚአነ ሃለታቸው ባሕርያቸው ነውና ወልብሰ ዚ አ ነ ንትኤረዝ በልጅነት ጸንተን እንኖራለን ይሉታል፡ (ጥቅስ) እስመ አልበስከኒ ልብሰ ትፍሥሕት ወከደንከኒ ክዳነ ኀሤት እንዲል፡ ኢሳ. ፷፩÷፲፡ ዳዕሙ ይሰመይ ስምከ በላዕሌነ ክርስቶስ ተብለህ ክርስቲያን አሰኘን እንጂ ወአኀድገነ ጽእለተ አግብርተ ዲያብሎስ አዕግተ ዲያብሎስ መባልን አስተወን እንጂ ሥ ጋ ህ ን ደምህን እንቀበላለን ይሉታል፡

፪፣ ይእተ አሚረ ያበርህ እግዚአ ብሔር በጸበ ምድር በምክረ ስብሐቲሁ፣

ኢሳይያስ የዜዋዌን ይዞ ሳለ ይእተ አሚረ ብሎ የሚጠ ትን፣ የሚጠትን ይዞ ሳለ የዜዋዌን ማምጣቱ ልማድ ነው፡ ያንጊዜ እግዚአብሔር በሚጠት በጌትነቱ በመከረው

ምክር ብርሀነ ረ ድ ኤ ቱ ን ያበራል፡

፫፣ ከመ ይዕቀብዎሙ ወያክብር ዎሙ ለእለ ተርፉ እምእስራኤል ወለእለ ተርፉ እምጽዮን፣

እምእስራኤል እምጽዮን አንድ ወገን ነው፡ አ ሥ ሩ ነገድ ተማርከው የቀሩ ሁለቱን ነገድ ቂሮስ ዳ ር ዮ ስ ፡ አንድም ነቢያት ካ ህ ና ት፡ አንድም ሠላሴ ይጠ ብ ቋ ቸ ው፣ ያከብ ሯቸው ዘንድ ብርሃነ ረድኤቱን ያበራል፡

ወተረፈ ኢ የ ሩ ሳ ሌ ም ቅዱሳነ ይሰመዩ፣

አሥሩ ነገድ ተማርከው የቀሩ ሁለቱ ነገድ ክቡራን ይባላሉ፡

ወኮሎሙ እለ ተጽሕፉ፣

ተረፈ ኢ የ ሩ ሳ ሌ ም ያለውን ወኮ ሎ ሙ እለ ተጽሕፉ ብሎ ደገመው፡

አንድም አ ሥ ሩ ነገድ ተማርከው የቀሩ እኒህ ክቡራን ይባላሉ፡ ትች፡

ሁሉም በልበ ሠላሴ የተቈ ጠሩ ናቸው፡ ትች፡

አንድም ለእለ ተርፉ እም እስራኤል ወለእለ ተርፉ እምጽዮን ወተረፈ ኢየሩሳሌም

ብሎ ወደ ላይ ከቶ ወቅዱሳነ ይሰመዩ እለ ተጽሕፉ፣ ክቡራን የሚሆኑ እኒህ ሁሉም በልበ ሠላሴ የተቈጠሩ ናቸው በልበ ሠላሴ የተቈ ጠሩ እኒህ፡

የሐይዉ በኢየሩሳሌም፣

በኢየሩሳሌም ይኖራሉ፡

፬፣ እስመ የሐዕቦሙ እግዚአብሔር እምርስሐቶሙ ለ ደ ቂ ቀ ጽዮን ወአዋልዲሃ፣

የጽዮንን ልጆች ወንዶችንም ሴቶችንም እግዚአብሔር ከኃ ጢአታቸው ያነጻቸዋልና፡

ወያነጽሕ ደመ እማዕከሌሙ፣

እስመ ደም ምሉዕ ዕደዊክሙ ብሎ ነበርና፡

ደሙን ከመካከላቸው ያርቃል፡ በቁሙ የሰው ደም እንዳያፈሱ ያደርጋል፡

አንድም የድህ ገንዘብ እንዳይ ቀሙ ያደርጋል፡

በመንፈሰ ኵነኔ ወበመንፈሰ ፍትሕ፣

ክፉ ክፉዎችን ፈርዶ በሚያጠ ፉበት በጎ በጎ ዎ ች ን ፈርዶ በሚያድንበት ሥልጣኑ ደምን ከመካከላቸው ያርቃል፡

www.ethiopianorthodox.org

፭፣ ወይመጽእ ወይከውን ኵሉ በሐውርት ለደብረ ጽዮን፣

በዔዋዌ ሂዶ የነበረ የእስራኤል ሀገር በሚጠት ይመጣል፤ ለእስ ራኤል ይሆናል፤

ወኵሉ ዘዓውዳ ይጼልል ደመና መዓልተ፣

በመዓልት ደመና ዙርያዋን ይከባታል፤ ማለት ረድኤት ቤተ እስራኤልን በመዓልት ቁሪያዋን ይከባታል፤

ወከመ ጢስ፣

(ጥቅስ) ወጢስ ለዐይን እንዲል፤

ጢስ ለዐይን እንዳይመች ቤተ እስራኤል ለጠላት አትመችም፤

ወብርሃነ እሳት ዘይነደድ ሌሊተ፣

ሌሊት የሚነድ የእሳት ብርሃን ደስ እንዲያሰኝ ለቤተ እስራኤል የተሰጠ ረድኤት ደስ ያሰኛል፤ ቀን ዐምደ ደመና ሁኖ ሲመራቸው የዋለው ሌሊት ዐምደ እሳት ሁኖ ከደብተራ አሪት ላይ ሰፍሮ ሲያበራላቸው ያድር ነበርና፤

ወይትከደኑ በስብሐት፣

በብርሃነ ረድኤቱ ደስ ይላቸ ዋል፤

አንድም በብርሃነ ረድኤቱ ይሠወራሉ፤ ብርሃንማ ይገልጣል እንጂ ይሠውራል፤ ቢሉ ሠውር እንጂ ቢለው ይሠውራል፤

አንድም በጌትነቱ ይሠወራሉ፤

፮፣ ወይከውን ጽላሎተ በመርቄ፣

በቆላ የተገኘ ጥላ ደስ እንዲያሰኝ ለእስራኤል የተሰጠ ረድኤት ደስ ያሰኛል፤

ወክዳነ በዘይትገለበቡ እምጠል ወእምዝናም፣

ከዝናም ከካፊያ የተነሣ የለበሱት ልብስ ደስ እንዲያሰኝ ለቤተ እስራኤል የተሰጠ ረድኤት ደስ ያሰኛል፤ ባለጸጋ ቢሆን በርኖስ፣ ድሀ ቢሆን ገሳ ይለብሳልና::

ምዕራፍ ፭

፩፣ አኀሊኬ ለፍቁርየ ማኅሌተ፣

ለወዳጄ ለቤተ እስራኤል የኀዘን ዘፈን እዘፍናለሁ፤ የኀዘን ዘፈን አለና ካህን ሲሞት መቋሚ ያውን፣ ጸናጽሉን ፤ ቋዱን፣ ቀሽመሬውን ይዘው እንዲያ ለቅሱ፤ ወታደር ሲሞት ጋሻውን፣ ጦሩን፣ ጐራዴውን ይዘው እንዲያለቅሱ፤

አንድም እትናገርኬ ነገረ እትኔበይኬ ትንቢተ ሲል ነው፤ ነገር ትንቢት እናገራለሁ

ሁለቱም አርእስት ነው፤ ለሁለቱም ያመጣል፤

እንዘይብል ዐፀደ ወይን ኮነ ለፍቁር በብሔር ጥሉል፣

እንተ ታውኅዝ ሀሊበ፤

በሚላት በኢየሩሳሌም ለፍቁር ለእግዚአብሔር የሕጉ ማደሪያ እስራኤል ነበሩት፤

፪፣ ወውስተ ማዕዘንቱ ፀቈንኩ ሎቱ ፀቈነ፣

በዙሪያው ቅጽር ቀጸርሁለት ማለት ረድኤት ሰጠሁት፤

ወአግዘዝኩ ሎቱ፣

ገረገር ሁለት ማለት ቅጽሩን፤

አንድም ረድኤቱን አጸናሁለት፤

ወተከልኩ ውስቴቱ ወይነ ኅሩየ ዘሴሬቅ፣

በውስጡም የተመረጠ የሴሬቅን ወይን ተከልሁበት፤ የሴሬቅ ወይን ከዓመት ሦስት ጊዜ ያፈራል፤ እስራኤልም ከዓመት ሦስት ጊዜ ለበዓል ይወጣሉና፤ ጥቅስ ለያስተርኢ ተባዕትከ ሠለስተ ጊዜያተ ለለዓመት ባለው ፤ ዘዳግ (፲፮÷፲፮) ፤ አንድም አንዱ ዘለላ ነጭ ጥቁር ቀይ ያፈራልና፤

አንድም አንዱ ፍሬ ቀይ ጥቁር ነጭ ይሆናል፤

እንደዚህም ሁሉ ከቤተ እስራ ኤል ክህነት መንግሥት፤ ትንቢት አይታጣምና፤

ወሐነፅኩ ማኅፈደ ማዕከሎ፣

በመካከሉ ለጠባቆች ግንብ ሠራሁ፤

ወአክረይኩ ሎቱ ምክያደ፣

ጕድጓድ አስቈፈር ሁለት በሀገራቸው ልማድ ተናግ ሮታል፤ በሀገራቸው ጕድጓድ ቈፍረው እንደ ፍንጃል ያለ ጭቃ አለ ውስጡን በዚያ ይለብጡታል፤ የተበሳሳ ብረት አምጥተው ይገጥሙታል፤ ፍሬ ውን እየለቀሙ በዚያ ላይ ይደፉታል፤ ጐበዝ ቀለል ያለ ልብስ ለብሶ ያሸዋል፤ እየወረደ ከታች ይከማቻል ፤ ከራሚ የወይን ጠጅ የሚሆን ይህ ነው፤ አንድም ማኅፈደ ደብተራ አሪትን ቤተ መቅደስን ሠራ ሁለት፤ ምክያደ ምሥዋዐ ብርትን ሠራሁለት፤ አንድም ማኅፈደ ልዕልና መንግሥትን ሰጠሁት ፤ ምክያደ ስፍሐ አእምሮን አሳደርኩበት፤

ወእምዝ ጸናሕክዎ ይፍረይ አስካለ፣

ከዚህ በኋላ ፍሬን ያፈራል ብዬ ጠበቅሁት፤

www.ethiopianorthodox.org

ወፈረየ አሥዋከ፣

እሾኽን አፈራ፤ አንድም እስራኤልን ምግባር ትሩፋት ይሠራል ብዬ ደጅ ጠናሁት፤ ወፈረየ አሥዋከ፣ ኃጢአት ሠራ፣ ጣዖት አመለከ፤

፫፣ ወይእዜኒ ሰብአ ይሁዳ ወእለኒ ትነብሩ ኢየሩሳሌም፣

አሁንም በይሁዳና በኢየሩሳሌም የምትኖሩ፤

ፍትሑ ማዕከሌየ ወማዕከለ ዐፀደ ወይንየ፣

በእኔና በእስራኤል መካከል ፍረዱ በጎ በጎዎችን እንዲህ ይላቸዋል፤

፬፣ ምንተ እንከ ዓዲ እግበር ለወይንየ ዘኢገበርኩ ሎቱ፣

ለወገኔ ለእስራኤል ምን ያላደረ ግሁለት አለና ምን ላድርግ ለት፤ አንድም ምን ያላደረግ ሁበት አለና ምን ላድርግበት፤

ናሁ ጸናሕክዎ ለወይንየ ይፍረይ አስካለ ወፈረየ አሥዋከ፣

እነሆ ፍሬ ያፈራ ዘንድ ጠበቅ ሁት፤ እሾኽ አፈራ፤

አንድም ምግባር ትሩፋት ይሠራል ብዬ ደጅ ጠናሁት፤ ኃጢአት ሠራ ጣዖት አመለከ፤

፭፣ ወይእዜኒ እነግረክሙ ዘእሬስዮ ለወይንየ፣

እትናገርኬ ነገረ ላለው ጨርሶ እትኔበይኬ ትንቢተ ላለው አመጣ አሁንም እናንተስ አልነ ገራችሁኝምና ወይኔን የማደርገውን እነግራችኋለሁ አለ፤ እስራኤልን የማደርገውን እነግራችኋለሁ፤

እነስት ፀቄኖ፣

ቅጽሩን አፈርሰዋለሁ ማለት ረድኤቱን አርቃለሁ፤

ወይትሐበለይዎ ነኪራን፣

ያልተከሉት ፍሬውን ይለቅ ሙታል ማለት አሕዛብ ገንዘቡን ይበዛበዙታል፤

ወአአትት ጥቅሞ፣

ረድኤቱን አርቃለሁ፤

ወይከውን ምክያደ፣

የአሕዛብ መገሳገሻ ይሆናል፤

፮፣ ወአነድኅ፣

ወይኑን እጥለዋለሁ ክረምት፤ ግዘፍ እንዲነሣ ብለው ከምድር ጥለውት ይከርማሉ፤ ኋላ በበጋ ያነሡታልና እስራኤልን በመከራ እጥለዋለሁ፤

ወኢይገምዶ፣

የወራ የወራውን አልቈርጥ ለትም ማለት ክፉ ክፉዎችን ለይቼ አላጠፋለትም፤

ወኢይከርዮ፣

አልቆፍረውም፤ ቍጭር የሚባል እንደ እንቅርት ያለ አለ፤ ያንን ቆፍረው አውጥተው አዲስ አፈር ሲያስታቅፉት ያፈራል፤ እንደዚህም ሁሉ አጅማኮንታን አላጠፋሉትም፤

ወይበቍል ሣዕር ወሦክ ውስቴቱ፣

እሾህ ሣር ይበቅልበታል ማለት ፍትወታት እኩያት ኃጣውእ ይሰለጥኑበታል፤

ወይማስን እንከ፣

ፈጽሞ ይጠፋል፤

ወእኤዝዝ እንከ ደመና ከመ ኢያዝንም ዝናመ ላዕሌሁ፣

ደመና እንግዲህ ወዲህ ዝናም እንዳያዘንም አዝዘዋለሁ ማለት ዝናም ለዘር፤ ጠል ለመከር እንዳይሰጥ አደርገዋለሁ፤

አንድም ኢይኤዝዝ ከመ ያዝንም ይላል፤ ዝናም ለዘር ጠል ለመከር ይሰጥ ዘንድ አላዝዘውም፤ አንድም ነቢያት ካህናትን እንዳያስተምሩ አደርጋቸዋለሁ፤ አንድም ያስተምሩ ዘንድ አላዝዛቸውም፤

፯፣ ዐፀደ ወይኑሰ ለእግዚአብሔር ቤተ እስራኤል ውእቱ ወሰብአ ይሁዳ ውእቱ ሐዲስ ተክል ዘአፍቀሮሙ፣

ዐፀደ ወይን ኮነ ለፍቁር በብሔር ጥሉል ብሎ ነበርና፤ ዐፀደ ወይኑም የተባሉ የወደዳቸው አዲስ ተክል የሚሆኑ አሥሩ ነገድ ሁለቱ ነገድ እስራኤል ናቸው፤ አንድም ከመ ተክል ሐዲስ ዘአፍቀሮሙ ይላል እንደ አዲስ ተክል የወደዳቸው አሥሩ ነገድ ሁለቱ ነገድ ናቸው፤

ሐዲሰ ተክለ ዘአፍቀሩ አዲስ ተክል ጣዖትን የወደዱ፤

ወጸናሕክዎሙ ይግበሩ ጽድቀ ወገብሩ ዓመፃ፣

ጸናሕክዎ ለወይንየ ያለውን ይተረጕማል፤ እስራኤልን ምግባር፤ ትሩፋት ይሠራሉ ብዬ ጠበቅኋቸው፤ ኃጢአት ሠሩ፣ ጣዖት አመለኩ፤

ወአኮ ርትዐ ዘእንበለ ገዓር፣

የቀና ፍርድን የፈረዱ አይደሉም፤ ድሀውን ከማስጮህ በቀር፤

አንድም የቀና ሕግን የያዙ አይደሉም፤ ከቤተ ጣዖት ገብተው ስምዓኑ በዓል፣ ስምዓኑ በዓል ከማለት በቀር፤

www.ethiopianorthodox.org

፰፣ አሌሎሙ ለእለ ያስተእኅዙ ቤተ ምስለ ቤት፣

ቤትን ከ ቤ ት አያይዘው ለሚሠሩ ሰ ዎ ች ወዮላቸው፤ ባለጸጋው ሂዶ ከድሀው አጠ ገብ፤ ቤት ይሠራል፤ ድሀው ምግብ ለመሻት ሂዶ ሳለ ፈረሱ፤ በቅሎው፤ ገረዱ ሎሌው ቤቱን፣ አጥሩን ያፈርሱበታል፤ ምነው ቤቴን አጥሬን አፈረሳችሁብኝ ይላቸዋል፤ ምን እንበልህ ገንዘብ ትለን እ ን ደ ሆ ነ ወርቁን እንስጥህ ቦታም ትለን እንደ ሆነ ከዚህ የ በ ለ ጠ እናንጥፍልህ ይሉታል፤ እንዲህ ማለታቸው ሊቀሙት ነው፤

ወእለ ያስተቃርቡ ገራህተ ምስለ ገራህት ከመ ይቅሥጡ ዘኮነ እምገራህተ ቢጾሙ፣

እርሻን ከ እ ር ሻ አቃርበው ለሚያርሱ ወዮላቸው፤ ከባልን ጀራቸው እርሻ የሆነውን ያህል አንድ ትልም፤ ሁለት ትልም ይሰርቁ ዘንድ ይህስ ቅሚያ ይባላል እ ን ጂ ስርቆትም አይባል ብሎ አንድ ምላሽ ሁለት ምላሽ ይሰርቁ ዘንድ፤

አንድም ዘኢኮነ ይላል ገንዘ ባቸው ያይደለውን ከባልንጀ ራቸው እርሻ አንድ ድግር ሁለት ድግር ይሰርቁ ዘንድ

ሁለቱም አ ር እ ስ ት ነው ለሁለቱም ያመጣል፤

ወይፈቅዱ ያ ግ ም ር ዋ ለምድር ባሕቲቶሙ፣

ምድርን ብቻቸውን አካተው ይወርሷት ዘ ን ድ ለሚወዱ ሰዎች ወዮላቸው፤

፱፣ እስመ ተሰምዐ ዝንቱ ነገር ውስተ ዕዝነ እግዚአብሔር ፀባዖት፤

ይህ ነገር ከ አ ሸ ና ፊ ከእግዚ አብሔር ዘንድ ደርሶአልና፤

፲፣ ወእመኒ አብዛኅክሙ አብያተ ይከውኑ መዝበረ፣

ቤተ ምስለ ቤት ላለው አመጣ፤ ቤቶችንም አብዝታችሁ ብት ሠሩ ምዝቡራተ ሲል ነው፤ የተፈቱ ይሆናሉ፤

ወእንዘ ዐበይት ወሠናያን እሙንቱ አልቦ ዘይነብር ውስቴቶሙ፣

ያማሩ የ ተ ነ ጠ ፉ የተጋረዱ የተንቈጠቈጡ ሲሆኑ የሚኖ ርባቸው የለም፤

፲፩፣ ወኢያሠልጡ አሠርቱ ዕምደ አባዕር፣

ገራህተ ምስለ ገራህት ላለው አመጣ፣ አሥር ጥማድ በሬዎች ግዳጅ አይፈጽሙም፤

ወኢይገብሩ አሐደ ፃሕበ፣

አንድ ፊቀን ወይን አያስ ገኙም፤

ዘዘርዐ ስድስ ያአቱ ሥልሰ፣

ስድስት ማድጋ የዘራ ሦስት ማድጋ ያገባል፤ ቍልቍል ንግድ ነው፤

አንድም ዘዘርዐ ሆሜረ ያአቱ ኢፈ ይላል፤ ሃያ ማድጋ የዘራ አሥር ማድጋ ያገባል፤

፲፪፣ አሌሎሙ ለእለ ይገይሡ በጽባሕ ቤተ መያሲ፣

ሲጠባ ገሥግሠው ከመሸተኛ ቤት ለሚሄዱ ወዮላቸው፤

ወይውዕሉ ውስተ ስ ታ ይ ወያነ ድዶሙ ወይን፣

ሲጠጡ ለሚውሉ ወይን ለሚያ ነድዳቸው ወዮላቸው፤

አንድም ወያነድዶሙ ወይን

ወይን የ ገ ደ ለ ው ን ወይን ያድነዋል ብ ለ ው አብዝተው ለሚጠጡ ሰዎች ወዮላቸው፤

አንድም ወይን ማጣቱ ለሚያ ናድዳቸው ወዮላቸው፤

፲፫፣ ወይሰትይዎ ለወይን እንዘ የኀልዩ በመሰንቆ ወበከበሮ ወበዕ እንዚራ ይሰትይዎ ለወይን፣

መሰንቆውን፤ ከበሮውን በገና ውን እየመቱ እየዘፈኑ ወይኑን ለሚጠጡት ወዮላቸው፤

አንድም መ ሰ ን ቆ እየመቱ፣ ከበሮ እየጸፉ በገና እየደረደሩ

ወይኑን ለሚጠጡት ሰዎች ወዮላቸው፤

ወኢይኔጽሩ ግብረ እግዚአብሔር፣

እግዚአብሔር የፈጠረውን ሥነ ፍጥረት ለማይመለከቱ ወዮላ ቸው፤ ሲጠጡ ውለው ፀሐይ ገባ ጨረቃ ወጣ እንተወው ለማይሉ ሲጠጡ አድረው ፀሐይ ወጣ ጨረቃ ገባ እንተወው ለማይሉ ወዮላቸው፤

ወኢይሬእዩ ተግባረ እደዊሁ፤

አሠርቱ ቃላትን ለማይመ ለከቱ ወ ዮ ላ ቸ ው፤ አንድም ግብረ እግዚአብሔር ኢታም ልክን ተግባረ እደዊሁ ዘጠ ኙን ሕግጋት ለማይመለከቱ ሰዎች ወዮላቸው፤

፲፬፣ ወበእንተ ዝንቱ ተዒወው ሕዝብየ፣

ስለዚህ ነገር ወገኖቼ ተማረኩ፤

እስመ ኢ ያ እ መ ር ዎ ለእግዚአ ብሔር፣

እግዚአብሔርን በሕግ በአምል ኮት አላወቁትምና፤

ወበዝኃ አብድንቲሆሙ በረኃብ ወበዕምዐ ማይ፣

በረኃብ በ ዕ ም ዕ የሞተው ሬሳቸው በዛ፤

፲፭፣ ወአርኅበ ሞት ነፍሶ፣

ሞት ሆ ዱ ን አሰፋ ማለት ቢገድል ቢገድል በቃኝ አላለም፤

www.ethiopianorthodox.org

ወአብቀወ አፉሁ ሲአል፣

መቃብርም አፉን ከፈተ ማለት ቢቀበል ቢቀበል በቃኝ አላለም፤ አንድም ወአርኀበ ሞት ነፍሶ ስልምናሶር እስራኤልን ቢማርክ ቢማርክ በቃኝ አላለም፤

ፋርስ ባቢሎንም እስራኤልን ብትቀበል ብትቀበል በቃኝ አላለችም፤ አንድም ዲያብሎስ አምስት ሺህ ከአምስት መቶ ዘመን ቢያስት ቢያስት በቃኝ አላለም፤ ሲአልም ነፍሳትን ብትቀበል ብትቀበል በቃኝ አላለችም፤

ከመ ኢያትርፍ፣

ስልምናሶር ምንም ምን እንዳያስቀር፤ አንድም ዲያብሎስ ምንም ምን እንዳያስቀር፤

ወይወርዱ ውስቴቱ ክቡራን፣

ነገሥታቱ፤

ወዐበይት፤

መኳንንቱ፤

ወአብዕልት፣

ባለጸጎች፣

ወኃጥኣን፣

ድሆች፣

(ጥቅስ) አነ ወወልድየ ሰሎሞን ንከውን ኃጥኣነ እንዲል፤ ፩ ነገ ፩÷፳፩፤

እነዚህ ሁሉ ተማርከው ይወርዳሉ፤

አንድም አብዕልት ኃጥአን ይላል ባለጸጎች ኃጥአን ተማርከው ይወርዳሉ፤

አንድም ወይወርዱ ውስቴቱ ክቡራን ብለህ መልስ፤ ጻድቃን ወዐበይት ነገሥታት መኳንንት፣ ወአብዕልት ባለ ጸጎች ወኃጥአን ድሆች ወደሲኦል ይወርዳሉ፤ (ጥቅስ) ኢይምሕሮ ለባዕላይ እንበይነ ብዕሉ ወለነ ዳይኒ እንበይነ ንዴቱ እንዲል፤ (ቅዳ. አትና.)፤

አንድም አብዕልት ኃጥአን ባለጸጎች ኃጥአን ወደሲኦል ይወርዳሉ፤

፲፯፣ ወየኀሥር ሰብእ ወየሐረትም ዕጓለ እመሕያው፣

ሰው ሁሉ ይዋረዳል ይጐሰቍላል፤

ወየኀሥራ አዕይንተ ዕቡያን፣

የትዕቢተኞች ዓይን በሞት ይፈስሳል፤

፲፯፣ ወይትሌዐል እግዚአብሔር ወባያት በጽድቅ ወበርትዕ፣

አሸናፊ እግዚአብሔር በውነት ነገር፤ በቀና ነገር ልዕልናውን ይገልጣል፤

ወይሴባሕ አምላክ ቅዱስ በጽድቅ፣

ፅኑዕ ክቡር የሚሆን ፈጣሪ በእውነት ይመሰገናል፤

፲፮፣ ወይትረዐዩ ከመ አሥዋር አለ ተማህረኩ፣

የተማረኩ እስራኤል እንደገች ወይፈን ይሰማራሉ፤

አንድም እንደተማረኩ ገቾች ይሰማራሉ፤

አንድም እንደገች የተማረኩ እስራኤል በፋርስ በባቢሎን ይሰማራሉ፤

ወይትረዐዩ ከመ አባግዕ ሐቅለ እንዘ የኀሣሡ ሲሳያተ አለ ተረስዑ፣

በበጎ ዘመን የተዘነጉ ጂዋት እንጂሞን ሲሹ እንደ በግ በምድረ በዳ ይሰማራሉ፤

አንድም ከቂሮስ ከዳርዮስ ግብር የተዘነጉ፤ አንድም ከልበ ሥላሴ የተዘነጉ እስራኤል እንደ በግ በምድረ በዳ ይሰማራሉ፤

በሥላሴ ዘንድ ዝንጋዔ ኑሮ አይደለም፤ ሥራቸው የሚያዘነጋቸው ስለሆነ እንዲህ አለ፤

፲፱፣ አሌ ሎሙ ለእለ ይስሕብዋ ለኃጢአቶሙ ከመ ሐብል ነዋህ፣

ኃጢአታቸውን እንደ ረዥም ገመድ ስበው ጐትተው ለሚያመጧት ሣለት በኃጢአታቸው ስልምናሶርን፤ ናቡከደነፆርን ስበው ጐትተው ለሚያመጧቸው ሰዎች ወዮላቸው፤

አንድም ገመድ በገመድ ላይ ሲቀጥሉት እንዲረዝም ኃጢአታቸውን አብዝተው ለሚሠሩ ሰዎች ወዮላቸው፤

አንድም ረጅም ገመድ ከሩቅ እንዲያመጣ የኃጢአታቸውን ፍዳ ከሰማይ ከፋርስ ለሚያመጧት ወዮላቸው፤

ወየዐሥርዋ ከመ አርዑተ ብዕራይ ለዐመሳሆሙ፣

ቀንበር በበሬ አንገት ላይ እንዲሰማማ ኃጢአታቸውን አስማምተው ለሚሠሩ ወዮላቸው፤

አንድም ቀንበር ሁለቱን አንድ እንዲያደርግ በደላቸውን ከሰው ነታቸው ጋራ አንድ ለሚያደርጉ ወዮላቸው፤

፳፣ አለ ይብሉ ፍጡነ ይግበር ወንርአይ፣

ፈዋፈ አለ ቢሉአቸው አንደ ፈርም መሰሏቸው ፈዋፈን ፈጥኖ ያድርግ፤ ወንርአይ ተደርጎ እንይ ለሚሉ ወዮላቸው፤

ወትምጻእ ምክረ ቅዱሰ እስራኤል፣

ጽንዐ እስራኤል ክብረ እስራኤል የመከራት ፈዋፈ ትምጣ፤

www.ethiopianorthodox.org

ወናእምር እንከ፣

ተደርጋ እ ን ወ ቃ ት ለሚሉ ወዮላቸው ፍና ተሣልቆ፤

፳፩፣ አሌ ሎሙ ለእለ ይብልዎ ለእኩይ ሠናየ ወለሠናይ እኩየ፣

ክፉውን መልካም፤ መልካሙን ክፉ ለሚሉ ወዮላቸው፤

አንድም ነቢየ ሐሰቱን ነቢየ ጽድቅ፣ ነቢየ ጽድቁን ነቢየ ሐሰት ለሚሉ ወዮላቸው፤

እለ ይብልዎ ለብርሃን ጽልመተ ወለጽልመት ብርሃነ፣

ብርሃኑን ጨለማ፣ ጨለማውን ብርሃን ለሚሉ ሰዎች ወዮላ ቸው፤

አንድም እግዚአብሔርን ጣዖት፤ ጣዖቱን እግዚአብሔር ለሚሉ ሰዎች ወዮላቸው፤

እለ ይብልዎ ለጥቡም መሪረ ወለመሪር ጥቡመ፤

ጣፋጩን መራራ፤ መራራውን ጣፋጭ ለሚሉ ሰዎች ወዮላ ቸው፤

አንድም ሕገ እግዚአብሔርን ሕገ ጣዖት፤ ሕገ ጣዖቱን ሕገ እግዚአብሔር ለሚሉ ሰዎች ወዮላቸው፤

፳፪፣ አሌ ሎሙ ለእለ ይጠበቡ ለእከይ፣

በክፉ ነገር ለሚራቀቁ ወዮላ ቸው፤

ወይብሉ ንሕነ ከመ ጠቢባን፣

እኛ እንደ ኢያኔስ እንደ ኢያን በሬስ ነን ለሚሉ ወዮላቸው፤

፳፫፣ አሌ ሎሙ ለጽኑዓን እለ ይሰትይዎ ለወይን፣

ወይኑን ለሚጠጡ ለጽኑዓን ወዮላቸው፤ ስንጠጣ ውለን ስንጠጣ ብናድር አንሰክርም ለሚሉ ወዮላቸው፤ ይህ ጽንዕ ወይን ለመጠጣት ነው እንጂ የጉልበት አይደለም፤

ወይነሥኡ ሕልያነ፣

መማለጃ ለሚቀበሉ፤

ወይዔምዕዎ ለጻድቅ፣

ጻድቁን አመፀኛ ለሚሉ፤

ወለኃያላን እለ ይቶስሕዎ ለሜስ፤

የማሩን ጠጅ ከወይኑ ጠጅ ቀላቅለው ለሚጠጡ ወዮላ ቸው፤ በሀገራቸውስ የማር ጠጅ የለም ብሎ የወይኑን ጠጅ ከአረቂ ቀላቅለው ለሚጠጡ ሰዎች ወዮላቸው፤

፳፬፣ ወያጸድቅዎ ለኃጥእ፣

ኀጥኡን ጻድቅ ለሚሉ፤

ወይሤውርዋ ለጽድቁ፣

መማለጃ ተቀብለው ሐሰተኛ ውን እውነተኛ ለሚሉ፤

አንድም ይ ሙ ት በቃውን ይድን በቃ፣ ይድን በቃውን

ይሙት በቃ ለሚሉ ወዮላ ቸው፤

፳፭፣ በእንተ ዝንቱ ከመ ይነድድ ሐሠር በአፍሐመ እሳት፣

ስለዚህ ነገር ገለባ በእሳት እንዲቃጠል፤

ወይውዒ በነበልባል፣

በነባልባሉ እንዲቃጠል፤

ከማሁ ይ ት በ ላ ዕ ሥርዎሙ ወርእሶሙ፣

አንድ ወገን አባትነታቸው ይጠ ፋል፤ አ ን ድ ም ሥርዎሙ፤ ልጅነታቸው፤ ወርእሶሙ ራሳ ቸው ይጠፋሉ፤

አንድም ሥርዎሙ ሰውነታ ቸው ወርእሶሙ፤ አለቃቸው ይጠፋል፤

እስከ የዓርግ ጢስ እምኔሆሙ፤

ዜና ጥፋታቸው እስኪሰማ ድረስ እምኔሁ ቢል ከሞታቸው የተነሣ እምኔሆሙ ቢል ከእርሳቸው ሞት የተነሣ፤ አንድም እምኔሁ ከእግዚአብሔር የተነሣ፤

እስመ ኢፈቀዱ ሕገ እግዚአብሔር ፀባዖት፣

የአሸናፊ የእግዚአብሔርን ሕግ አልወደዱምና፤

ወአምዕዕዎ ለቅዱሰ እስራኤል፣

ቅዱሰ እስራኤልን ክቡረ እስራ ኤልን አሳዝነውታልና፤

፳፮፣ በእንተ ዝንቱ ተምዐ እግዚ አብሔር ፀባዖት ፀቢየ መዐተ ላዕለ ሕዝቡ፣

ስለዚህ ነገር አ ሸ ና ፊ እግዚ አብሔር በወገኖቹ ላይ ፈጽሞ ፈረደ፤

ወአንሥአ እዴሁ ላዕሌሆሙ፣

እደ መዓቱን አነሣባቸው፤

ወቀሠፎሙ፣

በመከራ ገረፋቸው፤

ወተምዐ መዐተ ላዕለ አድባር፣

በነገሥታቱ ላይ ፈረደ፤

ወኮነ አብድንቲሆሙ ከመ መሬት ማዕከለ ፍኖት፣

ሬሳቸው በጎዳና አጠገብ እንዳለ ትቢያ በዛ፤

ወምስለ ዝንቱ ኵሉ ኢተመይጠት መዓቱ፣

ይህም ይህ ነው፤ ከዚህም ጋራ መዐቱ መቅሠፍቱ አልተመ ለሰችም

ወዓዲ እ ዴ ሁ ለእግዚአብሔር ልዕልት፣

ልዕልት የምትሆን የእግዚ አብሔር ሥልጣኑ ዳግመኛ አልተመለሰችም፤ አ ን ድ ም ዓዲሃ ልዕልት ገና እንደተ ቃጣች ናት፤

www.ethiopianorthodox.org

፳፯፣ ወይእዜኒ ይገብር ተአምረ ለአሕዛብ ርኁቃን፣

አሁንም በሩቅ ላሉ ለአሕዛብ ተአምራቱን ያደርጋል፤ ለነሰ ናክሬም ያሉ እንደሆነ በውነት መልአኩ ቅዱስ ሚካኤል በነጭ በግ አምሳል እየመራ ይዟቸው መጥቷልና ለነናቡከደነፆር ያሉ እንደሆነ ወደፊት ያመጣዋል፤

ወይስሕቦሙ እምአጽናፈ ምድር፣

ስልምናሶርን ናቡከደነፆርን ከፋርስ ከባቢሎን ስቦ ጐትቶ ያመጣቸዋል፤

ወናሁ ይመጽኡ ፍጡነ እንዘ ይረውጹ፣

እነሆ ፈጥነው ይመጣሉ፤

፳፰፣ ኢይርኅቡ ወኢይፀምዑ፣

የለናቡከደነፆርን ምልክት አመጣው አይራቡም፣ አይጠሙም፤

ወኢይደክሙ፣

አይደክሙም፤

ወኢይዴቅሱ፣

የሞት እንቅልፍ አያንቀላፉም፤

ወኢይፈትሑ ቅናውቲሆሙ እምሐቄሆሙ፣

ዝናራቸውን ከወገባቸው አይፈቱም፤

ወኢይትበተክቶታነ አሣዕኒሆሙ፣

የጫማቸው ማዘቢያ አይቈረጥም፤

፳፱፣ ወበሊሕ መዓብሊሆሙ፣

ዓረብ ቃራ ጪሆ የሚሆን ሰይፋቸው የተሳለ ነው፤

ወውሱቅ አቅስስቲሆሙ፣

ቀስታቸው የተቀፈረ ነው፤

ወከመ ዕብን ጽኑዕ እግረ አፍራሲሆሙ፣

የፈረሳቸው ኮቲ እንደ ደንጊያ ጽኑዕ ነው አያጐበጕብም፤

ወመንኰራኵረ ሠረገላቲሆሙ ይረውጽ ከመ አውሎ፣

የሠረገላቸውም መንኮራኵር እንደ አውሎ ፈጣን ነው፤

፴፣ ወከመ አናብስት ይቀውሙ፣

እንዋጋ ባሉ ጊዜ እንደ አንበሳ በማስፈራት ይቆማሉ፤

ወከመ ዕጓለ አንበሳ ይመሥጡ፣

እንማርክም ባሉ ጊዜ እንደ አንበሳ ግልገል ይነጥቃሉ፤

ወይጥኅሩ ከመ አርዌ ዘይወፅእ እምግቡ፣

ከመ ዘወፅአ እምግቡ ሲል ነው፤ ከጕድጓዱ እንደ ወጣ እባብ ያ ነድፎ እንዲንጸረጸር ማለት እንዲጮህ ገድለው፤ ሰልበው ይደነፋሉ፣ ያገራሉ፤

አንድም እንዳለ ይሆናል፤ ያ ለመንደፍ ሲወጣ እያዘመረ እንዲወጣ እነሱም እያዘመሩ ይወጣሉ፤

ወአልቦ ዘያድኅኖሙ፣

የሚያድናቸው የለም፤

፴፩፣ ወይእተ አሚረ የዐወይዉ በበይናቲሆሙ ከመ ድምፀ ባሕር ዘይትሀወክ፣

ያንጊዜ እንደሚታወክ እንደ መጣያ ውሀ እርስ በርሳቸው ይጮኻሉ፤

ወይኔጽሩ ውስተ ምድር፣

ምድር ምድር ይመለከታሉ፤ ቡቃያ ለማየት፤

ወይሬእዩ ጽልመተ ጽፉቀ፣

ጽኑ ድርቅን ያያሉ፤ አንድም ወይኔጽሩ ውስተ ምድር አንገታቸውን ይደፋሉ፤

ሰቢረ ክሣድ ትእምርተ ኃዘን ነውና፤

ወይሬእዩ ጽልመተ ጽፉቀ፤ ጽኑ መከራ ያያሉ፤

ወይትመነደቡ፣

በመከራ ይጨነቃሉ፤

ጉባዔ፣

ምዕራፍ ፮

፩፣ ወእምዝ በዓመተ ሞተ ዖዝያን ንጉሥ፣

እስከ ዝ ተነበየ በመዋዕለ ዖዝያን ብሎ ያመለክታል፤

እስከ አሁን ድረስ በዖዝያን ዘመን የተደረገውን ሲናገር መጥቶ ነበር፣ እንግዲህ ወዲህ ግን በኢዮአታም ዘመን የተደረገውን ይናገራል፤ በዓመተ ሞተ ዖዝያንም ይላል፤ አናቦ ዖዝያን በሞተበት ወራት፤

አንድም ዖዝያን በሞተ ባመቱ፤

ርኢክዎ ለእግዚአብሔር እንዘ ይነብር ዲበ መንበሩ ነዋኅ ወልዑል፣

ነዋኅ የወርድ ልዑል የቁመት ነው፤ (ጥቅስ) ወአልቦ ዘይመስሎ ቆመ ወኑኅ እንዲል፤

እግዚአብሔርን ልዑል በሆነ በዙፋኑ ላይ ተቀምጦ አየሁት::

ወምሉዕ ቤተ ስብሐቲሁ፣

ብርሃኑ ቤቱን መልቶ አንድም ወምሉዕ ቤት ስብሐቲሁ፣ ቤቱ ብርሃንን መልቶ አየሁት፤

ወሱራፌል ይቀውሙ ዓውጸ፣

ሱራፌል በዙሪያው ቁመው አየሁት፤

ሱራፌል ነገደ ሚካኤል፣ ኪሩቤል ነገደ ገብርኤል ናቸው፤

በዖዝያን ዘመን የነበረው ሊቀ ካህናት አዛርያስ ይባላል፤

በቀኙ እየተቀመጠ ፍርዱን ይገሥበታል፤ ምነው ፍርዴን

www.ethiopianorthodox.org

ትግሥብኛለህ አላው፤ (ጥቅስ) እምነ መንግሥት የዐቢ ክህነት እንዲል፤ እ ባ ል ጥ ህ የለም አለው፤ ዲዲስቅ እኴስ በአባቱ ከነገደ ይሁዳ ብወለድ በእናቱ ከነገደ ሌዊ እ ወ ለ ድ የለም ብሎ ልብሰ ተክህኖውን ለብሶ ሜዕጠንተ ወርቁን ይዞ ቀን አ ለ ቀ ን አጥናለሁ ብሎ ገባ፤ ዳዊት የሠራቸው ሁለት መቶ ሰማንያ ስ ም ን ት መዘምራን ነበሩ፤ አ ይ ሆ ን ም ቢሉት ንጉሥ ነውና ተጋፍቶ ገብቶ ሲያጥን ጢሱ ግንባሩን ቢነካው ለምዕ ወጣበት፤ በሻሽ ሸፈነው፤ ባሻሹ ላይ ወጣበት፤ አሪት ለምፃም በ ከ ተ ማ አይኑር ትላለችና፤

(ጥቅስ) ወአውዕአዎ ዘበአኀስ ሮት፤ ውጣ ውጣ ብለው አስወ ጡት፤ (ጥቅስ) ወነበረ ውስተ ቤተ ሐፍሶት ይላል፤ (፪ ዜና መዋ. ፳፮÷፳)፤

እንደ ተጋዘ ሙቷል፤ (ጥቅስ) ወኮነ ኢዮአታም የዐቅብ ቤተ መንግሥት፤ (፪ ነገ. ፲፭÷፭)፤ ልጁ ኢዮአታም በሱ ተተክቶ እንደ ም ስ ለ ኑ ሁኖ ሲገዛ ኑሯል፤ ያ ን ጊ ዜ ኢሳይያስ ለያዝያን ወዳጁ ነበር፤ ቢመክ ረው፤ ቢያስተምረው ይመለስ ነበር፤ አ ፍ ሮ ት ፈርቶት ሳይመክረው፤ ሳያስተምረው ቀረ፤ ያ ያፈርኸው፤ የፈራኸው ንጉሥ አለፈ እኴ ግን በባሕርዬ ሞት፤ በመንግሥቴ ኀልፊት የለብኝም ፤ በ ዘ ባ ነ ኪሩብ ስሥለስ፤ ስቀደስ እኖራለሁ ሲል እንዲህ ሁኖ ታይቶታል፤ በዚህ ምክንያት ከከንፈሩ ለምፅ ጠጣበት፤ ሃያ ሰባት ዘመንም ይላሉ፤ ሦስት ዓመትም ይላሉ ሀብተ ትንቢት ተነሥቶታል፤ ይኸንንም ይዘው መናፍቃን ለአብ መንበር አለው፤ (ጥቅስ) እግዚአብሔርስ ይነብር ዲበ መንበሩ ቅዱስ፤ መዝ. ፺፪÷፰፤ ለወልድ መ ን በ ር አለው፤ (ጥቅስ) መ ን በ ር ከ እግዚአ ለዓለመ ዓለም፤ መዝ. ፺፬÷፮፤ መንፈስ ቅዱስ ግን ሕፁፀ መንበር ነው ብለዋል፤ ኢሳይያስ እንዘ ይነብር ዲበ መንበሩ ያለውን ጳውሎስ ሠናየ ተነበየ መንፈስ ቅዱስ በአፈ ኢሳይያስ ብሎ ለመንፈስ ቅዱስ ሰጥቶ ተናግሮታል ፤ ኢሳይያስ እንዘ ይነብር ዲበ መንበሩ ያለውን ጳውሎስ ሠናየ ተነበየ መንፈስ ቅዱስ በአፈ ኢሳይያስ ብሎ ለመንፈስ ቅዱስ ሰጥቶ ከተናገረ መንፈስ ቅዱስ ሕፁፀ መንበር አይባልም ብሎ ሊቁ አስማም ቶታል፤

፫፡ ወለለ ፯፻፸፮ ክነፈሆሙ፤

ያንዱም ያንዱም ክንፋቸው ስድስት ስድስት ነው፤

በ፪ቱ ይከድኑ ገጸ-ሙ፤

በሁለቱ ክንፋቸው ፊታቸውን ይሸፍናሉ፤

በወ፪ቱ ይከድኑ እግሮ-ሙ፤

በሁለቱ ክንፋቸው እግራቸ ውን ይጋርዳሉ።

(ጥቅስ) ካመ ኢያውዕዮ-ሙ ነበልባሉ እንዲል፤ ቅዱ. ወል. ነጐ፤ ዋዕየ መለከቱ እንዳያቃጥ ላቸው፤ ያስ ቢሆን አካላቸው አይደለም ቢሉ ትእምርተ ፍርሀት ነው፤ አሁን ሰው ሾተል በመዘዙበት፤ ጦር በነጠ ቁበት ጊዜ እጁን ይጋርዳል አካሉ አይደለም ?

ወበ፪ቱ ይሠሩ እምጽንፍ እስከ ጽንፍ፤

በሁለቱ ክንፋቸው ጽንፍ እስከ ጽንፍ ይበራሉ አለ፤ ትእምርተ ተልእኮ ነው፤

አንድም በሁለቱ ክንፋቸው ፊታቸውን መሸፈናቸው ወደ ላይ ቢጣ- ቢወጡ ባሕርይህ አይመረመርም ሲሉ፤

በሁለቱ ክንፋቸው እግራቸ ውን መሸፈናቸው ወደታች ቢወርዱ ቢወርዱ ባሕርይህ አይመረመርም ሲሉ፤

በሁለቱ ክንፋቸው መብረራ ቸው ጽንፍ እስከ ጽንፍ ቢሄዱ ባሕርይህ አይመረ መርም ሲሉ፤

አንድም በሁለቱ ክንፋቸው ፊ ታ ቸ ው ን መሸፈናቸው በሰማይ ምሉ ነህ ሲሉ፤

በሁለቱ ክንፋቸው እግራቸውን መሸፈናቸው በምድር ምሉነህ ሲሉ፤ በሁለቱ ክንፋቸው ጽንፍ እስከ ጽንፍ መብረራቸው ጽንፍ እስከ ጽንፍ ምሉ ነህ ሲሉ።

አንድም በ ሁ ለ ቱ ክንፋቸው ፊታቸውን ይሸፍናሉ፤ በገጸ ልቡናችን ባሕርይህን እንመረ ምራለን ሲሉ፤

በሁለቱ ክንፋቸው እግራቸውን ይሸፍናሉ፤ በእግረ ልቡናችን ባሕር ያህን እንመረምራለን፤ ሲሉ፤

በሁለቱ ክንፋቸው ከጽንፍ እስከ ጽንፍ ይበርራሉ፤ የተቻለንን መርምረን ያ ል ተ ቻ ለ ን ን ፤ (ጥቅስ) ለሊከ ትጤይቅ ርእሰከ ብለን እንተዋለን ሲሉ፤

እንዲል፤ ቅዳ.ዮሐ. ወነጐ ፤

አንድም በሁለቱ ክንፋቸው ፊታቸውን ይሸፍናሉ፤ ፊትህን ማየት አይቻለንም ሲሉ፤

www.ethiopianorthodox.org

በሁለቱ ክንፋቸው እግራቸውን ይሸፍናሉ ፤ በፊትህ መቆም አይቻለንም ሲሉ ፤ አንድም በሁለቱ ክንፋቸው ፊታቸውን በሁለቱ ክንፋቸው እግራቸውን ሲሸፍኑ በሁለቱ ክንፋቸው ጽንፍ እስከ ጽንፍ ሲበሩ ትእምርተ መስቀል ይሆናል፤

(ጥቅስ ወይከድኑ ገጸመ· በአርአያ ትእምርተ መስቀል እንዲል አንቀጸ ብርሃን ቅዱስ ያሬድ፣ ከዕለተ ዓርብ አስቀድመው እንዲህ ሁነው መታየታቸው እንዲህ ባለ አርአያ ተሰቅለህ ዓለሙን ታድነዋለህ ሲሉ::

ከዕለተ ዓርብ ወዲህ እንዲህ ሁነው መታየታቸው እንዲህ ባለ አርአያ ተሰቅለህ ዓለሙን አዳንኸው ሲሉ::

፫፣ ወይኬልሑ አሐዱ አሐዱ ምስለ ካልዑ፣

ይኬልሑ ካለ አሐዱ ወካልዑ ምስለ ካልዑም ካለ ይኬልሕ ቢል በቀና ነበር፤ አንዱም አንዱም ከአንዱ ጋራ ጩኸው ያመሰግናሉ፣

ወይብሉ ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ እግዚአብሔር ፀባኦት፤

ጽኑዕ ክቡር ልዩ፤ ጽኑዕ ክቡር ልዩ፣ ጽኑዕ ክቡር ልዩ፤ እያሉ ያመሰግናሉ፡ ቅዱስ ቅዱስ፡ ቅዱስ ብለው ሦስትነቱን እግዚአብሔር ብለው አንድነቱን ተናገሩ፡

አንድም ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ ብለው አንድነቱን እግዚአብሔር ብለው፤ ሦስትነቱን ተናገሩ፡ እግዚአብሔር የሦስቱ ስም ነውና፤ ጥቅስ አንሰ ሶበ እቤ እግዚአብሔር እብል በእንተ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ እንዲል ሃይማኖተ አበው ባስልዮስ፣ አንድም ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ ያለው የሦስትነት ቃሉ አለመለወጡ የአንድነት ፤ አንድም ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ ያለው አንድነት ሦስትነት ይሆናል፤ እየራሳቸው ልብ፣ እየራሳቸው ቃል፣ እየራሳቸው እስትንፋስ ቢኖራቸው ቅዱሳን ቅዱሳን ባሉ ነበርና፤ ጥቅስ ወኢይቤሉ· ቅዱሳን ቅዱሳን አላ ይቤሉ· ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ እንዲል፤

ፍጹም ምሉዕ ሰማያተ ወምድረ ቅድሳተ ስብሐቲከ፣

አሸናፊ እግዚአብሔር ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ ተብለህ የምት መሰገነው ምስጋና በሰማይም በምድርም ፍጹም ነው ምሉ ነው ይላሉ፡

፬፣ ወእምገሣ ተለዐለ መርፈቀ ኖኅት አምቃል ዘይኬልሑ፣

ከዚህ በኋላ ጩኸው ከሚያመሰግኑት ምስጋና የተነሣ የደጁ መድረክ ሐፍ ሐፍ አለ፤ ለጊዜው የኪሩቤልን ትእምርተ ዕርገተ ጸሎታቸውን ሲያሳየው ነው፡ ፍጻሜው ግን የእስራኤልን መማረክ ሲያሳየው ነው፤ አንድም እምቃለ ዘይኬልሑ፣ ከሚያመሰግኑ ከመላእክት ቃል የተነሣ፤

ወመልዐ ቤት ጢሰ፣

ቤቱ ጢስን መላ፤

አንድም ወመልዐ ጢስ ቤተ ይላል፤ ጢሱ ቤቱን መላ፤ ለጊዜው የኪሩቤልን ዕርገተ ጸሎታቸውን ሲያሳየው ነው፤ ፍጻሜው ግን የእስራኤልን መማረካቸውን ሲያሳየው ነው፤

አንድም ፍጹም ጠቡን ሲያሳየው ነው፤ በሀገራቸው ልማድ ተናግሮታል፤ በሀገራቸው አማላጅ የሄደ እንደሆነ ጢስ አጢሰው ቤቱን ጠርገው ይቆዩ ታል፤ እንዳይቀመጥ ትቢያ ይሆንበታል፤ እንዳይቆም ዓይኑን ጢሱ ይወጋዋል አንድ ነገር ሁለት ነገር ተናግሮ ፈጥኖ ይሄዳል፤

እንደዚህም ሁሉ አልማለዳቸውም ሲለው ነው፤

አንድም ከቤት ጢስ ባጤሱ ጊዜ ተሐዋስያን እየወጡ ይሄዳሉ፤ እንደዚህም ሁሉ እስራኤል ይማረካሉ ሲለው ነው፤

አንድም የቄዋቄን ርችት ሲያሳየው ነው፤

፭፣ ወእቤ አሌ ሊተ አነ ኅርቱም፣

ወራዳ ነኝና ወረዳ ለምሆን ለእኔ ወዮልኝ፤

እስመ ሰብእ ርኩሰ ከናፍር አነ፣

እኔ ለምጻም ነኝና፤

አንድም እኔ ለምጻም ነኝና ለምጻም መምህር ለምሆን ለእኔ ወዮልኝ፤ ይህስ አይደለም፤

ወማዕከለ ሕዝብ ዘርኩስ ከናፍሪሁ ሀሎኩ አነ ብሎ ያመጣል፤ እስራኤልን ሁሉ ለምጻም ማለት ይሆናል ብሎ አፋር ነኝና አፋር መምህር ለምሆን ለእኔ ወዮልኝ፤

ወማዕከለ ሕዝብ ዘርኩስ ከናፍሪሁ ሀሎኩ አነ፣

ቢመክሯቸው ቢያስተምራቸው በማይሰሙ ወገኖች መካከል ላለሁ ለእኔ ወዮልኝ፤ አንድም ሕገ እግዚአብሔርን በማያውቁ

www.ethiopianorthodox.org

ወከመ ኢይለብዉ በልቦሙ፣

በልቡናቸውም ልብ እንዳያ ደርጉ አግዘፉ ልቦሙ ላለው፤

ወኢይትመየጡ ኀ ቤ የ ከመ እሣሃሎሙ፣

ይቅር እላቸው ዘንድ ወደእኔ እንዳይመለሱ፤

፲፩፣ ወእቤ አነ እ ስ ከ ማዕዜኑ እግዚአ፣

አቤቱ እኔ አለመላኬ እስከ መቼ ድረስ ነው አልኩት፤

ወይቤለኒ እስከ ይትመዘበራ አህጉር፣

የእስራኤል አገሮች በፄዋዌ እስኪፈቱ ድረስ ነው አለኝ፤ ኢሳይያስ እስከ ፄዋዌ ድረስ ኑሯል ቢሉ መጽሐፉ ስለቆየ ቦሙ ሙሴ ወነቢያት ኪ.ያሆሙ ለይስሙዑ እንዳለው ያለ ነው፤ ሉቃ. ፲፮÷፳፱፤

አንድም እስራኤል አለመመ ለሳቸው እስከ መቼ ድረስ ነው አልሁት ፤ አገራቸው በፄዋዌ እስኪፈታ ድረስ ነው አለኝ፤

ወዮኑልቅ ሰብእ፣

ሰውም እስኪያልቅ ድረስ ነው አለኝ፤ የሕዝቡስ ይሁን ምነው እሱሣ የሞተ በምናሴ ዘመን አ ይ ደ ለ ም ፤ ቢሉ ፍጻሜ የሌለው እስከ ነው፣

ወአልቦ እንከ ዘይነብር ውስተ አብያት፣

እንግዲህ ወዲህ በቤት የሚኖር ሰው የለም፤

ወትተርፍ ባሕቲታ ምድር ከመ በድው፣

ኢየሩሳሌም ብቻ ምድረበዳ ሁና ትቀራለች፤

፲፪፣ ወእምዝ ያነውኖ እግዚአብሔር ለሰብእ፣

ያበዝኖ ሲል ነው፤ ከዚህ በኋላ አሥሩ ነገድ ተማርከው የቀሩ ሁለቱን ነገድ፤ ሁለቱ ነገድ ተማርከው የቀሩ ትሩፋንን እግዚአብሔር ያበዛቸዋል፤

ወይበዝኑ እለ ተርፉ ዲበ ምድር፣

አሥሩ ነገድ ተማርከው የቀሩ ሁለቱ ነገድ፤ ሁለቱ ነገድ ተማርከው የቀሩ ትሩፋን በኢየሩሳሌም ይበዛሉ፤

፲፫፣ ወይከውኑ ትዕሥርተ፣

አሥር እጽፍ ይሆናሉ፤

ወካዕበ ይትነበለይዖሙ፣

ዳግመኛ ይ ማ ር ኪ ቸ ዋ ል ፣ ለአሥሩ ነገድ ሁለቱን ነገድ ለሁለቱ ነገድ መቃብያንን ካዕበ አለ፤

፲፬፣ ወይከውኑ ከመ ዕፀ ጠርቤ ንቶስ፣

እንደ ቡጥም እንጨት ይሆናሉ፤

ወከመ ዕፀወ ሊባኖስ ሶበ ይትነገፍ ቈጽሎሙ፣

ቅጠሉ እ ን ደ ረገፈ እንደ ደጋ ዛፍ ይሆናሉ፤ ገንዘባቸው ተዘርፎ አልቆ ባዶ እጃችውን ይቀራሉ።

ምዕራፍ ፯

ጉባዔ

፩ ወኮነ በመዋዕለ አካዝ ወልደ ኢዮአታም ወልደ አዝያን ንጉሠ ይሁዳ፣

እስከ ዝ ተ ነ በ የ በመዋዕለ ኢዮአታም ብሎ ያመለክታል፤ እስከ አሁን ድረስ በኢዮአታም ዘመን የተደረገውን ሲናገር መጥቶ ነበር፤ ከእንግዲህ ወዲህ ግን በአካዝ ዘመን የተደረገውን ይናገራል፣ በይሁዳው ንጉሥ በኢዮአታም ልጅ በአካዝ ዘመን እንዲህ ሆነ፤

ይርገ ረዓሶን ንጉሠ አራም፣

ኮነ ያለውን ዐርገ ብሎ አመ ጣው፤ የሶርያ ንጉሥ ረዓሶን ዘመተ፤ ታሪክ በአሥሩ ነገድ ፋቁሔ በሁለቱ ነገድ አካዝ ተናግሠዋል፤ የአሥሩ ነገድ ንጉሥ ፋቁሔ ሁለቱን ነገድ መግዛት ቢ ያ ም ረ ው እኔ ለአንተ ልገዛ፤ አንተ እነዚህን ሁለቱን ነገድ አስገዛኝ ብሎ ከረዓሶን ዘንድ ላከበት፤ ይሁን ብሎ ዘመተ አካዝም ይህን ሰምቶ ገብርከኒ ወልድከኒ የግድ ባርያህ ነኝ የውድ ልጅህ ነኝ፤ ነዓ ርድአኒ እምእዴሁ ለንጉሠ ሶርያ ወ እ ም እ ዴ ሁ ለንጉሠ ሰማርያ ብሎ ከቴልጌልቴልፌ ልሶር ዘንድ ላከ፤ ፪ኛ. ፲፮÷፲፯፤ አሆ ይቤሎ እሺ በጀ ብሎ መጣ፤ ደማስቆ ሲደርስ ይቺ የማን አገር ናት ብሎ ጠየቀ፤ የወዳጅህ የአካዝ የጠላቱ የፋቁሔ የወዳጁ የረዓሶን አገር ናት አሉት፤ መርዳት ከየት ይጀመራላ ብሎ ደማስቆን ያጠፋ ጀመር፤ የሰው አገር እናጠፋለን ስትሉ አገራችሁ ጠፋ አሏቸው፤ ተመልሰው ሲዋጉ ረዓሶን ሞተ፤ ቴልጌል ቴልፌልሶር ደማስቆን አጥፍቶ ተመልሷል፤

ወፋቁሔ ወልደ ሮሜልዩ ንጉሠ እስራኤል፣

የእስራኤል ንጉሥ የሮሜልዩ ልጅ ፋቁሔም ዘመተ፤

ይትቃተልዋ ለኢየሩሳሌም፣

ኢየሩሳሌምን ይወጓት ዘንድ ዘመቱ፤

ወስእንዋ ቀተሎታ፣

ማጥፋት ተ ሳ ና ቸ ው ፤ ምነው በሕዙፃን ከአሥራ ሁለት እልፍ

www.ethiopianorthodox.org

የሚበልጡ አጠፉ ይል የለም ቢሉ ጨርሰው ስላላጠፏቸው እንዲህ አለ፡

፪፣ ወዜነውዎሙ ለቤተ ዳዊት፣

ለአካዝ ወገኖች ነገሯቸው፡

ወይቤልዎሙ ፡ነብሩ አራም ምስለ ኤፍሬም፣

የሶርያ ሰዎች ከአሥሩ ነገድ ጋራ አንድ ሆኑ፡ ተባበሩ ብለው ነገሯቸው፡

ወሶበ ሰምዐ ዘንተ ዳዊት ደንገፀት ነፍሱ ወነፍሰ ኵሉ ሕዝቡ፣

አካዝ ይህን በሰማ ጊዜ ልቡናው ደነገጠች፣ የ ሕ ዝ ቡ ም ሁሉ ልቡና ደነገጠች፡ አካዝን ዳዊት አለው፡ ከዳዊት ወገን ስለ ተወለደ (ጥቅስ) ወበህየ አበቀሩል ቀርነ ለዳዊት እንዳለ መዝ. ፻፴፩÷፲፯፣ ዘሩባቤልን ዳዊት ብሎ፡

ወተህውኩ፣

ታወኩ፡

ወከኑ ከመ ዕበወ ገዳም ሶበ ይነፍሖ ነፋስ፣

ነፋስ በ ነ ካ ው ጊዜ ዛፉ እንዲወዛወዝ ወጀጅ ወጀጅ አሉ ተሸበሩ፡

፫፣ ወይቤሎ እግዚአብሔር ለኢሳይያስ ነቢይ ሑር ዛእ ተቀበሎ ለአካዝ፣

እግዚአብሔር ነቢዩ ኢሳይያስን ሂደህ አካዝን ተቀበለው አለው፡ ወዴት ሂዶ ነበር ቢሉ ግባት ለማየት፡ አ ን ድ ም የፊረሰ ግንብ ነበረ ያነን ለማሠራት፡

አንድም አደን ውሎ ነበር፡

አንተ ወኢዮሳብ ወልድከ፣

አንተና ልጅህ ኢዮሳብ ወጥታችሁ ተ ቀ በ ለ ት፡ ኢዮሳብ በእውነቱ ልጁ ነው፡

አንድም ደቀ መዝሙሩ ነው፡ አንድም የደቀ መዝሙሩ ደቀ መዝሙር ነው፡

በነበ ምጥማቃት እንተ ላዕላይ ፍኖተ ገራህተ መሐጥል፣

ታሕታይ አለና ላዕላይ አለ፡ ለሸማ አጣቢ ሪም አድርገው በሰጡት እርሻ አጠገብ ባለው ጐዳና ሂደህ ከላይኛው መዋኛ ከላይኛው መታጠቢያ ተቀበለው፡

አንድም እንድኪ በሚያገቡበት በፍታ በሚያፋጥቁበት በሚያ ሳርፉበት እርሻ አጠገብ ባለው ጐዳና ሂደህ ከላይኛው መዋኛ ከላይኛው መታጠቢያ ተቀበለው አለው፡ በዘያስጥሑ ቦቱ አልባሰም ይላል፡

፬፣ ወበሎ ተውቀብ ወአርምም፣

እዋጋለሁ ከማለት ተጠበቅ፡ እዋጋለሁ አትበል፡

ወኢትፍራህ፣

ድል እነሳለሁ ብለህ አትፍራ፡

ወኢትደንግፅ ነ ፍ ስ ከ እምእሉ ክልዔቱ ትንታጋተ ዕፀው እለ ይጠይሱ፣

አለን አለን ከሚሉ ከረዓሶንና ከሩቁሔ የተነሣ ልቡናህ አትደ ንግጥ፡

እስመ እማሰል እምድኅረ ቀውሩኩ በመዓትየ፣

ተቈጥቼ ካጠፋሁ በኋላ ይቅር እላለሁና እ ን ዳ ጠ ሩ በዚህ ይታወቃል፡

፮፣ ወልደ አራምስ ወወልደ ሮሜልዩ ተማከሩ እኩየ ምክረ ላዕሌከ፣

የሶርያው ንጉሥ ረ ዓ ሶ ን ና ሩቁሔ ወልደ ሮሜልዩ ባንተ ላይ ክፉ ምክር ተማከሩ፡ ተማማሉ፡

እንዘ ይብሉ ንዑ ንዕርግ ይሁዳ ወንማኢሙ ኀቤነ፣

ኑ ወደ ይሁዳ እንዝመት፡ ግርከን ወደእኛ እንመልሳቸው ብለው፡

ወይቤሉ ናንግሥ ለሙ ወልደ ጣብሔል፣

የጣብሔልን ልጅ እናንግሥላ ቸው አሉ፡ ከ ላ ይ ወ ል ደ ሮሜልዩ አለ፡ ከዚህ ወልደ ጣብሔል አለ፡ እንደምን ነው አይጣላም ቢሉ አ ይ ጣ ላ ም ፡ ጣብሔል እናቱ፡ ሮ ሜ ል ዩ አባቱ ነው፡

አንድም ለአንድ ሰው ሁለት ስም አለው፡

አንድም ጣ ብ ሔ ል አያቱ ሮሜልዩ አባቱ ነው፡

አንድም አንዱ የወለደው አንዱ ያሳደገው ስም ነው፡

፯፣ ከመዝ ይቤ እግዚአብሔር ወባያት፣

አሸናፊ እግዚአብሔር እንዲህ አለ፡

ዛቲ ምክሮሙ ኢትጸንዕ፣

ይች ምክራቸው አትጸናም፡

ወኢትከውናሙ፣

ኢ ት ረ ብሐ ሙ ፡ ወኢ ት በቀኑ ያሙ ሲል ነው፡ አ ት ረ ባ ቸ ው ም ፡ አትጠቅማቸውም፡

፯፣ ዳዕሙ ርእሰ አራም ደማስቆ፣

ደ ማ ስ ቆ የሶርያ መዲና ትሆናለች እንጂ የአሥሩ ነገድ መዲና አትሆንም፡

ወርእሰ ደማስቆ ረዓሶን፣

ረዓሶንም የሶርያ ንጉሥ ይሆናል እንጂ የአሥሩ ነገድ ንጉሥ አይሆንም፡

www.ethiopianorthodox.org

፰፡ ወዓዲ እስከ አሥርቱ ወኃምስቱ ዓመት ትጠፍእ መንግሥተ ኤፍሬም እምሕዝብ፡

ዳግመኛውም እስከ አሥራ አምስት ዘመን ድረስ የአሥሩ ነገድ መንግሥት ከሁለቱ ነገድ መንግሥት ተለይታ ትጠፋለች ፣ የሁለቱ ነገድ ያለ እንደሆነ ጨርሳ ትጠፋለች ፡ የአሥሩ ነገድ መንግሥት ያለ እንደሆነ ጥቂት ጥቂት እያለች ቆይታ ትጠፋለች፡ በሁለቱ ነገድ የቈጠሩ እንደሆነ የአካዝ ዘጠኝ የሕዝቅያስ ስድስት አሥራ አምስት ያለው ይህ ነው፡

በአሥሩ ነገድ የቈጠሩ እንደሆነ ፋቁሔና ሆሴዕ ወልደ ኤላ ሲዋገ አሥራ ሁለት ዘመን ጠፍ አለ፡ ከፋቁሔ ሦስት አምጥቶ አሥራ አምስት ያለው ይህ ነው፡

አንድም ወዓዲ እስከ ስላ ወኃምስቱ ዓመት ትጠፍእ መንግሥተ ኤፍሬም እመንግሥተ ያሆ ይላል፡ ያሆ ያለው ስልምናሶርን ነው፡ ስሙ ብዙ ነው፡ ኢያሪም አኔሚሴር አርና ያሆ ስልምናሶር ይለዋል፡ እንዲህ ስላለ ግን የፎሀን የቴልጌልን ጨምሮ ቈጥሮ ነው፡ አንድም እመንግሥተ ያዉ ይላል፡ ያዉ ያለው ኢዩ ነው፡ እንዲህ ስላለ ግን የልጅ ልጆቹን ጨምሮ ቈጥሮ ነው፡ በሁለቱ ነገድ የቈጠሩ እንደሆነ የያዝያን ዘመነ መንግሥቱ አምሳ ሁለት ነው፡ ከዚያ ሃያ ስድስቱን ያመጣል፡ የኢዮአታም አሥራ ሰባት፡ የአካዝ አሥራ ስድስት፡ የሕዝቅያስ ስድስት ፡ ስላ አምስት ያለው ይህ ነው፡

በአሥሩ ነገድ የቈጠሩ እንደሆነ ፋቁሔና ሆሴዕ ወልደ ኤላ ሲዋገ አሥራ ሁለት ጠፍ አለ፡ ዘካርያና ሴሎ ሲዋገ አሥራ ሁለት ጠፍ አለ፡ የፋቁሔ ሃያ የምናሄ አሥር የፋቁስያስ ሁለት የሆሴዕ ወልደ ኤላ ዘጠኝ ስላ አምስት ያለው ይህ ነው፡

፱፡ ወርእሰ ኤፍሬም ሳምሮን፡

ሰማርያ የአሥሩ ነገድ መዲና ትሆናለች እንጂ የሁለቱ ነገድ መዲና አትሆንም፡

ወርእሰ ሳምሮን ፋቁሔ ወልደ ሮሜልዩ፡

ፋቁሔም የአሥሩ ነገድ ንጉሥ ቢሆን እንጂ የሁለቱ ነገድ ንጉሥ አይሆንም፡

አንድም ዳዕሙ ርእሰ አራም ደማስቆ ወርእሰ ደማስቆ ረዓሶን ወርእሰ ኤፍሬም ሳምሮን

ወርእሰ ሳምሮን ፋቁሔ ወልደ ሮሜልዩ፡

ወዓዲ እስከ ስልሳ ወኃምስቱ ዓመት ትጠፍእ መንግሥተ ኤፍሬም እምሕዝብ ብሎም ተራውን ይጽፋል፡

ወእመሰ ኢአመንክሙኒ፡

ካላመናችሁኝ፡

ወኢለበውክሙኒ፡

ነገሬን ልብ ካላደረጋችሁስ፡

ውቁ ከመ ትጠፍኡ ያለበት ነው እንድትማረኩ ዕወቁ፡

፲፡ ወዳግመ ነበቦ እግዚአብሔር ለኢሳይያስ፡

ሑር ፃእ ተቀበሎ ብሎት ነበርና ዳግመኛ እግዚአብሔር ኢሳይያስን ተናገረው፡

ወይቤሎ ሑር በሎ ለአካዝ፡

ሂደህ አካዝን እንዲህ በለው፡

፲፩፡ ሰአል ለከ ትእምርተ እምኀበ እግዚአብሔር አምላክከ፡

ከፈጣሪህ ከእግዚአብሔር ምልክት አድርግልኝ ብለህ ለምነው አለው፡

እስመ አይሁድ የጎሥሡ ትዕምርተ ወዕርዕ ይሴአሉ ጥበበ እንዲል፡

፩ ቆሮ ፩÷፳፪ ፡ ምልክት ይሻሉና፡

እመ አኮ ውስተ ቀላይ ፣

እንደ ሙሴ ባሕር ከፍለህ ደመና ጋርደህ፡ ምልክት አድርግልኝ ባትለው እንደ ኢያሱ በረድ አዝንመህ፡ ፀሐይ አቁመህ፡ ምልክት አድርግልኝ ብለህ ለምነው፡

ወእመ አኮ ውስተ አርያም፣

እንደ ኢያሱ በረድ አዝንመህ ፀሐይ አቁመህ ምልክት አድርግልኝ ባትለው እንደ ሙሴ ባሕር ከፍለህ ደመና ጋርደህ ምልክት አድርግልኝ ብለህ ለምነው፡

፲፪፡ ወይቤ አካዝ ኢይስእል ወኢያመክሮ ለእግዚአብሔር አምላኪየ፣

አካዝ እኔስ አልለምንም፡ ፈጣሪዬ እግዚአብሔርንም አልፈታተነውም ጣዖታዊነኝ አለ፡ ኃጢአት እየሠሩ ጣዖት እያመለኩ ታምራት ይደረግልኝ ማለት እግዚአብሔርን መፈታተን ነውና፡

፲፫፡ ወይቤ ስምዑ ቤተ ዳዊት፣

የአካዝ ወገኖች ስሙ፡

ቀሊልኑ ቦኑቤከሙ አስተዋብሶተ ሰብእ፣

ነቢየ እግዚአብሔርን ማዳከም በእናንተ ዘንድ ቀሊልን ነው?

www.ethiopianorthodox.org

ወለእግዚአብሔርኒ ታስተፃብስዎ፣
እግዚአብሔርንም እንጂ መናቅ ማቃለል ነው፤

ወአኮ ሰብእ፣
ነቢየ እግዚአብሔርን ያይደለ፤

አንድም ወይቤ አካዝ ብለህ መልስ አካዝ ፈጣሪዬ እግዚአብሔርን፤ አልፈታተነውም፤ እንዲያው ያደርግልኛል አለ፤ የአካዝ ወገኖች ስሙ ነቢየ እግዚአብሔርን ማደከም በእና ንተ ዘንድ ቀሊልን ነበር ::

ወአኮ ሰብእ ዕሩቅ ብእሲን ያይደለ፤

፲፬፣ ናሁ ኬኒ በእንተ ዝንቱ ይሁበክሙ እግዚአብሔር ትዕምርተ፣

እነሆ ከሥጋ መቅሠፍት የምት ድኑበትን ምልክት ስላላመ ናችሁ እግዚአብሔር ከነፍስ መቅሠፍት የ ም ት ድ ኑ በ ት ን ምልክት ይሰጣችኋል፤ የያዘው የሥጋ መቅሠፍት ነበረ፤ ወደ ነፍስ መቅሠፍት ሄደሳ ቢሉ የዳ.ያብሎስ ድል መ ነ ሣ ት ለረዓሶን ድል መነሣት አምሳል ነውና ከ ነ ፍ ሱ መቅሠፍት ያዳነን ከሥጋው መቅሠፍት አያድነንምን ብለው እንዲ.ያ ምኑ፤

አንድም ከሥጋ መቅሠፍት የምትድኑበትን ምልክት ስላ መናችሁ ከ ነ ፍ ስ መቅሠፍት የምትድኑበትን ምልክት ይሰጣ ችኋል የረዓሶን ድል መነሣት ለዲያብሎስ ድል መነሣት አምሳል ነ ው ና ከሥጋው መቅሠፍት ያ ዳ ነ ን ከነፍሱ መቅሠፍት አያድነንምን ብለው እንዲያምኑበት፤

አንድም ከሥጋ መቅሠፍት የምትድኑበትን ምልክት ስላ መናችሁ፤ ከነፍስ መቅሠፍት የምትድኑበትን ምልክት ይሰ ጣችኋል፤ ምልክቱን ያምጣው፤

ናሁ ድንግል ትፀንስ ወትወልድ ወልደ፣

እነሆ ድንግል በድንግልና ትፀ ንሳለች፤ ትወልዳለች ምልክት ያለው ይህ ነው፤

ወትሰምዮ ስሞ አማኑኤል፤

ስሙንም አማኑኤል ትለዋ ለች፤ አማኑኤል ማለት አምላክ ወሰብእ እግዚእ ወገብር ማለት ነውና፤

መዓረ ወቅብዐ ብዑል፤

በማር በቅቤ የከበረ ነው፤ ጌታ ልስጥ ቢል አያጣምና፤ አንድም ይበልዕ ይላል፤ ማር ቅቤን ይመገባል፤ ጌታ ግዕዘ ሕፃናትን አላፋለሰም፤ ማር ቅቤ እየተመገበ አድጓልና፤

አንድም መዓር አሪትን፤ ቅብዕ ወንጌልን ያስተምራል፤ መዓር አላት አሪትን መዓር ለጊዜው ሲያዩት የሚለቅ አይመስልም፤ ኋላ ግን ሲያጥቡት ይለቃል፤ አ ሪ ት ም ለጊዜው ስትሠራ የማታልፍ ሕግ መስላ ነበር፤ ኋላ ግን አልፋለችና ቅብዕ አላት ወንጌልን፤ ቅቤ ለጊዜው ሲያዩት የሚለቅ ይመስላል፤ ኋላ ግን ቢያጥቡት አይለቅም ወንጌልም ለጊዜው ስትሠራ የምታልፍ መስላ ነበር፤ ኋላ ግን ፀንታ እስከ ምጽአት ድረስ ስትነገር ትኖራለችና፤

፲፭፣ አእሚሮ ሕፃን ያፈቅር ሠናየ ወይሜንን እኩየ፣

ሕፃን ወልደ እግዚአብሔር ክፉውን ከበጎው ለይቶ፣ በጎውን ይወዳል፤ ክፉውን ይጠላል፤ አንድም በባሕርይ ዕውቀቱ አውቆ አምላክ ወልደ አምላክ ያለውን ይወዳል፤ ዕሩቅ ብእሲ ወልደ ዮሴፍ ባለው ይፈር ድበታል፤

፲፮፣ ወትተርፍ ምድር እንተ ትፈርሆሙ ለ፪ቱ ነገሥት፡

ተዐርፍ ሲል ነው፤ ሁለቱን ነገሥታት ፋቁሔንና ረዓሶንን የምትፈራቸው ኢየሩሳሌም እነዚህ ጠፍተውላት፤ ታርፋ ለች፤

፲፯፣ ወያመጽእ እግዚአብሔር ላዕሌከ ወላዕለ ቤተ አቡከ መዋዕለ እለ ዓዲ ኢበጽሐ እምአመ አእተቶ ኤፍሬም ለንጉሠ ፋርስ እምይሁዳ፤

ለከ ወለቤተ አቡከ ሲል ነው፤ እምአመ አእተቶ ለኤፍሬም ንጉሠ ፋርስ እምይሁዳ ሲል ነው፤ ንጉሠ ፋርስ ስልምናሶር አሥሩን ነገድ ከሁለቱ ነገድ ለይቶ ከአራቀው ጀምሮ ገና ያልደረሰ ዘመነ ሕዝቅያስን ያመጣልኻል የልጁን ለእሱ ሰጥቶ ተናገረ፤

አንድም ከ አ ራ ቀ ው ጀምሮ ያመጽእ ለከ ያመጣልኻል፤

አንድም እንዳለበት ይሆናል አሥሩ ነገድ ለግዳጅ ለምርኮ በቅቶ የፋርስ ንጉሥ ስልም ናሶርን ከሁለቱ ነገድ ለይቶ ከአራቀው ጀምሮ ገና ያልደረሰ ዘመነ ሕዝቅያስን ያመጣልኻል ስ ል ም ና ሶ ር አሥሩን ነገድ ማርኮ ለኢህ ቦታ ሳልሰጣቸው ሁለቱን ነገድ ምን ያስፈልገኛል ብሎ ትቷቸው ሂዷልና፤

አንድም ከ አ ራ ቀ ው ጀምሮ ያመጽእ ለከ፤

አንድም ስልምናሶር አሥሩን ነገድ ከአራቃቸው በኋላ አመጣ ልኻለሁ፤ ይለዋል ሕዝቅያስን፤

www.ethiopianorthodox.org

አንድም ዓዲ ያመጽእ ለከ ብለሀ ግጠም፤ ከዚህ አስቀድሞ ተድላ ደስታ እንዳመጣልህ፣ ዘመነ ተድላን ያመጣልሃል ይለዋል አካዝን፤

፲፰፣ ውእተ አሚረ ይስሕቦሙ እግዚአብሔር ለጸናጺት እለ ይኬንኑ መንፈቀ ፈለገ ግብፅ፣

ያንጊዜ የዓባይን እኩሌታ የሚገዙ እነናቡከደነፆርን እነስ ልምናሶርን ስቦ ጐትቶ ያመጣቸዋል፤ ዓባይን እኩሌታውን የበጌምድር ሰው፣ እኩሌታውን የጐጃም ሰው እንዲገዛው፤ አንድም ፈለገ ፀብጽ ይላል፣ ኒል ቀለም ይገኝበታልና፤

አንድም ኒል ቀ ለ ም ይመስ ላልና፤

ወለንህብኒ ዘ ሀ ሎ ደወለ ብሔረ ፋርስ፣

በፋርስ አውራጃ ያለ ሰናክሬምን ስቦ ጐትቶ ያመጣዋል፤

፲፱፣ ወይመጽኡ ወየኀድሩ ውስተ ቈላት፣

መጥተውም በቈላው ሁሉ ይሰፍራሉ፤

ወበሐውርት፣

በየሀገሩ ይሰፍራሉ፤

ወውስተ ግበበ ምድር፣

በጕድጓዱ፣

ወውስተ ንቅዓታተ ኵኵሕ፣

በተከፈለው ዋሻ፤

ወውስተ ኵሉ ዕፀው፣

ንህብ ብሎት ነበርና በዛፉ ላይ በዚህ ሁሉ ይሰፍራሉ፤ ብዛታቸውን መናገር ነው፤

፳፣ ወውእተ አሚረ ይ ላ ፅ ዮ እግዚአብሔር በመላዊ ስክርት እንተ ማዕዶተ ፈለግ ለንዑ ፋርስ፣

ያንጊዜ ሰብአ ትካትን ሰብአ ሰዶምን በማጥፋት በሰከረች መዓት መቅሠፍት በዮርዳኖስ ማዶ የሰፈረ ሰናክሬምን ያጠ ፋዋል፤ አንድም ዘመጽአ ዐዲዎ ዮርዳኖስን ተሻግሮ የመጣ፤

አንድም ዘ መ ጽ አ ተዐዲዎ ተደፋፍሮ የመጣ ሰናክሬምን ያጠፋዋል፤

አንድም ወ ው እ ተ አሚረ ይላፅዮ እግዚአብሔር በመላዊ ስክርት ለንዑ ፋርስ እንተ ማዕዶተ ፈለግ ሲል ነው፤ ከወንዝ ማዶ የመጣ ሰናክሬምን ሰብአ ት ካ ት ን ፤ ሰብአ ሰዶምን በማጥፋት በተፈተነች ሥልጣኑ ያጠፋዋል፤

ርእሶሂ፣

ራሱን፤

ወፀጕሮሂ፣

ሠራዊቱን ፤

ወይገምዖ ጽሕሞሂ፣

ባለሟሉን ያጠፋል፤

፳፩፣ ወውእተ አሚረ ያመገዝዕ ሰብእ ዕጕለተ እምውስተ አልህ ምቲሁ፣

ያንጊዜ ሰናክሬም በጠፋ ጊዜ በሕዝቅያስ ዘመን ሰው ሁሉ ከላሙ እየለየ ጊደሩን ያሰባል ለመሥዋዕት ነው፤

ወዘአሐቲ ሀሊበ በግዕት ያፀግብ ለፀቱ ሰብእ፣

ወሀሊበ በግዕት አሐቲ ወሀሊብ ዘበግዕ አሐቲ ሲል ነው፤ ያንዲት በግ ወተት ለሁለት ሰው ያጠግባል፤ የዘመኑን መልካምነት የህገሩን መቅናት መናገር ነው፤

፳፪፣ ወይሴሰዩ መሓረ ወቅብዐ እለ ተርፉ ውስተ ምድር፣

አሥሩ ነገድ ተማርከው የቀሩ ሁለቱ ነ ገ ድ ማር ቅቤን ይመገባሉ፤

፳፫፣ ወይሠምር ወይንሂ ውእተ አሚረ ውስተ ኵሉ በሐውርት፣

ያንጊዜ ወይኑ በየሀገሩ የበጀ ይሆናል ፤ ወይከውን ሜጡ ለ፲፪ ዳሰ ወይን ፲ተ፪ተ ብሩረ፤

የሺሁ ዳስ ወይን ዋጋ ሽህ ወቄት ይሆናል፤ የዘመኑን መልካም ነት የወይኑን መበጀት መናገር ነው፤

አንድም ወ ው እ ተ አሚረ ያመገዝዕ ሰብእ ብለሀ መልስ ያንጊዜ በ ዘ መ ነ ሐዲስ ዲያብሎስ ድል በተነሣ ጊዜ ጌታ ከምእመናን እየለየ ጳጳስ ሊቀ ጳጳስ ይሾማል፤ ወዘአሐቲ ሀሊበ በ ግ ዕ ት የአንዲት የወንጌል ሥርዓት ለሕዝቡም ለአሕዛቡም ይበቃል፤ ወይሴሰዩ መዓረ ወቅብዐ እለ ተርፉ ውስተ ምድር ከ እ ን ቢ ታ ከክህደት የቀሩ ም እ መ ና ን አሪትን ወንጌልን ይማራሉ፤ ወይሠምር ወይንሂ በሕገ ወንጌል፤

አንድም በ ሥ ጋ ው በደሙ የሚገኝ ክብር ፍጹም ይሆናል፤ ወይከውን ሜጡ ለ፲፪ት ዳሰ ወይን በአሥርቱ ቃላት የሚገኝ ክብር ፍጹም ይሆናል፤ አንዱን መቶ አንዱን መቶ ብሎ ቈጥሮ አሥርቱ ቃላትን ሺህ በማለት ተናገራቸው፤ ሁ ሉ ም በየራ ሳቸው ፍጹም ክብር ፍጹም ዋጋ ያሰጣሉና፤

፳፬፣ ወእምዝ ካዕበ ትማስን ኵላ ምድር፣

ከዚህ በኋላ ኢ የ ሩ ሳ ሌ ም ዳግመኛ ትጠፋለች ለአሥሩ

www.ethiopianorthodox.org

ነገድ ሁለቱን ነገድ ለሁለቱ ነገድ መቃብያንን ካዕበ አለ፤

ወትመልዕ ሦክ ወምጕሕያ፣

እሾሁን ሙጃውን ትመላለች፤

ወይመጽእ እንከ ፍርሀት፣

ሽብር ይሆናል፤

፳፭፣ ወይበውእዋ ምስለ ሐፅ ወቀስት፣

ፍላፃ ጦር ይዘው ይገቡባታል፤

አንድም ወኢይበውእዋ ዘእንበለ ሐፅ ወቀስት ይላል፣

ፍላፃ ጦር ሳይዙ አይገቡባትም የምታስፈራ ሁና፤

እስመ ማሰነት ወመልዐት ሦክ ወምጕሕያ፣

ጠፍታለችና እሾህንና ሙጃንም መልታለችና፤

ወይከውን ምራዕየ አባግዕ ወላህም፣

የላም የበግ መሰማሪያ ይሆናል፤

አንድም ኀበ የሐርስዎ በላህም ይላል፣ በላም ይታረስ የነበረው ሁሉ ተፈቶ የመንጋ መሰማሪያ ይሆናል፤

ወለዘይትሐረስ በላህም ይከይዶ በግዕ ይላል፤

ወያማስኖ ሦክ ወምጕሕያ፣

እሾህ ሙጃ ያጠፋዋል፤

ምዕራፍ ፰

፩፣ ወይቤለኒ እግዚአብሔር ንሣእ ለከ ጦማረ ክርታስ ዐቢየ ብሉየ ወሐዲሰ፣

ክርታሰ ጦማር ሲል ነው፤ ጦማር የተጻፈበት ክርታስ ያልተጻፈበት ነው፤ ብሉየ ዔዋዌ የተጻፈበትን ሐዲሰ ሚጠት የተጻፈበትን ወረቀት ተቀበል አለኝ፤

አንድም ጦማረ ክርታስ ዐቢየ ታላቅ ወረቀት ተቀበል አለኝ፤

ወጸሐፍ ውስቴቱ መጽሐፈ በብርዐ ዕጓለ እመሕያው፣

በውስጡ ሰው ሰው አሳክለህ ማለት አጕልተህ ጻፍበት አለኝ፤ (ጥቅስ) ከመ ያፍጥን ዘያነብቦ እንዲል፤ ዕንባ ፪፣፪፤ አንድም በዕብራይስጥ ቋንቋ፤ አንድም በሰው አምሳል እነናቡከደነፆር እንደማረኩ እስራኤል እንደተማረኩ አድርገህ ጻፍበት፤

ዘይብል ፍጡነ ዔውው ወርውፀ ማህርክ፣

ፈጥነህ ማርክ፣ ሩጠህ ማርክ የሚል ጻፍበት አለኝ፤

፪፣ ወአስምዕ ሰብአ መሀይምናነ፣

አልነገርኸንም እንዳይሉ ደጋግ ሰዎችን አዳኝባቸው፤

አርያሃ ካህነ ወዘካርያስሃ ወልደ በራክዩ፣

አርያን የብራክዩን ልጅ ዘካርያስን አዳኝባቸው፤

አንድም እኒህም አርአያ ዘካርያስ ናቸው፤

እስመ መንፈሰ እግዚአብሔር ቦሙ፤

በሊህ መንፈስ ቅዱስ አድሮባቸዋልና፤

አንድም ቦሙ በእነዚህ አድሮ በእስራኤል ተናግሮባቸዋልና፤

ጉባዔ

፫፣ ወሖርኩ ኀበ ብእሲት ነቢይት፣

መጻእያትን ወደምታውቅ ወደ ኢየሩሳሌም ሄድሁ፤ ነቢዪት አላት፤ የሚጠቅማት ሕዝቅያስን አውቃ ስለ አነገሠች፣

ወፀንሰት፣

የሕዝቅያስ መንግሥት መታሰቡን መናገር ነው፤

ወወለደት፣

መንገሡን መናገር ነው፤

አንድም ወሖርኩ ኀበ ብእሲት ነቢዪት ብለህ መልስ፤ መጻእያትን ወደምታውቅ ወደ ባቢሎን ሄድሁ፤ ነቢዪት አላት፤ የሚጠቅማት ናቡከደ ነፆርን አውቃ ስለ አነገሠች፤

ወፀንሠት፣ የናቡከደነፆር መንግሥት መታሰቡን መናገር ነው፤

ወወለደት ናቡከነደፆር መንገሡን መናገር ነው፤

አንድም ወሖርኩ፣ ወደ እመቤታችን ሄድኩ ነቢዪት አላት፤ ናሁ እምይዜሰ ያስተበፅዑኒ ኵሉ ትውልድ ብላ ተናግራለችና፣ ወፀንሠት፣ ጌታን፤ ፀነሠች፣ ወወለደት፣ ወለደች፤

ወይቤለኒ እግዚአብሔር ስምዮ ስሞ ፍጡነ ማህርክ ወርውፀ ዔውው፣

ስሙን ፈጥነህ ማርክ ሩጠህ ማርክ በለው አለኝ፤

አንድም ፍጡነ ዔዋ፣ ወርውፀ፣ ምኅርካ ይላል፣ ስሙን በግብሩ ጠርቶ ጸሐፊ ጽፎ፤ ሠዓሊ ሥሎ ሲያበቃ ዘሚካኤል ዘገብርኤል ብሎ እንዲጽ ፍበት፤

፬፣ ዘእንበለ ያእምር ሕፃን ሰምየ አቡሁ ወእሙ፣

ሕፃን ሕዝቅያስ አባቴ መምለኬ ጣዖት ነው፤ እናቴ መምለኪተ ጣዖት ናት ሳይል ማለት ከነዚያ ግብር ሳይነሣ፤

አንድም አባቴ መምለኬ እግዚአብሔር ነው፣ እናቴ መምለ

www.ethiopianorthodox.org

ኪተ እግዚአብሔር ናት አይል የሁለት ጣዖታዊ ልጅ ነግሦ፤

ይነሥእ ኀይለ ደማስቆ፥

ብዕለ ደማስቆ ሲል ነው፤ የደማስቆን ብዕል እጅ ያደርጋል፤

ወምህርካ ሰማርያ፣

ይትካፈል ያለበት ነው የሰማርያን ምርኮ ይካፈላል፤

በቅድመ ንጉሥ ፋርስ፣

ዘሀሎ ያለበት ነው፤ በፋርስ ንጉሥ በሰናክሬም ፊት ያለውን ይካፈላል፤ ሕዝቅያስ ሰናክሬም በጠፋ ጊዜ ገንዘቡን እየዘረፈ አግብቷልና ብለዕ ደማስቆ ምኅርካ ሰማርያ ማለቱ ግን ሰናክሬም ሲመጣ ይህን ሁሉ እየወጋ መጥቷልና፤

አንድም ዘእንበለ ያእምር ሕፃን ሰምየ አቡሁ ወእሙ ሕፃን ናቡከደነፆር አባቴ ንጉሥ ነው፤ እናቴ ንግሥት ናት አይል የሁለት ባለጌ ልጅ ነግሦ ፤ ይነሥእ ኀይለ ደማስቆ፣ ብዕለ ደማስቆ ሲል ነው፤ የደማስቆን ብዕል እጅ ያደርጋል፤ ወምኅርካ ሰማርያ ይትካፈል ያለበት ነው፤ የሰማርያን ምርኮ ይካፈላል፤ በቅድመ ንጉሥ ፋርስ ዘሀሎ ያለበት ነው፤ በፋርስ ንጉሥ ፊት ያለውን ይካፈላል፤

(ታሪክ) ይህስ እንደምነው ቢሉ ንጉሡ ምናሴ ይባላል፤ በእሱ ዘመን አንድ ዕብራዊ ነበር፤ ከንጉሡ ጋራ ተጣላ ሂዳችሁ እጁን በእክት ፣ ከብቱን በእግት፤ ይዛችሁ አምጡት ብሎ አስፈለ ገው፤ ሰው ከሆነ ወዳጅ የሌለው የለምና እጅህ በእክት ከብትህ በእግት ሊያዝ ነው ብለው ነገሩት ሸሽቶ ወደ ባቢሎን ወረደ፤ ከዚያ ባሏ ከሌለበት ከአንድ ነጋዴ ሚስት ደረሰ፤ ናቡከደነፆር ተፀነሰ፤ ተወለደ፤ በዚያው ወራት የንጉሡ ልጅ ወፍ ወለደች የንጉሡ ልጅ ወፍ ወለደች እባል የለም? ብላ ገረዷን ከባሕር ጣዪው ብላ አስይዛ ሰደደቻት፤ ያችም የናቡከደነፆር እናት ባሌ ከሌለበት ወልጄ ብገኝ ሲመለስ ይገድለኝ የለም ብላ ገረዷን ከባሕር ጣዪው ብላ አስይዛ ሰደደቻት ፣ ሁለቱም በጎዳና ተገናኙ ወዴት ትሂጃለሽ አለቻት እመቤቴ ወፍ ወልደው ይህንን ከባሕር ጣዪው ብለውኝ ልጥል እሄዳለሁ አለቻት፤ አንቺስ አለቻት፤ እመቤቴ ባላቸው ከሌለበት ልጅ ወልደው ይህን ከባሕር ጣዪው ብለውኝ ልጥል እሄዳለሁ

አለቻት፤ እንግዲያስ ወፉን ጥለን ልጁን ይዘን እንሂድ አለቻት፣ እሺ ብላ ወፉን ጥለው ልጁን ይዘው ተመልሰዋል፤ ሂዳ ለንጉሡ ልጅ ሰጠቻት፤ ተውላጠ ያፍ፤ የያፍ ልዋጭ የሚያሰኘው ይህ ነው፤ የንጉሥ ልጅ እየተባለ አደገ፤ ንጉሡ ዘመቻ በሄደበት ሞተ እሱ ተተክቶ ነግሧል ኀይለ ደማስቆ ምኅርካ ሰማርያ ማለቱ ግን ናቡከደነፆር ያልወጋው አገር የለምና፤

አንድም ወሐርኩ ብለህ መልስ መጻእያትን ወደምታውቅ ወደ እመቤታችን በትንቢት ሂድሁ ነቢዩት አላት፤

ናሁ እምይእዜሰ ያስተበፅዑኒ ኵሉ ትውልድ ብላ ተናግራ ለችና፤ ሉቃ. ፩÷፵፰፤ ወፀንሠት ወወለደት ወልደ ከሦስቱ አካል አንዱን አካል ወልድን ፀንሳ ወለደች ፤ ወይቤለኒ እግዚአ ብሔር ስምዮ ስሞ ፍጡነ ማኅርክ ወርውፀ ዒውው ማኅርክ አሕዛብን ዒውው ሕዝቡን በትምህርት ማርክ ብለህ ስም አውጣለት በለው አለኝ፤ እስመ ዘእንበለ ያእምር ሕፃን ሰምየ አቡሁ ወእሙ ሕፃን ወልደ እግዚአብሔር አበ እመ ማለትን ሳያውቅ ይነሥዕ ኀይለ ደማስቆ የደማስቆን ብዕል እጅ ያደርጋል፤ ወምኅርካ ሰማርያ በቅድመ ንጉሡ ፋርስ ዘሀሎ ያለበት ነው፤ በፋርስ ንጉሥ ፊት ያለ የሰማርያን ምርኮ ይቀበላልና ሕዝቡን አሕዛቡን በትምህርት ማርክ ብለህ ስም አውጣለት አለኝ፤ ብዕለ ደማስቆ ምኅርካ ሰማርያ ያለው እንደ ምን ነው ቢሉ አዳም ሔዋንን ባስደነገጣት ጊዜ ሥላሴ ማጫ ችነን አምጣ አሉት፤ እናንተ የማታውቁት ምን ገንዘብ አለኝ አላቸው፤ መላእክትን ሦስት መቶ ወቄት ወርቅ፣ ዕጣኑን፣ ከርቤውን ወስዳችሁ ስጡት፤ አሏቸው፤ ወስደው ሰጡት አዳምም ማጫችሁን ተቀበሉኝ አላቸው፤ ከአንተ ዘንድ ይቆይልን አሉት፤ ኋላ እሱ ሲሞት ለሴት ሰጠው፤ ሴት ሲሞት ለሄኖስ ሰጠው፤ ከሄኖስ ሲወርድ ሲዋረድ ከኖኅ ደረሰ፤ ኖኅም ማየ አይኅ በደረሰ ጊዜ ወደ መርከብ ይዞት ገብቷል፤ ኖኅ በመርከብ ዓመት ተቀምጠ ሲወጣ ይዞት ወጥቷል፤ ኋላም ሲሞት ለልጁ ለሴም ሰጥቶታል፤ መልአኩ ከነገደ ካም የተወለደ መልከ ጼዴቅ የሚባል አለ፤ ከእናት ከአባቱ አሰናብተህ ድውይ የምንፈውስበት ቄጽለ

www.ethiopianorthodox.org

በለስ እናምጣ ብለህ ይዘኸው ሂድ አለው፡

ሂዶ እናት አባቱን ስጡኝ አላቸው፡ ለምንህ ነው ቢሉት ለድውያን የምንቀባው ፍሬ በለስን ልናመጣ ነው አላቸው፡ (ቄጽለ በለስን ም ብትል ይሆናል)፡ መልአከ ገጽ እየመራቸው ሂደው ቀራንዮ ሲደርሱ ዐፅመ አዳምን መሬት ተከፍቶ ዋጠው፡ ወርቁን ከዚያ ቀብሮ ሥርዓት ይሠራበታል፡ ኩን ጸዋሚ ተኃራሚ፣ ዝጉሃዊ ባሕታዊ ሁን፡ በወይን በስንዴ አስታኵት፡ ራስህን አትላጭ፣ ጥፍርህን አትቁረጥ ብሎታል፣ አብርሃም ለአምስቱ ነገሥተ ሰዶም ረድቶ አራቱን ነገሥተ ኮሎዶጎሞር ድል ነሥቶ ሲመለስ ኃይል ቢሰማው በዘመኑም የተደረገ ተአምራት ትገ ቢለው በመዋዕል የኑ ትፈኑ ወልደከ ወሚመ፣ ታርእየኒ ኪያሃ ዕለተ አለ አኮ ኪያሃ ዘአርእየከ አላአ ምሳሊሃ ዕድዎ ለዮርዳኖስ ወትረክቦ ለመልከ ጼዴቅ አለው ዮርዳኖስን ተሻግሮ ሂደ፡ መልከ ጼዴቅም ኅብስተ አኰቴት፣ ጽዋዐ በረከት ይዞ ተቀብሎታል፡ ምሳሌ ነው፡ አብርሃም የጥሙቃን ዮርዳኖስ የጥምቀት፡ መልከጼዴቅ የቀሳውስት፣ ኅብስተ አኰቴት፣ ጽዋዐ በረከት የሥጋው፡ የደሙ ምሳሌ፣ ወርቁን መልከ ጼዴቅ ለአብርሃም ሰጥቶታል፡ አብርሃም ሲሞት ለይስሐቅ፣ ይስሐቅ ለያዕቆብ፣ ያዕቆብ ሲሞት ለይሁዳ ሰጥቶታል፣ ከዚያ ሲወርድ ሲዋረድ ከዳዊት ደረሰ፡ ዳዊት ሲሞት ለሰሎሞን ሰጠው፡ ሰሎሞን ም ቤተ መቅደስን ሲሠራ ልሥራበት አላለም፡ ጥበበ እግዚአብሔር ጠብቆታል፣ ኋላም ሲሞት ለሮብአም ሰጠው፡ በሮብ አም ጊዜ መንግሥት ተከፈለ፡ በአሥሩ ነገድ ኢዮርብአም በሁለቱ ነገድ ሮብአም ተናገሡ፡ የአሥሩ ነገድ መንግሥት ሲያያዝ ከዮአስ፡ የሁለቱ ነገድ መንግሥት ሲያያዝ ከአሜስያስ ደረሰ፡ በአሥሩ ነገድ ዮአስ፡ በሁለቱ ነገድ አሜስያስ ተናገሡ፣ አሜስያስ ኤዶም ያስን ወግቶ ሲመለስ ኃይል ቢሰማው፡ ነዓ ንትረአይ ገጸ በገጽ ብሎ ወደዮአስ ላከበት፡ አቃኒ ለአከ ነበ ዕፀወ ቄድሮስ እንዘ ይብል ሀቦ ወለተከ ለወልድየ ወመጽኡ አራዊተ ገዳም ወቀተልዎ ለአቃኒ፡ ፪ኛ ነገ ፲፬፡ ፳-፲፬ አንተ እንደ ቅርስባ፣ እንደ ኩሽሽላ፣ እንደ ችፍርግ፡ እኔ እንደ ዋንዛ

እንደ ዝግባ፣ አንተ እንደ አይጥ፣ እኔ እንደ ዘንዶ፣ እንደ ዝሆን አይደለሁምን፡ አይጥ ከዘንዶ ከዝሆን ይጋባልን አለው፡ ሂዶ ተዋጋ ድል አደረገው፡ በአን ቀጸ ኤፍሬም አራት መቶ ክንድ አስጐተተው፡ ከነገደ ኤፍሬም የተወለደ እንዲህ አደረገ ይበሉኝ ብሎ ዮአስም ወርቁን ከዚያ አግኝቶ ወስዶታል፡ ምኅርካ ስማርያ ያሰኘው ይህ ነው፡ የአሥሩ ነገድ መንግሥት ሲያያዝ ከፋቁሔ የሁለቱ ነገድ መንግሥት ሲያያዝ ከአካዝ ደረሰ፡ በአሥሩ ነገድ ፋቁሔ፡ በሁለቱ ነገድ አካዝ ተናገሡ፡ የአሥሩ ነገድ ንጉሥ ፋቁሔ ሁለቱን ነገድ መግዛት ቢያምረው ከረዓሶን ዘንድ ላከ፡ አንተ እሊህን ሁለቱን ነገድ አስገዛኝ፡ እኔ ላንተ ልገዛ ብሎ ወርቁን እጅ መንሻ አድርጎ ሰዶለታል፡ አካዝም ይህን ሰምቶ ኩቴልጌል ዘንድ ላከ ነዓ ርድአኒ እምእዴሁ ለንጉሥ ሶርያ ወእምእዴሁ ለንጉሥ ስማርያ ገብርከኒ ወወልድከኒ፡ ፪ ነገ ፲፮. ፭-፱፡ የግድ ባርያህ የውድ ልጅህ ነኝ ብሎ ላከበት፡ ወይቤሎ አሆ፡ እሺ በጀ ብሎ ዘመተ፣ ደማስቆ ሲደርስ የግን አገር ናት ብሎ ጠየቀ፡ የወዳጅህ የአካዝ፣ የጠላቱ የፋቁሔ፡ የወዳጁ የረዓሶን አገር ናት አሉት፡ መርዳት የት ይጀመራል ብሎ ደማስቆን ያጠፋ ጀመር፡ የሰው አገር እናጠፋለን ስትሉ አገራችሁ ጠፋ አሏቸው፡ ተመልሰው ሲዋጉ ረዓሶን ሞተ፡ ቴልጌል ወርቁን ከዚያ አግኝቶ ወስዶታል፡ ብዕለ ደማስቆ ያሰኘው ይህ ነው፡ ኋላ ጌታ በተወለደ ጊዜ ሰብአ ሰገል አምጥተው ገብረውለታል፡ በቅድመ ንጉሥ ፋርስ ያለው ደረሰ፡ እንዲህ እንዲህ የሚያደርግ አምላክ ነውና ስምዮ ስሞ ላለው፡ እስመ ዘእንበለ ያእምር ሕፃን ሰምየ አቡሁ ወእሙ ሕፃን ወልደ እግዚአብሔር አበ እመ ማለትን ሳያውቅ የደማስቆን፣ የሰማርያን ሰዎች ይቀበላልና፣ በነፍስ ይማርካልና ሕዝቡን አሕዛቡን በትምህርት ገንዘብ አድርግ ብለህ ስም አውጣለት አለኝ፡

አንድም ስምዮ ስሞ ፍጡነ ማኅርክ ሕዝቡን ወርውፀ ፄውው አሕዛብን ማርክ በለው አለኝ፡ ሕፃን ወልደ እግዚአብሔር አበ እመ ማለትን ሳያውቅ ነፍሳትን እጅ ያደርጋል፡ ዘሀለ በቅድመ ንጉሥ ፋርስ፡ በዲያብሎስ ፊት ያሉ

www.ethiopianorthodox.org

ትን ጥቅስ ወመልአከ ንጉሠ ፋርስ ይቀውም ቅድሜየ ፳ወ፩ ዕለተ እንዲል፤ ዳን. ፲÷፲፫ ፤

ጊጋር ሶርያዊን እንዳዳነው እመቤታችን በተሰደደች ጊዜ ከጊጋር ሶርያዊ ቤት አደረች፤ ሄሮድስ ለምን አሳደርህ ብሎ አስገደለው፤ ወዲያው ጌታ በነፍስ አድኖታል ፤ ብዕለ ደማስቆ፤ ምኅርካ ሰማርያ ማለቱ ግን ሄሮድስ እመቤታችን ያደረ ችበትን ሁሉ አጥፍቷልና፤

፭፣ ወይቤለኒ እግዚአብሔር ዓዲ ምቱረ ምክረ ተማከሩ እሉ ሕዝብ በማየ ሰሊሆም ዘየሐውር ጽሚተ፣

ቀስ ቀስ ብሎ በሚሄድ በመስኖ ውሀ አምሳል፣ ቀስ ቀስ ብለው ፋቁሔና ረዓሶን ዳግመኛ ያለቀ፤ የተቈረጠ ምክር ተማከሩ አለኝ እግዚአብሔር፤

አንድም ያ እንዳይጎዳ የማይጎዳ ምክር ተማከሩ አለኝ፤

፮፣ ወይትናገሩ በለኖሳስ ወይፈቅዱ ይርከብዎ ለረዓሶን ወልደ አራም ይንግሥ ሎሙ፣

የአራምን ልጅ ረዓሶንን በቆይታ በመንግሥት ሊያገኙት ወደው ቀስ ቀስ እያሉ ይማከራሉ፤

አንድም በቆይታ ሊገናኙት ይወዳሉ፣

፯፣ በእንተ ዝንቱ ያመጽእ እግዚ አብሔር ላዕሌሆሙ ማየ ፈለግ ኀያለ፣

ረዓሶንን እናንግሥ ስለአሉ እግዚአብሔር ቴልጌልን ያመ ጣባቸዋል፤

ወብዙኀ ንጉሠ ፋርስ፣

ዘውእቱ ንጉሠ ፋርስ ሲል ነው፣ ይኸውም የፋርስ ንጉሥ ቴልጌል ነው፤

ወየዐርግ ውስተ ቈላቲሆሙ፣

ወደ ቈላ ወርዶ ወደ ደጋ ይወጣል፤

አንድም እንዳለበት ይሆናል የቈላ ደጋ አለና፤

ወያንሶሱ ውስተ አረፋቲሆሙ፣

በቅጽሩ ይመላለሳል፤

፰፣ ኵሉ ዘይበጽሕ እስከ ክሣድ፣

ማየ ፈለግ ብሎት ነበርና ውሀው እስከ አንገት የሚደርስ ነው፤ ማለት ጦሩ አንገት ከደረት የሚለይ ነው፤

ወያጠፍእ እምይሁዳ ብእሴ ተባዐ፣

ጌታ አርበኛ ረዓሶንን፤ አርበኛ ሰናክሬምን ከይሁዳ ያጠፋል፤

አንድም ሰናክሬም ከይሁዳ አርበኛውን ያጠፋል ማለት የሚዋጋኝ የለም ይላል፤

አንድም ሕዝቅያስ አርበኛ ያጠ ፋል ማለት እንዋጋለን አትበሉ እግዚአብሔር ያድነናል በሉ ይላል፤

አንድም ሕዝቅያስ በጸሎቱ አርበኛ ሰናክሬምን ከይሁዳ ያጠፋዋል፤

አንድም ጌታ አርበኛ ዲያብ ሎስን ከምእመናን ያጠፋዋል፤

ወያኀልቆሙ ለኀያላን፣

ኀያላንን ያጠፋቸዋል፤

ወይመልዕ ተዓይኒሁ ውስተ ምድር ስፉሕ ወበሐውርት፣

ሰናክሬም ሠራዊቱን በኢየሩ ሳሌም በሀገሩ ሁሉ ይመላል፤

፱፣ እስመ እግዚአብሔር ምስሌነ፣

እግዚአብሔር በረድኤት ከእኛ ጋራ አለና ሰናክሬምን ያጠፋል፤

አእምሩ አሕዛብ ወተመውዑ፣

አሕዛብ ድል እንነሣለን በሉ፣ ድል እንድትነሡ እወቁ፤

ወስምዑ እስከ አጽናፈ ምድር፣

በአራቱ ማዕዘን ያላችሁ አሕዛብ ስሙ፤

ኀያላን ተመውዑ፣

ድል አንነሣም ትሉ እንደሆነ ከእናንተ አስቀድመው የነበሩ ኀያላንስ እንኳ ድል ተነሡ፤

አንድም በጽንፈ ምድር ያሉ አሕዛብ እለ ሰናክሬም ድል እንደተነሡ ዕወቁ፤

ወእመሂ ካዕበ ጸናዕክሙ ወካዕበ ትትመውዑ፣

ዳግመኛ ድል አንነሣም በማለት ብትጸኑ ዳግመኛ ድል ትነሣ ላችሁ::

፲፣ ወእመሂ መከርክሙ ምክረ ይመይጥ እግዚአብሔር ምክረክሙ፣

አገራቸውን ተኩሰን፣ ሰዎችን ማርከን፣ ገንዘባቸውን ዘርፈን እንሄዳለን ብላችሁ ብትመክሩ እግዚአብሔር ምክራችሁን ይለ ውጠዋል፤

ወነገርኒ ዘተናገርክሙ ኢይከው ነክሙ፣

ሰዎችን ማርከን ገንዘባቸውን ዘርፈን፤ አገራቸውን ተኩሰን እንሄዳለን ብላችሁ የተናገራ ችሁት ነገር አይረባችሁም፣ አይጠቅማችሁም፤

እስመ እግዚአብሔር ምስሌነ፣

እግዚአብሔር በረድኤት ከእኛ ጋራ አለና፤

አንድም እስመ እግዚአብሔር ምስሌነ ብለህ መልስ፤ እግዚ አብሔር ከእኛ ሥጋ ጋራ አንድ አካል፣ አንድ ባሕርይ ሁኗልና ዲያብሎስን ያጠፋል፤

www.ethiopianorthodox.org

አንድም እግዚአብሔር ከእኛ ሥጋ ጋራ ተዋሀዷልና፤ አእምሩ አሕዛብ ወተመውዑ መናፍቃን እንረታለን በሉ፤ እንድትረቱ ዕወቁ ፤ ወስምዑ ፤ በአራቱ ማዕዝን ያላችሁ መናፍቃን ስሙ፤ ኀያላን ተመውዑ አንረታም ትሉ እንደሆነ ከእናንተ አስቀድመው የነበሩ ኀያላን አእምሮ ነን የሚሉ እነአርዮስ እነንስጥሮስ እንኳ ተረቱ፤ ወእመሂ ካዕበ ጸናዕክሙ ዳግመኛ ሁለት አካል ሁለት ባሕርይ በማለት ብትጸኑ ዳግመኛ ትረታላችሁ፤

ወእመሂ መክርክሙ ምክረ፣

ሁለት አካል ሁለት ባሕርይ እንላለን ብላችሁ ብትመክሩ እግዚአብሔር ምክራችሁን ይለውጥባችኋል፤

ወነገርኒ ዘተናገርክሙ፣

ሁለት አካል ሁለት ባሕርይ ብላችሁ የተናገራችሁትም ቢኖር አይረባችሁም፤ አይጠቅማችሁም፤

እስመ እግዚአብሔር ምስሌነ፣

እግዚአብሔር ከእኛ ሥጋ ጋራ ተዋሀዷልና።

፲፩፣ ከመዝ ይቤ እግዚአብሔር ፀባኦት፣

አሸናፊ እግዚአብሔር እንዲህ አለ፤

እንዘ ይጌሥጸኒ በእዴሁ ጽንዕት፤

ጽንዕት በሆነች ሥልጣኑ ሲገሥጸኝ፤

ወይዛለፈኒ በቃለ አፉሁ፣

ከቃሉ በወጣ ነገር ሲዘልፈኝ፤

እንዘ ይብል ኢትሑር በፍኖተ እሉ ሕዝብ፣

በእስራኤል ሥራ ጸንተህ አትኑር ብሎ፤

፲፪፣ ወኢትበል ዕቡበ ኵሉ ዘይቤሉ እሉ ሕዝብ፣

እስራኤል የተናገሩትን ዕውብ ዕውብ አትበል፤

ኢትፍርሁ ትግርምቶሙ ወኢት ደንግፁ፣

የአሕዛብን መገረማቸውን አትፍሩ፤ አትደንግጡ፤

፲፫፣ ለእግዚአብሔር ቀድስዎ፤

እግዚአብሔርን አመኑት እንጂ፤

አንድም እግዚአብሔርን አመስግኑት፤

አንድም አክብሩት አጽኑት እንጂ፤

ወውእቱ ይከውነክሙ ለቅዳሴ፤

እሱም ለማክበር፤ ለማጽናት ለማንጻት ይኾናችኋል፤

፲፬፣ ወለዕብነ ዕቅፍት ከመ ዕብን፣

ለዕቅፍት ሲል ነው፤ ደንጊያ እንዲያሰነካክል አንድም ጣዖት

እንዲያሰነካክል አያሰነካክልህም፤

ወእመሂ ተወከልከ ይቄድሰከ፣ ብታምንበት ያከብርሃል፤

ወኢያአቅፈከ ከመ ዕብነ ዕቅፍት ወኢከመ ኲኵሕ ዘያድኅዕ፣

የዐለት ደንጊያ እንዲያሰነካክል አያሰነካክልህም፤

ወፀፍሰ ቤተ ያዕቆብ ውስተ መሥገርት ወዳኅፅ ይነብሩ በኢየሩሳሌም፣

የአሥሩን ነገድ ሲናገር መጥቶ ነበርና፤ ሁለቱ ነገድ ግን በኢየሩሳሌም በአምልኮ ጣዖት፣ በገቢረ ኃጢአት ጸንተው ይኖራሉ፤ አንድም በአባር በቸነፈር ተይዘው ይኖራሉ፤

፲፭፣ በእንተ ዝንቱ ይደክሙ ብዙኃን እምውስቴትክሙ፣

ስለዚህ ነገር ከእናንተ ወገን ብዙ ሰዎች ይደክማሉ፤

ወይወድቁ ወይትቀጠቀጡ፣

በመከራ ይወድቃሉ፤ ይቀጠቀጣሉ፤

ወይቀርቡ ወያሠግሩ ሰብአ፣

ነቢያተ ሐሰት ካህናተ ጣዖት ሰውን ለማሳት ይቀርባሉ፤

አንድም ቀርበው ሰውን ያስታሉ፤

፲፮፣ ወያጸንዑ፣

ሰውን አጽንተው ይጣላሉ፤ አንድም ሕገ ጣዖትን አጽንተው ይይዛሉ፤

እሙንቱ እለ የኀትምዋ ለአሪት ከመ ኢይትመሀርዋ፣

አሪትን እንዳይማሯት የሚያጥፏት እሊህ ሰውን አጽንተው ይጣላሉ፤ አንድም እንዳይማሯት አሪትን የሚያጥፏት እሊህ ናቸው፤

አንድም ወይቀርቡ ወያሠግሩ ሰብአ ቢጸ ሐሳውያን፤ ወንጌል እንበለ አሪት፣ ጥምቀት እንበለ ግዝረት አትረባም እያሉ ሰውን ለማሳት፣ ይቀርባሉ፤ አሪትን ከማሯት የሚያጥፏት ምነው? እሊህማ ምሁራን አሪት አይደሉምን ቢሉ አሪት ነቢያ ያነሥእ ለክሙ ዘከማየ እምአኀዊክሙ ወሎቱ ስምዕዎ ትላለች፤ ዘደ. ፲፰÷፲፰፤ እነሱ ግን ይህንን አላመኑላትምና፤

፲፯፣ ወትብል እጸንሖ ለእግዚአብሔር ዘሜጠ ገጸ እምቤተ ያዕቆብ፣

ሰባ ዘመን ከያዕቆብ ወገን ገጸረድኤቱን የመለሰ እግዚአ

www.ethiopianorthodox.org

ብሔርን ደጅ እ ጠ ና ዋ ለ ሁ ትላለህ፤

ወእትቄከል ቦቱ ነየ አነ ወደቂቅ ዘወሀበኒ እግዚአብሔር፣

እግዚአብሔር የሰጠኝ እስራኤልና እኔ እናምንበታለን፤

አንድም ወትብል እጸንሖ ብለህ መልስ፤ ከአሥሩ ነገድ ፊቱን የመለሰ የሱን ገጸ ረድኤቱን ደጅ እ ጠ ና ዋ ለ ሁ ትላለህ ይለዋል ሕዝቅያስን፤

ወእትቄከል ቦቱ ነየ፤ እኔ ሕዝቅያስ አምንበታለሁ፤ ወደ ቂቅ ዘወሀበኒ፣ እግዚአብሔር፤ በሀብት ስቦ በረድኤት አቅርቦ የሰጠኝ ሁለቱ ነገድም ያምኑበ ታል፤

አንድም ወትብል እጸንሖ ሰባ ዘመን ከ ት ሩ ፋ ን ፊቱን የመለሰ እግዚአብሔን ደጅ እጠናዋለሁ ትላለህ ይለዋል ዘሩባቤልን፤

ወእትቄከል ቦቱ ነየ እኔ ዘሩባቤል አምንበታለሁ፤

ወደቂቅ ዘ ወ ሀ በ ኒ እግዚአ ብሔር፤ በሀብት ስቦ፤ በረድኤት አቅርቦ የሰጠኝ ትሩፋንም ያምኑበታል ትላለህ፤ አንድም ወ ት ብ ል ብለህ መልስ አምስት ሺህ ከአምስት መቶ ዘመን ከ ም ዕ መ ና ን ፊቱን የመለሰ እግዚአብሔርን ደጅ እጠናዋለሁ ትላለህ ይለዋል አዳምን፤

ወእትቄከል ቦቱ ነየ አነ፣ እኔ አምንበታለሁ፤

ወደቂቅ ዘወሀበኒ በሀብት ስቦ በረድኤት አቅርቦ የሰጠኝ ም እ መ ና ን ም ያምኑበታል፤ አንድም አምስት ሺህ ከአምስት መቶ ዘመን፣ ከያዕቆብ ዘነፍስ ገጸ ረድኤቱን የመለሰ እግዚ አብሔርን ደጅ እጠናዋለሁ ትላለህ ይለዋል፤ ሐዋርያውን፤

ወእትቄከል ቦቱ ነየ አነ እኔ አምንበታለሁ፤ ወደቂቅ ዘወሀ በኒ፤ በሀብት ስቦ በረድኤት አቅርቦ የሰጠኝ ምእመናንም ያምኑበታል፤

፲፮፣ ወአሜሃ ይከውን ተአምር ወመንክር ለእስራኤል እምነበ እግዚአብሔር ወባያት ዘይነብር ውስተ ደብረ ጽዮን፣

በጽዮን ከሚኖር ከአሸናፊ ከእግ ዚአብሔር ታገዘ ለእስራኤል ያን ጊዜ ተአምራት ይደረግላ ቸዋል፤

አንድም ሰክሬም በደብረ ጽዮን ያለ የእግዚአብሔር ማደሪያ ቤተ መቅደስን አፈርሳለሁ ከማለቱ የተነሣ ያን ጊዜ ለእስ

ራኤል ተአምራት ይደረጋል፤ የ ሰ ና ክ ሬ ም ጥፋት ነው፤ አንድም እ ም ነ በ እግዚአብ ሔር ይላል፤ ብልጣሶር ቤተ መቅደስን ከማፍረሱ የተነሣ ከእግዚአብሔር ዘንድ ታገዘ ለእስራኤል ተአምራት ይደረ ጋል፤ የ ሰ ና ክ ሬ ም ጥፋት የብልጣሶር ሞት ነው፤ ብልጣ ሶር ቤተ መቅደስን አፍርሶ አይደ ለም፤ የአባቱን ለእሱ ሰጥቶ ተናገረ፤

፲፱፣ ወ እ መ ቦ ዘይቤሉክሙ ጎሥዎሙ ለእለ ይትናገሩ በታሕተ ምድር፣

ሙት አስነሥተን እናናግራለን የሚሉ ሰዎችን ፈ ል ጓ ቸ ው የሚሉ ሰዎች ቢኖሩ፤

ወለእለ በሃውዕ፣

ምታት አሳይተን፤ በጸውየ ቢል ስመ አ ጋ ን ን ት ን ጠርተን እናናግራለን የሚሉ ሰዎችን ፈ ል ጓ ቸ ው ፤ የሚሉ ሰዎች ቢኖሩ፣ በሉ ኢትንግሩነ ከንቶ፤ ከንቱ ነገርን አ ት ን ገ ሩ ን በሏቸው፤

ወኢትንብቡነ ሐሰተ፣

ሐሰት ነ ገ ር ን ም አትንገሩን በሏቸው፤

አኮኑ አሕዛብ ሕያዋን ይስእሉ ጎበ ምውታን፣

ሕያዋን አ ሕ ዛ ብ ከምውታን ልቡና ከጣዖታቱ ይለምናሉና ከንቱ ነገርን አ ት ን ገ ሩ ን በሏቸው፤

፳፣ እስመ ሕገ ወሀበ ለረድኤት፣

ለልቡና አጋዥ ጠበቃ ሊሆን ሕግን ሠርቷልና፤ አንድም ሕያዋን አሕዛብ ከምውታን ግብር ከጣዖታቱ የሚለምኑ አይደለምን፤

አንድም ከ ም ው ታ ን ግብር ከጣዖታቱ ይለምናሉና፤

ሕዝብሰ ይስእል ጎበ አምላኩ ይላል፤ እስራኤል ግን ከፈጣሪው ከእግዚአብሔር ዘንድ ይለም ናል፤ እ ስ መ ሕገ ወሀበ ለረድኤት ያ ግን ለ ል ቡ ና አጋዥ ጠበቃ ሊሆን ሕግን ሠርቷልና፤

ከመ ይበሉ ኢኮነ ከመዝ ነገሩ፣

የጣዖቱ ነገሩ እንዲህ አይደለም ይሉ ዘንድ፤

ወኢየሀቡ ሐፍሰ በእንቲአሁ፣

ለጣዖቱ እፍኝ ዝግኝ ዘቢብ እንዳይሰጡ፤

፳፩፣ ወበዝ ይ መ ጽ እ ረኀብ ላዕሌክሙ፣

በዚህ ምክንያት ረኀብ ይመጣ ባችኋል፤

www.ethiopianorthodox.org

ወእምከመ ርኅብክሙ ትቴክዙ፡
ከተራባችሁም በኋላ ታዝናላችሁ፤
ወትነቡ ሕሙመ ላዕለ መልአክ ወላዕለ መኳንንት፣
በአለቃው ላይ ክፉ ነገር ትናገራላችሁ፤ የዕገሌ ዘመን ዘመን ሁኖ እያላችሁ በመኳንንቱም ላይ ክፉ ነገር ትናገራላችሁ፤ የነዕገሌ ዘመን ዘመን ሁኖ እያላችሁ፤
ወትኔጽሩ ላዕለ ውስተ ሰማይ፤ ላዕለና ውስተ ሰማይ አንድ ወገን ነው፤
ሰማይ ዝናም ለዘር፤ ጠል ለመከር ይሰጥ እንደሆነ ብላችሁ ወደሰማይ ታያላችሁ፤
ወታሕተ ውስተ ምድር፣
ታሕተና ውስተ ምድር አንድ ወገን ነው፤ ምድርም የዘሩባትን ታበቅል የተከሉባትን ታጸድቅ እንደሆነ ብላችሁ ወደምድር ትመለከታላችሁ፤
፳፪፣ ወትሬእዩ ጽፉቀ ጽልመተ፣
ድርቅን ታያላችሁ፤
አንድም አንገታችሁን ትደፋላችሁ፤ ሰቢረ ክሣድ ትዕምርተ ኀዘን ነውና፤ ወትሬእዩ ጽፉቀ ጽኑ መከራን ታያላችሁ፤
ወትትመነደዑ ዓቢየ ምንዳቤ፣
በጽኑ መከራ ተይዛችሁ ትጨነቃላችሁ፤
ወተሐሙ ፣
ታዝናላችሁ፤
ወትጼነሱ፤
ትቸገራላችሁ፤
ወይጸልመክሙ ቅድሜክሙ፤
ፊታችሁ በመከራ ይጠቁራል፤
ወኢትሬእዩ፤
ተድላ ደስታን አታዩም፤

ምዕራፍ ፱

ጌባዔ

፩፣ ወኢይትባላሕ ኵሉ ዘተመንደበ እስከ ይበጽሕ ዕድሜሁ ለዝ፣
ሰባ ዘመን በመከራ የተጨነቀ ትሩፍ ከሰባ ዘመን አስቀድሞ አይድንም፤ የሚጠት ጊዜው እስኪደርስ ድረስ፤
ወፍጡነ ይኬውን ዝንቱ እስከ ብሔረ ዛብሎን ወምድረ ንፍታሌም፣
ይህ ሚጠት እስከ ዛብሎን እስከ ንፍታሌም ዕፃ ድረስ ፈጥኖ ይደረጋል፤
ወተረፈ ጸራልዩ፣
ጽንፈ ባሕር ማለት ነው፤ እስከ ጽንፈ ባሕር ድረስ ይደረጋል፤
ወማዕዶተ ዮርዳኖስ፣
እስከ ዮርዳኖስ ማዶ ድረስ ፈጥኖ ይደረጋል፤

ወገሊላ ዘአሕዛብ፣
ዘሕዝብ አለና ዘአሕዛብ አለ፤ የአሕዛብ፤ ክፍል እስከምትሆን እስከ ገሊላ ድረስ ይደረጋል፤
፪፣ ወሕዝብ ዘይነብር ውስተ ጽልመት ርእዩ ብርሃነ ዓቢየ፣
በጨለማ የሚኖሩ ሰዎች ደገኛ ብርሃንን አዩ አለ፤ በመከራ የሚኖሩ ሰዎች ብርሃን ረድኤትን አዩ፤
ወለአለ ይነብሩ ውስተ ጽልመት ወጽላሎተ ሞት ብርሃን በርሀ ላዕሌሆሙ፣
ጨለማ በበዛበት፤ ሞት ጥላውን በጣለበት ለሚኖሩ ሰዎች ብርሃን ወጣላቸው ማለት በመከራ ለሚኖሩ ሰዎች ተድላ ደስታ ተደረገላቸው፤ ጽልመት ያለው የሁለቱ ነገድ፤ ጽላሎተ ሞት ያለው የአሥሩ ነገድ መከራ ነው፤ ጽላሎተ ሞት አለ፤ በዘመን ቀድመዋቸዋል በቦታም ርቀዋቸዋልና፤
አንድም ወኢይትባላሕ ኵሉ ዘተመንደበ ብለህ መልስ፤ አምስት ሺህ ከአምስት መቶ ዘመን በመከራ የተጨነቀም እመን ከዚህ አስቀድሞ ማለት ከአምስት ሺህ አምስት መቶ ዘመን አስቀድሞ አይድንም፤ የዚህ የሥጋዌ ጊዜው እስኪደርስ ድረስ፤
አንድም የሚጠተ ነፍስ ጊዜው እስኪደርስ፤ ይህ ሥጋዌ እስከ ዛብሎን እስከ ንፍታሌም ዕፃ ድረስ ፈጥኖ ይደረጋል፤
አንድም ይህ ሚጠተ ነፍስ ፈጥኖ ይደረጋል፤ ወተረፈ ጸራልዩ ወማዕዶተ ዮርዳኖስ ወገሊላ ዘአሕዛብ በዚህ ሁሉ ሥጋዌ ይደረጋል፤ አንድም በዚህ ሁሉ ሚጠተ ነፍስ ይደረጋል፤
ወሕዝብ ዘይነብር ውስተ ጽልመት ርእዩ ብርሃነ ዓቢየ፣
በገሃነም በጽኑ መከራ ተይዘው ይኖሩ የነበሩ ምእመናን ጌታ ተወልዶላቸው፤ ልጅነት ተሰጥቷቸው አዩ፤
ወለአለ ይነብሩ ውስተ ጽልመት ወጽላሎተ ሞት ብርሃን በርሀ ላዕሌሆሙ፣
ጽልመት በራሳቸው ፍዳ፤ ጽላሎተ ሞት በእናት ቢአባታቸው ፍዳ ለተያዙ ሰዎች ፍትሕ ወጣላቸው፤ ጽላሎተ ሞት አለ በራስ ፍዳ ላይ የእናት የአባት ፍዳ ሲታከል መከራ ይጸናልና፤
፫፣ ወዘይበዝኅ ሕዝበ አውረድከ በትፍሥሕት፣
ከእስራኤል የሚበዙትን በተድላ በደስታ አወረድኻቸው፤

www.ethiopianorthodox.org

ውነሊቆ ፫ ዓመት እትቤቀሎ ለንጉሠ ባቢሎን ወለኮሉ ሰብኡ ወእምድኅረ ፫ ዓመት እሑው ጸክሙ በሣህል ያለውን ሰም ተው ወርደዋልና፤

ወይትነሠዩ በቅድሜከ ከመ ዘእለ ይትካፈሉ በርበረ፤

እስራኤል ምርኮ እንደሚካፈሉ፤

ወከመ ዘእለ ይትፈሥሑ በማዕረር፤

በመከር ጊዜ ደስ እንደሚላቸው ሰዎች በፊትህ ደስ ይላቸዋል፤

፬፤ እስመ ተሥዕረ አርዑቶሙ ዘንቡር ዲበ መትከፍቶሙ፤

በሳቸው ላይ ጸንቶ የነበረ የሰናክሬም የልብጣሶር አገዛዝ ጠፍቶላቸዋልና፤ አንድም እስመ ተአተተ በትር ዘንቡር ዲበ መትከፍቶሙ ይላል፤ በሳቸው ላይ ሠልጥኖ የነበረ ሰናክሬም ብልጣሶር ጠፍቶላቸዋልና፤

እስመ ሜጠ በትሮሙ ለእለ ይትፈደዩ፤

ግብር ይቀበሉ የነበሩ የለሰናክሬምን የለብልጣሶርን ሥልጣን ወደጥፋት መልሶታልና፤

አንድም ፍዳ የሚቀበሉ የትሩፋንን ድካም ወደ ብርታት፤ ወደኃይል መልሷልና፤

ወዐለዎሙ ለእለ ያቀትዉ፤

ግብር ያስገብሩ የነበሩ ሰናክሬምን፤ ብልጣሶርን ወደጥፋት መልሷቸዋልና፤

ከመ አመ መዋዕለ ምድያም፤

ምድያም በጌዴዎን ጊዜ ወደ ጥፋት እንደተመለሰች ወደጥፋት መልሷቸዋልና (ጥቅስ) ዕልዋ እግዚኦ ለምክረ አኪጦፌል እንዲል፤ (፪ሳሙ፡ ፲፭÷፴፩)፤

አንድም ወዘይበዝኅ ሕዝበ አውረድከ በትፍሥሕት፤ ብዙዎች ምእመናንን በተድላ በደስታ አወረድኻቸው (ጥቅስ) በሐሙስ ዕለት ወበመንፈቃ ለዕለት እትወለድ እምወለተ ወለትከ ወእድኅክ ውስተ መርኅብከ ወእትቤዘወከ በመስቀልየ ወበሞትየ ያለውን ተስፋ ሰምተው ወርደዋልና፤

ወይትነሠዩ በቅድሜከ፤

ምእመናን ምርኮ እንደሚካፈሉ፤ በመከር ጊዜም ደስ እንደሚላቸው ሰዎች በፊትህ ደስ ይላቸዋል፤

እስመ ተሥዕረ አርዑቶሙ፤

በሳቸው ላይ ጸንቶ የነበረ የዲያብሎስ አገዛዝ ጠፍቶላቸዋልና፤

አንድም እስመ ተአተተ በትር ዘንቡር ዲበ መትከፍቶሙ፤

በሳቸው ላይ ሠልጥኖ የነበረ ዲያብሎስ ድል ተነሥቷልና ምእመናን ደስ ይላቸዋል፤

እስመ ሜጠ በትሮሙ ለእለ ይትፈደዩ፤

የነጢአት ፍዳን የሚቀበሉ የአጋንንትን ሥልጣን ወደጥፋት መልሶታልና፤

ወዐለዎሙ፤

የነጢአት ግብር ያስገብሩ የነበሩ አጋንንትን ወደጥፋት መልሷቸዋልና፤

ከመ አመ መዋዕለ ምድያም፤

ምድያም በጌዴዎን ጊዜ ወደጥፋት እንደተመለሰች አጋንንትን ወደጥፋት መልሷቸዋልና፤

ወይትነሠዩ በቅድሜከ ብለህ እሠር፤

፭፤ ወዘተቀብዐ ደመ ኮለንታሁ ልብስ አልቦ ዘይበቍዕ ለምንትኒ ዘእንበለ አውዕዮ በእሳት፤

ሁለንተናው ደም የተቀባ ልብስ በእሳት ይቃጠላል እንጂ ለምንም ለምን እንዳይረባ እንዳይጠቅም፤ ሰናክሬም ብልጣሶር ለምንም ለምን አይረባም፤ አይጠቅምም፤ እስመ ነሥአ አረዘኮሉበጕህሉት ወተፈድየ አልባሰበተውላጥየሚል አብነት ይገኛል፤ ሰናክሬም በተንኮል ብሔርየኒ ዘከመ ብሔርከሙ ብሔረ ስርናይ ወወይን፤ በማለት የእስራኤልን ሁሉ ገንዘብ ገንዘብ አድርጓልና፤

ወተፈድየ፤ ኀጢአታቸውን ለውጥ በማድረግ የሰውን ሁሉ ልብስ ወስዷልና ሁለንተናው ደም የተቀባ ልብስ በእሳት ይቃጠላል እንጂ ለምንም ለምን እንዳይረባ፤ እንዳይጠቅም፤ ሰናክሬም ለምንም ለምን አይረባም፤ አይጠቅምም፤

አንድም ብልጣሶር በተንኮል የእስራኤል ፈጣሪ ምን ቁም ነገር ነው፤ አያድን አይራዳ፤ አይታደግ በማለት የሰውን ሁሉ ገንዘብ ወስዶአልና፤

ወተፈድየ፤ ኀጢአታቸውን ለውጥ በማድረግ የሰውን ሁሉ ልብስ ወስዷልና ሁለንተናው ደም የተቀባ ልብስ በእሳት ይቃጠላል እንጂ ለምንም ለምን እንዳይረባ፤ እንዳይጠቅም ብልጣሶር ለምንም ለምን አይረባም፤ አይጠቅምም፤

አንድም ወዘተቀብዐ ደመ ኮለንታሁ ልብስ ብለህ መልስ፤ ሁለንተናው ደም የተቀባ ልብስ በእሳት ይቃጠላል እንጂ ለምንም ለምን እንዳይረባ እንዳይጠቅም፤

www.ethiopianorthodox.org

ዲያብሎስ ለ ም ን ም ለምን አይረባም፤ አይጠቅምም፤

አንድም እስመ ነሥአ አራዘ ኮሉ፣ ዲ ያ ብ ሎ ስ በተንኰል የሰውን ሁሉ ልጅነት ገንዘብ አድርጓልና፤

ወተፈድየ አልባሰ በተውላጥ፣

ኀጢአታቸውን ለውጥ በማድ ረግ የሰውን ሁሉ ልጅነት አጥፍቷልና፤ (ጥቅስ) እስመ አ ል በ ስ ከ ኒ ልብሰ ሕይወት ወ ከ ደ ን ከ ኒ ክዳነ ኀሜት እንዲል፤ ኢሳ. ፷፩÷፲ ፣

አንድም እስመ ነሥአ አራዘ ኮሉ በ ገ ሀ ለ ት፤ ጌታ በገሀሉት የሕዝቡን የአሕዛቡን ሥጋ ተዋሕዷልና በገሀሉት አለ፤ ዲ.ያብሎስ በ/ጋ ከይሲ ተሠውሮ አዳምን ቢ.ያስት ጌታ በ/ጋ ብእሲት ተሠውሮ ድል ነሥቶታል፤ (ጥቅስ) ወበከመ ተ·ነብዐ ሰይጣን በ ገ·ሀ ለ·ቱ ውስተ ሥጋ ከይሲ ከማሁ ኮነ ድኅነትነ፤ በ ተ ሠ ወ ሮ ተ ቃለ እ ግ ዘ አ ብ ሔ ር በዘመድነ እንዲል (መቅ ወን)፤ አንድም ለገሀሉት ይላል፤ ዲ.ያብሎስን ሊ.ከዳው የሕዝቡን የአሕዛቡን ሥጋ ገንዘብ አድርጓልና፤

ወተፈድየ ፣

አብልጁን ለምእመናን ለውጥ አድርጓልና፤(ጥቅስ) ወተዋለጠ፤ ዓለሞ በክርስቶስ እንዲል፡ ፪ኛ፣ ቆ፭-፲፱፤ አንድም ወልድ ራሱን ለምእመናን ለውጥ አድርጓልና ሁለንተናው ደም የተቀባ ልብስ በእሳት ይቃጠላል እንጂ ለ ም ን ም ለምን እንዳይረባ ዲ.ያብሎስ ለምንም ለምን አይረባም፤

፮፣ እስመ ሕፃን ተወልደ ለነ ፣

ሕዝቅያስ ዘሩባቤል ተወልዶል ናልና፤

ወልድ ተውህበ ለነ፣

ከዚህም በኋላ ለመንግሥት ተሰ ጥቶልናልና ሁለንተናው ደም የተቀባ ልብስ በእሳት ይቃጠላል እንጂ ለምንም ለምን እን ዳይረባ ሰናክክሬም ብልጣሶር ለ ም ን ም ለምን አይረባም፤ አንድም ሕዝቅያስ ዘሩባቤል ተወልዶልናልና ከዚህም በኋላ ለመንግሥት ተሰጠልን፤

አንድም ሕዝቅያስ ዘሩባቤል ተወለደልን፤ ከ ዘ ህ ም በኋላ ለመንግሥት ተሰጠልን፤

አንድም እስመ ሕፃን ተወልደ ለነ ብለህ መልስ፣ ሕፃን ጌታ፤ ተወልዶልናልና ከዚህም አስቀ ድሞ ለልብሰተ ሥጋ ተሰጥቶል

ናልና ሁለንተናው ደም የተቀባ ልብስ በእሳት ይ ቃ ጠ ላ ል እንጂ ለምንም ለምን እንዳይረባ ዲ.ያብሎስ ለ ም ን ም ለምን አይረባም፤

አንድም ሕፃን ጌታ ተ ወ ል ዶ ልናልና ከዚህም በኋላ ለሕማም ለሞት ተሰጠልን፤

አንድም ሕፃን ጌታ ተወለደልን፤ ከዚህም በኋላ ለሕማም ለሞት ተሰጠልን፤

ወቅድመት ኮነ ዲበ መትከፍቱ፣

ለሕዝቅያስ ለዘሩባቤል ሥል ጣን ተሰጠው፤

አንድም ወቀደምት ኮኑ ዲበ መትከፍቱ ይላል፤ እስራኤልን በሥልጣኑ አጸናቸው፤

ወይሰመይ ስሙ ዓቢየ ምክር፣

ሕ ዝ ቅ ያ ስ ዘሩባቤል ጽኑዐ ምክር ይባላል፤

አበ ዓለም፣

አበ ዓለም ይባላል፤

ወመልአከ ሰላም

መልአከ ሰላም ይባላል፣

፯ ፣እስመ አነ አመጽአ ሰላመ፣

ለመላእክት ለአለቆች ፍቅር አንድነትን አመጣለሁና፤

ወሕይወት ዚአሁ፣

ሕዝቅያስ ዘ ሩ ባ ቤ ል ማዳን መግደል ይቻለዋል፤

ወዕበይ ቅድሜሁ፣

በሕዝቅያስ በዘሩባቤል ፊት ትእምርተ መንግሥት አለ፤ ሳንቲ ዛጉፍ ይነፋል፣ ድብ አንበሳ ይ ሳ ባ ል ፣ ትሩፋንን ከባቢሎን ይዞ ሲወጣ ሳንቲ ዛጉፍ እያስመታ ድብ አንበሳ እያሳበ ወጥቷልና፤

ወአልቦ ማኅለቅት ለሰላሙ፣

ለሚያደርገው ተድላ ደስታ ፍጻሜ የለውም፤ በሕዝቅያስ በዘሩባቤል ጊዜ እስራኤል ጠ ላት ጠ ፍ ቶ ላ ቸ ው በወይኑ፣ በበለሱ ሥር ድ ን ኳ ና ቸ ው ን ተክለው፣ ጃንጥላቸውን ጥለው ሲበሉ ሲጠጡ ይውሉ ነበርና፤ (ጥቅስ) ይበልዑ ወ ይ ሰ ት ዩ ታሕተ በለሶሙ ወወይኖሙ ወይነብሩ ተአሚኖሙ እንዲል፤ (፩ ነገ፡ ፬÷፳፭)፤

አንድም ወቅድመት ኮነ ዲበ መትከፍቱ ለጌታ ሥልጣን የባሕርዩ ነው፤ አንድም መስቀል በትከሻው ላይ ሆነ፤ አንድም ወቀደምት ኮኑ ዲበ መትከፍቱ፤ ምእመናንን በነፍስ አጸናቸው፤ አንድም አበው በ ጫ ን ቃ ው ናቸው፤ የደከመን ሰው ተሸክሞ

www.ethiopianorthodox.org

እንዲ.ያሳርፉት፣ መከራ ተቀ ብሎ አበውን አድኗቸዋልና፡ (ጥቅስ) ወሶበ ረከቦ ያሮ ዲበ መትከፍቱ እንዲል፡ (ሉቃ ፲፫÷፭)፡ ወይሰመይ ስሙ ዓቢየ ምክር፡ ጌታ ምክሩ ሥጋዌ የተደነቀለት ይባላል፡ (ጥቅስ) እስመ ኢሳይያስ ሰመዮ መንክረ እንዲል፡ ኢሳ. ፱፡ መንክርሰ እግዚአብሔር በአርያሙ እንዲል፡ (መዝ ፺፪÷፬) ፡

አበ ዓለም፣

አበ ዓለም፡ ሐዲስ ይባላል፡

ወ መ ል አ ከ ሰላም መምህረ ወንጌል ይባላል፡ እስመ አነ አመጽእ ሰላመ ለመላእክት፡ እኤ ለ ሐ ዋ ር ያ ት ፍቅር አንድነትን አ መ ጣ ለ ሁ ና፡ ወሕይወት ዘአሁ ጌታ ሕይወት የ ባ ሕ ር ዩ ነው፡ ወዕበይ ቅድሜሁ፡ ሠላሳ ሦስት ዓመት ከሦስት ወር በፊቱ ተአምራት ይደረጋል፡ አንድም በአካለ ነፍስ ሲአል ወርዶ ነፍሳትን ከማውጣቱ አስቀድሞ በአግረ መስቀል ተአምራት ይደረጋል፡ ከአምስት መቶ የሚበዙ ከስድስት መቶ የሚያንሱ ሙታን ተነሥተዋልና፡ አ ን ድ ም ከሦስት ዓመት ከሦስት ወር አስቀድሞ ሠላሳ ዘመን በፊቱ ተአምራት ይደረጋል፡ ወአልቦ ማኅለቅት ለሰላሙ እያዘዘ ለሚያደርገው ተድላ ደስታ ፍጻሜ የለውም፡ በጌታ ጊዜ ሥጋዊ ጠላት ቅሉ ጠፍቶላቸው ነበርና (ጥቅስ) ወ አ ጠ ፍ እ ሠረገላ እምኤፍሬም ወአፍራሰ እምይሁዳ ወይከውን ሰላም በመዋዕሊሁ እንዲል ፡

ዲበ መ ን በ ረ ዳ ዊ ት ት ጸ ን ዕ መንግሥቱ፣

የጌታ መ ን ግ ሥ ቱ በዳዊት ዙፋን ላይ ት ጸ ና ለ ች ፡ ጌታ በዳዊት ዙፋን ነግሷል ቢሉ አምን ዳዊት ሥጋዊ አድርጎ የ ገ ዛ ው ን ጌታ መንፈሳዊ አድርጎ ገ ዝ ፈ ል ና፡ ዳዊት የጸጋ አድርጎ የገዛውን ጌታ የባሕርይ አድርጎ ገዝፈልና፡ አንድም በመስቀል ሲል ነው (ጥቅስ) አ ር ት ዕ ተ ሠራ ኅ ወ ን ገ ሥ ባለው፡ (መዝ.፵፬)፡ አንድም በሥልጣን ሲል ነው፡ (ጥቅስ) መ ን በ ር ከ እግዚአ ለዓለመ ዓለም ባለው (መዝ.፵፬) አንድም በምእመን ሲልነው (ጥቅስ) ስምዓ ወለትየ ወርእዪ ወ አ ዕ ም ዒ ዕዝነኪ ባለው (መዝ.፵፬) አ ን ድ ም በሥጋ ሲልነው፡ (ጥቅስ) አሜሃ ይነብር ልዑል ዲበ መንበሩ ዘፈጠረ እንዲል፡ (ዕዝሱቱ. ፮ ÷፴፫)፡

ወይትዌከፍ በ ጽ ድ ቅ ወበርትዕ እምይእዜ ወእስከ ለዓለም፣

ሕዝቅያስ ዘሩባቤል በእውነት ነገር በቀና ነገር የመጣለትን ከዛሬ ጀ ም ሮ ለ ዘ ለ ዓ ለ ሙ ይ ቀ በ ላ ል ፡ አንድም ጌታ በአሪት፡ በወንጌል ያመነውን ይቀበላል፡

ቅንዓተ እግዚአብሔር ይገብር ከመዝ.፣

እግዚአብሔር ለ አ ም ላ ክ ነ ቱ የ ሚ ቀ ና ው ቅናት እንዲህ ያደርጋል፡

፷፣ ወፈነወ እግዚአብሔር ሞተ ላዕለ ያዕቆብ፣

ይገብር ያለውን ፈነወ ብሎ አመጣው እግዚአብሔር በሁለቱ ነገድ ሞትን አ መ ጣ ባ ቸ ው ፡ አንድም ቅ ን ዓ ተ እግዚአብ ሔር ይገብር ከመዝ.፣ ለአምላክነቱ የቀናው ቅናት እንዲህ ያደርጋል ማለት የእስራኤልን ድኅነት የ አ ሕ ዛ ብ ን ጥፋት፡ አንድም የነፍሳትን የምእመ ናንን ድኅነት የአጋንንትን የ መ ና ፍ ቃ ን ጥፋት ያደር ጋል፡ ወፈነወ እግዚአብሔር፡ ወደ ብሉዩ ተመለሰ፡

ወመጽአ መቅሠፍት ላዕለ እስራኤል

በ አ ሥ ሩ ም ነ ገ ድ መዓት መቅሠፍት መጣባቸው፡

፱፣ ወ የ አ ም ሩ ኵሉ ሕዝበ ኤፍሬም ወእለ ይነብሩ ሰማርያ በኀሳሮሙ፣

በሰማርያ የሚኖሩ የኤፍሬም ወገኖች ሁሉ ይህ የመጣባቸው መዓት መቅሠፍት በኃጢአታ ቸው እንደሆነ ያውቃሉ፡

እለ ይብሉ በትዝኅርተ ልቦሙ፣

በልቡናቸው ትዕቢት እንዲህ የሚሉ ፣

ግንፋልሰ ወድቀ፡

ጡቡስ ወደቀ፡

ንዑ ንቀር ዕብነ፣

ኑ ደንጊያ እናለዝብ፣

ወንግዝም ጽሕደ፣

ጥዱንም እንቍረጥ፡

ሰግላሰ ነቅዘ፣

ሾላውስ ነቀዘ፡

ወንሕንዕ ማኅፈደ ለነ፣

ግንብ እንሥራ የሚሉ ተዘክሮተ እግዚአብሔር ጠፍቶባቸው፡

አንድም ቤቱ የማይፈርስ እነሱ የማይሞቱ መስሏቸው፡

፲፣ ወያንኅሉ እግዚአብሔር ዲበ እለ ይቀውሙ ውስተ ደብረ ጽዮን፣

በደብረ ጽዮን በሚኖሩ በሁለቱ ነገድ በ ጠ ላ ት ነ ት በተነሡ በአሥሩ ነገድ ኃጢአት የአሥ ሩን ነገድ ቤት ያፈርሰዋል፡ አንድም በ ደ ብ ረ ጽዮን በሚኖሩ በሁለቱ ነገድ ኃጢ

www.ethiopianorthodox.org

አት የሁለቱን ነገድ ቤት ያፈርሰዋል፤ አንድም በደብረ ጽዮን በሚኖሩ በአሥሩ ነገድ ኃጢአት የአሥሩን ነገድ ቤት ያፈርሰዋል አለ፤ የከተማ ቤት አላቸውና፤ አንድም በደብረ ጽዮን ያለ የአሥሩን ነገድ ቤት ያፈርሰዋል፤ ደብረ ጽዮን የሁለቱ ነገድ አገር ስም ብቻ አይደለም፣ የአሥሩም ነገድ አገር ደብረ ጽዮን ይባላልና፤

፲፩፣ ወያመጽኦሙ ለሶርያ እምሥራቀ ወሐይ፣

የሶርያን ሰዎች ከፀሐይ መውጫ ያመጣቸዋል፤

ወለአረማውያን እምዕራብ ወሐይ ፣

አረማውያንንም ከፀሐይ፤ መግቢያ ያመጣቸዋል፤ አራምያን ይላል፤ የሶርያ ሰዎች ናቸው፤ በአራም አራምያን አላቸው፤ የሶርያን ሰዎች ከፀሐይ መግቢያ ያመጣቸዋል፤

እለ ይውኀጥዎሙ ለእስራኤል፣

እስራኤልን እንደ ጥጎሎ የሚውጧቸው፤ እንደ እንቀት የሚጠጧቸው፤

ወአብቀዉ አፉሆሙ ላዕሌሆሙ፤

አፋቸውን በሳቸው ላይ አላቀቁ ትዕምርተ ፀብዕ ነው፤

ወምስለ ዝንቱ ኮሉ ኢተመይጠት መዓቱ፤

ከዚህም ጋራ መዓቱ አልተመለሰችም፤

ወዓዲ ዕዴሁ ልዕልት፣

ልዕልት የምትሆን ሥልጣኑ ኢተመይጠት ፤ አልተመለሰችም፤

አንድም ዓዲሃ ልዕልት ሥልጣኑ ገና እንደተቃጣች ናት፤

፲፪፣ ወሕዝብሂ ኢተመይጡ እስከ ተቀሥፈ እስራኤል፣

እስራኤል በመከራ እስኪገረፍ ድረስ አልተመለሰም፤

ወኢኀሠሦ ለእግዚአብሔር ኀያል፣

ኀያል የሚሆን እግዚአብሔርን በሕግ በአምልኮት አልተከተለውም፤

፲፫፣ ወመተረ እግዚአብሔር እም እስራኤል ርእሰ ወዘነበ፤

እግዚአብሔር ከእስራኤል ራስ ጅራት ቈረጠ፣

፲፬፣ ዓቢየ ወንዑሰ፣

ርእስ ያለውን ዓቢየ፤ ዘነበ ያለውን ንዑሰ ብሎ ደገመው፤

ወልሒቅ ዘያደሉ ለገጽ ውእቱ ርእስ፣

ርእስም ያልሁት ለሰው ፊት የሚያደላ ሽማግሌ ነው፤

ነቢይሂ ዘይሜህር ዓመፃ ውእቱ ዘነብ፣

ዘነብም ያልሁት ዓመፅን የሚያስተምር ነቢየ ሐሰት ነው፤

አንድም ወመተረ እግዚአብሔር ብለህ መልስ፤ እግዚአ

ብሔር ከእስራኤል ራስ ጅራት ቈረጠ ዓቢየ ወንዑሰ፤ ታላቁንም ታናሹንም አጠፋ፤ ርእስ ያልሁት ለሰው ፊት የሚያደላ ሽማግሌ ነው፤ ዘነብም፤ ያልሁት ዓመፅን የሚያስተምር ነቢየ ሐሰት ነው፤ የላይኛውን ተረጌመ፤

፲፭፣ ወይቤግዩ እለ ያስተበዕዖሙ ለዝንቱ ሕዝብ፣

እስራኤልን ሰላም ሰላም አይሏችሁ ቄዋቄ የለም እያሉ የሚያደናንቋቸው ነቢያተ ሐሰት ካህናተ ጣዖት ይበድላሉ፤

ወያስሕትዎሙ ከመ የኀጥዎሙ፣

እንደ ጥጎሎ ይውጧቸው፤ እንደ እንቀት ይጠጧቸው ዘንድ፤ አንድም ያጎጥእዎሙ አገራቸውን ያሳጧቸው ዘንድ ያስቷቸዋል፤

፲፮፣ በእንተ ዝንቱ ኢይትፌሣሕ እግዚአብሔር በወራዙቶሙ፣

ወይቤግዩ ብሎ ነበርና ስለዚህ ነገር እግዚአብሔር በጕልማሶቻቸው ደስ አይለውም፤ አንድም ወያስሕትዎሙ ከመ የኀጥዎሙ ብሎ ነበርና ስለዚህ ነገር እግዚአብሔር በጕልማሶቻቸው ደስ አይለውም፤

ወኢይሣሃል ወራዙቶሙ ወዕቤራቲሆሙ፣

ጕልማሶችን ፤ ባልቴቶችን ይቅር አይላቸውም፤

እስመ እኩያን ወጽልሑዋን፣

ክፉዎች ከዳተኞች ናቸውና ይቅር አይላቸውም፤

ወኮሎ አፍ ይነብብ ዓመፃ፣

የሰውም ሁሉ አንደበት ዓመፅን ይናገራልና፤

ወያስሕትዎሙ ላለው፣

ወበዝኀ ኢተመይጠት መዓቱ፣

በዚህም መዓቱ አልተመለሰችም፤

ወዓዲ እዴሁ ልዕልት፣

ልዕልት የምትሆን ሥልጣኑ ኢተመይጠት አልተመለሰችም፤ አንድም ዓዲሃ ልዕልት ገና እንደተቃጣች ናት፤

፲፯፣ ወትነድድ ከመ እሳት ኃጢአት ወከመ ጎሠር ይቡስ ዘበልዐቶ እሳት ወይውዕዩ ከመ ሣዕረ ገዳም፣

ኃጢአት እንደ እሳት ታጠፋለች፣ ሰዎቹም እሳት እንደ በላው ገለባ ይሆናሉ፤ እንደ ምድረ በዳ ሣር ይጠፋሉ፤

፲፰፣ ወይበልዕ ዘዓውዳ አውግር ኮሉ መቅሠፍተ መዓቱ ለእግዚአብሔር፣

የእግዚአብሔር መዓቱ መቅሠፍቱ በነገሥታቱ በመኳንንቱ

www.ethiopianorthodox.org

ዙሪያ የሰፈሩ ሠራዊትን ያጠ
ፋል፤

ታውዒ ኵሎ ምድረ፣

ታውዒ ኵሎ ምድረ፡ ማንሻ
መዓቱ መቅሠፍቱ አገሩን ሁሉ
ታጠፋለች፤ አንድም ወይበልዕ
ዘዓውጹ አውግር፣ በኮረብታ
ዙሪያ ያለ ሣር እንዲቃጠል
እንደዚያ ይጠፋሉ ፡ ኵሉ
መቅሠፍተ መዓቱ ለእግዚአ
ብሔር ታውዒ ኵሎ ምድረ
ኵሉ ካለ ያውዒ፣ ታውዒ
ካለ ኵላ፣ ቢል በቀና ነበር፡
ልማደ መጽሐፍ ነው ተቈጥቶ
ያመጣት መቅሠፍት ምድሩን
ሁሉ ታጠፋለች፤

አንድም ወ ይ በ ል ዕ ዘዓውጹ
አውግር ኵሉ መ ቅ ሠ ፍ ተ
መዓቱ ለእግዚአብሔር፤ እግዚ
አብሔር ተቈጥቶ ያመጣው
መ ቅ ሠ ፍ ት በንጉሡ ዙሪያ
ያሉ መኳንንቱን ያጠፋል፤
ወ ታ ው ዒ ይላል በቃል
አምጥቶ፤ መቅሠፍቱ ምድሩን
ሁሉ ታጠፋለች፤

ወ ይ ከ ው ኑ ሕ ዝ ብ ከመ ዋዕየ
እሳት፡

ይህ ሊመጣባቸው እስራኤል
እንደ ምድረ በዳ ቋያ ይሆናሉ
ያ እ ን ዲ ያ ጠ ፋ ያጠፋሉ
አንድም ከመ ዘአውዐዮ እሳት
ይላል፤ እስራኤል እሳት አንደ
አቃጠለው ቋያ ይሆናሉ፤ ያ
እንዲጠፋ ይጠፋሉ፤

፲፱፣ ወኢይምሕር ብእሲ እኅዋሁ፣

ወንድም ለወንድሙ አያዝንም፤

ወይበልዕ ፀጋሞ፣

የወንድሙን ገንዘብ ይበላል፤

ወኢይፀግብ ሰብእ እንዘ ይበልዕ
ሥጋ መዝራዕቱ፣

ቢበላ ቢበላ አ ይ ጠ ግ ብ ም
ማለት የወንድሙን ገንዘብ
ቢወስድ ቢ ወ ስ ድ በ ቃ ኝ
አይልም፡

፳፡ ወይበልዖ ኤፍሬም ለምናሴ፣

ኤፍሬም ምናሴን፤

ወምናሴ ይበልዖ ለኤፍሬም፣

ምናሴ ኤፍሬምን ይበላዋል
ማለት ገንዘባቸውን ይበላላሉ፤

እስመ ኀብሩ ይትቃተልዋ ለይሁዳ፣

ሁለቱን ነገድ ያጠፉ ዘንድ
መክረዋልና በዚያ ፍዳ ይጠ
ፋሉ፤ አንድም ነገደ ኤፍሬም
የነገደ ምናሴን ገንዘብ ይበላል፤
ነገደ ምናሴም የነገደ ኤፍሬምን
ገንዘብ ይበላል፤ እስመ ኀብሩ፣
አሥሩን ነገድ ሁለቱን ነገድ
ሊያጠፉ ተባብረዋልና እርስ
በ ር ሳ ቸ ው ይጠፋሉ፤ ወበዝ
ኢተመይጠት መዓቱ ወዓዲ
እዴሁ ልዕልት እንዳለፈው
ተርጕም፤

ጉባዔ

ምዕራፍ ፲

፩፣ አሌ ሎሙ ለእለ ይ ጽ ሕ ፉ
መጽሐፈ እኩየ፡

ሐሰት ትች ለሚተቹ ሰዎች
ወዮላቸው፤

አንድም መ ጽ ሐ ፈ ሥራይ
መጽሐፈ ሟርት፤ መጽሐፈ
ጥንቈላ ለ ሚ ጽ ፉ ሰ ዎ ች
ወዮላቸው፡

ወይመይጡ ፍትሐ ነዳይ ወምስኪን
ሕዝብየ፣

የወገኖቼ የድሀውን፤ የምስኪኑን
ፍርድ ለሚለውጡ ወዮላቸው፤

አንድም አሌ ሎሙ ለሕዝብየ
እለ ይመይጡ ፍትሐ ነዳይ
ወምስኪን፤ የድሀውን የምስ
ኪኑን ፍርድ ለሚለውጡ
ወገኖቼ ወዮላቸው፤

ወየሐይዱ ዕቤረ፣

ባልቴቲቱን ለሚቀሙ፤

ወይበረብሩ ዕጓለ ማውታ፣

እናት አባቱ ጥለውት የሞቱ
ትን ገንዘቡን ለሚቀሙ፤ ለሚበ
ዘብዙ ወዮላቸው፤

፪፣ ወምንተ ይሬስዩ አመ ዕለተ
ፍዳሆሙ፣

እንዲህ ሲ ያ ደ ር ጉ ኑረው
ፍዳውን ባመጣባቸው ጊዜ
ምን ያደርጋሉ ?

እስመ እምርኑቅ ይመጽኦሙ
ምንዳቤሆሙ፣

መከራቸው ከሰማይ፣

አንድም ከፋርስ ከ ባ ቢ ሎ ን
ይመጣባቸዋልና፤

አንድም ከእግዚአብሔር ይመ
ጣባቸዋልና፣ እግዚአብሔርን
ርኑቅ አለው፤ በ ም ል ዓ ት
በርቀት በስፋት ከሰው ርኑቅ
ነውና፤

ውኅበ መኑ ይትመሐፀኑ፣

ከማን ዘንድ ይጠጋሉ፤

አንድም ከዚህ አ ስ ቀ ድ ሞ
ከረዓሶን እንደተጠጉ ወደማን
ይጠጉ ይሆን?

ወመኑ ዘይረድኦሙ፣

የሚረዳቸውስ ማን ነው፤

አንድም ከዚህ አ ስ ቀ ድ ሞ
ረዓሶን እ ን ደ ረ ዳ ቸ ው ማን
ይረዳቸው ይሆን፤

፫፣ ወአይቴ የኀድጉ ትርሢቶሙ
ከመ ኢይደቁ ውስተ ኀሳር፣

ጌጣቸውን ወዴት ይተዋሉ፤
በደም እንዳይታለልባቸው እስ
ራኤል ደም የነካው እንደሆነ
ተጠይፈው አይለብሱትምና፤

አንድም በመከራ እንዳይወድቁ
ጌጣቸውን ለማን ይተዋሉ፣
ያጌጠውን በለው ይላልና፤

www.ethiopianorthodox.org

፱፣ ወበዝኒ ኮሉ ኢተመይጠት መዓቱ ወዓዲ እዴሁ ልዕልት፣

እንዳለፈው ተርጉም፡

፲፣ አሌ ሎሙ ለፋርስ በትረ መዓትየ ወቀስታምየ ውስተ እዴሆሙ፣

ብትሬ መንደርዶ በእጃቸው ለተያዘ ተይኒልና ለ ፋ ር ስ ሰዎች ወዮላቸው፣

፲፩፣ ወእፈኑ መቅሠፍትየ ላዕለ ሕዝብየ ኃጥአን፣

በወገኖቼ በእስራኤል መዓት መቅሠፍት አመጣለሁና፤

ወእኤገሠሙ ከመ ይበርብርዎሙ ለሕዝብየ፣

ወገኖቼ እስራኤልን ይበዘብ ዝቸው ዘንድ አዝጐቸዋለሁና፤

ወይኪድዎን ለአህጉሪሆሙ፣

አገራቸውን ይረጋግጡ ዘንድ ወይረስይዎን ከመ ፀ በ ል፤ እንደ ትቢያ ያደርጉት ዘንድ አዝጐቸዋለሁና ፤ ላዘዝኋቸው ለፋርስ ሰዎች ወ ዮ ላ ቸ ው ጥንቱን መምጣቱ እስራኤልን ለማጥፋት ነበር፤ ቦኑ ግልፎ ዘያድጎን ብሎ ጠ ፍ ቷ ል ና ወዮላቸው፤

፲፪፣ ውእቱሂ አኮ ከመ ተሐዘብዎ በልብ፣

ሰናክሬም ያ ጠ ፋ ል ብለው በልብ እንደ ተ ጠ ራ ጠ ሩ ት አይደለም፤

አንድም ኢየሩሳሌምን ይወ ጋል፤ እስራኤልን ይማርካል ብለው እንደ ተጠራጠሩት አይደለም፡

ወለነፍሱሂ አኮ ከመ ሐለይዋ፣

ሰውነቱንም ታጠፋለች ብለው እንደአሰቧት አይደለም፡

ዳዕሙ ይሜሩ አሕዛበ ብዙኃነ በምክሩ፣

ቦኑ ግልፎ ዘያድጎን በማለቱ ብዙ ሠ ራ ዊ ት ን ያጠፋል እንጂ፡

አንድም አሌ ሎሙ ለፋርስ በትረ መዓትየ ወቀስታምየ ውስተ እ ዴ ሆ ሙ ብለህ መልስ፡

ለፋርስ ሰዎች ወዮላቸው በትሬ መንደርዶ በእጃቸው ተይዞ ነበር፤ ትች፣ ወእፈኑ መቅሠ ፍትየ ላዕለ ሕዝብየ፤ መዓቴን መቅሠፍቴን በወገኖቼ አመጣ ለሁ፤ ብዬ ነበር፣ ትች:: ወገኖቼ አሕዛብን ይበዘ ብዟቸው ዘንድ አዝጐቸው ነበር፤ በተፈጥሮ ወገኖቼ ናቸውና አገራቸውን ይረጋግ ጡት እንደ ትቢያ ያደርጉት ዘንድ አዝጐቸው ነበር፣ ትች፤ ነገር ግን ሰናክሬም ቦኑ ግልፎ ብሎ ተሳድቧልና ወዮ ላቸው፤

ውእቱሂ አኮ ከመ ተሐዘብዎ በልብ፣

ሕዝቅያስ ይጠፋል ብለው በልብ እንደ ተጠራጠሩት አይደለም፤

ወለነፍሱሂ አኮ ከመ ሐለይዋ፣

ሰውነቱም ትጠፋለች ብለው እንደ አሰቧት አይደለም፤

ዳዕሙ ይሜሩ አሕዛበ ብዙኃነ በምክሩ፣

ሕዝቅያስ በምክሩ በጸሎቱ ብዙ አሕዛብ እለ ሰናክሬምን ያጠፋል እንጂ፤

፲፭፣ወእመኒ ይቤልዎ ባሕቲትከኑ መልአክ አንተ፣

ይህን ያህል የምትመካ አለቃ በውኑ አንተ ብቻ ነኽ ቢሉት እወ ያለበት ነው፤ አዎን ይላል፤

ወይብል ነሣእኩ ብሔረ ሔግትየ፣

ይህም ይታወቅ ዘንድ ሔግትን እጅ አደረግሁ፤

፲፮፣ ወበከመ ሔግት አርግትየ፣

ሔግትን ገ ን ዘ ብ እንደ አደረግሁ አርግትን ገንዘብ አደረግሁ፤

ወበከመ አርግት ሴፋሩሄም፣

አርግትን ገንዘብ እንዳደረግሁ ሴፋሩሄምንም ገንዘብ አደረ ግሁ፤

ወበከመ ሴፋሩሄም ካሌና፣

ሴፋሩሄምን ገንዘብ እንደአደ ረግሁ ካ ሌ ና ን ገንዘብ አደረግሁ፤

ወበከመ ካሌና ደማስቆ፣

ካሌናን ገንዘብ እንደ አደረ ግሁ ደማስቆን ገንዘብ አደ ረግሁ፤

ወበከመ ደማስቆ ሰማርያ፣

ደማስቆን እጅ እንዳደረግሁ ሰማርያን እጅ አደረግሁ፤

አንድም ወበከመ ካሌና ግዋ ወበከመ ግዋ ደማስቆ ይላል፣ ካሌናን ገንዘብ እንደ አደ ረግሁ ግዋን ገንዘብ አደረ ግሁ፣ ግዋንን ገንዘብ እንደ አደረግሁ ደማስቆን ገንዘብ አደረግሁ፤

ከማሁ እሬስያ ለይሁዳ፣

ሰ ማ ር ያ ን እንደአጠፋኋት ይሁዳን አጠፋታለሁ፤

ቦኑ ግልፎ ዘያድጎን በኢየሩሳሌም ወበሰማርያ፣

ሎቱ ስብሐት በውኑ በኢየሩ ሳሌም በሰማርያ የሚያድን ፈጣሪ አለን፤

ወበከመ ረ ሰ ይ ክ ዋ ለሰማርያ ወለግብረ እደዊሃ፣

ሰማርያን ጣዖቷን እንደአጠ ፋሁ፤

www.ethiopianorthodox.org

፲፣ ከማሁ እሬስያ ለኢየሩሳሌም ወለጣየታ፣

ኢየሩሳሌምን ጣየቷን አጠ ፋለሁ አለ፤ ሰማርያን እሱ አጥፍቷታል ቢሉ የአባት ዕዳ ለልጅ፣ የአፍንጫ እድፍ ለእጅ እንዲሉ፣ የአባቱን ለእሱ ሰጥቶ ተናገረ፤

አንድም አቤቶ ሲባል መጥቶ ወግቷታልና፤

አንድም አሁን ሲመጣ እግር መንገዱን አጥፍቷታልና፤

፲፩፣ ወእምዝ ፈጺሞ እግዚአ ብሔር ዘንተ ኵሎ ገቢረ በደብረ ጽዮን ወበኢየሩሳሌም፣

ሰናክሬም ቦኑ ግልፎ ዘያድጎን ብሎ ተናግሮ ከፈጸመ በኋላ፤

አንድም እግዚአብሔር በኢሳይ ያስ አድሮ ከዚህ ይውላል፤ ከዚህ ያድራል፤

ወኢይነድፍ ውስቴታ ሐፀ ብሎ በኢየሩሳሌም ተናግሮ ከፈፀመ በኋላ፤

፲፪፣ ያመጽእ እግዚአብሔር ላዕለ ኵሉ ዘያዐቢ ልቦ፣

ልቡናውን በሚያስታብይ በራሱ ስቲስ መዓት መቅሠፍት ያመጣል፤

ወላዕለ መልአከ ፋርስ፣

በሰናክሬም ላይ፤

ወዲበ አዕይንቲሁ፣

በነቢያተ ሐሰት ላይ፤

ወዲበ ትርሢቱ፣

በሠራዊቱ ላይ መዓት መቅሠፍት ያመጣል፤

፲፫፣ እስመ ይቤ በኃይልየ እገብር፣

በኃይሌ እስራኤልን አጠፋለሁ ብሏልና፣

ወበምክረ ጥበብየ እነሥእ በሐውርተ አሕዛብ፣

በጥበቤ በመከርሁት ምክር የአሕዛብን አገር እጅ አደርጋለሁ ብሏልና፤

ወእበረብሮሙ ኃይሎሙ፣

ሠራዊታቸውን አጠፋለሁ፤

አንድም ባለጸግነታቸውን እበዘ ብዛለሁ ብሏልና፤

ወአድለቀልቆን ለአህጉር እለ ይነብራ፣

ጠላት ጠፍቶላቸው ተዘልለው የሚኖሩትን አገሮች አነዋውጣ ቸዋለሁ ብሏልና፤

፲፬፣ ወአስተጋብዕ ኵሉ ዓለመ፣

ዓለሙን ሁሉ እጅ አደርጋለሁ ብሏልና፤

ወእትሜጠዎ በእዴየ ከመ ሕፃን፣

የዕለትን ልጅ በመሀል እጅ እንዲይዙ በእጄ እይዘዋለሁ ብሏልና፤

ወከመ አንቆቅሆ፣

እንቁላልን በመኻል እጅ እንዲይዙ በእጄ ጭብጥ፣ በእግሬ እርግጥ አድርጌ እይዛለሁ ብሏልና፤

ወአልቦ ዘያመስጠኒ፣

የሚያመልጠኝ የለም ብሏልና፤

ወአልቦ ዘይትዋሥአኒ፣

ገብር፣ ቀቅል ብለው አልገብርም አልቀቅልም ብሎ የሚከራከረኝ የለም ብሏልና መዓት መቅሠፍት ያመጣበታል፤

፲፭፣ ይትነሣእኑ ጕድብ ላዕለ ዘይገዝም ቦቱ፣

ገጀሞ በሚቈርጥበት ሰው ላይ በጠላትነት ይነሣልን፤ መነሣትስ እንዳይነሣ የለም እንጨቱን ቀኖረጥ ቢለው ተመልሶ አንተን ልቀኖረጥኽ ይለዋልን፤

ወይትሌዐልኑ ሞሰርት ላዕለ ዘይቄስር ቦቱ፣

መጋዝስ በሚቈርጥበት ሰው ላይ በጠላትነት ይነሣልን፤ መነሣትስ እንዳይነሣ የለም፤ እንጨቱን ቀኖረጥ ቢለው ተመልሶ አንተን ልቀኖረጥኽ ይለዋልን እንደዚህስ ሁሉ እስራኤልን አጥፋ ብየ ባመጣኽ ተመልሰኽ እኔን ቦኑ ግልፎ ሣለት ይቻልኻልን፣

እለ ይመትሩ ቦሙ ዕፀ፣

እንጨትየሚቈርጡባቸው ብሎ ለጕድብና ለሞሰርት ቀጠለ፤

፲፮፣ በእንተ ዝንቱ ይፈኑ ጎሳረ ዲበ ክብርከ፣

ስለዚህ ነገር በክብረ መንግሥትህ ላይ ተዋርዶን ያመጣብኻል፣

ወእሳተ ዲበ ትርሢትከ ዘያነድድ ወያውጺ፣

በሠራዊትኽም የሚያጠፋ መቅሠፍትን ያመጣብኻል ሰይፈ መልአክን ያመጣብኻል፤

፲፯፣ ወይከውን ብርሃነ እስራኤል እሳተ፣

የእስራኤል ጸሎታቸው አጥፊ ይሆናል፤

ወይትቄደሱ በእሳት ዘይነድድ ወያውጺ፣

የሚያጠፋ በሆነ በጸሎታቸው ይጸናሉ፤ ይከብራሉ፤

ወይበልዕ የመ ወሣዕረ፣

የሸአለቃውን የሰናክሬምን ሠራዊት ያጠፋል፤

አንድም ልዑላኑን፤ ትሑታኑን ያጠፋል፤

፲፰፣ ይእተ አሚረ ይጠፍኡ አድባር፣

ያንጊዜ ነገሥታቸ ይጠፋሉ፤

www.ethiopianorthodox.org

ወአውግር ወፆም፣

መኳንንቱ የሺ አለቃው ይጠ
ፋሉ፤

ወይበልዕ ነፍሰ ወሥጋ፣

በነፍስ፣ በሥጋ ያጠፋል፡

ወይከውን ከመ ዘይጐይይ እምነበ
ልባለ እሳት ዘይነድድ፣

ሰናክሬም ከቋያ የተነሣ እንደ
ሚሸሽ ጐሽ አጋዘን ይሆናል፤ ያ
እየወደቀ እየተነሣ እንዲሄድ
እሱም አጋንንት የመብረቅ
የነጐድጓድ ድምፅ እያሰሙት
እየወደቀ እየተነሣ ሂዷልና፡

፲፱፣ ወእለ ተርፉ እምውስቴቶሙ
ይከውኑ በኍልቍ፣

አሥራ ስምንት እልፍ
ከአምስት ሺህ ሰዎች አልቀው
ከእነሱ የቀሩትም በቍጥር
ይሆናሉ፤ የተቈጠረ እንዳይጠ
ፋ አይጠፉም፤

ወይጽሕፎሙ ሕፃን ንዑስ፣

ትንሽ ሕፃን ይቈጥራቸዋል፤
ልጅ አንድ ሁለት ሦስት
አራት አምስት ስድስት ሰባት
ብሎ ከዚህ በላይ አይቈጥርም፤
እሱም አሥራ ስምንት እልፍ
ከአምስት ሺህ ሰው አጥፍቶ
ሰባት ፈረሰኛ ሁኖ ቀርቷልና፤

አንድም ወእለ ተርፉ፤ አባቶች
አልቀው የቀሩ ልጆች፤

አንድም አሥሩ ነገድ ተማር
ከው የቀሩ ሁለቱ ነገድ
በቍጥር ይሆናሉ፤

አንድም አሥሩ ነገድ ሁለቱ
ነገድ ተማርከው የቀሩ ትሩፋን
በቍጥር ይሆናሉ፤ የተቈጠረ
እንዳይጠፋ አይጠፉም፤

አንድም ከእንቢታ፤ ከክህደት
የቀሩ ምእመናን በቍጥር
ይሆናሉ፤ የተቈጠረ እንዳይ
ጠፋ አይጠፉም፤ ወይ ጽሕፎሙ
ሕፃን ወልደ እግዚአብሔር
ሐዋርያ ይጠብቃቸዋል፤

፳፣ ወውእተ አሚረ ይትዌሰኩ
እንከ እለ ተርፉ እምእስራኤል፣

ያንጊዜ ስልምናሶር ናቡከደነፆር
አንድም ሰናክሬም መጣ
ባሏቸው ጊዜ በባሕር ጠልቀው
በገደል ወድቀው የነበሩት ኋላ
በሚጠት ይጨመራሉ፤ (ጥቅስ)
ወይነግርዎሙ ደሰያት ሠናይቶ
ለእግዚአብሔር የሚላቸው፤
(ማር.ይስ. አን. ፳፬÷፩፤)

ወእለ ድኅኑ እምያዕቆብ፣

አሥሩ ነገድ ተማርከው የቀሩ
ሁለቱ ነገድ ይጨመራሉ፤
ኢይትአመንዎሙ፤ ማንሻ
አንድም አሥሩ ነገድ ሁለቱ
ነገድ ተማርከው የቀሩ ትሩፋን

ኢይትአመንዎሙ እንከ ለእለ
አስሐትዎሙ፣

ያሳቷቸው ነቢያተ ሐሰትን፤
ካህናተ ጣዖትን አያምኗቸ
ውም፣

ዳዕሙ ይትዌከሉ በእግዚአብሔር
ቅዱሰ እስራኤል በጽድቅ
ወበርትዕ፣

በእውነት ነገር፤ በቀና ነገር
በጽንዐ እስራኤል፣ በክብረ
እስራኤል በእግዚአብሔር
ያምናሉ እንጅ፤

፳፩፣ ወይጸንዑ በእግዚአብሔር
እለ ተርፉ እምያዕቆብ፣

አሥሩ ነገድ ተማርከው የቀሩ
ሁለቱ ነገድ፤ አንድም አሥሩ
ነገድ ሁለቱ ነገድ ተማርከው
የቀሩ ትሩፋን በእግዚአብሔር
አምነው ይጸናሉ፤

አንድም በአምልኮተ እግዚአ
ብሔር ይጸናሉ፤ ያጸንዑ ቢል
አምልኮተ እግዚአብሔርን
ያጸናሉ፣

፳፪፣ ወእመ ኮነ ኍልቆሙ
ለደቂቀ እስራኤል ከመ ኆፃ ባሕር
ዘኢይሰፈር፣

የእስራኤል ልጆች ቍጥራቸው
እንደማይሰፈር እንደ ባሕር
አሸዋ ምንም ቢበዛ፤

እለ ተርፉ ይድኅኑ፤

በአሸዋ ከመመሰል፤

አንድም ጣዖት ከማምለክ የቀሩ
ይድናሉ እንጅ ሁሉ አይድኑም፤

፳፫፣ እስመ ኅሉቀ ወምቱረ ነገረ
ይገብር እግዚአብሔር በኵሉ
ዓለም፣

የሰናክሬምን የብልጣሶርን
ጥፋት በውነት በዓለሙ ሁሉ
ያለቀ የተቈረጠ አድርጓልና፣
አንድም የአሕዛብን ጥፋት የእስ
ራኤልን ድኅነት አድርጓልና፤

አንድም ወእመ ኮነ ኍልቆሙ
ለደቂቀ እስራኤል ብለህ መልስ
የምእመናን ቍጥራቸው እንደ
ማይሰፈር እንደ ባሕር አሸዋ
ምንም ቢበዛ እለ ተርፉ፤
ከእንቢታ ከክህደት የቀሩት
ይድናሉ እንጂ ሁሉ አይድኑም፤
ሥጋዌን በእውነት አድርጓልና፤

፳፬፣ ወበእንተ ዝንቱ ከመዝ ይቤ
እግዚአብሔር አምላከ እስራኤል
ፀባዖት፣ ስለዚህ ነገር አሸናፊ
የሚሆን የእስራኤል ፈጣሪ
እግዚአ ብሔር እንዲህ አለ፤

ኢትፍርሁ ሕዝብየ እለ ትነብሩ
ውስተ ጽዮን እምፋርስ፣

በጽዮን የምትኖሩ ወገኖቼ
ከፋርስ ሰዎች የተነሣ አትፍሩ
በእውነቱ፤

አንድም ፍና ተሳልቆ ነው፤

www.ethiopianorthodox.org

እስመ በበትር ይዘብጡከ፣
ባኮርባጅ ይመቱኻልና፤
እስመ መቅሠፍትየ አመጽእ ላዕሌከ፣
መከራ የማመጣብህ ስለሆነ፣
ከመ ትርአይ ፍኖተ ግብፅ፣
ተማርከኽ ስትሄድ የግብፅን ጐዳና ታይ ዘንድ፤
አንድም እርዱን እያሉ ይልኩባ ቸዋልና፤
አንድም በግብፅ ትቀበለው የነበረውን መከራ ትቀበል ዘንድ ባንተ መቅሠፍት የማመጣ ስለሆነ አስቀድሞ መከራ ያመጡብኻልና ኢትፍርሁ ብለህ እሠር፤
፳፭፤እስመ ዓዲ ጎዳጠ ኢይቈርር መዓትየ ወመቅሠፍትየ፣
መዓቴ መቅሠፍቴ ዳግመኛ የማይመለስ ስለሆነ፣
አንድም ከለሰናክሬም መዓቴ ገና ጥቂት አይበርድምና ኢትፍርሁ ላለው ላዕለ ምክሮሙ፤
መዓት መቅሠፍት የማመጣ በእስራኤል ብቻ አይደለም፤ ቦኑ ግልፎ በሚሉ በለሰናክሬምም ነው እንጂ፤
፳፮፤ ወያመጽእ እግዚአብሔር መቅሠፍተ ዲቤሆሙ በከመ መቅሠፍተ ምድያም፣

እንደ ምድያም መቅሠፍት ያለ ሌላ መቅሠፍት ያመጣባቸዋል፣
በውስተ ብሔረ ሕማም፣
ም ድ ያ ም ያለውን ብሔረ ሕማም ብሎ ደገመው፤
አንድም ብሔረ ሕማም ያላት ፋርስ ናት፤
አንድም ጌዴዎን ምድያምን እንደወጋ መከራ በበዛባት ሀገር በለኪሶ መቅሠፍት ያመጣል፤ የሠራዊቱን ጥፋት መናገር ነው፤ አንድም መከራ በበዛባት ሀገር በ ነ ነ ቄ መቅሠፍት ያመጣል፤ የንጉሡን ጥፋት መናገር ነው፤
ወጎምዙሂ መንገለ ፍኖተ ባሕር፣
ጠሩ በባሕር አጠገብ ያሉትን ያጠፋል፤
አንድም ኤርትራ ይደርሳል፤
ወውስተ ፍኖት ዘመንገለ ግብፅ፣
ወደ ግብፅ እስከሚወስደው ጐዳና ይደርሳል፤
፳፯፤ ወውእተ አሚረ ይሠዐር አርዑቱ እመትከፍትከ ወበትሩ እምክሣድከ፣
ያንጊዜ የሰናክሬም አገዛዙ፤ ሥልጣኑም ካንተ ይጠፋል፤ ይርቅልኻል፤

፳፰፤ እስመ ይመጽእ ላዕለ ሀገረ ጋይ፣
ወደ ጋይ ይመጣልና፤
ወየኀልፍ እንተ መጌዶን፤
በመጌዶንም በኩል ያልፋልና፤
ወደነብር ንዋዮ ውስተ ምክማስ፣
ም ክ ማ ስ ጽኑ አምባ ነው፤ ገንዘቡን በአምባ ያኖራልና፤
አ ን ድ ም ስ መ ሀ ገር ነው፤ ገንዘቡን ምክማስ በሚባል ሀገር ያኖራልና፤
ወየሐልፍ ቈላ፣
ወደበረሐ ይሄዳል፤
፳፱፤ ወበጺሖ ጋይ ይፈርሁ ሬማ፣
ጋይ በደረሰ ጊዜ የሬማ ሰዎች ይፈራሉ ማለት አይደለም፤ ጋይም ሬማም በደረሰ ጊዜ የ ጋ ይ ም የ ሬ ማ ም ሰዎች ይፈራሉ ሲል ነው፤ አንድም ይፈራሉና፤
ወገባያን ሀገረ ሳኦል፣
የሳኦል አገር ገባያንም ትፈራ ለች፤ ሀገረ ሳኦል ባለው ሀገረ ሳሙኤል ይላል፤
ወትጐይይ ወለተ ጋላን፣
ያለቃው ልጅ ትሸሻለች፤ አው ጋላተ ሜመነ እ ን ዲ ል አንድም ስመ ነገድ ነው፤
አንድም ስመ ሀገር ነው፤
፴፣ ወይሰማዕ በኤንሶን ወበአናቶት፣
ሰናክሬም መጣ መጣ ሲባል በኤንሶን በአናቶት ይሰማል፤
አንድም ይሰማልና፤
፴፩፣ወይደነግፁ መዴቤና፣
የመዴቤናም ሰዎች ይደነግጣሉ፤ አንድም ይደነግጣሉና፤
ወእለ ይነብሩ ጋቤር፣
በጋቤር የሚኖሩ ሰዎችም ይደነግጣሉ፤ አንድም ይደነግጣሉና መዴቤና በደረሰ ጊዜ የጋቤር ሰዎች ይደነግጣሉ ማለት አይደለም፤ መዴቤናም ጋቤርም በደረሰ ጊዜ በመዴቤ ናም በጋቤርም ያሉ ሰዎች ይደነግጣሉ ሲል ነው፤
፴፪፣ ወያስተበቍዑ በእንተ ፍኖቱ ከመ የሀልዉ በእዴሁ፣
በእጁ ጭብጥ፤ በእግሩ እርግጥ ብለው ይኖሩ ዘንድ በጤና አሳልፈው እያሉ ይለምናሉ፤ እንዲህ እንዲህ ያደርጋልና እን ዲህ እንዲህ ያደረገ ሰናክሬም ይሠዐር አ ር ዑ ቱ እመትከፍ ትከ፣ አ ገ ዛ ዙ ከ አ ን ተ ይጠ ፋል፤
አጽንዕዋ ለደብረ ወለተ ጽዮን ማንሻ፤ አንድም እንዲህ እንዲህ ያደረገ ሰናክሬም ይጠፋልና፤ ይጠፋል፤ ብላችሁ ነግራችሁ ፣

www.ethiopianorthodox.org

አጽንዕዋ ለደብረ ወለተ ጽዮን፤ የጽዮንን ልጅ አጸናኗት ማለት አይዞሽ አይዞሽ በሏት፤

ወለአውግረ ኢየሩሳሌም፤

የኢየሩሳሌምን አውራጃ አጸናኗት ማለት አይዞሽ አይዞሽ በሏት፤

፴፫፤ ናሁ እግዚአብሔር ፀባኦት የሀውኮሙ ለክቡራን በኃይል፤

እነሆ አሸናፊ እግዚአብሔር እነሰናክሬምን በኃይል ያውካቸዋል፤

ወይቀጠቅጦሙ ለዐበይት በጎሳር፤

መኳንንቱን ያጠፋቸዋል፤

ወዮኀስሩ ዐበይት፤

መኳንንቱ ይዋረዳሉ፤

፴፬፤ ወይወድቁ በመጥባሕት፤

በጦር ይጠፋሉ፤

አንድም በሰይፈ መልአክ ይወድቃሉ፤

ወይወድቅ ሊባኖስ ምስለ ነዋኃት አርዝ፤

ሰናክሬም ከሠራዊቱ ጋር ይጠፋል፤

አንድም ናሁ እግዚአብሔር ብለህ መልስ፤ እነሆ አሸናፊ እግዚአብሔር ሊቃኑ አጋንንትን ያውካቸዋል ማለት በኃይል ያሸብራቸዋል፤ ወይቀጠቅጦሙ፤ አጋንንትን ያጠፋቸዋል፤ ወዮኀሥሩ፤ አጋንንት ይዋረዳሉ፤ ወይወድቁ በመስቀል ድል ይነሣሉ፤ ወይወድቅ፤ ዲያብሎስ፤ ከሠራዊቱ ጋራ ድል ይነሣል፤

ገባዔ

ምዕራፍ ፲፩

፩፤ ወትወፅእ በትር እምሥርወ እሴይ፤

ከነገደ እሴይ ሕዝቅያስ ዘሩባቤል ይወለዳል፤

ወየዐርግ ጽጌ እምኔሃ፤

ከሕዝቅያስ ከዘሩባቤል ምግባር ሃይማኖት ይገኛል፤

፪፤ ወየአርፍ ዲቤሁ መንፈሰ እግዚአብሔር፤

በሕዝቅያስ በዘሩባቤል መንፈስ ቅዱስ ያድርበታል፤

መንፈሰ ጥበብ ወአእምሮ፤

ጥበብ፤ ዕውቀት የሚገልጥለት፤

መንፈሰ ኃይል፤

ኃይል የሚያደርግለት፤

ወምክር፤

ምክር የሚገልጥለት፤

መንፈሰ ልቡና ወጽድቅ፤

ልብ የሚያስደርገው ምግባር ትሩፋት የሚያሠራው መንፈስ ቅዱስ ያድርበታል፤

፫፤ ወይመልዕ ላዕሌሁ መንፈሰ ፍርሃተ እግዚአብሔር፤

እግዚአብሔርን የሚያስፈራ መንፈስ ቅዱስ በሕዝቅያስ፤ በዘሩባቤል ያድርበታል፤ አንድም ወትወፅእ በትር ብለህ መልስ፤ ከነገደ እሴይ በትረ ሕይወት እመቤታችን ትወለዳለች፤ ወየዓርግ ጽጌ፤ ጽጌ ክርስቶስ ከእመቤታችን ይወለዳል፤ አንድም ወትወጽእ ከነገደ እሴይ ከተወለደች ከእመቤታችን ጌታ ይወለዳል፤ ወየዓርግ፤ ከጌታ ክብር ልጅነት ይገኛል፤ ወየአርፍ ዲቤሁ መንፈሰ እግዚአብሔር፤ መንፈስ ቅዱስ በአምሳለ ርግብ ወርዶ በራሱ ላይ ይቀመጣል፤ መንፈሰ ጥበብ ወአእምሮ፤ ለሌላው ጥበብ ዕውቀት የሚገልጥበት መንፈሰ ኃይል ወምክር፤ ለሌላው ኃይል የሚያደርግበት፤ ለሌላው ምክር የሚገልጥበት መንፈሰ ልቡና ወጽድቅ፤ ለሌላው ዕውቀት የሚገልጥበት፤ ምግባር ትሩፋት እንዲሠራ የሚያደርግበት፤ ወይመልዕ ላዕሌሁ መንፈሰ ፍርሃተ እግዚአብሔር፤ እግዚአብሔር ነቱን የሚያስፈራ መንፈስ ቅዱስ በአምሳለ ርግብ ወርዶ በራሱ ላይ ይቀመጣል፤ (በህልውናው ይኖራል ብትልም ይሆናል) በኢሳይያስ የሚቈጥራቸው ሰባቱ ሀብታት እሊህ ናቸው፤ እሊህ ብቻ ሁነው አይደለም፤ በፍጹም ቈጥሮ እንዲህ አለ፤ (ጥቅስ) እስመ ኀልቈ ፯ቱ ፍጹም ውእቱ በጎበ ዕብራውያን እንዲል፤ (ሃይ. አበ. ሳዊ.)

ወኢያደሉ በውስተ ፍትሕ፤

ሕዝቅያስ ዘሩባቤል በፍርድ ጊዜ አያደላም፤

ወኢይትዋሣእ በነገር እኩይ፤

ሕዝቅያስ ዘሩባቤል በሐሰት ነገር አይከራከርም፤

ዳዕሙ በየዋህ ኮነኔ ይኬንን፤

ሕዝቅያስ ዘሩባቤል በውነት ይፈርዳል እንጂ ፤

፬፤ ወይዛለፎሙ ለክቡራነ ምድር፤

ክቡራንን ብትገብሩ ገብሩ፤ ብትቀቅሉ ቀቅሉ ያለዚያ እወጋችኋለሁ እያለ ይዘልፋቸዋል፤

ወይቀሥፋ ለምድር በቃለ አፉሁ፤

ሕዝቅያስ ዘሩባቤል ከቃሉ በወጣ ነገር ሽፋጭን ለዋጮን ያጠፋል፤

www.ethiopianorthodox.org

ወበመንፈሰ ከናፍሪሁ ያጠፍኦ ለኃጥኣ፤

ሕዝቅያስ ዘሩባቤል ከቃሉ በወጣ ፍርድ ሌባ ቀማኛን ያጠፋል፤

፭፤ ወይቀንት ጽድቀ ውስተ ሐቌሁ፤

ይቀንት ጽድቀ ግሥ ነው፤ እውነት ፍርድ ይፈርዳል፤

ወይትዐፀፍ ርትዐ ውስተ ገቦሁ፤

ይትዐፀፍ ርትዐ ግሥ ነው፤ ሕዝቅያስ ዘሩባቤል የቀና ፍርድ ይፈርዳል፤ አንድም ወኢያደሉ በውስተ ፍትሕ ብለህ መልስ፤ ጌታ በፍርድ ጊዜ አያደላም ተጎድገ ለከ ኃጢአትከ፤ ተኃድገ ለኪ ኃጢአትኪ ፈቀድኩ ንጻሕ፤ ይላል ወኢይትዋሣዕ፤ ጌታ በሥጋዊ ነገር አይከራከርም፤ ዳዕሙ በየዋህ ቡነዳጌ በቀልነት ይፈርዳል እንጂ፤ ወይዛለፎሙ ለክቡራን ምድር፤ ጸሐፍት ፈሪሳውያንን አሌ ለክሙ ጸሐፍት ፈሪሳውያን መደልዋን እለ ትበልዑ አብያተ መበለታት ወዕንለ ማውታ እያለ ይዘልፋ ቸዋል፤ ወይቀሥፋ ጌታ ኃጥአመና ፍቅን ያጠፋል፤ ወበመን ፈሰ ከናፍሪሁ ያጠፍኦ ለኃጥእ ጌታ በሥልጣኑ ኃጥእ ዲያብሎስን ያጠፋዋል፤ ወይቀንት

በሚጠት ከእስራኤል ጋራ አንድ ይሆናሉ ፤ አንድም በ ዘመነ ሐዲስ ምእመናነ አሕዛብ ከምእመናነ እስራኤል ጋራ አንድ ይሆናሉ፤ ወይት ረዐዩ አልህምት፤ በሚጠት እስራኤል ከአሕዛብ ጋራ አንድ ይሆናሉ፤

አንድም በዘመነ ሐዲስ ምዕመናነ እስራኤል ከምዕመ ናነ አሕዛብ ጋራ አንድ ይሆናሉ፤

ወይነድያሙ ሕፃን ንዑስ ሕዝቅያስ ዘሩባቤል ይጠ ብቁዋቸዋል፤ አንድም ጌታ ሐዋርያት ምእመናንን ይጠ ብቁዋቸዋል፤

ወይትሐፀኑዕጓላቲሆሙ ኀቡረ፤ ልጆቻቸውም አሪትን ወንጌልን እየተማሩ ባንድነት ያድጋሉ፤

ወይቀምሕ አንበሳ ኃሠረ፤ ከመ ላህም ፤

በሕዝቅያስ በዘሩባቤል ዘመን አረማዊ ሕገ ትሕትና አሪትን ይማራል፤ አንድም በዘመነ ሥጋዌ አይሁዳዊ ሕገ ትሕትና ወንጌልን ይማራል፤

፰፤ወይወዲ እዴሁ ሕፃን ንዑስ ውስተ ግበ አርዌ ምድር፤

ትንሽ ልጅ እጁን ወደ እባብ ጕድጓድ ይሰዳል፤

ወአልቦ ዘይነክዮ፤

ምንም ምን የሚነካው የለም፤

፱፤ ወኢይከል አሕስሞ ላዕሌሁ፤

በሱ ላይ ክፉ ነገር ማድረግ የሚቻለው የለም፤

ወኢላዕለ መኑሂ በደብረ መቅደስየ፤

ማንም ማን በኢየሩሳሌም ክፉ ነገር ማድረግ የሚቻለው የለም፤

እስመ መልዐ ላዕለ ኵሉ አእምሮ እግዚአብሔር ከመ ማይ ብዙኅ ዘይደፍን ባሕረ፤

ብዙ ውሀ በጐድጓድ እንዲመላ ዕውቀት በሰው ሁሉ ልቡና መልቷልና፤ አንድም ወይወዲ ብለህ መልስ፤ ሕዝቅያስ ዘሩባቤል ቃሉን ወደ አሕዛብ ከተማ ይሰዳል፤ ብትገብሩ ገብሩ፤ ብትቀቅሉ ቀቅሉ ያለዚያ እወጋችኋለሁ እያለ፤

ወአልቦ ዘይነክዮ፤ ከአሕዛብ ምንም ምን የሚነካው የለም፤

ወኢይከል አሕስሞ ላዕሌሁ፤ በሕዝቅያስ በዘሩባቤል ክፉ ነገር ማድረግ የሚቻለው የለም አለ፤ እስከ ጊዜው ድረስ፤ አንድም ወይወዲ እዴሁ ሕፃን ንዑስ ውስተ ግበ አርዌ ምድር፤ ልጁን ወደዚህ ዓለም ይልካል፤ አንድም ሕፃን ጌታ ቃሉን

www.ethiopianorthodox.org

ወደ አሕዛብ ከተማ ይሰዳል ማለት የአሕዛብን ከተማ ያስ ተምራል፤ አንድም እለ ውስተ ሲኦል ዓኡ ወ እ ለ ው ስ ተ ጽልመት ተከሠቱ፤ ብሎ ቃሉን ወደሲኦል ይሰዳል፤ አንድም እጁን በእውነት ወደሲኦል ይሰዳል፤ (ጥቅስ) አርአዮመ· የማነ እዴሁ ወ ኮ ነ ቶ መ· ጥምቀተ፡ እ ን ዲ ል መ.ኪ፡ ክፍ.፪፤

ወአልቦ ዘይነክዮ፤ ከአጋንንት የሚቄራኘው የለም፤ አንድም ሐዋርያ የ አ ሕ ዛ ብ ን ከተማ ያስተምራል፤ የሚነካው የለም፤ እስከ ጊዜው ድረስ ማንም ማን ክፉ ነገር በሱ ላይ ማድረግ የሚቻለው የለም፤

በምእመናንም ላይ ማንም ማን ክፉ ነገር ማድረግ የሚቻለው የለም፤

እስመ መልዐ በዘመነ ሐዲስ ዕውቀት በሰው ሁሉ ልቡና መልኧልና፤

፲፤ ወይቀውም ውእተ አሚረ ሥርወ እሴይ፤

ከነገደ እሴይ የ ተ ወ ለ ደ ሕዝቅያስ ዘሩባቤል ያንጊዜ ይነግሣል፤ አንድም ነገደ እሴይ ዘመናይ ይሆናል፤

ወዘተወይመ እ ም ኄ ሁ ይከውን መልአከ አሕዛብ፤

ከነገደ እ ሴ ይ ተ ወ ለ ደ የተሾመ ሕዝቅያስ ዘሩባቤል የ አ ሕ ዛ ብ አለቃ ይሆናል፤ አንድም ወ ይ ቀ ው ም ይእተ አሚረ ሥርወ እሴይ፤ ከነገደ እሴይ ከተወለደች ከእመቤታችን የተወለደ ጌታ ያንጊዜ ይነግሣል፤ አ ን ድ ም ከነገደ እሴይ የተወለደ ምእመን ጽንዐ ነፍስን አ ግ ኝ ቶ ይጸናል፤ ወዘተወይመ እምኄሁ ይከውን መ ል አ ከ አ ሕ ዛ ብ ከአብ የተሾመ፤ አ ን ድ ም ከራሱ የ ተ ሾ መ ጌታ የአሕዛብ መምህር ይሆናል፤

ወይትዌከሉ ቦቱ አሕዛብ፤

አሕዛብ በሱ ያምናሉ፤

ወከውን ምዕራፈ ዘዚአሁ ክብር፤

ከሱ የተገኘ ክብር የሕዝቡ የአሕዛቡ ማረፊያ መሳፈሪያ ይሆናል፤

፲፩፤ ወውእተ አሚረ ይደግም እግዚአብሔር አርአዮ እዴሁ፤

ዳግመኛ እግዚአብሔር ሥልጣኑን ይገልጣል፤ የብልጣሶርን ለሰናክሬም ይደግም አለ፤

ከመ ይቅናዕ ተረፈ ለእለ ተርፉ እምአሕዛብ፤

ከአሕዛብ ለቀሩ ለእስራኤል ይቀና ዘንድ እነዚያ ራርተው

ትተዋቸው ማለት አይደለም፤ አምልጠው ለቀሩ፤ አንድም በሥላሴ ቸርነት ለቀሩ፤

ዘአትረፉ ፋርስ ወግብፅ ወባቢሎን፤

ከፋርስ ከግብፅ ከባቢሎን ለቀሩ፤

ወኢትዮጵያ ወኤላሜጤን፤

ከ ኢ ት ዮ ጵ ያ ከኤላሜጤን ለቀሩ፤

ወእምሥራቀ ፀሐይ ወእምዕራብ፤

ከምሥራቅ ከምዕራብ ለቀሩ፤

፲፪፤ ወያርኢ ትእምርተ ለአሕዛብ፤

ለእስራኤል ሞተ ብልጣሶርን ያደርግላቸዋል፤

ወያስተጋብዖሙ ለእለ ተርፉ እም እስራኤል ወለእለ ተዘርዉ ውስተ ይሁዳ፤

ያስተጋብያሙ ውስተ ይሁዳ፤ ለእለ ተዘርዉ ውስተ ይሁዳ ነገደ ይሁዳ ብለህ ግጠም፤ አሥሩ ነገድ ሁለቱ ነገድ ተማርከው የቀሩ ትሩፋንን በይሁዳ ይሰበስባቸዋል፤ አን ድም ከሀገሪቱ የተበተኑትን፤

አንድም ከነገደ ይሁዳ ተወል ደው የተበተኑትን ይሰበስባ ቸዋል፤

ወያስተጋብዖሙ እምዐርባዕቱ አጽ ናፈ ምድር፤

ከአራቱ ማዕዘን ይሰበስባቸዋል፤ አንድም ከፋርስ፤ ከባቢሎን ከዕርዕ ከሚዶን ይሰበስባቸዋል፤

፲፫፤ ወይሠዐር ቅናተ ኤፍሬም፤

አሥሩ ነገድ በሁለቱ ነገድ የሚቀናው ቅናት ይጠፋል፤

ወይጠፍኡ ፀረ ይሁዳ፤

የሁለቱ ነገድ ጠላት አሥሩ ነገድ ይ ጠ ፋ ሉ ፤ አንድም የሁለቱ ነገድ ጠላትነት ይጠ ፋል፤

ወኢይቀንዕ ኤፍሬም በይሁዳ፤ ወይሁዳ ኢየሐምም በኤፍሬም፤

አሥሩ ነገድ በሁለቱ ነገድ አይቀናም ሁ ለ ቱ ም ነገድ በአሥሩ ነገድ አይቀናም፤

፲፬፤ ወይሠርሩ በመትከፈ ኢሎፍሊ፤

በኢሎፍላው ያን ትክሻ ይወረወ ራሉ ማለት ይሠለጥኑባቸዋል፤

ወያቀድሙ አውርዶ እዴሆሙ ዲበ ኤዶምያስ ወዲበ አሞን፤

ሊላውን አገር ሳይወጉ አስቀድ መው አ ሞ ን ን ኤዶምያስን ይወጋሉ፤ አ ን ድ ም እነዚያ ሳይወጓቸው አ ስ ቀ ድ መ ው እነዚህ ይወጓቸዋል፤ አንድም ጎረቤቶቻቸው ናቸውና በሩቅ ያሉ አ ሕ ዛ ብ ን ከመው ጋታቸው አስቀድሞ የኤዶም ያስን ሰዎች ይወጋሉ፤

፲፭፤ ወያነዕፋ እግዚአብሔር ለልሳነ ባሕረ ግብፅ፤

ልሳነ ባሕረ ግብፅ ጥቅል ስመ ሀገር ነው፤ እግዚአብሔር ልሳነ

www.ethiopianorthodox.org

ባሕረ ግብፅን ያጠፋታል፤ አንድም ልሳን ምንጭ የግብፅ ባሕር ምንጭን ያደርቃታል፤

አንድም ልሳን ንጉሥ ነው፤ የግብፅን ከተማ ንጉሥ ያጠፋዋል፤ አኂድም ለባሕረ ልሳነ ግብፅ ቢል፤ የግብፅን ንጉሥ ከተማ ያጠፋል፤

ወይቀሥፍ ፯ተ አፍላጋተ፣

ሰባት ውሀ ይከፍልላቸዋል፤ ከባቢሎን ሲወጡ ሰባት ውሀ ተከፍሎላቸዋልና፤

ከመ ይሑርዎን በአሣዕን፣

በጫማ ይሄዱባቸው ዘንድ፤

፲፮፣ ወይከውኖሙ መጽያሕተ ለሕዝብየ እለ ተርፉ እምፋርስ፣

ከፋርስ ለቀሩ ለወገኖቼ ጥርጊያ ጎዳና ይኾናቸዋል፤

ወይከውኖሙ ለእስራኤል ከመ አመ ወፅኡ እምግብፅ፣

ለእስራኤል ከግብፅ እንደወጡ ጊዜ ይደረግላቸዋል አለ ፤ ኤርትራ እንደተከፈለችላቸው ሰባት አፍላጋት ተከፍለውላቸዋልና፣

አንድም ወይቀሥፍ ፯ተ አፍላጋተ ብለህ መልስ፤ ሰባት አህጉር ይወጋላቸዋል፤ ከመ ይሑርዎን በአሣዕን፤ በጫማ ይሄዱባቸው ዘንድ፤ አንድም ጠላት ጠፍቶላቸው ተዘልለው ይሄዱባቸው ዘንድ፤ አንድም ጫማ እንዲረገጥ አህጉርን ይረግጧቸው ዘንድ፤ ሰባት አህጉር የተባሉ ፋርስ ባቢሎን ግብፅ፤ ኢሎፍሊ፤ ኤዶምያስ፤ ሞአብ አሞን ናቸው፤ ወይከ ውኖሙ መጽያሕተ፤ ጥርጊያ ጎዳና ይኾናቸዋል፤ ወይከ ውኖሙ ለእስራኤል ከመ አመ ወፅኡ እም ግብፅ፤ ከግብፅ እንደ ወጡ ጊዜ ይደረግላቸዋል አለ፤ ዓ ግ ሴ ዎ ን እንደጠፉ ላቸው ጎግ ማጎግን አጥፍተው ወጥተዋልና::

ምዕራፍ ፲፱

፩፣ ወትብል ይእተ አሚረ አአኮተከ እግዚአ፣

አቤቱ ያንጊዜ አመሰግንኻለሁ ትላለህ፤

እስመ ተማዕከኒ ወቀሠፍከኒ፣

ፈርደኽብኛልና፤ በመከራም ገርፈኸኛልና ይኸንን አይኻውም፤ ወካዕበ ተሠሀልከኒ፤ ዳመኛ ይቅር ብለኸኛልና አመሰግንኻለሁ፤

፪፣ ወትብል ናሁ አምላኪየ ወመድኃንየ፣

እነሆ ፈጣሪዬ መድኃኒቴ እሱ ነው ትላለህ፤

ወእትዌከል ቦቱ ወአሐዩ ቦቱ፣

በሱ አምኜ በሕይወት እኖራለሁ፤

ወኢይፈርህ እስመ እግዚአብሔር ክብርየ ወትርሚትየ፣

ሽልማቴ ክብሬ እግዚአብሔር ነውና መከራ ያገኘኛል ብዬ አልፈራም፤

ወውእቱ ኮነኒ መድኃንየ፣

እርሱ መድኃኒት ሆነኝ፤

፫፣ወትቀድሕ ማየ በትፍሥሕት እምአዘቅተ ሕይወት፣

ሰባ ዘመን ድርቅ ሁኖ ለግፈው ወንዶች ይሻላሉ ፤ እያሉ ይሰዷቸዋል፤ (ጥቅስ) ወአሥጡ ቀሳውቲሆሙ ዕራቆ እንዲል፤ ኤር.፲፫÷፫፤ ባዶአቸውን ይመለሱ ነበር፤

በሰባ ዘመን ዝናም ዘንሞላቸዋልና ደስ እያለህ ከአዘቅቱ ውሀውን ትቀዳለህ፤ አንድም ከነቢያት ከካህናት ትምህርት ረድኤት ታገኛለህ፤ አንድም የሕይወት መገኛ ከሚሆን ከጌታ ጐን በፈሰሰ ውሀ ተጠምቀህ ክብርልጅነትን ታገኛለህ፤

፬፣ ወትብል ይእተ አሚረ ሰብሕዎ ለእግዚአብሔር ወፀውዑ ስሞ፣

ያንጊዜ እግዚአብሔርን አመስግኑት ስሙንም ጥሩት ትላለህ፤

ወንግርዎሙ ለአሕዛብ ስብሐቲሁ፣

ጌትነቱን ለአሕዛብ ንገሯቸው፤

ወተዘከሩ ከመ ተለዐለ ስሙ፣

ስሙ ከፍ ከፍ እንዳለ አስቡ፤

፭፣ ሰብሑ ለስመ እግዚአብሔር፣

ለእግዚአብሔር ስም ምስጋና አቅርቡ፤

እስመ ገብረ ዓቢያተ ኮሎ፣

ድንቅ ድንቅ ሥራ ሠርቷልና፤

ንግሩ ዘንተ ለኵሉ ምድር፣

ይህን ለዓለሙ ሁሉ ንገሩ፤

፮፣ተፈሥሒ ወተጎሢዪ ወለተ ጽዮን፣

የጽዮን ልጅ ቤተ እስራኤል ፈጽሞ ደስ ይበልሽ፤

እስመ ተለዐለ በማዕከሌኪ ቅዱሰ እስራኤል፣

ጽንዐ እስራኤል ክብረ እስራኤል እግዚአብሔር በመካከልሽ ከፍ ከፍ ብሏልና ማለት በመካከልሽ ልዕልናውን ገልጧልና፤ አንድም ተፈሥሒ፤ የጽዮን ልጅ ምእመን ደስ ይበልሽ፤ አንድም ሕግ የምትጠብቂ ምእመን ደስ ይበልሽ፣ ወለተ ሕግ ብሎ ነው፤ እስመ ተለዐለ፣ እግዚአብሔር በመካከልሽ ተሰቅሏልና ጎንብርታ ወአክሊላ ለምድር ይላታልና::

www.ethiopianorthodox.org

ላች ዕለተ እግዚአብሔር ዜዋዌ ትመጣለችና፤ አንድም እንተ ምልዕት መቅሠፍተ መዓቱ ቢል፤ ባቢሎንን ታጠፋ ዘንድ መዓቱን የሚፈጽምበት መቅሠፍቱን የተመላች እግዚአብሔር የባቢሎንን ሰዎች የሚያጠፋባት ቀን እነሆ ትመጣለችና፤

ወተነልቆሙ ለብዙኃን እለ ይነብሩ ውስቴታ፣

በሷ ውስጥ የሚኖሩ ብዙ ሰዎችንም ታጠፋለች፤ አንድም ታጠፋለችና፤

፲፣ ወኢይበርሁ እንከ ከዋክብተ ሰማይ፣

እንግዲህ ወዲህ ከዋክብት አያበሩም፤ አንድም ሠራዊቱ መኪንንቱ ተድላ ደስታ አያደርጉም፤ አንድም አያደርጉምና፤

ወእለ አርዮብ፣

እለሥስቶ እለ ስድስቶ እለ ሰብዓቶ አያበሩም፤ አንድም ወጌቱ መማክርቲሁ ለንጉሥ የሚላቸው ተድላ ደስታ አያደርጉም፤ አንድም አያደርጉምና፤

ወኮሉ ዓለመ ሰማይ፣

የባቢሎን ሰው ሁሉ ይጠፋል አንድም ይጠፋልና፤

ወወሐይኒ ሠረቆ ይጸልም፤

፱ሐይ ታይቶ ይጠፋል፤ አንድም ንጉሡ ተድላ ደስታ አያደርግም፤ አንድም ንጉሡ ታይቶ ይጠፋል፤

ወወርኀኒ ኢትሁብ ብርሃና፣

ጨረቃ አታበራም፤ አንድም ቢትወደዱ ተድላ ደስታ አያደርግም፤ አንድም አያደርግምና፤ ወይትቀጸው ብለሀ ዕሠር፤

፲፭፣ ወእኤዝዝ እንከ እኪተ ላዕለ ኵሉ ዓለም፣

በባቢሎን መከራውን አዝዛለሁ፤

ወላዕለ ኵሉ ኃጥአን፣

በባቢሎን ሰዎችም ላይ መከራ አመጣለሁ፤

ወእሥዕር ጌጋዮሙ ወትዝኀርቶሙ ለዕቡያን፣

የትቢተኞችን ሰዎች በደላቸውን ትቢታቸውን በሞት አጠፋለሁ፤

፲፪፣ ሰማይኒ ያንቀለቅል እመሠረቱ በእንተ መቅሠፍቱ ለእግዚአብሔር አመ ይመጽእ በቍጥዓ፣

በመዓት በመጣ ጊዜ የእግዚአብሔር መቅሠፍቱ ስለመጣ የባቢሎን ሥር መሠረቷ ይጠፋል፤ ሰማይ አላት ስለ ልዕልናዋ፤

፲፫፣ ወእለ ተርፉ ይትበደሩ እምወርቅ ወእምብሩር፣

ከሞት የቀሩ እስራኤል ከወርቅ ከብር ይመረጣሉ፤ ወርቅ ብር ኪማርኩ (ከሚማርኩ) ሰዎችን ቢማርኩ ይወዳሉና፤

ወናሁ አነሥአሙ ለፋርስ እለ ኢይፈቅድዎ ለወርቅ ወኢይሔልይዎ፤ ለብሩር ብሎ እንዲ ያመጣው፤

ወይትበደር ሰብእ እምዕንቈ ሰንፔር፣

ሰውሰንፔር ከሚባል ዕንቍ ይወደዳል፤

በዕለተ ተሠሃሎሙ እግዚአብሔር፣

እግዚአብሔር ባጠፋቸው ቀን፤ (ጥቅስ) ለዘሂ መሐርክዎ እምሕሮ ወለዘሂ ተሠሃልክዎ እሠሃሎ፤ እንዲል ሮሚ.፱÷፲፭፤

፲፱፣ ወይከውኑ እለ ተርፉ ከመ ወይጠል ዘአምስጠ፣

ከሞት የቀሩት ከአዳኝ እንዳ መለጠ ፌቆ ይሆናሉ፤ ያ እንዳይገኝ አይገኙም፤

ወከመ በግዕ ዘተነጥአ፣

እንደ በረረ በግ ይሆናሉ፤ ያ እንዳይገኝ አይገኙም በግ ከበረረ የሰው ልጅ ካመረረ እንዲሉ፤ ያ በዱር በገደል እየተዳፋ እንዲሄድ የባቢሎንም ሰዎች እንደዚያ ይሆናሉ፤

አንድም ያ ፈጥኖ እንዲሸሽ ትሩፋንም ፈጥነው ይወጣሉ፤

ወአልቦ ዘያገብኦ ለሰብእ ውስተ ሕዝቡ፣

ሰውን ባለህ ቁም ብሎ የሚመልሰው የለም፤

ወአልቦ ዘይመይጦ፣

የሚመልሰው የለም፤

ወይትመየጥ ሰብእ ከመ ይእቱ ብሔሮ፣

የባቢሎን ሰው ወደሀገሩ ይገባ ዘንድ ይመለሳል፤ አንድም ወእለ ተርፉ ይትበደሩ እምወርቅ ወእምብሩር፤ አባቶች አልቀው የቀሩ ልጆች ፤ አንድም አሥሩ ነገድ ሁለቱ ነገድ ተማርከው የቀሩ ትሩፋን ከወርቅ ከብር ይወደዳሉ፤ ወይትበደር ሰንፔር ከሚባል ዕንቍም ይመረጣሉ፤ በዕለተ ተሠሃሎሙ እግዚአብሔር፤ ይቅር ባላቸው ቀን ወይከውኑ አሥሩ ነገድ፤ ተማርከው የቀሩ ሁለቱ ነገድ፤ አንድም አሥሩ ነገድ ሁለቱ ነገድ ተማርከው የቀሩ ትሩፋን ከአዳኝ እንዳመለጠ ፌቆ ይሆናሉ፤ ያ እንዳይገኝ አይገኙም፤ ወከመ በግዕ፤ እንደ በረረ በግ ይሆናሉ፤ ያ እንዳይገኝ አይገኙም፤ ወአልቦ

www.ethiopianorthodox.org

አንተ የአባቴ ባርያ አይደ
ለህምን፤ አንተ የ ወ ን ድ ሜ
ባርያ አይደለህምን ብሎ የሚመ
ልሳቸው የለም፤ ወይትመየጥ፤
ትሩፍ ወደሀገሩ ወደ ኢየሩ
ሳሌም ይገባ ዘንድ ይመለሳል፤

አንድም ወእለ ተርፉ፤ ከእንቢታ
ከክህደት የቀሩ ምእመናን
ከወርቅ ከብር ይመረጣሉ፤

ወይትበደሩ ሰንፔር ከሚባል
ዕንቊ ይመረጣሉ ፤ በዕለተ
ተሠሃሎሙ፤ እግዚአብሔር
በሞተላቸው ቀን፤ (ጥቅስ)
እስመ ይኄይስ እምሐዲው
ሣህልከ እንዲል፤ መዝ.፷፱፤

ወይወከውኑ፣ ከእንቢታ፣ ከክህ
ደት፤ የቀሩ ምእመናን ከአዳኝ
እንዳመለጠ ፈቆ ይሆናሉ፤ ያ
እንዳይገኝ አይገኙም ወከመ፤
በግዕ፤ እንደ በረረ በግ ይሆናሉ፤
ያ እ ን ዳ ይ ገ ኝ አይገኙም፤
ወአልቦ፤ አንተ የዲያብሎስ
ባርያ አይደለህምን አ ን ቺ
የዲያብሎስ ባርያ አይደለሽምን
ብሎ የሚመ ልሳቸው የለም፤
ወይትመየጥ፤ ምእመን፣ ወደ
ሀገሩ ወደገነት ወደመንግሥተ
ሰማያት ይገባ ዘንድ ይመለሳል፤

፲፩፣ወእለሂ ተዘርዉ ይመውቱ፣

የተበተኑት ባሕር ጠልቀው፣
ገደል ወድቀው ይሞታሉ፣

ወእለሂ ተጋብዑ ይወድቁ በኲናት
የተሰበሰቡትም በጦር ይጠፋሉ፤
፲፪፣ ወይነጽሑ ውሉዶሙ፣

ልጆቻቸውን ቂሮስ ዳርዮስ
እየወጉ ይጥሏቸዋል፤

ወይበረብሩ አብያቲሆሙ በቅድሜ
ሆሙ፣

ቤታቸውን በፊታቸው ይበዘብ
ዙታል፤

ወይስሕቡ አንስቲያሆሙ፣

ሚስቶቻቸውን ያለፈቃዳቸው
እየሳቡ ይደርሱባቸዋል፤

፲፫፣ ወናሁ አነሥእሙ ላዕሌክሙ፣
ለፋርስ እለ ኢይፈቅድዎ ለወርቅ
ወኢይሔልይዎ ለብሩር፣

ብርን የማይሹ ወርቅን የማይ
ወዱ የፋርስን ሰዎች በእናንተ
ላይ አስነሣለሁ፤

፲፮፣ እለ ይቀጠቅጡ ወየሐስዩ
ነፍሰ ወሬዛ፣

የጐልማሳውን ሰውነት የሚያ
ጠፉ የፋርስን ሰዎች አስነሣለሁ፤
አንድም እለ ይቀጠቅጡ ወየሐ
ስዩ ነፍሰ ወሬዛ የጐልማሳውን
ሰውነት ያጠፋሉ እንጂ ወርቅ
ብር የማይሹ፤

ወኢይምሕሩ ሕፃናተ፣

ለሕፃናቱ አይራሩም፤

ወኢይምሕኩ አዕይንቲሆሙ ለውሉ
ድከሙ፣

ዓይኖቻቸው ለልጆቻችሁ አይ
ራሩም፤ አንድም ለልጆቻችሁ

ዓይን አይራሩም፤ የልጅ ዓይኑ
ብክን ብክን ሲል ያሳዝናልና፤
፲፰፣ ወትከውን ባቢሎን ክብርተ
መንግሥታት፣

የነገሥታቱ መከበሪያ ባቢሎን፤

ወምክሐ ዕበየ ከላውዴዎን፣

የከላውዴዎን የገናንነቷ መመ
ኪያ የመርዓ ዘውዷ ባቢሎን፤
ከመ ሰዶም ወ ገ ሞ ራ እለ
ገፍትዖን እግዚአብሔር ትከ
ውን ከመ ሰዶም ወገሞራ ብለህ
ግጠም፤ እግዚአብሔር እንዳጠ
ፋቸው እንደ ሰዶም እንደ ገሞራ
ትሆናለች፤ አንድም እንደ ዓሣ
መቅሎ እንደ ቄላቸው እንደ
ሰዶም እንደ ገሞራ ትሆናለች፤

፳፣ ወኢትሄሉ ለዓለም፣

ለዘለዓለሙ አትኖርም፤

ወ ኢ ት ነ ብ ር እንከ ለትውልደ
ትውልድ፣

እንግዲህ ወዲህ ለልጅ ልጅ
ዘመን አትኖርም፤

ኢይበውእዋ ወኢየኀልፍዋ ዓረብ፤

ነጋድያንን የምታስፈራ ሁና
አይገቡባትም፤ አይሄዱባትም፤
ይበውእዋ ቢል ፍላፃ ይዘው
ይሄዱባታል፤

ወኢየወርፉ ውስቴታ ኖሎት ፣

ዘላኖች በ ው ስ ጧ አይኖሩባ
ትም፤ የምታስፈራ ሁና፤

፳፩፣ ወየኀድራ አራዊተ ገዳም፣

አራዊት ይኖሩባታል፤

ወይመልዕ ውስቴታ መጽአሞ፣

ደስክ ይመላባታል፤

ወየወርፉ ህየ ጴዴኔታት፣

እለ ሄለይ ይኖሩባታል፤

ወመራክባት፣

ከአራቱ መዓዝን የተሰበሰቡ፤

አንድም እንደ ሰበድዓት መልክ
አ ስ ተ ባ ብ ረ ው የያዙ
ይኖሩባታል፤

ወይዘፍኑ በህየ አጋንንት፣

እነትግሪዳ ይዘፍኑባታል፤

፳፪፣ ወየኀድሩ እለ ጽፍረ ላህም
እገሪሆሙ፣

እለ ጐሽ እለ አጋዘን ይኖሩ
ባታል፤

፳፫፣ወይትራከቡ ውስቴታ ፍጥረተ
ጺም ወኢም፣

ፍጥረተ የማን ወጸጋም ፍጥረተ
ባሕር ወየብስ ሲል ነው፤
በቀኝ በግራ በባሕር በየብስ
ያሉ ፍጥረታት ይኖሩባታል፤

ወዝ ኮሉ ይከውን ፍጡነ ወኢይ
ጐነዲ፣

ይህ ሁሉ ፈጥኖ ይደረጋል፤ አይ
ዘገይም፤ ምነው ሰባ ዘመን ኑሮ
የለም ቢሉ አይቀርም ሲል
ነው::

www.ethiopianorthodox.org

ምዕራፍ ፲፬

፩፣ ወይሠለሎ እግዚአብሔር ለያዕቆብ፣
እግዚአብሔር ያዕቆብን ይቅር ይለዋል፤
ወዮነርዮ ካዕበ ለእስራኤል፣
ዳግመኛ እስራኤልን ይመርጠ ዋል፤
ወየዐርፉ ውስተ ብሔሮሙ፣
በሀገራቸው አርፈው ይኖራሉ፤
ወይትቄሰኩ ውስቴቶሙ ፈላስያን፣ ወይትቄሰኩ ውስተ ቤተ ያዕቆብ፣
በ ሚ ጠ ት ያመኑ አሕዛብ ከያዕቆብ ወገኖች ጋራ አንድ ይሆናሉ፤ አ ን ድ ም ከፋርስ ከ ባ ቢ ሎ ን አምነው የመጡ አሕዛብ ከትሩፋን ይጨመ ራሉ፤
፪፣ ወይነሥእዎሙ ለአሕዛብ ወየአትውዎሙ ብሔሮሙ፣
አሕዛብን ወስደው ወደሀገራ ቸው ያገቧቸዋል፤
ወይትካፈልዎሙ፣
ይካፈሏቸዋል ዛሬ ለክብረ በዓል የመጣውን ካህን እንዲካፈሉ፤
ወይበዝኑ ውስተ ውእቱ ብሔር፣
በኢየሩሳሌም ይበዛሉ፤
ወይከውኑ በሀየ አግብርተ ወአዕማተ፣
በኢየሩሳሌም ሴት ባሪያ ወንድ ባሪያ ይሆናሉ፤ ማለት የፈቃድ ተገዥ ይሆናሉ፤ አንድም በቤተ ክርስቲያን ቄስ ዲያቆን እየሆኑ ያገለግላሉ፤
ወይቀንይዎሙ፣
እስራኤል የፈቃድ ተቀንዮ ይገዟቸዋል፤
ወይትቀነዩ፣
አሕዛብም የፈቃድ ተቀንዮ ይገዛሉ፤
፫፣ ውእተ አሚረ ያዐርፈከ እግዚ አብሔር እምሕማምክ፣
ያንጊዜ እግዚአብሔር ከመከ ራህ ያሳርፍሃል
ወእመዓትክ፣
እነዚያ ይቄጡኽ ከነበረ ቍጣ ያሳርፍኻል፤ አንድም አንተ ሌላውን ትቄጣው ከነበረ ቍጣ ያሳርፍኻል፤
ወእምቅኔክ እኩይ ዘተቀነይክ ሎሙ፣
ትገዛላቸው ከነበረ ከክፉ አገዛዝኽ ያሳርፍኻል፤
፬፣ ወትነሥእ ዘንተ መንበረ ዘመንግሥተ ባቢሎን፣
የባቢሎንን መንግሥት ዘውድ እጅ ታደርጋለህ፤ ዘሩባቤል ነግሦ መውጣቱ በባቢሎን ነውና፤ አንድም ቂሮስ ዳርዮስ ወንበር ሰጥተው አንግሠው ሰደውታልና፤

ወትብል ይእተ አሚረ እፎኑ ተሥዕረ ዘያቀቱ፣
ያንጊዜ ሰውን ሁሉ ያስገብር የነበረ ሰ ና ክ ሬ ም ብልጣሶር እንዴት ጠፋ?
ወእፎኑ ተሥዕረ ዘያሚምዕ፣
ሰውን ሁሉ ያሸብር የነበረ ሰናክሬም ብልጣሶር ያንጊዜ እንዴት ጠፋ ትላለኽ?
፭፣ እስመ ቀጥቀጠ እግዚአብሔር ለአርዑተ ኃጥኣን፣
የነናቡከደነፆርን ሥልጣን እግ ዚአብሔር አ ጥ ፍ ቶ ታ ል ና፤ አንድም በእስራኤል ቀንበር ይሆንባቸው የነበረ የነናቡከደ ነፆርን ሥልጣን አጥፍቶታ ልና፤ አንድም ኃጥአን ሠራዊቱ በሌላው ቀ ን በ ር ያደርጉት የነበረ፤
አንድም በ ራ ሳ ቸ ው ቀንበር ይሆንባቸው የነበረ ሰናክሬም ብልጣሶር ጠፍቷልና፤
ወለአርዑተ መላእክት፡
የነናቡከደነፆርን አለቆች ሥል ጣን አጥፍቶታልና፤ አንድም በእስራኤል አለቆች ቀንበር ይሆንባቸው፤ የነበረ የነናቡከደ ነፆርን ሥልጣን አጥፍቶታልና፤
፮፣ ወቀሠፎሙ እግዚአብሔር ለአሕዛብ በመቅሠፍተ መዓቱ፤
እግዚአብሔር ተቈጥቶ ባመ ጣው መቅሠፍት አሕዛብን አጠፋቸው፤ አንድም መዓቱን በሚፈጽምበት መቅሠፍት አሕዛብን አጠፋቸው፤
ወኢይምሕኮሙ ለአሕዛብ እመቅ ሠፍተ መዓቱ፤
መዓቱን የሚፈጽምበት መቅሠ ፍት ከ መ ገ ለ ጡ የተነሣ ለአሕዛብ አይራራላቸውም፤
፯፣ ወአዕረፈት እንከ ተአሚና ኵላ ምድር እንዘ ትኬልሕ በትፍሥሕት፣
ምድር ቤተ እስራኤል ሰናክሬም ብልጣሶር ጠፍተውላት ተዘልላ እያመሰገነች ኖረች፤
፰፣ ወይትነሠዩ ብኪ ዕፀው ሊባኖስ፣
ከአብርሃም የተወለዱ እስራ ኤል ሰ ና ክ ሬ ም ብልጣሶር ባንተ ጥፋት ደስ ይላቸዋል፤
እንዘ ይብሉ እምአመ ሰከብከ ኢዐርገ ዘይገዝመነ፣
ዕፀው ብ ሏ ቸ ው ነበርና ዘይገዝመነ አለ፤ አንተ ከጠ ፋህ ጀምሮ እኛን የሚያጠ ፋን ጠላት አልተነሣም እያሉ፤
አንድም እምአመ አስከብከ እምአመ አስከብካሁ ይላል፤ ሰናክሬምን ብልጣሶርን ካጠ ፋኸው ጀምሮ እኛን የሚያጠ ፋን ጠላት አ ል ተ ነ ሣ ም ይ ሉ ታ ል ጌታን ፤ አንድም

www.ethiopianorthodox.org

ሰናክሬምን ብልጣሶርን ካጠፋኸው በኋላ እኛን የሚዋጋን የሚጣላን አልዘመተብንም እያሉ ባንተ ቸርነት በአንተ አምላክነት ደስ ይላቸዋል፤

፱፣ ሲኦልኒ በታሕቱ መረት፣

መቃብር ባቢሎን ጥልቅልቅ አለች፣ ሰለቸች፤

ማለት ብትቀበል ብትቀበል በቃኝ አልል አለች፤

ወተቀበለከ ወተንሥኡ ምስሌከ ኮሎሙ እለ ያርብሕ እለ ኵነንዋ ለምድር፣

ይችን ዓለም የሚገዟት አርበኞች ሁሉ ከአንተ ጋራ ይነሣሉ፣ ይቀበሉኻል፤ አንድም ምስሌከ እለ ኵነንዋ ለምድር ይላል፤ ከአንተ ጋራ እንደ አንተ ይችን ዓለም የሚገዟት አርበኞች ከመቃብር ተነሥተው ይቀበሉኻል፤

እለ አንሥእዎሙ እመናብርቲሆሙ ለኮሎሙ ነገሥተ ምድር፣

የዚህን ዓለም ነገሥታት እየወጉ ከዙፋናቸው የሚጥሏቸው አርበኞች ይቀበሉሃል፤

፲፣ ወይሰጠዉከ ወይብሉከ ኮሎሙ አንተሂ ተሠገርከ ከማነ፣

ሁሉም ይመልሱልኻል፤ አንተም እንደ እኛ ጠፉኽ ይሉኻል፤

ተሥዕረኑ ምክርከ፣

ሰዎችን ማርኬ ገንዘባቸውን ዘርፌ አገራቸውን ተኩሼ እሄዳለሁ ብለህ የመከርኸው ምክር ቀረን፤

፲፩፣ ወ ወ ደ ቀ ውስተ ሲኦል እምክብርከ ብዙኅ፣

ሰናክሬም ከብዙ ባለጸግነትኽ ተለይተኽ በመቃብር ወደቅኽ፤

ወተነጸፍከ ምስሐገ በታሕቴከ፣

ሰናክሬም እንደ ሣር በመቃብር ተነጠፍህ? አንድም በመቃብር ምንጣፍ ሁነኽ ተ ነ ጠ ፍ ህ ? አንድም ተነጽፈ ለከ ምስሐግ ብልጣሶር በ በ ታ ች ኽ ሣር ተነጠፈልኽ? ቸ ብ ቸ ቦ ው ን ቄርጠ በሣር ጠቅልሎ ወስዶ በጽንፈ ት ዕ ይ ን ት ለቂሮስ ለዳርዮስ ሰጥቷቸዋልና፤

ወዐፀዮት ዕየትከ፣

መግነዝኽ ሽተተችን፤

አንድም ቄረትኑ እ ሳ ት ከ ይላል መንፈርኽ መድፈርኽ ቀረን፤ አንድም ወይትነሥዩ፤ ብከ ዕፀወ ሊባኖስ ብለህ መልስ፤ ከአብርሃም የተወለዱ ምእመናን ዲያብሎስ ባንተ ጥፋት ደስ ይላቸዋል፤ እንዘ ይብሉ እ ም አ መ ሰከብከ ኢዐርገ ዘይገዝመነ፣ አንተ ድል ከተነሣኽ ጀምሮ እኛን የሚያ

ስተን ጠላት አ ል ተ ነ ሣ ም እያሉ፤ አ ን ድ ም እምአመ አስከብኩ እምአመ አስከብካሁ ይላል፤ ወ ል ድ ዲያብሎስን ድል ከነሣኽው ጀምሮ እኛን የሚያስተን ጠላት አልተነሣም እያሉ ባንተ ቸ ር ነ ት ደስ ይላቸዋል፤ አንድም እምአመ አስከብከ ቢል፤ ለወልድ አንተ በመቃብር ስ ኩ ብ ከሆንኽ ጀምሮ እኛን የሚያስተን ጠላት አልተነሣም እያሉ ደስ ይላቸዋል፤ አንድም እምአመ አስከብኩ እምአመ አስከብካሁ ቢል፤ ለአብ ል ጅ ህ ን በመቃብር ስኩብ ካደረግኽው ጀምሮ እኛን የሚያስተን ጠላት አ ል ተ ነ ሣ ም እያሉ፤ ባንተ ቸርነት ደስ ይላቸዋል፤ ሲኦልኒ በ ታ ሕ ቱ መረት፤ ሲኦል ገሃነም ጥልቅልቅ አለች ስለቸች ማለት ነ ፍ ሳ ት ን ብትቀበል ብትቀበል በቃኝ አልል አለች፤ ወ ተ ቀ በ ሉ ከ ወተንሥኡ ምስሌከ ኮሎሙ እለ ያ ር ብ ሕ እለ ኵነንዋ ለምድር ይችን ዓለም የሚገዟት አዳምንና ሔዋንን ከልጅነት የለዩአቸው አጋንንት ከገሃነም ተነሥተው ይቀበሉሃል፤ አን ድም ምስሌከ እለ ኵነንዋ ለምድር ይላል፤ ይችን ዓለም ካንተ ጋራ እንደ አንተ የገዟት አጋንንት ከገሃነም ወጥተው ይቀበሉኻል፤ ወ ይ ሰ ጠ ዉ ከ ወይብሉከ ኮ ሎ ሙ አንተሂ ተሠገርከ ከማነ አጋንንት ይመልሱልኻል እንዲህ ይሉኻል፤ አንተም እንደ እኛ ድል ተነሣኽ ይሉሃል፤ ተሥእረኑ ምክርከ ሥጋትን በመቃብር አፍርሼ አበስብሼ ነፍሳትን በሲኦል ተቄራኝቼ እቀራለሁ ብ ለ ህ የ መ ከ ር ኽ ው ምክር ቀረን ወወደቀ ውስተ ሲኦል እምክብርከ ብዙኅ ዲያብሎስ ከብዙ ክብርህ ተለይተኽ በገሃነም ወደቅኽ፤ ወተነጸፍከ ምስሐገ በታሕቴከ ወዐፀዮት ዕየትከ፤ የ ዲያብሎስ ጥሰቱ ልናውን መናገር ነው፤

ጉባዔ

፲፪፣ እፎ ወድቀ እምሰማይ ኮከበ ጽባሕ ዘይሠርቅ ሶበ ይገውህ፣

ሲገሠግሥ አድሮ ማለዳ ወራሪ የሚሰድ ሰናክሬም ብልጣሶር እንዴት ጠፋ፤ አንድም እንዴት ጠፋ ይሉሃል፤

ወተቀጥቀጠ ውስተ ምድር ዘይልእክ ኀበ ኵሉ አሕዛብ፤

ብትገብሩ ገብሩ፤ ብትቀቅሉ ቀቅሉ ያለዚያ እወጋችኋለሁ እያለ የሚልክ ሰናክሬም ብልጣሶር እንዴት ጠፋ፤

www.ethiopianorthodox.org

፲፫፣ ወአንተሰ ትቤ በልብከ አዐርግ ውስተ ሰማይ፣

ሰናክሬም ብልጣሶር ልዑላኑን እገዛለሁ ብለህ ነበር፤ አንድም ካልዑላኑ በላይ ነኝ ብለህ ነበር፤

ወአነብር መንበርየ መልዕልተ ከዋክብተ ሰማይ፣

ሠራዊቱን እገዛለሁ ብለህ ነበር፤

ወእነብር መልዕልተ ደብር ነዋኅ

ንጉሡን እገዛለሁ ብለህ ነበር፤

ወውስተ አድባር ነዋኃት ዘመንገለ ደቡብ፣

ዘመንገለ ኵለሄ ሲል ነው፤ ባአራቱ መዓዝን ያሉ ነገሥታቱን እገዛለሁ ብለህ ነበር፤

፲፬፣ ወአዐርግ መልዕልተ ደመናት፣

ሰናክሬም ብልጣሶር ኃያላኑን እገዛለሁ ብለህ ነበር፤ አንድም ከኃያላኑ በላይ ነኝ ብለህ ነበር፤

ወእከውን ከመ ልዑል፤

ብልጣሶር ቢሉ እንደ ናቡከ ደነፆር፣ ሰናክሬም ቢሉ እንደ ስልምናሶር እሆናለሁ ብለህ ነበር፤ አንድም ሁሉን እንደ ሚያስተባብር እንደ ናምሩድ እሆናለሁ ብለህ ነበር፤

፲፭፣ ወይእዜሰኬ ትጸድፍ ውስተ ሲኦል ወትወርድ ውስተ ማዕምቅቲሃ ለምድር፤

ሰናክሬም ብልጣሶር ዛሬ ግን ወደ ምድር ወደ ጥልቅነቷ ወደመቃብር ትወርዳለኽ፤ አንድም እፎ ወድቀ እምሰማይ ኮከበ ጽባሕ፤ ብለህ መልስ፤ ለማሳት የሚፋጠን ኮከበ ጽባሕ ዲያብሎስ እንዴት ድል ተነሣ ይሉኻል፤ ኮከበ ጽባሕ አለው፤ የአጥቢያ ኮከብ ለጊዜው ሲወጣ አምሮ ደምቆ ይታያል ኋላ ግን ፈጥኖ ይጠፋል፤ ዲያብሎስም አኃዜ መንጦላዕት ቅሩበ እግዚአብሔር አቅራቤ ስብሐት ሁኖ ተፈጥሮ ፈጥኖ ክዷልና፤ ወተቀጥቀጠ ውስተ ምድር ዘይልእክ ኀበ ኵሉ አሕዛብ፤ ኃጢአትን ከሁሉ የሚያዳርስ በሰው ልቡና አእምሮ መንፈሳዊ በተሣለ ጊዜ ያነን ለማጥፋት፤ (ጥቅስ) ወይፌኑ፤ ፩ደ ፩ደ እመላእክቲሁ እንዲል ሣዊ. ዘእስ. ድር፤ ፪፣

አንዳንድ እየሰደደ የሚያቈራኝ ኮከበ ጽባሕ ዲያብሎስ እንዴት ድል ተነሣ፤

ወአንተሰ ትቤ በልብከ አዐርግ ውስተ ሰማይ፤ ዲያብሎስ አንተ ግን ሰማይን የፈጠርሁ እኔ ነኝ ብለህ ነበር፤ ወአነብር መንበርየ መልዕልተ ከዋክብተ ሰማይ ዲያብሎስ ከዋክብትን የፈጠርሁ እኔ ነኝ ብለህ ነበር፤ አንድም ዙፋኔን በከዋክብት ላይ ዘርግቼ እዋጋለሁ ብለህ ነበር፤ ወእነብር መልዕዕተ ደብር ነዋኅ፣ ተራራውን የፈጠርሁ እኔ ነኝ ብለህ ነበር፤ (ጥቅስ) ወሖረ ውስተ ደብር ነዋኅ እንዲል ኢዮብ፤ ወውስተ አድባር ነዋኃት ዘመንገለ ደቡብ፤ ዘመንገለ ኵለሄ ሲል ነው፤ በአራቱ መዓዝን ያሉ ተራሮችን የፈጠርሁ እኔ ነኝ ብለህ ነበር፤

ወአዐርግ፤ ደመናትን የፈጠርሁ እኔ ነኝ ብለህ ነበር፤

ወእከውን ከመ ልዑል

ዲያብሎስ እንደ ልዑል እንደ እግዚአብሔር እሆናለሁ ብለህ ነበር፤ ወይእዜሰኪ ዛሬ ግን ወደ ሲኦል ወደገሀነም ትወርዳለህ፤

፲፮፣ ወያነክሩ እለ ርእዩከ፣

ሰናክሬም ብልጣሶር ያዩኽ ሁሉ ያደንቃሉ፤

ወይብሉ ዝንቱ ብእሲ ዘአማሰና ለምድረ ጽዮን ወለነገሥታ፣

ኢየሩሳሌምን ነገሥታቷን ያጠፋ ይኽ ነው ይሉኻል፤

፲፯፣ ወረሰያ ለኵላ ዓለም ሐቅለ፣

አገሩን ሁሉ ምድረ በዳ ያደረገ፤ አንድም ምድረ በዳ አደርጋለሁ ያለ ይኽ ነው ይሉኻል፤

ወነሰተ አህጉራተ፣

አገሩን ሁሉ ያጠፋ፤ አንድም አገሩን ሁሉ አጠፋለሁ ያለ፤

ወኢፈትሐ ሙቁሓነ፣

የታሠሩትን ያልፈታ ሰናክሬም በካሌና ሠላሳ ሦስት ነገሥታት አሥሮ አግዞ ነበርና፤ ናቡከደ ነፆር ብልጣሶር ቢሉ ኢኮንያንን ሴዴቅያስን ያልፈታ ኢኮንያንን ሠላሳ ስድስት ዘመን አሥሮት ነበርና፤

፲፰፣ ወአኖሞሙ ለኵሎሙ ነገሥተ አሕዛብ፣

የአሕዛብን ነገሥታት ሁሉ የሞት እንቅልፍ እንዲያንቀላፉ ያደረጋቸው ይኽ ነው ይሉኻል፤

ለለብእሲ በክብሩ ውስተ ቤቱ ፣

አንዱም አንዱም ሰው በባለ ጸግነቱ ፀንቶ የኖረውን ያጠፋ ይኽ ነው ይሉኻል፤ አንድም ከተዘጋ ቤቱ ከተዳፈነ እሳቱ

www.ethiopianorthodox.org

እንዲሉ፤ ሰው ሁሉ በየክብሩ በየቤቱ ሳለ ያጠፋው ይኸ ነው ይሉኻል፤

፲፱፣ ወኪያከኒ ይገድፈከ እግዚአ ብሔር ውስተ አድባር ከመ በድን ርኩስ፣

አንተንም እግዚአብሔር እንደ ውሻ ሬሳ በ ተ ራ ራ ላይ ይጥልኻል፤

ምስለ ብዙኃን አብድንት እለ ውጉዛን በኲናት እለ ይወርዱ ውስተ ሲኦል፣

በጦር ከተወጉ ወደመቃብር ከሚወርዱ ከብዙ ሬሳዎች ጋራ ይጥልኻል፤

አንድም ወያነክሩ እለ ርእዩከ ብለህ መልስ፤ ዲያብሎስ ያዩህ ሁሉ ያ ደ ን ቃ ሉ፤ ወይብሉ ዝንቱ ብእሲ ዘ አ ማ ሰ ና ፤ ልጅነትን ያጠፋት፤ አዳምና ሔዋንን ከልጅነት የለያቸው ይኸ ነው ይሉኻል፤ ወረሰያ ለኵላ ዓለም ሐቅለ፤ ሰውን ሁሉ ከልጅነት የለየ ይኸ ነው ይሉኻል፤

ወነሰ አህጉራተ፣

ገነት መንግሥተ ሰማያትን የፈታ ይኸ ነው ይሉኻል፤

ወኢፈትሐ ሙቁሓነ፣

ቍራኝነትን ያለቀቀ፤ አንድም በፍዳ የተያዙትን ያላሰናበተ፤ ወ አ ኖ ሞ ሙ ለ ኵ ለ ሙ፤ አዳምንና ሔ ዋ ን ን የሞት እንቅልፍ እንዲያንቀላፉ ያደረ ጋቸው ይኸ ነው ይሉኻል፤

ለለብእሲ በክብሩ ውስተ ቤቱ አንዱም አንዱም ሰው በልጅ ነት ጸንቶ ይኖር የነበረውን ከልጅነት የለየው ይኸ ነው ይሉኻል፤

ወኪያከኒ ይገድፈከ፤ አንተንም እግዚአብሔር እንደ ውሻ ሬሳ በገሃነም ይ ጥ ል ኻ ል ፤ ምስለ ብዙኃን አብድንት፤ በመስቀል ድል ከተነሡ ወ ደ ሲ አ ል ከሚወርዱ ከብዙ አ ጋ ን ን ት ጋራ ድል ይነሣኻል፤

፳፣ ወከመ ልብስ ዘምሉዕ ደመ፣

ሁ ለ ን ተ ና ው ደም የተቀባ ልብስ፤

ወኢኮነ ንጹሐ

ወከመ፤ ኢኮነ ንጹሐ ሲል ነው፤ ንጹሕ እንዳይደለ፤

ከማሁ አንተሂ ኢኮንከ ንጹሐ፣

አንተም ሰናክሬም ብልጣሶር ከኃጢአት ንጹሕ አይደለኽም፤ አንድም ዲያብሎስ ከሐሰት ንጹሕ አይደለኽም፤

እስመ አጥፋእከ ምድርየ ወቀተልከ ሕዝብየ፣

ብልጣሶር አገሬ ኢየሩሳሌምን ወገኖቼ እ ስ ራ ኤ ል ን አጥፍተ

ኻልና፤ አንድም ሰናክሬም ለኪ ሶን አጥፍተኻልና፤ አንድም ዲ ያ ብ ሎ ስ ቤተ ክርስቲያንን አጥፍተኻልና ንጹሕ አይደለ ኽም፤

ወኢትነብር እንከ ዘርዕ እኩይ ለዓለም፣

ዘር እኩይ ብልጣሶር ለዘለ ዓለሙ አ ት ኖ ር ም ፤ አንድም ክፉ ፍጥረት ዲያብሎስ በባለ ሟልነት ለዘለዓለሙ ጸንተኽ አትኖርም፤

፳፩፣ አስተዳሉ ደቂቀከ ይቅትል ዎሙ በኃጢአተ አቡሆሙ፣

በአባታቸው ኃጢአት ምክን ያት ያጠፏቸው ዘንድ ልጆ ችኽን ለጥፋት አዘጋጅ፤ ማዳን ስለአልተቻለው፤ አንድም ምክ ንያት ሁኖ ስለአጠፋቸው እንዲህ አለ፤ (ጥቅስ) ኤፍሬምኒ አውዕአ ደቂቆ ይቅትልዎሙ በኃጢአተ አቡሆሙ እንዲል፣ (ሆሴ.፱÷ ፲፫)፤

ከመ ኢይትነሥኡ ወኢይረስዋ ለምድር፣

በጠላትነት ተነሥተው ምድርን እንዳይወርሷት፤

ወከመ ኢያብዝኑ ቀትለ በውስተ ምድር፣

በዚህ ዓለም ሰልፍ እንዳያበዙ፤

፳፪፣ ወእትነሣእ ላዕሌሆሙ ይቤ እግዚአብሔር ፀባዖት፣

አሸናፊ እግዚአብሔር በመዓት እነሣባቸዋለሁ አለ፤

ወአጠፍእ ስሞሙ ወ ዘ ር ዖ ሙ ወተረፎሙ፣

ስማቸውን፣ ልጃቸውን፣ የልጅ ልጃቸውን አጠፋለሁ፤

፳፫፣ ከመዝ ይቤ እ ግ ዚ አ ብ ሔ ር ፀባዖት፣

አሸናፊ እግዚአብሔር እንዲህ አለ፤

ወእሬስያ ለባቢሎን ከመ ይንበራሃ አዕዋፍ፣

ባቢሎንን ተፈትታ አዕዋፍ እንዲኖሩባት አደርጋታለሁ፤

ወትከውን ከመ ወኢምንት፣

እንደ ኢ ምንት ትሆናለች፤

ወእሬስያ ከመ ዕቡረ ዓምዓም በሙስና፣

በጥፋት ጊዜ ረግረግ እንዳ ለበት ጭቃ አደርጋታለሁ አለ፤ ያ ረግረግ ያለበት ጭቃ የገባበትን ይዞ እንዲያስቀር፤ እሷም በውስጧ ያሉትን ይዛ ትጠፋለች፤ አንድም በጥፋት እንደ ረግረግ ጭቃ እንድትሆን አደርጋታለሁ፤ የረግረግ ጭቃ

www.ethiopianorthodox.org

ይዞ እንዲያስቀር በመከራ ተይዛ እንድትቀር አደርጋ ታለሁ፤

፳፬፤ ከመዝ ይቤ እግዚአብሔር ፀበያት፣

አሸናፊ እግዚአብሔር እንዲህ አለ፤

በከመ ነበብኩ ከማሁ ይከውን፤

አሁን እንደ ተናገርሁት ይሆናል፤

ወበከመ መከርኩ ከማሁ ይከውን፣

አሕዛብ ይጥፉ እስራኤል ይዳኑ ብዬ እንደመከርሁ ይሆናል፤

፳፭፤ ወይነብር ፣

ይኸ የተናገርሁት ነገር ጸንቶ ይኖራል፤

ከመ አጥፍአሙ ለፋርስ እምድርየ ወእምደወልየ፣

እምድርየ ወእምደወልየ፤ አንድ ወገን፤ የፋርስን ሰዎች ከኢየሩሳሌም አጠፋቸው ዘንድ ምነው የፋርስ ሰዎችማ አጥፊዎች አይደሉም ቢሉ፤ ግብረ አበር የሆኑት አብረው ጠፍተዋልና፤ አንድም ኋላ በደበያት ይጠፋሉና፤ አንድም እስራኤል ካሉባት ከባቢሎን አጠፋቸዋለሁ፤ ምድርየ አለ፤ በተፈጥሮ ገንዘቡ ናትና፤ አንድም የፋርስ ሰዎች የሚሆኑ አጅማ /አጅም/ ኮንታን ከኢየሩሳሌም አጠፋ ዘንድ የባቢሎንን ሰዎች ከባቢሎን አጠፋለሁ፤

ወይከይድምሙ ወይሠዐር እምኔሆሙ አርዑቶሙ፣

በመከራ ይረጋግጧቸዋል ሥልጣናቸውም ከሳቸው ይጠፋል፤

ወያሮሙ ይትነደግ እመት ከፍቶሙ፤

አገዛዛቸው ይቀራል፤

፳፮፤ ዛቲ ይእቲ ምክር እንተ መከረ እግዚአብሔር ላዕለ ኵሉ ዓለም፣

እግዚአብሔር በዓለሙ ሁሉ የመከራት ምክር ይች ናት፤

ወዛቲ ይእቲ እዴሁ ልዕልት ዲበ ኵሉ አሕዛብ፣

በአሕዛብ ላይ የምትመጣ ገናና ሥልጣኑ ይች ናት፤

፳፯፤ እስመ እግዚአብሔር ፀባያት መከረ፣

አሸናፊ እግዚአብሔር መክሯልና፤

ወመኑ ይመይጥ ምክሮ ለእግዚአብሔር፣

የእግዚአብሔርን ምክሩን የሚለውጠው ማነው፤

ወመኑ ይክል እዴሁ ቅዱሰ ወልዑለ፤

ጽኑ ክቡር ልዩ የሚሆን ሥልጣኑን የሚችል ማነው፤

፳፰፤ በዓመቲ ሞተ አካዝ ንጉሥ ኮነዝ ነገር፣

እስከ ዝ ተነበየ በመዋዕለ አካዝ ብሎ ያመለክታል፤ እስከ አሁን በአካዝ ዘመን የተደረገውን ሲናገር መጥቶ ነበር፤ እንግዲህ ወዲህ በሕዝቅያስ ዘመን የተደረገውን ይናገራል፤ አካዝ በሞተበት ወራት ይህ ነገር ተደረገ፤

፳፱፤ ኢትትፈሥሑ ኵልክሙ ኢሉፍሊ፣

ኮነ ያለውን ኢትትፈሥሑ ብሎ አመጣው፤ ኢሉፍላውያን ሁላችሁ ደስ አይበላችሁ፤

እስመ ተቀጥቀጠ አርዑተ ኃይልክሙ፣

በሠራዊቶቻችሁ ቀንበር ይኾን ባቸው የነበረ አካዝ ሙቷልና፤ አካዝ ሞተ ብላችሁ ደስ አይበላችሁ፤ በአካዝ ሕዝቅያስ ተተክቷልና፤ አንድም በሠራዊቶቻችሁ ቀንበር የሚሆን አካዝ ስለሞተ ደስ አይበላችሁ፤ ልጁ ሕዝቅያስ ተተክቷልና፤

አ ዘርዐ አራዊተ ምድር፣

እናንት የእባብ ልጆች የትውልድ አይደለም፤ የግብር ነው፤

ወትውልደ ቃግስት ዘይሠርር፣

ከዚያውም ዘንድ የሚወረወር የእፉኝት እባብ ልጆች ደስ አይበላችሁ፤

፴፣ ወይትረዐዩ ነዳያን በውስቴ ትክሙ፣

ነዳያን እስራኤል በእናንተ ዘንድ ይኖራሉ፤

ወየዐርፉ ሰብእ ነዳያን በሰላም ፣

እስራኤል በተድላ በደስታ ይኖራሉ፤

ወያጠፍአሙ ረኀብ ለዘርዕክሙ ፣

ልጆቻችሁን ቀጠና ያጠፋቸዋል፤

ወየኀልቁ እለ ተርፉ እምኔክሙ፣

ከእናንተ ወገን ከቀጠና የዳኑት በጦር ይጠፋሉ፤

፴፩፤ ወወውዑ በውስተ አናቅጸ አህጉር፣

ይኾንላችሁ እንደሆነ በአደባባይ ደንፉ አግሩ፤

ወደንግፁ ኵልክሙ ኢሉፍላውያን፣

ኢሉፍላውያን አይኾንላችሁምና ደንግጡ፤

እስመ እምሰሜን መጽአ ጢስ፤

ከባቢሎን ናቡከደነፆር ከኢየሩሳሌም ሕዝቅያስ መጥቷልና፤ ምነው ኢየሩሳሌም ምሥራቅ ናት እንጂ ሰሜን ናት? ቢሉ፤ ለአንዱ ምሥራቅ ብትኾን ለአንዱ ሰሜን ናትና፤ አንድም ምሥራቅ ሰሜን የሌለው አገር የለምና፤

www.ethiopianorthodox.org

ወኢትሄልዉ እንከ፣

እንግዲህ ወዲህ በሕይወት አትኖሩም፤

፴፪፣ ወምንተ ትብሉ ነገሥተ አሕዛብ፣

የአሕዛብ ነገሥታት ምን ትላላችሁ፤

ናሁ እግዚአብሔር ሣረራ ለጽዮን፣

እነሆ እግዚአብሔር ጽዮንን በረድኤት አጸናት፤

ወአድኃኖሙ ለትሑታን ሕዝብ፣

ትሑታን ወገኖችን አዳናቸው ምን ትላላችሁ፤

ምዕራፍ ፲፭

ጉባዔ

፩፣ ነገር በእንተ ሞአብ፤

ሞአብ እንድትጠፋ የተናገረው ነገር ይህ ነው፤

በሌሊት ያጠፍአዋ ለሞአብ፣

ቀን ሲገሠግሡ ውለው ሌሊት አዳጋ ጥለው ሞአብን ያጠፏታል፤

አንድም በሌሊተ መከራ ተይዛ ሳለች፤

አንድም ሰነፍ ዕርቅ አድርገው ያጠፏታል፤ (ጥቅስ) ሀቡ ጽጌ ለሞአብ እንዲል ኤር. (፵፰÷፱)፤

ወበሌሊት ያንኀልዋ ለጥቅመ ሞአብ፣
ቀን ሲገሠግሡ ውለው ሌሊት አዳጋ ጥለው፤
አንድም በሌሊተ መከራ ተይዛ ሳለች፤ አንድም ሰነፍ ዕርቅ አድርገው የሞአብን ቅጽር ያፈርሷታል፤ አንድም ሞአብ ገሃነምን ሥላሴ በሌሊተ ዓርብ ያጠፏታል፤
ወበሌሊት ያንኀልዋ ለጥቅመ ሞአብ ፍትወታት እኩያት ኃጣውዕን ያጠፉሉ፤
፪፣ ተክዙ ለርእስክሙ፣
ለራሳችሁ እዘኑ አልቅሱ፤
እስመ ተኀጕለት ዴቦር ኀበ ይነብር ጣያትክሙ፣
ከዚያ ሂደን እንድናለን እንዳትሉ ጣያታችሁ ያለባት ዴቦር ጠፍታለችና ዴቦር መካነ ጣያት ናት፤
ውኀበ ሀሎ ምሥዋዒክሙ ሀየ ዕርገ፣
እስኪ ትድኑ እንደሆነ ምሥዋዕ ወደአለበት ውጡ፤
ወብክዩ በውስተ ናባው ዘሞአብ፣
የሞአብ ክፍል በምትሆን በናባው አልቅሱ፤
ውስተ ኵሉ ርእስ ብርሃት፣
በሰው ሁሉ ራስ ቡህነት ትወጣለች፤ ትብትብ ምንጣፍ በመሸከም፤
፫፣ ወይትመተር ኵሉ መዝራዕት በውስተ መርኀባ፣
የሰው ሁሉ ክንድ ባደባባይዋ ይቈረጣል፤

ለአፍርሆ ክንዳቸውን እየቈረጡ የአህያ መንጃ አድርገው ታልና፤

አንድም አርበኛ ካደባባይዋ ይጠፋል፤

ቅንቱ ሠቀ፣

ምንጣፍ ማቅ ታጠቁ፣

ወብክዩ በውስተ አንሕስቲሃ፤

በግምቡ ውስጥ አልቅሱ፤

ወአውይዉ ውስተ አስኳቲሃ እንዘ ትብክዩ፣

አስኳት ሸንጎ ምስቅል ጐዳና ነው፤ እያዘናችሁ በሸንጎ አልቅሱ፤

፬፣ እስመ አወየወት ሐሴቦን ወነገረት እስከ ኢያሳ፣

ሐሴቦን ጩኻለችና እስከ ኢያሳ ድረስ ተናገረች፤

ወተሰምዐ ቃሎሙ፣

ቃላቸው ዕንፍ እስከ ጽንፍ ተሰማ፤ እንደ ቅማንት፣ ቅማንት አንዱ ሲጮኽ የሰማ እንደሆነ ነገሩን ሳያውቀው አያይዘ ይጮኻል፤

በእንተ ዝንቱ የሐምም ሐቋ ሞአብ፣

ልበ ሞአብ ሲል ነው፤ ስለዚህ ነገር የሞአብ ልቡና ያዝናል፤

አንድም ሐቋ ያለው ንጉሡን ነው፤ ወገብ የላዩንም የታቹንም እንዲያጸና ንጉሡም ልዑላኑን ትሑታኑን ያጸናልና ሐቋ አለው ንጉሡ ያዝናል፤

፭፣ ወትግዕር ሞአብ ላዕለ ርእሳ፣

ሞአብ ራሷን ይዛ ታለቅሳለች፤ አንድም በራሷ በመጣባት ኃጢአት ታለቅሳለች፤

ወይትዐወቃ ለልባ ለሞአብ፣

ይህ የመጣባት መከራ በኃጢአቷ እንደሆነ ሞአብ ለልቡናዋ ይታወቃታል ይረዳታል፤

ወተዐወዩ ባሕቲታ እስከ ሴጎር፣

ሴጎር ማለት ምሥጋረ እግር ዘአዕረፈ ባቲ ሎጥ ማለት ነው፤ እስከ ሴጎር ድረስ ብቻዋን ታለቅሳለች፤

እስመ ዕጕለት ይእቲ ሞዓብ ዘሠለስቱ ክረምታ፣

ሞዓብ ሦስት ዓመት የሆናት ጊደር ናትና ሦስት ዓመት የሆናት ጊደር ለመታረድ ትቀርባለች፤ እሷም ለመከራ ቀርባለችና፤ አንድም ያች እንድትቀናጣ ፈጣሪ የለኝም አለች፤

በውስተ ዐቀባ ትበኪ፣

በተራራው ታለቅሳለች፤

የዐርጉ ወይትመየጡ ፍኖተ አሮሜን፣

የሞዓብ ሰዎች እነናቡከደነፆርን ለማየት ወደ ተራራ ይወጣሉ፤ ብዛታቸውን አይተው በደበቁ ጎዳና ይመለሳሉ፤

አንድም እነናቡከደነፆር ወደ ተራራ ይወጣሉ፤ ብዛታቸውን

www.ethiopianorthodox.org

አይተው ለግዳይ ለምርኮስ
እኒህ ይበቁናል ብለው በደበቁ
ጎዳና ይመለሳሉ፤
ወየዐወይዉ፣
ይጮኻሉ፤
ወይትቃተሉ፣
ይዋጋሉ፤
ወይከውን ድልቅልቅ፣
ንውጽውጽታ ይሆናል፤
፮፣ ወይነጽፍ ማየ ኔምሬም፣
የኔምሬም ውሀ ይደርቃል፤
ድርቅ ሁኖ፤ አንድም የናቡከደ
ነፆር ወገን ጠጥቶት፤
ወይየብስ ሣዕራ፣
ሣሯ ይደርቃል ድርቅ ሁኖ፤
አንድም የናቡከደነፆር ወገን
በልቶት፤
ወኢይትረከብ ሐመልማል በውስ
ቴታ ፣
በውስጧ ልምላሜ አይገኝም
ድርቅ ሁኖ፤
አንድም የናቡከደነፆር ወገን
በልቶት፤
፯፣ ወምስለ ከመዝ ሀለወከ ከመ
ኢትድኅን፣
ከዚህም ጋራ እንዳትድን መሆን
አለህ፤
እስመ እመጽእ ውስተ ቈላተ አራባስ
ወእነሥኣ፣
ከዚያ ሂጄ እድናለሁ እንዳትል
ወደአራባስ ቈላ በመዓት እመጣ
ለሁ፤ እጅ አደርጋታለሁና፤

፰፣ እስመ ኀብረት አውያተ ምስለ
በሐውርተ አሞን፣
ከአሞን አውራጃ ጋራ በጩኸት
ተባብራለችና፤
አጋሌም ወውዑ እስከ አዘቅተ ኤላም፣
የአጋሌም ሰዎች ይኾንላችሁ
እንደሆነ እስከ ኤላም ምንጭ
ድረስ ደንፉ አግሩ፤
፱፣ ወይመልዕ ደም ውስተ ማየ
ኔምሬም፣
በኔምሬም ውሀ ደም ይመላ
በታል እነናቡከደነፆር ተቀራ
ደው አልቀውበት፤
እስመ መጽአት ሬሞን፣
ባቢሎን መጥታለችና፤
አንድም ሞዓብ ወደምትጠ
ፋበት ቦታ መጥታለችና፤
አንድም እስከ ራማ ይላል፤
ራማ የብንያም ዕፃ ናት፤
እሷን አጥፍታ ነበርና በዚያ
ፍዳ ትጠፋለች፤
ወእነሥእ ዘርዐ ሞዓብ ወአርያል፣
የሞዓብንና የአርያልን ልጅ
በፍዳ እይዛለሁ፤
ወለእለ ተርፉ እምአዳማህ
እፌንዎሙ ከመ አራዊት ውስተ
ምድር፣
ከኤዶምያስ ሰዎች ከሞት
የቀሩትን እባብ በልቡ ተስቦ
እንዲሄድ በልባቸው ተስበው
እንዲሄዱ አደርጋቸዋለሁ::

ምዕራፍ ፲፮

፩፣ ገዳምኑ ይእቲ ደብረ ጽዮን፣
አልደፈርም ትል እንደሆነ ኢየ
ሩሳሌም ምድረ በዳ ነበረች
እኔ ባጠፋት ነው እንጂ፤
አንድም ኢየሩሳሌም ምድረ፤
በዳ ነበረች፤ አንተ ብታጠፋት
ነው እንጂ፤
እስመ ኮነት ከመ ፆፍ እንተ
አሥረረት ዕጐሊሃ ውኅደገት፣
ገላግልቷን አሳድጋ ቤቷን ጥላ
እንደሄደች ወፍ ሁናለችና፤
፪፣ ወኮነት ወለተ ሞዓብ ከመ
መሐስዐ በግዕ፣
የሞዓብ ልጅ እንደ በግ ጠቦት
ሆነች፤ ያ እንዲያለኸልኸ
አለኸለኸች፤
፫፣ ወትመክር ከመ ትግበር ላቲ
ዳሰ ኀበ ትነብር ውስተ ምስሐግ
ወትረ መዓልተ ወሌሊተ፣
ተሰዳ ሂዳ ቀን የምት ውልበት
ሌሊት የምታድርበት በቋያው
ዳስ ትሠራ ዘንድ ትመክራለች፤
ወይደነግዑ ወይሜምዑ
ይደነግጣሉ ይሸበራሉ፤
፬፣ ወኢታብእዎሙ ኀቤክሙ፣
ወደእናንተ አታስገቧቸው፤
ወኢታንብርዎሙ ለእለ ወተጉ እምነ
ሞዓብ፣
ከሞዓብ ሸሽተው የመጡትን
ከእናንተ ጋራ አታኑሯቸው፤
ከመ ኢይኩኑክሙ ፀረ ምስለ እለ
ሮዱክሙ፣
ከከበቧችሁ ሰዎች ጋራ ጠላት
እንዳይኾኗችሁ፤
እስመ ኀልቁ መስተቃትላን፣
የሞዓብ አርበኞች ጠፍተዋ
ልና፤
ወተኀጕለ መልአክ ዘላዕለ ኵሉ
ምድር፣
የሞዓብ አለቃ ጠፍቷልና፤
አንድም ዘይከይድ ኵሎ
ምድረ ይላል፤ ዓለሙን ሁሉ
የሚገዛ ንጉሥ ጠፍቷልና::
፭፣ ወይረትዕ መንበሩ በምፅዋት፣
ስሙ ያልታወቀ የእስራኤል
ንጉሥ ቸርነቱን ምጽዋት
አድርጎ ሰጥቶት ዙፋኑ የቀና
ይሆናል፤ አንድም የሕዝቅያስ
የዘሩባቤል ዙፋኑ በምጽዋት
የቀና ይሆናል፤
ወይነብር ውስቴቱ በጽድቅ፣
ስሙ ያልታወቀ የእስራኤል
ንጉሥ፤ አንድም ሕዝቅያስ
ዘሩባቤል በእውነት ነገር ጸንቶ
ይኖራል፤

www.ethiopianorthodox.org

ወይኳንን በቤተ ዳዊት፣

በዳዊት ወገን ይፈርዳል፡

ወየኃሥሥ ፍትሐ ወይደሜን ጽድቀ፣

ስሙ ያልታወቀ የእስራል ንጉሥ የቀና ፍርድ ይፈርዳል፡ ሕጉን ይጠብቃል፡

አንድም እስመ ኀልቁ መስተ ቃትላን ብለህ መልስ፡ የሰናክሬም የብልጣሶር አርበ ኞች ጠፍተዋልና ወተንገሠለ መልአክ ዘላዕለ ኵሉ ምድር፣ በሀገሩ ሁሉ የነገሠ፣

አንድም ዘይከይድ ዓለሙን ሁሉ የሚገዛ ዲያብሎስ ድል ተነሥቷልና፡

ይረትዕ መንበሩ በምጽዋት ሥጋውን ደሙን ምጽዋት አድርጎ ሰጥቶት የጌታ ማደሪያ ምእመን ጽንዐ ነፍስ አግኝቶ ይጸናል፡

ወይነብር በሃይማኖቱ ምክንያት ጌታ ያድርበታል፡ ወይኳንን ከዳዊት ወገን በነሣው ሥጋ ጌታ ተነድገ ለክኃጢአትከ ተነድገ ለኪኃጢአትኪ ፈቀድኩ ንጻሕ ተንሥእ ንሣእ ዓራተከ እያለ ይፈርዳል፡

ወየኀሥሥ ፍትሐ ወይዴግን ጽድቀ፣

ሕዝቅያስ ዘሩባቤል የቀና ፍርድ ይፈርዳል ሕጉን ይጠብቃል፡

አንድም ጌታ አራትን ወንጌልን ያስተምራል፡

፮፡ ወቅሚዕነ ትዕቢቶሙ ለሞዓብ፣

የሞዓብን ሰዎች ትዕቢታቸውን ሰማነ፡

ወትዝኅርቶሙ ፈድፋደ፣

ብዙ የሆነ መታበያቸውንም ሰማን፡

ወአዐትት ትዕቢቶሙ ወሰገሌሙ፡

ትዕቢታቸውን ጥንቈላቸውን አርቃለሁ፡

አኮ ከማሁ

እናንተ እንድናለን እንዳላችሁ አይደለም፡

፯፣ ወወውዑ ሞዓብ፣

የሞዓብ ሰዎች አልቅሱ፡

እስመ ሞዓብ ኮሉሙ አውየዉ፣

የሞዓብ ሰዎች አልቅሰዋልና እኩሌቶች እኩሌቶችን እንዲህ ይሏቸዋል፡

ወእለ ይነብሩ ዳሴም ኢያመስጡ፣

በዳሴም የሚኖሩ ሰዎች ከመከራ አያመልጡም፡

ወይሰሐጡ፣

አንተ እንጂ ኃጢአት ሥራ፡ ጣዖት አምልክ ብለኸኝ ነው እያሉ ይዘባበላሉ፡

አንድም ብንጣራ ሰው ይሰማናል ብለው እርስበርሳቸው ይቈናጠጣሉ፡

አንድም ሲበድሉ ኑረው መከራ በመጣባቸው ጊዜ ይዘባበሉ ማለት ፍሬ ያሌለውን ንግግር ያበዛሉ ፡

ወይትኃፈሩ ደቂቀ ሐሴቦን ፣

የሐሴቦን ልጆች በመከራ ያፍራሉ ፡

፰፣ ወትላሁ ወይነ ሱባማ ፣

የሱባማ ወይን ታለቅሳለች፡ የሰዎችን ለወይኑ ሰጥቶ ተናገረ፡ አንድም ወትላሁ በእንተ ወይን ሱባማ፣ ሱባማ ስለ ወይኑ ጥፋት ታለቅሳለች ፡

፱፣ ወአኬድዎ ለወይና እስከ ኢያዜር፣

እስከ ኢያዜር ድረስ ወይኗን አበራይተውታልና ፡

አይቴ በጽሐ ሐዋርያቲሃ ፣

መልእክተኞቿ ወዴት ደረሱ ፡

ዔሉ ውስተ ገዳም ፣

እነሆ ፍርሃታቸውን አውቃለሁ፡ ምድረ በዳውን ዙረው ሂደው ይሆናል ፡

ወእለ ተርፉ ዐደዉ ባሕረ ፣

ከነዚያ የቀሩት ፍርሀት የጸናባቸው ወንዙን ተሻግረው ሂደው ይሆናል ፡

ወበእንተ ዝንቱ ትበኪ ብካየ ኢያዜር፣

ስለዚህ ነገር የኢያዜርን ልቅሶ ታለቅሳለች ፡ ኢያዜር ቃለ ቀጭን ናት ቃሏን አቅጥና አንድም ኢያዜር ስመ ሀገር ናት ኢያዜር ልቅሶን ታለቅሳለች ፡

ወአስተጋብዓ ወይነኪ ሱባማ ፣

ሱባማ ይህን ጊዜ እነናቡከደነፆር ሳይመጡ ወይንሽን ሰብስቢ ፡

ወዕፀወኪ ሐሴቦን ፣

ሐሴቦንም ዑድሺን ሰንደልሽን ሰብስቢ ፡

ወነበበት በእንተ ማዕረር ወቀስም፣

ስለወይኑ ፡ ስለእህሉ መከር ተናገረች፣ ይህን ጊዜ የእህሉን መከር ፣ ይህን ጊዜ የወይኑን መከር እሰበስብ ነበር እያለች፣ የአይቶ አጣ ነገር ትናገራለች፡ አንድም ይህን ጊዜ እነናቡከደነፆር ሳይመጡ የወይኑን፣ የእህሉን መከር ሰብስቡ እያለች ተናገረች፡ አንድም እንዲህ ብላ የተናገረችውን ወአከይድ እነናቡከደነፆርን አምጥቼ አበራየዋለሁ፣ አንድም ወትነብብ ይላል፡ ይህን ጊዜ ባቄላውን ፣ ገብሱን ስንዴውን ፣ ጤፉን ሰብስቡ ፡ ወይኑን ዘይቱን ልቀሙ እል ነበር እያለች ፡ የአይቶ አጣ አነጋገር ትናገራለች ፡

www.ethiopianorthodox.org

፲፣ ወእሥዕር ትፍሥሕተ ወጎሜተ እምወይን ፣

ወይኑን ጠጥቶ የሚያደርገውን ተድላ ደስታ አጠፋለሁ ፤ ረድኤት መንሣቱን መናገር ነው ፤ አንድም ወይኑን ጠጥተውት አያረካም፤ አንድም ወይኑን አጥፍቼ ተድላ ደስታውን አጠፋለሁ ፤

ወኢይትፌሥሑ እንከ በወይን ፣

እንግዲህ ወዲህ ወይን ጠጥተው ደስ አይላቸውም አንድም ወይን አጥተው ደስ አይላቸውም ፤

ወኢያከይዱ ወይነ ውስተ ምክያድ፣

ወይኑንም ባውድማ አያበራዩ ትም ፤

እስመ ጠፍአ ፣

ጠፍቷልና ፤

፲፩፤ በእንተ ዝንቱ ትነቁ ከርሥየ ከመ መሰንቆ በእንተ ሞዓብ ፣

በእንተ ሞዓብና በእንተ ዝንቱ አንድ ወገን ነው፤ ይቤ ነቢይ ብሎ ያመለክታል ፤ ስለዚህ ነገር ልቡናዬ እንደ መሰንቆ ትጮኻለች አለ ፤ ነቢይ ለሁሉ ያዝናልና ፤ አንድም ርኅሩኅ እግዚአብሔር አድሮበታልና ፤

ወአዕዕምትየ ከመ ምረገ ዓረፍት እንተ ገየሩ ፣

አጥንቴም እንደተመረገ እንደ ተለሰነ ግርግዳ ሆነ ፤ ያ ምርጉን ባስለቀቁት ጊዜ መሸከ እንዲ ገኝ ፤

፲፪፤ ወትከውን ለጎሣር ፣

ለመከራ ትሆናለች ፤

እስመ ሰርሐት ሞአብ በጣየታ ፣

ሞአብ በጣየታ ደክማለችና ፤

ወተሐውር ኀበ አማልክቲሃ ትጸሊ ፣

ከጣየታቷ ትለምን ዘንድ ትሄዳ ለች ፤

ወኢይክሉ አድኅኖታ ፣

ማዳን ግን አይቻላቸውም ፤

፲፫፤ ዝንቱ ነገር ዘነበበ እግዚአብሔር በእንተ ሞዓብ እምቀዲሙ ፣

ከጥንት ጀምሮ እግዚአብሔር ስለሞዓብ የተናገረው ነገር ይህ ነው ፤

፲፬፤ ወይእዜኒ እብል ዘሠለስቱ አመ ታተ አሳብ ይእቲ ሞአብ ፣

እስመ ዕጐልት ይእቲ ሞአብ ዘይቤቱ ክረምታ ብሎ ነበርና አሁንም ሞአብ ሦስት ዓመት የሆነው ምንደኛ ናት ፣ ያ ቀኑ ከደረሰ በኋላ ልዋል ልደር እንዳይል ልዋል ልደር ሳትል ዕለቱን ተማርካ ትሄዳለች ፤ አንድም

ሦስት ዓመት የሆነው ምንደኛ እኔ ከገባሁ ገንዘቡ በዝቷልና ልካፈል እንዳይል፣ እርሷም ከገንዘቧ ጥቂት ሳትይዝ ተማርካ ትሄዳለች ፤ አንድም ምንደኛ የሌሊት ቀሮር የመዓልት ሐሩር ይታገሣል እሷም ታግሣለችና፤

በእንተዝ ተኀስር ሞዓብ እምኵሉ ብዕላ ብዙኅ ፣

ወትከውን ለሀሣር ብሎ ነበርና ስለዚህ ነገር ሞዓብ ከብዙ ባለ ጸግነቷም ተለይታ ትጠፋለች ፤

ወኢይተርፍ ኀዳጥ ፣

ጥቂትስ እንኳ ገንዘብ አይቀርላ ትም፤

ወኢይትረከብ ክብራ ፣

ባለጸግነቷም አይገኝም ::

ምዕራፍ ፲፯

ጉባዔ

ነገር በእንተ ደማስቆ ፣

ደማስቆ እንድትጠፋ አይቶ የተናገረው ነገር ይህ ነው ፤

፩፤ ናሁ ትጠፍእ ደማስቆ እም ብዙኃት አህጉር ፣

እነሆ ደማስቆ ከብዙ አህጉር ተለይታ ትጠፋለች ፣ አንድም ምስለ ብዙኃት አህጉር ሲል ነው ፤ ከጥቃቅኑ አህጉር ጋራ ትጠፋለች ፣

ወትወድቅ ወትትመዘበር ለዓለም ፣

ለዘለዓለሙ ፈጽማ ትጠፋለች፤

፪፤ ወየዐርፉ ውስቴታ ኖሎት ፣

ተፈትታ ዘላኖች ይኖሩባታል፤ ኢየዐርፉ ቢል ፈጽማ ጠፍታ ምድረ በዳ ሁና ዘላኖች አይኖሩባትም ፤

ወአልቦ ዘይረድኣ ፣

የሚረዳት የለም ፤

፫፤ ወአልቦ ፀወን ኀበ ይፀወን ኤፍሬም ፣

አሥሩ ፤ ነገድ የሚጠጋበት የለም፤ ቀድሞ ፋቁሔ ከረዓሶን እንደ ተጠጋ ፤

ወኢይነግሥ እንከ ንጉሥ በደማስቆ ፣

ከእንግዲህ ወዲህ በደማስቆ እንደረዓሶን ያለ ንጉሥ አይነግሥም ፤

ወእለሂ ተርፉ እምሶርያ ይወድቁ በኩናት ፣

ከሶሪያ የቀሩት ሰዎች በጦር ይጠፋሉ ፤

፬፤ አንተኒ ትኄይስ እምደቂቀ እስራኤል ፣

አንተኑ ትኄይስ እምደቂቀ እስራኤል ልጆች አንተ ትበልጣለህን፤

www.ethiopianorthodox.org

ወእምክብሮሙ ፣

ክብረ መንግሥትህስ ከክብረ መንግሥታቸው ይበልጣልን፣

ከመዝ ይቤ እግዚአብሔር ጸባዖት፣

አሸናፊ እግዚአብሔር እንዲህ አለ ፤

፬፡ ውእተ አሚረ የኀልቅ ክብሩ ለያዕቆብ ፣

ያንጊዜ በዔዋዌ የያዕቆብ ባለ ጸግነቱ ሂዶ ሂዶ ያልቃል፤ አንድም በሚጠት ገንዘቡ መጥቶ መጥቶ ፍጹም ይሆናል፣

ወያድለቀልቅ ዘይበዝኅ ትርሢቱ ፣

ብዙ ሺልማቱ በዔዋዌ ሂዶ ሂዶ ያልቃል፤ አንድም በሚጠት መጥቶ መጥቶ ፍጹም ይሆናል፤

፭፡ ወይከውን ከመ ዘያስተጋብእ ማዕረረ ዘበጽሐ ቅድመ ፣

አስቀድሞ የደረሰውን መከር እንደሚሰበስብ ሰው ይሆናሉ፤

ወከመ ሰዊት ዘበሰለ ድኅረ በውስተ ቈላት ፣

በቆላ በኋላ የደረሰውን እሸት እንደሚሰበስብ ይሆናሉ ፤ እሸት የሚወደድ በፊት የደረሰ ወይም በኋላ የደረሰ ነውና ያ እየሳሳ ፍሬውን እንዲመገብ በዔዋዌ አሕዛብ እየሳሱ እስራኤልን ይማርኳቸዋል ፤ አንድም በሚጠት እስራኤል እየሳሱ አሕዛብን ይማርኳቸዋል ፤

ወይተርፍ ቀሪሙ ፣

ደገኛው መከር ካለፈ በኋላ ቃርሚያው እንዲቀር ገንዘቡ አልቆ አገሩ ብቻ ይቀራል ፤ እንደ ፊተኛው አዝመራ አሥሩ ነገድ፣ እንደ ኋለኛው አዝመራ ሁለቱ ነገድ፣ አንድም እንደ ፊተኛው አዝመራ አሥሩ ነገድ ፣ እንደ ቃርሚያው ሁለቱ ነገድ ናቸው ፤

፮፡ ወከመ ሕንባባተ ዘይት ክልኤቲ፣

ሁለት የሚሆኑ የዘይት ፍሬዎች ፤

ወእመ አኮ ሠላስ ውስተ ርእስ ነዋኅ ፣

ሦስትም ቢሆኑ በረጅም ዛፍ ላይ ፣

ወውስተ አዕፁቂሃ ፣

በጫፎቿ ያሉ ሁለትም ሦስትም ቢሆኑ ፤

ወእመ አኮ አርባዕ ፣

አራትም ቢሆኑ ፤

ወእመ አኮ ሐምስ ይተርፉ ፣

አምስትም ቢሆኑ ጥቂት እንደ ሆኑ ከእስራኤል ጥቂት ሰዎች ይቀራሉ ፤ ለከርሚ ወለሄሬቢ የሚላቸው ወይን የሚያርሙ ፣

የሚኮተኩቱ ናቸው ፤ አንድም ሁለትና ሦስት ፣ አራትና አምስት ፣ አሥራ አራት ይሆናሉ ፤ እንደዚህም ሁሉ ከእስራኤል አሥራ አራት ሰዎች ይቀራሉ ማለት ጥቂቶች ሰዎች ይቀራሉ፤ አንድም አምስትና ሁለት ሰባት ፣ አራትና ሦስት ሰባት ፣ ሰባትና ሰባት አሥራ አራት ይሆናሉ ፤ ከወረዱት አሥራ አራት አበው ይመለሳሉ የቀሩት አልቀው ፤

ከመዝ ይቤ እግዚአብሔር አምላከ እስራኤል ፣

የእስራኤል ፈጣሪ እግዚአብሔር እንዲህ አለ ፤

፯፡ ውእተ አሚረ ይትዌከል ሰብእ በፈጣሪሁ ፣

ያንጊዜ ሰው ሁሉ በፈጣሪው ያምናል ፤

ወይኔጽራ አዕይንቲሁ ኀበ ቅዱሰ እስራኤል ፣

ዓይኖቹ ወደጽንዐ እስራኤል ወደክብረ እስራኤል ይመለከታሉ ፤

፰፡ ወኢይትአመኑ እንከ በጣዖቶሙ፣

እንግዲህ ወዲህ በጣዖታቸው አያምኑም ፤

ወኢበግብረ እደዊሆሙ ዘገብሩ በአፃብዒሆሙ ፣

በጣታቸው በሠሩት በእጃቸው ሥራ አይታመኑም ፤

ወኢይገዝሙ ዕፀ ለርኩሶሙ ፣

ኃጢአት ሊሆንባቸው፤ አንድም ለርኩሶሙ ጣዖት አድርገው ሊሠሩት እንጨት አይቈርጡም ፤

፱፡ ውእተ አሚረ ይከውና አህጉሪከ መዝበረ ፣

ምዝቡራተ ሲል ነው ፤ ያንጊዜ አገሮችህ የተፈቱ ይሆናሉ ፤

ከመ መዝበረ አሞሬዎን ወኤዌዎን ዘመዝበረ እምቅድመ ገጾሙ ለደቂቀ እስራኤል ፣

በኢያሱ ጊዜ ከእስራኤል ፊት እንደጠፉ እንደአምሬዎን እንደ ኤዌዎን ይጠፋሉ፤ አንድም ከመ መዝበረ አሞሬዎን ወኤዌዎን፣ አሞሬዎንና ኤዌዎን እንደ ፈረሰ ፍራሽ ይሆናሉ ፤

ወትከውን ገዳመ ፣

የእስራኤል አገር ምድረ በዳ ትሆናለች ፤

፲፡ እስመ ኀደጎ ለአምላክከ ፣

ፈጣሪህን በሕግ በአምልኮት ትተኸዋልና ፤

www.ethiopianorthodox.org

ወመድኅኔከ ፣

መድኃኒትህ እግዚአብሔርን ትተኸዋልና ፤

ወኢተዘከርኮ ለእግዚአብሔር ዘአጽንዐከ ፣

ኢታምልክ ባዕደ አምላከ ብሎ ያጸናህን ፤ አንድም ዘአስተርአየከ በደብረ ሲና፣ በደብረ ሲና የታየህን እግዚአብሔርን አላሰብኸውምና ፤

ወበእንተ ዝንቱ ትተክል ተክለ ሐሰት ፣

ስለዚህ ነገር የሐሰት ተክል ትተክላለህ ፣ ጣዖቱ አለመለመልኝ የሚለውን ተክለ ሐሰት አለው ፤

ወትዘርዕ ዘርዓ ኀሳር ፣

ዘርዓ ኀሳርን ትዘራለህ ፤ ጣዖቱ አበቀለልኝ የሚለውን ዘርዓ ኀሳር አለው ፤

፲፩፡ ወአመ ትተክል ትጌጊ ፣

ዘር በዘራህ ፣ ተክል በተከልህ ጊዜ ትበድላለህ ፤ ጣዖቱ አበቀለልኝ ፣ ጣዖቱ አለመለመልኝ ትላለህ ፤

ወኢይፈሪ ዘዘራዕከ ፣

የዘራኸው አያፈራም ፤

ወታወርስ መርገመ ለውሉድከ ፣

ለልጆችህ መርገምን ታቆያቸዋለህ ፣ አንድም በእንተ ዝንቱ ትተክል ተክለ ሐሰት ብለህ መልስ ፤ ስለዚህ ነገር ልጅ ትወልዳለህ ፣ ወትዘርዕ ዘርዐ ኀሳር አንድ ወገን ልጅ ትወልዳለህ ፤ ጣዖቱ ሰጠኝ የሚለውን ተክለ ሐሰት ዘርዐ ኀሳር አለው ፤ ወአመ ትተክል ትጌጊ ፤ ልጅ በወለድህ ጊዜ ጣዖቱ ሰጠኝ እያልህ ትበድላለህ ፤ ወኢይፈሪ ዘዘራዕከ ፣ ልጅህ ልጅ አይወልድም ፤ ወታወርስ መርገመ ለውሉድከ ፣ ልጆችህን የርጉማን ልጆች ታሰኛቸዋለህ ፤ አንድም ወበእንተ ዝንቱ ትተከል ብለህ መልስ ፤ ስለዚህ ነገር ጣዖት ታመልካለህ ፤ ወትዘርዕ አንድ ወገን ጣዖት ታመልካለህ (ጥቅስ) እስመ ዘርዑ ነፋሰ ወዐረሩ ዓውሎ ወአልቦ ኃይል ለከላስስ ቲሆሙ ፤ ሆሴ. ፰፣፯ ፤

ወአመ ትተክል ትጌጊ ፣

ጣዖት ባመለክህ ጊዜ ትበድላለህ ማለት ለጣዖቱ ዕጣን መሥዋዕት ታቀርባለህ ፣ ወኢይፈሪ ለጣዖቱ ያቀረብኸው ዕጣን መሥዋዕት ክብር ረድኤት አያሰጥህም ፣ ወታወርስ መርገመ ለውሉድከ ፣ ልጆችህን ሑሩ እምኔየ ርጉማን ታሰኛቸዋለህ፤

፲፪፡ አሌ ሎሙ ለብዙኃን አሕዛብ እለ መልዑ ከመ ማይ ፣

እንደውሃ በዝተው ለሚሄዱ ለብዙ አሕዛብ ወዮላቸው ፤

ወከመ ውኂዘ ማይ ዘይወርድ እምደብር በተታልዎ ፣

የመጣያ ውሃ ቀጥሎ ቀጥሎ እንዲወርድ ቀጥሎ ቀጥሎ መዓት መቅሠፍት መጥቶባቸው ፤

ከማሁ ይጠፍዑ ነምቀዳሚ እስከ ደኃሪ ፣

ከፊት በር እስከ ኋላ ዳረግንድ ድረስ ይጠፋሉ ፤ አንድም ከታላቁ እስከ ታናሹ ይጠፋሉ ፤ አንድም ከንጉሡ እስከ ሠራዊቱ ይጠፋሉ፤ አንድም በፊት ሠራዊቱ በኋላ ንጉሡ ይጠፋሉ፤ በሰናክሬም ጊዜ ፤ አንድም በፊት ንጉሡ በኋላ ሠራዊቱ ይጠፋሉ በብልጣሶር ጊዜ ፤

ወከመ ፀበል ዘይነሥኦ ነፋሰ ገውሎ ፍና ምሴት ፣

ጊዜ ምሴት ሲል ነው ፤ ባምሽት ጊዜ ነፋስ እንደሚነት ነው ትቢያ ይሆናሉ ፤

፲፫፡ ወይላህዉ ዘእንበለ ይጽባሕ ፣

እስራኤል ሰናክሬም መጣ ብለዋቸው ሳይነጋ ያለቅሳሉ፣ አንድም እነሰናክሬም ሳይነጋ ያለቅሳሉ ፤ ነገውን ድል የሚነሣ ጦር ሲሸበር ያድራልና ፤

ወይብሉ ይእተ አሚረ ቤተ ይሁዳ ዝንቱ ውእቱ ርስቶሙ ለእለ ወረሱነ፣

ያንጊዜ ነገደ ይሁዳ እንዲህ ይላሉ፤ ወርሰውን ለነበረ ለነብልጣሶር፤ አንድም ሊወርሱን ለነበሩ ለነሰናክሬም ይህ ጥፋቱ ርስታቸው ፣ ጉልታቸው ነው ይላሉ ፤

ወዝንቱ መክፈልቶሙ ለእለ በርበሩነ፣

ገንዘባችንን ለበዘበዙን ለእነብልጣሶር፤ አንድም ገንዘባችንን ሊበዘብዙን ለነበሩ ለነሰናክሬም ይህ ጥፋቱ ዕድል ፈንታቸው ጽዋ ተርታቸው ነው ይላሉ ፤

ምዕራፍ ፲፰

፩፡ አሌ ሎን ለአሕማር እለ ቦን ክንፍ ውስተ አፍላገ ኢትዮጵያ ፣

በኢትዮጵያ ወንዝ ለሚሄዱ ዓላማ ላላቸው መርከቦች ማለት አጃግሬ ላላቸው ለነሰናክሬም ወዮላቸው ፤

፪፡ ወይፌኑ ሐመረ ውስተ ባሕር ፣

መርከቡን ወደባሕር ይሰዳል፤

ወመጻሕፍተ ፣

ብትገብሩ ገብሩ ፣ ብትቀቅሉ ቀቅሉ፣ ያለዚያ እወጋችኋለሁ የሚል ፤ አንድም ይህን ያህል ግብር ቀረ፤ ይህን ያህል ግብር መጣ የሚል ደብዳቤ ይሰዳል፤

www.ethiopianorthodox.org

መልዕልተ ማይ ዘየሐውሩ መላእክት ረዋዕያን ኀበ አሕዛብ ነዊኃን ፣

ርሑቃን ሲል ነው ፤ በሩቅ ወዳ አሉ ፤ አሕዛብ በባሕር ላይ የሚሄዱ መልእክተኞች ፈጣኖች ናቸው ፤

መኑ እሙንቱ ሕዝብ ቅቡዓን ፣

ተስፋ ያጡ ወገኖች እሊህ እነማን ናቸው ፣ ተስፋማ እንዳጡ ይቀሩ ዘንድ እስራኤል አይደሉምን ፤

ወክዩዳን ፣

በመከራ የተረጋገጡ ኀዩያን ይላል፤ ቸል የተባሉ ዕዩያን ይላል፤ አውታታዎች ባካናዎች ፈዛዛዎች ፤

፫፤ ወይእዜሰ ኮሉ አፍላገ ምድር ከመ ሰብአ ብሔር ንቡራን ፣

ዛራ ግን አፍላገ ምድር እስራኤል ባላገር እንደመሆናቸው ጠላት ጠፍቶላቸው ተዘልለው ይኖራሉ ፤ አንድም ደሴት በውሀ እንዲከበብ በመከራ የተከበቡ እስራኤል እንደ ባላገር ፤

ወይሄልዉ በበበሐውርቲሆሙ ፣

በየሀገራቸው ይኖራሉ ፤ በበሐውርቲሆሙ ባገራቸው ይኖራሉ ፣ አንድም በበበሐውርቲሆሙ በሐውርቲሆሙ ይላል ፤

እንደ ንባቡ ተርጥም፤ ሀገራቸው በተድላ በደስታ ይኖራል ፤ በሀገራቸውም ሰዎችን መናገር ነው፤

ወከመ ትእምርት ይነሥእዎ እም አርእስተ አድባር ፣

በተራራ ላይ ያለ ዐላማ ከሩቅ እንዲታይ፣ የሰናክሬምን ጥፋት ከሩቅ ይሰሙታል ፤

ወይሰማዕ ከመ ቃለ ቀርን ፣

የነጋሪት ድምፅ ከሩቅ እንዲሰማ የሰናክሬም፣ የብልጣሶርም ሞት ከሩቅ ይታያል፤ ከሩቅ ይሰማል፤

፬፤ እስመ ከመዝ ይቤለኒ እግዚአብሔር ትጸንዕ ሀገርየ ከመ ብርሃነ መዓልት ቀትረ ፣

ብርሃነ ፀሐይ በቀትር ጊዜ እንዲጸና እግዚአብሔር አገሬ ኢየሩሳሌም ትጸናለች ብሏልና ትጸናለች ፤

ወከመ ዝናም በመዋዕለ ክረምት ዘእምቅድመ ማዕረር ፣

ከእህሉ መከር አስቀድሞ የሐምሌ የነሐሴ ዝናም እንዲጸና ፣ አንድም ለዝናም ቅሉ መከራ አለው ፤ ብሎ ከሐምሌ፣ ከነሐሴ አስቀድሞ በግንቦት ፣ በሰኔ የለቆው ዝናም እንዲጸና ፣ አገሬ ኢየሩሳሌም ትጸናለች አለ፤ አንድም ትጸናለች ብሏልና ትጸናለች ፤

፭፣ ጎሊቆ ጽጌ ወቆዕ ፣

አበባው ረግፎ ይጨረቋል ፤

ወይፈሪ ፍሬ መጺጸ ፣

ብሱሉም ይላል ያፈራል ፤

ወይገምዱ አስካሉ ደቂቅ በማዕፀድ፣

ልጆች ፍሬውን በማጭድ ይቈርጣሉ ፤

፮፤ ወይትበውሁ ላዕሌሁ አዕዋፈ ሰማይ ወአራዊተ ገዳም ፣

አራዊት አዕዋፍ ይሠለጥኑበታል ፣ በመከር ጊዜ የማይበላ የለምና ፤ አንድም ጎሊቆ ጽጌ ሰናክሬም መንግሥን መናገር ነው ፤ ወቆዕ ፣ ቦኑ ግልፎ ልበል ብሎ ማሰቡን መናገር ነው ፤ ወይፈሪ ፍሬ መጺጸ ቦኑ ግልፎ ማለቱን መናገር ነው ፤ ወይገምዱ አስካሉ ደቂቅ በማዕፀድ ፣ መላእክት የሰናክሬምን ሠራዊት ያጠፋሉ ፤

ወይመትሩ ሠርያ ፣

መላእክት ሰናክሬምን ያጠፋሉ፤ ደቂቅ አላቸው ፣ ስለንጽሕናቸው (ጥቅስ) ንጽሐሙ ለሕፃናት ዕደው ወአንስት በነፍሶሙ ወሥጋሆሙ ከመ መላእክት እንዲል (ማር.ይስ. አን. ፵፬ ፣ ፩) ፤

ወይትበውሁ ላዕሌሁ አዕዋፈ ሰማይ ወአራዊተ ምድር ፣

በሰናክሬም አዕዋፍ አራዊት ይሠለጥኑበታል ፤ አሥራ ስምንት ዕልፍ ከአምስት ሺህ ሰው ተቀብሮ አያልቅምና፤ አንድም ጎሊቆ ጽጌ ብለህ መልስ ፤ ብልጣሶር መንግሥን መናገር ነው፤ ወቆዕ ብልጣሶር በዓሕሉ ፈትፍታችሁ አብሉበት፤ በጽዋው ቀድታችሁ አጠጡበት ልበል ብሎ ማሰቡን መናገር ነው ፤ ወይፈሪ ፍሬ ብልጣሶር በዓሕሉ ፣ ፈትፍታችሁ አብሉበት በጽዋው ቀድታችሁ አጠጡበት ማለቱን መናገር ነው ፤ ይህስ እንደምነው ቢሉ ፣ ብልጣሶር ቂሮስ ዳርዮስን ድል ነስቶ ሺህ መኪንንት ይዞ በአዳራሽ ተገኘ ፤ ሲያበላ ሲያጠጣ ዛሬ እንጂ እስራኤል ከቂሮስ ከዳርዮስ ጋራ ተደርበው ሊወጉህ ነበር አሉት፤ ቢረዱስ ምን ጉድተው ፣ ባይረዱስ ምን ጠቅመው ፈጣሪያቸው አያድን ፣ አይራዳ አይታደግ ብሎ አያቱ ናቡከደነፆር አክብሮ ያኖረው የነበረውን ንዋየ ቅድሳቱን አምጥቶ በዓህሉ ፈትፍታችሁ አብሉበት ፤ በጽዋው ቀድታችሁ አጠጡበት አለ ፤ በጸሐሉ ፈትፍተው አብሉበት በጽዋው ቀድተው አጠ

www.ethiopianorthodox.org

ጡበት፤ (ጥቅስ) ወወጽአት አጽባ
እተ እደ ሰብእ ይላል ዳን. ፭፡፭፤
በሰው እጅ አምሳል ስለታየች
ነው እንጂ አጽባዕተ መልአክ
ናት (ጥቅስ) ወጸሐፈት ቅድመ
ኖኅት ኀበ ምረገ ዓረፍት ዳን.
ም. ፭ ፡ ፭ ፤በደጃፉ አንጻር ከግ
ድግዳው ጻፈች ፤ አንድም በደ
ጃፉ አንጻር ባለው በዓምዱ ላይ
ማኔ፣ ቴቄል፣ ፋሬስ ብላ ጻፈች፤
ንባቡ በእብራይስጥ፤ ትርጓሜው
በሱርስት ነው ፤ ከበላው አብ
ልቶ ከጠጣው አጠጥቶ የሚ
ያኖራቸው ጠቢባን መፈክራን
ነበሩት ፤ ይህንን አንብባችሁ
ተርጉማችሁ ንገሩኝ አላቸው፣
የማይሆንላቸው ሆነ ፤ በዚህ
አዝኖ ሳለ የብልጣሶር አያት
የዮርማሮዴቅ እናት የናቡከደ
ነፆር ሚስት ናት ፤ ዛሬ ልጄ
ምሳ አድርጎ ውሎ ነበር ፤ ምሳው
ቀናለት ይሆን ብላ ከእዳሪ ጠየ
ቀች ምሳውስ ቀንቶለት ነበር ፣
ነገር ግን እንዲህ ያለ ነገር አይቶ
አዝኗል አሏት ፤ ለዚህማ ርእሱ ፤
ዘወርቅን ለአባቱ ለናቡከደነፆር
የተረጐመለት ዳንኤል ያለ
አይደለምን ብላ ሴት ፈጣን
ናትና ቀሚሷን አንጠልጥላ
ገብታ ነገረችው ፤ ዳንኤልን አስ
ጠርቶ ይኸን አንብበህ ተርጥ
መህ ብትነግረኝ የመንግሥቴን
ሲሶ እሰጥኻለሁ ፣ ቢትወደድ
አድርጌ እሾምኻለሁ አለው፣
እሱም የገንዘብ የሹመት ፈቲው
የለበትምና ፣ ሀብትከኒ ይኩን
ለከ ወፍተ መንግሥትከኒ ሀብ
ለባዕድ ፤ ዳን. ፭፡፲፮-፲፯ ፤ ሹመ
ቱን ሽልማቱን ለሌላ ስጥ ፤
ይኸን ግን አንብቤ ተርጥሜ
እንግርኻለሁ አለው ፤ ማኔ ፤
ቴቄል ፤ ፋሬስ ብሎ አነበበ
ለት ፤ ማኔ ማለት ሰፈራ እግዚ
አብሔር ለመንግሥትከ ወሠ
ለጣ ማለት ነው ፤ ቴቄል ማለት
ደለዋ በመዳልው ወተረክበት
ሕፅፅተ ፤ በሚዛን መዘናት ሻ
ብላ ጐድላ ተገኘች ማለት ነው ፤
ፋሬስ ማለት ተውህበት መንግ
ሥትከ ፤ ለፋርስ ወለሜዶን ፤
መንግሥትህ ለፋርስ ለሜዶን
ተሰጠች ማለት ነው ብሎ ተረ
ጐመለት ፤ ምንም ክፉ ቢተረ
ጥምበት አሕዛብ መሐላቸውን
አጽኚ ናቸውና ቢትወደድ አድ
ርጎ ሹሞታል ፤ ወበይእቲ
ሌሊት ሞተ ብልጣሶር ፣ በዚ
ያች ሌሊት ብልጣሶር ሞተ ፣
ሲበጣበጥበት የዋለው ጠጅ
መልከኛው ሹመቱን ለዳንኤል
የሰጠበት ዳንኤል ሲተረጥም
ለት የሰማ ሌላ ሲመሰገንበት ፣
እኔ ልመስገንበት ብሎ ቸብቸቦ
ውን ቆርጦ በሣር ሸፍኖ ወስዶ

በጽንፈ ትዕይንት ለቂሮስ ለዳ
ርዮስ ሰጥቷቸዋል፤ ወይገምዱ
አስካሎ ደቂቅ በማዕፀድ፤ ቂሮስ
ዳርዮስ የብልጣሶርን ሠራዊት
ያጠፋሉ ፤ ወይመትሩ ፤ ቂሮስ
ዳርዮስ ብልጣሶርን ያጠፋሉ ፤
ወይትበውሁ ላዕሌሁ ፤ በብል
ጣሶር እስራኤል አሕዛብ ይሠ
ለጥኑበታል ፤ አንድም ኀሊቆ
ጽጌ ብለህ መልስ ፤ ዲያብሎስ
አኀዜ መንጦላዕት ቅሩበ እግዚ
አብሔር ሁኖ መፈጠሩን መና
ገር ነው ፤ ወቆዕ ፤ አነ ፈጣሪ
ሆሙ ለእሉ ፍጡራን ልበል
ብሎ ማሰቡን መናገር ነው ፤
ወይፈሪ ፤ አነ ፈጣሪሆሙ ለእሉ
ፍጡራን ብሎ ማለቱን መና
ገር ነው ፤ ወይገምዱ ፣ ሥላሴ
ሠራዊተ አጋንንትን ያጠፋሉ ፤
ወይመትሩ ፤ ዲያብሎስን ያጠ
ፋሉ ደቂቅ አላቸው ስለ ኀዳጌ
በቀልነታቸው ፣ (ታሪክ) ሥላሴ
መላእክትን ሕያዋን ፣ ለባው
ያን ፣ ነባብያን፤ ማዕምራን አድ
ርገው ፈጥረዋቸው ነበርና ፤
ምንት ንሕነ ወእምአይቴ መጻ
እነ ወመኑ ፈጠረነ ወሚመ
በበርእስነኑ ተፈጠርነ ተባባሉ ፣
ዲያብሎስን አኀዜ መንጦላዕት
ቅሩበ እግዚአብሔር አድርጎ
ፈጥሮት ነበርና አሻቅቦ ቢያይ
ድምፅ አጣ ፣ አቆልቁሎ ቢያይ
እንዲህ ሲባባሉ ሰማ ፤ አነ ፈጣ
ሪሆሙ ለእሉ ፍጡራን ልበል
ብሎ አሰበ ፤ አስቦም አልቀረ ፤
አነ ፈጣሪሆሙ ለእሉ ፍጡራን
አለ ፤ የሱ ወገኖች ከሦስት
ተከፈሉ ፤ የተጠራጠሩ አሉ ፤
አዎን ፈጠርኸን ያሉም አሉ ፤
ምን አንተ ትፈጥረን እኛ ፈጠ
ርንኸ እንጂ ያሉም አሉ ፤ ያን
ጊዜ መላእክት ሽብር ጸናባቸው፤
(ጥቅስ) ወአኀድዖሙ መልአከ
ሰላም በቃሉ እንዲል (አክሲ.
ዘዕሑ) መልአኩ ቅዱስ ገብርኤል
ንቁም በበህላዌነ እስከ ንረክቦ
ለአምላክነ ብሎ አጽንቷቸዋል፤
(አክሲ.) የተጠራጠሩት በአየር
ቀርተዋል ፤ አዎን ፈጠርኸን
ያሉት ወደዚህ ዓለም ወርደዋል፤
ምን አንተ ትፈጥረን እኛ ፈጠ
ርንኸ እንጂ ያሉት አብረውት
ወርደዋል ፤ (ጥቅስ) ቦ ዘወድቀ
ውስተ አየር ወቦ ዘወድቀ ውስተ
ምድር፣ ወቦዘወድ ቀውስተ
እንጦርጦስ ዘውእቱ መትሕተ
ታሕቲት እንዲል (አክሲማሮስ)
ከዚያ በኋላ ጨርሰው ሳይክዱ
ብሎ ብርሃንን ፈጥሮላቸው ያው
ዕውቀት ሁኗቸው ቅዱስ ቅዱስ
ቅዱስ ብለው አመስግነዋል ፤
ወይትበውሁ ምእመናነ እስራ
ኤል ፣ ምእመናነ አሕዛብ ይሠለ
ጥኑበታል ፤

www.ethiopianorthodox.org

፯፡ ወይእተ አሚረ ያበውኡ መሥ
ዋዕተ ለእግዚአብሔር ጸባዖት ሕዝብ
ትሑታን እምሕዝብ ዓቢያን ፣

ያንጊዜ ሰናክሬም በጠፋ ጊዜ
አሥሩ ነገድ ተማርከው የቀሩ
ሁለቱ ነገድ ፡ አንድም ከሰናክ
ሬም የቀሩ ሁለቱ ነገድ ለአሸ
ናፊ እግዚአብሔር መሥዋ
ዕት ያቀርባሉ ፡ አንድም ከአብ
ርሃም የተወለዱ፡ አንድም ከእ
ንቢታ ከክህደት የቀሩ ምእመ
ናን ለእግዚአብሔር መሥዋዕት
ያቀርባሉ ፡

እምይእዜ ወእስከ ለዓለም ፣

ከዛሬ ጀምሮ ለዘለዓለሙ ፡

፰፡ ወሕዝብሰ ዘይትአመን ይትከየድ
ዘሀሎ ውስተ ፈለገ ብሔሩ በጎበ ተሰ
ምየ እግዚአብሔር ጸባዖት በደብረ
ጽዮን ፣

በጣዖቱ የሚታመን በሀገሩ
ሰፍሮ የነበረ ሰናክሬም ፣ ይትከ
የድ በደብረ ጽዮን ፣ የእግዚአብ
ሔር ስም በተጠራባት በደብረ
ጽዮን ይጠፋል ፡ አንድም በሀ
ገሩ ወንዝ ያለ ጣዖትን የሚታ
መን ሰናክሬም የእግዚአብሔር
ስም በተጠራባት በደብረ ጽዮን
ይጠፋል ፡ የሠራዊቱን ጥፋት
መናገር ነው ፡ አንድም በኢየሩ
ሳሌም ሰፍሮ የነበረ በጣዖቱ
የሚታመን ሰናክሬም ይትከ
የድ ውስተ ፈለገ ብሔሩ ፣ በሀ
ገሩ ወንዝ ይሞታል ::

ምዕራፍ ፲፱

ጉባዔ

ራዕይ ዘበእንተ ግብፅ ፣

ግብፅ እንድትጠፋ አይቶ የተ
ናገረው ነገር ይህ ነው ::

፩፡ ናሁ እግዚአብሔር ይነብር ዲበ
ደመና ቀሊል ወይመጽእ ውስተ
ግብፅ ::

እነሆ እግዚአብሔር በኤርም
ያስ አድሮ ወደ ግብፅ ይመ
ጣል ፡

ወያድለቀልቅ ግብረ እደዊሆሙ
ለግብፅ እምቅድመ ገጹ ፣

የኤርምያስ ገጸ መዓቱ ከመገ
ለጡ የተነሣ የግብፃውያን የእጃ
ቸው ሥራ ጣዖት ይጠፋል ፡

ወይትቀጠቀጥ ልቦሙ በላዕሌሆሙ፣

በሳቸው ላይ ያለ ልቡናቸው
ይርዳል ፣ ይንቀጠቀጣል ፡

፪፡ ወይትነሥኡ ግብፅ ላዕለ ግብፅ፣

ግብፅውያን በግብፅውያን ላይ
ይነሣሉ ፡ እኩሌቶች ከባላገር
እኩሌቶች ከኤርምያስ እየሆኑ፡

ወይቀትል እኁ እኁዋሁ ፣

ወንድም ወንድሙን ይገድላል፡

ወሀገር ለሀገር ፣

አንዱ ሀገር አንዱን አገር ይወ
ጋል ፡ እኩሌቶች ከኤርምያስ
እኩሌቶች ከባላገር እየሆኑ ፡

ወሕግ ዲበ ሕግ ፣

ሕግ በሕግ ላይ ይነሣል ፣ ኤርም
ያስ የናንተን ሕገ ጣዖት ተዉ
የእኔን ሕገ ኦሪት ያዙ እያለ፡
አንድም ናሁ እግዚአብሔር ይነ
ብር ዲበ ደመና ቀሊል ብለሀ
መልስ ፡ እነሆ እግዚአብሔር
በኤርምያስ አድሮ ወደ ግብፅ
ይመጣል ፡ ወያድለቀልቅ ፣ ከኤ
ርምያስ ፊት መገለጥ የተነሣ
የግብፃውያን የእጃቸው ሥራ
ጣኦት ይጠፋል ፡ ወይትቀጠ
ቀጥ በሳቸው ላይ ያለ ልቡና
ቸው ይርዳል ፡ ይንቀጠቀጣል ፡
ይነሣል ፡ ይወድቃል ፣ ወይትነ
ሥኡ ግብፅ፣ ግብፃውያን በግብፃ
ውያን ላይ ይነሣሉ ፡ እኩሌቶች
ከባላገር ፣ እኩሌቶች ከኤርም
ያስ እየሆኑ ፣ ወይቀትል እኁ
እኁዋሁ ፣ ወንድም ወንድሙን
ይገድላል ፣ ወሀገር ለሀገር ፣
አንዱ ሀገር አንዱን ሀገር ይወ
ጋል ፣ እኩሌቶች ከኤርምያስ
እኩሌቶች ከባላገር እየሆኑ ፣
ወሕግ ዲበ ሕግ ፣ ሕግ በሕግ
ላይ ይነሣል ፡ ኤርምያስ ሕገ
ጣዖትን ተዉ፡ ሕገ ኦሪትን ያዙ
እያለ፡ አንድም ናሁ እግዚአብ
ሔር ይነብር ዲበ ደመና ቀሊል
ብለሀ መልስ ፡ እነሆ እግዚአብ
ሔር በዘባነ ማርያም ሕዙል ሁኖ
ወደ ግብፅ ይመጣል፡ ዲበ ደመና
ቀሊል ባለው ዲበ ደመና መፍ
ጠኒት ይላል ፡ ደመና ኢሳይያስ
የሚያሰኛት ይህ ነው ፡ ይኸንም
ደመናሰ ዘይቤ ይእቲኬ ማር
ያም እንተ ያረቶ ዲበ ዘባና
ብሎ ሊቁ ቅዱስ ያሬድ ወስዶ
ታል ፡ ወያድለቀልቅ የጌታ ገጸ
መዓቱ ከመገለጡ የተነሣ የግብ
ፃውያን የእጃቸው ሥራ ጣዖት
ይነዋወጣል ፡ ጣዖታተ ግብፅ ቀጥ
ቂጠ በበትሩ እንዲል ፡ ሰቆቃወ
ድንግል፡ አንድም ናሁ እግዚአ
ብሔር ይነብር ብለሀ መልስ ፣
እነሆ እግዚአብሔር በማርቆስ
አድሮ ወደ ግብፅ ይመጣል ፣
ወያድለቀልቅ ከማርቆስ ፊት
መገለጥ የተነሣ የግብፃውያን
የእጃቸው ሥራ ጣዖት ይጠፋል፡
አድያመ ግብፅ ዘአድመዐ
እንዘይሰብክ ወንጌለ እስከ
አዕርዐ ምሕራማተ ጣዖት እን
ዲል ፣ አባ ጊዮርጊስ ፡ ወይትቀ
ጠቀጥ ልቦሙ በላዕሌሆሙ ፣
በሳቸው ላይ ያለ ልቡናቸው ይር
ዳል ይንቀጠቀጣል ፡ ይነሣል ፣
ይወድቃል ፡ ወይትነሥኡ
ግብፅ ፣ ግብፃውያን በግብፃው
ያን ላይ ይነሣሉ ፡ እኩሌቶች

www.ethiopianorthodox.org

ከማርቆስ ፤ እኩሌቶች ከባላገር እየሆኑ ወይቀትል እጎዋሁ ፣ ወን ድም ወንድሙን ይገድላል ፤ ወሀገር ለሀገር አንዱ ሀገር አን ዱን ሀገር ይወጋል ፤ እኩሌቶች ከማርቆስ እኩሌቶች ከባላገር እየሆኑ ፣ ወሕግ ዲበ ሕግ፤ ሕግ በሕግ ላይ ይነሣል ፤ ማርቆስ ሕገ አሪትን ተዉ ሕገ ወንጌ ልን ያዙ እያለ ፤

፫፤ ወትደነግፅ ነፍሶሙ ለግብፅ በላዕሌሆሙ ፣

የግብፃውያን ልቡናቸው ትደነ ግጣለች ፤

ወእመይጥ ምክሮሙ ፣

ምክራቸውን እለውጠዋለሁ ፤

ወይሴአልዎሙ ለአማልክቲሆሙ ወለ ጣያቶሙ ፣

ካህናቱን ጣያታቱን ይጠይቋ ቸዋል ፤

ወለእለ ይትናገሩ በታሕተ ምድር ፣

ሙት አስነስተን እናናግራለን የሚሉትን ፤

ወለእለ በፃውዕ ፣

በምትሐት በፀውያ ቢል፣ ስመ አጋንንትን ጠርተን እናናግራ ለን የሚሉትን ይጠይቋቸዋል ፤ እንዲህ እንዲህ የሚያደርጉትን

፬፤ ወአገብአሙ ለግብፅ ውስተ እደ ሰብእ አለ እኩየ ቅኔ ይቀንይዎሙ፣

ግብፃውያንን ክፉ አገዛዝ በሚ ገዟቸው ሰዎች እጅ እጥላቸዋ ለሁ ፤

ወለነገሥት አለ እኩየ ኮነኔ ይኬ ንንዎሙ ፣

ነገሥታቱን ም ጽኑ አገዛዝ በሚገዟቸው ሰዎች እጅ እጥላች ዋለሁ ፤ አንድም ኮነኔ ይኬንን ዎሙ ፣ ክፉ ቅጣት በሚቀጣ ቸው በነገሥታቱ እጅ እጥላች ዋለሁ ፤

ከመይዝ ይቤ እግዚአብሔር ጸባዖት፣

አሸናፊ እግዚአብሔር እንዲህ አለ ፤

፭፤ ይሰትዩ ግብፅ ማየ አምጥቃ ባሕር፣

ግብፃውያን ከባሕሩ አጠገብ ከአ ሸዋው እየጫሩ ውሃውን ይጠ ጣሉ፣

እስመ ይነጽፉ ወይየብሱ ኮሉ አፍላገ ማይ ፣

ውሃ የሚሔድበት ወንዙ ሁሉ ይደርቃልና ፤ ድርቅ ሁኖ አን ድም የናቡከደነፆር ወገን ጠጥ ቶት ፤

፮፤ ወይነጽፉ አፍላገ ማይ ኀበ ይቀ ውሙ ፣

ፈሳሾች ውሆች ሁሉ ከፃሙ ባት ይደርቃሉ ፣ ድርቅ ሁ

አንድም የናቡከደነፆር ወገን ጠጥቶት ፤

ወኮሉ ያመ ብርዕ ወሕለት ፣

ቀርቀሃው ሸንበቆው ይደር ቃል ፤ ወኮሉ ሐመልማለ ሣዕር ዘጥቃ ፈለግ ፣ በወንዝ አጠገብ የሚበቅለው ፈላው ቀጤማው ፤

፯፤ ወኮሉ ዘይዘራዕ ድንጋገ ፈለግ ይየብስ ወየዐብር ፣

በባሕር አጠገብ የሚዘራው እንደ አቆምብራ ያለው ይደር ቃል ፣ ያራል ፣ አቆምብራ ባሕር ሸሽ ነው ፤

ወይቁኅዙ መሠግራን ፣

ዓሣ ወጋሮች ያዝናሉ ፤

ወይበክዩ ኮሉሙ እለ ያወርዱ መሣ ግሪሆሙ ውስተ ፈለግ ፣

መረባቸውን በባሕር የሚጥሉ ዓሣ ወጋሮች ያለቅሳሉ ፤

ወእለ ይረብቡ መርበብቶሙ ፣

መረባቸውን የሚነዙ ፤

፰፤ ወይላህዉ መሠግራን ፣

ዓሣ ወጋሮች ያዝናሉ ፤

ወይትነፈሩ እለ ያስተሣንዩ መሣ ግረ ብቱክ ፣

የተቈረጠውን የሚቀጥሉ፣ ያደ ፈውን የሚያጥቡ፣ የተኰፋተረ ውን የሚያረቱ፣ ወይም የሚ ያፍታቱ ዓሣ ወጋሮች ያዝናሉ፤ ያፍራሉ ፣ በየቋንቋው መላልሶ ተናገረው፣ ብዙ ስም አለውና መረብ፣ መግለቦ ፣ መንዝጎ ፣ መቃጥን፣ ዘረመትር ይለዋልና፤

ወእለ ይትጌበሩ ሜላተ የሐምሙ ፣

ነጭ ሐር የሚአዘጉት (የሚያዘ ጋጁት) ያዝናሉ ፤

፱፤ ወይትመሰዉ ኮሉሙ እለ ይት ጌበሩ በመዳልው ፣

የሐር ኩብ የሚያኰቡ ሁሉ እንደሰም ይቀልጣሉ ፤ ዱድ የሚባል ያፍ አለ፤ ነጭ ቅጠል በልቶ ነጭ ሐር፣ ጥቁር ቅጠል በልቶ ጥቁር ሐር ፣ ቀይ ቅጠል በልቶ ቀይ ሐር፣ ይዘጋል (ያደ ራል)፤ ድርቅ ሆኖ እሱ የሚበ ላው አጥቶ ጠፍቶባቸው፤ አን ድም እሱስ የሚአዘጋው አንድ ነጭ ሐር ነው ብሎ፣ እነሱ የወ ደዱትን ያገቡታል ፤ አንድም ጥቁር ቅጠል ቀይ ቅጠል ሲቀ ቡት የወደዱትን ይሆንላቸው ነበር ፤ ድርቅ ሆኖ የሚበላው አጥቶ ሙቶ ነጋድያን ያዝናሉ፤

ወየሐምም ነፍሶሙ ፣

ልቡናቸው ያዝናል ፤ ባለመግለ ቦዎችም ውሀው ሲደርቅ ዓሣው አልቆ ያዝናሉ ፤

www.ethiopianorthodox.org

፲፡ ወየዐብዱ መላእክተ ጣኔዎስ ፣

የጣኔዎስ አለቆች አእምሮአቸውን ያጣሉ ፤

ወትለስሕ ምክሮሙ ለጠቢባን ፣

የጦር ጥበብ እናውቃለን የሚሉ ሰዎች ምክራቸው አልጫ ትሆ ናለች ማለት ትጠላለች ፤

ወለመካርያነ ነገሥት ፣

የነገሥታቱ መካሮችም ምክራቸው ትጠላለች ፤

፲፩፡ ወእፎ ትብልዎ ለንጉሥ ደቂቀ ጠቢባን ንሕነ ፣

ፈርዖንን እኛ የኢያኔስ የኢያንበሬስ ልጆች ነን እንደምን ትሉታላችሁ ፤

ወደቂቀ ነገሥት ቀደምት ፣

የቀደሙ የነገሥታት ልጆች ነን እንደምን ትሉታላችሁ ፤ አንድም ደቂቀ ቄዴም ይላል ፣ የምሥራቅ ልጆች ነን እንደምን ትሉታላችሁ ? የምሥራቅ ልጅ ብልህ ነው ይባላልና ፤

፲፪፡ አይቴ ሀለዉ ይእዜ ጠቢባኒከ ፣

ፈርዖንን እንዲህ ይለዋል ፣ ዐዋቆችህ ወዴት አሉ ? አንድም ፈላስፎችህ ወዴት አሉ ?

ይዜንዉከ እስኩ ወይንግሩከ ምንት ውእቱ ፤ ምክሩ ለእግዚአብሔር ዘመ ከረ ላዕለ ግብፅ ፣

እግዚአብሔር በግብፃውያን ላይ የመከረው ምክር ምን እንደ ሆነ እስኪ ይንገሩህ ፤ አንድም እግዚአብሔር በግብፃውያን ላይ የመከረው ምክር ምንድር ነው እስኪ ይንገሩህ ፤

፲፫፡ ጎልቁ መላእክተ ጣኔዎስ ፣

እነዚያስ አይነግሩህምና እኔ ልንገርህ ይላል ኢሳይያስ ፣ የጣኔዎስ አለቆች ጠፉ ፤

ወጠፍኡ መላእክተ ሜምፎስ ፣

የሜምፎስ አለቆችም ጠፉ ፤

ወስሕቱ ግብፅ በበሕዘቢሆሙ ፣

ግብፃውያን በየወገናቸው ሳቱ፤

እስመ አስሐቶሙ እግዚአብሔር በጋኔን መስሕት ፣

እግዚአብሔር በሚያስት ጋኔን አስቷቸዋልና ፤ አሁን እግዚአብሔር የሚያስታቸው ሁኖ አይደለም ፤ ረድኤት መንሣቱን መናገር ነው ፤ (ጥቅስ) ወወሀቦሙ መንፈሰ ድንዙዘ በይነ ምንት አስሐትከነ እግዚኦ እምፍኖትከ ሠናይት እንዳለው ያለ ነው ፤ ሮሜ. ፲፩፡፲፭ ፤

፲፬፡ ወስሕቱ ግብፅ በዙሉ ምግባሮሙ ፣

ግብፃውያን በሚሠሩት ሥራ ሁሉ ሳቱ ፤

ከመ ዘይስሕት ሰኩር ወከመ ዘአንኮለሉ ደም ፣

የሰከረ ሰው እንዲስት ደም እንዳፈታበት ሰው ሳቱ ፣

፲፭፡ ወኢይትረከብ ለግብፅ ውስተ ምግባሮሙ ዘቦ ርእስ ወዘነብ ፣

ግብፃውያን በሚሠሩት ሥራ ሁሉ ሎሌ ያለው ጌታ ፣ ጌታ ያለው ሎሌ አይገኝም ፤

በጥንቱ ወበማኅለቅቱ ፣

ጌታ ከሎሌው ጋራ ፣ ሎሌ ከጌታው ጋራ አይገኝም ፣

፲፮፡ ውእተ አሚረ ይከውኑ ግብፅ ከመ አንስት በፍርሃት ወበረዓድ ፣

ያን ጊዜ ግብፃውያን በፍርሀት በረዓድ ተይዘው እንደ ሴቶች ይሆናሉ ፤

እምቅድመ ገጹ ለእግዚአብሔር ፀባዖት እንተ ያወርድ ላዕሌሆሙ ሕማመ፣

መከራ ከሚያመጣባቸው አሸናፊ ከሚሆን ከእግዚአብሔር ገጸ መዓት የተነሣ ፤

፲፯፡ ወይከውንዎሙ ግብፅ መግረምቶሙ ለብሔረ አይሁድ ፣

ለነገደ አይሁድ ሲል ነው፤ ግብፃውያን በነገደ አይሁድ ግሩም ይሆኑባቸዋል ፣ ርዱን እያለ ወደ ግብፅ ይልኩባቸው ነበርና እነዚያ ሲጠፉ አይተው ግሩም ይሆኑባቸዋል ፤

ወእምኀመ ሰምዑ ብሔረ አይሁድ ይፈርሁ በእንተ ምክረ እግዚአብሔር ፀባዖት እንተ መከረ ላዕለ ግብፅ ፣

አሸናፊ እግዚአብሔር በግብፃውያን የመከረውን ምክር በሰሙ ጊዜ ነገደ ይሁዳ ይፈራሉ ፤

፲፰፡ ውእተ አሚረ ብዙኃት አህጉረ ግብፅ ይነብባ በነገረ ከነዓን ፣

ያን ጊዜ በግብፅ አውራጃ ያሉ ብዙ አገሮች በዕብራይስጥ ቋንቋ ይናገራሉ፤ አንድም በረዓብ ዘማ ሃይማኖት ያምናሉ ፤ አንድም በነገረ ከናንዩ ይላል በንዑሳን ካህናት ትምህርት ያምናሉ ፤

ወየኀብራ አህጉረ ግብፅ በስመ እግዚአብሔር እግዚአ ኀይል ፣

እግዚአ ኀይል በሚሆን በእግዚአብሔር ስም አምነው ብዙ አገሮች በምግባር በሃይማኖት አንድ ይሆናሉ ፤ አንድም በምግባር በሃይማኖት አንድ ሁነው፣ በስመ እግዚአብሔር ይሰመያ፣ በእግዚአብሔር ስም ይጠራሉ ማለት ሕዝበ እግዚአብሔር ይባላሉ ፣

www.ethiopianorthodox.org

፲፱፡ ወትከውን አሐቲ ሀገር ምሥዋዖ ለእግዚአብሔር ውስተ ደወሎሙ ለብሔረ ግብፅ ፣

በግብፅ አውራጃ ያለች አንዲት ሀገር ምሥዋዐ እግዚአብሔር ትሆናለች፤ ኤርምያስ አንድም ማርቆስ ያረፈባት፤ አንድም ጌታ ያረፈባት እስክንድርያ ደብረ ቍስቋም አስቄጥስ ፤

ወቤተ እግዚአብሔር ትከውን ፣

ቤተ እግዚአብሔር ትሆናለች ፤

፳፡ ትእምርተ እግዚአብሔር በብሔረ ግብፅ ለዓለም ፣

ይትረከብ ያለበት ነው በግብፅ ለዘለዓለሙ የእግዚአብሔር ምልክት ይገኛል ፣ የመስቀል ምልክት አስኬማ ፤ የአክሊለ ሦክ ምልክት ቆብ ይገኛል ፤

እስመ የአወይዉ ኀበ እግዚአብሔር እምእለ ይረውድዎሙ ፣

ግብፃውያን ከከበቧቸው ሰዎች የተነሣ ይጮኻሉ ይጨነቃሉና፤

ወይፌኑ ሎሙ ብእሴ ዘያድኅኖሙ፣

የሚያድናቸው ኤርምያስን ፤ አንድም በጥሊሞስን ይሰድላቸዋል፤ አንድም እስመ የዐወይዉ ምእመናን ነፍሳት፣ ከከበቧቸው ከአጋንንት የተነሣ ይጮኻሉና

ወይፌኑ የሚያድናቸው ማርቆስን፤ አንድም ጌታን ይሰድላቸዋል ፤

ይኴንንሂ ወያድኅንሂ ፣

ያስተምራል ፣ ያድናል ፤

፳፩፡ ወትከውን ግብፅ ትእምርተ ለእግዚአብሔር ፣

ግብፅ የእግዚአብሔር ምልክት ትሆናለች፣ እስክንድርያ ደብረ ቍስቋም አስቄጥስ ፣ ወየአምርዎ ግብፅ ለእግዚአብሔር ግብፃውያን እግዚአብሔርን በሕግ በአምልኮት ያውቁታል ፤

ውእተ አሚረ ይሠውዑ መሥዋዕተ ለእግዚአብሔር ፣

ያንጊዜ ለእግዚአብሔር መሥዋዕት ይሠዋሉ ፤

ወይበፅዑ ብፅዓተ ፣

ስዕለቱን ይሳላሉ ፤

ወያበውኡ መባአ ፣

መባዓውን ያቀርባሉ ፤

፳፪፡ ወይቀስፎሙ እግዚአብሔር መቅሠፍተ ፣

ከዚህ አስቀድሞ እግዚአብሔር በመከራ ይገርፋቸዋል ፤

ወያሐይዎሙ ሕይወተ ፣

ኋላ ግን ያድናቸዋል ፤

ወእምዝ ይትመየጡ ኀበ እግዚአብሔር ፣

ከዚህ በኋላ በሕግ በአምልኮት ወደ እግዚአብሔር ይመለሳሉ፤

ወይሰምዖሙ ወይሣሃሎሙ ፣

ልመናቸውን ይሰማቸዋል ይቅር ይላቸዋል ፤

፳፫፡ ይእተ አሚረ ይከውን ፍኖተ ግብፅ ኀበ ፋርስ ፣

ያንጊዜ የግብፅ ጎዳና ወደ ፋርስ ይሆናል ፤

ወፋርስኒ የሐውሩ ኀበ ግብፅ ፣

የፋርስም ሰዎች ወደ ግብፅ ይሄዳሉ ፍቅር ሁነው ፤

ወግብፅኒ ይበውኡ ኀበ ፋርስ ፣

ግብፃውያንም ወደፋርስ ይገባሉ ፤

ወይትቀነዩ ግብፅ ለፋርስ ፣

ግብፃውያን ለፋርስ ይገዛሉ አለ የፈቃድ፤ አንድም በዘመነ ሐዲስ አራቱ ሊቃነ ጳጳሳት አንድ ይሆናሉ ፤ አንድም ሃይማኖት ተናውጾም እንደሆነ ሥርዓትም ፈርሶ እንደሆን ያንን ለማጽናት የፋርሱ ወደ ግብፅ የግብፁ ወደ ፋርስ ይሄዳሉ ፤

፳፬፡ ይእተ አሚረ ይከውኑ እስራኤል ሣልሶሙ ለግብፅ ወለፋርስ ፣

ያንጊዜ እስራኤል ለግብፅና ለፋርስ ሦስተኛ ይሆናሉ ፤ ምነው የሃይማኖት መደበኞችማ እስራኤል አይደሉምን ቢሉ አሕዛብን ደስ ለማሰኘት፤ አንድም የያዘው አንቀጹ የአሕዛብ ነውና ፤ አንድም የቍጥር ግብፅ፣ ፋርስ፣ እስራኤል ፣ አንድም ባለሲሶ እንጂ ማለት ባለርስት ማለት ነው ፤ እንደዚህም ሁሉ የሃይማኖት መደበኞች እስራኤል ናቸውና ፤

ወይትባረኩ በምድር እንተ ባረካ እግዚአብሔር ፣

እግዚአብሔር ባከበራት በግብፅ ይበዛሉ ፤

፳፭፡ ወይባርኮሙ እግዚአብሔር ፀባዖት ፣

አሸናፊ እግዚአብሔር ያበዛቸዋል ፤

እንዘ ይብል ቡሩክ ሕዝብየ ዘውስተ ግብፅ ወዘውስተ ፋርስ ፣

በፋርስ በግብፅ ያሉ ወገኖቼ ብሩካን ናቸው ብሎ ፤

ወርስትየኒ እስራኤል ፣

ማደሪያዎቼ እስራኤል ንዑዳን ክቡራን ናቸው ብሎ ::

www.ethiopianorthodox.org

ምዕራፍ ፳

፩፡ በዓመተ ቦአ ጣንታ ውስተ አዛጦን አመ ፈነዎ ፆርና ንጉሠ ፋርስ፣

ፆርና ያለው ስልምናሶርን ነው፣ ብዙ ስም አለው፣ አኔሜሴር፣ ኢያሪም ያሆ ፆርና ስልምናሶር ይለዋል ፤ ጣንታ ቢትወደዱ ነው፤ ፆርና በላከው ጊዜ ጣንታ አዛጦን በገባበት ወራት ፤ አንድም ሌላ ፆርና ሌላ ጣንታ ነው፤

ወቀተላ ለአዛጦን ፣

አዛጦንን በወጋት ጊዜ ፤

ወአስተጋብዐ ንዋያ ፣

ገንዘቧን እጅ ባደረገ ጊዜ ፤

፪፡ ይእተ አሚረ ነበቦ እግዚአብሔር ለኢሳይያስ ወልደ አሞፅ ፣

ያንጊዜ እግዚአብሔር የአሞፅ ልጅ ኢሳይያስን ተናገረው ፤

ወይቤሎ ልበስ መንጸፈ ላዕለ ውስተ ሐቈከ ፣

ምንጣፉን ያለገበር ልበስ አለው ለምልክት ፤

አንድም አእትት መንጸፈ ይላል ፣ ምንጣፍነቱን አርቀው ማለት ልበሰው ፣

ወፍታሕ አሣዕኒከ እምእገሪከ ፣

ጫማህን ከእግርህ አውልቅ ፤

ወሑር ዕራቀከ ዘእንበለ አሣዕን ፣

ያለጫማ ባዶህን ሂድ ፤

ወገብረ ከማሁ ፣

እንዳለው አደረገ ፤

ወሖረ ዕራቆ ዘእንበለ አሣዕን ፣

ያለጫማ ባዶውን ሄደ ፤

፫፡ ወይቤ እግዚአብሔር በከመ ሖረ ኢሳይያስ ቀ'ልዔየ ዕራቆ ዘእንበለ አሣዕን ፣

እግዚአብሔር እንዲህ አለ ወዳጄ ኢሳይያስ ያለጫማ ባዶውን እንደሄደ ፤

ከማሁ ይከውን ትእምርት ወመንክር ሠለስተ ዓመተ በግብፅ ወሠለስተ ዓመተ በኢትዮጵያ ፣

ሦስት ዓመት በግብፅ፣ ሦስት ዓመት በኢትዮጵያ ተአምራት ይደረጋል ፤ እንዲህ ስላለ የግብፅ ሦስት ዓመት የምድያም ሦስት ዓመት ስድስት ማለት አይደለም፤ ሁሉም አንድ ጊዜ ነው ፤ በሦስቱ ዓመት በኢትዮጵያም በግብፅም ተአምራት ይደረጋል ሲል ነው ፤

፬፡ ወከማሁ ይወስዶሙ ንጉሠ ፋርስ ለግብፅ ወለኢትዮጵያ ፣

አሁን እንደ ተናገርሁት ናቡከ ደነፆር የግብፅን የምድያምን ሰዎች ማርኮ ይወስዳቸዋል ፤

ወይዜውውዎሙ ለአዕሩጊሆሙ ወለ ወራዙቲሆሙ ዕራቃኒሆሙ ዘእንበለ አሣዕን ፣

ሽማግሎችን ጐልማሶችን ማርከው ያለጫማ ይወስዷቸዋል፤

ወይትቀፈጽ ኃሣሮሙ ለግብፅ ፣

የግብፃውያን መከራቸው ይገለጣል ፣

፭፡ ወይትመውዑ ግብፅ ምስለ ኢትዮጵያ ፣

ግብፃውያን ከኢትየጵያ ሰዎች ጋራ ድል ይነሣሉ ፤

ወይትኃፈሩ ግብፅ ምስለ እለ ተወከሉ ቦሙ ፣

ግብፃውያን ይረዱናል ብለው ከሚታመኗቸው ከእስራኤል ጋራ ይጠፋሉ ፤ አንድም እሳቸው ይረዱናል ብለው ከሚታመኗቸው ከፉጥ ፣ ከልዳ ከኢትዮጵያ ጋራ ይጠፋሉ ፤

፮፡ ወይብሉ ይእተ አሚረ እለ ይነብሩ ውስተ ኢየሩሳሌም ፣

በኢየሩሳሌም የሚኖሩ ሰዎች ያንጊዜ እንዲህ ይላሉ ፤

እፎ ኪያነ ያድኅኑነ ወርእሶሙ ኢይክሉ አድኅኖ እምንጉሠ ፋርስ ፣

ራሳቸውን ከፋርስ ንጉሥ ማዳን ያልተቻላቸው እኛን እንደምን ያድኑናል ይላሉ ::

ምዕራፍ ፳፩

ጉባዔ

ነገር በእንተ ብሔረ በድው ፣

ባቢሎን እንድትጠፋ የተናገረው ነገር ይህ ነው ፤

፩፡ ዓውሎ ኀለፈ እምገዳም ውስተ ብሔረ በድው ፣

ቂሮስ ከፋርስ ወደባቢሎን ሄደ፤ ዓውሎ አለው ስለ ፍጥነቱ ሁለቱንም ገዳም አላቸው ፤ በምድረ በዳ ዘር ተክል እንዳይገኝ በነዚህም ምግባር ፣ ሃይማኖት አይገኝምና ፤

ወመጽአ እምብሔር ግሩም ፣

ከፋርስ ወደ ባቢሎን መጣ ፣ ግሩም አለ፤ የፈረስ ምስል መመለክ የተጀመረ በፋርስ ነውና ፤

፪፡ ዘአስተርአየኒ ዕፁበ ዜና ነገረኒ በእንቲአሁ ፣

ስለ ቂሮስ የታየኝ የተነጋገረኝ መልአክ ጭንቅ ነገር ነገረኝ ማለት ዔዋዌን፤ አንድም ድንቅ ነገር ነገረኝ አለ ሚጠትን ፤

ዘክህደኒ ኪያየ ይክህድ ፣

እኔን የካደ ነቢዩን መካዱ ነው፤

ወዘኒ አበሰ ሊተ አበሰ ፣

እኔን የበደለ ነቢዩን መበደሉ ነው ፤ አንድም ዘክህደኒ ፣ ነቢ

www.ethiopianorthodox.org

ዩን የካደ ኪያየ ክህደ ፣ እኔን መካዱ ነው ፤ ወዘኒ አበሰ ነቢ ዩን የበደለ ሊተ አበሰ እኔን መበደሉ ነው ይላል እግዚአብ ሔር ፤ (ጥቅስ) ዘኪያክሙ ሰምዐ ኪያየ ሰምዐ ዘኪያክሙ ዐበየ ኪያየ ዐበየ እንዲል ፤ ማቴ. ፲ ፣ ፵ ፤

፫ ፤ ሰብአ ኤላምሂ ወተናብልተ ሜዶን ይመጽኡ ኀቤየ ፣

የኤላም ሰዎችና የሜዶን መል እክተኞች ወደኔ ይመጣሉ ፤ ኤላም በፋርስ መካከል ያለች አገር ናት ፤ አንድም ፋርስ ናት ፤ አንድም በፋርስና በሜዶን መካ ከል ያለች ሀገር ናት ፤

ይእዜሰ እቴክዝሂ ፣

ዛሬ ግን በእስራኤል ጥፋት አዝ ናለሁ ፤

ወእትናዘዝሂ ፣

ፍርዱ ስላልቀረ እረጋጋለሁ ፣ አንድም እቴክዝሂ ፣ በአሕዛብ ጥፋት አዝናለሁ ወእትናዘዝሂ ፍርዱ ስላልቀረ እረጋጋለሁ ፣ ነቢይ ለሁሉ ያዝናልና ፣ አን ድም ርኅሩኅ እግዚአብሔር አድሮበታልና ፤ አንድም እቴክ ዝሂ በዜዋዌ አዝናለሁ ፣ ወእት ናዘዝሂ በሚጠት እረጋጋለሁ ፤

፬ ፤ በእንተ ዝንቱ ይቀጸቅጸኒ ሐቋየ ፣

ስለዚህ ነገር ወገቤን ይፈጨ ኛል ፤ ይቈረጥመኛል ፤ ወአኀ ዘኒ ማሕምም ከመ እንተ ትወ ልድ ፣ እንደምትወልድ ሴት ምጥ ያዘኝ ፤

አበስኩ ወኢትጸመመኒ ፣

በደልሁ ቸል አትበለኝ ፤

ጌገይኩ ወኢትነጽረኒ ፣

በደልሁ በዓይነ መዓት አትመ ልከተኝ ፣ በራሱ እንዲህ አለ ፣ አንድም በሕዝቡ ተገብቶ ፤

፭ ፤ ወስሕተ ልብየ ፣

ልቤ ከእውነተኛ ሕግ ወጥቶ ሳተ ፤

ወደፈነኒ ኃጢአትየ ፣

ኃጢአቴም በመከራ ሸፈነኝ ፣ በራሱ እንዲህ አለ ፣ አንድም በሕዝቡ ተገብቶ ፤

ወደንገፀኒ ነፍስየ ፣

ልቡናዬ ደነገጠብኝ ፤

፮ ፤ ሠርዑ ማዕደ ፣

እስራኤል ማዕድ ሠሩ ፤

በልዑ ወሰትዩ ፣

በሉ ጠጡ ፤

ወተንሥኡ መላእክት ፣

አለቆች ሲጠግቡ ሊዘፍኑ ተነሡ ፤

ወተረሠዩ በንዋየ ሐቅሎሙ ፣

በበዳፀብታቸው ተፀረሩ ፤ አን ድም ሠርዑ ማዕደ ፣ እስራኤል ለጣዖት ማዕድ ሠሩ ፣ በልዑ በሉ ጠጡ ወተንሥኡ ፣ አለቆች ለጣዖቱ ሊዘፍኑ ተነሡ ፣ ወተ ረሰዩ በበዳፀብታቸው ተፀረሩ ፤ አንድም ሠርዑ እስራኤል ማዕድ ሠሩ ፣ በልዑ ወሰትዩ ፤ በሉ ጠጡ ፤ ወተንሥኡ የባቢ ሎን አለቆች እስራኤልን ለመ ማረክ ተነሡ ፣ ወተረሰዩ በበዳፀ ብታቸው ተፀረሩ ፤ አንድም ሠርዑ የባቢሎን ሰዎች ማዕድ ሠሩ ፤ በልዑ ወሰትዩ ፣ በሉ ጠጡ ፣ ወተንሥኡ ፣ አለቆች ሲጠግቡ ሊዘፍኑ ተነሡ ፤ ወተረሰዩ በበዳ ፀብታቸው ተፀረሩ ፤ አንድም ሠርዑ ፣ የባቢሎን ሰዎች ለጣ ዖት ማዕድ ሠሩ ፣ በልዑ በሉ ጠጡ ፣ ወተንሥኡ የባቢሎን አለቆች ለጣዖቱ ሊዘፍኑ ተነሡ ፤ ወተረሰዩ በበዳፀብታቸው ተፀ ረሩ ፤ አንድም ሠርዑ የባቢሎን ሰዎች ሰባ ዘመን ማዕደ ተድላ አደረጉ ፣ በልዑ በሉ ጠጡ ፣ ወተንሥኡ ቂሮስ ዳርዮስ ፣ የባቢሎንን ሰዎች ለመማረክ ተነሡ ፤ ወተረሰዩ በበዳፀብታ ቸው ተፀረሩ ፤ አንድም ሠርዑ ቂሮስ ዳርዮስ በጽንፈ ትዕይ ንት ማዕድ ሠሩ ፤ በልዑ በሉ ጠጡ ፣ ወተንሥኡ ቂሮስ ዳር ዮስ አስተጋብተው አሰባስበው ተነሡ ፤ ወተረሰዩ በበዳፀብታ ቸው ተፀረሩ ፤

፯ ፤ እስመ ከመዝ ይቤለኒ እግዚአ ብሔር ፣

እግዚአብሔር እንዲህ ብሎኛ ልና ፤

ሑር ፍጡነ ወፈኑ ሰብአ ዓይን ፣

ፈጥነህ ሂደህ ጉበኛ ስደድ ፤

ዘርእየ ይነግር ወዘሰምዐ ይዜኑ እም ኀቤሆሙ ፣

ከነዚያ የሰማውን የሚያወራ ያየውን የሚናገር ጉበኛ ስደድ ብሎኛልና ፤

፰ ፤ ወፈነውኩ ሰብአ ዓይን ፣

ጉበኛ ሰደድሁ ፤

ወርእየ ክልኤተ መስተጽእናነ ፣

በአህያ በግመል የተቀመጡ ሁለት ሰዎችን አየ ፤

አሐዱ ይዜዓን አድገ ፣

አንዱ በአህያ ተቀምጧል አለ ፤ ዳርዮስ ነው ፤ አህያ ጠላቱን ተበ ቅሎ አያጠፋም ፤ እሱም ጠላቶ ቹን ተበቅሎ አላጠፋምና ፤

www.ethiopianorthodox.org

አንድም አህያ አጭር ነው ፤ የእ
ርሱም ዘመነ መንግሥቱ አጭር
ነውና ፤

ወአሐዱ ይዜዓን ገመለ ፣

አንዱ በግመል ተቀምጧል አለ ፤
ቂሮስ ነው ፤ ግመል መስተበቅል
ነው ፣ እሱም ተበቅሎ ጠላቶቹን
አጥፍቷልና ፤ አንድም ግመል
ረጅም ነው ፤ የሱም ዘመነ መንግ
ሥቱ ረጅም ነውና ፤ ወሣልሱ
ይዜዓን ፈረሰ ቀይሐ የሚል ይገ
ኛል ፤ ሦስተኛው በሐመር ፈረስ
ተቀምጧል አለ ፤ ቅዱስ ሚካ
ኤል ነው ፤ የባቢሎንን ሰዎች
ደም አፈሳለሁ ሲል በሐመር
ፈረስ ተቀምጦ ይታየዋል ፤
ወድምፆሙሰ ድምፀ ብዙኃን
መስተፅዕናን ፣ ድምፃቸው ግን
በፈረስ የተቀመጡ የብዙ
ሰዎች ድምፅ ነው ፤

፱፤ ወተጸውዐ አርያስ ሰብአ ዓይኑ
ለእግዚአብሔር ፣

ሰብአ ዓይን ካለ ዘእግዚአብሔር
ለእግዚአብሔር ካለ ሰብአ ዓይኑ
ቢል በቀና ነበር ፤ ልማደ መጽ
ሐፍ ነው ፤ የእግዚአብሔር ጉበ
ኛው አርያስ ተጠራ ፤

ወይቤ ነየ አነ ፣

እነሆ እኔ አለሁ አለ ፤

ወይቤ ቆምኩ ኵላ ዕለተ ወኵላ
ሌሊተ ውስተ ትዕይንት

በከተማው አንድ መዓልት
አንድ ሌሊት ቆምኩ ፤

፲፤ ወመጽኡ መስተፅዕናን እምፍ
ኖት ፣

በፈረስ የተቀመጡ ሰዎች በጎ
ዳናው መጡ ፤

ተሠጥዉኒ ወይቤሉኒ ፣

መለሱልኝ እንዲህ አሉኝ ፣ ባቢ
ሎንሳ እንዴት ሆነች አልኋ
ቸው ፤

ወድቀት ባቢሎን ፣

ጠላት ባቢሎንን ይሁን ፣ ባቢሎ
ንስ ጠፋች አሉኝ ፤ አሁን የባቢ
ሎንን ጥፋት ከኢሳይያስ ሠውሮ
ለአርያስ ብቻ የገለጠለት ሁኖ
አይደለም ፤ የባቢሎንን ጥፋት
ያየ ኢሳይያስ ብቻ አይደለም ፣
አርያስም አይቷል ለማለት ምስ
ክር ለማብዛት ነው ፤ ምስክር
ከአንድ ሁለት ከሁለት ሦስት
ከሦስት አራት ይጸናልና ፤ አን
ድም አርያስን ቀኖና ግባ በለው
አለው ፣ አርያስ ቀኖና ገብቶ
ሲያይ ሁሉንም ኢሳይያስ
ያያል ፤ አንድም ቀኖና ግባ
በለው አለኝ ፣ ቀኖና ግባ አል
ሁት ቀኖና ገብቶ ሲያይ ወር
እየ ሁሉንም ኢሳይያስ ያያል ፣

አንድም ጌታ ለኢሳይያስ አር
ያስን ቀኖና ግባ በለው ሲለው
ኢሳይያስ አርያስ ቀኖና ግባ
ሲለው አርያስ ቀኖና ገብቶ የባ
ቢሎንን ጥፋት ሲያይ ኢሳይያ
ስም ያያል ፤

ወተቀጥቀጠ ኵሉ ጣዖታ ወኵሉ
ግብረ እደዊሃ ውስተ ምድር ፣

ጣዖቷ የእጇ ሥራ ሁሉ ጠፋ ፤

፲፩፤ ስምዑ እሉ ተረፍክሙ ፣

ከሞት የቀራችሁ እስራኤል
ስሙ ፤

ወእለሂ ተሐምሙ ስምዑ ዘሰማዕኩ
እምኀበ እግዚአብሔር ፀባዖት ፣

መከራ የምትቀበሉ እናንተ ከአ
ሸናፊው ከእግዚአብሔር ዘንድ
የሰማሁትን ነገር ስሙ ፤

አምላከ እስራኤል ዘዜነወኒ ፣

የእስራኤል ፈጣሪ የነገረኝን
ስሙ ፤ አንድም ዘዜነወኒና ዘሰ
ማዕኩ አንድ ወገን ነው ፤ ከእስራ
ኤል ፈጣሪ ከእግዚአብሔር የሰ
ማሁት የነገረኝን ስሙ አለ ፤
አንድም እየራሱ ለማውጣት
ከነገረኝ ከእግዚአብሔር የሰማ
ሁትን ስሙ አለ ፤

ነገር በእንተ ኤዶምያስ ፣

ኤዶምያስ እንድትጠፋ የተና
ገረው ነገር ይህ ነው ፤

፲፪፤ ፀውዖሙ ኀቤየ እምኀበ ሴይር ፣

ሴይር በኤዶምያስ ያለች ሀገር
ናት ፤ ከነዚያ የቀረበውን አንዱ
ንም አንዱንም ከሴይር ወደ
እኔ ጥራቸው ይለዋል ፤

ይዕቀቡ መዓልተ ወሌሊተ ፣

በመዓልትም በሌሊትም ይጠ
ብቁ ዘንድ ጥራቸው ፤

፲፫፤ እመኒ ተኀሥሥ ኀሥሥ ኀበ
ትነብር ወትበይት ሌሊተ ውስተ
ዖም በፍኖተ ዴዳን ቅድሜሆሙ
ለእለ ፀብዑከ ፣

ከተጣሉህ ሰዎች የተነሣ በደ
በቁ ጎዳና ሸሽተህ ሂደህ ከዛፉ
ሥር ቀን የምትውልበትን
ሌሊት የምታድርበትን ትሻ
ዘንድ ሻ እለው ዘንድ ጥራቸው ፤

፲፬፤ አምጽኡ እክለ እለ ትነብሩ
ብሔረ ቴማን ፣

በኤዶምያስ የምትኖሩ እህሉን
አምጡ በእውነቱ ፤ አንድም
ፍና ተሳልቆ ፤

፲፭፤ ወተቀበልዎሙ ለእለ አምሰጡ
እምብዙኃን እለ ተቀትሉ ፣

ከሞቱ ከብዙ ሰዎች ተለይ
ተው ፤ አንድም ከነዚያ አምል
ጠው የመጡትን ተቀበሏቸው ፤

ወእምብዙኃን እለ ጐዩ ፣

ከብዙ ሰዎች ተለይተው ፤ አን
ድም ከነዚያ ሸሽተው የመጡ
ትን ፤

www.ethiopianorthodox.org

ወእምብዙኃን ሰብአ ኩናት ፡

ጦር ከያዙ ከብዙ ሰዎች ሸሽ ተው፡ አንድም ከነዚያ አምል ጠው የመጡትን ፡

ወእምብዙኃን ሰብአ ሐሪ ፡

ፍላፃ ከያዙ ሰዎች ሸሽተው ፡ አንድም ከነዚያ ተለይተው የመጡትን ተቀበሏቸው ፡

ወአቅስስቲሆሙ ውሱቃት ፡

ቀስታቸው የተዘጋጀ ከሆነ አን ድም ቀስታቸው ከተቀፈረ ከአ ሕዛብ የዳኑትን ተቀበሏቸው ፡ ፍና ተሳልቆ ፡ አንድም እንዳለባ ቸው መናገር ነው ፡

ወእምብዙኃን እለ ወድቁ በውስተ ቀትል ፡

በሰልፍ ከሞቱ ከብዙ ሰዎች ተለ ይተው፡ አንድም ከነዚያ ሸሽ ተው የመጡትን ተቀበሏቸው ፡

፲፮፡ እስመ ከመዝ ይቤለኒ እግዚአ ብሔር ፡

እግዚአብሔር እንዲህ ብሎኛ ልና ፡

ዓዲ እምዓመት እስከ ዓመት የኀልቅ ወስቦሙ ወክብሮሙ ለደቂቀ ቄዳር፣

ዳግመኛ ከዓመት እስከ ዓመት ድረስ የእስማኤል ልጆች ባለጸ ግነታቸው ያልቃል ብሎኛልና ያልቃል ፡

፲፯፡ ወእለ ተርፉ ኀዳፍያን ወጽኑዓን እምደቂቀ ቄዳር ዮኀልቁ ይቤ እግ ዚአብሔር አምላክ እስራኤል ፡

ከእስማኤል ልጆች ጽኑዓን ኃያ ላን ከሚሆኑ ከጦር የዳኑት የእ ሥራኤል ፈጣሪ እግዚአብሔር በቀጠና ያልቃሉ አለ ::

ምዕራፍ ፷፪

ነገር በእንተ ቄላተ ጽዮን ፡

አህጉራተ ጽዮን ሲል ነው፣ በጽ ዮን በቆላውም በደጋውም የተና ገረው ነገር ይህ ነው ፡

፩፡ ምንተ ኮንክሙ ይእዜ ኮልክሙ ዘወረግሙ አንሕስተ ለከንቱ ፡

ከንቱ ጣዖትን ለማምለክ ወደ ግንቡ ለምን ወጣችሁ፡ አንድም ከንቱ ነገርን ለመሻት ወደ አም ባው ለምን ወጣችሁ ፡

፪፡ ወመልዓት ሀገርክሙ አውያተ ፡

ሀገራችሁ ልቅሶን መላች ፡

ቅቱላንኪኒ ኢኮኑ ቅቱላነ በኲናት ፡

የሞቱትም በጦር ተዋግተው የሞቱ አይደሉም ፡

አብድንትኪኒ ኢኮኑ አብድንተ ቀትል ፡

ሬሳዎችሽም ባፅር ታጥቀው ዘገር ነቅንቀው ጋሻ ነጥቀው ሲዋጉ የሞቱ አይደሉም ፡

አላ ኮሉሙ መላእክትኪ ጐዩ ፡

አለቆችሽ ሁሉ ሲሸሹ በባሕር ጠልቀው በገደል ወድቀው ሞቱ እንጂ ፡

፫፡ ወለእለ ተዒወዉ አሕመምዎሙ በመዋቅሕት ፡

የተማረኩትንም በግዞት መከራ አጸኑባቸው ፡

ውኀያላንኪኒ ነዋኑ ጐዩ ፡

ኃያላኖችሽም ፈጽመው ሸሹ፡

፬፡ በእንተ ዝንቱ ኀድጉኒ እብኪ መሪረ፡

ስለዚህ ነገር ጽኑዕ ልቅሶ አለቅስ ዘንድ ተዉኝ ፡

ወኢታብዝኑ አስተብቍዖትየ ፡

እኔን አብዝታችሁ አትማል ዱኝ ፡

በእንተ ቅጥቃጤሃ ለወለተ ሕዝ ብየ ፡

የወገኔ ልጅ በመከራ ስለተቀ ጠቀጠች ፡

፭፡ እስመ ዕለተ ሀከክ ፡

የፀብ የክርክር ቀን ነውና ፡

ወኀጕል ፡

የጥፋት ቀን ነውና ፡

ወኪደት ፡

በመከራ የሚረገጡበት ቀን ነውና ፡

ወስብረት እምነበ እግዚአብሔር ጸባኦት ላዕለ ቄላተ ጽዮን ፡

ከአሸናፊ ከእግዚአብሔር ዘንድ ታገዘሀ በጽዮን በቄላውም በደጋ ውም ድል የመነጣት ቀን ነውና ፡

ወይጐይዩ ንዑሰሙ ወዓቢዮሙ ፡

ታላቁም ታናሹም ይሸሻሉ ፡

ወየዓይሉ ውስተ አድባር ፡

ተራራውን ይዞራሉ ፡

፮፡ ወሰብአ ኤላም ይነስኡ ምጥንጳ፣

የኤላም ሰዎች ግን ጐራንጕሬያ ቸውን (ጐራዴያቸውን) ይይ ዛሉ ፡

ወሰብእ መስተቃትላን ፡

አርበኞች ሰዎች ፡

ወመስተዕዕናነ አፍራስ ፡

በፈረስ የተቀመጡት ፡

ወትዕይንተ ሠራዊት ፡

የአርበኞች ሠራዊት ፍላፃቸውን ይይዛሉ ፡

፯፡ ወይመልዕ ሠረገላ በውስተ ቄላ ትኪ ፡

ሠረገላው በቄላው በደጋው ይመላል ፡

ወየዐግቱ አፍራስ አናቅጻኪ ፡

በፈረስ የተቀመጡ ሰዎች በር ሽን ይከባሉ ፡ አንድም ኃያላ ኑን ይከባሉ ፡

www.ethiopianorthodox.org

፰፡ ወያርኅውዎን ለአናቅጸ ይሁዳ ፣

የይሁዳን በር ይከፍታሉ ፤ አን
ድም የይሁዳን አርበኞች ያጠ
ፋሉ ፤

ወይፈትኑ ይእተ አሚረ አብያቲ
ሆሙ ለዓበይተ ሀገር ፣

ያንጊዜ የነገሥታቱን የመኳን
ንቱን ቤት ይበዘብዛሉ ፤

ወያርኅዉ መዛግብቲሆሙ ለዓበይተ
ቤተ ዳዊት ፣

የዳዊት ወገኖች የሆኑ የመኳን
ንቱን ሣጥን ይከፍታሉ ፤

፱፡ ወይሬእዩ ብዝኖሙ ወይሰወጡ
ውስተ ሀገር ፣

እስራኤል የነናቡከደነፆርን
ብዛት አይተው ወደ ኢየሩሳ
ሌም ይመለሳሉ ፤ አንድም እነና
ቡከደነፆር እስራኤልን አይተው
ለግዳይ ለምርኮስ እኒህ ይበቁ
ናል ብለው ይመለሳሉ ፣

እስከ ምጥማቃት ዘትካት ፣

እስከ ቀድሞው መዋኛ እስከ
ቀድሞው መታጠቢያ ድረስ ይሸ
ሻሉ ፤ አንድም እነናቡከደነፆር
እስከዚያ ድረስ ሂደው ይማ
ርኳቸዋል ፤

ውነበ አውፅኡ ማየ ማዕከለ ፪ ዓረ
ፍት ፣

ሕዝቅያስና ኢሳይያስ በአምስ
ቱና በስድስቱ ቆመ ብእሲ መካ
ከል በጸሎት እስከ አፈለቁት
ውሀ ድረስ ይሸሻሉ ፤ አንድም
እስከዚያ ድረስ ሂደው ይማርኳ
ቸዋል ፤

ወኀበ አብያቲሃ ለኢየሩሳሌም ፣

እስከ ኢየሩሳሌም ቤት ድረስ
ይሸሻሉ ፤ አንድም እስከዚያ
ድረስ ሂደው ይማርኳቸዋል፤

ወዓረፍተ ጥቅማ ፣

እስከ ግንቡ ቅጽር ድረስ ይሸ
ሻሉ ፤ አንድም እስከዚያ ድረስ
ሂደው ይማርኳቸዋል ፤

፲፡ ወኢነጸርክምዎ ለዘፈጠራ ቅድመ ፣

አስቀድሞ የፈጠራት እግዚአ
ብሔርን አላሰባችሁትም ፤

ወኢያእመርክምዎ ለዘገብራ ፣

ኢየሩሳሌምን የፈጠራት እግዚ
አብሔርን አላወቃችሁትም ፤

፲፩፡ በእንተዝ አምጽአ እግዚአብ
ሔር ይእተ አሚረ ብካየ ፣

ስለዚህ ነገር ያንጊዜ እግዚአ
ብሔር ልቅሶን ፤

ወላህ ወመንጸፈ ወብልባሌ ፣

ኃዘንን ምንጣፍ መልበስን
ጨርቅ መልበስን አመጣ ፤

፲፪፡ አንትሙሰ ገበርክሙ በዓለ ፣

እናንተ ግን ለጣዖቱ በዓል አደ
ረጋችሁ ፤ አንድም በዓል ለማ
ድረግ ከዚህ አስቀድሞ ፍሥሐ
ወኃሤተ ፣ ተድላ ደስታ አደረ
ጋችሁ ፤

ወጠባሕክሙ አልህምተ ወአባግዐ ፣

ላሙን በጉን አረዳችሁ ፤

ወበላዕክሙ ሥጋ ወሰተይክሙ ወይነ ፣

ሥጋ በላችሁ ወይን ጠጣችሁ ፣

እንዘ ትብሉ ንብላዕ ወንስተይ
ጌሠመ ንመውት ፣

እንብላ እንጠጣ ነገ እንሞታ
ለን እያላችሁ ፣

፲፫፡ ወተሰምዐ ዝንቱ ነገር ውስተ
ዕዘኒሁ ለእግዚአብሔር ጸባዖት ፣

ይህ ነገር ከአሸናፊ ከእግዚአብ
ሔር ጆሮ ደርሶአልና ፤

ወኢትሠረይ ለክሙ ዛቲ ኃጢአት
ክሙ ፣

ይች ኃጢአታችሁ አትሠረይ
ላችሁም ፤ ንስሐ ከገቡ አይሠረ
ይላቸውም ማለት አይደለም ፤
ንስሐ አይገቡም ሲል ነው ፤

እስከ ትመውቱ ፣

እስክትሞቱ ድረስ አትሠረይላ
ችሁም ፤ ከሞቱ በኋላ ይገባሉ
ማለት አይደለም፤ ፍጻሜ የሌ
ለው እስከ ነው ፤

፲፬፡ ከመዝ ይቤ እግዚአብሔር ፀባ
ዖት ፣

አሸናፊ እግዚአብሔር እንዲህ
አለ ፤

ሑር ቤተ ሳምናስ ወልደ ጣምያ ፣

ከጣምያ ልጅ ከሳምናስ ቤት
ሂደህ ፤

፲፭፡ ወበሎ ምንት አምጽአከ ዝየ ፣

ከዚህ ምን አመጣህ በለው ፤ አን
ድም ለምንት መጻእከ ዝየ ፤
ከዚህ ለምን መጣህ በለው
ምናሴ ወልደ ምናሴ ነው ፤

ወምንተኑ ተሀበልከ በዝየ ትግበር
ለከ መቃብረ ፣

በዚህ መቃብር ትሠራ ዘንድ
ለምን ደፈርህ ፤

ወአውቀርከ ለከ ዝኅረ ውስተ ኰኵሕ
ዘውስተ ወግር ፣

ከኮረብታው በታች ባሸዋው
መቃብር ለምን ሠራህ ፤

ወገበርከ ለከ ቤተ ፣

ቤት ለምን ሠራህ ፤

፲፮፡ ወናሁ እግዚአብሔር ጸባዖት
ያወፅአከ እምህየ ፣

እነሆ አሸናፊ እግዚአብሔር ከቤ
ትህ ያወጣሃል ፤

ወይቀጠቅጠከ ፣

በመከራ ያጠፋሃል ፤

ወይሰልበከ አልባሲከ ፣

መጎናጸፊያህን ይገፍሃል ፤

www.ethiopianorthodox.org

ወአክሊለ ክብርከ ፣

የምትከበርበት ኵፌትህን ፤

፲፯፡ ወይገድፈከ ውስተ ብሔረ ሕማም ፣

ተማርከህ በሄድክበት ሀገር በመ ከራ ይጥልኻል ፤

ወትመውት በህየ ፤

በዚያ ትሞታለህ ፤

ወዮኀስሮ ለሠረገላከ ሠናይ ፣

ይሰብሮ ሲል ነው ያማረውን ሠረገላህን ይሰብረዋል ፤

ወይከይድዎ ለቤተ መልአክከ ፣

የሰንባላጥን ወገን በመከራ ይረ ጋግጡታል ፤

፲፰፡ ወትሠዐር እምግብከ ፣

ከሹመትህ ትሻራለህ ፤ አንድም አጥብቆ እምግብከ ከከተማ ያወጣኻል ፤

ወእምኵናኒከ ፣

ከአገዛዝህ ይሽርኻል ፤ ይህ ምናሴ ወልደ ምናሴ እስራኤል ድኅረ ሚጠት በሴት በልጅ ምክንያት በወደዱበት ይኖራሉ ፣ ከዘመ ዶቹ ተለይቶ ሂዶ ለሰንባላጥ ገባ ፣ እሱም ዘመዶቹን ጠልቶ እኔን አምኖ ቢመጣ ብሎ አክብሮ አኑሮታል ፤ የሰንባላጥን ልጅ አግብቶ በኢየሩሳሌም የሚሠራ ውን ሥራ እየሠራ በባቢሎን የሚኖር ሁኗል ፤ ይህንን እግዚ አብሔር አልወደደለትም ፤ አን ድም በመሥዋዕት ነገር ተጣ ልቶ ከሰንባላጥ አገር ወረደ ፤ ከኔ የመጣ ዘመዶቹን ጠልቶ እኔን ወዶ አይደለም ብሎ ደብ ተራ ሠርቶ አሥራት ቀዳም ያት አውጥቶ ያኖረው ነበር ፤ ከዚያ በመኖሩም ምክንያት ዝለፈው ብሎት ጽፎ ይልክበ ታል ፤

፲፱፡ ውእተ አሚረ እጼውዖ ለቍል ዔየ ኤልያቄም ወልደ ኬልቅዩ ፣

ኤልያቄም ያለው ሕርቃሎስ ነው ፤ ያንጊዜ የኬልቅዩስን ልጅ ወዳጅ ሕርቃሎስን እጠራዋ ለሁ ፤

፳፡ ወአለብሶ አልባሲከ ፣

መጐናጸፊያህን አለብሰዋለሁ ፤

ወእሁቦ አክሊለከ ፣

ኵፌትህን እሰጠዋለሁ ፣

ወአሜግቦ ምግበከ ፣

ሹመትህን እሰጠዋለሁ ፤

ወአኳንኖ ምኵናኒከ ፣

አገዛዝህን አስገዛዋለሁ ፤

ወእሬስዮ መትከለ ውስተ መካን ቅዱስ ፣

በክቡር ቦታ በኢየሩሳሌም ኵላብ አደርገዋለሁ ፣

፳፩፡ ወይሰቀሉ ቦቱ ከመ ንዋየ ልሕ ኵት ንዑሶሙ ወዓቢዮሙ ፣

ብርሌ ብርጭቆ በኵላብ እንዲ ሰቀል ታላቁም ታናሹም በሱ ይጸናሉ ፣

ወእሁቦ መራኑተ ቤተ ዳዊት ፣

የዳዊትን ወገን ሥልጣን እሰጠ ዋለሁ ፤

ለእመ አርኀወ ውእቱ አልቦ ዘየዐቡ ፣

እሱ ቢሾም የሚሽር የለም ፤

ወለእመ ዐፀወ አልቦ ዘያርኁ ፣

እሱ ቢሽር የሚሾም የለም ፤

፳፪፡ ውእተ አሚረ ከመዝ ይቤ እግ ዚአብሔር ፣

ያንጊዜ እግዚአብሔር እንዲህ አለ ፤

ለያንቀልቅል መትከል ፣

ሕርቃሎስ ይጥፋ አለ ፤

ወይሰበሩ እለ ስቁላን ላዕሌሁ ፣

በሱ ጸንተው የሚኖሩ ሁሉ ይጥፉ ፤

፳፫፡ ወካዕበ እሠይም መልአከ ምእ መነ ለብሔር ፣

ዳግመኛ በኢየሩሳሌም የታመነ ሌላ ሹም እሾማለሁ አለ ፤

ወአነብሮ ዲበ መንበረ ክብር ዘቤተ አበሁ ፣

የአባቱ ወገኖች በሚቀመጡበት ክብር ባለው ዙፋን አስቀምጠዋ ለሁ ፤

ለንዑሶሙ ወለዓቢዮሙ ፣

ታላቁንም ታናሹንም ያጸናቸ ዋል ፤

፳፬፡ ወካዕበ ይቤ እግዚአብሔር ፀባ ዖት ፣

አሸናፊ እግዚአብሔር ዳግመኛ እንዲህ አለ ፤

ለያንቀልቅል ብእሲ ዘይቀውም ውስተ ብሔር ጽኑዕ ፣

በኢየሩሳሌም የተሾመው ሹም ይጥፋ አለ ፤

ወይደቁ እለ አስመኩ ላዕሌሁ ፣

በሱ የጸኑ ሁሉ ይጥፉ አለ ፤ ስምንቱ ደቂቀ ክስሙና ይን እየተተካኩ መንግሥት ከክህ ነት እየደረቡ ገዝተዋል ፡፡

ምዕራፍ ፳፫

ጉባኤ

ነገር በእንተ ጢሮስ ፣

ጢሮስ እንድትጠፋ የተናገ ረው ነገር ይህ ነው ፤

www.ethiopianorthodox.org

፩፡ ለየዓውይዋ አሕማረ ኬልቄዶን እስመ ተነገሩላ ፣

ተሰብረዋልና የኬልቄዶን መር ከቦች ያልቅሱ ፤ አንድም የኬል ቄዶን መርከቦች ተሰብረዋልና የጢሮስ ሰዎች ያልቅሱ ፤ የሰዎ ችን ለመርከቦች ሰጥቶ ተናገረ፤

አሕማረ ኬልቄዶን እስመ ተኃጕላ፣

የኬልቄዶን መርከቦች ጠፍተ ዋልና ፤

ወኢይመጽኣ እንከ እምብሔረ ኬጢ ም ፣

ከእንግዲህ ወዲህ ከሮም መርከ ቦች አይመጡም ፤ ኢያመጽአ ቢል እንግዲህ ወዲህ ወርቅን ብርን አያመጡም ወያመጽእ ዎሙ ዒዋ ይወስድዎሙ ሲል ነው፣ ሣርከው ይወስዷቸዋል ፤ አንድም ነቢዩ በባቢሎን እንዳለ ሁኖ ያመጽእዎሙ አለ፤ (ጥቅስ) ወያመጽኡ ክብራ ለወለተ ጽዮን እንዲል ፤ (ኢሳ. ፷ ፡፲፫) ፤

፪፡ ምንተ ይመስሉ እለ ይነብሩ ደሴተ ፈላስያን እመፈንቂስ እለ ዐደዉ ብሔረ ማይ ብዙኅ ፣

ብሔረ ማይ ባለው ባሕረ ማይ ስፋሕ ይላል ፤ ከፈንቂስ ተሰደው ሰፊ ውሀ ያለበትን ተሻግረው በደሴት የሚኖሩ ሰዎች ማንን ይመስላሉ ፤ አንድም ማንን ይመ ስላሉ ቢሉ ፤

፫፡ ከመ ዘርዕ ዘይትቄለጥ አመ ማዕ ረር ፣

ከዛሬ ነገ ከነገ ማግስት እናጭደ ዋለን ሲሉ በረድ መትቶት አን በጣ በልቶት የሚቀረውን አዝ መራ ይመስላሉ ፤ አንድም ዘኢይ ትቄለጥ ይላል ፤ ፈርሶ ቧሽቶ የሚቀረውን ዘር ይመስላሉ ፤

እለ ቦኡ አሕዛብ ፈላስያን ፣

እለ ዐደዉ ያለውን እለ ቦኡ ብሎ አመጣው ፤ ወደ ደሴት የገቡ ፈላስያን አሕዛብ የማይ ለወጠውን ዘር ይመስላሉ ፤

፬፡ ተነፈሪ ሲዶና ፣

ሲዶና እፈሪ ፤

ትቤ ባሕር ኢፀነስኩ ወኢሐመምኩ፣

ጢሮስ ወንድ ልጅ አልፀነስኩም ወንድ ልጅ አላማጥሁም አለች፤

ወኢወለድኩ ወኢያልሐቁ ወራዙተ፣

ወንድ ልጅ አልወለድሁም ወንድ ልጅ አላሳደግሁም አለች ፤

አላ ደናግለ ፣

ኮኑ ያለበት ነው፤ የግብር ደና ግል ሆኑ እንጂ ፤

፭፡ እስመ እመኩመ አልሐቅዎሙ ይፄውውዎሙ ባቢሎን ፣

ከሳደግኋቸው በኋላ የባቢሎን ሰዎች ሣርከው ይወስዷቸዋ ልና ፣

፮፡ ሕማማ ለጢሮስ ሖረ ኬልቄዶን፣

የጢሮስ መከራዋ ናቡከደነፆር ወደ ኬልቄዶን ሄደ ፤ በፊት ጢሮስን ወግቶ በኋላ ኬልቄዶ ንን ወግቷልና ፤ አንድም የጢ ሮስዜና ጥፋቷኬልቄዶን ደረሰ፤ አንድም ለንግድ መጥተው አል ቀው ቀርተዋልና ፤ አንድም ረዳት ሁነው መጥተው አልቀ ዋልና ፤

ወየዐወይዉ ላቲ እለ ይነብሩ ደሴተ፣

በደሴት የሚኖሩ ሰዎች ያዝኑላ ታል ፤

፯፡ ዛቲ ዕረፍት ኢኮነት እንተአ ክሙ ፣

ይች ዕረፍት ለናንት የምትገባ ችሁ አይደለም ፣

አላ ተዓወዉ ፣

ተሣርካችሁ ሂዱ እንጂ ፤

፰፡ መኑ ከመዝ ገብረ ላዕለ ጢሮስ፣

በጢሮስ ላይ እንዲህ ያደረገ ማነው ፣

አኮኑ ይእቲ ዘተዐቢ ወትኤይስ እም ኮሉ ብሔር ፣

ከሀገሩ ሁሉ በምትበልጥ በምት ከብር ፤

ወኢይክሉ ሜጣ ክቡራን መላእክተ ምድር ፣

የከበሩ የዚህ ዓለም አለቆች ዋጋ ዋን የማይችሉ በሆነች በጢ ሮስ እንዲህ ያደረገ ማነው ?

አኮኑ እግዚአብሔር ፣

እግዚአብሔር አይደለምን ፤ አን ድም እንዲህ ያደረገ ማነው ቢሉ ፤

፱፡ እግዚአብሔር ዐባያት መከረ ይሥ ዐር ኮሉ ጽዕለቶሙ ለክቡራን፣

አሸናፊ እግዚአብሔር የባለ ጸጎ ችን ስድብ ያጠፋ ዘንድ መከረ፤

ወያነስሮሙ ለኮሉሙ ዓበይተ ምድር ፣

የዚህን ዓለም መኳንንቱን ሁሉ ያጐሰቍላቸው ዘንድ መከረ ፤ ዘኢይክሉ ሜጣ አለ ፤ የጢሮስ ሰው ጢሮሳዊ ግምጃ ይዞ ወደ ኢየሩሳሌም ሄደ ፤ በከተማ ያሉ መኳንንት ካህናት ዋጋ ንገር አሉት ፤ ሦስት መቶ አላቸው፤ ቁም ነገር ቢጠይቁት ዋዛ ፈዛዛ ይናገራል አሉት ፤ መቶ አምሳ አላቸው ይልቁንስ ቁም ነገሩን ንገረን አሉት ፤ መቶ አላቸው፤ እንዲህ እያሉ ወደአምሳ አዩ በት ፤ ብረት ምጣድ አምጥቶ በፊታቸው ቢቆላው ሐሩ ነዶ

www.ethiopianorthodox.org

ወርቁ ብቻ አምሳ ወቄት ሁኗል ፡

፲፥ ተገበሩ እንኳ ፣

ከእንግዲህ ወዲህስ እረሱ፣ ቆፍሩ አሁን እርሻ ቁፋሮ ዛር ጋር ሁኖ አይደለም፤ንግድየ ለመደን ሰው እረስ፣ ቆፍር ቢሉት ዛር ጋር ይሆንበታልና።

እስመ ኢይመጽኣ አሕማር እምኬልቄዶን ፣

ከኬልቄዶን መርከቦች አይመጡምና ፡

፲፬፥ ወትደክም እንኳ እዴሆሙ ለእለ መንገለ ባሕር ፣

ከእንግዲህ ወዲህ በጢሮስ ያሉ ሰዎች እጃቸው ከመወርወር ቃላቸው ከመምከርት ደክማለች ፡

እንተ አምዕዐቶሙ ለነገሥት ፣

ነገሥታቱን የምታበሳጫቸው ብሎ ለጢሮስ ቀጠለ ፤ አንድም ጢሮስ የዋዛ አገር ናት ፤ ነገሥታቱን የምታበሳጫቸው አይደለምን ፤እንወጋታለን ብለው ይሄዳሉ ፤ በባሕር የተከበበች ናትና የማይሆንላቸው ሁኖ ከዳር ቁመው በዘንጋቸው ተክዘው ይመለሳሉና እንዲህ አለ፤

እስመ እግዚአብሔር ፀባኦት አዘዘ ያጥፍዑ ኃይለ ከነዓን ፣

አሸናፊ እግዚአብሔር ጢሮስ ሲዶናን ያጠፋ ዘንድ አዘዘ፤ ጢሮስ ሲዶና የከነዓን ልጆች፤ ናቸው፤ (ጥቅስ) ወከነዓን ወለዶ ለሲዶን በኵሩ እንዲል ፤ (ዘፍ. ፲፡፲፭)፤ አንድም በኢያሱ ጊዜ ከነዓንን ያጠፋ ዘንድ አዝሏልና።

እንዘ ይብል ኢተዐምዕዋ ለወለተ ጽዮን ፣

የጽዮንን ልጅ አትበድሏት ብሎ፣

፲፪፥ ወእመኒ ሖርከ ብሔረ ኬጤ ምን በህየኒ ኢተዐርፍ ፣

ወደሮምም ብትሄድ ከዚያ አታርፍም ፡

፲፫፥ እስመ ለብሔረ ኬጤምን አማሰንዋ ፋርስ ፣

ሮምን የፋርስ ሰዎች አጥፍተዋታልና ፤

ወወድቁ አረፋቲሃ ፣

ቅጽሯ ፈረሰ ፤ አንድም አርበኞቿ ጠፉ ፤

፲፬፥ ወአውዐይዋ ሰብአ ባቢሎን ፣

የባቢሎን ሰዎች አቃጠሏት ፤

እስመ ተሰብረ ፀወንክሙ ፣

አምባችሁ ፈርሷልና ፤ አንድም ንጉሣችሁ ድል ተነስቷልና ፤

፲፭፥ ወውእተ አሚረ ትነብር ጢሮስ ሰብዓ ዓመተ መጠነ መዋዕለ ንጉሥ፣

ያንጊዜ ጢሮስ ኢየሩሳሌም ንጉሥ ጠፍቶባት የነበረውን ዘመን ያህል ትኖራለች ፤ሰባ ዘመን ንጉሥ ጠፍቶባት ኑራለችና ፤ አንድም የዳዊትን ዘመን ያህል ትኖራለች፤ በዚህ ዓለም ሰባ ዘመን ኑሯልና ፤

ወመጠነ መዋዕለ ሰብእ ፣

ኢየሩሳሌም ሰው ጠፍቶባት የነበረውን ዘመን ያህል ትኖራለች፤ አንድም የሰውን ዘመን ያህል ትኖራለች ፤

ወእምድኅረ ሰብዓ ዓመት ትከውን ጢሮስ ከመ ዘማ ኀላዪት ፣

ከሰባ ዘመን በኋላ ጢሮስ እንደ ተላይቶ ዘፋኝ ሴት ትሆናለች፤

፲፮፥ ወትነሥእ መሰንቆ ወትዘብጥ ፣

መሰንቆውን ይዛ ትመታለች፤

ወብዙኀ ተኀሊ ፣

እንደመለከተኛ ወርቹንወርቹን እያለች ብዙ ትዘፍናለች ፤

ከመ ይዘከርዋ ፣

ቂሮስ ዳርዮስ በግብር ያስቧት ዘንድ ፤ አንድም ሥላሴ በምሕረት ያስቧት ዘንድ ፤

እስመ ተረስዐት ፣

ከጌቶቿ ከቂሮስ ከዳርዮስ ግብር ተዘንግታለችና፤ አንድም ከልበ ሥላሴ ተዘንግታለችና ማለት ጦር ታዝዛባታልና ፤

፲፯፥ ወእምድኅረ ሰብዓ ዓመት ይሔውፃ እግዚአብሔር ለጢሮስ በሣህል፣

ከሰባ ዘመን በኋላ እግዚአብሔር ጢሮስን በይቅርታ ይጐበኛታል ፤

ወትገብዕ ካዕበ ከመ ትካት ፣

እንደቀደመው ወደመሆን ትመለሳለች ፤

ወትከውን ምቅዳሐ ለኵሉ ነገሥተ ዓለም ፣

የነገሥታቱ ሁሉ መገናኛ ትሆናለች ፤አንድም ለነገሥታቱ ሁሉ ገበያ ትሆናለች ፤ አንድም የነገሥታቱ ሁሉ መናገሻ ትሆለች ፤

ወትከውን ምስትግባረ ፣

የነገሥታት ሁሉ መናገጃ ትሆናለች ፤

ወዕሤቱ ለቅዱስ እግዚአብሔር፣

ይትወሀባ ያለበት ነው ፤ጽኑ ክቡር ልዩ የሚሆን የእግዚአብሔር ዋጋው ይሰጣታል በውነቱ ፤ አንድም ፍሬ ተሳልቆ ፤አን

www.ethiopianorthodox.org

ድም ዕሤቶ ቢል የቸርነቱን ዋጋ መሥዋዕት ታቀርባለች፤

፲፮፤ ወአኮ አመንቱ ዘይትጋብዑ ፤

ፍና ተሳልቆ ቢሉ የጢሮስ ሰዎች የሚሰበሰቡ አይደለም፤

ዳዕሙ እለ ይነብሩ ቅድመ እግዚአ ብሔር ወባያት ፤

በእግዚአብሔር ፊት በባለሟ ልነት ጸንተው የሚኖሩ እስራ ኤል ናቸው እንጂ ፤ አንድም በውነቱ ባለው የጢሮስ ሰዎች መላው የሚሰበሰቡ አይደለም፤ በጎ በጎዎች ናቸው እንጂ ፤

ወኮሉ ተግባራ ለበሊዕ ወለሰትይ ወለ ጽጋብ ፤

የፃረችበት ፤ የጋረችበት ገንዘ ቧን ትበላዋለች ፤ ትጠጣዋለች ፤ ፀውነቱ ፤ አንድም ፍና ተሳልቆ ወትሁብ ተዝካራ ፤ አሥራቱን በኮራቱን ለራሷ መታሰቢያ አድርጋ ለእግዚአብሔር ትሰጣ ለች ፤ አንድም ለአሕዛብ ተሰ ጥታለች ::

ምዕራፍ ፷፬

፩፤ ናሁ እግዚአብሔር ያማስና ለዓ ለም ፤

እነሆ እግዚአብሔር ሰማርያን ያጠፋታል ፤ አንድም ኢየሩሳ ሌምን ለዘላለሙ ያጠፋታል ፤

ወያመዘብራ ፤

ያጠፋታል ፤

ወይቀፍጻ ገጻ ፤

ያጐሰቍላታል ፤

ወይዘርዎሙ ለእለ ይነብሩ ውስቴታ፤

በሷ የሚኖሩትን ሰዎች ይበትና ቸዋል ፤

፪፤ ወይከውን ሕዝብ ከመ ካህን ፤

ይህ ለመጣበት ጨዋው እንደ ካህኑ ይሆናል ፤ መክበር መኩ ራት የካህን ነበር ፤ ጨዋው ይታበያል ፤ ወካህን ከመ ሕዝብ ይላል ፤ ካህኑም እንደ ጨዋው ይሆናል ፤ ማለት ትብትብ ምንጣፍ በመሸከም ፤ አንድም ትብትብ ምንጣፍ መሸከም ለጨዋ ነበር ካህኑ ይሸከማል፤

ወገብር ከመ እግዚኡ ፤

ባርያ እንደጌታው ይሆናል ማለት ይታበያል ፤ አንድም ጌታ እንደባርያው ይሆናል ማለት ትብትብ ምንጣፍ በመሸከም፤

ወአመት ከመ እግዝእታ ፤

ሴት ባርያ እንደእመቤቷ ትሆ ናለች ማለት ትታበያለች ፤ አን ድም ወእግዝእት ከመ አመት እመቤትእንደ ባርያ ትሆናለች ማለት ትብትብ ምንጣፍ በመሸ ከም ፤

ወዘይሠይጥ ከመ ዘይሣየጥ ፤

ይሸጥ የነበረው እንደሚገዛ ይሆ ናል ፤ ብክን ብክን እያለ ግዙኝ ይላል ፤ አንድም ወዘይሣየጥ ከመ ዘ ይ ሠ ይ ጥ ይ ላ ል ፤ ይገዛ የነበ ረው እ ን ደ ሚ ሸ ጥ ይ ሆ ና ል ፤ ከቤቱ ተቀምጦ ሻጩን አምጣ ልኝ ይለዋል ::

ወዘይሴቅሕ ከመ ዘይትሌቃሕ ፤

ያበድር የነበረው እንደሚበደር ይሆናል ተዋርዶ ፤ አንድም ወዘ ይትሌቃሕ ከመ ዘይሌቅሕ ይላል ፤ ይበደር የነበረው እንደ ሚያበድር ይሆናል ኮርቶ ፤

ወዘይፈዲ ከመ ዘበዐለ ዕዳ ፤

ብድር የሚከፍለው ብድር እን ደሚቀበል ሰው ይሆናል ኮርቶ ፤ አንድም በዐለ ዕዳ ከመ ዘይፈዲ ይላል ፤ አበዳሪ ተዋርዶ እንደ ተበዳሪ ይሆናል ::

፫፤ ናሁ ማስኖ ትማስን ምድር ፤

እነሆ ምድር ፈጽማ ትጠፋለች፤

እስመ አፉሁ ለእግዚአብሔር ነበበ ከመዝ ፤

እግዚአብሔር ትጠፋለች ብሎ ተናግሯልና ፤

፬፤ ለሀወት ወተገፍትዐት ምድር ፤

ትሑታኑ በውስጥ በአፍአ አዘኑ፤ አንድም ምድር ኢየሩሳሌም ጠፉች ፤

ማሰነት ወተገፍትዐት ዓለም ፤

ዓለም ኢየሩሳሌም ግልብጥብጥ አለች ፤

ለሀወ ወበይተ ምድር ፤

መኳንንቱ ነገሥታቱ አዘኑ ፤

፭፤ እስመ አበሰት ምድር ምስለ እለ ይነብሩ ውስቴታ ፤

ትሑታኑ ከመኳንንቱ ጋር በድ ለዋልና ፤ አንድም ምድር ኢየ ሩሳሌም በውስጧ ከሚኖሩት ሰዎች ጋራ በድላለችና ፤

እስመ ዐለዉ ሕገ እግዚአብሔር ፤

ሕገ እግዚአብሔርን ስለአፈ ረሱ ፤

ወወለጡ ሥርዓቶ ፤

ሥርዓቱን ስለለወጡ ፤

ወከህዱ ኪዳኖ ዘለዓለም ፤

ለዘለዓለም የሚሆን መሐላውን ስለካዱ ፤ አንድም ለዘለዓለም ጸንቶ የሚኖር አምልኮቱን ስለ ካዱ ፤

፮፤ ወበእንተ ዝንቱ እንጋ ትውኅጦሙ ምድር ፤

ስለዚህ ነገር ምድር ትውጣቸ ዋለች ፤ አንድም ስለዚህ ነገር ምድር ትውጣቸው ይሆን እንጂ፤

እስመ አበሱ እለ ይነብሩ ውስቴታ፤

በሷ የሚኖሩ ሰዎች በድለዋልና፤

www.ethiopianorthodox.org

ወበእንተ ዝንቱ ይጼነሱ እለ ይነ
ብሩ ውስተ ምድር ፣

ስለዚህ ነገር በዚህ ዓለም የሚ
ኖሩ ሰዎች ይቸገራሉ ፤

ወይተርፉ ኅዳጣን ሰብእ ፣

ጥቂት ሰዎች ይቀራሉ ፤

፯፡ ለይላሁ ወይን ፣

ወይኑ ያልቅስ ፤ የሰዎችን ለወ
ይኑ ሰጥቶ ተናገረ ፤

ወአዕፃደ ወይን ፣

የወይኑ ቦታዎች ያልቅሱ ፤

ወይብክዩ ኵሎሙ እለ ይትፌሥሑ
በነፍሶሙ ፣

በልቡናቸው ደስ የሚላቸው
ሰዎች ሁሉ ያልቅሱ ፤

፰፡ ኀልቀ ትፍሥሕተ ክብሮሙ ፣

በባለጸግነታቸው የሚያደርጉት
ተድላ ደስታ ጠፋ ፤

ወኀልቀ ትዝኅርት ወብዕለ ኃጥአን ፣

የባለጸጎች ብዕል ትዕቢት ጠፋ ፤

ወኀልቀ ቃለ መሰንቆ ፣

የመሰንቆው ድምጽ ጠፋ ፤

፱፡ ወተኀፍሩ እለ ይሰትይዎ ለወ
ይን ፣

ወይን የሚጠጡ ሰዎች መከራ
መጥቶባቸው አፈሩ ፤

መሪረ ኮነ ሜስ ለእለ ይሰትይዎ ፣

ወ ይ ን ለ ሚ ጠ ጡ ት ሰ ዎ ች
መራራ ሆነ ፤ ወይን ጠጥተው

ኃጢአት ሠርተው መከራ መጥ
ቶባቸው ተመርረዋልና ፤

፲፡ ወመዝበራ ኵሎን አህጉር ፣

ሀገሩ ሁሉ ጠፋ ፤

ወተዐፅዋ ኵሎን አብያት ከመ ኢይ
ባኡ ውስቴቶን ፣

እንዳይገቡባቸው ቤቶች ሁሉ
ተዘጉ ፤

፲፩፡ ብክዩ ብካየ በእንተ ወይን ፣

ወይኑ ስለጠፋ ፤ አንድም ወይን
ጠጥታችሁ መከራ ስለመጣባ
ችሁ አልቅሱ ፤

እስመ ተሥዕረ ትፍሥሕት እም
ኵሉ ምድር ፣

ከሀገሩ ሁሉ ተድላ ደስታ ጠፍ
ቷልና ፤

፲፪፡ ወይትኃደጋ አህጉር ምዝቡረ ፣

አገሩ ሁሉ ይፈታል ፤

ወአብያትኒ የዐርቃ ፣

ቤቶችም ባዶአቸውን ይሆናሉ ፤

ወይትኀደጋ ወይትኀጐላ ፣

ፈጽመው ይጠፋሉ ፤

፲፫፡ ዝንቱ ኵሉ ይከውን ውስተ
ብሔር ማዕከለ አሕዛብ ፣

ይህ ሁሉ በሞአብና በአሞን መካ
ከል ባለች በኢየሩሳሌም ፈጥኖ
ይደረጋል ፤

በከመ ይቀስምዎ ለዘይት ከማሁ ይቀ
ስምዎሙ ለእስራኤል ፣

ደገኛው መከር ካለቀ በኋላ ቃር
ሚያውን እንዲለቅሙ ፤ አሥሩን
ነገድ ከማረኩ በኋላ ሁለቱን
ነገድ ይማርኳቸዋል ፤

ወእመኒ ኀልቀ ማዕረር ይኬልሑ
በቃሎሙ ፣

መከራም በመጣባቸው ጊዜ
ይጮኻሉ ፤ አንድም በከመ ሕን
ባባተ ዘይት ውስተ ተቅራም
ሶበ ኀልቀ ቀስም ይላል አብ
ነት ፣ ደገኛው መከር ካለቀ በኋላ
ቃርሚያውን እንዲለቅሙ ፣
አሥሩን ነገድ ከማረኩ በኋላ
ሁለቱን ነገድ ይማርኳቸዋል ፣
እንደ ፊተኛው አዝመራ አሥሩ
ነገድ ፣ እንደ ኋለኛው አዝመራ
ሁለቱ ነገድ ፣ አንድም እንደ
ዓይነተኛው አዝመራ አሥሩ
ነገድ ፣ እንደቃርሚያው ሁለቱ
ነገድ ናቸው ፤ አንድም በከመ
ይትቄረም ሰብእ ዘይተ ከማሁ
ይትቄርምዎሙ ለደቂቀ እስራ
ኤል አመኒ ኀደገ ማዕረሮ አመሰ
ኀደገ ማዕረሮ እሙንቱሰ ዘልፈ
ይኬልሑ በቃሎሙ ወየዐወይዉ
ይላል ፣ ደገኛው መከር ካለቀ
በኋላ ቃርሚያውን እንዲለቅሙ
አሥሩን ነገድ ከማረኩ በኋላ
ሁለቱን ነገድ ይማርኳቸዋል ፤
አንድም ኋላ ሐዋርያት አሕዛ

ብን በትምህርት እንዲለቅሟ
ቸው ፤ ነቢያት እስራኤልን በት
ምህርት ይለቅሟቸዋል ፤ አመኒ
ኀደገ ማዕረሮ እንዲሰሟቸውም
ባደረገ ጊዜ እሙንቱሰ ይኬልሑ
በቃሎሙ ፣ ይወርዳል ይወለዳል
ብለው ያስተምራሉ ፤ አንድም
ኋላ አሕዛብ ሐዋርያትን በሞት
እንዲለቅሟቸው እስራኤል ነቢ
ያትን በሞት ይለቅሟቸዋል ፣
አመሰ ኀደገ ማዕረሮ ፣ እንዳይ
ሰሟቸውም ባደረገ ጊዜ እሙን
ቱሰ ይኬልሑ ፤ ሠረይነ ሰብአ
ወኢያሕየውነ ፈውስናሃ ለባቢ
ሎን ወኢተፈወሰት ይላሉ ፤ አን
ድም ነቢያት እስራኤልን በት
ምህርት እንዲለቅሟቸው ሐዋር
ያት አሕዛብን በትምህርት ይለ
ቅሟቸዋል ፤ አመኒ ኀደገ ማዕ
ረሮ እንዲሰሟቸውም ባደረገ
ጊዜ እሙንቱሰ ይኬልሑ ፣
ወረደ ተወለደ ብለው ያስተም
ራሉ ፤ አንድም እስራኤል ነቢ
ያትን በሞት እንዲለቅሟቸው
አሕዛብ ሐዋርያትን በሞት ይለ
ቅሟቸዋል ፤ አመሰ ኀደገ ማዕ
ረሮ መከራ ባጸኑባቸውም ጊዜ
እሙንቱሰ ይኬልሑ ፤ ሐዋር
ያት እንከሰ ንትመየጥ መንገለ
አሕዛብ እያሉ ይጮኻሉ ፤ አን
ድም ዐበይት ነቢያትን ማር
ከው ደቂቅ ነቢያትን ይማርኳ

www.ethiopianorthodox.org

ቸዋል አመኒ ኀደገ ማዕረሮ ፤ መከራም ባጸኑባቸው ጊዜ ይጮኻሉ ፤ አንድም እንደ ደገኛው መከር በእናት ባባታቸው ፍዳ የተያዙት ፣ እንደ ቃርሚያው በራሳቸው ፍዳ የተያዙት ናቸው ፤ በራሳቸው በእናት ባባታቸው ፍዳ የተያዙትን አጋንንት ይለቅሟቸዋል ፤ አመኒ ኀደገ ማዕረሮ ፣ መከሩ ነፍሳትን በአጋንንት መካከል በጣላቸው ጊዜ ይጮኻሉ ፤ አንድም በራሳቸው ኃጢአት ከተቈራኟቸው በኋላ በእናት ባባታቸው ኃጢአት ይቈራኟቸዋል ፤ አመሰ ኀደገ ማዕረሮ ፣ አጋንንት መከራ ባጸኑባቸው ጊዜ እሙንቱሰ ይኬልሑ ፤ ነፍሳት አንሥእ ኃይለከፈኑ እዴከ እያሉ ይለምናሉ ፤

፲፬፡ ወእለ ተርፉ ውስተ ምድር ይትፈሥሑ ኀቡረ በስብሐተ እግዚአብሔር ፣

አሥሩ ነገድ ተማርከው የቀሩ ሁለቱ ነገድ ፣ አንድም አባቶች አልቀው የቀሩ ልጆች ፣ አንድም ከእንቢታ ከክህደት የቀሩ ምዕመናን እግዚአብሔር ባደረገላቸው ተአምራት አንድነት ደስ ይላቸዋል ፤

ወይትከወስ ማየ ባሕር ፣

ሰናክሬም ብልጣሶር ይጠፋል ፣ አንድም ዲያብሎስ ይጠፋል ፤

፲፭፡ ወይሴባሕ እግዚአብሔር አምላክ እስራኤል እስከ አጽናፈ ምድር ፣

የእስራኤል አምላክ እግዚአብሔር እስከ ምድር ዳርቻ ድረስ ይመሰገናል ፤

፲፮፡ ሰማዕነ ምክረ ተስፋሁ ለጻድቅ ፣

የጻድቀ ባሕርይ የእግዚአብሔር የአለኝታውን ምክር ሰማነ ፤ አንድም ለጻድቅ ለቤተ እስራኤል የተመከረውን ምክር ሰማነ ፣ አንድም ጻድቅ እግዚአብሔር ለቤተ እስራኤል የመከረውን ምክር ሰማነ ፤ አንድም የጻድቀ ባሕርይ የክርስቶስን የአለኝታውን ምክር ሰማን ፤ አንድም ለጻድቅ ለአዳም የተመከረውን ምክር ሰማነ ፤ አንድም ጻድቀ ባሕርይ ክርስቶስ ለአዳም የመከረውን ምክር ሰማነ ሥጋዌን ፤

አሌ ሎሙ ለዐላውያን እለ ዐለዉ ሕገ እግዚአብሔር ፣

ወይቤራ ይላል ፣ ሕገ እግዚአብሔርን ሳፈረሱ ለአሥሩ ነገድ ወዮላቸው ፤

፲፯፡ ፍርሀት ወፀድፍ ፣

ፍርሃት መጥቶባቸው በገደል ወድቆ በባሕር ጠልቆ መሞት መጥቶባቸው ፣

ወመሥገርት ላዕሌሆሙ ለእለ ይነብሩ ውስተ ምድር ፣

በዚህ ዓለም በሚኖሩ ሰዎች የእዳሪ ጦር መጥቶባቸው ፣

አንድም ፍርሀት ፎሀ መጥቶባቸው ፣ ወፀድፍ ቴልጌል መጥቶባቸው ፣ ወመሥገርት ስልምናሶር ናቡከደነፆር መጥቶባቸው ፤

፲፰፡ ወዘጐየ እምፍርሀት ይወድቅ ውስተ ፀድፍ ፣

ከቤት ጦር ያመለጠውን የእዳሪ ጦር ያጠፋዋል ፤

ወዘሂ ወፅአ እምፀድፍ ይእኅዞ መሥገርት ፣

ከእዳሪ ጦር ያመለጠውን የሜዳ ጦር ያጠፋዋል ፤ አንድም ከፎሀ ያመለጠውን ቴልጌል ፣ ከቴልጌል ያመለጠውን ስልምናሶር ያጠፋዋል ፤ አንድም ከስልምናሶር ያመለጠውን ሰናክሬም ፣ ከሰናክሬም ያመለጠውን ናቡከደነፆር ፣ ከናቡከደነፆር ያመለጠውን አንጥያኮስ ያጠፋዋል ፤

እስመ መሳክወ ሰማይ ይትረኀዋ ፣

መዓት መቅሠፍት ከሰማይ ይታዘዛልና ንጉሡ ይጠፋል ፤

ወያድለቀልቃ መሠረታተ ምድር ፣

የትሑታኑ መሠረት የሚሆኑ መኳንንቱ ይጠፋሉ ፤

፲፱፡ ወትደነግፅ ምድር ፣

ትሑታኑ ይደነግጣሉ ፤

ወትትሀወክ ምድር ፣

ትሑታኑ ይታወካሉ ፤

ወተኀስር ምድር ፣

ትሑታኑ ይዋረዳሉ ፤

ወትጸንን ፣

ለጥፋት ትቀርባለች ፤

፳ ወታድለቀልቅ ከመ ልገተ ዐቃቤ ቀምሕ ፣

እንደ ፍሬ ጠባቂ ጐጆ ትጠፋለች ፤

ወትተነትን ከመ ስኩር በወይን ፣

በወይን እንደሰከረ ሰው በመከራ ትፍገመገማለች ፤

ወትወድቅ ፣

በመከራ ትወድቃለች ፤

ወኢትክል ተንሥኦ ፣

መነሣት አይቻላትም ፤

እስመ ከብደ ኃጢአታ ፣

ኃጢአቷ በዝቷልና ፤

፳፩፡ ይእተ አሚረ ያመጽእ እግዚአብሔር እዴሁ ዲበ ሠርጐ ሰማይ ፣

ያንጊዜ በዔዋዌ በኢየሩሳሌም በሚኖሩ በእስራኤል እግዚአብሔር እደ መዓቱን ያመጣባቸዋል ፣ ያገር ሽልማቱ ሰውነውና ዲበ ሠርጐ ሰማይ አለ ፤ አንድም በሚጠት በባቢሎን ሰዎች እደ መዓቱን ያመጣባቸዋል ፤

ወላዕለ ነገሥተ ምድር ፣

በዔዋዌ በነኢኮንያን በነሴዴቅያስ እደ መዓቱን ያመጣባቸ

www.ethiopianorthodox.org

ዋል ፣ አንድም በሚጠት በነብ
ልጣሶር እደ መዓቱን ያመጣ
ባቸዋል ፤

፳፪፡ ወይትዐፀዉ ፣

በሞት ይዘጋሉ ፤

ወይትጋብዑ ወይዔወኑ ፣

ተሰብስበው ከአምባ ይጠጋሉ ፤

ወይትዐሠሩ ለካልዕ ትውልድ ፣

በሁለተኛው ትውልድ ሊወጡ
ይቀጠራሉ ፤ በእስራኤል የቈ
ጠሩ እንደሆነ በኢኮንያን ተማ
ርከዋል ፤ የተማረኩበትን አይ
ሻም በሰላትያል ተስፋ ሰምተው
በዘሩባቤል ወጥተዋል ፤ በአሕ
ዛብ የቈጠሩ እንደሆነ በናቡከ
ደነፆር ተማርከዋል ፤የተማረኩ
በትን አይሻም ፤ በዮርማሮዴቅ
ተገዝተው በብልጣሶር ወጥተ
ዋል ፤

፳፫፡ ወእምከመ ሐወፆሙ ይትመ
ሰው ብዝሆሙ ፣

በመዓት በጐበኛቸው ጊዜ ብዛ
ታቸው ይጠፋል ፤

ወይወድቅ ዓረፋቲሆሙ ፣

ቅጽራቸው ይፈርሳል ፤ አንድም
አርበኛቸው ይጠፋል ፤

እስመ ይትነሣእ እግዚአብሔር ዘሎቱ
ኃይል በጽዮን ወበኢየሩሳሌም ፣

ኃይል ያለው እግዚአብሔር
በጽዮን በኢየሩሳሌም ላይ በመ
ዓት ይነሣልና ፤ አንድም በጽዮን
በኢየሩሳሌም ኃይል ያለው እግ
ዚአብሔር በባቢሎን ላይ በመ
ዓት ይነሣልና ፤

ወይሴባሕ በቅድመ ሊቃውንት ፣

በሊቃውንትም ፊት ይመሰገ
ናል ::

ምዕራፍ ፳፭

፩፡ እግዚአብሔር አምላኪየ እሴብ
ሐከ ፣

ፈጣሪዬ እግዚአብሔር አመሰ
ግንኻለሁ ፤

ወእገኒ ለስምከ ፣

ለስምህ እገዛለሁ ፤

እስመ ገበርከ መንክረ ግብረ ፣

ድንቅ ሥራ ሠርተኻልና ማለት
ድንቅ ሚጠትን አድርገኻልና ፤
አንድም ድንቅ ሥጋዌን አድር
ገኻልና ፤

ወእሙነ ኮነ ምክረ ትካት ፣

የቀደመው ምክር ዔዋዌ እው
ነት ሆነ ፤ አንድም የቀደመው
ምክር የታመነ ሆነ አለ ፤ ውነ
ሊቆ ሰብዓ ዓመት ያለው ፣ አን
ድም በሐሙስ ዕለት ያለው ፤

፪፡ እስመ ረሰይኮን ለአህጉር መሬተ ፣

አገሮችን ሁሉ ትቢያ አድርገኻ
ቸዋልና ፤ አንድም የባቢሎንን
ሰዎች አዋርደኻቸዋልና ፤

አንድም አጋንንትን አዋርደኻ
ቸዋልና ለስምህ እገዛለሁ ፤

ወአውደቀ አህጉረ ጽኑዓተ ፣

የጸኑ ሀገሮችንም አጥፍተኻቸ
ዋልና ፤

ወመሠረተ ኃጥአን ፣

የኃጥአንን ሥር መሠረታቸውን
አጥፍተኻልና ፤ አንድም የኃጥ
አንን አባትነት አጥፍተኻልና
ለስምህ እገዛለሁ ፤

ወኢይትሐነፃ ለዓለም አህጉሪሆሙ ፣

አገራቸው ለዘላለም አይታነፅም ፤

፫፡ ወበእንተ ዝንቱ ይባርኩከ ሕዝብ
ነዳያን ፣

ስለዚህ ነገር ነዳያን እስራኤል
ያመሰግኑኻል ፤

ወይባርኩከ አህጉረ ሰብእ ግፉዓን ፣

ነገደ ሰብእ ሲል ነው ፤ የተበደሉ
ሰዎች ወገኖች ያመሰግኑኻል ፤

፬፡ እስመ ኮንከ ረዳኤ ለኵሉ አህ
ጉረ ሰብእ ትሑታን ፣

ነገደ ሰብእ ሲል ነው ፤ ትሑ
ታን ለሆኑ ሰዎች ወገኖች ረዳት
ሁነኻልና ፤

ወከደንኮሙ ትፍሥሕተ ለእለ ይቴ
ክዙ በተጽናሶሙ ፣

በችግር ተይዘው ያዘኑትን ደስ
አሰኝተኻቸዋልና ፤

እምለብእ እኩያን ባላህኮሙ ፣

ከክፉ ሰዎች አዳንኻቸው ፤

፭፡ ወአስተይኮሙ ትፍሥሕተ ለነ
ፍሰ ሰብእ ግፉዓን ፣

የተበደሉትን ሰዎች ልቡና ደስ
አሰኘኸው ፤

ወለነፍሰ ሰብእ እንቡዛን ፣

አእምሮ ያጡትን ሰዎች ልቡና
ደስ አሰኘኸው ፤

ለእለ ፀምዑ በጽዮን ፣

በጽዮን የተጠሙትን ፤ አንድም
ከትምህርት ከልጅነት የተጠ
ሙትን ደስ አሰኝተኻቸዋልና ፤

እምሰብእ ኃጥአን እለ ሎሙ መጠ
ውኮሙ ፣

ባላሕኮሙ ያለበት ነው ፤ አሳል
ፈህ ከሰጠኻቸው ከክፉ ሰዎች
አዳንኻቸው ፤

፮፡ ወይገብር እግዚአብሔር ፀባያት
ለኵሉ ሕዝብ ፣

አሸናፊ እግዚአብሔር ለሕዝቡ
ሁሉ እንዲህ ያደርጋል ፤

በዝንቱ ደብር ከመ ይስተዩ ወይነ ፣

በኢየሩሳሌም ወይን እንዲጠጡ
ያደርጋቸዋል ፤

ወይግበሩ ትፍሥሕተ ፣

ደስ እንዲላቸው ያደርጋቸዋል ፣
አንድም በዚህ ዓለም በቤተ
ክርስቲያን ሥጋውን ፣ ደሙን ፣
መንፈስ ቅዱስን እንዲቀበሉ
ያደርጋቸዋል ፤

www.ethiopianorthodox.org

ወይትቀብው ዕፍረተ ፣

ሽቱ እንዲቀቡ ያደርጋቸዋል፤ አንድም ልጅነት እንዲያገኙ ያደርጋቸዋል ፤

፮፤ በዝንቱ ደብር መጠዎሙ ዘንተ ኮሎ ለሕዝብ ፣

በኢየሩሳሌም ይህን ሁሉ ለሕዝቡ ሰጣቸው፣ አንድም በቤተ ክርስቲያን ሥጋውን ደሙን ሰጣቸው ፤

እስመ ዛቲ ምክር ለኮሉ ሕዝብ ይእቲ ፣

ይህች ሚጠት ለሁሉ ናትና፣ አንድም ይህች ሥጋው ደሙ ለሁሉ ናትና ፤

፯፤ ውኀጠ ሞት ውነየለ ፣

ሞት ሁሉን አጠፋ በረታ፣ አንድም ስልምናሶር ናቡከደነፆር ሁሉን አጠፋ በረታ፤ አንድም ተውኀጠ ሞት ዘነየለ የተበረታታ ስልምናሶር ናቡከደነፆር ጠፋ፤ አንድም ዲያብሎስ አምስት ሺህ ከአምስት መቶ ዘመን ሁሉን አሳተ በረታ፤ አንድም ተውኀጠ ሞት ዘነየለ የተበረታታ ዲያብሎስ ጠፋ ፤

ወካዕበ ሠዐረ እግዚአብሔር አንብዐ እምኮሉ ገጽ ፣

ዳግመኛ እግዚአብሔር ከሰው ሁሉ ፊት እንባን አራቀ ፤

ወሠዐረ ጽዕለተ ሕዝብ እምኮሉ ምድር ፣

የሕዝቡን ስድብ ከሀገሩ ሁሉ አጠፋ ፤

እስመ እግዚአብሔር ነበበ በአፉሁ፣

እግዚአብሔር ይጥፋ ብሎ በቃሉ ተናግሯልና ፤

፰፤ ወይብሉ ይእተ አሚረ ነዋ እግዚአብሔር አምላክነ ዘኪያሁ ተወከልነ ፣

ያንጊዜ ያመንበት ፈጣሪያችን እግዚአብሔር ከሀሊ ነው ይላሉ፤

ተፈሣህነ ወተንሠይነ በመድኃኒነ ፣

በመድኃኒታችን አምነን በውስጥ በአፍአ ደስ አለን ፤

፱፤ ወይሁበነ እግዚአብሔር ዕረፍተ በዝንቱ ደብር ፣

በኢየሩሳሌም እግዚአብሔር ዕረፍትን ይሰጠናል፤ አንድም በቤተ ክርስቲያን ዕረፍተ ነፍስን ይሰጠናል ፤

ወይከይድዎ ለሞአብ ዘከመ ያከይዱ እክለ በመንኰራኵር ፣

እህሉን በመንኰራኵር እንዲያበራዩ ሞአብን በመከራ ይረጋግጡታል ፤

፲፩፤ ወያነሥኡ እደዊሆሙ ላዕሌሁ፣

እጃቸውን፣ ቃላቸውን፣ ሰላጥናቸውን፣ ትእዛዛቸውን በሱ ያነሡባታል ፤

በከመ ውእቱ አሕሰመ ወቀተለ ፣

እሱ ሌላውን እንደ ገደለ ክፉ ነገር እንደ አደረገ ፤

ወይስዕር ጽዕለቶ ዘአንሥአ እዴሁ ላዕሌሆሙ ፣

በነሳቸው ላይ ያነሣው የነበረውን ቃሉን ስድቡን ያጠፋል፤

፲፪፤ ወያንኀሉ ላዕሌሁ ዐረፍተ በወኑ ፣

የተጠጋበት ቅዕሩን በላዩ ላይ ያፈርሰበታል ፤

ወይቴሐት እስከ ምድር ፣

ምድር እስኪሆን ድረስ ይዋረዳል ::

ምዕራፍ ፷፪

፩፤ ወይእተ አሚረ ዮኅልዩ ዘንተ ማኅሌተ ላዕለ ይሁዳ ፣

በይሁዳ የሚኖሩ ሰዎች ያን ጊዜ ይህን ምስጋና ያመሰግናሉ ፤

እንዘ ይብሉ ናሁ ሀገር ጽንዕት ወመድኃኒትነ እንተ ትገብር ዓረፍተ ወጥቅመ ፣

ረድኤተ እግዚአብሔርን አጥር ቅጥር አድርጋ የምትኖር፣ ድኅነታችን የሚደረግባት የጸናች ሀገር ኢየሩሳሌም እንዲህ ያለች ናት እያሉ ያመሰግናሉ ፤

፪፤ አርኅዉ አናቅጸ ፣

ነቢያት ካህናት አንቀጹ ትምህርትን ክፈቱ ፤

ወይባእ ሕዝብ ዘየዐቅብ ጽድቀ፣

እውነተኛ ሕግን የሚጠብቅ እስራኤል ወደትምህርቱ ይግባ ፤

ወይትዌከፍ ርትዐ ፣

የቀና ሕግን የሚቀበል፤ አንድም አርኅዉ ቂሮስ ዳርዮስ፣ አንድም አጅግ ኮንታ የኢየሩሳሌምን ደጅ ክፈቱ፣ ይባዕ ሕዝብ ወይትዌከፍ ዘጠኙን ቃላት ኢታ ምልክን የሚጠብቅ እስራኤል ወደ ኢየሩሳሌም ይግባ ፤

ወይትመሐፀን ሰላመ እስከ ለዓለም፣

ፍቅር አንድነትን ለዘለዓለም ገንዘብ ያደርጋል፤ አንድም ሕግ ሰላም አሪትን የሚጠብቅ እስራኤል ወደ ኢየሩሳሌም ይግባ ፤

፫፤ ኪያከ ተወከልኩ እግዚኦ አምላክ ወቢይ ዘለዓለም ፣

ለዘለዓለም የምትኖር ገናና ፈጣሪ አቤቱ ባንተ አመንሁ ፤

፬፤ ዘአትሐትኮሙ ወአውረድኮሙ ለእለ ይነብሩ ውስተ አርያም ፣

በልዕልና የሚኖሩትን ፈጽመህ ያዋረድኻቸው፣ አንድም ለዘለዓለም ገናና ፈጣሪ የምትሆን አቤቱ አንተን አመንሁ፤ በልዕ

www.ethiopianorthodox.org

ልና የሚኖሩ የባቢሎንን ሰዎች ያዋረድኻቸው፣ አንድም አጋንንትን ያዋረድኻቸው ፤

ወትነጽሖን ለአህጉር ጽኑዓት ፣

የጸኑ አገሮችን በመከራ የምትጥላቸው ፤

ወታወርዶን እስከ ምድር ፣

ምድር እስኪሆኑ ድረስ የምታዋርዳቸው አቤቱ ባንተ አመንሁ ፤

፭፡ ወይከይዶን እግረ የዋሃን ወትሑታን ፣

ትሑታን የዋሃን የሚሆኑ የእስራኤል እግር ይረጋግጣቸዋል፤

፮፡ ወይከውን ፍኖተ ርቱዐ ለጻድቃን፣

ለእስራኤል የቀና ሕግ ይሠራላቸዋል ፤

ወትጸያሕ ፍኖተ ራትዓን ፣

የእስራኤል ሥራ የቀና ይሆናል አንድም በሰባ ዘመን የትሩፋን መንገድ ትጠረጋለች ፤

፯፡ እስመ ርቱዕ ውእቱ ፍኖተ እግዚአብሔር ፣

የእግዚአብሔር ሕጉ የቀና ነውና፤

ወተወከልነ በስሙ ቅዱስ ፣

ጽኑ ክቡር በሚሆን በስሙ አመን ፤

ወረከብነ ፍትወተ ነፍስነ ፣

ልቡናችን የወደደችውን ሚጠትን አገኘን ፤

ጉባዔ

፰፡ በሌሊት ትገይሥ መንፈስየ ኀቤከ እግዚኦ አምላኪየ ፣

አቤቱ ፈጣሪዬ ልቡናዬ ሌሊት ለጸሎት ወደ አንተ ትገሠግሣለች ይላል ሕዝቅያስ ፤

እስመ ብርሃን ትእዛዝከ በዲበ ምድር ፣

ሕግህ በዚህ ዓለም ብርሃን ነው፤ ፋና አያሻምና ፤ አንድም በሌሊተ መከራ ተይገፍ ሳለ ልቡናዬ ወደ አንተ ትገሠግሣለች ይላል ሕዝቅያስ፣ እነሰናክሬም ይጥፉ እነሕዝቅያስ ይዳኑ ብለህ ያዘዝኸው ትእዛዝህ ብርሃን ደስ እንዲያሰኝ ደስ ያሰኛልና፣ አንድም ሰባ ዘመን በመከራ ተይገፍ ሳለ ልቡናዬ ወደ አንተ ትገሠግሣለች ይላል ትሩፍ ፤ የባቢሎን ሰዎች ይጥፉ ፤ ትሩፋን ይዳኑ ብለህ ያዘዝኸው ትእዛዝህ ብርሃን ደስ እንዲያሰኝ ደስ ያሰኛልና ፣ አንድም አምስት ሺህ ከአምስት መቶ ዘመን በሌሊተ መከራ ተይገፍ ሳለ ልቡናዬ ወደ አንተ ትገሠግሣለች ይላል ምዕመን፣ አጋንንት ይጥፉ ምእመናን ይዳኑ [illegible]

ዛዝህ ብርሃን ደስ እንዲያሰኝ ደስ ያሰኛልና ፤

ተመሐሩ ገቢረ ጽድቅ እለ ትነብሩ ውስተ ዓለም ፣

በይሁዳ የምትኖሩ ሁለቱ ነገድ በጎ ነገር ማድረግን ተማሩ ፤

፱፡ እስመ ኀልቀ ኃጥእ ዘኢይት ሜህር ገቢረ ጽድቅ በዲበ ምድር ወኢይገብር ሠናየ ፣

እውነት ነገርን የማይማር ፣በጎ ነገርን የማያደርግ ሰናክሬም ጠፍቷልና ፤ አንድም በይሁዳ የምትኖሩ ሁለቱ ነገድ በጎ ነገር ማድረግን ተማሩ ፤ እውነት ነገርን የማይማር፣ በጎ ነገርን የማያደርግ አሥሩ ነገድ ጠፍቷልና፤ አንድም በከነዓን የምትኖሩ ውሉድ በጎ ነገር ማድረግን ተማሩ ፤ እውነት ነገርን የማይማር ፤ በጎ ነገርን የማያደርግ ስሳው እልፍ አጋር በምድረ በዳ እንደ ሻሽ ተነጥፎ ፤ እንደ ቅጠል ረግፎ ቀርቷልና ፤ አንድም በኢየሩሳሌም የምትኖሩ ትሩፋን በጎ ነገር ማድረግን ተማሩ ፤ እውነት ነገርን የማይማር፤ በጎ ነገርን የማያደርግ አሥሩ ነገድ ሁለቱ ነገድ ጠፍቷልና ፤ አንድም በዚህ ዓለም የምትኖሩ ምእመናን በጎ ነገር ማድረግን ተማሩ ፤ እውነት ነገርን የማይ

ማር በጎ ነገርን የማያደርግ ኃጥእ ዲያብሎስ ጠፍቷልና ፤

ያአትትዎ ለኃጥእ ከመ ኢይርአይ ስብሐተ እግዚአብሔር ፣

ኃጥእ ሰናክሬም የእግዚአብሔርን መከበሪያ እለመሶበ ወርቅን እለ ተቅዋመ ወርቅን እንዳያይ ሥላሴ ከይሁዳ ያርቁታል፤ አንድም ኃጥእ አሥሩን ነገድ ሥላሴ በሞት ያርቁታል ለሁለቱ ነገድ የተደረገውን ተአምራት እንዳያይ፤ አንድም ስሳውን እልፍ አጋር በሞት ያርቁታል፤ ለውሉድ የተደረገውን ተአምራት እንዳያይ፤ አንድም ኃጥእ ይሁዳን ሥላሴ መላእክት ከደብረ ታቦር ያርቁታል፤ የእግዚአብሔርን ብርሃነ መለኮቱን እንዳያይ ፣ ምነው ስምንቱስ ቀርተው የለም ቢሉ መቅረታቸው በሱ ምክንያት ነውና፣ ከነገሩ እንጂ የገባሁ ከተአምራቱ ቢለየኝ ነው እንዳይል፤ ስለቀሩ ግን ለሦስቱ የተገለጠላቸው ተገልጦላቸው አይተዋል ፤ አንድም ኃጥእን ሰው ሥላሴ ሑር እምኔየ ብለው ያርቁታል ፤ የእግዚአብሔርን ክብሩን እንዳይወርስ፤(ጥቅስ) ዘኢተወልደ እማይ ወእመንፈስ ቅዱስ ኢይሬእያ ለመንግሥተ እግዚአብሔር እንዲል ፤ (ዮሐ. ፫፡፫) ፤

www.ethiopianorthodox.org

፲፡ እግዚኦ ልዑለ መዝራዕተከ ኢያ
እመሩ ፣

አቤቱ እነሰናክሬም ገናና ሥል
ጣንህን አላወቁም ፤

እምከመሰ አእመሩ ይትኃፈሩ ፣

ምነው አያውቁ ሰብአ ትካትን
በማየ አይኅ ሰብአ ሰዶምን
በእሳት ሳጠፋ ትለኝ እንደሆነ
ካወቁስ የዐዋቂ በዳዮች ናቸውና
ይጥፉ፤ አንድም በከነዓን የሚ
ኖሩ ውሉድ ገናና ሥልጣንህን
አላወቁም ፤ ምነው አያውቁ ስሳ
ውን እልፍ አጋር በምድረ በዳ
እንደ ሻሽ ሳነጥፋቸው ፤ እንደ
ቅጠል ሳረግፋቸው ትለኝ እንደ
ሆነ፣ ካወቁስ የዐዋቂ በዳዮች
ናቸውና ይጥፉ ፤ አንድም በኢየ
ሩሳሌም የሚኖሩ ትሩፋን ገናና
ሥልጣንህን አላወቁም ፤ ምነው
አያውቁ አሥሩን ነገድ በስልም
ናሶር ፣ ሁለቱን ነገድ በናቡከደ
ነፆር ሳስማርካቸው ትለኝ እንደ
ሆነ ካወቁስ የዐዋቂ በዳዮች ናቸ
ውና ይጥፉ ፤ አንድም አይሁድ
ገናና ሥልጣንህን አላወቁም፤
ምነው አያውቁ ፤ በደረቅ ግንባር
ዓይን ስፈጥር ፣ የዕለት ሬሣ
ወልደ መበለትን፣ ወለተ ኢያኢ
ሮስን፣ የአራት ቀን ሬሣ አልዓዛ
ርን ሳስነሣ ትለኝ እንደሆነ ካወ
ቁስ የዐዋቂ በዳዮች ናቸውና
ይጥፉ ፤

ቅንዓት አኀዞሙ ለሕዝብ አብዳን፣

እነራፋስቂስን እነሰናክሬምን
ቅንዓት ያዛቸው ፤ አንድም አይ
ሁድን ቅንዓት ያዛቸው ፤ ተአም
ራቱ ምትሐት ነው ፤ ትምህርቱ
ሐሰት ነው እያሉ ፤(ጥቅስ) ለም
ንት ታፀምዕዎ እስመ ጋኔን አኀዞ
ወየአብድ ብለውታልና (ዮሐ.
፲ : ፳) ፤

ወይእዜኒ እሳት ትበልዖሙ ለፀር ፣

እነራፍስቂስን ፣ እነሰናክሬምን፤
አንድም አይሁድን መዓት መቅ
ሠፍት ታጠፋቸዋለች ፤

፲፩፡ እግዚኦ አምላክነ ሰላመ ሀበነ ፣

አቤቱ ፈጣሪያችን ፍቅር አን
ድነትን ስጠን ፤

እስመ ኵሎ ወሀብከነ ፣

ከዚህ አስቀድሞ ሁሉን አምጥ
ተህብናልና ፤

፲፪፡ እግዚኦ አምላክነ አጥርየነ ፣

አስተጋብዐነ ሲል ነው ፤ አቤቱ
ፈጣሪያችን ከፋርስ፣ ከባቢሎን፣
ከፅርዕ፣ ከሜዶን ሰብስበን ፤

እግዚኦ ዘእንበሌከ ባዕደ ኢነአምር ፣

አቤቱ ካንተ በቀር ሌላ አናው
ቅም ፤

ወስመ ዚአከ ንሰሚ ፣

ንጼውዕም ይላል፤ ያንተን ስም
እንጠራለን ፤

፲፫፡ ሙታንሰ ኢይሬእይዋ ለሕይ
ወት፣

ሙታን እነሰናክሬም ሕይወትን
አያይዋትም ፤

ወዐቀብተ ሥራይኒ ኢያነሥኡ ፣

ባለመድኃኒቶቻቸው ነቢያተ
ሐሰት ካህናተ ጣዖትም አንተ
የገደልኸውን አያነሡም ፤

በእንተዝ አምጻእኮሙ ወአጥፋእ
ኮሙ፣

ስለዚህ የማያድኑ ስለሆኑ በነጭ
በግ አምሳል እለ ሰናክሬምን ወደ
ሀገራቸው አምጥተህ አጠፋኻ
ቸው ፤

ወአእተትከ ኵሎ ትዕቢቶሙ ፣

ትዕቢታቸውንም አራቅህ ፤ አን
ድም ሙታን አሥሩ ነገድ
ሁለቱ ነገድ ሕይወትን አያዩዋ
ትም፤ ባለመድኃኒቶቻቸው ነቢ
ያተ ሐሰት ካህናተ ጣዖትም
አንተ የገደልኸውን አያነሱም፣
ስለዚህ ነገር በአሥሩ ነገድ ስል
ምናሶርን ፣ በሁለቱ ነገድ ናቡከ
ደነፆርን አምጥተህ አጠፋኻ
ቸው፣ ትዕቢታቸውንም አራ
ቅህ፣ አንድም ሙታን ነፍሳት
አምስት ሺህ ከአምስት መቶ
ዘመን ሕይወትን አያዩዋ
ትም ፤ ባለመድኃኒቶቻቸው
ነቢያት ካህናትም አንተ የገደል
ኸውን አያነሱም፣ አምስት ሺህ
ከአምስት መቶ ዘመን ደም ቢያ
ፈሱ፣ ስብ ቢያጤሱ በእደ እግዚ
አብሔር ለመያዝ አበቁ እንጂ
ማዳን አልተቻላቸውምና ፣
(ጥቅስ) ሠረይነ ሰብአ ወኢያሕ
የውነ እንዲል (ቄር እስት) ወኮነ
ጽድቅነ ከመፀርቀ ትክቶ (ኢሳ.
፷፬:፮) ፤ ፈውስናሃ ለባቢሎን
ወኢትፈወሰት እንዲል ፤ (ኤር.
፶፩ : ፱) ስለዚህ ነገር አምላኪየ
አምላኪየ ብለህ አጋንንትን ወደ
መስቀል አምጥተህ አጠፋኻ
ቸው ፣ ትዕቢታቸውንም አራ
ቅህ ፤ አንድም ሙታነ ልቡና
አይሁድ ሕይወት ወልድን አያ
ምኗትም (ጥቅስ) ስቅልተ ትሬ
እያ እስራኤል ለሕይወትከ
ቅድመ ገጽከ ወኢትትአመና
እንዲል፡ መምህሮቻቸው ጸሐ
ፍት ፈሪሳውያንም አንተ የገደ
ልኸውን አያነሡም ስለዚህ ነገር
በአርባ ዘመን ጥጦስ አስፋስያ
ኖስን አምጥተህ አጠፋኻቸው ፤
ትዕቢታቸውንም አራቅህ ፤

፲፬ ወስኮሙ እግዚኦ እኪተ ፣

አቤቱ በመከራ ላይ መከራ አም
ጣባቸው ፤

ወስኮሙ እኪተ ለክቡራነ ምድር ፣

ክቡራነ ምድር ለማለት ደግሞ
ታል ፤ በወዲህ ዓለም እንጂ

www.ethiopianorthodox.org

በወዲያው ዓለም ክብር የላቸ
ውምና ፤

፲፭፡ እግዚኦ በምንዳቤየ ተዘከርኩከ፣

አቤቱ በመከራዬ ቀን አሰብ
ሁህ ይላል ሕዝቅያስ ፤

ወበኅዳጥ ሕማም ገሠፅከኒ ፣

በጥቂት መከራ ገሠፅኸኝ አለ፤
ደዌው ሦስት ቀን ነውና፤ አን
ድም አቤቱ በመከራዬ ቀን አሰ
ብሁህ ፡ በጥቂት መከራ ገሠ
ፅኸኝ ፡ የሰባውን ዘመን መከራ
ኅዳጥ አለው ፡ የኋላው ተድላ
ደስታ በዝቶላቸዋልና፤ አንድም
አቤቱ በመከራዬ ቀን አሰብ
ሁህ ይላል ምእመን ፣ በጥቂት
መከራ ገሠፅከኝ ፣ የአምስቱን
ሺህ ከአምስት መቶ ዘመን
መከራ ኅዳጥ አለው ፤ የኋላው
ተድላ በዝቶላቸዋልና ፤

፲፮፡ ከመ እንተ ውስተ ማሕምም
እንተ አልጸቀት ለወሊድ ፣

ለመውለድ የደረሰች በምጥ
የተያዘች ሴት ፡

ወአውየወት በሕማማ ፣

ከመ እንተ ታዐወዩ በሕማማ
በምጡ እንድትጨነቅ ፡

ከማሁ ኮነ ለፍቁርከ ፣

ለወዳጅህ ለሕዝቅያስ እንዲህ
ተጨነቅን ፡

እግዚኦ በምንዳቤነ ተዘከርናከ ወበኅ
ዳጥ ሕማም ገሠጽከነ ፣

አቤቱ በመከራችን ጊዜ አሰብ
ንህ ፤ በጥቂት መከራ ገሠጽከን
ይላሉ ፤ ትሩፋን የሰባውን ዘመን
መከራ ኅዳጥ አለው ፤ ከፋርስ፤
ከባቢሎን ወጥተው ኢየሩሳሌም
ገብተው ኋላ የሚያደርጉት
ተድላ ደስታ በዝቶላቸዋልና ፤
አንድም በምንዳቤየ ይላል ፤ ሕዝ
ቅያስ በመከራዬ ጊዜ አሰብሁህ
በጥቂት መከራ ገሠጽከኝ ኅዳጥ
አለው ደዌው ሦስት ቀን ነውና፤
አንድም እግዚኦ በምንዳቤነ ተዘ
ከርናከ ወበኅዳጥ ሕማም ገሠጽ
ከነ በጥቂት መከራ ገሠጽከን
ይላሉ ምዕመናን ፤ ያምስቱን
ሺህ ካምስት መቶ ዘመን መከራ
ኅዳጥ አለው ከሲኦል ከገሃነም
ወጥተው ገነት መንግሥተ ሰማ
ያት ገብተው የሚያደርጉት የኋ
ላው ተድላ ደስታ በዝቶላቸዋ
ልና ፤ አንድም በአዝማነ መን
ግሥተ ሰማይ መጠን ኅዳጥ
አለው ፤

ከመ እንተ ውስተ ማሕምም እንተ
አልጸቀት ለወሊድ ፣

ለመውለድ የደረሰች በምጥ የተ
ያዘች ሴት ፤

ወአውየወት በሕማማ ፣

ከመ እንተ ተዐወዩ በሕማማ
በምጡ እንድትጨ ነቅ ፡

ከማሁ ኮነ ለፍቅሩከ እምቅድመ
ገጽከ ፣

ከገጸ መዓትህ የተነሣ ለወዳ
ጅህ ለሕዝቅያስ እንዲህ ተጨ
ነቅን ይላሉ ነቢያት ካህናት፤
አንድም ከማሁ ኮነ ፍቁርከ እም
ቅድመ ገጽከ ይላል፣ ወዳጅህ
ሕዝቅያስ ዘሩባቤል እንዲህ
ተጨነቀ ፤ አንድም ከመ እንተ
ውስተ ማሕምም ብለህ መልስ፤
ለመውለድ የደረሰች በምጥ የተ
ያዘች ሴት በምጡ እንድትጨ
ነቅ ለወዳጅህ ለምዕመን እንዲህ
ተጨነቅን ይላሉ መላእክት ፤
ወንድም ለወንድሙ እንዲያዝን
መላእክትም ለሰው ያዝናሉና ፣
አስተሐምሞተ አኀው ዐቢያን
ከመ ዘለንዑሳን እንዲል ፤

፲፯፡ በእንተ ፈሪሆትከ እግዚኦ ፀነስነ፣

አቤቱ አንተን መፍራት ፣ አን
ተን ማምለክ ስለተውን ዔዋዌ
አለ ሲሉ ሰማን ፤

ሐመምነሂ ፣

ከዚህ አስቀድሞ በአባር በቸነ
ፈር ተያዝነ ፤

ወወለድነ ፣

ዔዋዌን ተቀበልነ ማለት ተደ
ረገብን፤ አንድም አምልኮትህን
ስለያዝን ሚጠት አለ ሲሉ ሰማነ፤
ሐመምነሂ ከዚህ አስቀድሞ
ዔዋዌ ተደረገብን ፣ ወወለድነ፣
ሚጠትን አገኘን ማለት ተደረ
ገልን ፤ አንድም በእንተ ፈሪሆ
ትከ እግዚኦ ፀነስነ ፣ አቤቱ አን
ተን መፍራት ፤ አንተን ማም
ለክ ስለተውን ዔዋዌ ነፍስ አለ
ሲሉ ሰማን ፣ ሐመምነሂ ከዚህ
አስቀድሞ ርኂቅ እምእግዚአብ
ሔር አገኘን ፤ ወወለድነ ዔዋዌ
ነፍስን ተቀበልን ማለት ተደረ
ገልን ፤ አንድም አምልኮትህን
ስለያዝን ሚጠተ ነፍስ አለ ሲሉ
ሰማን ፣ ሐመምነሂ ከዚህ አስቀ
ድሞ ዔዋዌ ነፍስ አገኘን ማለት
ተደረገብን ፣ ወወለድነ ሚጠተ
ነፍስ ተደረገልን ፤

መንፈሰ አድኅኖትከ በዲበ ምድር፣

ትድግናህንየምትገልጥበት መን
ፈሰ ረድኤትህ በዚህ ዓለም ይሰ
ጣል ፤ አንድም ድኅነተ ነፍስ
የሚደረግበት ሕይወትህ መን
ፈስ ቅዱስ ለምዕመናን ይሰጣል፤

ወይወድቁ እለ ይነብሩ ዲበ ምድር፣

በለኪሶ የሠፈሩ እነሰናክሬም
ይጠፋሉ ፤

፲፰፡ ሙታን ይትነሥኡ ፣

በይሁዳ ያሉ ይነሣሉ ፤

ወየሐይዉ እለ ውስተ መቃብር፣

በለኪሶ ያሉ ይድናሉ ፣ እለ
ውስተ መቃብር አለ፣ በይሁዳ
ካሉ በለኪሶ ባሉ መከራ ፀንቶ
ባቸዋልና፤

www.ethiopianorthodox.org

ወይትፈሥሑ እለ ውስተ ምድር ፣ ሰናክሬም መጣ መጣ ባሏቸው ጊዜ በባሕር ጠልቀው ፣ በገደል ወድቀው የነበሩት እሱ ጠፍቶ ላቸው ደስ ይላቸዋል ፡

እስመ ጠል ዘእምኀቤከ ሕይወቶሙ ውእቱ ፣

ካንተ የተገኘ ጠለ ረድኤት ሕይወታቸው ነውና ፡ አንድም ሙታን ይትነሥኡ ፣ በይሁዳ የሚኖሩ ሁለቱ ነገድ ይነሣሉ ፡ ወየሐይዉ ፣ ዐሥሩ ነገድም ይነሣሉ ፡ እለ ውስተ መቃብር አለ፡ በቦታም በዘመንም አርቀዋቸዋልና ፡ ወይትፈሥሑ ስልምና ሶር ናቡከደነፆር መጣ መጣ ባሏቸው ጊዜ በባሕር ጠልቀው ፣ በገደል ወድቀው የነበሩት እሱ ጠፍቶላቸው ደስ ይላቸዋል ፣ (ጥቅስ) ወይነግርዎሙ ለደሰ ያት ሠናይቶ ለእግዚአብሔር እንዲል ፡ (ኢሳ. ምዕ. ፶፪ ፡ ፲፪) ፡

እስመ ጠል ዘእምኀቤከ ፣

ከአንተ የተገኘ ጠለ ረድኤት ሕይወታቸው ነውና ፡ አንድም ሙታን ይትነሥኡ እንደ ወልደ መበለት እንደ ወለተ አ.ያኢሮስ ያሉት ይነሣሉ ወየሐይዉ እንደ አልዓዛር ያሉትም ይነሣሉ ፡ ወይትፈሥሑ እለ ውስተ ምድር እንደ መዓጉዕ ያሉ በደዌ ዳኛ ባልጋ ቍራኛ ተይዘው የሚኖሩ ደስ ይላቸዋል፡

እስመ ጠል ዘእምኀቤከ ካንተ የተገኘ ጠለ ተአምር ሕይወታቸው ነውና ፡ አንድም ሙታን ይትነሥኡ እንደ ዐዳ እንደ ወግዳ ባለ የወደቁ ይነሣሉ ፣ ወየ ሐይዉ እለ ውስተ መቃብር የተቀበሩትም ይነሣሉ ፣ ወይትፈሥሑ እለ ውስተ ምድር ፡ ተለ ውጠው የሚገቡ ደስ ይላቸዋል ፡ (ጥቅስ) ንሕነ ንትዌለጥ በም ዕር ወኢንበጽሐሙ ለምውታን እንዲል ፡ ፩ ቆሮ.ም.፲፭ቁ.፶፪ ፡ አንድም እንደ ካፊያ የሚያረ ፈርፋቸው አለ ፡ ወይነፈንፎሙ ነፍኒፍ እንዲል ፣ እስመ ጠል ዘእምኀቤከ ሕይወቶሙ ውእቱ ካንተ የተገኘ ጠል መንፈስ ቅዱስ ሕይወታቸው ነውና ፡ አንድም ሙታን ይትነሥኡ በራሳቸው ፍዳ የተያዙ ይነሣሉ ፣ ወየሐይዉ እለ ውስተ መቃብር በናት ባባታቸው ፍዳ የተያዙትም ይድናሉ ፣ በራስ ፍዳ ላይ የናት ያባት ፍዳ ሲጨመር መከራ ይፀናልና ፣ ወይትፈሥሑ እለ ውስተ ምድር በዚህ ዓለም የሚኖሩ ምዕመናን ደስ ይላቸዋል ፣ እስመ ጠል ዘእምኀቤከ ሕይወቶሙ ውእቱ ፣ ካንተ የተገኘ ጠል መንፈስ ቅዱስ ሕይወታቸው ነውና ወታጠ ፍዕ ምድሮሙ ለኃጥኣን ፣

የሰናክሬምን ሀገር ታጠፋለህ ፡

፲፱፡ ሑር ሕዝብየ ወባእ ቤተከ ፣

ወገኔ ሁለቱ ነገድ ሐድ ፣ ወደ ቤትህ ግባ ፡ ከሰናክሬም ጋራ እዋጋለሁ አትበል ፡

ወዕዉ ኖኅተከ ወተኅባዕ ኀዳጠ ምዕረ ፣

ደጅህን ዘግተህ ጥቂት ወራት ተሠወር ፡

እስከ ዮኅልፍ መዓቱ ለእግዚአብሔር ፣

መዓቱ ሰናክሬም እስኪያልፍ ድረስ ፡ አንድም የእግዚአብሔር መዓቱ በሰናክሬም እስኪያልፍ ድረስ ፡ አንድም ወታጠፍዕ ምድሮሙ ለኃጥኣን ፣ የእስራኤልን አገር ታጠፋለህ ፣ ሑር ሕዝብየ ወባእ ቤተከ ፣ ወገኔ ሁለቱ ነገድ ሂድ ወደ ቤትህ ግባ ለዐሥሩ ነገድ ረዳለሁ አትበል ፣ ወእዑ ኖኅተከ ወተኅባዕ ሕዳጠ ምዕረ ፣ ደጅህን ዘግተህ ጥቂት ወራት ተሠወር ፣ እስከ ዮኅልፍ ፣ የእግዚአብሔር መዓቱ በዐሥሩ ነገድ እስኪያልፍ ድረስ ፣ አንድም ወታጠፍእ ምድሮሙ ለኃጥኣን ፣ የአይሁድን የአጋንንትን የመናፍቃንን አገር ታጠፋለህ ፣ ሑር ሕዝብየ ፣ ወገኔ ምዕመን ሂድ ወደቤትህ ግባ ደጅህን ዘግተህ ጸልይ ውዳሴ ከንቱ ፣ ስብሐት ብጡል እንዳይሆንብህ ፡ አንድም አስተጋብዕ ሕዋሳቲከ ብሎ ወስዶታል ፣ ጸሎት በያዙ ጊዜ ዐይንን ከርእይ ፣ ዕዝንን ከሰሚዕ ፣ እጅን ከገሚሥ ፣ እግርን ከሐዊር ተዐምቶ ሊጸልዩ ይገባልና ፡ አንድም አንቀጸ ጸሎት አለና ስልት ስልቱን ዐውቀህ ጸልይ ሲል ነው ፡ እስከ ዮኅልፍ ፣ ይህ ዓለም እስኪያልፍ ድረስ ፣ ይህን ዓለም መዓት አለው ፣ መዓቱም ፡ ምሕረቱም ይደረግበታልና ፡

፳፡ ናሁ እግዚአብሔር ያመጽእ መቅሠፍተ እምነ መቅደሱ ዲበ እለ ይነብሩ ውስተ ምድር ፣

እነሆ እግዚአብሔር ከምስጋናው ማደሪያ ከሰማይ በለኪሶ በሰፈሩ በነሰናክሬም መዓቱን ፣ መቅሠፍቱን ያመጣል ፡

ወትክሥት ምድርኒ ደማ ፣

ለኪሶ ደሟን ትገልጣለች ፣ በሰይፈ መልአክ እንደጠፉ ለማ ጠየቅ ፣ ባፋቸው ፣ ባፍንጫቸው ደም እየሆነ ተገኝቷልና ፡ አንድም ናሁ እግዚአብሔር ያመጽእ መቅሠፍተ እምነ መቅደሱ ብለህ መልስ ፣ እነሆ እግዚአብሔር ከምስጋናው ማደሪያ ከሰማይ በኢየሩሳሌም ባሉ በእስራኤል መቅሠፍት ያመጣል ፣ ወትክሥት ምድርኒ ደማ ፣ ቤተ እስራኤል ከባቢሎናውያን ደሟን ትመልሳለች ፡

www.ethiopianorthodox.org

ወኢትከድኖሙ ለቅቱላን ፣

ለኪሶ የሞቱትን አትሠውራቸ ውም ማለት ዕገሌ የዕገሌ ገዳይ ነው ትላለች ፣ አሁን ዔዋዊንና ሚጠትን አንድ ጊዜ አወረደ፤ አንድም ናሁ እግዚአብሔር ያመጽእ ብለህ መልስ ፤ እነሆ እግዚአብሔር ከምስጋናው ማደሪያ ከሰማይ በባቢሎን ሰዎች መቅሠፍት ያመጣል ፤ ወትከሥት ምድርኒ ደሟ፣ ቤተ እስራኤል በሰባ ዘመን ደሟን ትመል ሳለች ወኢትከድኖሙ ለቅቱላን፤ አንተ ያባቴ ደመኛ አንተ የወንድሜ ደመኛ አይደለህምን እያለች የሞቱትን አትሠውራቸውም::

ምዕራፍ ፷፯

፩፤ ይእተ አሚረ ያመጽእ እግዚአብሔር መጥባሕተ ዐቢየ ወዕኑዐ ላእለ ከይሲ ፣

ያንጊዜ እግዚአብሔር በእባብ ላይ ተራዛሚ ዕኑ ሾተልን ያመጣል ማለት ናቡከደነጾርን በኪራም ላይ ያመጣል ፤

ወአርዌ ምድር ዘየአኪ እምከይሲ ፣

ዘየአኪ ለማለት ደገመው ከእባብ የሚከፋ እባብን ያመጣል አለ፣ ከኪራም የሚከፋ ናቡከደነጾርን ያመጣል፣ አንድም ላዕለ ከይሲ መጥባሕተ ዐቢየ ወአርዌ ምድር ዘየአኪ እምከይሲ ይላል፣ ከኪራም የሚከፋ ናቡከደነጾርን በኪራም ላይ ያመጣዋል ፤

ወይቀትሎ ለከይሲ ዘውስተ ባሕር ፣

በባሕር ውስጥ ያለ ኪራምን ይገድለዋል ፣ ታሪክ በባሕር ውስጥ የኪራም ሞት እንደምን ነው ቢሉ፣ ኪራም የሚኖር በደሴት ነው፤ ነገሥታቱ ሊወጉት ይመጣሉ፣ ከደሴት ሆኖ አልመቻቸው እያለ ይመለሱ ነበር፣ ናቡከደነጾርም ሊወጋው መጥቶ ከበበው አልመቸው ቢል ሠራዊቱ ብዙ ናቸውና ደንጊያውን እየፈነቀላችሁ እንጨቱን እየቈረጣችሁ መሬቱን እየቈፈራችሁ ባሕሩን ምሉት አላቸው፤ ድንጊያውን እየፈነቀሉ እንጨቱን እየቈረጡ መሬቱን እየቆፈሩ ባሕሩን ይመሉት ጀመር ፣ ይህንን ኪራም ሰማ፤ እሸሻለሁ መስሎት ወርቁን ብሩን ከባሕር ያስጥል ጀመር ናቡከደነጾር ያስጣለው እንጨት ደንጊያ የሱ ገንዘብ ተገናኝቶ እንደድልድይ ሆነ፣ እንግዲህማ በዚህ ተሻግሮ ሊገድለኝ አይደለምን ብሎ በብረት ሣጥን አድርጋችሁ ምግቤን ጨምራችሁ ከባሕር ጣሉኝ አለ በብረት ሣጥን አድርገው ምግቡን ጨምረው ከባሕር ላይ ጣሉት፣ ማዕበሉ እያንጓለለ ናቡ

ከደነጾር ካለበት ወሰደው ፤ አምጡት ብሎ አስመጥቶ ቢያየው ንጉሡ ኪራም ሆነ ፤ ከሣጥኑ አስወጥቶ እንደ በግ አሳርዶታልና ዘየአኪ እምከይሲ አለ ፤

፪፤ ውእተ አሚረ ዐወደ ወይን ሠናይ ወመፍትው ዘእምትካት ዘዚአሃ ሀገር ዕንዕት ፣

ዘዚአሃ ለዐወደ ወይን እንደማለት ያንጊዜ አውራጃዋ ሁሉ የፀና ከጥንት ጀምሮ ያማረች የተወደደች ሕጉ የሚነገርባት ኢየሩሳሌም ነበረች ፤

፫፤ አሐተ ሀገረ ይዐብዑ ፣

ነገር ግን እነሰናክሬም አንዲት አገር ለኪሶንን ይወጋሉ ፤ አንድም ከጥንት ጀምሮ ያማረች የተወደደች አውራጃዋ ሁሉ የፀና አንዲት አገር ኢየሩሳሌም እንነናቡከደነጾር ይወጋሉ፤

ወከንቶ አስተይከሞ ፣

ከንቱ የሚያደርጋት የመቅሠፍቱን አረቂ አጠጣኋት ፤

ሌሊተ ትሠገር ፣

ቀን ሲገሠግሡ ውለው ሌሊት አደጋ ጥለው ያጠፏታል፣ አንድም በሌሊተ መከራ ተይዛ ሳለች ያጠፏታል ፤

ወመዓልተ ይወድቅ ዐረፍታ ፣

በመዓልት ቅጽሯ ይፈርሳል ፤ አንድም ዐርበኛዋ ይጠፋል ፤

ወአልቦ ዘያነሥኣ ፣

የሚያድናት የለም ፤

ጉባዔ

፬፤ መኑ ይሁበኒ ሕለተ ወሣዕረ በእንተ ፀብአ አውዕዮ በእሳት፣

ይቤ ነቢይ ብሎ ያመለክታል፣ ነቢዩ ኢሳይያስ ስለጠቡ ምልክት አድርጌ በእሳት አቃጥለው ዘንድ ቀርቅሃ ሸንበቆ ማን በሰጠኝ አለ፣ ነቢያት ሳያጡ መመኘት ልማዳቸው ነው ፣ ሂኖክ መኑ ይሁበኒ ከመ ይኩና አዕይንትየ ደመናተ ማይ እንዳለ፣ ኤርምያስም መኑ ይሁበኒ ማየ ለርእስየ ወፈልፋለ አንብዕ ለአዕይንትየ እንዳለ ፣ ኤር. ፱፥፩ ሂኖ ፴፮፡ ፲፱ኢሳይያስም እንዲህ አለ፣ እንደ እሳቱ እነና ቡከደነጾርን ፣ እንደ ቅርቅሃው፣ እንደ ሸንበቆው አስራኤልን አድርጎ ተናገረ ፣ ሕለተ ወሣዕረ ባለው ዐቃበ የሚል አብነት ይገኛል፣ ሕለተወሣዕረ ማለት ነው፣

ወይእዜኒ ናሁ በእንተ ዝንቱ ጉባረ እግዚአብሔር ኮሎ ዘነበበ ፣

ስለዚህ ነገር እግዚአብሔር የተናገረውን ሁሉ አደረገ ፤ አንድም እስራኤል የሚጠፉ ስለሆነ እግዚአብሔር በነቢያት አድሮ አስማርካችኋለሁ ብሎ የተናገረውን አደረገ ፤

www.ethiopianorthodox.org

እስመ ውዕዩ ፣

በኃጢአት ተናደዋልና ፤

፭፡ ወዐውየዉ እለ ይነብሩ ውስተ ምድር ፣

በኢየሩሳሌም የሚኖሩ ሰዎች ከቤተ ጣዖት ገብተው ስምዐነ በዐል፣ ስምዐነ ቤል እያሉ ጩኸ ዋልና፣ አንድም ድኸውን አስ ጩኸዋልና፤ አንድም አጥፉን አጥፉን ብለው ጩኸውናልና ፣ አጥፉን አጥፉን ብለው ጩኸው አይደለም፣ ሕገ እግዚአብሔርን አፍርሶ ኃጢአት መሥራት ፣ ጣዖት ማምለክ አጥፉን ብሎ መጮኸ ነውና ፤

፮፡ ወካዕበ ይከውን ሰላም ለቤተ እስራኤል ወለቤተ ይሁዳ ፣

ዳግመኛም ለዐሥሩ ነገድና ለሁ ለቱ ነገድ ተድላ ደስታ ይደ ረጋል፣ ለዔዋዊ ሚጠትን ያልተ ካከለ ካዕበ አለ ፡ አንድም የተ ካከለ ለዳዊት ለሰሎሞን ካዕበ አለ ::

እስመ ይሠርፅ ወይፈሪ ያዕቆብ ወእስ ራኤል ፣

ዐሥሩ ነገድ ሁለቱ ነገድ በረ ድኤት ይለመልማል ፤ ልጅ ይወልዳልና ፤

ወይመልዕ ዓለመ ፍሬሆሙ ፣

ልጃቸው በዓለም ይመላል ፤

ወኢይትቀሠፉ ዳግመ ፣

ዳግመኛ በመከራ አይገረፉም፡ ለዐሥሩ ነገድ ሁለቱን ነገድ፣ ለሁለቱ ነገድ መቃብያንን ዳግመ አለ ፣

፯፡ ዳዕሙ በከመ እሙንቱ ተቀሥፉ ወበከመ እሙንቱ ተቀትሉ ፣

እነሱ በመከራ እንደተገረፉ እነ ዚያ እንደሞቱ ፤

፰፡ ከማሁ ይቀሥፉ ወይቀትሉ ሰብአ በባእስ ወበዝንጓጌ ፣

በማሽሚጠጥ በፀብ ሌላውን ይገ ድላሉ ፣ ሌላውን ይገርፋሉ እንጂ ፣ ኢይትቀሠፉ ዳግመ ላለው ይቀንይዎሙ ብሎ ማንሻ፣ አንድም እነሱ እንደተቀ ሠፉ፣ እነሱ እንደሞቱ በባእስ ወበዝንጓጌ ይቀንይዎሙ ለእለ ቀተልዎሙ ፣ ያጠፏቸውን ሰዎች በጠብ በማሽሚጠጥ ይገ ዟቸዋል ፣ አንድም ማካፈል ነው፣ ይቀትሉ ሰብአ በባእስ ፣ በጠብ ሰውን ይገድላሉ እንጂ ፣ ኢይትቀሠፉ ላለው ወበዝንጓጌ ይቀንዮሙ ለእለ ቀተልዎሙ በማሽሚጠጥም ያጠፏቸውን ሰዎች ይገዙአቸዋል ፤

በመንፈሰ መዓት ወበመንፈስ እኩይ፣

በቁጡ ልቡና በክፉ ልቡና ማለት ተቈጥተው ይገዙዋቸዋል፣

፱፡ በእንተ ዝንቱ ተሥዕረ ኃጢአቱ ለያዕቆብ ፣

ይሠዐር ሲል ነው ፤ ስለዚህ ነገር የያዕቆብ ኃጢአቱ ይሠረያል ፤ አንድም መከራ ስለተቀበለ የያ ዕቆብ ኃጢአቱ ተሠረየ ፤

ወዝንቱ ውእቱ በረከቱ አመ አዕተ ትኩ ኃጢአቶ ፣

ኃጢአቱን ባራቅሁለት ጊዜ የሚ ያገኘው ክብሩ በረከቱ ይህ ነው፤

ኀበ አንበሩ ዕበኒሆሙ ይከውን ከመ ግብሱስ ድቁቅ ፤

ጣዖቱን ካኖሩበት እንደለዘበ ደንጊያ እንደ ደቀቀ ገለባ ይሆ ናል ፡

ውኀበ አንበሩ ዕፀዊሆሙ ወምኅራ ማተ ጣዖቶሙ ይየብስ ከመ ዘተገ ዝመ ያም ፣

ጣዖታቸው መስገጃቸው እንደ ተቈረጠዛፍ ካኖሩበት ቦታ ይደ ርቃል ማለት በነፍስ በሥጋ ጥቅም አያሰጥም ፤ አንድም ውኀበ አንበሩ ጣዖቶሙ ይየብስ ይላል፡ ጣዖቱን ያኖሩበት ቦታ ይደርቃል አለ ፡ ጠለ ረድኤት አይገኝበትም ፤

፲፡ ወይከውን ከመ ማኅደረ መራ ዕይ ዘኀደግዎ ጕንዱየ መዋዕለ ፣

ብዙ ዘመን እንደ ተዉት እንደ ላሙ ምሳግ ይሆናል ፤

ወጐንድዮ ይየብስ ፣

ዘግይቶ እንደሚደርቅ፣ አንድም ዘግይቶ ይደርቃል ፤

ወኢይትረከብ ውስቴቱ ኵሉ ሐመ ልማል ፣

በውስጡ ልምላሜ እንደማይገ ኝበት እንደ ምሳጉ ይሆናል፣ አን ድም ልምላሜ አይገኝበትም ፤

፲፩፡ አንስት እለ ትመጽኣ እምነ ቲያሳ ነዓ ብክያ ፣

ቲያሳ ቲአሳ ትያሳ ይላል ፤ ቲያሳ በግብፅ ያለች ሀገር ናት፣ አንድም በኢየሩሳሌም ያለች ሀገር ናት ፣ ያልቃሽ የዘፋኝ አገር ናት፡ ከቲያሳ የምትመጡ ሴቶች ኑ አልቅሱ ፤

ወአስቈቅዋ በእንተ ሕዝብየ ፣

ስለወገኖቼ ሙሾውን አውጡ ፤

እስመ ሕዝብ ዘአልቦሙ ልብ እሙ ንቱ ፣

እስራኤል አእምሮ የሌላቸው ወገኖች ናቸውና ፤

፲፪፡ በእንተ ዝንቱ ኢይሠሃሎሙ እግ ዚአብሔር ፈጣሪሆሙ ፣

ስለዚህ ነገር አእምሮ የሌላቸው ስለሆኑ ፈጣሪያቸው እግዚአብ ሔር ይቅር አይላቸውም ፤

ወኢይምሕሮሙ ዘገብሮሙ ፣

የፈጠራቸው እግዚአብሔር አይ ራራላቸውም ፤

www.ethiopianorthodox.org

፲፫፡ ወውእተ አሚረ የኀፅር እግዚአ ብሔር እምነ ፈለግ እስከ ሪኖን ቆሪ ኖን ፣

እምጽንፍ እስከ ጽንፍ እም ባሕር እስከ ባሕር ሲል ነው ያን ጊዜ እግዚአብሔር ከጽንፍ እስከ ጽንፍ ከባሕር እስከ ባሕር ድረስ በጦር ያጥረዋል፤ አንድም ሪኖን ቆሪኖን ስመ ሀገር ነው፤ እስከ ሪኖን ቆሪኖን ድረስ በጦር ይከ ባል ፤

ወአንትሙሰ አስተጋብዕዎሙ ለደ ቂቀ እስራኤል በበአሐዱ ፣

አሕዛብ በዔዋዌ የእስራኤልን ልጆች ሰብስቧቸው ፣ አንድም ነቢያት ካህናት እንደነሱ እንዳ ትሆኑ እስራኤልን ምከሯቸው፣ አስተምሯቸው፣ አንድም ቂሮስ ዳርዮስ በሚጠት እስራኤልን ሰብስቧቸው ፤

፲፬፡ ወውእተ አሚረ ይነፍሑ በቀ ርን ዐቢይ ፣

ቀርነ ዐቢየ ሲል ነው፣ ያንጊዜ እስራኤል በሚጠት ነጋሪቱን ይመታሉ፣ እስራኤል ከፋርስ ሲወጡ ነጋሪት እየመቱ እየዘ ፈኑ ወጥተዋልና ፤

ወይመጽኡ እለ ተነጕሉ በግብጽ ይስ ግዱ ለእግዚአብሔር በደብረ መቅ ደሱ ዘኢየሩሳሌም ፣

በግብፅ ጠፍተው የነበሩ እስራ ኤል በኢየሩሳሌም ባለ በቤተ መቅደስ ለእግዚአብሔር ይሰ ግዱ ዘንድ ይመጣሉ ::

ምዕራፍ ፳፰

፩፡ አሌ ሎ ለአክሊለ ትዕቢቱ ወጽ እለቱ ለኤፍሬም ፣

ኤፍሬም ዐሥሩ ነገድ ለሚሳደ ብበት ለሚታበይበት ለዘውዱ ወዮለት ፤

ይከውን ከመ ጽጌ ዘወድቀ እም ከተማሁ እምውስተ ርእሰ ደብር ግዙፍ ፣

ልዑል ሲል ነው፤ ከረጅም ተራራ ራስ ከጫፉ እንደ ወደቀ አበባ ይሆናል፣ አንድም ከጫፉ ከተራ ራው ራስ እንደ ወደቀ አበባ ይሆናል፤ ዛፉ ያለ ከተራራው ላይ ነው፣ ከዛፉ በተራራው ላይ ሲወድቅ ከተራራው ላይ ነፋስ ይጠራርገዋልና ፤

ግዝምዎሙ ለእለ ሰክሩ ዘእንበለ ወይን ፣

ቅትልዎሙ ሲል ነው፣ ወይን ሳይጠጡ በኃጢአት አረቂ የሰ ከሩትን አጥፉዋቸው ፤

፪፡ ናሁ ፅኑዕ ወዕቡብ መቅሠፍተ መዓቱ ለእግዚአብሔር ፣

እነሆ እግዚአብሔር ተቈጥቶ የሚያመጣው መቅሠፍት ጭንቅ ነው ድንቅ ነው፤ ሕጉን

ያልጠበቁ አምልኮቱን ያላፀኑ ሰዎችን ያስጨንቃልና፣ ጭንቅ ነው አለ፣ ሕጉን ለጠበቁ አምል ኮቱን ላፀኑ ያስደንቃልና ድንቅ ነው አለ ፤

ከመ በረድ ዘይወርድ በኀይል ፣

በዝቶ እንደሚወርድ በረድ ፤

ወኢይትመየጥ ብዝኑ ፣

ከብዛቱ እንዳይከፈል ፤

ወምሉዕ ዘይውኅዝ ፣

በዝቶ እንደሚወርድ ፤

ወይገብር ዕረፍተ በምድር ወበብሔር ፣

በከተማውም በገጠሩም ፀንቶ እንደሚውል እንደሚ ያድር በረድ ፅኑ ነው ይገብር ዕረፍተ ማለቱ ድካም ኖሮበት ያርፋል ማለት አይደለም ፣ የሚ ረጋ በረድ ፅኑ እንደሆነ ፅኑ ነው፤

፫፡ ወይከይድዎ በእገሪሆሙ ወእደ ዊሆሙ ለአክሊለ ዕዕለቶሙ ለሰብአ ኤፍሬም ፣

ዐሥሩ ነገድ የሚሳደቡበትን ዘውድ በዔዋዌ ከራሳቸው በእ ጃቸው አውርደው በእግራቸው ይረጋግጡታል ፤

፬፡ ወይከውኑ ከመ ጽጌ ፣

እንደ አበባ ይሆናሉ ማለት አበባ በደረቀ ጊዜ ከዚህ ደረሰ እንዳ ይባል ይጠፋሉ ፤

ወይወድቁ እምትውክልተ ክብሮሙ ፣

በባለጸግነታቸው ከመታመን ይርቃሉ አንድም ከሚከበሩበት ከባለጸግነታቸው ተለይተው ይጠፋሉ ፤

ውስተ ርእሰ ደብር ነዋኅ ከመ ዘር እየ በኵረ በለስ ፣

ፍሬ በለስ ሲል ነው፣ አንድም እንዳለ ይሆናል፤ በረጅም ተራራ ላይ በኵረ በለስን ያየ ሰው ፤

ይረውፅ ኀቤሃ ፣

ፈጥኖ ወደሷ እንዲሄድ ፤

ወይፈቅድ ከመ ይንሥአ በእዴሁ ወይትመጠዋ በአፉሁ ፣

በእጁ ቆርጦ እየሳሳ በአፉ እን ዲመገባት፣ በዔዋዌ አሕዛብ እስ ራኤልን ፣ በሚጠት እስራኤል አሕዛብን እየሳሱ ይማርኳቸ ዋል ፤

፭፡ ወውእተ አሚረ ይከውኖሙ እግ ዚአብሔር ጸባዖት አክሊለ ስብሐት ዘተፀፍረ ፣

ያንጊዜ በሚጠት እግዚአብሔር የተነቀሰ የተቀረፀ የተኰላ የተ ታታ ዘውድ ይሆናቸዋል ፤ ያ እንዲያስከብር ያስከብራቸዋል፤

ለእለ ተጽዕሉ ሕዝብ ፣

ለተሰደቡ ወገኖች ፤

www.ethiopianorthodox.org

ወእለ ተርፉ በመንፈሰ ኵነኔ ወፍ
ትሕ ፤

ጠላቶቹን ፈርዶ በሚያጠፋበት
ወዳጆቹን ፈርዶ በሚያድንበት
ሥልጣኑ ለቀሩ፣ አንድም ፈርዶ
የባቢሎንን ሰይፍ በሚያጠፋ
በት ፈርዶ እስራኤልን በሚያ
ድንበት ሥልጣኑ ለቀሩ ፤

፭፡ ወበጎይለ እግዚአብሔር ፤

በጎይለ እግዚአብሔር እለ ተርፉ
ብለህ ግጠም ፤ በእግዚአብሔር
ጎይል ለቀሩ ወገኖች ያ እንዲ
ያስከብር ያስከብራቸዋል ፤

ወይነጽሑ አንቆቅሆሙ ፤

እንቁላላቸውን እየጣሉ ይሸ
ሻሉ፣ አንድም ልጆቻቸውን እየ
ጣሉ ይሸሻሉ ፤ አንድም ጣያታ
ቸውን እየጣሉ ይሸሻሉ ፤

፮፡ እስመ እለ ሰክሩ በወይን ፤

በወይን የሰከሩ ናቸውና ፤

ወአስሐቶሙ ሜስ ፤

ወይን አስቷቸዋልና ፤

ወአደንገየሙ ሜስ ለካህናት ወለነ
ቢያት ፤

ነቢያተ ሐሰትን፣ ካህናተ ጣያ
ትን ወይን አስደንግጧቸዋልና
ወይን ጠጥተው፣ ኃጢአት ሠር
ተው መከራ መጥቶባቸው ደን
ግጠዋልና ፤

ወአስጠሞሙ ወይን ፤

ወይን በባሕረ መከራ አሰጠማ
ቸው ፤

ወጊገዩ በስካር ፤

ሰክረው በደሉ ፤

ወዝኒ ምትሐተ ዐይን ውእቱ ፤

ይኸውም ያይን ምሣ ነው፤ ለጊ
ዜው ደስ ያሰኛልና፣ አንድም
ለዐይን ምትሐት ነው አለ
ታይቶ ይጠፋልና ፤

፰፡ ወመልዐ ትፋአ ኵሉንታሁ
ማዕድ፣

ማዕዳቸው ትፋዕን መላ ማለት
በልተው ጠጥተው ከዚያው ይተ
ፋሉና፣ አንድም ወመልዐ ትፋዕ
ማዕደ ሕጋቸው ሕግ ጣያችን
መላ ፤

ወይመክሩ ከመ ይትወገሉ ነዳየ ፤

ድሀውን ይቀሙ ዘንድ ይመክ
ራሉ ፤

ለመኑ ንዜኑ ዜና ፤

አንትሙስ አስተጋብዕዎሙ ለደ
ቂቀ እስራኤል ብሎ ነበርና ፤
አንተ አስተምሩ ትለናለህ እንጂ
ለማን እናስተምራለን ፤

፱፡ ኵሉሙ ኵኑ ከመ ሕፃናት እለ
አጥድግዎሙ ጠቢወ ጥብ ፤

ሁሉም ጡት እንዳስጣሏቸው
ሕፃናት ሆነዋል ፤ ሕፃናት እን

ዳይሰሙ አይሰሙም ፤ ሕፃናት
እንዲበሳጩ ይበሳጫሉ ፤ ለመኑ
ንዜኑ አስተምሩ ትለናለህ እንጂ
ለማን እናስተምራለን ፤

፲፡ ወኢይሰምዑ ከመ ዘበካልዕ ልሳን
ይትናገርዎሙ ፤

አበ እመ ብለው በሚናገሩበት
በዕብራይስጥ ቋንቋ ቢነግሯ
ቸው በሌላ ቋንቋ እንደነገሯ
ቸው አድርገው የማይሰሙ ሆነ
ዋል፤ ትች፤ አስተምሩ ትለናለህ
እንጂ ብናስተምርስ ማን ይሰ
ማናል ፤ አንድም ነቢይ እየሞተ
ነቢይ ፤ ካህን እየሞተ ካህን ተተ
ክቶ ቢያስተምራቸው የማይ
ሰሙ ሆነዋል ፤ ትች ፤ አንድም
ከመ ዘበካልዕ ልሳን ይትናገር
ዎሙ ፤ ኋላ አሕዛብ ማርከው
ወስደው በማያውቁት ቋንቋ
ይናገሯቸው ዘንድ የማይሰሙ
ሆነዋል ፤ ትች፤ አስተምሩ ትለ
ናለህ እንጂ ብናስተምርስ ማን
ይሰማናል ፤ አንድም ሥላሴ
ነቢይ ቢሞት ነቢይ ፤ ካህን
ቢሞት ካህን እያስነሡ በአብራ
ይስጥ ቋንቋ ቢያስተምሯቸው
በሌላ ቋንቋ እንደሚያስተም
ሯቸው አድርገው አይሰሙም፤
ለመኑ ንዜኑ ዜና ፤ አስተምሩ
ትለናለህ እንጂ ለማን እናስተ
ምራለን ፤

፲፩፡ ወይብልዎሙ ዝንቱ ድቀቱ
ለዘይሰቲ ወይነ ፤

ወይን ለሚጠጣ ሰው ጥፋት
ይህ ነው ይሏቸዋል ፤

ወዝንቱ ቅጥቃጤሁ ፤

በመከራ መቀጥቀጡ ይህ ነው፤

፲፪፡ ወዐበዩ ሰሚዐ ዘይክውኖሙ
ቃለ እግዚአብሔር ፤

ዘይረብሖሙ ዘይበቍዖሙ ሲል
ነው፤ የሚረባቸውን፣ የሚጠቅ
ማቸውን ቃለ እግዚአብሔር
መስማትን እንቢ አሉ ፤

፲፫፡ ሕግመ በዲበ ሕማም ተወክፉ፣

በመከራ ላይ መከራ ተቀበሉ
ማለት በአባር በቸነፈር ላይ
ዔዋዌን ተቀበሉ ፤

ወተመጠዉ ተስፋ በዲቦ ተስፋ ፤

ውነሏቸው ሰብዓ ዓመት ባለው
ላይ ሚጠትን አገኙ ፤

ዓዲ ጎዳጠ ወዓዲ ጎዳጠ ፤

አሁንም ጥቂት ቆይተው አሁ
ንም ጥቂት ቆይተው፤ አንድም
ነቢያተ ሐሰት፣ ካህናተ ጣያት
አባር ቸነፈር አይመጣባችሁም
ዔዋዌ አይደረግባችሁም እያሉ
በተስፋ ላይ ተስፋ እየሰጧቸው
እስራኤል አሁንም ጥቂት ቆይ

www.ethiopianorthodox.org

ተው፣ አሁንም ጥቂት ቆይተው በመከራ ላይ መከራ ተቀበሉ፤

ከመ ይሑሩ ፣

ተማርከው ይሄዱ ዘንድ ፤

ወይደቁ ድኅሪተ ፣

ወደኋላ ይወድቁ ዘንድ ማለት ወደኋላ የጣሉት እንዲጎዳ ይጎዱ ዘንድ ፣

ወይትቀጥቀጡ ፣

በመከራ ሥጋ ይቀጠቀጡ ዘንድ

ወይሠገሩ ፣

በመከራ ሥጋ ይያዙ ዘንድ ፤

ወይትመንደቡ ፣

በመከራ ሥጋ ይጨነቁ ዘንድ፤ አንድም ሕማመ በዲበ ሕማም ተወክፉ ብለኸ መልስ፤ ሰማዕታት በመከራ ላይ መከራ ተቀበሉ፤ ወተመጠዉ ተስፋ በዲበ ተስፋ፣ በክብር ላይ ክብር አገኙ፤ ዓዲ ኀዳጠ ወዓዲ ኀዳጠ፣ አሁንም ጥቂት ቆይተው፣ አሁንም ጥቂት ቆይተው በትሩፋት ላይ ትሩፋት እየሠሩ፣ መከራ እየተቀበሉ በክብር ላይ ክብር አገኙ፣ ተወስኮ ዘነሣእያን አይገታምና፤ ጥቅስ ወራኅበ እንግድዓ ዘአልቦ መሥፈርት ፣ ወሀለወ ይትዌሰክ ስን በዲበ ስን እንዲል ፤ ዮሐ.አ.ተ.ግ. ፤ አንድም ስማቸው እየተጠራ ገድላቸው እየተነበበ በክብር ላይ ክብር ሲጨመር ይኖራልና፣ ከመ ይሑሩ፣ ወደ ዐላውያን ነገሥታት፣ ወደ ዐላውያን መኳንንት ይሄዱ ዘንድ፣ ወይደቁ ድኅሪተ፤ በሥጋ ይጐዱ ዘንድ ወይትቀጥቀጡ፣ በመከራ ይቀጠቀጡ ዘንድ፣ ወይሠገሩ፣ በመከራ ይያዙ ዘንድ፣ ወይትመንደቡ፣ በመከራ ይጨነቁ ዘንድ ፤

፲፬፡ ወበእንተ ዝንቱ ስምዑ ቃለ እግዚአብሔር ዕደው ዕቡያን ፣

ስለዚህ ነገር ትዕቢተኞች ሰዎች የእግዚአብሔርን ቃል ስሙ፣ ዕደው ጥውቃን በመከራ የተጨነቃችሁ ዕደው ስሙያን፣ ስመ ጥሩዎች ዕደው ጽሙማን ጽሙማነ ዕዝን የምትሆኑ ስሙ ፤

ወመላእክተ ሕዝብ ዘኢየሩሳሌም ፣

በኢየሩሳሌም ያሉ የሕዝቡ አለቆች ስሙ ፤

፲፭፡ እስመ ትቤሉ ተመሐልነ ምስለ ሲኦል ወተካየድነ ምስለ ሞት ፣

ከሞት ከመቃብር ጋራ ተማምለናል ብላችኋልና ማለት ሞት መቃብር አያገኘንም ብላችኋልና፤ አንድም ሲኦል ያላት ፋርስ ባቢሎን፤ አንድም ገሃነም ናት፤ ሞት ያለው ስልምናሶር ናቡከደ

ነፆር፣ አንድም ዲያብሎስ ነው፤ ፋርስ ባቢሎን አንወርድም ስልምናሶር ናቡከደነፆር አያገኘንም ብላችኋልና ፤ አንድም ዲያብሎስ ገሀነም አያገኘንም ብላችኋልና ፤

ከመ ይበጽሐክሙ ዐውሎ ወየሐፍሰክሙ ነፋስ ፣

ዕኑ መከራ እንዲመጣባችሁ ስሙ፤ አንድም ስልምናሶር ናቡከደነፆር ፤ አንድም ዲያብሎስ እንዲማርካችሁ እነግረክሙ ያለበት ነው እነግራችኋለሁ ፤

ወትብሉ ይእተ አሚረ ሐሰት ውእቱ ተስፋነ ወተካየድነ ለከንቱ ፣

አለኝታችን ሐሰት ነው፤ ለከንቱ ነገር ተማማልን ብላችሁ ንስሐ ካልገባችሁ ተስፋችን ፣ አለኝታችን ከንቱ ነው ትላላችሁ ፤

፲፮፡ ወበእንተ ዝንቱ ከመዝ ይቤ እግዚአብሔር እግዚእ ፣

ስለዚህ ነገር ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ አለ፤ ምን አለ?

ናሁ አነ እሠይም ውስተ ጽዮን ዕብነ ማዕዘንት ውስተ መሠረታ ኅሪት ወክብርት ፣

ውስተ ጽዮንና ውስተ መሠረታ አንድ ወገን ነው ፤ ኅሪት ክብርት የምትሆን ባራቱ ማዕዘን የምትነገር ኦሪትን በጽዮን መዲና በኢየሩሳሌም እንድትነገር አድርጋታለሁ ፤

እንተ ብዙኅ ሤጣ ፣

የምታሰጠው ክብር ብዙ የሆነ፤

ወዘአምነ ባቲ ኢይትኀፈር ፣

ያመነባት ሁሉ የማያፍር የሆነ ኦሪትን በጽዮን መዲና በኢየሩሳሌም እንድትነገር አደርጋታለሁ፤ አንድም ናሁ አነ እሠይም ብለህ መልስ፤ እነሆ እኔ ኅሩይ ክቡር የሚሆን አራቱን ማዕዘን የሚገዛ ዘሩባቤልን በኢየሩሳሌም አነግሠዋለሁ፤ እንተ ብዙኅ ሤጣ የምግባር የሃይማኖቱ ዋጋ ብዙ የሚሆን ወዘአምነ ባቲ ኢይትኀፈር፣ በሱ ያመነ የማያፍር የሆነ ዘሩባቤልን በኢየሩሳሌም አነግሣለሁ ፤

፲፯፡ ወእሬሲ ተስፋ በጽድቅ ፣

ውነሊቆ ሰብዓ ዓመት፣ እትቤቀሎ ለንጉሠ ባቢሎን ወለኵሉ ሰብኡ ኤር. ም. ወእምድኅረ ሰብዓ ዓመት እሔውፀክሙ በሣህል ያልሁትን በውነት አደርጋለሁ ፤

ወሣህልየኒ በመዳልው ፣

ይቅርታዬንም መጥኜ መጥኜ አደርጋለሁ ማለት በሰባ ዘመን አደርጋለሁ፤ አንድም ናሁ አነ እሠይም ብለህ መልስ ፣ ኅሩይ ክቡር የሚሆን ባራቱ ማዕዘን ምሉ የሆነ ክርስቶስን በማኅፀነ

www.ethiopianorthodox.org

ማርያም እንዲያድር አደርጋለሁ፣ እንተ ብዙኅ ሜጣ፡ ለምዕመናን የሚሰጠው ክብር ብዙ የሆነ፣ ወዘአምነ ባቲ ኢይትኅፈር፣ በሱ ያመነ ሁሉ የማያፍር የሆነ ክርስቶስን በማኅፀነ ማርያም አሳድራለሁ፡ አንድም ናሁ እሠይም ፡ ኅሪት ክብርት የምትሆን ባራቱ ማዕዘን የምትነገር ሕገ ወንጌልን በኢየሩሳሌም እንድትነገር አደርጋታለሁ ፡ እንተ ብዙኅ ሜጣ፣ የምታሰጠው ክብር ብዙ የሆነ ሕገ ወንጌልን በኢየሩሳሌም እንድትነገር አደርጋታለሁ፡ ወእሬሲ መንፈስ ቅዱስን በውኅት እሰጣለሁ ፡ ጥቅስ እፈኑ ተስፋሁ ለአበየ እንዲል ፡ ሉቃ ምዕ. ፳፬ ቁ ፵፱ ፡ ወማህልየኒ በመጻልው ይቅርታዬንም መጥኜ መጥኜ አደርጋለሁ፡ አንድም ሀብተ መንፈስ ቅዱስን መጥኜ መጥኜ እሰጣለሁ፡ ጥቅስ ወበከመ ይደልም ይበቍየ እንዲል ፣ ፩ቆሮ. ፲፪፡፲፩ ፡ እንደሃይማኖቱ ዕናት እንደ ምግባሩ ብዛት ስፋት ይሰጠዋልና ፡

ወእለሰ ይትዌከሉ በከንቱ ፣

በከንቱ ነገር በከንቱ ጣዖት የሚተመኩ ፣

ወበሐሰት ኢያመስጡ እምዐውሎ፣

በሐሰት ነገር ፡ በሐሰት ጣዖት የሚታመኑ ሰዎች ከመከራ አያመልጡም ፣

፲፮፡ ወየዐልወክሙ መሐላክሙ ዘም ስለ ሞት ፣

ከሞት ጋር የተማማላችሁት መሐላ ይክዳችኋል ማለት ስልምናሶር ናቡከደነፆር አያገኘንም የምትሉት ሐሰት ይሆንባችኋል አንድም ገሃነም ዲያብሎስ አያገኘንም የምትሉት ሐሰት ይሆንባችኋል ፣

ወኪዳንክሙ ዘምስለ ሲኦል ኢይቀውም ፣

ከመቃብር ከገሃነም ጋራ የተመሳማላችሁት መሐላ አይጸናም፡

ወእመኒ መጽአ ዐውሎ ኅላፊ ይከ ይደክሙ ፣

ስልምናሶር ናቡከደነፆር በመጣ ጊዜ ያጠፋችኋል ፡

ወትደክሙ ፣

በጐዳና ትደክማላችሁ ፡

፲፱ ወእምከመ መጽአ የሐፍስክሙ ለሰጽላሉ ፣

ሜዋዊ በደረሰ ጊዜ ፈጥኖ ይማርካችኋል ፡

ወትቀርበክሙ ዕለትክሙ ፣

ዕለተ ሜዋዊ ታገኛችኋለች ፡

ወሌሊታኒ ሕዝብት እኪት ፣

ሌሊቷም የምትጠረጠር ክፉ ናት ፡

፳፡ ተመሀሩ ስሚዐ ቃለ ምንዱባን፣

የነቢያት የካህናትን ቃል መስማት ተማሩ፡ አንድም ተመሀሩ ስሚዐ ቃለ ምንዱባን ይላል፣ ሳይናበብ በመከራ የተጨነቃችሁ እስራኤል ሕጉን ተማሩ፡ አንድም በጀስ ካላችሁ ባለጸጎች የነዳያንን ቃል ስሙ ፡

ኢትክሉ ላኪ ወጋዕዘ ምስለ እግዚአብሔር ፣

አይሆንም ግን ብትሉ ከእግዚአብሔር ጋራ ጠብ ክርክር አይቻላችሁም ፡

ለሊነ ሠራሕነ ከመ ናስተጋብዕክሙ፣

መክረን አስተምረን በምግባር በሃይማኖት እንመልሳችሁ ዘንድ እኛ ደከምን ይላሉ ነቢያት ካህናት ፡

ከመ ሕንፃ ደቂቅ ፣

ከንክሙ ያለበት ነው፣ እንደ ልጅ ሕንፃ ሆናችሁ ፡ ልጅ እንቢያን ከቦ ቤት ሠራሁ ይላል ያ አይረባም፡ አንድም ከመ ሐፀ ደቂቅ ይላል፡ እንደ ልጅ ፍላፃ ሆናችሁ፡ ልጅ እሾሁን በሣር ላይ ሰክቶ ፍላፃ አበጀሁ ይላል ያ አይረባም ፡ አንድም ከመ ሕንፃ ደቂቅ አእምሮ እንደ ሰብአ ሰናአር ሕንፃ ሆናችሁ ፡

፳፩፡ በእንተ ዝንቱ ይትነሣእ ፀር፣ የማትረቡ ስለሆናችሁ ስልም ናሶር ፡ ሰናክሬም ናቡከደነፆር በጠብ ይነሣል ፡

ወይሄሉ ውስተ ቄላተ ገባአን ፣

በገባአን አውራጃ ይሰፍራል፡

ወይገብር ግብሮ በመዓት መሪር፣

ሥራውን በሚያሳዝን ነገር ይሠራዋል ፡

መዓቱኒ ዕፁብ ይገብር

ቍጣውም ፈጭንቅ ነገር ያደርጋል ፡

ወኅምዙኒ ነኪር ፣

የናቡከደነፆር ጦሩ ልዩ ነው፡ አንድም የሰናክሬም መርዙ ልዩ ነው ፡ ለልማዱ እባብን መርዙ አይገለውም ፡ እሱን ግን ቦኑ ግልፎ ዘያድኅን ብሎ የተናገረው ቃል አጥፍቶታልና ፡

፳፪፡ ወኢይፀንዕ ቀኦርክሙ ፣

አዕንታችሁ የመከራችሁት ምክራችሁ አይፀናም ፡

www.ethiopianorthodox.org

እስመ ጎሉቀ ወምቱረ ነገረ ሰማ
ዕኩ እምነበ እግዚአብሔር ፀባያት
ዘይገብር በሶሉ ምድር ፣

ከአሸናፊ ከእግዚአብሔር ዘንድ
በዓለሙ ሁሉ የሚያደርገውን
ያለቀ፣ የተቈረጠ ነገር ሰምቻ
ለሁና ፤

፷፫፡ ስምዑኒ ቃልየ ወአዕምዑኒ ፣

ነገሬን ስሙኝ አድምጡኝ ፤

ወለብዉ ፣

ልብ አድርጉት አስተውሉት ፤

ወስምዑኒ ነገርየ ፣

ነገሬን ስሙኝ ፤

፷፬፡ ቦኑ ኮሶ አሚረ የሐርስ ዘየ
ሐርስ ፣

በውኑ የሚያርስ ሰው ላያበቅል
ሁል ጊዜ ያርሳልን ፤ እንደዚ
ሁስ ሁሉ የሚያስተምር ነቢይ
ካህን ሁል ጊዜ ያስተምራልን
ካልሰሙት ፤

ወያቀድምኑ ዘሪዐ ዘእንበለ ይሕርስ
ምድሮ ፣

ምድሩን ላያርስ አስቀድሞ ዘር
ይዘራልን፤ እንደዚህስ ሁሉ በነ
ቢያት ላያናግር ያጠፋልን ፤

፷፭፡ አኮኑ አቀምጢዎ ገራሀቶ ፣

ገምሶ ገማምሶ ከፍሎ ከፋፍሎ፤

አሜሃ ይዘርዕ ጎዳጠ መለንሰ ወከ
ሙነ ፣

ያንጊዜ ጥቂት ኑግ ፈጦ ተልባ
የሚዘራ አይደለምን ፤

ወካዕበ ይዘርዕ ሥርናየ ወሰገመ ፣

ዳግመኛ ስንዴውን ገብሱን የሚ
ዘራ አደለምን፤ ባለሰለሰው ባልተ
ኰሰተረው ኑግ ተልባ እንደመዝ
ራት አባር ቸነፈርን ያመጣል፤
በለሰለሰው በተኰሰተረው ስንዴ
ገብስ እንደመዝራት ፄዋዌን
ያመጣል ፤

፷፮፡ ወትትመሐር ምድር ኮነኔ እግ
ዚአብሔር ፣

ምድር ለታበቀ ል ያለውን አዝ
ርዕትን ፣ አትክልትን ታስገኛ
ለች ፤ አንድም ቤተ እስራኤል
ሕገ እግዚአብሔርን ትማራ
ለች ፤

ወትትፈሣሕ ፣

ምድር ደስ ይላታል ማለት እስ
ራኤል ደስ ይላቸዋል ፤

፷፯፡ እስመ አኮ በተነይሉ ዘያከይ
ድዎ ለመለንስ ፣

ኑጉን በመበረታታት የሚያበ
ራዩት አይደለምና ፣

ወአኮ በመንኰራኵሪ ሠረገላ ዘየሐ
ስይዎ ለከሙን ፣

ፈጦውን ፣ ተልባውን በሠረገላ
መንኰራኵር የሚያበራዩት
አይደለምና ፤

ለከሙንሂ በበትር ይዘብጥዎ ፣

ፈጦውን ተልባውን በብትር
ይወቁታል እንጂ ፤

ወለመለንስሂ በሙቃዕ ይወቅዕዎ ፣

ኑጉንም በመውቂያ ይወቁታል
እንጂ በመበረታታት የሚያበ
ራዩት አይደለምና ፤

፷፰፡ ወአነሂ አኮ ለዓለም ዘእትመ
ዐክሙ ፣

እኔም አንድ ጊዜ ብቆጣ ሁል
ጊዜ የምቆጣ አይደለም ፤ አን
ድም ገብስን በጎይል እንዲያ
በራዩት ፣ ፈጦ ተልባን በሠረ
ገላ መንኰራኵር እንዲያሄዱት
ተቈጥቼ የማጠፋችሁ አይደ
ለም ፤

ወአከይደክሙ በመዓትየ ፣

ተቈጥቼ የማጠፋችሁ አይደ
ለም፤

፷፱፡ ወዝንቱ ነገር ዘወፅአ እምነበ
እግዚአብሔር ፀባያት ፣

ከአሸናፊ ከእግዚአብሔር ዘንድ
[illegible]

መንክረ ምክር ዓቢይ ፣

ምክሩ ዬዋዌ ምክሩ ሚጠት የተ
ደነቀለት ፤ አንድም ምክሩ
ሥጋዌ የተደነቀለት ፤ ጥቅስ
መንክርሰ እግዚአብሔር በአር
ያሙ እንዲል፤ መዝሙር ፺፪፡፭፤

አንትሙሰ ትፈቅዱ ታዕብይዎ ለከ
ንቱ በዕበድ ፣

እናንተ ግን በስንፍና ጣዖቱን
ልታከብሩት ልታገኑት ትወዳ
ላችሁ፤ አንድም በከንቱ ለዕበድ
ይላል ፤ ጣዖቱን በከንቱ ልታከ
ብሩት ልታገኑት ትወዳላችሁ፤
አንድም ለዕበድ በዕበድ ይላል፤
በስንፍና ጣዖቱን ልታከብሩት
ልታገኑት ትወዳላችሁ ::

ምዕራፍ ፷፱

ጉባዔ

፩፡ አሌ ላ ለአርያል ሀገር እንተ
ፀብዓ ዳዊት ፣

ዳዊት ለወጋት ለኤዶምያስ
ወዮላት ፤

ዘአስተጋብዑ እክላ በማዕረር ዘዘዓ
መት በልዑ ሞዐብ ፣

ባመት ባመት በመከር ጊዜ
የሰበሰበችውን እህሏን የሞ
ዐብ ሰዎች በሉባት ፤ አንድም
በመከር የሰበሰበችውን እህሏን

www.ethiopianorthodox.org

የሞዐብ ሰዎች ባመት ባመት እየመጡ በለባት ፤

፪፤ እስመ እማቅያ ለአርያል ፣

በኤዶምያስ መከራ አፀናባታ ለሁና፣ ይህች ኤዶምያስ ሦስት ጊዜ ተወግታለች፤ ቀድሞ ዳዊት ወግቷታል፤ ኋላም ሞአብ ወግቷታል ፤ ኋላም ሐርቃሎስ አጥ ፍቷታልና ፤

ወትከውን ዛቲ ኃይል ፣

ዛቲ ብዕል ሲል ነው ፤

ወዝንቱ ብዕል ዚአየ ፣

ዛቲ ኃይል ያለውን ብዕል ብሎ ገለጠው ይህ ብዕል በተፈጥሮ የኔ ገንዘብ ነው ፤

፫፤ ወአዐግተኪ ከመ ዳዊት ፣

ዳዊት በጦር እንደከበበኽ እኪ ብሻለሁ ፤

ወአነዕረኪ በማኅፈድ ፣

በጦር አጥርሻለሁ፤ አንድም በዐ ርበኛ እከብሻለሁ ወነደቀ ተባ ዕተ በዐውዳ እንዲል ምዕ ፤

፬፤ ወይሠጠም ውስተ ማይ ነገርኪ፣

ነገርሽ በውኃ ውስጥ ይሰጥ ማል ፤

ወትከውኒ ከመ ዘይትናገር በታሕተ ማይ ፣

በውኃ ውስጥ እንደሚናገር ሰው ትሆኛለሽ በውኃ ውስጥ ሆኖ የሚናገር ሰው ነገሩ እን ዳይሰማ ቃልሽ አይሰማም ፤

ወትደክሚ ፣

ትደክሚያለሽ ፤

ወይቴሐት ቃልኪ ውስተ ማይ ፣

ቃልሽ በውኃ ውስጥ ይሰላል፤

፭፤ ወይከውን ከመ ፀበል ዘእምዐ ረፍት ብዕሎሙ ለኃጥኣን ፣

እነናቡከደነፆር እነሰናክሬም ከሀ ገራቸው ያመጡት ገንዘባቸው በቅጽር ላይ እንዳለ ትቢያ ይሆ ናል፤ አንድም የእራኤል ገንዘባ ቸው በቅጽር ላይ እንዳለ ትቢያ ይሆናል፤ አንድም ከግድግዳ እየ ተቀረፈ እንደሚወድቅ ልስን ይሆናል ፤

ወከመ ንጋፍ ዘያመጽኦ ነፋስ ፣

ነፋስ እንደሚያመጣው ጥራጊ ይሆናል ፤ አንድም ነፋስ እንደ ሚያመጣው መዓዛ ይሆናል ፤

ወይከውን በጊዜሃ ለምዕር እምነበ እግዚአብሔር ፀባዖት ፣

ካሸናፊ ከእግዚአብሔር ዘንድ ታገዘ ይህ ሳይውል ሳያድር ፈጥኖ ይደረጋል፤ አንድም ከእ ግዚአብሔር ታገዘ በምትጠፋ በት ጊዜ እንደ ትቢያ ይሆናል፤

፮፤ እስመ ይዋሂ በፀዓዕ ፣

በብልጭልጭታ ፤

ወበድልቅልቅ ፣

በንውጽውታ ፤

ወበዐቢይ ቃል ፣

በመብረቅ በነጐድጓድ ፤

ወበዐውሎ ዘይመጽእ ፣

በሚመጣ ጥቅል ነፋስ ፤

ወበነበልባለ እሳት በላዒ ፣

በሚያቃጥል እሳት ይጎበኛልና ማለት ከእግዚአብሔር ታገዘ በሚመጣ መቅሠፍት ያጠፋ ልና ፤

፯፤ ወይከውን ብዕሎሙ ለኮሎሙ አሕዛብ ከመ ዘየሐልም ሕልመ ፣

የእነሰናክሬም ብዕላቸው ሕልም እንደሚያልም ሰው ይሆናል ያመጣዋል ፤

፰፤ ወኮሎሙ እለ ፀብዕዎሙ ለእስ ራኤል ፣

እስራኤልን የወጓቸው ሰዎች ሁሉ ፤

ወኮሎሙ እለ ፀብዕዋ ለኢየሩሳ ሌም ፣

ኢየሩሳሌምን የወጓት ሰዎች ሁሉ ፤

ወኮሎሙ እለ ተጋብዑ ላዕሌሃ ወሮድዋ ፣

በሷ ላይ ተሰብስበው የከበቧት ሁሉ ፤

ይከውኑ ከመ እለ ይበልዑ ወይሰ ትዩ በሕልሞሙ ፣

በሕልማቸው እንደሚበሉ እን ደሚጠጡ ሰዎች ይሆናሉ ፤

ወሶበ ይነቅሑ ይሔስዎሙ ሕል ሞሙ ፣

በተነሡ በተቀሰቀሱ ጊዜ ሕል ማቸው ሐሰት እንዲሆንባቸው፤

፱፤ ወበከመ ዕሙዕ ዘየሐልም እንዘ ይሰቲ ማየ ፣

የተጠማ ሰው በሕልሙ ውኃ እንዲጠጣ ፤

ወነቂሖ ዓዲሃ ዕምዕት ነፍሱ ፣

በተነሣ በተቀሰቀሰ ጊዜ ሰው ነቱ ገና እንደተጠማች እንዲ ያገኛት ፤

ወከንቶ ተሰፈወ ፣

ይህን በከንቱ ተስፋ እንዳደረገ፤

ከማሁ ውእቱ ብዕሎሙ ለኮሎሙ አሕዛብ እለ ፀብዕዋ ለደብረ ጽዮን፣

ደብረ ጽዮንን የወጓት የአሕዛብ ሁሉ ባለጸግነታቸው እንደዚህ ነው፣ ሕልም ያለው የእስራኤ ልን ገንዘብ ነው፤ እነሰናክሬም ሲመጡ ሰዎችን ማርከን ገንዘ ባቸውን ዘርፈን አገራቸውን ተኩሰን እንሄዳለን ብለው ነበር፤ ይህ ቀርቶባቸዋልና ደክሙ ማንሻ፤ አንድም ኮሎሙ እለ ፀብዕዋ ለደብረ ጽዮን ደብረ

www.ethiopianorthodox.org

ጽዮንን የወጓት አሕዛብ ሁሉ ደክሙ በመከራ ደከሙ ፤

፲፤ ወደኒገፁ ወሰክሩ ፣

በመከራ ተይዘው ደነገጡ ሰከሩ ፤

አኮ በወይን ወአኮ በሜስ ፣

የወይን ጠጅ ጠጥተው ፣ የማር ጠጅ ጠጥተው አይደለም ፣ በሀገራቸውስ የማር ጠጅ የለም ብሎ ጥሩ ጠጅ ጉሽ ጠጥተው አይደለም ፤

፲፩፤ እስመ አስተዮሙ እግዚአብሔር ጋኔነ ዘያደነግፆሙ ፣

እግዚአብሔር የሚያስደነግጣ ቸው ጋኔን አምጥቶባቸዋልና ስለዚህ ነው እንጂ እግዚአብ ሔር የሚያመጣባቸው ሆኖ አይደለም ፣ ረድኤት መንሣቱን መናገር ነው ፤

ወከደኖሙ አዕይንቲሆሙ ለነቢያ ቲሆሙ ፣

የነቢያተ ሐሰትን ዐይነ ልቦ ናቸውን ሠውሮታልና ማለት የሰናክሬምን ጥፋት እንዳያውቁ አድርጓቸዋልና ፤

ወለመላእክቲሆሙ እለ ይሬእዩ ዘኅ ቡዕ ፣

የተሠወረውን እናውቃለን የሚሉ አለቆችን እንዳያውቁ አድርጓቸዋልና ፤

፲፪፤ ወይከውኖሙ ዝንቱ ኵሉ ነገር ከመ ነገረ መጽሐፍ ኅቱም ፣

የሰናክሬም ነገር በነቢያተ ሐሰት እንደታጠፈ መጽሐፍ ይሆንባቸ ዋል ፤

ዘይሁብዎ መጽሐፈ ለብእሲ ዘየአ ምር መጽሐፈ ፣

መጽሐፍ ለሚያውቅ ሰው መጽ ሐፉን አጥፈው ሰጥተው ፤

ወይብልዎ አንብብ ዘንተ ፣

ይህን አንብብ እንዲሉት ፤

፲፫፤ ወካዕበ ይሁብዎ መጽሐፈ ለብ እሲ ዘኢየአምር መጽሐፈ ፣

ዳግመኛ መጽሐፍ ለማያውቅ ሰው መጽሐፍ ዘርግተው ሰጥ ተው ፤

ወይብልዎ አንብብ ዘንተ ፣

ይህን አንብብ እንዲሉት ፤

ወይብል ኢየአምር መጽሐፈ ፣

መጽሐፍ አላውቅም እንዲል ነቢያተ ሐሰትም የሰናክሬምን ጥፋት አያውቁምትም ፤ አንድም አግብቶ መተርጐም ነው ፤ መጽ ሐፍ ለሚያውቅ ሰው መጽሐ ፉን አጥፈው ሰጥተው አንብ እንዲሉት ታጥፏልና ማንበብ አይቻለኝም እንዲል ፣ ዳግመኛ መጽሐፍ ለማያውቅ ሰው መጽሐፉን ዘርግተው ሰጥተው

አንብብ እንዲሉት አላውቅም እንዲል ፣ በነቢያተ ሐሰትም የሰ ናክሬም ጥፋት ጭንቅ ይሆንባ ቸዋል አያውቁትም ፤ አንድም ዘየአምር መጽሐፈ ዘኢየአምር መጽሐፈ የተባለ ዮሴፍ ነው ፣ ዘየአምር መጽሐፈ ማለት ሚስ ቱን በግብር ያውቃታልና ፣ ዘኢ የአምር መጽሐፈ እምቤታችንን በግብር አያውቃትምና ፣ በድን ግልና ፀንሳ በድንግልና መውለዷ ጭንቅ ይሆንበታል ፤ አያውቀ ውም ፤ አንድም አግብቶ መተር ጐም ነው ፤ መጽሐፍ ለሚያውቅ ሰው መጽሐፉን አጥፈው ሰጥ ተው አንብብ እንዲሉት ታጥ ፏልና ማንበብ አይቻለኝም እን ዲል ዳግመኛ መጽሐፍ ለማያ ውቅ ሰው መጽሐፉን ዘርግተው ሰጥተው አንብብ እንዲሉት አላ ውቅም እንዲል ይህ በዚያ ሰው ጭንቅ እንዲሆንበት በድንግልና ፀንሳ በድንግልና መውለዷ በዮ ሴፍ ጭንቅ ይሆንበታል ፤ አን ድም ዘየአምር መጽሐፈ ዘኢየ አምር መጽሐፈም የተባለች እመቤታችንናት ፤ መጽሐፉ ለኢሳይያስ እንዲላት መጽ. ምሥ. ዘየአምር መጽሐፈ ማለት በመልክ ያውቃታልና ፣ ዘኢየአ ምር መጽሐፈ በግብር አያውቃ ትምና ፣ በድንግልና ፀንሣ በድን ግልና መውለዷ በዮሴፍ ጭንቅ ይሆንበታል ፤ አንድም ይህ በዮ ሴፍ ጭንቅ እንዲሆንበት የጌታ ነገር በአይሁድ ጭንቅ ይሆንባ ቸዋል ፤ አንድም አግብቶ መተር ጐም ነው መጽሐፍ ለሚያውቅ ሰው መጽሐፉን አጥፈው ሰጥ ተው አንብብ እንዲሉት ታጥ ፏልና ማንበብ አይቻለኝም እን ዲል ፣ ዳግመኛ መጽሐፍ ለማያ ውቅ ሰው መጽሐፉን ዘርግተው ሰጥተው አንብብ እንዲሉት አላ ውቅም እንዲል ፣ ይህ በዚያ ሰው ጭንቅ እንዲሆንበት የጌታም ነገር በአይሁድ እንደዚያ ጭንቅ ይሆንባቸዋል ፤ በደረቅ ግንባር ዐይን መፍጠሩ ፣ በተዘጋ ቤት ሳይከፍት ገብቶ ሳይከፍት መው ጣቱ ፣ የለት ሬሳ እለ ወለተ ኢያኢሮስን እለ ወልደ መበለ ትን ፣ ያራት ቀን ሬሳ እለ አል ዓዛርን ማስነሣቱ ፤

፲፬፤ ወይቤለኒ እግዚአብሔር ዝንቱ ሕዝብ ይቀርቡኒ በከናፍሪሆሙ ፣

እሉ ሕዝብ ሲል ነው እግዚአ ብሔር እሊህ ወገኖች በአፋ ቸው እንወድሃለን እናመልክ ሃለን ይሉኛል ፤

ወበልቦሙሰ ነዋኅ ይርኅቁ እምኔየ ፣

በልቡናቸው ግን ፈጽመው ከኔ ይርቃሉ ፤

www.ethiopianorthodox.org

ወከንቶ ያመልኩኒ ፣

በከንቱ እናመልክሃን ይሉኛል ፤

ወይሜህሩ ትምህርተ ትእዛዘ ሰብእ ፣

ሰው ሠራሽ ጣኦትን እያመለኩ ፤ አንድም በሰው አምሳል የተ ሠራ ሕገ ጣዖትን እያስተማሩ ፤ አንድም ወይቤለኒ ብለህ መልስ እግዚአብሔር ቢጽ ሐሳውያን ጸሐፍት ፈሪሳዊያን በከንፈራ ቸው ወደድንህ ይሉኛል ፤ ወበል ቦሙሰ በልባቸው ግን ፈጽመው ከኔ ይርቃሉ ፣ ወከንቶ በከንቱ እናመልክሃለን ይሉኛል በሕገ አሪት ላይ ሥርዓተ ረበናትን እያስተማሩ ፤

፲፭፡ ወበእንተ ዝንቱ ናሁ እደግም አፍልሶቶሙ ለዝንቱ ሕዝብ ፣

ስለዚህ ነገር ዳግመኛ እስራኤ ልን አስማርካቸዋለሁ ፣ የሁለቱን ነገድ ላሥሩ ነገድ ዳግመ አለ ፤ አንድም የመቃብያንን ላሥሩም ለሁለቱም ነገድ ዳግመ አለ ፤

ወአኅጥሎሙ ጥበቦሙ ለጠቢባን ፣

የጦር ጥበብ እናውቃለን የሚ ሉትን ጥበባቸውን አጠፋባቸዋ ለሁ ፤ አንድም የአይሁድን ምክ ራቸውን እሠውራለሁ ፤

ወኦሪሥዖሙ ምክሮሙ ለመካርያን ፣

የጦር ምክር እናውቃለን የሚ ሉትን ምክራቸውን እሠውርባ

፲፮፡ አሌ ሎሙ ለእለ ይመክሩ ዕሙቀ ምክረ ፣

ጥልቅ ምክር ለሚመክሩ ሰዎች ወዮላቸው ፤

ከመ ይኅብዑ እምእግዚአብሔር ፣

ከእግዚአብሔር የሠወርን መስ ሏቸው ፤

፲፯፡ አሌ ሎሙ ለእለ ይከብቱ ምክረ ፣

በጎውን ምክር ለሚሠውሩ ሰዎች ወዮላቸው ፤

ወይገብሩ በጽልመት ግብሮሙ ፤

ሥራቸውን ሠውረው ለሚሠሩ ሰዎች ወዮላቸው ፤

ወይብሉ አልቦ ዘይሬእየነ ፣

የሚያየን ሰው የለም ፣ የሚያ የን ሰው አይኑር ለሚሉ ወዮ ላቸው ፤

ወአልቦ ዘየአምር ዘንገብር ፣

የምንሠራውን ሥራ የሚያውቅ የለም ፣ የሚያውቅ አይኑር ለሚሉ ወዮላቸው ፤

፲፰፡ አኮኑ ከመ ዕቡረ ለብሐዊ አንትሙ ፣

እናንተ በኔ ዘንድ እንደ ሸክላ ሠሪ ጭቃ አይደላችሁምን ፤

ይክልኑ ልሕኵት ብሂሎቶ ለለሐ ኵሁ ኢትግበረኒ ከመዝ ፣

ሸክላ ሠሪውን እንዲህ አድር ገህ አት[illegible] ሊለው ይቻለ

ዋልን ፣ መንቀል ኵስኵስት አድ ርጎ ቢሠራው ተንጠልጥዬ እን ድኖር መንቀል ኵስኵስት አድ ርገህ ለምን ሠራኸኝ ፣ ተቀምጬ እንድኖር ጋን እንስራ አድርገህ ባልሠራኸኝም ነበር ሊለው ይቻ ለዋልን ፣ አንድም ጋን እንስራ አድርጎ ቢሠራው ተቀምጬ እን ድኖር ጋን እንስራ አድርገህ ለምን ሠራኸኝ ተንጠልጥዬ እን ድኖር መንቀል ኵስኵስት አድ ርገህ ባልሠራኸኝም ነበር ሊለው ይቻለዋልን ፤

ወይብሎኑ ግብር ለገባሪሁ ኢትግበ ረኒ ከመዝ ወኢያሠነይከ ገቢሮትየ ፣

ሥራስ ሠሪውን አከናውነህ አል ሠራኸኝም ሊለው ይቻለዋልን ሠረገላ ጠርብ አድርጎ ቢሠራው ተጋድሜ እንድኖር ሠረገላ ጠርብ አድርገህ ለምን ሠራኸኝ ቁሜ እንድኖር መቃን መድረክ አድርገህ ባልሠራኸኝም ነበር ሊለው ይቻለዋልን ፤ አንድም መቃን መድረክ አድርጎ ቢሠ ራው ቁሜ እንድኖር መቃን መድረክ አድርገህ ለምን ሠራ ኸኝ ተጋድሜ እንድኖር ሠረገላ ጠርብ አድርገህ ባልሠራኸኝም ነበር ሊለው ይቻለዋልን ፤

ወአልቦ እንከ ኅዳጠ ፣

ምንም የሚናገረው ጥቂት ነገር የለም ፣ እንደዚህስ ሁሉ እኔስ እንደ ወደድሁ የማደርጋችሁ አይደለምን ማለት ክፉ ክፉ ዎችን ለመከራ በጎ በጎዎችን ለተድላ ለደስታ ባደርጋቸው ለምን ማለት ይቻላችኋል ፣

፲፱፡ ወእምዝ ይከውን ከርሜል ከመ ዖም ፣

ከዚህ በኋላ በዜዋዌ ችፍርጉ ገኖ እንደ ዛፍ ይሆናል ፤

ወዖም ይከውን ከመ ሊባኖስ ፤

ጥቃቅኑ ዛፍ እንደ ታላቅ ዛፍ ይሆናል ፣ አንድም ስትበድሉ ኑራችሁ መከራ ከመጣባችሁ በኋላ አገራችሁ ተፈቶ ችፍርግ ትንሽ ዛፍ ይሆናል ፣ አንድም ከሰባ ዘመን በኋላ ጥቂት ገንዘብ ያልነበረው ጥቂት ገንዘብ እን ደነበረው ይሆናል ፣ ጥቂት ገን ዘብ የነበረው ብዙ ገንዘብ እንደ ነበረው ይሆናል ፤

ወይእተ አሚረ ይሰምዑ ዕሙማን ነገረ መጽሐፍ ፣

ያንጊዜ ጽሙማነ አእምሮ የአሪ ትን ነገር ይሰማሉ ፤

www.ethiopianorthodox.org

ወእለሂ ውስተ ጽልመት ወእለሂ ውስተ ጊሜ ፣

ጽልመት ጊሜ አንድ ወገን በድንቁርና የሚኖሩ ሰዎች የኦሪትን ነገር ይሰማሉ ፡

፳፡ ውእተ አሚረ ይሬእያ አዕይንተ ዕውራን ፣

ያንጊዜ ዕውራነ ልቡና እስራኤል ምሥጢር ያያሉ ፡

፳፩፡ ወይትፌሥሑ ነዳያን በእግዚአብሔር በኀሤት ፡

ነዳያን እስራኤል በእግዚአብሔር አምነው በፍጹም ደስታ ደስ ይላቸዋል ፡

ወይፀግቡ ትፍሥሕተ ሰብእ ቅቡፃን በቅዱሳ እስራኤል ፣

ሰባ ዘመን ተስፋ የቆረጡ እስራኤል በፅንዐ እስራኤል በክብረ እስራኤል በእግዚአብሔር አምነው ተድላ ደስታ ይጠግባሉ ፡

፳፪፡ እስመ ኀልቀ ኃጥእ ፣

ሸፋጭ ለዋጭ ጠፍቷልና ፣ አንድም እስመ ኀልቀ ኃጥእ የባቢሎን ሰው ጠፍቷልና ፡

ወጠፍአ ዕቡይ ፣

ዕቡይ ብልጣዕር ጠፍቷልና ፣ አንድም ወይእተ አሚረ ይሰምዑ ሰሙ ማን ነገረ መጽሐፍ ብለህ

መልስ፤ በዘመነ ሥጋዌ ደንቆሮዎች ጆሮአቸው ተከፍቶላቸው የወንጌልን ነገር ይሰማሉ፤

ወእለሂ ውስተ ጽልመት ወእለሂ ውስተ ጊሜ ፣

ጽልመት ጊሜ አንድ ወገን ነው፤ በድንቁርና የሚኖሩ ሰዎች የወንጌልን ነገር ይሰማሉ፣ ውእተ አሚረ ይሬእያ አዕይንተ ዕውራን ያንጊዜ ዕውራን በታአምራት ያያሉ ወይትፌሥሑ ነዳያን በእግዚአብሔር በኀሤት፣ ነዳያን ምዕመናን በእግዚአብሔር አምነው በፍጹም ደስታ ደስ ይላቸዋል፣ ወይፀግቡ ትፍሥሕተ ሰብእ ቅቡፃን በቅዱሰ እስራኤል ፣ አምስት ሺህ ካምስት መቶ ዘመን ተስፋ የቈረጡ ምዕመናን በፅንዐ እስራኤል በክብረ እስራኤል በእግዚአብሔር አምነው ልጅነትን ያገኛሉ፣ ሥጋውን ደሙን ይጠግባሉ ፣ እስመ ኀልቀ ኃጥእ ፣ ኃጥእ መናፍቅ ጠፍቷልና ወጠፍአ ዕቡይ ፣ ዕቡይ ዲያብሎስ ጠፍቷልና ፡

ወተሠረዉ እለ ይዔምዑ በእኩይ

ኃጢአት በመሥራት ጣዖት በማምለክ የሚበድሉ ነቢያተ ሐሰት አንድም ጌታን እሩቅ ብእሲ፡ ወንጌልን ዲቃላ ሕግ የሚሉ ጠፉ ፣

፳፫ ወእለ ያስሕቱ ሰብአ በነገር፣

ሰውን በነገር የሚያስቱ ፣

ወኵሎሙ እለ ይትዋቀሱ በኀበ አናቅጽ ፣

በዓደባባይ የሚከራከሩ ሁሉ ፣

ወያመጽኡ ማዕቀፈ ፣

በሰውም መሰናክል የሚያመጡ፡

ወይጠውይዋ ለጽድቅ በዐመፃ ፣

እውነትን በሐሰት የሚለውጧት ነቢያተ ሐሰት ጠፉ፡ አንድም ወንጌል እንበለ ኦሪት፣ ጥምቀት እንበለ ግዝረት አትረባም እያሉ በሰው መሰናክል የሚያመጡ፣ ጌታን ሩቅ ብእሲ የሚሉ ቢጽ ሐሳዊያን ጠፉ ፡

፳፬፡ ወበእንተ ዝንቱ ከመዝ ይቤ እግዚአብሔር ለቤተ ያዕቆብ ፣

ስለዚህ ነገር ለያዕቆብ ወገኖች እግዚአብሔር እንዲህ አለ ፡

ዘአውፅኦ ለአብርሃም እምከላውዴዎን ወለያዕቆብ እምሶርያ ወለእስራኤል እምግብፅ ፣

አብርሃምን ከከላውዴዎን ያዕቆብን ከሶርያ እስራኤልን ከግብፅ ያወጣው እግዚአብሔር እንዲህ አለ ፡

አኮ ይእዜ ዘኢተኀፍር ያዕቆብ ፡

ያዕቆብ ዛሬ በመከራ የማታፍር አይደለም ታፍራለህ ፡

ወአኮ ይእዜ ዘኢይትዌለጥ ገጽከ፣

ዛሬ ፊትህም በመከራ የማይለወጥ አይደለም ማለት በዔዋዌ ነው፤ አንድም አኮ ይእዜ ዘተኀፍር ያዕቆብ ዘትትኀፈር ሲል ነው፤ ያዕቆብ በሚጠት በመከራ የምታፍር አይደለም፤

ወአኮ ይእዜ ዘኢይትዌለጥ ገጽከ ዘይትዌለጥ ሲል ነው፤ ፊትህም በመከራ የሚለወጥ አይደለም፤

፳፭፡ ወሶበ ርእዩ ደቂቅከ ምግባርየ በእንቲአየ ይቄድሱ ስምየ ፡

ልጆችህ ሥራዬን ባዩ ጊዜ በኔ ስላመኑ ስሜን ያመሰግናሉ፣ አንድም ልጆችህ ተአምራቴን ባዩ ጊዜ እኔን ስለማምለክ ስሜን ያመሰግናሉ ፡

ወይትቄደሱ ቤተ ያዕቆብ ፣

የያዕቆብ ወገኖች ይከብራሉ ፡

ወለአምላከ እስራኤልኒ ይፈርህዎ ፣

የእስራኤልንም ፈጣሪ ይፈሩታል ያመልኩታል ፡

፳፮፡ ወየአምሩ ጥበበ እለ ስሕቱ በመንፈሶሙ ፣

በልቡናቸው የሳቱ ሰዎች ሕገ እግዚአብሔርን ያውቃሉ ፡

www.ethiopianorthodox.org

ወእለሂ ያንጐረጕሩ ይትሜህሩ ተአ
ዝዞ ፤

በመከራ ተይዘው የሚያዝኑ የሚ
ያንጐራጕሩ ለሕገ እግዚአብ
ሔር መታዘዝን ይማራሉ ፤

ወይትሜህር አውስአ ሰላም ልሳን
አያፍ ፤

ሰባ ዘመን ዲዳ የነበረ አንደ
በት አሪትን ይማራል፤ አንድም
አምስት ሺህ ካምስት መቶ
ዘመን ዲዳ የነበረ አንደበት
ወንጌልን ይማራል ::

ምዕራፍ ፷፩

፩፡ አሌ ሎሙ ለውሉድ ዐላውያን ፤

ይህን ሁሉ ኃጢአት ሲሠሩ
ከኖሩ በላ መከራ መጥቶባቸው
ወንጀለኞች ለሆኑ ልጆች ወዮ
ላቸው፤ አንድም ለውሉደ ዐላው
ያን ይላል ለወንጀለኞች ሰዎች
ልጆች ወዮላቸው ፤

ከመዝ ይቤ እግዚአብሔር ገበር
ክሙ መንክረ ፤

እግዚአብሔር እንዲህ አለ ፤
ድንቅ ሥራ ሠራችሁ የክፉ
ድንቅ ነው፤

ወአኮ በእንቲአየ ፤

እኔን ደስ ይበለው ብላችሁ አይ
ደለም ፤

ወወራዕክሙ ፤

ለጣዖት ማዕድ ሠራችሁ ፤

ወአኮ በእንተ መንፈስየ ፤

ልቡናዬን ደስ ይበለው ብላችሁ
አይደለም ፤ አንድም ሕይወቴ
መንፈስ ቅዱስን ደስ ይበለው
ብላችሁ አይደለም ፤

አላ ከመ ትወስኩ ኃጢአተ በዲበ
ኃጢአት ፤

በኃጢአት ላይ ኃጢአትን ትጨ
ምሩ ዘንድ ነው እንጂ ፤

፪፡ ወተሐውሩ ወትወርዱ ብሔረ
ግብፅ ፤

ርዱን እያላችሁ ወደግብፅ ትሄ
ዳላችሁ ፤

ወኢሰአልክሙኒ እርዳእክሙ ከመ
ትትረድኡ በረድኤተ ፈርዖን ወግ
ብፅ ፤

በፈርኦንና በግብፃውያን አጋዥ
ነት ትረዱ ዘንድ ርዱን እያላ
ችሁ ወደግብፅ ትሄዳላችሁ፤ አን
ድም እምረድኤተ ፈርዖን ወግ
ብፅ ከግብፃውያን ከፈርዖን ረዳ
ትነት አሳንሳችሁኝ ረዳችሁ
ዘንድ አለመናችሁኝም ፤

፫፡ ወይከውነክሙ ፈርዖን ወልታ
ኀሣር ፤

ፈርዖን አያስጥል አግሬ ይሆ
ንባችኋል፤ አያስጥል አግሬ ጎን
ያስብር እንጂ ፤

ወለእመ ተወከልክሙ ትከውኑ ጽእለተ
ለመላእክተ ኤጣን ፤

በግብፃውያን ብታምኑ ለሮም
አለቆች ስድብ ትሆናላችሁ ፤

፬፡ ወከንቶ ይፃምው ሐዋርያት እኩ
ያን ኀበ ሕዝብ እለ ኢይበቍዕምሙ
ለረድኤት ዘእንበለ ለኀሣር ወለጽእ
ለት ፤

ለስድብ ለተዋርዶ ይሆኗቸዋል
እንጂ ሊረዷቸው ወደግይረባ
ቸው ወደግይጠቅሟቸው ወደ
አሕዛብ የሚሄዱ መልእክተ
ኞች በከንቱ ይደክማሉ ፤

ጉባዔ

ራዕይ በእንተ እንስሳ ገዳም በሐግም
ወበምንዳቤ ፤

በአባር በቮነፈር ተይዘው ሳሉ
እስራኤል እንዳጠፉ አይቶ የተ
ናገረው ነገር ይህ ነው ፤

፭፡ አንበሳ ፤

ስልምናሶር ፤

ወዕጓለ አንበሳ ፤

ናቡከደነፆር ፤

ወእምኔሆሙ አራዊተ ምድር
እምታሕቴሆሙ ሲል ነው ከሳ
ቸው በታች ያሉ ሠራዊቱ መጥ
ተውባቸው በመከራ በፀዋትወ
መከራ ተይዘው ሳሉ በእስራኤል
ያየው ራእይ ይህ ነው ፤ አንድም
አንበሳ ናቡከደነፆር ወዕጓለ አን
በሳ መኳንንቱ ወእምኔሆሙ
አራዊተ ምድር ከሳቸው በታች
ያሉ ሠራዊቱ፤ አንድም አንበሳ
ስልምናሶር ወዕጓለ አንበሳ ሰናክ
ሬም ወእምኔሆሙ አራዊተ
ምድር፤ ከነዚህ ወገን የሚሆኑ
ሞዐብ አሞን መጥተውባቸው
በመከራ በፀዋትወ መከራ ተይ
ዘው ሳሉ በእስራኤል ያየው
ራእይ ይህ ነው ፤

እለ ይሄዕኑ በአግማል ወበአእዱግ
ብዕሎሙ ፤

ራእይ በእንተ እንስሳ ገዳም
ያለውን እለ ይሄዕኑ ብሎ አመ
ጣው፤ ባለጸግነታቸውን ባህያ
በግመል የሚጭኑ ናቸው፤ አን
ድም ግብፃውያን ብዕሳቸውን
ባህያ በግመል ጭነው ወደ ግብፅ
በሚ ወስዱባቸው በእስራኤል
ያየው ራእይ ይህ ነው፤ ያንንስ
ከንቱኬ ግብፅ ብሎ ያመጣ
ዋል ብሎ እሊህ ከእስራኤል
ገንዘባቸውን በግመል ጭነው
የሚወስዱ ናቸው ፤

ወይወስዱ ኀበ አሕዛብ እለ ኢይ
በቍዕምሙ ለረድኤት ዘእንበለ ለኀ
ሣር ወለጽእለት ፤

ለስድብ ለተዋርዶ ይሆኗቸዋል
እንጂ ሊረዷቸው ወደግይረባ

www.ethiopianorthodox.org

ቸው ወደማይጠቅሟቸው ወደ
አሕዛብ ገንዘባቸውን በአህያ በግ
መል ጭነው በሚወስዱ በእስራ
ኤል ያየው ራዕይ ይህ ነው ፤

፮፡ ከንቱኬ ግብፅ ፣

ራዕይ በእንተ እንስሳ ገዳም ያለ
ውን አመጣው፣ ግብፃውያን
ከንቱ ናቸው ፤

ኢይበቍዑክሙ ፣

አይረቧችሁም አይጠቅሟች
ሁም ፤

ንግሮሙ ከመ ከንቱ ዘተመዐዱ ፣

የተማማሉት መሓላቸው ከንቱ
እንደሆነ ንገራቸው ፤ አንድም
የተማከሩት ምክራቸው ከንቱ
እንደሆነ ንገራቸው ፤

፯፡ ወይእዜኒ ንበር ወጸሐፎ ለዝንቱ
ውስተ ሰሌዳ ፣

አሁንም ተቀምጠህ ይህንን በብ
ራና ጻፈው ፣

ዘይከውን በመዋዕለ ዕድሜሁ ፣

በጊዜው ጊዜ የሚደረግ ፤

ወእስከ ለዓለም ፣

ለዘለዓለም የሚሆን ፤

፰፡ እስመ ሕዝብ ዐላውያን እሙንቱ፣

ወንጀለኞች ወገኖች ናቸውና ፤

ወውሉደ ሐሰት እለ ዐበዩ ሰሚዐ
ሕገ እግዚአብሔር ፣

ሕገ እግዚአብሔርን መስማት
እንቢ ያሉ የሐሰት የጣዖት
ልጆች ናቸውና ፤

፱ እለ ይብልዎሙ ለነቢያት ኢት
ዜንዉነ ፣

ነቢያትን ከመዝ ይቤ እግዚአብ
ሔር ብላችሁ አትንገሩን የሚ
ሏቸው ናቸውና ፤

ወለእለሂ ይሬእዩ ራእየ ኢትንግሩነ፣

ራእይ የሚያዩትንም አትንገ
ሩን የሚሏቸው ናቸውና ፤

ወእመሰ ትነግሩነ ካልዐ ነገረ ንግ
ሩነ ፣

የምትነግሩንስ ከሆነ ከሕገ እግ
ዚአብሔር ልዩ የሆነ ሕገ ጣዖ
ትን ንገሩን የሚሉ ናቸውና ፤

፲፡ ወሚጡነ እምዝንቱ ፍኖት ፣

ከዘጠኙ ቃላት መልሱን የሚሉ
ናቸውና ፤

ወአኅድጉነ ዘንተ ዐሠረ ፣

ኢታመልክን አስተዉን የሚሉ
ናቸውና፣ ዐሠር አላት ኢታም
ልክን ፍለጋ ከሀገር ከመንደር
እንዲያደርስ ኢታምልክም ከዘ
ጠኙ ታደርሳ[illegible]

ወሠዐሩ እምኔነ ትምህርተ ቅዱሰ
እስራኤል ፣

የዕንዐ እስራኤል የክብረ እስራ
ኤል የእግዚአብሔርን ትምህ
ርት ከኛ አርቁ የሚሉ ናቸ
ውና ንግሮሙ የተማማሉት
ከንቱ እንደሆነ ንገራቸው ፤

፲፩፡ ወበእንተ ዝንቱ ከመዝ ይቤ
ቅዱሰ እስራኤል ፣

ስለዚህ ነገር ዕንዐ እስራኤል
ክብረ እስራኤል እግዚአብሔር
እንዲህ አለ ፤

እስመ ክህድክምዎ ለዝንቱ ነገር ፣

ይህን ነገር ክዳችሁታልና ፤

ወተወከልክሙ በሐሰት

በሐሰት በጣዖት አምናችኋልና፤

ወአንጐርጐርክሙ በዝንቱ ነገር
እንከ ፣

በዚህ ነገር ተበሳጭታችልኋና ፤

፲፪፡ በእንተ ዝንቱ ትከውነክሙ ዛቲ
ኃጢአትክሙ ከመ ዐረፍት ውድ
ቅት ፣

ስለዚህ ነገር ይህች ኃጢአታ
ችሁ እንደፈረሰች ግንብ ትሆን
ባችኋለች ፤

እንተ በጊዜሃ ሀገር ዕንዕት ፣

በጊዜዋ ጊዜ የፀናች ሀገር እን
ደነበረች ፤

ወድቀት ግብተ ፣

ድንገት እንደ ወደቀች እንደ
ፈረሰች ፤

፲፫፡ ወድቀታሂ ከመ ቅጥቃጤ ፃሕለ
ልሕኵት ፣

አወዳደቋም እንደ ሸክላ ወጭት
ስባሪ የሆነ ፤

ወይከውኑ ደቃቀ አግልዕተ ፤

የደቀቁ ገሎች እንዲሆኑ ፤

ወኢይትረከብ እምውስቴቱ ገልዕ
በዘይወስዱ እሳተ ወኢበዘያዌክፉ
ማየ ኅዳጠ ፣

ጥቂት የምላጭ ውሀ የሚወስ
ዱበት ፣ አንድ ፍሕም እሳት
የሚጭሩበት ገል የማይገኝ እስ
ኪሆን ድረስ የደቀቁ እንዲሆኑ
ያች ግንብ በወደቀች ጊዜ
በውስጧ ያለውን ሁሉ ይዛ እን
ድትወድቅ እናንተንም ኃጢአ
ታችሁ ይዟችሁ ይጠፋል ፤

፲፬፡ ከመዝ ይቤ እግዚአብሔር ቅዱሰ
እስራኤል ፣

ዕንዐ እስራኤል ክብረ እስራኤል
እግዚአብሔር እንዲህ አለ ፤

እምከመ ነሳሕክሙ ወበከይክሙ ተሐ
ይዉ ፣

አልቅሳችሁ ንስሐ ከገባችሁ ትድ
ናላችሁ ፤

www.ethiopianorthodox.org

ወትነብሩ ኀበ ሀሎክሙ ፣

ባላችሁበት አገር በተድላ በደ
ስታ ትኖራለላችሁ ፤ አንድም
ወትነብሩ ኀበ ሀሎክሙ በኀድ
ዓት ይላል ፤ በፀጥታ በደስታ
ትኖራላችሁ ፤

እስመ ተወከልክሙ በከንቱ ከንቶ ይከ
ውነክሙ ኃይልክሙ ፣

በከንቱ ጣዖት አምናችኋልና
ኃይላችሁ ሠራዊታችሁ ከንቱ
ይሆንባችኋል እንጂ ፤

፲፭፡ እመሰ ዐበይክሙ ሰሚዐ ፣

መስማቱን ግን እንቢ ብትሉ፤

ወትቤሉ በአፍራሲነ ናመስጥ ወንዒ
ዐን ረዋዒ ፈረሰ ፣

በፈረሳችን፣ በበላ ፈረሳችን ተቀ
ምጠን እናመልጣለን ብትሉ ፣

በእንተ ዝንቱኬ ረዋፅያን እሙንቱ
እለ ይዴግኑክሙ ፣

ስለዚህ ነገር የሚከተሏችሁ
ሰዎች ፈጣኖች ናቸው ፤

፲፮፡ ወይሜምዑ ዐሠርቱ ምእት
እምኔክሙ እምድምፀ አሐዱ ፣

ከናንተ ወገኖች ሺሁ ሰዎች
ካንድ ሰው ድምፅ የተነሣ ይሸ
ሻሉ ፤

ወእምቃለ አሐዱ ይጐይዩ ብዙኃን፣

ካንድ ሰው ድምፅ የተነሣ ብዙ
ሰዎች ይሸሻሉ ፤

እስከ ትከውኑ ከመ ሐሠር ውዑይ፣

እሳት እንደበላው ገለባ እስክት
ሆኑ ድረስ ፤

፲፯፡ ወካዕበ ይሠሃለክሙ እግዚአብ
ሔር ፣

ካዕበ ያልተያያዘ ነው፤ ዳግመኛ
እግዚአብሔር ይቅር ይላችኋል፤
አንድም የዘሩባቤልን ለዳዊት
ለሰሎሞን ካዕበ አለ ፤

ወበእንተ ዝንቱ ተለዐለ ከመ ይም
ሐርክሙ ፣

ስለዚህ ነገር ይቅር የሚላችሁ
ስለሆነ ልዕልናውን ገለጠ ፤

እስመ እግዚአብሔር አምላክነ መኰ
ንን ውእቱ ፣

ፈጣሪያችን እግዚአብሔር እው
ነተኛ ዳኛ ነውና ፤

ወአይቴ ውእቱ ክብርክሙ ፣

ባለጸግነታችሁ ወዴት ነው አል
ጠፋምን ፤

ብዑዓን እለ ይትዔገሥዎ ፣

ለፈተና ብሎ መከራ ቢያመ
ጣባቸው መከራውን ታግሠው

የሚቀበሉ ሰዎች ንዑዳን ክቡ
ራን ናቸው ፤

፲፰፡ እስመ ሕዝብ ቅዱስ የኀድር
ውስተ ኢየሩሳሌም ፣

ክቡር ወገን በኢየሩሳሌም ይኖ
ራልና ንዑዳን ክቡራን ናቸው፣
በጽዮን ብካየ ብክዩ ማንሻ ነው፤
አንድም ክቡር ወገን በኢየሩሳ
ሌም ይኖራልና በጽዮን ብካየ
ብክዩ በጽዮን ልቅሶን አልቅሱ፤

ተሠሃለነ በሉ ፣

ይቅር በለን በሉ ፤

ወይሰምዕ ቃለ ዐውያቲክሙ ሶበ
ርእየ ሕማመክሙ ወምንዳቤክሙ ፣

መከራችሁን ፀዋትወ መከራች
ሁን ባየ ጊዜ አልቅሳችሁ የለ
መናችሁትን ይሰማችኋል ፤

፲፱፡ ወይሁበክሙ እግዚአብሔር ሲሳ
የክሙ ፣

እግዚአብሔር የምትበሉትን
ምግባችሁን ይሰጣችኋል ፤

ወማየሂ ዘትሰትዩ ፣

የምትጠጡትን ውሀ ይሰጣች
ኋል፣ አንድም እክለ ረድኤትን
ማየ ረድኤትን ይሰጣችኋል፣
አንድም ትምህርትን ይሰጣች
ኋል፣ አንድም ሥጋውን ደሙን
ይሰጣችኋል ፤

ወኢይቀርቡ እንከ እለ ያስሕቱክሙ፣

ሰላም ሰላም እያሉ የሚያስቷ
ችሁ ነቢያተ ሐሰት ካህናተ
ጣዖት እንግዲህ ወዲህ አይቀ
ርቡም ፤

ወኢይሬእያ አዕንቲከ እለ ያስሕቱከ፣

የሚያስቱህ ነቢያተ ሐሰትን ካህ
ናተ ጣዖትን ዐይኖችህ አያዩም፤

፳፡ ወኢይሰምዓ አዕዛኒከ ድምፆሙ
ለእለ ስሕቱ በድኅሬከ ፣

ጆሮችህም ነቢያተ ጽድቅን እየ
ተከተሉ የሚያስቱ የነቢያተ ሐሰ
ትን የካህናተ ጣዖትን ድምፅ
አይሰሙም ፤

እለ ይብሉ ንሑር በዛቲ ፍኖት ፣

በዚች ሥራ ፀንተን እንኑር
የሚሉ ፤

እመሂ ለየማን ወእመሂ ለፀጋም ፣

ወደቀኝም ሆኖ ወደ ግራም ሆኖ
የማንን ጠልቶ አይደለም ፀጋ
ምን ሲያይ ነው፣ የማንን ቅሉ
ይጠላል የማን መስሎ የሚሠራ
ኃጢአት አለና ፤

፳፩፡ ወእመሂ መንገለ ጣዖት እለ
ቅፉላን በብሩር ወሥርግዋን በወርቅ፣

በብር በተለበጡ በወርቅም
ባጌጡ ወደ ጣዖትም ሁኖ በዚህ
ሥራ ፀንተን እንኑር የሚሉ ፤

www.ethiopianorthodox.org

ይእተ አሚረ ይከውኑ ደቃቀ ከመ መሬት ፣

ያንጊዜ እንደ ትቢያ የደቀቁ ይሆናሉ ፤

ወይትሐመጉ ከመ ማይ ፣

ታጥቦ እንደሚያፈሱት ውሀ ይሆናሉ፤ አንድም ድፍርስ ውሀ እንዲናቅ ጣዖታቱ ይናቃሉ ፤

ወይገድፉ ውስቴቶሙ ዕዳዋተ ፣

ትቢያውን ጉድፉን ይጥሉባቸ ዋል ፤

፳፪፤ ውእተ አሚረ ይዘንም ለዘርዓ ምድርከ ፣

ያንጊዜ ለሀገርህ ዘር ዝናብ ይዘ ንማል ፤

ወይከውን ፅጋበ ለእንስሳ ምድርከ ፣

ለሀገርህም ከብት ጥጋብ ይሆ ናል ፤

ወይሰብሑ መራዕይከ ፣

መንጋዎችህ ይሰባሉ ይወፍራሉ የዘመኑን መልካምነት መናገር ነው ፤

ወይትረዐዩ ብሔረ ሥዑረ ወርኂበ ፣

ሰፊ በሆነች በለመለመች አገር በኢየሩሳሌም ይኖራሉ ፣ አን ድም ሰባ ዘመን በተፈታች በኢ የሩሳሌም ይኖራሉ ፤ አንድም በለመለመች በኢየሩሳሌም ይሰ ማራሉ ካል. ነገ. ም ፤

፳፫፤ ወይቀምሑ ሐሠረ ብዕራይክሙ ወአዕዱጊክሙ ይሴሰዩ ሰገመ ፣

በሬዎቻችሁ ገለባውን ደፈጫ ውን ፣ አህዮቻችሁ ገፈራውን ይቅማሉ ፤

፳፬፤ ወይከውን ውሰተ አድባር ነዋ ኃት ፣

በረጅሙ ተራራ እንዲህ ይሆ ናል ፤

ወውስተ አውግር ልዑላት ፣

ከፍ ባሉ ኰረብታዎች እንዲህ ይሆናል ፤

ይውኅዝ ማይ ፣

ይከውን ያለውን ይውኅዝ ብሎ አመጣው፣ ምንጭ ይመነጫል፣ በዔዋዌ ጊዜ ደርቆ የነበረውን መናገር ነው፣ በሚጠት መን ጭቷልና፤ አንድም ከነገሥታት ከመኳንንት ተድላ ደስታ ይገ ኛል ፤ አንድም ከነቢያት ከካህ ናት ትምህርት ረድኤት ይገ ኛል፤ አንድም ከጳጳሳት ከሊቃነ ጳጳሳት ክብር ልጅነት ይገኛል፤

ውእተ አሚረ አመ ኀልቁ ብዙኃን ፣

ሠራዊተ ሰናክሬም በጠፉ ጊዜ ፤

ወአመ ወድቀ ማኅፈድ ፣

ሰናክሬም በጠፉ ጊዜ ፤

ይከውን ብርሃነ ከዋክብት ከመ ብር ሃነ ወርኅ ፣

የሠራዊቱ ተድላ ደስታ እንደ ቢትወደዱ ይሆናል ፤

ወብርሃነ ወርኅ ከመ ብርሃነ ፀሐይ፣

የቢትወደዱ ተድላ ደስታ እን ደንጉሡ ይሆናል ፤

ወብርሃነ ፀሐይ ምስብኢተ ፣

የንጉሡ ተድላ ደስታ ፍጹም ይሆናል፣ አንድም ውእተ አሚረ አመ ኀልቁ ብዙኃን ብለህ መልስ፣ ሠራዊተ አጋንንት ድል በተነሡ ጊዜ ወአመ ወድቀ ማኅ ፈድ፣ ዲያብሎስ ድል በተነሣ ጊዜ ይከውን ብርሃነ ከዋክብት ከመ ብርሃነ ወርኅ፣ የሰባ አርድ እት ክብር እንደ ዐሥራ ሁለቱ ሐዋርያት ክብር ይሆናል ወብር ሃነ ወርኅ ከመ ብርሃነ ፀሐይ ያሥራ አንዱ ሐዋርያት ክብር እንደ ጴጥሮስ ክብር ይሆናል፣ ወብርሃነ ፀሐይ ምስብኢተ የጴ ጥሮስ ክብር ፍጹም ይሆናል ፤

፳፭፤ ወይእተ አሚረ አመ ፈወሰ እግዚአብሔር ቍስለ ሕዝቡ ፣

ያንጊዜ በሰባ ዘመን እግዚአብ ሔር የወገኖቹን ቍስለ መከራ ባራቀ ጊዜ ፤

ወይፌውስ ሕማመ መቅሠፍትከ በጊዜሁ ፣

በሰባ ዘመን መከራውን ባራቀ ልህ ጊዜ ፤

፳፮፤ ናሁ ይመጽእ እግዚአብሔር በጥንዱይ መዋዕል ፣

በሰባ ዘመን እግዚአብሔር በረ ድኤት ይመጣል፤ አንድም ወይ እተ አሚረ አመ ፈወሰ እግዚ አብሔር ቍስለ ሕዝቡ ብለህ መልስ፣ ባምስት ሺህ ካምስት መቶ ዘመን እግዚአብሔር የም ዕመናንን ቍስለ ነፍስ ባራቀ ጊዜ ወይፌውስ ሕማመ ባምስት ሺህ ካምስት መቶ ዘመን ሕማመ ነፍስን ባራቀ ጊዜ (ኵነኔ ነው) ናሁ ይመጽእ እግዚአብሔር በጥንዱይ መዋዕል ባምስት ሺህ ካምስት መቶ ዘመን እግዚአ ብሔር ሰው ሁኖ ሥጋ ለብሶ ምዕመናንን ለማዳን ይመጣል፤

ወይነድድ መዓቱ ምስለ ቃለ ከና ፍሪሁ ፣

መዓቱ በከንፈሩ ተናግሮ ከሚ ያደርገው ተአምራት ጋራ ይመ ጣል ፤

www.ethiopianorthodox.org

ወምሉዕ መዓተ ቃሉ ፤

ቃሉ መዓትን የተመላ ነው፤

ወትበልዕ ከመ እሳት መቅሠፍተ መዓቱ ፤

ተቈጥቶ ያመጣት መዓት መቅሠፍት እንደ እሳት ታጠፋለች ፤

፳፯፤ ወይውኅዝ መዓቱ ከመ ማይ ዘውስተ ሙራድ ፤

መዓቱ እንደ መጣያ ውሀ ቀጥሎ ቀጥሎ ይመጣል ፤

ወይበጽሕ እስከ ክሣድ ፤

ውሀው እስከ አንገት ይደርሳል ማለት የጌታ መዓቱ አንገት ከደረት የሚለይ ነው ፤

ወይትነፈቅ ከመ ይሁከሙ ለአሕዛብ ፤

ሰናክሬም እስራኤልን ያውካቸው ዘንድ ፤

ወያስሕቶሙ ውስተ ከንቱ ፤

በከንቱ ጣዖትም ያስታቸው ዘንድ ከሠራዊቱ ተለይቶ ወደ ነነዌ ይሄዳል ሰናክሬም ነነዌ ሄዶ እሱ የኤን ሠራዊት ቢያጠፋ እኔስ የሱን ሠራዊት አላጠፋም ብሎ አምሳ አምስት ቀን ከእስራኤል የቀሩትን ሲያጠፋ ሰንብቷልና፣ አንድም ብልጣሶር አሕዛብን ያውካቸው ዘንድ ወያስሕቶሙ ውስተ ከንቱ በከንቱ ጣዖት ያስታቸው ዘንድ ከሠራዊቱ በሞት ይለያል፣ አንድም ያስሕቶሙ ይላል ብልጣሶር ባልሆነ ነገር ያስታቸዋል፣ እሱ ከሞተ በኋላ መከራ ቢፀናባቸው ጌታችን ብልጣሶር ሳለ በባሕር ጠልቀን በገደል ወድቀን ብንሞት በተሻለ ነበር ብለዋልና ፤

ወይዴግኖሙ ጌጋይ ወይእኅዘሙ ፤

ኃጢአታቸው እየተከተለ በመከራ ይይዛቸዋል ፤

ወይትቤቀሉመሙ ውስተ ገጾሙ ፤

ፊት ለፊት ተበቅሎ ያጠፋቸዋል ፤

፳፰፤ ወትረኑ ትትፈሥሑ ፤

እነሰናክሬምን ወትሮ ወትሮ ደስ ይላችኋልን ፤

ወትበውኡ ውስተ መቅደስየ ፤

ወደቤተ መቅደስ ትገባላችሁን፤ አንድም እነ ብልጣሶርን ወትሮ ወትሮ ደስ ይላችኋልን ወትሮ ወትሮ ወደ ቤተ መቅደስ ትገባላችሁ? ይላቸዋል፣ አያቱ ናቡከደነፆር ገብቷልና ያያቱን ለሱ ሰጥቶ ተናገረ ፤

ወአኮ ዘልፈ ዘትገብሩ በዐለ ፤

ዘወትር በዓልን የምታደርጉ አይደለም ፤

ወአኮ ከመ ፍሡሓን ዘትበውኡ በዕንዚራ ውስተ ደብረ እግዚአብሔር ኀበ እስራኤል ፤

እንደ ነቢያት እንደ ካህናት በገናውን እየመታችሁ ከእስራኤል ዘንድ ወደቤተ እግዚአብሔር የምትገቡ አይደለም፤ አንድም እስራኤል ወዳሉባት ወደ ኢየሩሳሌም ደስ እያላችሁ የምትገቡ አይደለም ፤

፳፱፤ ወያሰምዕ እግዚአብሔር ቃለ ስብሐቲሁ ፤

እግዚአብሔር የጌትነቱን ነገር ያሰማል ፤

ወያርኢ መዓተ መዝራዕቱ ፤

ሥልጣኑን የሚገልጥበት መዓቱን ያሳያል ፤

ወመቅሠፍተ መዓቱ ፤

መዓቱን የሚፈጽምበት መቅሠፍቱን ይገልጣል ፤

ወያነድድ በእሳት በላዒ ፤

በሚያጠፋ መቅሠፍት ያጠፋል፤

ወበኃይለ ፀዓዕ ፤

በብልጭልጭታ ፤

ወከመ ዝናም ጎያል ወበረድ ዐቢይ ዘይወርድ በቃለ እግዚአብሔር ፤

ብርቱ ዝናብ በእግዚአብሔር ትእዛዝ የሚወርድ ጽኑ በረድ ቀጥሎ ቀጥሎ እንዲወርድ ቀጥሎ ቀጥሎ መዓት መቅሠፍት መጥቶባቸው ፤

ወይትመውዑ ፋርስ በመቅሠፍት ዘይቀሥፎሙ ፤

የፋርስ ሰዎች በሚያጠፋ መቅሠፍት ይጠፋሉ ፤

፴፤ ወየዐግትዎ እለ ተሰፈወ ይርድእዎ ፤

ሰናክሬምን ይረዱት ዘንድ ተስፋ ያደረጋቸው ልጆቹ ይከዱታል ፤

ወእለ ኪያሆሙ ተአመነ እሙንቱ ይፀብዕዎ በቀኦር ፤

የታመናቸው ልጆቹ ሰናክሬምን ጨክነው ይጣሉታል ፤ (አዕንተ ውም ብትል ይሆናል) ፤

www.ethiopianorthodox.org

ወበከበሮ ወበመሰንቆ ፣

ከበሮ መሰንቆ የሚመታ ሰው እንዳያፍር ሳያፍሩ ይጣሉታል ፤

እስመ ኢኮነ እለ እምቀዲሙ ይት ሔዘቦሙ ፣

ሰናክሬም ከጥንት ጀምሮ ልጆቹን ይገድሉኛል ብሎ አይጠራጠርም ነበርና ፤ አንድም ወየዐግ ትዎ ብለህ መልስ፣ ብልጣሶርን ይረዱት ዘንድ ተስፋ ያደረጋቸው ቂሮስ ዳርዮስ ይከቡታል ፤

ወእለ ኪያሆሙ ተአመነ ፣

የታመናቸው ቂሮስ ዳርዮስ ብልጣሶርን ጨክነው ይጣሉታል ፤ ወበከበሮ ወበመሰንቆ ቂሮስ ዳርዮስ ነገሥታት ናቸውና ነጋሪቱን መሰንቆውን እያስመቱ መጥተው ብልጣሶርን ይገድሉታል ፤

እስመ ኢኮነ ፣

ብልጣሶር ከጥንት ጀምሮ ቂሮስ ዳርዮስ ይገድሉኛል ብሎ አይጠራጠርም ነበርና፣ ፋርስና ባቢሎን ቅሉ ጎረቤቶች ናቸውና::

፳፩፤ አንተሂ ትንግሥኑ ተደለውከ፣

ዳግመኑ ሲል ነው፤ አንተም ዳግመኛ ትነግሥ ዘንድ ተበጃጀህን (ተዘጋጀህን) ፤

ናሁ ተደለወ ለከ ቄላ ርኁብ ወግብዕሙቅ ፣

እነሆ ላንተስ መቃብር ገሃነም ተዘጋጅቶልሃል ፤

ወዕፀው ውጡሕ ወእሳት ውስቴቱ፣

እንጨት ተከምሮበታል በውስጡም እሳት ይነድበታል፣ አሁን በመቃብር እንጨት የሚከመር እሳት የሚነድ ሁኖ አይደለም የሥጋው ከነፍሱ የሚያደርሰው ስለሆነእንዲህአለ፤አንድም ብልጣሶርን እንዲህ ይለዋል፣ አንተም ትነግሥ ዘንድ ተዘጋጀህ? ላንተስ መቃብር ገሃነም ተዘጋጅቶ ልሃል፣እንጨት ተከምሮበታል ፣ በውስጡም እሳት ይነድበታል፣ አሁን በገሃነም በእንጨት የሚነድ እሳት ኑሮ አይደለም፣ ሰው በሚያየው በሚያውቀው መስሎ ለመናገር ነው፤

ወብዙኅ መዓተ እግዚአብሔር ከመ ተይ ዘይነድድ በገጻም ፣

የእግዚአብሔር መዓቱ መቅሠፍቱ በምድረ በዳ እንደሚቃጠል ድኻ ነው ::

ምዕራፍ ፴፩

፩፤ አሌ ሎሙ ለእለ ይወርዱ ብሔረ ግብፅ ይርድእዎሙ ፣

ይረዷቸው ዘንድ ወደግብፅ ለሚሄዱ ለእስራኤል ወዮላቸው ፤

ወይትአመኑ በአፍራሲሆሙ ወበሠረገላቲሆሙ ፣

በፈረሳቸው በሠረገላቸው ለሚታመኑ ሰዎች ወዮላቸው ፤

እስመ ብዙኅ አፍራሲሆሙ ወመልዐ ፈድፋደ ፣

ፈረሳቸው ብዙ ነውና እጅግም በዝቷልና ፤ አንድም ፈረሳቸው ሠረገላቸው ብዙ ነውና ብለው በፈረሳቸው በሠረገላቸው ለሚታመኑ ለእስራኤል ወዮላቸው ይላል ነቢዩ ፤

ወኢተወከሉ በቅዱስ እስራኤል ፣

በዕንቀ እስራኤል በክብረ እስራኤል በእግዚአብሔር አላመኑምና ፤

ወኢነሥኡ ለእግዚአብሔር ፣

እግዚአብሔርን በሕግ በአምልኮት አልፈለጉትምና ወዮላቸው፤

፪፤ ወውእቱ ጠቢብ አምጽአ ላዕሌሆሙ እኪተ ፣

የባሕርይ ዐዋቂ የሚሆን እሱ በነሳቸው መከራ አመጣባቸው፤ አንድም እሱ ግን የባሕርይ ዐዋቂ ነውና በነሳቸው መከራ አመጣባቸው ፤

ወኢይሔሱ ቃሉ ፣

ዘኢይሔሱ ቃሉ ሲል፣ ነውሐሰት የማይናገር ፤

ወያነሥእ ዕደወ እኩያነ ላዕለ ትውክልቶሙ ፣

እስራኤል በሚታመኑባቸው በግብፃውያን ላይ ክፉ ሰዎችን ያስነሳባቸዋል ፤ አንድም በክብራቸው በጌትነታቸው ላይ ስልምናሶርን ናቡከደነፆርን ያስናሣል፤

፫፤ ግብፅሰ ከንቱ ዕጓለ እመሕያው፣ ግብፃውያንስ ከንቱ ሰዎች ናቸው፤

ወኢኮኑ አምላከ ፣

አምላክ አይደሉም ፤

አፍራሲሆሙኒ ዘሥጋ ፣

ፈረሶቻቸውም ግዙፋን ናቸው፤

ወአኮ ዘመንፈስ ፣

ረቂቃን አይደሉም ፤ አንድም እንደ ኪሩቤል አይደሉም፤ አንድም እንደ ኪሩቤል ያይደሉ ሥጋውያን ናቸው ፤

ወያመጽእ እግዚአብሔር እዴሁ ላዕሌሆሙ ፣

እደ መዓቱን ያመጣባቸዋል ፤

ወይደክሙ እለ ይረድእዎሙ ፣

እስራኤልን የሚረዷቸው ግብፃውያን ይደክማሉ ፤ አንድም ግብፃውያንን የሚረዷቸው ፋጥልዳ ፣ ኢትዮጵያ ይደክማሉ ፣

www.ethiopianorthodox.org

አንድም ፉጥ ልዳ የሚረዷቸው
እስ ራኤል ይደክማሉ ፤

ወይትኀጐሉ ኵሎሙ ኅቡረ ፣

ሁሉም አንድ ሁነው ይጠፋሉ ፤

እስመ ከማሁ ይቤለኒ እግዚአብሔር ፣

እግዚአብሔር እንዲህ ብሎኛ
ልና ፤

፬፡ በከመ ይጥሕር አንበሳ ወዕጓለ
አንበሳ ላዕለ ዘይመስጥ ፣

ላዕለ ዘመሰጠ ሲል ነው፤ አባት
አንበሳ ፣ ያንበሳ ወይፈን በነጠ
ቀው ላይ እንዲጮህ ፤

ወይኬልሕ ላዕሌሁ እስከ ይመልዕ
አድባረ ቃሉ ፣

ቃሉ ተራራውን እስኪያናው
ጠው ድረስ በእርሱ ላይ እንዲ
ጮህ ፤

ወይኬልሑ ላዕሌሁ ኵሎሙ ኖሎት ፣

እረኞች በሱ ላይ እንዲጮሁ ፤

ኢይፈርህ እምብዝሆሙ ፣

ከብዛታቸው የተነሣ እንዳይ
ፈራ ፤

ወኢይደነግፅ እምቃሎሙ ፣

ከቃላቸው የተነሣ እንዳይደነ
ግጥ ፤

ወይትመውዑ ፣

ወእምብዝኀ መዓቱ ይደነግፁ ፣

ከቁጣው ብዛት የተነሣ እንዲደ
ነግጡ ፤

ከማሁ ይወርድ እግዚአብሔር ፀባ
ዖት ይፃባዕ በእንተ ደብረ ጽዮን
ውስተ አድባሪሃ ፣

ያ በማስፈራት እንዲነሣ አሸ
ናፊ እግዚአብሔር ደብረ ጽዮ
ንን ነገሥታቱን ይጣላ ዘንድ
በመዓት በማስፈራት ይመጣል ፤

፭፡ ከመ ያፍ ዘይሠርር ፣

በዓየር የሚበር ወፍ ፈጥኖ ካሰ
በው እንዲደርስ ፤

ከማሁ ይፀበዕ እግዚአብሔር ፀባዖት
በእንተ ኢየሩሳሌም ፣

አሸናፊ እግዚአብሔር ፈጥኖ
ኢየሩሳሌምን ይጣላል ፣ ይረድ
እሂ ማንሻ ፤ አንድም በእንተ
ደብረ ጽዮን ውስተ አድባሪሃ ፣
ስለ ኢየሩሳሌም ስለ ነገሥታቱ
ባቢሎንን ይጣላ ዘንድ አሸናፊ
እግዚአብሔር በመዓት በማስፈ
ራት ይመጣል ፣ ያፍ ፈጥኖ ካሰ
በው እንዲደርስ ፤

ይረድእሂ ወያድኅን ወይባልሕ ወያ
ሐዩ ፣

ይባልህና ያሐዩ አንድ ወገን
ነው ፣ አሸናፊ እግዚአብሔር ስለ
ኢየሩሳሌ[illegible]

፮፡ ተመየጡ እለ እሙቀ ምክረ ትመ
ክሩ ከመ ተዓምፁ ፣

ትበድሉ ዘንድ ጥልቅ ምክር
የምትመክሩ ሰዎች ተመለሱ ፤

፯፡ እስመ ውእተ አሚረ የዐልዉ
ሰብእ አማልክቲሆሙ ዘወርቅ ወዘብ
ሩር ዘገብሩ በእደሆሙ ፣

ያንጊዜ ሰዎች በእጃቸው የሠሯ
ቸው የወርቅ የብር የሚሆኑ ጣዖ
ቶቻቸውን ይወነጅላሉና ማለት
ይተዋሉና ፤

፰፡ ወይወድቅ አሶር በኵናት ፣

ሰናክሬም በጦር ይጠፋል ፤

ወአኮ በኵናተ ሰብእ ፣

በሰው ጦር የሚጠፋ አይደለም ፤

ወአኮ መጥባሕተ ብእሲ ዘትበልዖሙ ፣

የሰው ሰይፍ የምታጠፋቸው
አይደለም ፣ አላ በሰይፈ መል
አክ ያለበት ነው ፣ በመልአኩ
ሰይፍ ነው እንጂ ፤

ወአኮ እምገጸ ኵናት ዘይጐይዩ ወራ
ዙቶሙ ፣

ከሰው ጦር የተነሣ ጐልማሶች
የሚሸሹ አይደለም ፤

ወይትመውዑ ፣

ከሰው ጦር የተነሣ ድል የሚ
ነሱ አይደለም ፤

፱፡ ወኰኵሕ ትውሕጦሙ ፣

[illegible] ሕዝቅያስን ፅኑ ረድኤት
ትጠብቃ[illegible] ፣ [illegible]ንድም እነ

ሰናክሬምን ፅኑ መቅሠፍት ታጠ
ፋቸዋለች ፤

ወይትመውዑ ፋርስ ፣

የፋርስ ሰዎች ድል ይነሣሉ ፤

ወዘሂ አምሠጠ ይሠገር ፣

በነነዌ ያለበት ነው ፣ ከለኪሶ
ያመለጠ ሰናክሬም በነነዌ ይጠ
ፋል ::

ምዕራፍ ፴፪

ጉባዔ

፩፡ ከመዝ ይቤ እግዚአብሔር ፣

እግዚአብሔር እንዲህ አለ ፤

ብፁዕ ዘቦ ዘርዕ በጽዮን ፣

ሰናክሬም በጠፋ ጊዜ ገንዘቡን
እየዘረፈ የሚያገባ በጽዮን ልጅ
ያለው ሰው ንዑድ ነው ክቡር
ነው ፤

ወዘቦ አብያት በኢየሩሳሌም ፣

የሰናክሬምን ገንዘብ ዘርፎ የሚ
ያገባበት በኢየሩሳሌም ቤት
ያለው ሰው ንዑድ ነው ክቡር
ነው ፤

እስመ ናሁ ጻድቅ ንጉሥ ይነግሥ ፣

ጻድቅ ንጉሥ ሕዝቅያስ ይነግ
ሣልና ፤

ወመላእክትኒ በጽድቅ ይኴንኑ ፣

አለቆችም በውነት ይፈርዳሉና
ብፁዕ ዘቦ ዘርዕ ብለህ እሠር ፤

www.ethiopianorthodox.org

ወየ·ነብዕ ሰብእ ቃሎ ማንሻ ነው፤ አንድም እንዲህ ነውና፤

፪፤ ወየ·ነብዕ ሰብእ ቃሎ ፣

ሸፋጭ ለዋጭ ቃሉን ይሠውራል፤ አንድም ከባቢሎን ወጥቶ በጽዮን የሚዘራው ዘር ያለው ሰው ንዑድ ነው ክቡር ነው፤ ከባቢሎን ወጥቶ በኢየሩሳሌም የሚገባበት ቤት ያለው ሰው ንዑድ ነው ክቡር ነው፤ ጻድቅ ንጉሥ ዘሩባቤል ይነግሣልና አለቆችም በውነት ይፈርዳሉና ብፁዕ ብለህ እሠር፤ አንድም እንዲህ ነውና፤ ወየ·ነብዕ ሸፋጭ ለዋጭ ቃሉን ይሠውራል፤ አንድም በጽዮን ዘርዕ ሃይማኖት በኢየሩሳሌም ቤተ ምግባር ያለው ሰው ንዑድ ነው ክቡር ነው፣ አንድም በዚህ ዓለም ዘርዐ ሃይማኖት ቤተ ምግባር ያለው ሰው ብፁዕ በጽዮን ወበኢየሩሳሌም፤ በግነት በመንግሥተ ሰማያት ንዑድ ነው ክቡር ነው ፤ ጻድቅ ጌታ ይነግሣልና ፤ ሐዋርያትም በውነት ያስተምራሉና ፤ ብፁዕ ብለህ እሠር ፤ አንድም እንዲህ ነውና ኃጥእ መናፍቅ ይጠፋል ፤ አንድም በጽዮን ሰማያዊት ዘርዐ ሃይማኖት፤ በኢየሩሳሌም ሰማያዊት አብያተ ምግባር ያላቸው ሰዎች ንዑዳን ክቡራን ናቸው፣ በሰማይ ሃይማኖት ይዘው ምግባር ሠርተው የሚጠቀሙ ሁነው አይደለም፤ በሃይማኖት ጸንተው ምግባር ትሩፋት ሠርተው የተገኙ ሰዎች ብፁዕ ብለህ እሠር ፤ ጻድቀ ባሕርይ ክርስቶስ ይነግሣልና ሐዋርያትም በእውነት ይፈርዳሉና፣ ብፁዕ፤ አንድም እንዲህ ነውና ወየ·ነብዕ ሰብእ ቃሎ ኃጥእ መናፍቅ ቃሉን ይሠውራል ፤

ወይት·ነባዕ ከመ ዘይሠጣም ውስተ ማይ ፣

በውሀ ውስጥ እንደሚሠጥም እንደ ቋትለኛው እንደ ዓሣው ይሠጥማል ፤

ወያስተርኢ በጽዮን ከመ ፈለግ ዘይውኅዝ ክብሩ በምድር ዕምዕት ፣

በተጠማች ምድር እንደሚፈስ ውሀ ክብሩ ብዙ የሆነ ጌታ በሰባ ዘመን በጽዮን በረድኤት ይገለጣል፤ አንድም በተጠማች ምድር እንደሚፈስ ውሀ ክብሩ ብዙ የሆነ ዘሩባቤል በኢየሩሳሌም ይገለጣል፤ አንድም እንደ ፈሳሽ ውሀ ክብሩ ብዙ የሆነ ጌታ ያስተርኢ በጽዮን ፤ ምድር ዕምዕት ብሎ መግጠም ነው፤ ከዘር ከሩካቤ በተጠማች በማኅፀነ ማርያም ያድራል ፤ ዕምዕት ምድር

ዘኢሳይያስ ቅዱስ ያሬድ ነሐሴ ኪ/ም የሚያሰኛት ይህ ነው ፤ አንድም ክብሩ እንደ ፈሳሽ ውሀ ብዙ የሆነ ጌታ ሰው ሁኖ ሥጋ ለብሶ በጽዮን ይገለጣል ፤

፫፤ ወኢይትቄከሉ እንከ በዕንለ እመ ሕያው ፣

እንግዲህ ወዲህ በሰው ሠራሽ ጣዖት አያምኑም፤ አንድም ቃል ባልተዋሐደው በዘርዐ ዳዊት አያምኑም ፤

ጸዕሙ· ያዐምው በዕዝኖሙ· ፣

በጆሮዋቸው ይሰማሉ እንጂ ፤

፬፤ ወልብኒ ድኩም ይሰምዕ አእምሮ፣

ሰባ ዘመን በኃጢአት በጣዖት ደክሞ የነበረ ልቡና ዕውቀትን ገንዘብ ያደርጋል፣ አንድም አምስት ሺህ ካምስት መቶ ዘመን በመከራ የደከመ ልቡና ዕውቀትን ያውቃል ፤

ልሳንኒ ጸያፍ ፍጡነ ይትሜህር ነገረ ሰላም ፣

ሰባ ዘመን በኃጢአት በጣዖት ዲዳ የነበረ አንደበት ኦሪትን ፈጥኖ ይማራል ፤ አንድም ሕገ ሰላም ወንጌልን ይማራል ፤

፭፤ ወኢታዕምዕዎ እንከ ለዐብድ ፣

ሰነፍ ሰው ኃጢአት ሥራ ፣ ጣዖት አምልክ ቢልህ አትስማ፣

ወሶበ ይብለከ ወዓሊከ አርምም ፣

ሎሌህም ኃጢአት ሥራ ፣ ጣዖት አምልክ ቢልህ ዝም በል አለ አትስማ ፣

፮፤ እስመ ዐብድሰ ዕበደ ይነብብ ፣

ሰነፍ የስንፋናን ነገር ይናገራልና ፤

ወልቡኒ ከንቶ ይሔሊ ከመ ይግብር ዐመፃ ፣

ዐመፅን ያደርግ ዘንድ ልቡ ከንቱ ነገርን ያስባልና ፤

ወከመ ይንብብ ኃጢኣተ በኀበ እግዚኣብሔር ፣

በእግዚኣብሔር ዘንድ ኃጢአት የሚሆን ነገር ይናገር ዘንድ፤

ወከመ ይዝራዕ ነፍሰ ርኅበተ ፣

ሰባ ዘመን ከረድኤት ከትም ህርት የተራበችውን ሰውነት እንደ ተራበች ያስቀር ዘንድ ፤

ወከመ ያዕርቅ ነፍሰ ዕምዕተ ፣

ሰባ ዘመን ከረድኤት ከትም ህርት የተጠማችውን ሰውነት እንደ ተጠማች ያስቀር ዘንድ ልቡ ከንቱ ነገርን ያስባልና ፤

፯፤ እስመ ሕሊናሆሙ ለእኩያን ዓመፃ ትመክር ፣

የክፉ ሰዎች ልቡናቸው ኃጢአት ሥራ ፣ ጣዖት አምልክ እያለች ትመክራለችና ፤

www.ethiopianorthodox.org

ከመ ይቅትልዎ ለነዳይ በነገረ ዓመ ፃሆሙ ፣

ድሀውን በኃጢአታቸው ነገር ያጠፉት ዘንድ ፣

ወከመ ይገፍትዑ ፍትሐ ምስኪን፣

የድሀውን ፍርድ ይለውጡ ዘንድ የክፉ ሰዎች ልቡናቸው ኃጢአት ሥራ ፣ ጣዖት አምልክ እያለች ትመክራለችና ፤ አንድም የምት መክር ስለሆነ ዕበደ ይነብብ ፤ ሰነፍ ስንፍናን ይናገራልና፤ ወኢ ታዕምዕዎ እንከ ለዐብድ ወሶበ ይብለከ ወዓሊከ አርምም ላለው ጻድቃንሰ ማንሻ ነው፣ አንድም የእኩያን ልቡና ዐመፅን ትመ ክራለችና ፤

፰፡ ጻድቃንሰ ጥበበ ይመክሩ ፣

እስመን የተከተለ ሰ ቀሪ ነው ፣ አይተረጐምም ጻድቃን ጥበብን ይመክራሉ ፣ አንድም እንዲህ ነውና ጻድቃን ግን ምግባር ትሩ ፋት ሥሩ እያሉ ይመክራሉ ፤ አንድም ወኢታዕምዕዎ እንከ ለዐብድ ብለህ መልስ ፤ ነቢየ ሐሰት ካህነ ጣዖት ኃጢአት ሥራ ፣ ጣዖት አምልክ ቢልህ አትስማ ፤ ወሶበ ይብለከ ወዓ ሊከ አርምም ሎሌህም ኃጢአት ሥራ ጣዖት አምልክ ቢልህ አት ስማ ፤ ሁለቱም አርእስት ነው ፤ ለሁለቱም ያመጣል፤ ሰነፍ የስን ፍናን ነገር ይናገራልና ልቡም ከንቱ ነገርን ያስባልና በእግዚ አብሔር ዘንድ ኃጢአት የሚ ሆን ነገር ይናገር ዘንድ ያስባ ልና ፤ ከልጅነት ከክብር የተራ በችውን ሰውነት እንደተራበች ያስቀር ዘንድ ያስባልና ፣ ከልጅ ነት ከክብር የተለየችውን ሰው ነት እንደተለየች ያስቀር ዘንድ ያስባልና ፤ ኢታዕምዕዎ ላለው የክፉ ሰዎች ልቡናቸው ኃጢ አት ሥራ፣ ጣዖት አምልክ እያ ለች ትመክራለችና ፣ ድሀውን ኃጢአት በሚሆን ነገራቸው ያጠ ፉት ዘንድ ፣ የድሀውን ፍርድም ይለውጡ ዘንድ ፣ የክፉ ሰዎች ልቡናቸው ኃጢአት ሥራ ጣዖት አምልክ እያለች ትመክራለ ችና ፤ ወሶበ ይብለከ ወዓሊከ አርምም ላለው ፤ አንድም እን ዲህ ነውና ፣ ጻድቃንሰ ጥበበ ይመክሩ እስመን የተከተለ ሰ ቀሪ ነው ፣ አይተረጐምም ጻድ ቃን ጥበብን ይመክራሉ ፤ አን ድም እንዲህ ነውና ፣ ወጻድቃ ንሰ ፣ ጻድቃን ግን ምግባር ትሩ ፋት ሥሩ እያሉ ይመክራሉ፤

ወትነብር ይእቲ ምክር ለዓለም ፣

እንዲህ ምብለው የመከሯት ምክር ለዘለዓለም ፀንታ ትኖራ ለች ፤

፱፡ አንስት ብዑላት ተንሥኣ ወስም ዓኒ ቃልየ ፣

በአዝርዕት በአትክልት የከበራ ችሁ ሴቶች ተነሥታችሁ ነገ ሬን ስሙኝ፤ ስንኳን የሰማያዊ ንጉሥ ነገርና የምድራዊ ንጉሥ ነገርስ ስንኳ ቢሆን ተነሥቶ ታጥቆ መስማት ይገባናልና ፤ አንድም በወርቅ በብር የከበራ ችሁ ሴቶች ነገሬን ስሙኝ ፤ አንድም በምግባር በሃይማኖት የከበራችሁ ሠላሳ ስድስቱ ቅዱ ሳት አንስት ተነሥታችሁ ነገሬ ወንጌልን ስሙኝ ፤

አዋልድ ምዕመናት አፅምዓኒ ነገ ርየ ፣

የታመናችሁ ሴቶች ነገሬን አድምጡኝ ፤ አንድም የምግባር የሃይማኖታችሁን ዋጋ እናገኛ ለን ብላችሁ የምታምኑ ምዕመ ናን ፤ አንድም በጌታ የምታምኑ ሠለሳ ስድስቱ ቅዱሳት አንስት ነገሬ ወንጌልን አድምጡኝ ፤

፲፡ ለለመዋዕል ወለለዓመት ደንግፃ ዕለተ ሕማም እንዘ ትትሐዘባ ፣

እየቀኑ እየዘመኑ ዕለተ ዔዋዌን እያሰባችሁ እዘኑ ደንግጡ፤ አን ድም እየቀኑ፣ እየዘመኑ ዕለተ ስቅለትን እያሰባችሁ እዘኑ ደን ግጡ ፤

ኀለፈ ቀስም ወኀልቀ ማዕረር ፣

እንዲህ የምትለን ምን ሰምተ ህብናል ትሉኝ እንደሆነ፣ የወ ይኑ የስንዴው መከር አለፈ ፤

ወኢይመጽእ እንከ ፣

ከእንግዲህ ወዲህ አይመጣም ፤

፲፩፡ ደንግፃ ወተክዛ እለ ትትአመና ፣

በጣዖቱ የምታምኑ እዘኑ ደን ግጡ ፤ አንድም እለ ተአንማ ዕርቃ ወተሰለባ ፤ ቋሬውን ዙፋ ሬውን የምትፈትሉ ሴቶች ተገ ፈፉ ራቁታችሁን ሁኑ፤ አንድም እለ ትትአመና ፣ በእግዚአብ ሔር የምታምኑ ምዕመናን ተገ ፈፉ ራቁታችሁን ሁኑ ፤

ወእሥራ ሐቄክን ፣

እንደ ወትሮው እየወጡ እየ ገቡ መጠልቀጥ (መሰልቀጥ) የለምና ፣ ወገባችሁን አሥራችሁ ከንፈራችሁን አሳርራችሁ ኑሩ፤

፲፪፡ ወሕፍጣ ገጸክን ፣

ፊታችሁን ንጩ አጥባተክንም ይላል ፤

www.ethiopianorthodox.org

በእንተ ምድረ ሕዝብየ መፍትው ፣

ስለምትወደድ ስለወገኖቼ አገር ስለኢየሩሳሌም ፤

፲፫፡ ወይበቍል ሦክ ወአሜከላ ውስተ ገራውሂሆሙ ፣

በርሻቸው እሾህ አሜከላ ይበቅ ልበታል ፤

ወይሠዐር ትፍሥሕት እምኵሉ አብ ያቲሆሙ ፣

ከቤታቸው ተድላ ደስታ ይጠ ፋል ፤

ሀገር መፍትው ወብዕልት ይትመ ዘበራ አብያቲሃ ፣

አብያቲሃ ለሀገር መፍትው ሲል ነው ፤ በአዝርዕት በአትክ ልት የከበረች የተወደደች አገር የኢየሩሳሌም ቤቶቿ ይፈርሳሉ፤

፲፬፡ ወየኀድጉ አህጉሪሆሙ ብዑላተ፣

በአዝርዕት በአትክልት የከበረ አገራቸውን ትተው ይሄዳሉ ፤

ወትርሢተ አብያቲሆሙ ፣

ወርሡይ ሲል ነው ፣ የተጋረደ የተነጠፈ ቤታቸውን ትተው ይሄዳሉ ፤

ወይከውና አህጉሪሆሙ በአታተ እስከ ለዓለም ፣

አገራቸው ለዘላለሙ ዋሻ ይሆ ናል ፤

በዓሎሙ ለአእዱገ ገዳም ፣

ዕረፍቶሙ ሲል ነው ፣ የምድረ በዳ አህዮች ማረፊያ ይሆናል፤

ወምራዕየ እንስሳ ፣

የከብት መሠማሪያ ይሆናል ፤

እስከ ይመጽእ ላዕሌሆሙ መንፈስ እምአርያም ፣

ረድኤት ከሰማይ እስኪመጣላ ቸው ድረስ ፤

፲፭፡ ወይከውን በድው ከርሜለ ፣

ምድረበዳው ችፍርግ ብቻ ይሆ ናል ፤

ወከርሜል ዖመ ፣

ችፍርጉም በዔዋዌ ገኖ ዛፍ ይሆ ናል፤ አንድም ጥቂት ገንዘብ ያል ነበረው ጥቂት ገንዘብ እንዳለው ይሆናል ፤

፲፮፡ ወየዐርፍ ፍትሑ ውስተ ገዳም፣

ፍርዱ ዔዋዌ ፍርዱ ሚጠት ከምግባር ከሃይማኖት ምድረ በዳ በሆነች በኢየሩሳሌም ያር ፋል ፤

ወጽድቁሂ ውስተ ቀርሜሎስ የኀድር፣

እውነተኛ ፍርዱ ዔዋዌ ፤ አን ድም ሚጠት በቀርሜሎስ ያድ ራል ይደረጋል ፤ አንድም ወየዐ ርፍ ፍትሑ ፣ ሰባ ዘመን ምድረ

በዳ በሆነች በኢየሩሳሌም ፍር ዱን በማቅናት ያርፋል ፤

ወጽድቁሂ ፣

ቸርነቱም በኢየሩሳሌም ጸንቶ ይኖራል ፤

፲፯፡ ወካዕበ ይከውን ሰላም ፣

ዳግመኛ ተድላ ደስታ ይሆናል፣ ለዔዋዌ ሚጠትን ካዕበ አለ ፣ ያልተካከለ ፤ አንድም የመቃብ ያንን ለትሩፋን ካዕበ አለ ፤

ወምግባረ ጽድቅ ፣

ምግባር ትሩፋት ይሠራል ፤

ወትእኅዝ ጽድቅ መካነ ምዕራፋ ፣

ምግባር ሃይማኖት የእስራኤ ልን ልቡና ትይዛለች ፤

ወይትዌከሉ ቦቱ እስከ ለዓለም ፣

ለዘለዓለሙ ያምኑበታል ፤

፲፰፡ ወይነብሩ ሕዝብ ውስተ ሀገረ ሰላም ፣

እስራኤል ፍቅር አንድነት በሚ ደረግባት በኢየሩሳሌም ይኖ ራሉ ፤

ወይነብሩ ተአሚኖሙ ፣

ጠላት ጠፍቶላቸው ተዘልለው ይኖራሉ ፤

ወየዐርፉ ውስተ ብዕል ፣

ከብረው ይኖራሉ ፤

፲፱፡ ወእመኒ ወረደ በረድ ኢይበጽ ሐክሙ ፣

መዓት መቅሠፍት ቢመጣ አያ ገኛችሁም ፤

ወይትአመኑ እለ ይነብሩ ውስተ ገዳም ወእለ ይነብሩ ሐቅለ ፣

በምድረ በዳ በዛፉ ሥር የሚ ኖሩ ሁሉ ጠላት ጠፍቶላቸው ተዘልለው ይኖራሉ ፤

፳፡ ብዑዓን እለ ይዘርዑ ኀበ ቦቱ ማይ ፣

ውሃ ካለበት የሚዘሩ ሰዎች ንዑ ዳን ክቡራን ናቸው ፤

ወኀበ ይከይድዎ አድግ ወላህም ፣

አህያ ላም ከረገጡት ማለት ከጭጨቱ የሚዘሩ ሰዎች ንዑ ዳን ክቡራን ናቸው ፤ አንድም ነቢያት ያስተማሯቸው እስራኤ ልን የሚያስተምሩ ሐዋርያት ንዑዳን ክቡራን ናቸው ፣ ያልተ ማረውን ከማስተማር ተምሮ የገ ደፈውን ማስተማር አያስቸግ ርምና ፤ አያፅርምና ብትልም ይሆናል ::

ምዕራፍ ፴፫

፩፡ አሌ ሎሙ ለእለ ያኀሥሩክሙ ፣

ለሚያዋርዷችሁ ሰዎች ወዮላ ቸው ፤

www.ethiopianorthodox.org

ወለክሙሰ አልቦ ዘያኀሥረክሙ

እናንተንስ የሚያዋርዳችሁ የለም ፤

ወዘለክሙ ዐለወ አኮ ኪያክሙ ዘየ ዐሉ ፣

እናንተን የወነጀለ ሰው እናን ተን የወነጀለ አይደለም ፤

ወይሠገሩ ዐላውያን ፣

ዐሥሩ ነገድ በመከራ ይያዛሉ ፤

ወይእኅዝዎሙ ፣

በመከራ ይይዟቸዋል ፤

ወከመ ቍንቍኔ ልብስ ከማሁ ይት በልዑ ፣

ብል ልብስን እንዲያጠፋ እንደ ዚህም ሁሉ ይጠፋሉ ፤

፪፡ እግዚኦ ተሠሃለነ እስመ ኪያከ ተወከልነ ፣

ባንተ አምነናልና አቤቱ ይቅር በለን ፤

ወኮነ ዘርዖሙ ለዐላውያን ለኀጕል፣

ያሥሩ ነገድ ልጃቸው ለጥፋት ሆነ ፤

ወመድኀኒትነስ ለአመ ምንዳቤነ ውእቱ ፣

መድኃኒታችን ሚጠት ግንበመ ከራችን ጊዜ ይደረግልናል ፤

፫፡ ወእምግርማ ቃልከ ደንገፁ አሕ ዛብ በፈሪሆትከ ፣

ከቃልህ መፈራት የተነሣ አን ተን በመፍራት አሕዛብ ደነገጡ፤

ወተዘርዉ አሕዛብ በፈሪሆትከ ፣

አንተን በመፍራት አሕዛብ ተበ ተኑ ፤

፬፡ ወይእዜኒ ናሁ ይትጋባዕ ምኅርካ ክሙ ንዑሱ ወዐቢዩ ከመ ይትጋባዕ አንበጣ ፣

አንበጣ ከባሕር ወርዶ እንዲሰ በሰብ ታላቁም ታናሹም ምርኮ ዋችሁ ይሰበሰባል፣ ከማሁ ማንሻ ነው፤ አንድም አንበጣ በባሕር እንዲሰበሰብ ፤

፭፡ ከማሁ ይትጋባዕ ለክሙ ቅዱሰ እግዚአብሔር ዘየኀድር ውስተ ጽዮን ወውስተ አርያም ፣

በጽዮን በልዕልና የሚኖር ፅንዐ እስራኤል ክብረ እስራኤል እግ ዚአብሔር ያድርባችኋል ፤

ወመልዐት ጽዮን ጽድቀ ወርትዐ ፣

ጽዮን ምግባር ሃይማኖትን መላች ፤

፮፡ ወአስተጋብዕዎሙ በሕግ ውስተ መዛግብተ መድኀኒትነ ፣

ነቢያት ካህናት ድኅነታችን በሚደረግባት በኢየሩሳሌም በሕግ ይሰበስቧቸዋል ፤

መጽአት ጥበብ ወምክር ፣

ጥበብ ምክር ሚጠት መጣች ፤

ወጽድቅ እምኀበ እግዚአብሔር ፣

ውኀሊቆ ሰብዓ ዓመት ያላት ከእግዚአብሔር ዘንድ ታዝዛ ተደረገች ፤

እስመ ተረከበት ጽድቅ ፣

ውኀሊቆ ሰብዓ ዓመት ያላት ደርሳለችና ፤

፯፡ ናሁ እምግርማክሙ ፈርሁክሙ እለ ቀዲሙ ትፈርህዎሙ አንትሙ፣

እነሆ ቀድሞ እናንተ ትፈሯ ቸው የነበሩ አሕዛብ ከግርማ ቸሁ የተነሣ ፈሯችሁ ፤

ወትርዕዱ እምኔሆሙ ፣

ከነሱ የተነሣ ትርዱ ትንቀጠ ቀጡ የነበረ ፤

ወይትፌነዉ ሐዋርያት እንዘ መሪረ ይበክዩ ፣

መልእክተኞች ፅኑ ልቅሶ እያ ለቀሱ ይላካሉ ፤

ወይስእሉ ሰላመ ፣

እንዘ ይስእሉ ሰላመ ሲል ነው፣ ፍቅር አንድነትን ሲሹ፣ በዔዋዌ እስራኤል አሕዛብን ተዉን እን ገብር እንቀቅል ብለው ይልኩ ባቸዋል፣ ሂደው ይነግሯቸዋል፣ አይሆንም ይሏቸዋል፣ ተመል ሰው ሒደው ለእስራኤል አይ ሆንም አሉን ብለው ይነግሯቸ ዋል፣ ዳግመኛ ሄዳችሁ ንገሩዋ ቸው ይሏቸዋል፣ ላይሰሙን ያታ ክቱናል እያሉ እያለቀሱ ይላ ካሉ፣ አንድም በሚጠት አሕ ዛብ እስራኤልን ተዉን እንገ ብር እንቀቅል ብለው ይልኩባቸ ዋል፣ አይሆንም እንደ ወጉን እንወጋቸዋለን እንደ ዘረፉን እን ዘርፋቸዋለን ይሏቸዋል፣ ከዚያ ተመልሰው እንዲህ አሉን ብለው ለአሕዛብ ይነግሩዋቸ ዋል ፣ ዳግመኛ ሒዳችሁ ንገሩ ዋ ቸ ው ይሏቸዋል ላይሰሙን ያታክቱናል ብለው እያዘኑ እያ ለቀሱ ይሄዳሉ ፤

፰፡ እስመ ማሰነ ፍኖቶሙ ፣

ሥራቸው ጠፍቷልና ፤

ውኀለፈ ግርማሆሙ ለአሕዛብ ፣

የእስራኤል (አሕዛብ) መፈራታ ቸው አልፏልና ፤

ወተሥዕረ ኪዳኖሙ ፣

ዳዊት ከኪራም ፤ ኪራም ከሰሎ ሞን የተማማሉት መሐላ ፈር ሷልና ፤

ወትሬስይዎሙ ከመ ዕዳው ፣

እንደ ትቢያ ታደርጓቸዋላችሁ፤ አንድም ወኢትሬስይዎሙ ከመ ዕደው፤ እንደ ሴት እንጂ እንደ ወንድ አታደርጓቸውም ፤

www.ethiopianorthodox.org

፱፡ ለሀወት ምድር ፣

ትሑታኑ አዘኑ ፣ አንድም ምድር ኢየሩሳሌም በዔዋዌ ፣ ባቢሎን በሚጠት አለቀሰች ፤

ወተኀፍረ ሊባኖስ ፣

ንጉሡ በመከራ አፈረ ፤

ወፆመ ኮነ ሣሮን ፣

አክርማውም በዔዋዌ ገኖ ዛፍ ኾነ ፤

ወተዐውቀ ገሊላ ፣

ገሊላ በዔዋዌ በጥፋት በሚጠት በልማት ታወቀ ፤

ወቀርሜሎስሂ ፣

ቀርሜሎስም በዔዋዌ በጥፋት በሚጠት በልማት ታወቀ ፤

፲፡ ናሁ ይእዜ እትነሣእ ይቤ እግዚ አብሔር ፣

እነሆ እግዚአብሔር ፈጥኜ እነሳለሁ አለ ፤

ወይእዜ እሴባሕ ፣

ዛሬም እመሰገናለሁ ፤

ወይእዜ እትሌዐል አነ ፣

ዛሬም እኔ ልዕልናዬን እገልጣለሁ ፤

፲፩፡ ወይእዜ ትሬእዩኒ ፣

ዛሬ ስረዳችሁ ታዩኛላችሁ ፤

ወይእዜ ታነክሩኒ ፣

አይታችሁም ታደንቁኛላችሁ ፤

ወይከውን ከንቶ ኃይለ መንፈስ ክሙ ፣

የልቡናችሁ ዕውቀት ከንቱ ይሆናል ፤

ወእሳት ትበልዐክሙ ፣

ጦር አንድም መዓት መቅሠፍት ታጠፋችኋለች ፤

፲፪ ወይከውኑ አሕዛብ ከመ ዋዕየ ሦክ ዘገዳም ውዑያነ ወግዱፋነ ፣

ይህ ሊመጣባቸው አሕዛብ በምድረ በዳ እንዳለ ቋያ በመከራ የተጣሉ በእሳት የተቃጠሉ ይሆናሉ ፤ አንድም አሕዛብ በዔዋዌ እንደ ቋያ ይሆናሉ አለ አጥፊ ይሆናሉ ፤ አንድም ከመ ዘአውዐዮ በሰባ ዘመን ቋያ እንዳቃጠለው እሾህ ይሆናሉ አለ ጠፊ ይሆናሉ ፤

፲፫፤ ወይሰምዑ ዘገበርኩ እለሂ እምርኁቅ ወእለሂ እምቅሩብ ፣

በሩቅም በቅርብም ያሉ ሰዎች ያደረግሁትን ያውቃሉ የአምሩ ኀይልየ ብሎ ማንሻ ነው ፤ አንድም በሩቅም በቅርብም ያሉ ሰዎች ፣

የአምሩ ኀይልየ ፣

ኀይሌን ያውቃሉ ፤ አንድም ማካፈል ነው ፣ በሩቅ ያሉ ሰዎች ያደረግሁትን ይሰማሉ በቅርቡም ያሉ ሰዎች ኀይሌን ያውቃሉ ፤

፲፬፡ ዐለዉኒ እለ ውስተ ሰማርያ ወዐመፁኒ ፣

በሰማርያ የሚኖሩ አሥሩ ነገድ ወነጀሉኝ በደሉኝ ፤

ወናሁ ይእኅዞሙ ረዓድ ለኃጥአን ወለዐማፅያን ፣

ኃጥአንን ዐመፅያንን ዐሥሩን ነገድ ፍርሀት ረዓድ ይይዛቸዋል ፤

መኑ ይነግረክሙ ከመ እሳት ትነድድ መዓትየ ፣

መዓቴ መቅሠፍቴ እንደ እሳት እንድትነድ ማን ይነግራችኋል?

፲፭፡ ወመኑ ይነግረክሙ ብሔረ ዘለዓለም ዘየሐውር በጽድቅ ፣

በእውነተኛ ሕግ በምግባር በሃይማኖት ፀንቶ የሚኖር ሰው በኢየሩሳሌም በገነት በመንግሥተ ሰማያት እንዲኖር ማን ቢነግራችሁ ታምናላችሁ ፤

ወዘይነብብ ርትዐ ፣

የቀና ነገርን የሚናገር ፤

ወዘይጸልእ ፍኖተ ዓመፃ ፣

የዐመፅን ሥራ የሚጠላ ፤

ወዘይጸልእ ኃጢአተ ወጽልሑተ ፣

ኃጢአትን ክዳትን የሚጠላ ሰው በኢየሩሳሌም ፤ አንድም በገነት በመንግሥተ ሰማያት እንዲኖር ማን ቢነግራችሁ ታምናላችሁ ?

ወዘይመይጥ እዴሁ እምሕልያን ፣

እጅ መንሻ ከመቀበል እጁን የሚመልስ ፤

ወዘይመይጥ እዝኖ ከመ ኢይስማዕ ኵነኔ ነፍስ ፣

ይሙት በቃ የተፈረደበትን እንዳይሰማ ጆሮውን ከመስማት የሚመልስ ፤

ወዘይከድን ዐይኖ ከመ ኢይርአይ ግፉዐ ፣

የተበደለውን እንዳያይ ዐይኑን ከማየት የሚሸፍን በኢየሩሳሌም ፤ አንድም በገነት በመንግሥተ ሰማያት እንዲኖር ማን ቢነግራችሁ ታምናላችሁ ፤

፲፮፤ ዘከመዝኬ ይነብር ውስተ ልዑል በአተ ኰኵሕ ፅኑዕ ፣

እንዲህ ያለ ሰው በፅኑ ዋሻ ፤ አንድም በፅኑ ረድኤት ተጠብቆ ይኖራል ፤

www.ethiopianorthodox.org

ወይትወሀቦ እክልሂ ወማይሂ በጽድቅ ፣

በእውነት የሚበላው እህል የሚጠጣው ውሀ ይሰጠዋል እንደ ኤልያስ፤ አንድም እክለ ትምህርት ማየ ረድኤት ይሰጠዋል፤ አንድም ዘከመ ዝኬ ይነብር ውስተ ልዑል በአተ ኩሉሕ ፤ እንዲህ ያለ ሰው በገነት በመንግሥተ ሰማያት ይኖራል፣ በእውነት ሥጋው ደሙ ይሰጠዋል ፤

፲፮፡ ወትሬእይዎ ለንጉሥ ምስለ ስብሐት ፣

ዘሩባቤልን ዘውድ ደፍቶ ታዩ ታላችሁ ፤ አንድም ጌታን አክሊለ ሦክ ደፍቶ ታዩታላችሁ፣

ወይሬእያ አዕይንቲክሙ· ምድረ ርኁቀ ፣

ዐይኖቻችሁ ከባቢሎን የራቀች ኢየሩሳሌምን ያያሉ ፤ አንድም ከኢየሩሳሌም የራቀች ብሔረ አዛፍን ያያሉ፤ አንድም ከሲኦል ከገሃነም የራቀች መንግሥተ ሰማያትን ያያሉ ፤

፲፯፤ ወትትኄዘብ ነፍስክሙ· ፍርሀተ፣

ሰውነታችሁ ፍርሀትን ትጠራ ጠራለች ማለት አትፈራም ፤

አይቴ ሀለዉ ጸሐፍት ፣

ሹማምንቱ ወዴት አሉ ?

ወአይቴ እሙንቱ· መማክርት ፣

መካሮች ወዴት አሉ አልጠፉም ?

ወአይቴ ሀሎ ብዝኆሙ· ለዐላውያን ንዑሰ ወዐቢዩ ፣

ያሥሩ ነገድ ብዛታቸው ፣ ታናሹም ታላቁም ወዴት አለ አልጠፉም ?

፲፱፡ ወአመጽእ ላዕሌክሙ· አሕዛበ ዘኢተአምሩ ፣

ወደዔዋዌ ተመለሱ የማታው ቋቸው አሕዛብን በናንተ ላይ አመጣለሁ ፤

ወትሰምዑ ነገረ ዕሙቀ ሕዝብ ዐላውያን ፣

ወንጀለኞች ወገኖች የማታው ቁትን ቋንቋ ትሰማላችሁ ውሪ ውሪ ይሉባችኋል ፤

ወዘኒ ይሰምዕ ከሙ ዘአልቦ ልብ ፣

ይህን የሚሰማ ሰው አእምሮ እንደ ሌለው ይሆናል ማለት ዐዋቂው እንደ አላዋቂ ይሆናል፡

ጉባዔ

፳፩፡ ነያ ጽዮን ሀገረ መድኀኒትነ ፣

ድኅነታችን የሚደረግባት ጽዮን እነሆ እንዲህ ያለች ናት ፤

ወትሬእዩ በአዕይንትኪ ኢየሩሳሌም ሀገር ብዕልት ፣

በአዝርዕት በአትክልት የከበርሽ ኢየሩሳሌም የጠላቶችሽን

ጥፋት በዐይኖችሽ ታያለሽ ፤ አንድም ወትሬኢ በአዕይንቲሃ እንደ ማለት የጠላቶቿን ጥፋት በዐይኖቿ የምታይ በአዝርዕት በአትክልት የከበረች የገነነች ኢየሩሳሌምም እንዲህ ናት አለ፣ እንዲህ ያለች ናት ፤

ወአብያቲሃኒ ዘኢያንቀለቅላ ፣

ቤቶቿ የማይነዋወጡ ማለት የማይፈርሱ ፤

ወዘኢይትሀውስ መታክለ ደብተራሃ ለዓለመ ዓለም ፣

የድንኳኗ ካስማ ለዘለዓለም የማይነቃነቅ አለ የማይነቀል፤

ወአሕባሊሃኒ ዘኢይትበተክ ፣

አውታሯ የማይቈረጥ ማለት ባለ ድንኳን የማይጠፋባት ጽዮን እነሆ እንዲህ ያለች ናት ፤

፳፩፡ እስመ እግዚአብሔር ዐቢይ ለክሙ· ፣

እግዚአብሔር ለናንተ ደግ ነውና ፤

ወይከውን ብሔርክሙ· አፍላግ ማይ ወመ·ኃዘ ማይ ርኁብ ወስፉሕ ፣

አገራችሁ የውሀ መፍሰሻ ይሆናል አለ፣ በሚጠት ውሀ ፈልቆላቸዋልና ፤ አንድም አገራችሁ የተድላ የደስታ መገኛ ይሆናልና ፤

ወኢየሐውሩ እንከ ዛተ ፍኖተ ፣

አሕዛብ በዚች ጐዳና አይሄዱም ማለት መገሣገሻ አያደርጓትም፤

ወአሕማርኒ ኢየሐውራ ፣

ነገሥታቱም አይሄዱባትም ማለት መገሣገሻ አያደርጓትም ፤

፳፪፡ እስመ ዐቢይ ውእቱ እግዚአብሔር አምላክነ ፣

ፈጣሪያችን እግዚአብሔር ገናና ነውና ፤

ወኢይትሄየየነ እግዚአብሔር መኰንንነ ፣

ገዢያችን የሚሆን እግዚአብሔር ቸል አይለንምና ፤

ወእግዚአብሔር አምላክነ ፣

እግዚአብሔር ፈጣሪያችን ነውና ፤

ወእግዚአብሔር ንጉሥነ ውእቱ ፣

እግዚአብሔር ንጉሣችን ነውና፤

ወእግዚአብሔር ያድኅነነ ፣

እግዚአብሔር ከመከራ ያድነናልና ፤

፳፫፡ ተበትከ አሕባልኪ ፣

ለኪሶ ለኪሶ አንቺ ግን ባለድንኳን ጠፋብሽ ፤ አንድም ነያ ጽዮን ሀገረ መድኀኒትነ ብለህ መልስ ነያን አስጠብቅ ድኅነታችን የሚደረግብሽ ጽዮን የጠላቶችሽን ጥፋት በዓይኖችሽ የምታዪ በአዝርዕት በአትክልት የከበርሽ የገነንሽ ኢየሩሳሌም ፤

www.ethiopianorthodox.org

ወአብያቲሃኒ ዘኢያንቀለቅላ ፤

ቤቶችሽ የማይነዋወጡ ማለት የማይፈርሱ ፤

ወዘኢይትሐወስ መታክለ ደብተራሃ ለዓለመ ዓለም ፣

የድንኳንሽ ካስማ ለዘለዓለም የማይነቃነቅ አለ፣ ባለ አልጋ ባለ ድንኳን ጠፋባት የምትባይ ጽዮን ፤

ወአሕባሊሃኒ ዘኢይትበትክ ፣

አውታሯ የማይቈረጥ ማለት ባለድንኳን የማይጠፋብሽ ጽዮን እግዚአብሔር ለናንተ ደግ ነውና አገራችሁ የተድላ የደስታ መገኛ ይሆናልና አሕዛብ በዚች ጐዳና አይሄዱም ማለት መገሣገሻ አያደርጓትም፣ ነገሥታቱም አይሄዱባትም ማለት መገሣገሻ አያደርጓትም ፤

እስመ ዐቢይ ውእቱ እግዚአብሔር አምላክነ ፣

ፈጣሪያችን እግዚአብሔር ገናና ነውና ገዢአችን የሚሆን እግዚአብሔር ቸል አይለንምና እግዚአብሔር ፈጣሪያችን ነውና እግዚአብሔር ንጉሣችን ነውና እግዚአብሔር ከመከራ ያድነናልና ፤

ተበትከ አሕባልኪ ፣

እንዲህ እንዲህ የምትሆኚ ጽዮን ነያ ተበትከ እነሆ ዛሬ ግን ባለ ድንኳን ጠፋብሽ ፤

እስመ ኢረትዐ ፣

አልቀናምና ፤ አንድም አለቃሽ ንጉሥሽ ልቡናሽ አልቀናምና ፤

ዐምድኪ ፀነ ፣

ምሰሶሽ አዘነበለ ማለት አለቃሽ ንጉሥሽ ልቡናሽ ወደ ኃጢአት ተመለሰ ፤

ወኢበጽሐ ሠርዌኪ ፣

ተራዳሽ ከገበታው አልደረሰም ማለት አለቃሽ ንጉሥሽ ልቡናሽ ከእግዚአብሔር አልደረሰም ፤

ወኢያነሥእ ትእምርተ እስከ ይእኅዝዎ ወይማኅርክዎ ፣

ሰናክሬም ብልጣሶር እስኪይዙት እስኪማርኩት ድረስ ዓላማውን በተራራ ላይ አይተክልም ስንፍናውን መናገር ነው ፤

ወእፎ እንከ ይማኅርኩ ብዙኃን ሐንካሳን ፣

ሰናክሬም በጠፋ ጊዜ ብዙ አንካሳዎች እንዴት ይማርኩ ይሆን ፤

፳፬፤ ወኢይብል ደከምኩ ሕዝብ ዘይነብር ውስቴቶሙ ፣

በዚያ የሚኖር ወገን የሰናክሬምን ገንዘብ ከመሰብሰብ ደከምሁ አይልም ፤

እስመ ይትኀደግ ሎሙ ኃጢአቶሙ ፣

ኃጢአታቸው ይሠረይላቸዋልና ጥንቱን ድካም የሚሆንባቸው ኃጢአታቸው ነውና ::

ምዕራፍ ፴፬

፩፤ ተጋብኡ ሕዝብ ፣

የኤዶምያስ ሰዎች ወደምትጠፉበት ቦታ ተሰብሰቡ ፤

ወስምዑ መላእክት ፣

የኤዶምያስ አለቆች ስሙ ፤

ወትስማዕ ምድርኒ ፣

ኤዶምያስም ትስማ ፤

ወእለሂ ይነብሩ ውስቴታ ፣

በሷ የሚኖሩ ሰዎችም ይስሙ ፤

ወዐለዉኒ አሕዛብ እለ ይነብሩ ውስቴታ ፣

በሷ የሚኖሩ አሕዛብ ወነጀሉኝ፣ ከዱኝ ፤

፪፤ እስመ መዓተ እግዚአብሔር ዲበ ኵሉ አሕዛብ ፣

የእግዚአብሔር መዓቱ በአሕዛብ ላይ ይመጣልና ፤

ወመቅሠፍቱኒ ዲበ ኍልቆሙ ከመ ያጥፍኦሙ በኵናት ፣

በጦር ያጠፋቸው ዘንድ መቅሠፍቱም በሠራዊቱ ይመጣልና፣ አንድም የእግዚአብሔር መቅሠፍት በኤዶምያስ ሰዎች በቍጥራቸው ላይ ነው አንድ ሳይቀር ያጠፋቸዋል ፤

፫፤ ወይትገደፍ አብድንቲሆሙ ለቅቱላን ፤

በጦር ተወግተው የሞቱ ሰዎች ሬሳቸው ይወድቃል ማለት አይቀበርም ፤

ወይዜኑ ዜዓቶሙ ፣

ሽታቸው ከሩቅ ይሸታል ማለት ዜና ጥፋታቸው ከሩቅ ይሰማል ፤

ወይርሕሱ አድባር እምደሞሙ ፣

ከደማቸው የተነሣ ተራሮች ይርሳሉ ማለት የጥፋታቸውን ብዛት መናገር ነው ፤

፬፤ ወትጠወም ሰማይ ከመ ክርታስ፣

ኤዶምያስ እንደ ወረቀት ትጠቀለላለች ማለት ትጠፋለች ሰማይ አላት ስለልዕልናዋ ፤

ወይወድቁ ኵሉ ከዋክብት ከመ ቈጽለ በለስ ፣

ሠራዊቱ እንደ ቅጠል ይረግፋሉ ፤

፭፤ ሰክረት መጥባሕትየ እምደሞሙ ለኤዶምያስ ፣

ከኤዶምያስ ሰዎች ደም የተነሣ ሥልጣኔ ሰከረች፣ አንድም የሰናክሬም የስልምናሶር ሾተል በተፈጥሮ ገንዘቡ ናትና ፤

ወትወርድ ዲበ ሕዝብ ኅጉላን ምስለ ኵነኔ ፣

አእምሮ ባጡ ወገኖች ከመቻያ ጋራ ትመጣለች ፣

፮፤ መጥባሕተ እግዚአብሔር ጸግበት ደመ ፣

የእግዚአብሔር ሥልጣኑ ደምን ጠገበች ፤

www.ethiopianorthodox.org

ወስብሐ እምስብሐ አባግዕ ወእም ስብሐ አጣሊ ወሐራጊት ፣

ሴቶችንም ወንዶችንም አጥፍታ ተገለጠች ፤

እስመ መሥዋዕተ እግዚአብሔር በባሦር ፣

በኤዶምያስ መዓት መቅሠፍት አለና መሥዋዕት ደስ እንዲያ ሰኝ መቅሠፍቱም በሚገባ ሲሆን ደስ ያሰኛልና ፤

ወዐቢይ ጥብሕ በኤዶምያስ ፣

በኤዶምያስ ታላቅ ገች አለ ማለት ለጥፋት የቀረበ ንጉሥ አለ፤ አንድም መዓተ እግዚአብ ሔር አለ የኢሳይያስ እኩሌታ ይህ ነው፣ ለመጻሕፍት እኩሌታ እኩሌታ አላቸው የዳዊት መር ሆሙ መዝ.፸፯ የጳውሎስ ኦዐብ ዳን ስብአ ገላትያ ም.፫ ቁ.፩፡

የሐዋርያ እንተ አልባቲ ዘይገሀግሃ ፪ጴጥ. ም.፪ ቁ.፲፬፡ የቀለምሲስ ወተዔ. ወወኒ ሕሊናየ ም.፲፫ ቁ.፲፣

የሃይማኖት አበው ለኀበ ነገሥት ኄራን ፤

፯፡ ወይወድቁ ተባዕያን ምስሌሆሙ፣

ዐርበኞች ከነገሥታቱ ጋራ ይጠ ፋሉ ፤

ወሐራጊትኒ ወአሥዋር ፣

ወንዶችም ሴቶችም ይጠፋሉ፤

ወትሰክር ምድር እምደሞሙ ወት ጠልል እምስብሐሙ ፣

ምድር ከደማቸው የተነሣ ትሰ ክራለች ከስባቸው የተነሣ ትለ መልማለች ማለት የጥፋታቸውን ብዛት መናገር ነው ፤

፰፡ እስመ ዕለተ ኵነኔሁ ለእግዚአ ብሔር ፣

እግዚአብሔር የሚፈርድበት ቀን ነውና ፤

ወአመ ዕለተ ፍዳ ኵነኔሃ ለጽዮን፣

ጽዮን ተፈርዶባት ከኤዶምያስ ጋራ ፍዳዋን የምትቀበልበት በደ ረሰ ጊዜ፤ አንድም ተፈርዶላት ብድራቷን የምትከፈልበት በደ ረሰ ጊዜ አቶ አደራህን ግን ጠን ቅቀው ቈጥረው የኢሳይያስ እኩ ሌታ ወአመ ዕለተ ፍዳ ኵነኔሃ ለጽዮን ነው ብለዋል፤ ባሦር ከተ ማው ፣ ኤዶምያስ መላው ነው ፤

ወይትመየጡ ቈላቲሃ ወይከውኑ ፒሳ ፣

ቈላው ሁሉ ወደ ጥፋት ይመ ለሳል በረሀ ይሆናል ፤

ወይከውን ተየ ፣

በረሀ ይሆናል ፤

፱፡ ወይነድድ ምድራ መዓልተ ወሌ ሊተ ከመ ፒሳ ፣

ምድሯ በመዓልትም በሌሊትም ይነዳል ማለት በረሀ ይሆናል ፤

ወኢይጠፍእ ለዓለም ፣

ለዘለዓለም አይጠፋም ፤

ወየዐርግ ጢሱ ላዕለ ፣

ዜና ጥፋቷ ይሰማል ፤

ወትማስን ለትውልደ ትውልድ ፣

ለልጅ ልጅ ዘመን ትጠፋለች፤

ወለነዋኅ መዋዕል ትጠፍእ ፣

ለብዙ ዘመን ትጠፋለች ፤

፲፡ ወዮኅድሩ ውስቴታ አዕዋፍ ፣

አዕዋፍ ጉጉት ይኖሩባታል ፤

ወቈዓት ፣

ቁራዎች ይኖሩባታል ፤

ወሆባያት ፣

አንጭት ጭላት ይኖሩባታል፤

ወቅንፉዝ ፣

ጃርት ይኖርባታል ፤

ወይሜጥኑ በሐብል መሠረታ ፣

ባለ ርስት በገመድ ተካፍሎ እን ዲኖር እነሱም ተካፍለው ይኖሩ ባታል ፤

ወዮኅድሩ ውስቴታ አጋንንት ፣

እለ ትግሪዳ ይኖሩባታል፣ ዛሬ ይታረድበት ይጠጅበት የነበረ ቦታ በተፈታ ጊዜ ደባስ የሚባል ጋኔን እንዲያድርበት ፤

ወጼዴናታት ፣

እለ ሔለይ ይኖሩባታል ፤

፲፩፡ ወዮኅልቁ ነገሥታ ፣

ነገሥታቷ ሁሉ ይጠፋሉ ፤

ወይትኀጐሉ መላእክቲሃ ወመሳፍን ቲሃ ፣

አለቆቿ መሳፍንቷ ይጠፋሉ፤

፲፪፡ ወይበቍል ዕፅ ወሦክ በውስተ አህጉሪሆሙ ፣

በሀገራቸው እሾህ እንጨት ይበ ቅልበታል ፤

ወውስተ አዕዋኒሆሙ ፣

በአምባቸው ይበቅልበታል ፤

ወትከውን ሀገረ አጋንንት ፣

የነትግሪዳ አገር ትሆናለች ፤

ወዐፀደ ሰገኖ ፣

የሰጐን ቦታ ትሆናለች ፤

፲፫፡ ወይትራከቡ በህየ አጋንንት ፣

አጋንንት ይገናኙባታል ፤

ወጼዴናታት ይጸርሑ ወይኬልሑ በህየ ኵሎሙ ፣

እለ ሔለይ አንድ ሁነው ይጮ ሃሉ ፤

ወዮኅድሩ በህየ እለ ሰኰና ላህም እገሪሆሙ ፣

እለ ጐሽ እለ አጋዘን ይኖሩባታል፤

ወይረክቡ ሎሙ ምዕራፈ በህየ ፣

በኤዶምያስ ማረፊያ መሳፈሪያ ያገኛሉ ፤

ወይትዋለዱ ፣

ይበዛሉ ፤

www.ethiopianorthodox.org

፲፬፡ ወኢታድኅን ምድር ደቂቃ በኃይል ፤

ኤዶምያስ ልጆቿን በኃይል ማዳን አይቻላትም ፤

ወይትራከቡ በህየ ኀየላት ፤

ዋልያዎች ይገናኙባታል ፤

ወይትረአዩ ገጸ በገጽ በበይናቲሆሙ፣

እርስ በርሳቸው ፊት ለፊት ይተያያሉ ፤

፲፭፡ ወዮኀልፉ በበኑኍልቆሙ ፤

በፋሶጥር ይኖራሉ የተቈጠረ እንዳይጠፉ አይጠፉም ፤

ወኢይትኀጐል ፩ዱ እምኔሆሙ ፤

ከነዚያ አንዱ አይጠፉም ፤

ወኢይትነሠኡ በበይናቲሆሙ ፤

እርስ በርሳቸው በጠብ አይፈላለጉም፣ ለልማዱ አራዊት ሲበዙ ይጣላሉ አሁን ግን አይጣሉም፤

እስመ እግዚአብሔር ፀባኦት አዘዘመ፣

አሸናፊ እግዚአብሔር አዝዟቸዋልና ፤

ወመንፈሰ ዚአሁ አስተጋብኦሙ ፤

ሥልጣኑ ሰብስቧቸዋልና ፤

፲፮፡ ወውእቱ ወህቦሙ መክፈልቶሙ፣

ኤዶምያስን እድል ፈንታ አድርጎ ሰጥቷቸዋልና ፤

ወእዴሁ አስተዋረሰቶሙ ፤

ሥልጣኑ ኤዶምያስን አውርሳቸዋለችና ፤

ወይትረዐዩ ለዓለም ፤

ለዘለዓለሙ በኤዶምያስ ይኖራሉ ፤

ወይትዋረሱ ለትውልደ ትውልድ፣

ለልጅ ልጅ ዘመን ይወርሷታል፣ አንድም ወይትራከቡ በህየ ኀየላት፣ በኤፈሶን ለአውግዞተ ንስጥሮስ የተሰበሰቡ ሁለቱ መቶ ሊቃውንት ይገናኙባታል፣ ኀየላት አላቸው ፤ ይህ ዋልያ እንደ በረሀ ፍየል እባብ ሰንጥቆ ይበላል፤ እነዚህም አዲስ ከይሲ ንስጥሮስን አውግዘው ለይተዋልና፤ ወይት ረዐዩ ገጸ በገጽ በበይናቲሆሙ፣ ሊቃውንቱ እርስ በርሳቸው ልብ ለልብ ይተዋወቃሉ፤

ወዮኀልፉ በበኑኍልቆሙ ፤

በፋሶጥር ይኖራሉ የተቈጠረ እንዳይጠፉ አይጠፉም ፤

ወኢይትኀጐል አሐዱ እምኔሆሙ፣

ከሊቃውንቱ አንዱ በክህደት አይገኝም ፤

ወኢይትነሠኡ በበይናቲሆሙ ፤

እርስ በርሳቸው አይከራከሩም መከራከርማ ሊቃውንት እኩሌቶች እንደ ቅዱስ ቄርሎስ፣ እኩሌቶች እንደ ንስጥሮስ እየሆኑ ይከራከሩ የለም ? በሥጋዊ ነገር አይጣሉም ሲል ነው ፤

እስመ እግዚአብሔር ፀባኦት አዘዘመ፣

አሸናፊ እግዚአብሔር አዝዟቸዋልና ፤

ወመንፈሰ ዚአሁ አስተጋብኦሙ ፤

መንፈስ ቅዱስ ሰብስቧቸዋልና፤

ወውእቱ ወህቦሙ መክፈልቶሙ ፤

ሃይማኖትን እድል ፈንታ አድርጎ ሰጥቷቸዋልና ፤

ወእዴሁ አስተዋረሰቶሙ ፤

ሥልጣኑ ሃይማኖትን አዕንታ ላቸዋለችና ወይትራከቡ ብለህ እሠር ፤

ወይትረዐዩ ለዓለም ፤

ለዘለዓለሙ በሃይማኖት ፀንተው ይኖራሉ ፤

ወይትዋረሱ ለትውልደ ትውልድ፣

ምዕመናን ለልጅ ልጅ ዘመን ሃይማኖትን ገንዘብ ያደርጋሉ፤

ወየዐርፉ ውስቴታ ፤

በሃይማኖት ፀንተው ይኖራሉ።

ምዕራፍ ፴፭

፩፡ ይትፌሣሕ በድው ዕሙዕ ፤

ሰባ ዘመን የተጠማ ምድረ በዳ በሰባ ዘመን ዝናም ዘንሞ ደስ ይለዋል ፤

ወይትነሠይ ገዳም ፤

ምድረ በዳው ደስ ይለዋል ማለት ሰባ ዘመን ምድረ በዳ የነበረች ኢየሩሳሌም ዝናም ለዘር ጠል ለመከር አግኝታ ደስ ይላታል፤

ወይፈሪ ከመ ጽጌ ፤

እኩሌታው አበባ እንደ እኩሌታው አበባ ይሆናል ፤

፪፡ ወይትነሠይ ሐቅል ዘዮርዳኖስ፣

የዮርዳኖስ አውራጃ ደስ ይለዋል፤ አንድም ይትፌሣሕ በድው ዕሙዕ፣ ሰባ ዘመን ከትምህርት ከረድኤት የተጠማ ትሩፍ ትምህርቱን ረድኤቱን አግኝቶ ደስ ይለዋል ፤

ወይትነሠይ ገዳም ፤

አንድ ወገን ነው ትሩፍ ደስ ይለዋል ፤

ወይፈሪ ከመ ጽጌ ፤

ጥቂት ገንዘብ ያልነበረው ጥቂት ገንዘብ ያለው ይሆናል ፤

ወይትነሠይ ሐቅል ዘዮርዳኖስ ፤

በዮርዳኖስ አውራጃ የሚኖሩ ትሩፋን ደስ ይላቸዋል ፤

ወክብረ ሊባኖስ ተውህበ ላቲ ፤

ለቤተ እስራኤል ብዕለ አሕዛብ ተሰጣት ፤

ወክብረ ቀርሜሉስ ፤

የንጉሡ ገንዘብ ተሰጣት ፤

አንድም ይትፌሣሕ በድው ዕሙዕ ወይትነሠይ ገዳም ፤

አምስት ሺህ ካምስት መቶ ዘመን ከልጅነት ከክብር የተጠማ ምዕ

www.ethiopianorthodox.org

መን ባምስት ሺህ ካምስት መቶ ዘመን ልጅነትን ክብርን አግኝቶ ደስ ይለዋል ፤

ወይትጎሠይ ገዳም ፣

አሕዛብ ልጅነትን አግኝተው ደስ ይላቸዋል ፤

ወይፈሪ ከመ ጽጌ ፣

እንደ አዳምና እንደ ሔዋን ልጅ ነትን ያገኛሉ ፤

ወክብረ ሊባኖስ ተውህበ ላቲ ወክብረ ቀርሜሎስ ፣

ለምዕመን ሕገ አሕዛብ ወንጌል ተሰጣት ፤

ወይሬእዩ አሕዛብ ስብሐትየ ፣

ወገኖቼ ሚጠትን ያያሉ፣ አንድም ምዕመናን ባምስት ሺህ ካምስት መቶ ዘመን ልጅነትን ያገኛሉ፤

፫፤ ወያሌዕልዎ ለእግዚአብሔር ዕደው ዕውሳት ፣

በመከራ የደከሙ ሰዎች እግዚ አብሔርን ያከብሩታል ፤

፬፤ ወአእጋር ሐንካሳን ናዝዝዎን ለአ ልባቢክሙ ፣

ሐንካሳነ ልቡና ልቡናችሁን አረ ጋጉት ፤

ዕንቢዛን ዕንዑ ወኢትፍርሁ ፣

አእምሮአችሁን ያጣችሁ በሃይ ማኖት ዕኑ አትፍሩ ፤

ናሁ አምላክነ ያገብእ ፍትሐ ወይ ትቤቀል ፣

እነሆ ፈጣሪያችን ይፈርድል ናል ተበቅሎ ጠላታችንን ያጠ ፋልናል ፤

ለሊሁ ይመጽእ ወያድኅነነ ፣

በሰባ ዘመን እሱ በረድኤት መጥቶ ከመከራ ያድነናል፤ አን ድም ፤ ናሁ አምላክነ ያገብእ ፍትሐ ወይትቤቀል፣ እነሆ ፈጣ ሪያችን እግዚአብሔር ባምስት ሺህ ካምስት መቶ ዘመን ተበ ቅሎ አጋንንትን ያጠፋልናል፤

ለሊሁ ይመጽእ ወያድኅነነ ፣

ባምስት ሺህ ካምስት መቶ ዘመን ሰው ሁኖ ሥጋ ለብሶ ይመጣል፤ ከፍዳ ነፍስም ያድናል ፤

፭፤ ወውእተ አሚረ ይትከሠታ አዕ ይንተ ዕውራን ፣

ያንጊዜ ዕውራነ ልቡና እስራኤል ምሥጢር ያያሉ፤ አንድም ባም ስት ሺህ ካምስት መቶ ዘመን ዕውራን ሥጋ በተአምራት ዕው ራነ ነፍስ በትምህርት ይድናሉ፤

ወይሰምዑ ዕሙማን ፣

ሰባ ዘመን ዕሙማን የነበሩ እስ ራኤል ትምህርት ይሰማሉ፣ አን ድም አምስት ሺህ አምስት መቶ ዘመን ዕሙማነ ሥጋ በተአምራት

ዕሙማነ ነፍስ በትምህርት ይድ ናሉ ፤

፮፤ ውእተ አሚረ ይረውፁ ከመ ጎየል ሐንካሳን ፣

ሰባ ዘመን ሐንካሳን የነበሩ እስራኤል እንደ ዋልያ ፈጥነው ይወጣሉ፤ አንድም አምስት ሺህ ካምስት መቶ ዘመን ሐንካሳን የነበሩ ሐንካሳነ ሥጋ በተአም ራት እንደ ዋልያ ይሮጣሉ (ሐን ካሳነ ነፍስ አይልም ጠንቀቅ)፤

ወይረትዕ ልሳነ በሐማን ፣

ሰባ ዘመን ዲዳ የነበሩ ሰዎች አንደበት በትምርት ይቀናል ፤ አንድም በሐማነ ሥጋ በተአም ራት በሐማነ ነፍስ በትምህርት ይቀናሉ ፤

እስመ ነቅዐ ማይ በውስተ በድው፣

ሰባ ዘመን ምድረ በዳ በነበረች በኢየሩሳሌም ምንጭ መንፈሰ ልና ፤

ወውኅዘ በውስተ ብሔር ዕሙዕ ፣

ሰባ ዘመን በተጠማ አገር ፈሳ ልና ፤

፯፤ ወይበቍል ያም ውስተ በድው፣

በምድረ በዳ ዛፍ ይበቅላል ፤

ወይፈለፍል ውስተ ምድር ዕምዕት፣

ሰባ ዘመን በተጠማች በኢየሩ ሳሌም መንፈስ ቅዱስ

ሀየ መካኖሙ ለአዕዋፍ ፣

የአዕዋፍ ቦታ በነበረች ፤

ብሔረ ሕለት ወሣዕር ፣

የሣር፣ የቀርቀሀ፣ የሸንበቆ አገር በምትሆን በኢየሩሳሌም ምንጭ ይመነጫል ፤ አንድም አምስት ሺህ ካምስት መቶ ዘመን ከትም ህርት ከልጅነት ምድረ በዳ በነ በሩ በምዕመናን ትምህርት ልጅ ነት ይነገራል ፤

ወይበቍል ያም ውስተ በድው ወይፈ ለፍል ውስተ ምድር ዕምዕት ፣

ዘሩባቤል በኢየሩሳሌም ይነግ ሣል፣ አንድም ጳጳስ ሊቀ ጳጳስ ይነሣል ከትምህርት በተጠማች አገር ያስተምራል ፤

ሀየ መካኖሙ ለአዕዋፍ፡ ብሔረ ሕለት ወሣዕር ፣

የአጋንንት ማደሪያ የነበረ አእ ምሮ መንፈሳዊ ተሥሎበት በነ በረ ሰው ሁሉ ትምህርት ልጅነት ይሰጣል ፤

፰፤ ወትሰመይ ፍኖታ ንጽሕተ ወቅ ድስተ ፣

ጐዳናዋ ንጽሕት ክብርት ትባ ላለች ፤

ወኢየኅልፍ እንከ ሀየ ርኩስ ፣

እንግዲህ ቄሳፍ አረማዊ ወደ ዚያ አይሄድም አንድም በቤተ እስራኤል መካከል አይኖርም፤

www.ethiopianorthodox.org

ወእለሂ ተዘርዉ የሐውሩ ውስቴታ ፣

በፋርስ በባቢሎን በዕርዕ በሜዶን የተበተኑ እስራኤል ይኖሩ ባታል ፤ አንድም ወትሰመይ ፍኖታ ንጽሕተ ወቅድስተ፣ የም ዕመን ሥራዋ የቀና ይሆናል፤ ርኩስ ሰይጣን በምዕመናን መካ ከል አያድርም ፤ በአዳም ጊዜ የተበተኑ ሰባቱ ሀብታት ይኖሩ ባታል እንጂ ፤

ወኢይስሕቱ ፣

በኃጢአት በጣዖት አይስቱም፤

፱፡ ወአልቦ ህየ አንበሳ ወአርዌ እኩይ፣

አንበሳ ናቡከደነፆር ወአርዌ እኩይ ስልምናሶር በዚያ የለም አለ አይመጣም፣ አንድም አን በሳ ግዙፉ ወአርዌ እኩይ ረቂቁ የለም ፤

ወኢየዐርግ እንከ ውስቴታ ፣

እንግዲህ ወዲህ አሕዛብ ወደ ኢየሩሳሌም አይወጣም ፤

ወኢይትረከብ በህየ ፣

በኢየሩሳሌም አይገኝም ፤ አን ድም በገነት በመንግሥተ ሰማይ አይገኝም ፤

ዳዕሙ እለ አምሰጡ የሐውሩ ባቲ፣

ከመከራ የዳኑ እስራኤል ይኖሩ ባታል እንጂ፤ አንድም በአዳም ጊዜ የተበተኑ ሀብታት ይሰጣ ታል እንጂ ፤

፲፡ ወእለ ተጋብዑ በእግዚአብሔር ይመጽኡ ባቲ ፣

በእግዚአብሔር አምነው የተሰ በሰቡ እስራኤል ይኖሩባታል ፤

ወየዐትዉ ውስተ ጽዮን በትፍሥሕት ወበ ነሢት ዘለዓለም ፣

ለዘለዓለም በፍጹም ደስታ ደስ እያላቸው ከባቢሎን ወደ ኢየሩ ሳሌም ይመለሳሉ ፤

እንዘ ውስተ ርእሶሙ ሀሎ አክሊለ ክብር ፣

ዘሩባቤል ዘውድ ደፍቶላቸው፤

ፍሥሓ ወነሢተ ወሕይወተ ይረክቡ፣

ተድላውን ደስታውን ሕይወቱን ያገኛሉ ፤

እስመ ጠፍአ ሕማም ወትካዝ ወነዘን፣

የሰባው ዘመን መከራ ኀዘን ትካዝ ጠፍቷልና፤ አንድም፤ ወየዐትዉ ውስተ ጽዮን በትፍሥሕት ወበ ነሢት ዘለዓለም ፣ ምዕመናን ለዘለዓለም በፍጹም ደስታ ደስ እያላቸው ወደገነት ወደመንግ ሥተ ሰማያት ይመለሳሉ ፤

እንዘ ውስተ ርእሶሙ ሀሎ አክሊለ ክብር ፣

ጌታ አክሊለ ሦክ ደፍቶላቸው ኀዘንተ ሥጋ ኀዘንተ ነፍስን ሕይ ወት ሥጋ ሕይወተ ነፍስን ያገኛሉ ያምስቱ ሺህ ካምስት መቶ ዘመን መከራ ኀዘን ትካዝ ጠፍቷልና ::

ምዕራፍ ፴፮

ጉባዔ

፩፡ ወአመ ዐሠርቱ ወአርባዕቱ ዓመተ መንግሥቱ ለሕዝቅያስ ዐርገ ሰናክሬም ንጉሠ ፋርስ ላዕለ አህጉረ ይሁዳ አለ ቦን ጥቅም ፣

ሕዝቅያስ በነገሠ በዐሥራ አራ ተኛው ዘመን የፋርስ ንጉሥ ሰናክሬም ቅጽር ወዳላቸው ወደ አህጉረ ይሁዳ ዘመተ፤ ዐሥራ አራት ያለው እንደምነው ቢሉ ሕዝቅያስ በነገሠ በስድስት ዘመን ዐሥሩ ነገድ ተማርከዋል፤ ዐሥሩ ነገድ በተማረኩ በስምንተኛው ዘመን ሰናክሬም ወደ ይሁዳ ዘም ቷል፤ ዐሥራ አራት ያለው ይህ ነው፤ ስለምን ቢሉ ጌታ በሁለቱ ነገድ ቢያዝንባቸው መልአኩ ቅዱስ ሚካኤል በነጭ በግ አም ሳል እየመራ ይዞት መጥቷል ፤ አንድም ሆሴዕ ወልደ ኤላ ያሥሩ ነገድ ንጉሥ ነው፤ ስመ ግብርናት ሲያወጡለት ራፋስቂስ ብለው ታል፤ ነዊነ ቅልጥም ሊቀ ቀዳህ ያን ሲሉ እሱ ባለጌ ራሱ ለከፈለ አያዝንም ባልንጀራው ለቀረ ነው እንጂ እንዲሉ፣ አባትህ ዐሥሩን ነገድ ማርኮ ንጉሠ ነገሥት ተባለ አንተስ እነዚህን ሁለቱን ነገድ ማርከህ ንጉሠ ነገሥት አትባልም? ብሎ ይዞት መጥቷል፤ አንድም እሱ ከልቡ አንቅቶ አባቴ ዐሥ ሩን ነገድ ማርኮ ንጉሠ ነገሥት ተባለ እኔስ እኒህን ሁለቱን ነገድ ማርኬ ንጉሠ ነገሥት አልባልም? ብሎ መጥቷል ፤

ነሥአን ወአስተጋብያን ፣

በሕሊና ገንዘብ አደረጋቸው፣ አንድም በለኪሶ ያሉትን እን ጨት ሰባሪዎችን ውሀ ቀጂዎችን ማረከ ፤

፪፡ ወፈነዎ ንጉሠ ፋርስ ለራፋስቂስ እምለኪሶ ውስተ ኢየሩሳሌም ኀበ ሕዝቅያስ ንጉሥ ምስለ ብዙኅ ሠራ ዊት ፣

የፋርስ ንጉሥ ሰናክሬም ራፋ ስቂስን ከብዙ ሠራዊት ጋራ ከሕ ዝቅያስ ዘንድ ወደ ኢየሩሳሌም ላከው ፤

ወቆመ ኀበ መ·ነዘ ማይ ዘምጥማቃት ላዕላይ ዘውስተ ገራህተ መሐጥል ፣

ታሕታይ አለና ላዕላይ አለ ፤ ለሽማ አጣቢ እሪም አድርገው በሰጡት እርሻ አጠገብ ባለው ጉዳና ሂዶ ከላይኛው መዋኛ ከላ ይኛው መታጠቢያ ተቀመጠ ፤ አንድም ሕንድኪ በሚያገቡበት በፍታ በሚያፋጥቁበት እርሻ አጠገብ ባለው ጉዳና ሂዶ ከላይ ኛው መዋኛ ከላይኛው መታጠ ቢያ ተቀመጠ፤ አንድም በዘያስ ጥሑ ቦቱ አልባሰም ይላል ፤

፫፡ ወወጽኡ ኀቤሁ ኤልያቄም ወልደ ኬልቅዩስ መጋቢ ፣

የኬልቅዩስ ልጅ ኤልያቄም መጋቢ ራቅ ሣሠሪያ ፤

www.ethiopianorthodox.org

ወሳምናስ ጸሐፊ ፤

ጸሐፌ ትእዛዝ ሳምናስ ፤

ወኢዮአቄም ወልደ አሳፍ ጸሐፌ ተዝ
ካር ፤

፩ብሬት ጠባቂ የአሳፍ ልጅ ኢዮ
አቄም ወጡ ፤

፪፤ ወይቤሎሙ ራፋስቂስ በልዎ ለሕ
ዝቅያስ ከመዝ ይቤ ንጉሠ ሩርስ ፤

ራፋስቂስ ሕዝቅያስን የሩርስ
ንጉሥ ሰናክሬም እንዲህ አለ
በሉት አላቸው ፤

በመኑ ትትዌከል ፤

በማን ትታመናለህ ፤

፭፤ በምክርኑ ፤

ምክር በማውጣት በማውረድ
ነው ፤

ወበነገረ ከናፍርኑ ይከውን ቀትል፣

ከንፈርስ በማንቀሳቀስ ሰልፍ ይደ
ረግ ይመስልሃል ?

ይእዜኒ በመኑ ተወኪለከ ዐለውከኒ፣

አሁንስ እኔን የወነጀልኸኝ በማን
ታምነህ ነው ?

፮፤ ናሁ ተወከልከ በበትረ ብርዕ ቅጥ
ቁጥ ፤

እነሆ በተቀጠቀጠ መቃ መሰዬ
ብትር ታመንህ ፤

እንተ በግብፅ ፤

ዘውእቱ ንጉሠ ግብፅ ሲል ነው
ይኸውም የግብፅ ንጉሥ ፈርዖን
ነው ፤

ብእሲ ዘአስመከ ላዕሌሁ ይበውእ
ስርዋጽ ውስተ እዴሁ ፤

ለዘአስመከ ሲል ነው ለተጠጋ
በት ሰው ስንባጭ (ስንጥር) ወደ
እጁ የሚገባ በሆነ በተቀጠቀጠ
መቃ መስዬ ብትር ታመንህ፤

ከማሁ ውእቱ ፈርዖን ንጉሠ ግብፅ
ለኵሉሙ እለ ይትዌከሉ ቦቱ ፤

የግብፅ ንጉሥ ፈርዖንም ለሚታ
መኑበት ሰዎች ሁሉ እንደዚህ
ነው ፤ እንደ መሰበሩ ድል መነ
ሣት ስንባጭ በጁ እንደ መግ
ባት፤ አንድም ስንባጩ እጅን
እንዲያቈስል አንተንም ይዞህ
ይጠፋል አለው ፤

፯፤ ወእመሰ ትብል በእግዚአብሔር
አምላክነ ተወከልነ ፤

በፈጣሪያችን በእግዚአብሔር
አመነ ትል እንደሆነ ፤

አኮኑ አንተ ዘሰበርከ መባእ ቤተ
እግዚአብሔር ወፈነውከ ለእግዚእየ
ንጉሠ ሩርስ ፤

የቤተ እግዚአብሔሩን ጌጥ ወር
ቁን ብሩን ሰብረህ ለጌታዬ ለሰ
ናክሬም የሰደድኸው አይደለም?
አለው በምን ዐውቆ እንዲህ አለ
ቢሉ የቤት ሰው ነውና፤ አንድም
ከዚያው ዘሮቤል ዘጋድ የሚል
አለበትና ሰናክሬም ሕዝቅያስን
ግብሬን ስጠኝና ልመለስልህ
አለው፤ እሱም ቤተ መቅደስ በወ
ርቅ በዕንቁኦ ተሠርታ ነበረችና

እስራኤል ከሚጠፉ ቤተ መቅደስ
ትፍረስ ብሎ ወርቁን እያስላጠ
ብትኑን፤ አንድም ወንበርም እያ
ሠራ ቢሰድለት ይህስ ያለፈው
ግብሬ ነው፤ የሚመጣውን ግብ
ሬን ስደድልኝ ብሎታልና ፤

፰፤ ወይእዜኒ እመ ትክል እሁበከ
እስራ ምእተ አፍራሰ ፤

አሁንም ትችል እንደሆነ ሁለት
ሺህ ፈረስ ልስጥህ ፤

አምጽአ ዘይክል ተዕዕኖቶሙ ፤

በነዚህ ተቀምጠ የሚዋጋኝ ሰው
ስጠኝ አለው ፤

፱፤ ወእፎ ትክሉ መዲጠ ገጸ አሐዱ
ንዑስ እምአግብርተ እግዚእየ ንዑሳን፣

ንዑሳን ከሚሆኑ ከጌታዬ ባሮች
ያንዱን ፊት መመለስ እንደምን
ይቻላችኋል፤ አንድም ያንዱን
ቤት ጭፍራ ፊት መመለስ እንደ
ምን ይቻላችኋል ፤

ወኵሉሙ እለ ይትዌከሉ በግብፅ
በእንተ አፍራስ ወሠረገላት አግብ
ርት እሙንቱ ለእግዚእየ ፤

ፈረሳቸው ሠረጋላቸው በዛ
ብለው በግብፃውያን የሚታመኑ
ሁሉ የጌታዬ ተገዢዎች ናቸው፤

፲፤ ወይእዜኒ ዘእንበለ እግዚአብሔ
ርኑ ዐረግነ ውስተ ዝ ብሔርክሙ፣

እግዚአብሔር ያድነናል የምትሉ
አሁንስ ያለ እግዚአብሔር ፈቃድ
የዘመትነ ይመስልሃል በውነቱ
መልአኩ ቅዱስ ሚካኤል በነዮ
በግ አምሳል እየመራ አምጥቶ
ታልና ፤ አንድም ለማስፈራት
ነው ፤

ከመ ንቅትልክሙ ፤

እናጠፋችሁ ዘንድ ያለ እግዚአ
ብሔር ፈቃድ የዘመትነ ይመስ
ልሃል ፤

እስመ እግዚአብሔር ይቤለነ ዕርገ
ውስተ ብሔሮሙ ወቅትልዎሙ ፤

እግዚአብሔር ወደ ሀገራቸው
ዝመቱ አጥፏቸው ብሎናልና፤

፲፩፤ ወይቤልዎ ኤልያቄም ወሳም
ናስ ወኢዮአቄም ለራፋስቂስ ፤

ኤልያቄም ሳምናስ ኢዮአቄም
ራፋስቂስን እንዲህ አሉት ፤

ንግሮሙ ለአግብርቲከ ሱርስተ እስመ
ንሰምዕ ፤

እንሰማለንና ለኛ ለባሮችህ በሱ
ርስት ቋንቋ ንገረን ፤

ወኢትንግረነ ዕብራይስጠ ፤

በዕብራይስጥ ቋንቋ አትንገረን
አሉት ዘመድ መስሏቸው ፤

ወለምንትኑ ትነግረነ በዘይሰምዑ እሉ
ሰብእ እለ ዲበ ዐረፍት ፤

ባጥር በቅጥር ያሉ ሰዎች በሚ
ሰሙ ገንዘብ በዕብራይስጥ ቋንቋ
ለምን ትነግረናለህ አሉት ያምባ
ሰው ተሸባሪ ነውና ፤ አንድም
ዘመድ መስሏቸው ፤

www.ethiopianorthodox.org

፲፱፡ ወይቤሉሙ ራፋስቂስ ቦኑ ነገ
እግዚእክሙ ውነቤክሙ ፈነወኒ እግ
ዚእየ ፣

በውኑ ጌታዬ ከናንተና ከጌታ
ችሁ ዘንድ ብቻ ልኮኛል ?

አኮኑ ነገ እሉ ሰብእ ከመ እንግሮሙ
ዘንተ ነገረ ለእለ ይነብሩ ዲበ ዐረፍት፣

ባጥር በቅጥር ለሚኖሩ ይህን እነ
ግራቸው ዘንድ ወደነዚህ የላከኝ
አይደለምን ፤

ከመ ይብልዑ ኮስሐሙ ወይስተዩ
ስንቶሙ ምስሌክሙ ፣

ከናንተ ጋራ መከራቸውን ያዩ
ዘንድ ፤ አንድም ከመ ይበልዑ
ወይስትዩ ቢል ከናንተ ጋራ መከ
ራቸውን እንዲያዩ የላከኝ አይ
ደለምን? አንድም ከመ ይብልዑ
ኮስሐሙ ወይሰተዩ ስንቶሙ
ምስሌክሙ ፣ ከናንተ ጋራ አሠ
ራቸውን ይበሉ አሠራቸውን
ይጠጡ ዘንድ፤ አንድም ከመ
ይበልዑ ወይሰትዩ ቢል ከናንተ
ጋራ አሠራቸውን እንዲበሉ አሠ
ራቸውን እንዲጠጡ ባምባ ለሚ
ኖሩ ሰዎች ይህን ነገር እነግራ
ቸው ዘንድ ወደነዚህ የላከኝ አይ
ደለምን?

፳፫፡ ወቆመ ራፋስቂስ ወከልሐ በዐ
ቢይ ቃል በነገረ ዕብራይስጥ ፣

ራፋስቂስ ተናዶ ተቀምጦ የነበረ
ቆመ፣ ቀስ ቀስ ብሎ ይናገር የነ
በረ በዕብራይስጥ ቋንቋ አሰምቶ
ተናገረ ፤

ወይቤ ስምዑ ቃሎ ለንጉሥ ዐቢይ
ንጉሠ ፋርስ ፣

ገናና የሚሆን የፋርስ ንጉሥ የሰ
ናክሬምን ነገር ስሙ ፤

፳፬፡ ከመዝ ይቤ ኢያስሕትክሙ
ሕዝቅያስ በነገር ዘኢይክል አድኅኖ
ተክሙ ፣

ሕዝቅያስ ዘኢይክል በነገር ዘኢ
ይክል ብሎ መግጠም ነው፤ እና
ንተን ማዳን የማይቻለው ሕዝቅ
ያስ በነገር አያስታችሁ፤ አንድም
ሕዝቅያስ እናንተን ማዳን በማ
ይቻለው ነገር አያስታችሁ አለ፤

፳፭፡ ወእመኒ ይቤለክሙ ሕዝቅያስ
አምላክክሙ ያድኅነክሙ ፣

ሕዝቅያስ ፈጣሪያችሁ ያድናች
ኋል ቢላችሁ ፤

ወኢትገብእ ዛቲ ሀገር ውስተ እዴሁ
ለንጉሠ ፋርስ ፣

ኢየሩሳሌም በሰናክሬም እጅ አት
ያዝም ቢላችሁ ፤

ኢትስምዕዎ ለሕዝቅያስ ፣

ሕዝቅያስን አትስሙት ፤

፳፮፡ ከመዝ ይቤ ንጉሠ ፋርስ ፣

የፋርስ ንጉሥ ሰናክሬም እንዲህ
አለ ፤

ለእመ ትፈቅዱ ትሕየዉ ዛኣ ነቤየ
ኮልክሙ ፣

ትድኑ ዘንድ ከወደዳችሁ ሁላች
ሁም ወደኔ ኑ ለመሐላ ነው ፤

ወትበልዑ ወይነክሙ ወበለሰክሙ፣

ወይናችሁን በለሳችሁን ትበላላ
ችሁ ፤

ወትሰትዩ ማየ አዘቃቲክሙ ፣

ያገራችሁን ውሀ ትጠጣላችሁ፤

እስከ እመጽእ ወእነሥአክሙ ውስተ
ብሔርየ ፣

ሎምናን ወግቼ መጥቼ ወደ
ሀገሬ እስክወስዳችሁ ድረስ ያገ
ራችሁን ውሀ ትጠጣላችሁ አለ፤

፳፯፡ ዘከመ ብሔርክሙ ብሔረ እክል
ወወይን ወሥርናይ ወዐዐደ ወይን ፣

ብሔርየኒ ያለበት ነው፤ አገሬም
እንደ አገራችሁ የእህል የወይን
የስንዴ አገር ነው፤ የወይን ቦታ
ነው ፤

፳፰፡ ኢያስሕትክሙ ሕዝቅያስ በነ
ገር ወኢይበልክሙ እግዚአብሔር ያድ
ኅነክሙ ፣

ሕዝቅያስ እግዚአብሔር ያድና
ችሁኋል እያለ በነገር አያስታ
ችሁ ፤

ቦኑ ዘአድኅኑ አማልክቲሆሙ ለአ
ሕዛብ ኮሉ በሐውርቲሆሙ እም
እዴሁ ለንጉሠ ፋርስ ፣

ዛሬ ያድናችሁ ዘንድ ከዚህ ቀድሞ
የአሕዛብ አማልክት አገራቸውን
ከፋርስ ንጉሥ ከሰናክሬም ያዳ
ኑት ማዳን አለ ?

፳፱፡ አይቴ ውእቱ አምላከ ሄማት
ወአርማት ፣

የሄማት የአርማት ፈጣሪ ወዴት
አለ ?

ወአይቴ ውእቱ አምላከ ሴፋሩሃም፣

የሴፋሩሃም ፈጣሪ ወዴት አለ?

ክህሉኑ አድኅኖታ ለሰማርያ እም
እዴየ ፣

ሰማርያን ከኔ እጅ ማዳን ተቻ
ላቸውን ሰማርያን እሱ አጥፍቷ
ታል ቢሉ ያባት ዕዳ ለልጅ፣ ያፍ
ንጫ እድፍ ለእጅ እንዲሉ ያባ
ቱን ለእርሱ ሰጥቶ ተናገረ፤ አን
ድም አቤቶ ሲባል ከአባቱ ጋራ
መጥቶ ወግቷታልና ፤ አንድም
አሁን ሲመጣ እግረ መንገዱን
ወግቷታልና፤

፳፪፡ ቦኑ እንከ እምኮሉ አማልክተ
አሕዛብ ዘአድኅነ ብሔሮ እምእዴየ፣

በውኑ ከአሕዛብ አማልክት አገ
ሩን ከኔ እጅ ያዳነ አለ ?

ከመ ያድኅና እግዚአብሔር ለኢየሩ
ሳሌም እምእዴየ ፣

እግዚአብሔር ኢየሩሳሌምን ከኔ
እጅ ያድናት ዘንድ ፤

፳፭፡ ወአርመሙ ወኢተሠጥውዎ
ቃለ ፣

ዝም አሉ ቃል አልመለሱለትም፤

www.ethiopianorthodox.org

እስመ አዘዘ ንጉሥ ከመ ኢይሰጠውዎ ቃለ ፣

ሕዝቅያስ ቃል እንዳይመልሱለት አዝዟቸዋልና ፈሪ በነገሩ ይታወቃል እንዲሉ፤ አንድም ከጣየታዊ ጋራ መነጋገር አይገባም ብሎ ፤ አንድም እግዚአብሔርን ማሰደብ ይሆናል ብሎ፣ አንድም ነገር ሲፋፋግ ከኔ ዘንድ ይደርሳል ብሎ ፤

፳፪፤ ወቦኡ ኤልያቄም ወልደ ኬል ቅዩስ መጋቢ ፣

ዕራቅ ማሠሪያ ፤ ኤልያቄም ፤

ወሳምናስ ጸሐፌ ሠራዊት ፣

ጸሐፌ ትእዛዝ ሳምናስ ፤

ወኢዮአስ ወልደ አሳፍ ጸሐፌ ተዝካር ኀበ ሕዝቅያስ እንዘ ስጡጥ አልባሲሆሙ ፣

ዕብሬት ጠባቂ የአሳፍ ልጅ ኢዮአስ እሊህ ልብሳቸውን ቀደው አስልበው ወደ ሕዝቅያስ ገቡ፤

ወነገርዎ ነገረ ራፋስቂስ ፣

የራፋስቂስን ነገር ነገሩት ::

ምዕራፍ ፴፯

፩፤ ወሰሚያ ሕዝቅያስ ንጉሥ ሰጠጠ አልባሲሁ ፣

ሕዝቅያስም የእግዚአብሔርን ስድብ ሰምቶ ልብሱን ቀደደ አሰለበ ፤

ወለብሰ መንጸፈ ወዐርገ ቤተ እግዚአብሔር ፤

ምንጣፍ ለብሶ ወደ ቤተ እግዚአብሔር ወጣ ፤

፪፤ ወፈነምሙ ለኤልያቄም መጋቢ ወለሳምናስ ጸሐፊ ወለረበናት ወለካህናት·እንዘ ስጡጥ አልባሲሆሙ· ኀበ ኢሳይያስ ነቢይ ወልደ አሞጽ ፣

ኤልያቄምን ሳምናስን መምህራንን ካህናትን ምንጣፍ ለብሰው ወደ አሞጽ ልጅ ወደ ኢሳይያስ ላካቸው ፤

፫፤ ወበጽሑ ወይቤልዎ ከመዝ ይቤ ሕዝቅያስ ፣

ከኢሳይያስ ዘንድ ደርሰው ሕዝቅያስ እንዲህ አለ አሉት፤

ዕለተ ምንዳቤ ፣ ወነሣር ፣ ወመንሱት ዛቲ ዕለት ዮም ፣

ይች ዕለት ዛሬ የመከራ ፣ የተዋርዶ ፣ የጥፋት ፣ ቀን ናት ፤

ከመ አልባ ኃይል ለእንተ ትወልድ ወአኀዝ ማሕምም ፣

ለምትወልድ ምጥ ለያዛት ሴት ኃይል እንደሌላት ኃይል የማ ይደረግባት ቀን ናት ፤

፬፤ ለይስማዕ እግዚአብሔር አምላክከ ቃሉ ለራፋስቂስ ዘለአኮ ንጉሠ ፋርስ፣

ሰናክሬም የላከው የራፋስቂስን ነገር ፈጣሪህ እግዚአብሔር ይስማ ፤

ከመ ይትዐየሮ ለእግዚአብሔር አምላክ ሕያው ፤

ሕያው አምላክ የሚሆን እግዚአብሔርን ይገዳደረው ዘንድ፤

ወተዐየሮ በነገር ዘሰምዐ እግዚአብሔር አምላክከ ፣

ፈጣሪህ እግዚአብሔር በሰማው ነገር ተገዳደረው ፤

ወጸሊ ኀበ እግዚአብሔር አምላክከ፣

ከፈጣሪህ ከእግዚአብሔር ዘንድ ለምን ፤ አምላክከ ማለቱ ለነሱ ሌላ አምላክ ሌላ ፈጣሪ ኑሮአቸው አይደለም፣ እሱ ግን ከሰው ተለይቶ በሕጉ ፀንቶ የሚኖር ስለሆነ ከነሱ በባለሟልነት እሱ ይቀርበዋልና፤ አምላክከ ይለዋል ፤

በእንተ እሉ እለ ተርፉ ፣

ዐሥሩ ነገድ ተማርከው ስለቀሩ ስለሁለቱ ነገድ፤ አንድም ከሞት ስለቀሩ ስለነዚህ ሰዎች ወደ እግዚአብሔር ለምን አሉት ፤

፭፤ ወበጺሖሙ ደቀ ሕዝቅያስ ንጉሥ ኀበ ኢሳይያስ ፣

የሕዝቅያስ ብላቴኖች ከኢሳይያስ ዘንድ ደርሰው ፤

ነገርዎ ዘንተ ነገረ ዘለአኮሙ ሕዝቅያስ ፣

ሕዝቅያስ የላካቸውን ነገር ነግሩት ፤

፮፤ ወይቤሎሙ ኢሳይያስ ከመዝ በልዎ ለእግዚእክሙ ሕዝቅያስ ፣

ኢሳይያስ ጌታችሁ ሕዝቅያስን እንዲህ በሉት አላቸው ፤

ከመዝ ይቤ እግዚአብሔር ፣

እግዚአብሔር እንዲህ አለ ፤

ኢትፍራህ እምነገር ዘሰማዕከ ዘተዐየረኒ ንጉሠ ፋርስ ፣

የፋርስ ንጉሥ ሰናክሬም እኔን ከተገዳደረኝ ተግዳሮት ከሰማኸው ነገር የተነሣ አትፍራ አለ እግዚአብሔር በሉት አላቸው፤

፯፤ ናሁ አነ አመጽእ ላዕሌሁ ጋኔነ፣

እነሆ እኔ ጋኔን አመጣበታለሁ፤

ወይሰምዕ ዜና ፣

ድምፅ ሲል ነው፤ አጋንንት የመብረቅ የነጐድጓድ ድምፅ ያሰሙታል፤ አንድም ናሁ አነ አመጽእ ላዕሌሁ ጋኔነ፣ እነሆ እኔ ምት ሐት አመጣበታለሁ፤ ወይሰምዕ ዜና ፣ ድምፅ ሲል ነው፤ የፈረስ የሠረገላ ድምፅ ይሰማል ፤

ወይሠወጥ ብሔሮ ፣

ወደ ሀገሩ ይመለሳል ፤

ወይመውት በመጥባሕት በብሔሩ፣

በሀገሩ በጦር ይሞታል አለ በሉት አላቸው ፤

www.ethiopianorthodox.org

፮፡ ወተሠውጠ ራፋስቂስ ፣

ራፋስቂስ ራፋቂስ ራፋስቂስ ይላል፣ ይህን ተናግሮ ተመለሰ፤

ወረከቦ ለንጉሠ ሩርስ እንዘ ይትቃ ተላ ለሎምና ሶበ ሰምዐ ከመ ግዕዘ እምለኪሶ ሰሚያ በእንተ ተራቅታ ንጉሠ ኢትዮጵያ ዘይቤልዎ መጽአ ይትቃተል ምስሌከ ፣

ካንተ ጋራ ይዋጋ ዘንድ መጣ ያሉት የተራቅታን ነገር ሰምቶ ሰናክሬም ከለኪሶ እንደ ተጓዘ በሰማ ጊዜ ሰናክሬምን ሎምናን ሲወጋ አገኘው ፤ አንድም ካንተ ጋራ ይዋጋ ዘንድ መጣ ያሉት የተራቅታን ነገር ሰምቶ እንደ ሄደ በሰማ ጊዜ ፤

ግዕዘ እምለኪሶ ወረከቦ እንዘ ይትቃ ተላ ለሎምና ፣

ራፋስቂስ ከለኪሶ ሄደ ሰናክሬምን ሎምናን ሲወጋ አገኘው አንድም ሶበ ሰምዐ ባለው እስመ ሰምዐ ይላል ካንተ ጋራ ይዋጋ ዘንድ መጣ ያሉት የተራቅታን ነገር ሰምቶ ሰናክሬም እንደተጓዘ ሰምቷልና ሰናክሬምን ሎምናን ሲወጋ አገኘው ፤

፱፡ ወተመውዐ ተራቅታ ንጉሠ ኢትዮጵያ ወተሠውጠ ፣

የኢትዮጵያ ንጉሥ ተራቅታ ድል ተነሥቶ ተመለሰ፤ ታራም ተራቅታም ይላል፤ አንድም ሰናክሬም ድል ነሥቶ ተመለሰ ፤

፲፡ ወፈነወ ሐዋርያተ ኀበ ሕዝቅያስ ንጉሠ ይሁዳ እንዘ ይብል ፡ ከመዝ በልዎ ለሕዝቅያስ ንጉሠ ይሁዳ ፣

የይሁዳውን ንጉሥ ሕዝቅያስን እንዲህ በሉት ብሎ ወደ ሕዝቅያስ መልክተኞችን ላከ ፤

ኢያስሕትከ አምላክከ ዘቦቱ ተወከልከ እንዘ ይብል ኢትገብእ ኢየሩሳሌም ውስተ እዴሁ ለንጉሠ ሩርስ፣

ኢየሩሳሌም በሩርስ ንጉሥ እጅ አትያዝም እያለ ያመንህበት ፈጣሪህ አያስትህ በሉት አላቸው ፤

፲፩፡ ኢሰማዕከኑ ዘገብሩ ነገሥተ ሩርስ በኵሉ በሐውርት ዘከመ አጥፍእዎሙ ከመ ትድኅን አንተ ፣

አንተ ትድን ዘንድ እንዳጠፏቸው መጠን የሩርስ ነገሥታት በየሀገሩ ያደረጉትን አልሰማህ ምን ፤

፲፪፡ ቦኑ ዘአድኀንዎሙ አማልክቲሆሙ ለአሕዛብ ፣

በውኑ የአሕዛብ አማልክቶቻቸው ያዳኑት ማዳን አለ ?

ዘቀተሉ አበውየ በብሔረ ጎዛን ወራሴን ወካራን ዘደወለ ቴማን ፣

በቴማን አውራጃ አባቶቼ ባጠፉት ጎዛን ራሴን ካራን በሚባለው አገር ያዳኑት ማዳን አለ ?

፲፫፡ አይቴ እሙንቱ ነገሥተ ሄማት ወአርማት ፣

የሂማት የአርማት ነገሥታት ወዴት አሉ ፤

ወአህጉረ ሴፋሩሃም ፣

የሴፋሩሃም አውራጃ ፡

ወምናሄ ወግዋ ፣

የምናሄ የግዋ ነገሥታት ወዴት አሉ ፤

፲፬፡ ወተመጠወ ሕዝቅያስ ይእተ መጽሐፈ እምኀበ ሐዋርያት ፣

ሕዝቅያስ ከመልክተኞች ክታቡን ተቀብሎ ፤

ወአንበባ ፣

አነበባት ፣ የተላለፈ ነው ፤

ወዐርገ ቤተ እግዚአብሔር ወከሠታ ቅድመ እግዚአብሔር ፣

ይህ ቢቀድም ይቀናል ፤

ወዐርገ ቤተ እግዚአብሔር ወከሠታ ወአንበባ ቅድመ እግዚአብሔር ሲል ነው፤ ከቤተ እግዚአብሔር ወጥቶ ክታቢቱን ዘርግቶ በእግዚአብሔር ፊት አነበባት፣ ከዚህ ቀድሞ በራፋስቂስ ቃል ለቃል ልኮበት ነበር፤ አሁን ግን ሎምናን ወግቶ ሲመለስ ቡኒይል ላይ ጎይል ጨምሮ ክታብ ጽፎ ሁለት ብላቴኖች አሲዞ ሰዶለታል፣ ዐርገ ውስተ ቤተ እግዚአብሔር ወተመጠዋ ከሠታ ወአንበባ ወደቤተ እግዚአብሔር ወጥቶ ክታቢቱን በመስኮት ተቀብሎ ርኢ ትዕይርቶ ለሰናክሬም እያለ አንቧታል ፤

፲፭፡ ወጸለየ ሕዝቅያስ ኀበ እግዚአብሔር እንዘ ይብል ፣

ሕዝቅያስም ወደ እግዚአብሔር እንዲህ ብሎ ለመነ ፡

፲፮፡ እግዚአብሔር አምላከ እስራኤል ዘትነብር ዲበ ኪሩቤል ፣

በኪሩቤል ላይ የምትኖር የእስራኤል ፈጣሪ

አንተ ውእቱ አምላክ ባሕቲትከ ዲበ ኵሉ ነገሥተ ምድር ፣

በዚህ ዓለም ነገሥታት ላይ ፈጣሪ አንተ ብቻ ነህ፤ አንድም ፈጣሪ አንተ ብቻ የምትሆን ፤

አንተ ዘፈጠርከ ሰማየ ወምድረ ፣

ሰማይን ምድርን የፈጠርህ አንተ ነህ፤ አንድም ሰማይን ምድርን የፈጠርህ አንተ ፤

ሰማዕ እግዚኦ ፣

አቤቱ የሰናክሬምን ነገር ስማ፤

፲፯፡ ወርኢ ነገሮ ለሰናክሬም ዘለአከ ከመ ይትዐየሮ ለእግዚአብሔር ሕያው ፣

ሕያው የሚሆን እግዚአብሔርን ይገዳደረው ዘንድ ሰናክሬም የላከውን ነገር እይ ፤ አንድም በሕያውነት የሚኖር እግዚአብሔርን ይገዳደረው ዘንድ የላከ የሰናክሬምን ነገር ስማ ፤

፲፰፡ አማን አማሰኑ ኵሎ ዓለመ ነገሥተ ሩርስ ፣

የሩርስ ነገሥታት ዓለሙን ሁሉ በውነት አጠፉ፤ አንድም እስመ አማን በውነት አጠፉ እኮን ፤

www.ethiopianorthodox.org

ወበሐውርቲሆሙ ፤

አገራቸውንም አጠፉ ፤

፲፱፡ ወአውዕዩ አማልክቲሆሙ በእ
ሳት ፤

ጣዖታቸውንም በእሳት አቃ
ጠሉ ፤

እስመ ኢኮኑ አማልክተ ፤

እኒያ ግን አማልክት አይደሉ
ምና አማልክት ስላልሆኑ ፤

አሳ ግብረ እደ ሰብእ እሙንቱ ፤

የሰው እጅ ሥራ ናቸው እንጂ፤

ዕፀው ወአእባን እሙንቱ ፤

እንጨት ደንጊያ ናቸው ፤

፳፡ ወአንተሰ እግዚኦ አምላክነ አድ
ኅነነ እምእዴሁ ፤

አቤቱ ፈጣሪያችን አንተ ግን
ከሰናክሬም እጅ አድነን ፤

ከመ ያእምሩ ኵሉሙ ነገሥተ ምድር
ከመ አንተ እግዚአብሔር አምላክ
ባሕቲትከ ፤

አቤቱ ፈጣሪ አንተ ብቻ እንደ
ሆንህ የዚህ ዓለም ነገሥታት ሁሉ
ያውቁ ዘንድ አድነን ፤

፳፩፡ ወተፈነወ ኢሳይያስ ነቢይ ወልደ
አሞጽ ኀበ ሕዝቅያስ ፤

የአሞጽ ልጅ ኢሳይያስ ወደ
ሕዝቅያስ ተላከ ፤

ወይቤሎ ከመዝ ይቤ እግዚአብሔር
አምላክ እስራኤል ፤

የእስራኤል ፈጣሪ እግዚአብሔር
እንዲህ አለ አለው ፤

ሰማዕኩ ዘጸለይከ ኀቤየ በእንተ ሰናክ
ሬም ንጉሠ ሩርስ ፤

የሩርስ ንጉሥ ሰናክሬምን አጥፋ
ልኝ ብለህ ከኔ ዘንድ የለመንኸ
ውን ልመና ሰማሁ ፤

፳፪፡ ዝንቱ ነገር ዘይቤ እግዚአብ
ሔር በእንቲአሁ ፤

ስለሱ እግዚአብሔር የተናገረው
ነገር ይህ ነው ፤

በእንተ ዘጸለለኪ ወአስተሐቀረኪ ወለተ
ጽዮን ፤

የጽዮን ልጅ አንቺን ስለናቀሽ
ስለአቃለለሽ ስለሰደበሽ ፤

ወአንሥአ ርእሶ ላዕሌኪ ወለተ ኢየ
ሩሳሌም ፤

የኢየሩሳሌም ልጅ ራሱን ባንቺ
ላይ ስለነቀነቀ እግዚአብሔር
ስለሱ የተናገረው ነገር ይህ ነው፤

፳፫፡ መነ ተዐየርከ ፤

ማንን ተገዳደርህ እኔን አይደ
ለም ?

ወወሐከ ፤

ቅሠፈኝ ቅሠፈኝ ብለህ ማንን
አነጣሞህ እኔን አይደለም ?

ወበመኑ አንሣእከ ርእሰከ ፤

ራስህን በማን ላይ ነቀነቅህ፣ በኔ
አይደለም ?

ወበመኑ አዕበይከ ቃለከ ፤

ቃልህን በማን ላይ ከፍ ከፍ አድ
ርገህ፣ ተናገርህ በኔ አይደለም?

ወኢታኅሥእኑ ውስተ አርያም ዐይ
ነከ ፤

ስንኪን ከኔ ከፈጠርሁት ከሰማይ
መድረስ ይቻልህ እንደሆነ አንገ
ትህን አቅንተህ አታይምን፤

ወትኔጽር ኀበ ቅዱሰ እስራኤል ፤

ከዚህ በኋላ ከተቻለህ ወደ ዕንዓ
እስራኤል ወደ ክብረ እስራኤል
ወደ እግዚአብሔር ትመለከታ
ለህ ፤

ከመ ትትዐየሮ ለእግዚአብሔር በሐ
ዋርያቲከ ፤

እግዚአብሔርን በመልክተኞችህ
ትገዳደረው ዘንድ ፤

፳፬፡ አንተሰ ትቤ በብዙኀ ሠራዊትየ
አዐርግ ውስተ ነዋኅት አድባር ፤

አነተስ በሠራዊቴ ብዛት ነገሥ
ታቱን እገዛለሁ ብለህ ነበር ፤

ወውስተ ርእሰ ሊባኖስ ፤

ጎያላኑን እገዛለሁ ብለህ ነበር፤

ወአገዝም ነዋኅተ አርዚ ፤

ልዑላኑን እገዛለሁ ብለህ ነበር፤

ወዕፀወ ቂድሮስ ፤

ዐርበኞችን እገዛለሁ ብለህ ነበር፤

ወቦአኩ ውስተ አሐዱ ገጸ ፤

ወደ አንድ አገር ወደ ለኪሶ ገባሁ
ብለህ ነበር፤ አንድም ባንድ ወገን
ገብቼ ሁሉን እገዛለሁ ብለህ ነበር
አንድም ሁሉን አንድ አድርጌ
እገዛለሁ ብለህ ነበር ፤

፳፭፡ ውኅዘርኩ ፤

በጦር አጥረዋለሁ ብለህ ነበር፤

ወአንጸፍኩ ማየ ፤

ሠራዊቱን አጠፋለሁ ብለህ ነበር፤

ወኮሎ ምቅዋመ ማይ ፤

ከተማውን አጠፋለሁ ብለህ
ነበር ፤

፳፮፡ ኢሰማዕከኑ ዘንተ ዘገበርኩ አነ
ትካት በመዋዕል ዘቀዲሙ ፤

ትካትና ዘቀዲሙ አንድ ወገን
ነው፤ እኔ በቀድሞ ዘመን ያደረ
ግሁትን አልሰማህምን ፤

ወአዘዝኩ ያጥፍእዎሙ ለአሕዛብ በው
ስተ አዕዋኒሆሙ ፤

አሕዛብን በአምባቸው ውስጥ
ያጠፏቸው ዘንድ አዘዝሁ ፤

ወእለሂ ይነብሩ ውስተ አህጉር ፤

በየሀገሩ ያሉትን ያጠፏቸው
ዘንድ አዘዝሁ ፤

ወይዒውኑ ፤

በአምባ የተጠጉትን ያጠፏቸው
ዘንድ ፤

፳፯፡ ወአመጽአ እዴየ ወይየብሱ ፤

እደ መዓቴን አመጣለሁ ይጠ
ፋሉ ፤

ወይከውኑ ከመ ሣዕር ዘይየብስ በው
ስተ ናሕስ ፤

በግንብ ላይ እንደ ደረቀ ሣር
ይሆናሉ ፤

www.ethiopianorthodox.org

ወከመ ተሐግ ፣

በበግ ፊት እንዳለ ሰርዶ ይሆ ናሉ ፤

፳፰፡ ወይእዜሰ አእመርኩ ምብያቲከ ወሙሳኢከ ፣ ወሙሳኢከ ፣

ሙሳኢከ ያለው ይቀድማል፣ ከነ ነፄ መውጣትህን ምብያቲከ ሰፈርህን ወሙሳኢከ ለኪሶ መግባትህን አወቅሁ ፤ አንድም ወሙሳኢከ ለኪሶ መግባትህን ወሙሳኢከ ከለኪሶ መውጣትህን ምብያቲከ ሰፈርህን አወቅሁ ፤ አንድም ሙሳኢከ ከለኪሶ መውጣትህን ምብያቲከ ሰፈርኽን ወሙሳኢከ ተመልሰህ ነነፄ መግባትህን አወቅሁ ፤

፳፱፡ ወመዓተከሂ ዘተማዕከ ፣

የተቈጣኸውን ቍጣህንም አወቅሁ ፤

ወምረትከኒ ዐርገ ኀቤየ ፣

ቦኑ ግልፎ ዘያድኅን ብለህ የተናገርኸው ነገር ከኔ ደረሰ አንድም ፍሐሌትከ ይላል መንፈርህ መድፈርህ ከኔ ደረሰ ፤

ወእወዲ ብዙ ዝማማተ ውስተ አንፍከ ወልኃመ ውስተ ከናፍሪከ ፣

ባፍንጫህ ልባብ በከንፈርህ ልጓም አገባብሃለሁ ማለት በሥልጣኔ ገትቼ እመልስሃለሁ ፤

ወእመይጠከ በፍኖት እንተ ባቲ መጻእከ ፣

በመጣህባት ጒዳና እመልስሃለሁ ማለት ባዶ እጅህን እንደ መጣህ ባዶ እጅህን እመልስሃለሁ፤ አንድም እንተ ባቲ ኢመጻእከ ይላል ባልመጣህባት ጒዳና እመልስሃለሁ፣ ሲመጣ በእልልታ በግርማ ርታ መጥቶ ነበር፣ አሁን ግን ዐሥራ ስምንት እልፍ ካምስት ሺህ ሰው አጥፍቶ ሰባት ፈረሰኛ ዐሥራ አምስት ፈረሰኛ ሁኖ አጋንንት የመብረቅ የነጐድጓድ ድምፅ እያሰሙት እየወደቀ እየ ተነሣ ሂዷልና ፤

፴፡ ወዝንቱ ትእምርትከ ፣

የሚደረግልህም ምልክት ይህ ነው ፤

ብላዕ ዘንተ ዓመተ ዘዘራዕከ ፣

ሕዝቅያስ ከሰናክሬም ባመልጥ ቀጠናው ይገድለኝየለምን ብሏል፣ ሰናክሬም ዓመተ ኅድገት አይቶ መጥቶበታል እስራኤል ባምስተኛው ዘመን የዘሩትን በስድስተኛው ዘመን የዘሩትን በስድስተኛው ዓመተ ኅድገት ያደርጋሉ፤ በስምንተኛው እንደገና ይዘራሉ፣ ይለቅማሉ፣ ብላዕ ዓመተ ዘዘራዕከ ባራተኛው ዘመን የዘራኽውን ባምስተኛውም በስድስተኛውም ብላ ፤

ወበካልዕ ዓመት ዘአትረፍከ ፣

ከዘያ የቀረውን በሰባተኛው ዓመት ብላ ፤

ወበሣልስ ዓመት ትዘርዑ ወተዐርሩ፣

በስምንተኛው ዘመን እንደገና ትዘራላችሁ ትለቅማላችሁ፣ እንዲህ ማለቱ አበረክትልሃለሁ ሲለው ነው፡ አንድም ይህ ሁሉ እስኪደረግ ድረስ አልቆየም ወዲያው ፈጥኖ ጠፍቶለታል ብሎ እንደ ቀደመው ሁኗል ፤

ትተክሉ ወይነ ወትቀስሙ ፣

ወይኑን ትተክላላችሁ ትለቅማላችሁ ፤

ወትበልዑ ቀምሐ ፣

ፍሬውን ትበላላችሁ ፤

፴፩፡ ወይሠርዕ ሥርዎሙ ለእለ ተርፉ በይሁዳ ፣

ዐሥሩ ነገድ ተማርከው በይሁዳ የቀሩ ሁሉቱ ነገድ አባትነታቸው በረድኤት ይለመልማል ፤ አንድም አባቶች አልቀው የቀሩ ልጆች በረድኤት ይለመልማሉ፤

ወይፈሪ ዘርዖሙ በላዕሉ ፣

ልጃቸው ልጅ ይወልዳል ፤

፴፪፡ እስመ በኢየሩሳሌም ይከውኑ እለ ድኅኑ ወእለ ተርፉ እምደብረ ጽዮን ፣

ዐሥሩ ነገድ ተማርከው የቀሩ ሁለቱ ነገድ በኢየሩሳሌም ይኖራሉና ፤

እስመ ቅንዐቱ ለእግዚአብሔር ይገብር ዘንተ ፣

እግዚአብሔር ለአምላክነቱ የቀናው ቅናት እንዲህ ያደርጋልና፤

፴፫፡ በእንተ ዝንቱ ከመዝ ይቤ እግዚአብሔር ፣

ስለዚህ ነገር እግዚአብሔር እንዲህ አለ ፤

ለንጉሠ ፋርስ ፣

ንጉሠ ፋርስ ሰናክሬምን ነገር አድርጎ ተናገረው፤ አንድም በንጉሠ ፋርስ ተናገረ፣ ነገሩን ኢይበውኣ ብሎ ያመጣዋል፤ አንድም እግዚአብሔር እንዲህ ብሎ ተናገረ ፤

ንጉሠ ፋርስ ኢይበውኣ ለዛቲ ሀገር፣

ንጉሠ ፋርስ ሰናክሬም ወደ ኢየሩሳሌም አይገባም አለ ፤

ወኢይነድፍ ውስቴታ ሐፀ ፣

ፍላፃ አይወረውርባትም ፤

ወኢይሠይም ወልታ ላዕሌሃ ፣

በጋሻም አይመጣባትም ፤

ወኢየኀፅራ ፣

በጦር አይከባትም ፤

፴፬፡ ወይሠወኖ በፍኖት እንተ ባቲ መጽአ ፣

በመጣባት ጒዳና ይመለሳል ፤

ወኢይበውኣ ለዛቲ ሀገር ፣

ወደዚህች ከተማም አይገባም፤

www.ethiopianorthodox.org

፴፮፤ ከመዝ ይቤ እግዚአብሔር እረድኣ ለዛቲ ሀገር ፣

እግዚአብሔር ይችን አገር ረዳ ታለሁ ብዬ ነበር፣ ረዳኋት እን ግዲህ ወዲህም ረዳታለሁ አለ፤

ወአድኅና-በእንተአየ ፣

በኔ ስላመነች እኔን ስላመለከች አድናታለሁ ብዬ ነበር አዳንኋት እንግዲህ ወዲህም አድናታለሁ፤

ወበእንተ ዳዊት ገብርየ ፣

ስለ ወዳጄ ስለ ዳዊት አድናታ ለሁ ብዬ ነበር አዳንኋት እንግዲህ ወዲህም አድናታለሁ ፤

፴፯፤ ወእምዝ መጽአ መልአከ እግዚ አብሔር ፣

ከዚህ በኋላ መልአከ እግዚአብ ሔር ቅዱስ ሚካኤል መጣ ፤

ወቀተለ እምትዕይንተ ፋርስ ዐሠርተ ወስምንተ አልፈ ወሐምሳ ምእተ ነደወ ፣

ገሩርስ ሠራዊት መቶ ሰማንያ አምስት ሽሕ ሰዎችን አጠፋ ኖነው በእም ተናገረው መላው ኣልቀው የለም ቢሉ ትብትብ ምንጣፍ ተሸክመው የመጡት ኣንደ ራፋስቂስ በግብር ያልተ ገበሩት ሰናክሬም በጠፋ ጊዜ ኣልል እያሉ ወደ ሕዝቅያስ ገብ ተዋልና፤ አንድም ነሥአን ወአ ነተጋብዖን የሚላቸው በሕሊና ነለማረካቸው ድነዋልና፤ አንድም ሰባቱ ፈረሰኞች ዐሥራ አምስቱ ፈረሰኞች ቀርተዋልና፤ ከዚህ ዐሥራ ስምንት ዕልፍ ካምስት ሺህ አለ፣ ቄርሎስ መቶ ሰማንያ አምስት ሺህ አለ ፤ አይጣላም ቢሉ አይጣላም፣ ቅዱስ ቄርሎስ ቀፊ ገበሬውን ቋሚ ለጓሚውን ቄጥሮ መቶ ሰማንያ አምስት ሺህ አለ፣ ከዚህ ኢሳይያስ ዐርበኛ ዐርበኛውን ቄጥሮ ዐሥራ ስም ንት እልፍ ካምስት ሺህ አለ ፤ አንድም በሀገራቸው ዕልፍ የሚል ቍጥር የለም ብሎ ዐሥሩን እልፍ መቶ ሺህ ስምንቱን እልፍ ሰማንያ ሺህ አለ አምስቱ ባለበት ነው፤ አንድም በሀገራቸውም በሀ ገራችንም የእልፍ አሐዝ እንጂ የሺህ ኣኀዝ የለም ፤ ሺሁን በእ ልፍ ኣኀዝ አግብቶ ሰማንያ አም ስት እልፍ አለ ፤

ወነቂሆሙ በጽባሕ ረከቡ አብድን ቲሆሙ ኮሉሙ በጎበ ሞቱ ፣

ሲጠባ በተነሡ ጊዜ ሁሉም በሞ ቱበት ቦታ ወድቀው ሬሳቸውን አገኙ በለኪሶ ያሉት ነሥአን ወአ ስተጋብዖን የሚላቸው፤ አንድም ሰባት ፈረሰኞች ዐሥራ አምስት ፈረሰኞች ሕዝቅያስም ጉበኞች ሰዶ ነበርና ፤

፴፰፤ ወተሠውጠ ሰናክሬም ንጉሠ ፋርስ ፣

የፋርስ ንጉሥ ሰናክሬም ተመ ለሰ ፣

ወዐተወ ወነበረ ውስተ ነነዌ ፣

ነነዌ ገብቶ ተቀመጠ፣ እሱ የኔን ወገን ቢያጠፋ እኔስ የሱን ወገን አላጠፋም ብሎ ከእስራኤል የቀ ሩትን እያጠፋ አምሳ አምስት ቀን ተቀምጧል ፤

፴፯፤ ወእንዘ ይሰግድ ውስተ ቤተ ሊድራክ አምላኩ አድራሜሌክ ወሶ ርሶር ደቂቁ ቀተልዎ በመጥባሕት፣

ሶርሶርም ይላል ፣ ደራክስስም ይላል፣ ከቤተ ጣዖት ገብቶ ሲሰ ግድ ዐሥራ ስምንት እልፍ ካም ስት ሺህ ሰው አጥፍቶ በማን ሊነግሥ መጥቷል ብለው በጦር ገደሉት ፤

ወአምሠጡ ውስተ ዓራራተ ሀገር፣

ዓራራጥም ይላል ወደ ዐራራት አመለጡ ስለምን አገሩ ገብቶ እንዲሞት አደረገው ቢሉ ኢየሩ ሳሌም ክብርት ሀገር ናት፣ የጣ ያታዊ ደም አይፈሰስባት ብሎ ምነው ሌሎችስ መምለክያነ ጣዖት አይደሉም ቢሉ የሱ ይፀና ልና፤ አንድም መከራ ይፅናበት ብሎ ሲመጣ በእልልታ በግርማ ርታ መጥቶ ነበር ፤ አሁን ግን አጋንንት የመብረቅ የነጐድጓድ ድምፅ እያሰሙት ሰባት ፈረሰኛ፣ ዐሥራ አምስት ፈረሰኛ ሁኖ እየ ወደቀ እየተነሣ ሂዷልና፤ አንድም የጣዖቱን ደካማነት ለማስረዳት በሀገሬ ቢሆን ጣዖቱ ያድነኛል ባለ ነበርና፤ አንድም የነቢዩ ትን ቢት እንደተፈጸመ ለማጠየቅ ወእሬስዮ ለስብከከ መቃብሪከ እንዲል ፤

ወነግሠ አስራዶን ወልዱ ህየንቴሁ፣

ልጁ አስራዶን ስለሱ ፈንታ ነገሠ ይህ ከነገር ያልገባ ነው፤ ብዙ ስም አለው አስራዶን ፤ ሆነኽርድን ዐስበ ቀፈች ፤ ንዑስ ሰናክሬም ይለዋል እሱ ነግሷል ::

ምዕራፍ ፴፰

ጉባዔ

፩፤ ወውእተ አሚረ ደዌየ ሕዝቅያስ ወበጽሐ ለሞት ፣

ሰናክሬምን ልጆቹ ገደሉት ብሎ ነበርና ያንጊዜ ሕዝቅያስ ታመመ ለሞትም ደረሰ፣ ሰናክሬም በሞተ ጊዜ ነቢያተ ሐሰት ሂደው ሕዝ ቅያስን አባቶቻችን የቀን ዘለሳ የሌሊት ግሥገሣ እያማታቸው ጠላታቸውን ድል ይነሡ ነበር አንተ ግን ከቤትህ ሳትወጣ ጠላ ትህን ድል ነሣህ፣ እንዳንተ ያለ እንጂ ደግ የለም አሉት፤ እሆን ይሆናላ ብሎ የተናገረበትን ልቡን ወግቶ ይዞታል ፤ አንድም ሕገ ሰብሳብ ርኩስ ሕገ ድንግልና ንጹሕ ብሏል ፤ ከሴት ሳልለይ እንዲህ ያለ ተአምራት የተደ ረገልኝ ከሴትማ ብለይ እንደ ምን ያለ ተአምራት ይደረግልኝ ነበር ብሏል፤ ከሱ ምናሴ ከምናሴ

www.ethiopianorthodox.org

ጌታ የሚወለድ ነውና ሕገ ሰብሳ
ብን ቢያቃልል ልቡን ወግቶ ይዞ
ታል፤ በዚህስ ዕዳ አይልበትም
ይኸውም ይታወቅ ዘንድ የሕጋ
ውያንን ክብራቸውን ሠላሳ ሲያ
ደርግ የደናግልን ስሳ አድርጎሳ
ቸዋል ብሎ ነቢያተ ሐሰት ድን
ግል የተባለች ኢየሩሳሌም ናት፤
ከዚህ ቀድሞ የአሕዛብ ፍላፃቸው
አልተወረወረባትም አለንጋቸው
አልጮኸባትምና፣ ወልድ የተባ
ልህ አንተ ነህ አሉት ፤ እሆን
ይሆናላ ብሎ የተናገረበትን ልቡን
ወግቶ ይዞታል፣ ምነው ይህንማ
የተናገረ ኢሳይያስ አይደለምን
ዳኛው ሳይለወጥ ሸንጎው ሳይመ
ለጥ እንዲሉ አይደለህም አይ
ለውም ብሎ ጊዜው ቢደርስ
ታመመ ፤

ወመጽአ ኀቤሁ ኢሳይያስ ወልደ
አሞጽ ፣

የአሞጽ ልጅ ኢሳይያስ ወደሱ
መጣ ፤

ወይቤሎ ከመዝ ይቤ እግዚአብሔር፣

እግዚአብሔር እንዲህ አለ ፤

ሥራዕ ቤተከ እስመ ትመውት ወኢ
ተሐዩ ፤

ትሞታለህ እንጂ አትድንምና
ቤትህን አዘጋጅ አለው፤ አንድም
ትሞታለህ እንጂ አትድንምና
ቤትህን ሥራ ማለት ስጥ መጽ
ውት መንግሥትህን አውርስ
አለው ፤

፪፤ ወመጠ ገጸ ሕዝቅያስ ኀበ ዐረፍት፣

ተነሥቶ መዞር የማይሆንለት
ቢሆን ከነዙፋኑ ፊቱን ወደቤተ
እግዚአብሔር አዙሩኝ ብሎ ፤

ወጸለየ ኀበ እግዚአብሔር ፣

ወደ እግዚአብሔር ለመነ፤ አን
ድም እሱ ፊቱን ወደ አልጋው
መመለስ ባይቻለው አልጋውን
ወደቤተ መቅደስ አዞሩለት፤ አን
ድም ሕዝቅያስ ፊቱን ወደ ኖራው
ወደ ግንቡ መልሶ ወደ እግዚአብ
ሔር ጸለየ ፤

፫፤ ወይቤ ተዘከር እግዚኦ ዘከመ
ሖርኩ ቅድሜከ በጽድቅ ወበልብ
ርቱዕ ፣

አቤቱ በቅን ልቡና በውነት ነገር
በፊትህ ፀንቼ እንደ ኖርሁ አስብ፣
አንድም በቀና ልቡና በምግባር
በሃይማኖት ፀንቼ እንደ ኖርሁ
አስብ ፤

ወገበርኩ ቅድሜከ ሥምረተከ ፣

በፊትህም ፈቃድህን እንዳደረ
ግሁ አስብ አለ ፤

ወበከየ ሕዝቅያስ ዐቢየ ብካየ ጥቀ፣

ምን ጊዜስ እግዚአብሔር የልቡ
ናን ቅንነት ያያል እንጂ የአፍን
መቀባጠር ያያል ብሎ ሁለቱን
ነገር ተናግሮ ዕኑ ለቅሶ አለቀሰ፤

፬፤ ወኮነ ቃለ እግዚአብሔር ኀበ ኢሳ
ይያስ ነቢይ ፣

ሥራዕ ቤተከ እስመ ትመውት
ወኢተሐዩ ብሎ ነግሮት ካምስቱ
ቆመ ብእሲና ከስድስቱ ቆመ
ብእሲ መካከል ደርሶ ነበር፤ ወደ
ነቢዩ ኢሳይያስ ቃለ እግዚአብ
ሔር መጣ፣ ተነገረ ፤

፭፤ ወይቤሎ ሑር በሎ ለሕዝቅያስ፣

ሂደህ ሕዝቅያስን እንዲህ በለው፤

ከመዝ ይቤ እግዚአብሔር አምላከ
ዳዊት አቡከ ፣

ያባትህ የዳዊት ፈጣሪ እግዚአ
ብሔር እንዲህ አለ ፤

ሰማዕኩ ጸሎተከ ወርኢኩ አንብዐከ፣

ልመናህን ሰማሁ ልቅሶህንም
አየሁ ፤

ወናሁ ወሰኩከ በዲበ ክራማተከ ዐሠ
ርተ ወሐመስተ ክራማተ ፣

እነሆ በዕድሜህ ላይ ዐሥራ
አምስት ዓመት ጨምሬልሀለሁ
አለው፤ የሱ አልተፈጸመም ነበር
ቢሉ የሱን ጨርሶለታል ፣ የሱ
ተፈጽሞ ነበር ቢሉ የሰናክሬምን
ጨምሮለታል ፤

፮፤ ወአድኅነከ አምእዴሆሙ ለነገ
ሥተ ፋርስ ፣

ከፋርስ ነገሥታት እጅ አድን
ሃለሁ ፤

ወእቀውም ላቲ ለዛቲ ሀገር ፣

ለዚች አገር ጠበቃ ሁኜ እቆምላ
ታለሁ ብዬ ነበር ቆምሁላት እን
ግዲህም ወዲህ እቆምላታለሁ፤

፯፤ ወዝንቱ ትእምርቱ እምኀበ እግዚ
አብሔር ከመ ይግበር ዘንተ ነገረ ፣

የተላለፈ ነው፤ ይህን ነገር ያደ
ርግ ዘንድ ከእግዚአብሔር ዘንድ
ታገዘ የሚሆን ምልክቱ ይህ ነው፤

ናሁ ይወርድ ጽላሎት ዲበ ዐሠርቱ
መዐርጋት ፣

እነሆ ጥላ ከዐሥረኛው እርከን
ደርሷል፣ የቤተ መቅደስ እርከን
ነው ይላሉ፤ አንድም አባቱ አካዝ
ያሠራው ግንብ እርከን ነውም
ይላሉ ፤

ለእመ ይትመየጥ ጽላሎት ድኅሬሁ
ዐሠርተ መዐርጋተ ፣

ጥላ ተመልሶ ከመጀመሪያው እር
ከን ቢሆን በዚህ ዕወቅ አለው ፤

፰፤ ወይቤ ሕዝቅያስ ኢይፈቅድ ዘንተ
ትእምርተ ፣

ሕዝቅያስ እንዲህ ያለ ምልክትስ
አልሻም አለ፣ ይህንማ ከኔና ካንተ
በቀር ሌላ የሚያውቀው አለ፤

እመሰ ይትከሀል ይግባእ ዐሐይ ዲበ
ዐሠርቱ መዐርጋት ፣

የሚቻልስ ከሆነ ሠርክ ሁኗል
ተመልሶ ተሰደት ይሁንልኝ
አለው ፤

www.ethiopianorthodox.org

፬፡ ወይቤ ኢሳይያስ ይኩን በከመ ትቤ ፡

ኢሳይያስ እንዳልህ ይሁንልህ አለው ፡

ወኮነ ከማሁ ፡

እንዳለው ሆነ ፡

፭ወግብአ ፀሐይ ዐሠርተ መዐርጋተ፣

ሠርክ የነበረው ተመልሶ ተሲያት ሆነ፣ ዐሥር ኬክሮስ ተመለሰ፤ አንድም ናሁ ይወርድ ጽላሎት ዲበ ዐሠርቱ መዐርጋት ጽላሎት ያለው ፀሐይን ነው ፤ ጥላ ያለ ፀሐይ አይታወቅምና በግብሩ ጽላሎት ብሎታል መዐርጋት የተባለ ኬክሮስ ነው፤ እነሆ ሠርክ ሁኗል ተመልሶ ተሲያት ቢሆን በዚህ ዕወቅ አለው ፡

ወይቤ ሕዝቅያስ ኢይፈቅድ ዘንተ ትእምርተ ፡

ሕዝቅያስ እንዳህ ያለ ምልክት አልሻም የሚቻልስ ከሆነ ሠርክ ሁኗል ተመልሶ ሠለስት ይሁንልኝ አለው፤ ኢሳይያስም እንዳልህ ይሁንልህ አለው፤ እንዳለው ሆነ ሠርክ የነበረው ተመልሶ ሠለስት ሆነ አርባ ኬክሮስ ተመለሰ ፡

ጸሎተ ሕዝቅያስ ንጉሠ ይሁዳ አመ ደወየ ወሐይወ እምደዌሁ ፡

የይሁዳ ንጉሥ ሕዝቅያስ ታሞ በዳነ ጊዜ የጸለየው ጸሎት ይህ ነው፤ አንድም ደወየኝ ቅሱ ይሻል የይሁዳ ንጉሥ ሕዝቅያስ ታሞ በዳነ ጊዜ የተናገረው ነገር ይህ ነው ፡

፩፡ አንሰ እቤ በኑኅ መዋዕልየ ፡

እኔስ ባለ ዘመኔ ሁሉ ጻድቅ ነኝ ብዬ ተመክቼ ፡

ውስተ አናቅጸ ሲኦል ኀደጉ ዘተርፈ ዓመትየ ፡

ይህን ዐሥራ አምስቱን ዓመት በመቃብር አጣሁ ብዬ ነበር ፤

ወእቤ ኢይሬኢ ሰብአ እምአዝማድየ፣

ከዘመዶቼ ወገን ሰውን አላይም ብዬ ነበር ፡

ውኑጐልኩ ዘተርፈ ሕይወትየ ፡

ይህን የቀረውን ዐሥራ አምስቱን ዓመት በመቃብር አጣሁ ብዬ ነበር ፡

፲፩፡ ወዕአት ውነሰፈት እምኔየ ፡

ነፍሴ ሥጋዬን በመቃብር ትታት ሄደች ብዬ ነበር ፡

ከመ ዘይተክል ደብተራሁ ወየኀድር ወይዴረር ፡

ይዴረር ወየኀድር ሲል ነው፤ መሸ አዳሪ ድንኳኑን ተክሎ ራቱን ተመግቦ አድሮ በነጋው ድንኳኑን ነቅሎ እንዲሄድ ፡

ከማሁ ኮነት ነፍስየ በላዕሌየ ፡

ነፍሴ ሥጋዬን በመቃብር ጥላት ሄደች ብዬ ነበር ፡

ወከመ ዕጡፈ ፀምር ዘአልጸቀ ይግምድዎ ፡

ዕጡፍ ፀምር ሲል ነው፤ ስጠተ ልብስ ንፍቀ ታቦት እንዲል ሊቄርጡት የቀረበ የተጠቀለለ ሸማ በቄረጡት ጊዜ መቹኩ ወደ ላይ ተንጠልጥሎ እንዲቀር ሸማው ዘነፍ ብሎ ወደጥድንዱ እንዲገባ ነፍሴ ሥጋዬን በመቃብር ትታት ሄደች ብዬ ነበር ፡

፲፪፡ ወውእተ አሚረ ተሐወኩ ከመ አንበሳ እስከ ይጸብሕ ፡

ያንጊዜ እስኪጠባ ድረስ እንደ አንበሳ ታወክሁ፣ አንበሳ ምግብ ለመሻት ሌሊት ሲታወክ ያድራል ፡

ወከመ ዘመጽአ ማሕምም ለእንተ ትወልድ አኀዘኒ እምነግህ እስከ ሠርክ፣

ምጥ የያዛት ሴት እንድትጨነቅ ነቅ ከነግህ እስከ ሠርክ ያዘኝ፣ ምነው ሦስት ቀን አይደለም ቢሉ ያው እየመሸ እየጠባ ነውና፤ አንድም የዐናበትን ለይቶ ተናገረ ፡

ወከማሁ ተቀጥቀጣኒ አዕፅምትየ ፡

አሁን እንደ ተናገርሁት አጥንቶቼ በመከራ ተቀጠቀጡብኝ፤

፲፫፡ ወከመ ማዕነቅ ከማሁ እነቁ ፡

እንደ ዋኖስ እጮኻለሁ ፡

ወከመ ርግብ ከማሁ እኑብብ

ርግብ እንድትጮኽ እጮኻለሁ፤

፲፬፡ ደክማ አዕይንትየ ወስእንዝኩ ነጽሮ ኀበ እግዚአብሔር ሰማየ ፡

ዐይኖቼ ደከሙ፣ እግዚአብሔር ወዳለበት ወደሰማይ አቅንቶ ማየት ተሳነኝ ፡

፲፭፡ ተሠሃለኒ ወአዕትት ሕማማ ለነፍስየ ፡

ይቅር በለኝ የሰውነቴን መከራዋን አርቅላት ፡

፲፮፡ እግዚኦ በእንቲሃ እቤለከ ፡

አቤቱ ስለሷ እንዲህ እልሃለሁ፤

ወአንሣእካ ለነፍስየ ፡

ሰውነቴን አድናት እልሃለሁ፤

ተፈሣሕኩ ወሐዮኩ ፡

ሐዮኩ ወተፈሣሕኩ ሲል ነው፤ ከደዌዬ ተፈወስሁ በሰናክሬም ሞት ደስ አለኝ፣ አንድም ተፈሣሕኩ በሰናክሬም ሞት ደስ አለኝ ወሐዮኩ ከደዌዬ ተፈወስሁ ፡

፲፯፡ ወተሣሃልካ ለነፍስየ ከመ ኢት ትነሥል ፡

ሰውነቴን እንዳትጠፋ ይቅር አልኻት ፡

ወገደፍከ ድኅሬከ ኵሉ ኃጢአትየ፣

ኃጢአቴን ወደ ኋላህ ጣልህ ፡ ወደኋላ የጣሉት እንዳይታሰብ ኃጢአቴን አላሰብህብኝም ፡

፲፰፡ እስመ አኮ አለ ውስተ ሲኦል ዘይሴብሑከ ፡

በመቃብር ያሉ ሰዎች የሚያመሰግኑህ አይደለምና ፡

www.ethiopianorthodox.org

ወአኮ እለ ይመውቱ ዘይባርኩከ ፣

የሞቱ ሰዎች የሚያመሰግኑህ አይደለምና ፤

፲፱፡ ወኢይሴፈዉ ሣህለከ እለ ውስተ ሲኦል ፣

በመቃብር ያሉ ሰዎችም ዝናም ለአብቅሎ ፀሐይ ለአብስሎ ይሰጠናል ብለው ተስፋ አያደርጉምና ፤

ጻዕሙ ሕያዋን ይባርኩከ ከመ አነ ይእዜ ፣

ዛሬ እኔ እንዳመሰግንህ በሕይወት ያሉ ያመሰግኑሃል እንጂ፤ አንድም ሕያዋን አለን አለን ሲሉ ያመሰግኑሃል እንጂ፤ በመቃብር ያሉ ሰዎች የሚያመሰግኑህ አይደለምና ወተሣሃልካ ለነፍስየ ከመ ኢትትጎንፅል ብለህ እሠር ፤

እምዮምሰ እገብር ደቂቀ አለ ይነግሩ ጽድቀከ ፣

ሕ፻ ሰብሳብን አቃሎ ነበርና እንግዲህ ወዲህስ ቸርነትህን የሚናገሩ ልጆችን በዘር በሩካቤ እወልዳለሁ፤ አንድም በትምህርት ቸርነትህን የሚናገሩ ልጆች እወልዳለሁ፤ አንድም እምይእዜሰ እገብር ደቂቀ ይላል ምናሴ እንዳል ተወለደ በዚህ ይታወቃል፣ ይኸን ባለው ዛቲ ተግሣጽ ትኩንኒ እምዮም እግዚአ ይላል ፤

፳፩፡ እግዚእየ ወመድኃንየ አንተ ፣

ጌታዬ መድኃኒቴ አንተ ነህ ፤

ወአነሂ ኢየኀድግ ባርኮተከ በመዝሙር በኵሉ መዋዕለ ሕይወትየ ፣

እኔም ባለ ዘመኔ ሁሉ አንተን በበገና ማመሰገን አልተውም ፤

በቅድመ ቤተ እግዚአብሔር ፣

በቤተ እግዚአብሔር አንተን ማመሰገን አልተውም ፤

፳፪፡ ወይቤሎ ኢሳይያስ ለሕዝቅያስ፣

ኢሳይያስ ሕዝቅያስን እንዲህ አለው ፤

ንሣእ ዐጽቀ በለስ ፣

ዐጽቀ በለስ ቈጽለ በለስ ፍሬ በለስ ደመ በለስ ይላል ይህንን አምጣ አለው ፤

ወሕርዕ ወተቀባዕ ኀበ እበጥኒ ወተሐዩ ፣

ደቁሰህ ያበጠውን ቅባው ትድናለህ አለው ፤

፳፫፡ ወይቤ ሕዝቅያስ ምንት ትእምርቱ ከመ እዕርግ ውስተ ቤተ እግዚአብሔር ፣

ሕዝቅያስ (ከደዌዬ ተፈውሼ) ወደ ቤተ እግዚአብሔር እንድወጣ ምልክቱ ምንድን ነው አለ፣ እስከ ሠሉስ ዕለት ተዐርግ ውስተ ቤተ እግዚአብሔር አለው ይላል በነገሥት እንዲህ ቢለው በምንት አአምር ከመ [illegible]

እግዚአብሔር ከደዌዬ ተፈውሼ ወደ ቤተ እግዚአብሔር እንድወጣ በምን አውቀዋለሁ አለው ወናሁ ይወርድ ጽላሎት ዲበ ዐሥርቱ መዐርጋት ብሎታል የተሳለፈ ቀለም ነው፤ አንድም ወይቤ ሎሙ ኢሳይያስ ለአግብርተ ሕዝቅያስ ንሥዑ አጽቀ በለስ ቈጽለ በለስ ፍሬ በለስ ደመ በለስ ወሕርዑ ወቅብዑ እበጠ ለእግዚእክሙ ኀበ እበጡ ለእግዚእክሙ ወየሐዩ ይላል፣ ይህንን ደቁሳችሁ ያበጠውን ቅቡት ይድናል አላቸው፣ ዝኒ ትእምርቱ ምልክቱ ይህ ነውን አሉ፡ ይኸውም የመናቅ የማቃለል አይደለም የማድነቅ የማስተዋል ነው ::

ምዕራፍ ፴፱

፩፡ ወውእተ አሚረ ለአከ መሮዳህ ንጉሠ ባቢሎን በልዳንሃ ወልደ በልዳን ፣

ያንጊዜ የባቢሎን ንጉሥ መሮዳህ የበልዳንን ልጅ በልዳንን ላከ፡

ወመጻሕፍተ ፣

ይህን ያህል ግብር ቀረ፣ ይህን ያህል ግብር መጣ የሚል ደብዳቤ ላከ፣ አንድም ተግሣጽ ሰሎሞንን ላከ ፤

ወተናብልተ ፣

[illegible]

ወአምጻ ኀበ ሕዝቅያስ ፣

እጅ መንሻውን ወደ ሕዝቅያስ ላከ ፤

አስመ ሰምዐ ከመ ደዌየ ወበጽሐ ለመዊት ወሐይወ ፣

ታሞ ለሞት ከደረሰ በኋላ እንደዳነ ሰምቷልና ይህስ እንደምነው ቢሉ ሕዝቅያስ ከደዌው በተፈወሰ ጊዜ ሠርክ የነበረው ተመልሶ ሠለስት ሆነ፣ ተአምራቱ ከሁሉ ደርሷል፣ የባቢሎን ንጉሥ መሮዳህ ዛሬ ሠርክ የነበረው ተመልሶ ሠለስት የሆነበት ነገሩ ምንድን ነው ብሎ ጠየቀ፣ ደግሞው ንጉሥ ሕዝቅያስ ከደዌው የተፈወሰበት ቀን ነውአሉት፣ ለዚህስ ባይገብሩ እግዚአብሔር ዕዳ ይላል ብሎ እጅ መንሻ ሰደለታል ፤

፪፡ ወተፈሥሐ ሕዝቅያስ በእንተ አሠሙ ወቤየ ፍሥሓ ፣

ሕዝቅያስ መልክተኞች ስለመጡ ፈጽሞ ደስ አለው፤ አንድም በእንቲአሁ ይላል፣ በመሮዳህ ግብር መላክ ደስ ተሰኘ ፤

ወአርአዮሙ ቤተ ኒቆታሁ ፣

ሕዝቅያስን አንዳንድ ጊዜ ትዕቢት አያጣውምና እኔ የምሻው ፍቅር ነው እንጂ የገንዘብስ ድህ አይደለሁም ብሎ ዕቃ ቤቱን አሳያቸው ፤

www.ethiopianorthodox.org

ወርቆ ወብሩሮ ፣

ወርቁን ብሩን ፤

ልብሶ ወልብኖ ፣

ልብሱን ልባንጃ ሽቱውን ፤

ዕንቈ ወዕጣናተ ፣

ዕንቍን ዕጣኑን ፤

ወኵሎ ንዋየ ቤተ ጊዛን ፣

በቃ ቤት ያለውን ገንዘብ ሁሉ፤

ወኵሎ ዘውስተ መዛግብቲሁ ፣

በሣጥን ያለውን ገንዘብ ሁሉ አሳ ያቸው ፤

ወአልቦ ዘተርፈ ዘኢያርአዮሙ ሕዝ ቅያስ ፣

ሕዝቅያስ ያላሳያቸው የለም፤ አን ድም ሳያሳያቸው የቀረ የለም፤

ዘውስተ ቤቱ ፣

እንደ ጐንደር ያለውን ፤

ወዘውስተ ምኵናኑ ፣

እንደ ፀዳ ያለውን፤ አንድም ዘው ስተ ቤቱ እንደ ጐንደር እንደ ፀዳ ያለውን ወዘውስተ ምኵናኑ እንደ አሪንጎ እንደ ይባባ ያለውን ያላሳያቸው የለም (እንደ ጐንደር ባለቤቱ ብትልም ይሆናል) ፤

፫፡ ወመጽአ ኢሳይያስ ኀበ ሕዝቅያስ ንጉሥ ፣

ኢሳይያስ ወደ ሕዝቅያስ መጣ፤

ወይቤሎ ምንተ ይቤሉከ እሉ ዕደው፣

እሉ ሳዊኝ ምን አሉህ አለው፤

ወእምአይቴ መጽኡ ኀቤከ ፣

ወደ አንተ ከወዴት መጡ ፤

፬፡ ወይቤሎ ሕዝቅያስ ለኢሳይያስ፣

ሕዝቅያስ ኢሳይያስን እንዲህ አለው ፤

እምርኁቅ ብሔር መጽኡ ኀቤየ እም ባቢሎን ፣

እምርኁቅ ብሔርና እምባቢሎን አንድ ወገን ከሩቅ አገር ከባቢ ሎን ወደኔ መጥተዋል፤ አንድም ከወዴት መጥተዋል አለ፣ ከሩቅ አገር መጥተዋል አለው፣ ከወዴታ ቢለው ከባቢሎን አለው፤

፭፡ ወይቤሎ ኢሳይያስ ምንተ ርእዩ በቤትከ ፣

ኢሳይያስ በቤትህ ምን አዩ አለው ፤

ወይቤሎ ሕዝቅያስ ኵሎ ንዋየ ዘው ስተ ቤትየ ርእዩ ፣

ሕዝቅያስ በቤቴ ያለውን ገንዘብ ሁሉ አዩ አለው ፤

ወአልቦ ዘኢርእዩ ዘሀሎ ውስተ ቤትየ ወዓዲ ዘውስተ መዛግብትየሂ ፣

በቤቴም በቃ ቤትም ካለው ሁሉ ያላዩት የለም አለው ፤

፮፡ ወይቤሎ ኢሳይያስ ለሕዝቅያስ ስማዕኬ ቃለ እግዚአብሔር ፀባዖት፣

ኢሳይያስ ሕዝቅያስን አሸናፊ እግዚአብሔር የተናገረውን ነገር ስማ አለው ፤

፯፡ ናሁ መዋዕል ይመጽእ ፣

እነሆ እንዲህ ያለ ወራት ይመ ጣል ፤

ወይነሥኡ ኵሎ ዘውስተ ቤትከ ፣

በቤትህ ያለውን ገንዘብ ሁሉ ይወስዱታል ፤

ወኵሎ ዘዘገቡ አበዊከ እስከ ዛቲ ዕለት ወይወስዱ ባቢሎን ፣

አባቶችህም እስከ ዛሬ ድረስ የሰበሰቡትን ገንዘብ ሁሉ ወደ ባቢሎን ይወስዱታል ፤

ወአልቦ ዘየኀድጉ ለከ ፣

የሚተዉልህ የለም ፤

፰፡ ወዓዲ ውሉደከሂ ዘወለድከ ዘወ ፅኡ እምሐቋከ ፣

ዳግመኛ የወለድሃቸውን ልጆች ህን ካብራክህ የወጡትን ፤

ይነሥእዎሙ ፣

ማርከው ይወስዷቸዋል ፤

ወይሬስይዎሙ ደቀ ጽርሕ ወገዛዕተ ለቤተ ንጉሠ ባቢሎን ፣

ማርከው ወስደው የእልፍኝ አሽ ከር ደቀ ጽርሕ መንቀል አጣኝ ለባቢሎን ንጉሥ ዳታን አሳላፊ ዙፋን ጠራጊ ያደርጓቸዋል ፤

፱፡ ወይቤሎ ሕዝቅያስ ለኢሳይያስ፣

ሕዝቅያስ ኢሳይያስን እንዲህ አለው ፤

ሠናይ ውእቱ ቃለ እግዚአብሔር ዘይቤ ፣

ሕዝቅያስን አንዳንድ ጊዜ ክፋት አያጣውምና እግዚአብሔር የተ ናገረው ነገር መልካም ነው አለ፤

ወባሕቱ ጽድቅ ወሰላም ይኩን በመ ዋዕልየ ፣

ነገር ግን በዘመኔ ተድላ ደስታ በጎ ነገር ይደረግ፣ አንድም በዘ መኔ ተድላ ደስታ ይደረግ እንጂ ኋላስ እንደ ወደደ አለ ::

ምዕራፍ ፵

፩፡ ገሥጽዎሙ ለሕዝብየ ይቤ እግ ዚአብሔር ፣

ነቢያት ካህናት ወገኖቼን ምከ ሯቸው፣ አስተምሯቸው አለ እግ ዚአብሔር ፤

፪፡ ካህናቲሃኒ ንብዋ ለኢየሩሳሌም ውስተ ልባ ፣

ዘይበውእ ያለበት ነው ፤ ካህና ቱም ኢየሩሳሌምን ከልቧ ጥልቅ ብሎ የሚገባ ነገርን ንገሯት ፤

ወገሥጽዋ ፣

ምከሯት አስተምሯት ፤

እስመ በዝኀ ኀሣራ ፣

ኃጢአቷ በዝቷልና ፤

ወተርፈ ኃጢአታ ፣

በዝኀ ያለውን ተርፈ ኀሣራ ያለ ውን ኃጢአታ ብሎ ደገመው፤

www.ethiopianorthodox.org

ወተፈድየት እምእደ እግዚአብሔር ካዕበተ ኃጢአታ ፤

የኃጢአቷ እጽፍ የሚሆን ፍዳ ዋን ከእግዚአብሔር እጅ ተቀበለች ፤

ጉባዔ

፫፡ ቃለ ዐዋዲ በገዳም ፤

ይሰማዕ ያለበት ነው የአዋጅ ነጋሪ የኢሳይያስ ቃል ይሰማል፤

ሂሑአ ፍኖቶ ለእግዚአብሔር ፤

ለእግዚአብሔር መንገድ ጥረጉ፤

ወፀርዩ መጽያሕቶ ለአምላክክሙ ፤

ለፈጣሪያችሁ መንገድ ጥርጊያ አድርጉ ፤

፬፡ ኑሉ ማዕምቅ ይምላእ ወኮሉ ደብር ወአውግር ይተሐት ፤

ጕድጓዳው ይምላ፣ ተራራው ኮረብታው ሁሉ ይተካከል ፤

ወይኩን ኑሉ መብአስ መጽያሕተ ፣

ጕዳፕዱ ሁሉ የቀና ይሁን ፤

ወይኩን ቁላተ ምድር ርኁበ ፤

ሸለቆው ሁሉ የሰፋ ይሁን የሚል ያዋጅ ነጋሪ ቃል ይሰማል፤ በልማደ ንጉሥ ተናግሮታል፣ ንጉሥ በመጣ ጊዜ ተራራው ተንዶ ጉድጓዳው መልቶ ጕዳፕዱ ቀንቶ ይቆየዋል ፣ ትሩፋንም በወጡ ጊዜ ይህ ሁሉ ተደርጓልና ለአምላክክሙ ማለቱ በረድኤት ስላልተለያቸው ነው፤ አንድም ቃለ ዐዋዲ ብለህ መልስ፤ ኢሳይያስ በምድረበዳ ሲያስተምር ይሰማል ፤

ሂሑአ ፍኖቶ ለእግዚአብሔር ፤

ለእግዚአብሔር ማደሪያ ሊሆን ልቡናችሁን ከኃጢአት ከጣዖት ጥርጊያ አድርጉ እያለ ሲያስተምር ይሰማል ፤

ወፀርዩ መጽያሕቶ ለአምላክክሙ ፤

ለፈጣሪያችሁ ማደሪያ ሊሆን ልቡናችሁን ከኃጢአት ከጣዖት ጥርጊያ አድርጋችሁ አሳዩ ፤

ኑሉ ማዕምቅ ይምላእ ወኮሉ ደብር ወአውግር ይተሐት ፤

በኃጢአት በጣዖት ያልተካከለው በአሪት የተካከለ ይሁን ፤

ወይኩን ኑሉ መብአስ መጽያሕተ፣

በኃጢአት በጣዖት ጕጓጅጽ የሆነው ሁሉ በአሪት የተካከለ ይሁን አንድም ፤

ኑሉ ማዕምቅ ይምላእ ፤

በቀቢፀ ተስፋ የሚኖር ልቡና ተስፋ ሚጠትን ይያዝ ፤

ወኮሉ ደብር ወአውግር ይተሐት፣

በልዕልና የሚኖሩ የባቢሎን ነገሥታት መኳንንት ይዋረዱ ፤

ወይኩን ኑሉ መብአስ መጽያሕተ ወይኩን ቁላተ ምድር ርኁበ ፤

ሰባ ዘመን በኃጢአት በጣዖት ፀንቶ ይኖር የነበረ የሰው ሁሉ

ልቡና ጥርጊያ ጕዳና ይሁን የሚል የኢሳይያስ ቃል ይሰማል፤

፭፡ ወያስተርኢ ስብሐተ እግዚአብሔር ፤

የእግዚአብሔር ተአምራቱ ይገለጥ ፤

ወይርአይ ኑሉ ዘነፍስ መድኀኒተ እግዚአብሔር ፤

ሥጋዊ ደማዊ ሁሉ ሚጠትን ይይ፤ አንድም ቃለ ዐዋዲ በገዳም ዮሐንስ በምድረ በዳ ሲያስተምር ይሰማል፣ ቀላዔ እንጂ ማለት ቃለ ዓዔ ማለት ነው ፤ ቃለ ክርስቶስ ሲል ቃለ ዐዋዲ አለ፤ አንድም ቃለ ዐዋዲ ሳይና በብ ነው አካላዊ ቃልን የሚያስተምር ዮሐንስ ይሰማል፣ ቃለ ዐዋዲ ይላል ዙሮ የሚያስተምር ዮሐንስ ይሰማል ቃል ዘይኬልሕ እንዲል ፤

ሂሑአ ፍኖቶ ለእግዚአብሔር ወፀርዩ መጽያሕቶ ለአምላክክሙ ፤

ዮሐንስ ለእግዚአብሔር ማደሪያ ሊሆን ልቡናችሁን ከኃጢአት ከጣዖት ከአሪት ጥርጊያ አድርጉ፤ ጥርጊያ አድርጋችሁ አሳዩ እያለ ሲያስተምር ይሰማል፤

ኑሉ ማዕምቅ ይምላእ ወኮሉ ደብር ወአውግር ይተሐት ፤

በኃጢአት በጣዖት በአሪት ያልተካከለው ሁሉ በወንጌል የተካከለ ይሁን፤ አንድም፤ ኑሉ ማዕምቅ ይምላእ ፤

ዓሣ ወጋሪ ልብደ ሠሪ የነበሩ ሐዋርያት ልጅነትን፣ ልዕልና ነፍስን ያግኙ ፤

ወኮሉ ደብር ወአውግር ይተሐት፣

ካህናተ አሪት ይዋረዱ ፤

ወይኩን ኑሉ መብአስ መጽያሕተ ወይኩን ቁላተ ምድር ርኁበ ፤

በኃጢአት በጣዖት በአሪት ጕጓጅጽ የሆነ ሁሉ በወንጌል የተካከለ ይሁን ፤

ወያስተርኢ ስብሐተ እግዚአብሔር፣

የእግዚአብሔር ተአምራቱ ይገለጥ፤ አንድም ልጅነት ክብር ይገለጥ ፤

ወይርአይ ኑሉ ዘነፍስ መድኀኒተ እግዚአብሔር ፤

ሥጋዊ ደማዊ ሁሉ ድኀነተ ዓለም የሚደረግበት ወልድን ይይ ፤

፮፡ እስመ እግዚአብሔር ነበበ ቃለ ዘይብል ክላእ ወበል ፤

እግዚአብሔር አሰምተህ አስተምር የሚል ቃል ተናግሯልና፤

ወአቤ ምንተ እኬልሕ ፤

ምን ብየ አስተምራለሁ ፤

ኑሉ ዘሥጋ ከመ ሣዕር ፤

ሥጋዊ ደማዊ ሁሉ እንደ ሣዕር ሁኗል ማለት ለሣር አእምሮ እንደ ሌለው አእምሮ የሌለው ሁኗል፤ አንድም እግዚአብሔር

www.ethiopianorthodox.org

እንዲህ ብለህ አስተምር ብሎኛልና ምን ብዬ ላስተምር አልሁት ሰው ሁሉ እንደ ሣር ሁኗል ብለህ አስተምር አለኝ ፤

ወኮሉ ክብሩ ለሰብእ ከመ ፍሬ ሣዕር ፤

የሰው ሁሉ ክብሩ፤ አንድም አእምሮው እንደ ሣር ፍሬ ይጠፋል፤

፰፡ ይዮብስ ሣዕሩ ወይወድቅ ፍሬሁ፤

ሰውነቱ ልጁ ይጠፋል ፤

እስመ መንፈስ እግዚአብሔር ይነ ብብ ቦቱ ፡

መንፈስ ቅዱስ በሰው ጥፋት ተናግሮበታልና ፤ አንድም ብየ መንፈስ ቅዱስ በኔ አድሮ ተና ግሯልና ፤

አእኩ ሣዕር ሕዝብ ፤

ሣዕር የተባሉ ሕዝቡ ናቸውና፤

፰፡ ይየብስ ሣዕር ፤

ሰውነቱ ይጠፋል ፤

ወይትነገሩ ጽጌ ፤

ተድላ ደስታው ይጠፋል ፤

ወቃለ እግዚአብሔርሰ ይነብር ለዓለም ፤

እግዚአብሔር የተናገረው ነገር ግን ለዘለዓለም ፀንቶ ይኖራል፤

፱፡ ውስተ ደብር ነዋኅ ይዕርግ ዘይ ዜንዋ ለጽዮን ፤

ለጽዮን የሚጠትን ነገር የሚነ ግራት ወደ ተራራ ይውጣ በሀ ገራቸው ወሬ የሚያወራ ልብስ የሚያጥብ ራስ የሚላጭ ባለ ወግ አለና ፡

ክላሕ በኀይልከ ፤

አሰምተህ አስተምር ፤

ወአንሥእ ቃለከ ወዜንዋ ለኢየሩሳ ሌም ፤

ቃልህን ከፍ ከፍ አድርገህ የሚ ጠትን ነገር ለኢየሩሳሌም ንገ ራት ፤

፲፡ ክልሑ ወኢትፍርሁ ፤

ነቢያት ካህናት ጩኹ አትፍሩ ሚለት አስተምሩ ፤

ወበልዎን ለአህጉረ ይሁዳ ፤

ነገደ ይሁዳን እንዲህ በሏቸው፤

፲፩፡ ነዋ እግዚአብሔር አምላክከሙ ይመጽእ ምስለ ኀይሉ ፤

እነሆ ፈጣሪያችሁ እግዚአብሔር በዘሩባቤል አድሮ ይመጣል ፤

ወይኬንን በመዝራዕቱ ፤

ዘሩባቤል በሥልጣኑ ይፈርዳል፤

ወነዋ ዕዜቱ ምስሌሁ ፤

የምግባሩ ዋጋ ሚጠት የሃይማ ኖቱ ዋጋ መንግሥት ከሱ ጋራ አለ ፤

ወምግባሩ ቅድመ ገጹ ፤

በዘሩባቤል በፊቱ ትእምርተ መንግሥት አለ፣ ሰንደቅ ይተከ ላል ዓላማ ይ[illegible]

(መለከት) ይነፋል ድብ አንበሳ በፊቱ ይሳባል ኒጋሪት ይመታል፤ አንድም ወበልዎን ለአህጉረ ይሁዳ ብለህ መልስ ፤

የምዕመናን ወግኖችን ጌታ መላ እክትን አስከትሎ ይመጣል በሷ ቸው፤ አንድም ተአምራት ከሣ ድረግ ጋራ ይመጣል በሷቸው፤

ወይኬንን በመዝራዕቱ ፤

በሥልጣኑ ተነድገ ለከ ኃጢአ ትከ ተነድገ ለከ ኃጢአትከ. ፈቀድኩ ንጻሕ ተንሥእ ንሣእ ዓራተከ እያለ ይፈርዳል ፤

ወነዋ ዕዜቱ ምስሌሁ ፤

የሥጋው የደሙ ዋጋ አዳም ከሱ ጋራ አለ ፤ አንድም ለጻድቃን የሚሰጠው ክብር ገንዘቡ ነው፤

ወምግባሩ ቅድመ ገጹ ፤

ሠላሳ ሦስት ዓመት በፊቱ ተአም ራት ይደረጋል፣ ሙት ይነሣል፣ ድውይ ይፈወሳል፣ ለምጽ ይነ ጻል ፤ አንድም ሦስት ዓመት ከሦስት ወር አስቀድሞ ሠላሳ ዘመን በፊቱ ተአምራት ይደረ ጋል፤ አንድም በአካለ ነፍስ ሲኦል ወርዶ ነፍሳትን ከማውጣቱ አስ ቀድሞ በእግረ መስቀል ተአም ራት ይደረጋል ፤ ካምስት መቶ የሚበዙ ከስድስት መቶ የሚያ ንሱ ሙታን ተነሥተዋልና ፤

፲፪፡ ወያስተጋብዕ አሳግዒሁ በመዝ ራዕቱ ፤

ዘሩባቤል እስራኤልን በሥልጣኑ ይሰበስባቸዋል፤ አንድም ጌታ ምዕ መናንን በሥልጣኑ ይሰበስባቸ ዋል ፤

ወያስተፈሥሖን ለጽኑሳት ፤

ሰባ ዘመን የተቸገሩ እስራኤልን ዘሩባቤል ብዕለ አሕዛብን ዘርፎ ደስ ያሰኛቸዋል፤ አንድም አም ስት ሺህ ካምስት መቶ ዘመን ከልጅነት ከክብር የተቸገሩ ምዕ መናንን ጌታ ልጅነትን ክብርን ሰጥቶ ደስ ያሰኛቸዋል ፤

፲፫፡ መኑ ዘሠፈሮ ለማይ በኀፍኑ ፤

ዘለፋ ጣዖት ነው፤ ውሀውን በእ ፍኙ የሰፈረው ማነው እኔ ነኝ ወይስ ጣዖት ፤

ወለሰማይኒ በሥዝሩ ፤

ሰማይንስ በስንዝሩ የሰፈረው ማነው? እኔ ነኝ ወይስ ጣዖት ፤

ወዘአኀዛ ለኮላ ምድር ፤

ዓለምን እንደ ጥና እንደ ዕንቁ ላል በመሀል እጁ የያዛት ማነው እኔ ነኝ ወይስ ጣዖት ፤

፲፬፡ መኑ አቀሞሙ ለአድባር በመ ዳልው ፤

ተራሮችን መጥኖ መጥኖ የፈ ጠራቸው ማነው ፤

www.ethiopianorthodox.org

ወለአውግርኒ በመድሎት ፤

ከረብታዎችንስ መጥኖ መጥኖ የፈጠራቸው ማነው እኔ ነኝ ወይስ ማየት ፤

፲፯፡ መኑ አእመረ ሕሊናሁ ለእግ ዘአብሔር ፤

እግዚአብሔር ይህን ዓለም ልፍጠር ብሎ ያሰበውን አሳቡን ማን አወቀ አንድም ሰው ልሁን ሥጋ ልልበስ ብሎ ያሰበውን አሳብ ማን አወቀ ?

ወመኑ መማክርቲሁ ዘአምህሮ ፤

ይህን ዓለም ፍጠር ብሎ የመከረው ማነው፤ አንድም ሰው ሁን ሥጋ ልበስ ብሎ የመከረው ማነው ፤

፲፩፡ ወምስለ መኑ ተማከረ ፤

ይህን ዓለም ልፍጠር፣ አንድም ሰው ልሁን ሥጋ ልልበስ ብሎ ከማን ጋራ ተማከረ ፤

ወአምህሮ ፤

ይህን ዓለም ፍጠር ፤ አንድም ሰው ሁን ሥጋ ልበስ ብሎ ማን መከረው ፤

ወመኑ አርአዮ ፍትሐ ፤

ይህን ዓለም የሚፈጥርበትን አምሳል መርገፍ ማን አሳየው፤ አንድም ድኅነተ ዓለም በካሳ ይሁን ብሎ የፈረደውን ማን ገለጠለት፤

ወፍናተ ጥበብኒ መኑ አርአዮ ፤

ለእመ በላዕክሙ እምእንትኩ ዕፅ ሞተ ትመውቱ ያለውን ማን ገለጠለት፤ አንድም ዲያብሎስን ሲያወጣ በዲያብሎስ ስፍራ አዳምን ሲያገባ ፍርድን ማን ገለጠለት ፤

፲፫፡ ኮሎሙ አሕዛብ ከመ ነጥበ ማሕየብ እሙንቱ ፤

ሰዎች ሁሉ በአብሻት (የውሃ መቅኛ) ላይ እንደ ወደቀ ጠብታ ናቸው ፤

ወከመ እንተ ታገብእ ዐይነ መዳልው እሙንቱ ፤

የሚዛን ውልብልቢት እንደም ትመልስ እንደ ሰናፍጭ ቅንጣት ናቸው ፤

ወከመ ወኢምንት እሙንቱ ፤

እንደ ኢምንት ናቸው ፤

፲፮፡ ወኢየአክል ሊባኖስ ለእንድዶ፣

እንደ አምላክነቱስ የደጋው እንጨት ማገዶ ሊሆን አይበቃም፤

ወኮሉ እንስሳ ለአቃርዮ ፤

ለሠዊዕ ሲል ነው እንስሳት ሁሉ መሥዋዕት ሊሆኑ አይበቁም፤

፲፱፡ ወኮሉሙ አሕዛብ ከመ ዘኢሀ ለዉ ፤

አሕዛብ ሁሉ ሳሉ እንደ ሌሉ ናቸው፣ አንድም ካሉ ከሌሉ አይታወቁም ፤

ወከመ ወኢምንት ይመስሉ ፤

እንደ ኢምንት ናቸው ፤

፳፡ በመኑ ታስተማስልዎ ለእግዚአ ብሔር ፤

እንዲህ የሚሆን እግዚአብሔርን በማን ትመስሉታላችሁ ፤

ወበአምሳለ መኑ ታስተዐርይዎ ፤

ከማን ምስል ማንስ ከመሰለው ምስል ጋራ ታስተካክሉታላችሁ፤

፳፩፡ በምስልኑ ዘገብሮ ፀራቢ ፤

እንጨት ጠራቢ በሠራው ምስል ነውን ፤

ወሚመ በወርቅኑ ዘሰበኮ ነሀቢ ፤

ወይስ ጃን ሸላሚ መትቶ በሠራው በወርቅ ትመስሉታላችሁን ፤

ወዘቀፈሉ በወርቅ ወገብሮ ወመሰሎ፣

አንጥረኛ ወርቅ ለብጦ መስሎ በሠራው ምስል ትመስሉታላችሁን ፤

፳፪፡ እስመ ዕፀ ዘኢይነቅዝ ዮነሪ ሎቱ ፀራቢ ፤

እንጨት ጠራቢ የማይነቅዝ እንጨትን ይመርጣልና ማለት ጣዖት የሚሠራ ሰው የማይነ ቅዘውን እንጨት ይመርጣልና፤

ወበጥበቡ ዮነሥሥ ዘከመ ያቀውም ምስሌ ከመ ኢያንቀልቅል ፤

ከልቡ ባነቃው ጥበብ እንዳይ ነዋወጥ አድርጎ ምስሉን የሚ ያቆምበትን ነገር ይፈልጋልና፤

፳፫፡ ኢየአምር ወኢይሰምዕ ፤

እንዲህ አድርጎ የሠራው ሰው አያውቅም አይሰማም፤ አንድም ጣዖቱ አያውቅም አይሰማም፤

ወኢይነግረክሙ ዘትካት ፤

በቀዳሚ ገብረ እግዚአብሔር ሰማየ ወምድረ ያለውን አይነግራችሁም ፤

ወኢየአምር መሠረተ ምድር ፤

መሠረተ ምድርን አያውቅም፤ ከታች ነፋስ፣ ቀጥሎ እሳት፣ ቀጥሎ ውሀ፣ ቀጥሎ መሬት መሆኑን አያውቅም ፤

ዘያፀንዕ አጽናፈ ምድር ፤

አጽናፈ ምድርን ያፀናበትን አያውቅም፤ አንድም አጽናፈ ምድርን ያፀና እሱ ነው ፤

፳፬፡ ወእለሂ ይነብሩ ውስቴታ ከመ አንበጣ ፤

በውስጧም የሚኖሩ ሰዎች እንደ አንበጣ የተናቁ ናቸው፤

ዘሰፍሖ ለሰማይ ከመ ቀመር ፤

ሰማይን እንደ ሙሴ ድንኳን የዘረጋው እሱ ነው፤ ብስጉን ሲያይ እንዲህ አለ፤

ወተከለ ከመ ደብተራ ማኅደር ፤

ከሙሴ ከአሮን ጋራ ያድርባት የነበረ፤

www.ethiopianorthodox.org

፳፭፡ ወይሬስዮሙ ለመላእክት ከመ
አልቦ ዘይትኤዘዝ ሎሙ ፣
ለነብልጣሶር፤ ለነሰናክሬም አለ
ቆች የሚታዘዝላቸው እንዳይኖር
የሚያደርግ እሱ ነው ፤

ወገብራ ለምድር እምኀበ ወኢምንት፣
ምድርን እምኀበ አልቦ አምጥቶ
የፈጠራት እሱ ነው ፤

፳፮፡ ወአብቈለ ላዕሌሃ ያመ ወሣዕረ፣
ሣሩን ዛፉን በላይዋ ላይ ያበቀ
ለባት እሱ ነው ፤ አንድም ጥቃ
ቅኑን ታላላቁን ዛፍ አዝርዕትን
አትክልትን አበቀለባት ፤

ወባዕደኒ ብዙኀ ፍጥረታተ ዘኢይት
ኄለቍ ፣
ሌላም የማይቈጠር የማይሰፈር
ብዙ ፍጥረትን የፈጠረ እሱ ነው ፤

ወእምከመ ነፍሐሙ ነፋስ ይየብሱ፣
መዓት መቅሠፍት በመጣባቸው
ጊዜ ይጠፋሉ ፤

ወይነሥኦሙ ዐውሎ ከመ ሐሠር ፣
ዐውሎ ነፋስ ገለባውን እንዲወ
ስድ መዓት መቅሠፍት ያጠፋ
ቸዋል ፤

፳፯፡ ወይእዜኒ በመኑ ታስተማስሉኒ ፣
አሁንስ እንዲህ የማደርግ እኔን
በምን ትመስሉኛላችሁ ፤

ወእትሜካሕ ይቤ እግዚአብሔር
ቅዱስ ፣
አምላክነቱን አስረዳና ፅኑዕ
ክቡር የሚሆን እግዚአብሔር

፳፰፡ አንሥኡ አዕይንቲክሙ ውስተ
ሰማይ ወርእዩ ፣
ስንኳን ከኔ ከፈጠርሁት ከሰ
ማይ ትደርሱ እንደሆነ አንገ
ታችሁን አቅንታችሁ እዩ ፤

መኑ ዘገብረ ዘንተ ኵሎ ፣
ይህን ሁሉ (የፈጠረ) ያደረገ
ማነው ፤

ዘይኋልቆሙ ለክዋክብት በምልዖሙ፣
ከዋክብትን ፈጽሞ የሚቈጥራ
ቸው እሱ ነው ፤

ወያመጽኦሙ በበዕድሜሆሙ ፣
በየጊዜያቸው የሚያመጣቸው
እሱ ነው ፣ የዘጠና አንድ ቀን
መጋቢ ፣ የወር መጋቢ ፣ የዕለት
መጋቢ የዕለት ፣ የሺ አለቃ አለና ፣

ወይጼውዖሙ ለኵሎሙ በበአስማቲ
ሆሙ ፣
ሁሉንም በየስማቸው የሚጠራ
ቸው እሱ ነው ፤ ሕልመልሜሌክ
ምልክኤል ምልኤል ናርኤል
ብሎ ፤

በብዝኀ ስብሐቲሁ ወበፅንዐ ኀይሉ
አልቦ ዘይትረስዖ ፣
በጌትነቱ ብዛት በከሃሊነቱ ፅናት
የሚዘነጋው የለም ፤

፳፱፡ ቦኑ ትብሎ ያዕቆብ ምንተ ነበ
ብከኒ ፣
ማእዜ ነበብከኒ ሲል ነው ፤ ያዕ
ቆብ በውኑ መች ነገርኸኝ ትለ
ዋለህን ፤

ተኀብዐት ፍኖትየ እምእግዚአብሔር ፣
ኃጢአቴ ከእግዚአብሔር ተሠ
ወረች ትለዋለህን ፤

ወርኀቀ አምላኪየ እምኔየ ፣
ፈጣሪዬ የኔን ኃጢአት ከማወቅ
ራቀ ትለዋለህን ፤

ወኀደገ ፍትሕየ ፣
ለኔ ሕግ መሥራትን ተወ ትለ
ዋለህን ፤ አንድም ቦኑ ትብሎ
ያዕቆብ ፤ ያዕቆብ በውኑ ምን
ትለዋለህ ፣

ምንተ ነበብከኒ ፣
ምን ሕግ ሠራህልኝ ትለዋለህን
ምናልህ ፣ ምን አልኸኝ ፣ ምን
ምን አልኸኝ ፤

ተኀብዐት ፍኖትየ እምእግዚአብሔር ፣
ኃጢአቴ ከእግዚአብሔር ተሠ
ወረች ትላለህን ምን አልኸ ፣
ምን አልኸኝ ፣ ምን ምን አል
ኸኝ ፤

ወርኀቀ እምኔየ አምላኪየ ፣
ፈጣሪዬ በኔ ከመፍረድ ራቀ
ትላለህን ፤

ወኀደገ ፍትሕየ ፣
በኔ መፍረድን ተወ ትላለህን
ምን አልህ ፣ ምን አልኸኝ ፣ ምን
[illegible]

፴፡ ወይእዜኒ ኢያእመርክሙኑ ወኢ
ሰማዕክሙኑ ከመ አነ ውእቱ አምላክ
ዘለዓለም ፣
ለዘለዓለም የምኖር ፈጣሪ እኔ
እንደሆንሁ አላወቃችሁም ?
አልሰማችሁም ?

ወከመ ውእቱ አምላክ ዘፈጠረ ሰማየ ፣
ሰማይን የፈጠረ አምላክ እንደ
ሆነ አላወቃችሁም ? አልሰማ
ችሁም ?

ወኵሎ አጽናፈ ምድር ፣
አጽናፈ ምድርን የፈጠረ እሱ
እንደሆነ አላወቃችሁም ፣ አልሰ
ማችሁም ፤

ኢይርኀብ ወኢይፀምዕ ፣
ይህንን እንዲህ አድርጎ የፈጠረ
እግዚአብሔር አይራብም ፤ አይ
ጠማም ፤ በባሕርዩ ረሀብ ፣ ፅምዕ
የለበትም ፣

ወኢይደክም ፣
በባሕርዩ ድካም የለበትም ፤

ወአልቦ ዘየአምር ምክሮ ፣
ምክሩን የሚያውቅ የለም ፤

፴፩፡ ወይሁቦሙ ኀይለ ለድኩማን ፣
ለድኩማን ኀይልን የሚሰጣቸው
እሱ ነው ፤

ወኢያቴክዞሙ ለእለ የሐምሙ ፣
በኃጢአታቸው መከራ የሚቀ
በሉትን አያሳዝናቸውም ፤

www.ethiopianorthodox.org

፴፪፡ ይርኅቡ መሐዛት ፣

መራብስ ጐልማሶችም ይራባሉ፡

ወይደክሙ ወራዙት ፣

ጐልማሶችም ይደክማሉ ፣

ወይፀብሱ ፅኑዓን ፣

ፅኑዓንም ይደክማሉ ፣

፴፫፡ ወእለሰ ይሴፈውዎ ፣

ዋጋችንን ይሰጠናል ብለው ተስፋ የሚያደርጉት ፣

ወይትዔገሥዎ ለእግዚአብሔር ፣

ለፈተና ብሎ መከራ ቢያመጣባቸው መከራውን ታግሠው የሚቀበሉ ሰዎች ፣

ይሔድሱ ውርዙቶሙ ወኀይሎሙ፣

ሰውነታቸውን ኀይላቸውን በረድኤት ያድሳሉ ፣

ወይበቍል ክነፊሆሙ ከመ ንስር፣

ሰውነታቸው እንደ ንስር ይታደሳል፤ ንስር ባረጀ ጊዜ ዐብዶ የሚባል ጭቃ አለ ያነን ተቀብቶ እንጨቱን ከምሮ ወያስተጣግዕ ክነፊሁ ክንፍና ክንፉን ያማታዋል ፣

ወይወፅእ እሳት እምአካለ ዝኩ ያፍ ፣ እንዲል ጊዮርጊስ ወልደ አሚድ ፤ ከአካሉ እሳት ወጥቶ እንጨቱን ያቃጥለዋል ፤ እሱም አብሮ ይቃጠላል፤ በግብፅ ዝናም ዘንሞ አያውቅም፤ ባምስት መቶ ባምስት መቶ ዘመን ለሐድሶተ ንስር እንደ ካፊያ ያለ ይዘንማል፤ በመጀመሪያ ቀን ትል ያህላል፤ በሁለተኛው ቀን ያፍ ያህላል፤ በሦስተኛው ቀን በሮ ይሄዳል፤ እንደዚህም ሁሉ በሚጠት ሰውነታቸው በረድኤት ይታደሳል፤

ይረውፁ ወኢይደክሙ ወኢይርኅቡ፣

ሲሄዱ ውለው ሲሄዱ ቢያድሩ አይደክሙም ፣ አይራቡም::

ምዕራፍ ፵፩

ጉባዔ

፩፡ ተመየጡ መንገሌየ ደሰያት ፣

ደሴት በውሀ ፣ ውሀ በደሴት እንዲከበብ በመከራ የተከበባችሁ እስራኤል በሕግ ፣ በአምልኮት ወደእኔ ተመለሱ ፤ አንድም ደሴት በውሀ ፣ ውሀ በደሴት እንዲከበብ ሰባ ዘመን በጦር የተከበባችሁ ትሩፋን በሕግ በአምልኮት ወደኔ ተመለሱ ፤ አንድም ደሴት በውሀ ፣ ውሀ በደሴት እንዲከበብ አምስት ሺህ ካምስት መቶ ዘመን በመከራ ነፍስ የተከበባችሁ ምዕመናን በሕግ በአምልኮት ወደኔ ተመለሱ ፤

እስመ ይትዌለጥ ኀይሎሙ ለመላእክት ፣

የባቢሎን አለቆች ኀይላቸው ወደ ድካም ይለወጣልና ፤ አንድም የሊቃነ አጋንንት ኀይላቸው ወደ ድካም ይለወጣልና ፤

ይቅረቡ ወይንግሩ ኀቡረ ወያይድዑ ፍትሐ ፣

እሊህ ነቢያተ ሐሰት ካህናተ ጣዖት እናውቃለን ይላሉ ፤ አንድ ሁነው ቀርበው የሚመጣውን ነገር እስኪ ይንገሯችሁ ፤

፪፡ መኑ አንሥኦ ለጻድቅ እምጽባሕ፣

ቂሮስን ከፋርስ ያስነሣው ማነው ፤

ወጸውዖ ፣

ቂሮስ ብሎ የጠራው ማነው ?

ወትተልውዎ ድኅረ እገሪሁ ፤

እግሩን ተከትላችሁ ትሄዳላችሁ ፤ ማራኪ በፊት ተማራኪ በኋላ ነውና ፤

ወያመጽእ ድንጋዔ ላዕለ አሕዛብ ወነገሥት ፣

በነገሥታቱ በሠራዊቱ ላይ ድንጋዔን ያመጣል ፤

ወያገድፎሙ ውስተ ምድር ኵያንዊሆሙ ፤

ጦራቸውን በምድር ያስጥላቸዋል ፤

ወከመ ሐሠር ይትነገፉ አቅስስቲሆሙ ፤

ቀስቶቻቸው እንደ ገለባ ይሆናሉ ፤

፫፡ ወይዴግኖሙ ፣

እየተከታተለ ይወጋቸዋል ፤

ወየሐውራ እገሪሁ ፍኖተ ሰላም ፣

እግረ ልቡናው በፍቅር ጐዳና ፀንቶ ይኖራል ፤ አንድም አሕዛብን ለጥፋት ይከተላቸዋል ፤ እግሮቹም የፍቅር ጐዳናን ይሄዳሉ ፤ ለትሩፋን ነው ፤

፬፡ መኑ ዘአፅንዓ ወገብረ ዘንተ ከመዝ፣

ሚጠትን ያፀና ማነው ፤ አንድም ውኀሊቆ ሰብዓ ዓመት ያለውን ያፀና ይህን ሁሉ ያደረገ ማነው?

ወጸውዖ እምፍጥረተ ዓለም ፣

ከጥንት ጀምሮ ቂሮስ ብሎ የጠራው ማነው ? አንድም ዓለም ከተፈጠረ ጀምሮ ቂሮስን የመረጠው ማነው ? አንድም ከሰባ ዘመን ከመጀመሪያው ጀምሮ ቂሮስ ብሎ የጠራው ማነው ?

አነ ውእቱ እግዚአብሔር ቀዳማዊ ወደኀራዊ አነ ውእቱ ፣

ቅድመ ዓለም የነበርሁ ፣ ዓለምን አሳልፌ የምኖር እኔ ነኝ ፤

፭፡ ርእዩ አሕዛብ ዘአጽናፈ ምድር፣

በጽንፈ ምድር በባቢሎን ያላችሁ አሕዛብ እዩ ፤

ወፍርሁ ወቅረቡ ወምጽኡ ኀቡረ ፣

ፍሩ አንድ ሁናችሁ ወደምት ጠፉበት ቦታ ኑ ፤

፮፡ ወኵሉ ይትዋቀሶ ለእኁሁ ፣

ወንድም ወንድሙን ይውቀሰው ፤

www.ethiopianorthodox.org

ወነሶሉ ይርዳእ ቢጾ ፤
ሁሉም ባልንጀራውን ይርዳ ፤
ወያዕንየ ብእሲ ለእኅዉ ፤
ወንድም ወንድሙን በምክር ያዕናው ፤
፮፡ ወእኮ ከመ ነህቢ ዘይበቀኖ አፍ ሐመ በምንሃብ ፤
ጀን ሸላሚ በአኅዶ በወናፍ እሳ ትን እንዲጭር ፤
ወያወዕል ወርቀ እምቁናማት ፤
ወርቁን ከዕቃ አቀኖማዳ እንዲ ያወጣ ፤
ወይደልዎ በመዳልው ፤
በሚዛን እንዲመዝነው ፤
ወይወድዮ ውስተ ሕንቅርት ማዕከለ እሳት ፤
በከውር አድርጎ በእሳት መካ ከል እንዲጥሰው ፤
ወያወዕሉ በጉጠት ወይዘብጦ በሰፌ ልያ ፤
በጕጠት አውጥቶ በመዶሻ እን ዲዐቃታው ፤
ወያፀንዖ ከመ ኢያንቀልቅል ፤
እንዳይነዋወጥ አድርጎ እንዲያ ዐናው አይደለም ማለት ያ ጥሮ ግሮ እንዲሠራው ጥሬ ማሬ የፈ ጠርሁህ አይደለም ?
፰፡ አንተሰ እስራኤል አኮ ከመዝ ዳዕሙ አኅዝኩከ በመዝራዕትየ ወተ መጠውኩከ በእዴየ ፤
እስራኤል ሳልጥር ሳልግር ፈጥ ሬሃለሁና በሥልጣኔ ያገዘሁህ እንጂ ፤ አንድም ያ ጥሮ ግሮ ሠርቶ እንዲያመልከው ጥረህ ግረህ ፈጥረህ የምታመልከኝ አይደለም፤ ሳልጥር ሳልግር ፈጥ ሬሃለሁና በሥልጣኔ ያገዘሁህ እንጂ ፤
ዘርዐ አብርሃም ዘአፍቀርኩከ ፤
የወደድሁህ የአብርሃም ልጅ ፤
፱፡ ወተመጠውኩከ እምአጽናፈ ምድር፤
ከባቢሎን በረድኤት ተቀበል ሁህ ፤
ወጸዋዕኩከ እምግበቢሃ ፤
ከባቢሎን ከተማ አወጣሁህ ፤
ወእቤለከ ገብርየ አንተ ፤
ባሪያዬ አንተ ነህ አልሁህ ፤
ወኢየነድገከ ፤
አልለይህም ፤
ውነረይኩከ ፤
መረጥሁህ ፤
፲፡ ወኢትፍራህ ሀሎኩ አነ ምስሌከ፤
እኔ ካንተ ጋራ በረድኤት አለ ሁና አትፍራ ፤
ወዑቅ ኢያስሕቱከ ፤
እንዳያስቱህ ዕወቅ ፤
አነ ውእቱ አምላክከ ዘአዕናዕኩከ ፤
በረድኤት ያፀናሁህ ፈጣሪህ እኔ ነኝ ፤

ወረዳእኩከ ወአኅዝኩከ በየማነ እዴየ፤
የረዳሁህ በሥልጣኔ የያዝሁህ እኔ ነኝ ፤
፲፩፡ ናሁ ይትኔፈሩ ወጽነሥሩ ኵሎሙ እለ ይትቃወሙከ ፤
አንተን የሚቃወሙህ ሰዎች ሁሉ ያፍራሉ፣ ይጐሰቍላሉ፤
ወይከውኑ ከመ ዘኢተፈጥሩ ፤
እንዳልተፈጠሩ ይሆናሉ፤ እንዳ ልነበሩ ይሆናሉ ብትል ይሆናል፤
ወይትኔሉ ኵሎሙ ፀርከ ፤
ጠላቶችህ ሁሉ ይጠፋሉ ፤
ወይትኔተሙ ፤
ለጥፋት ይቈጠራሉ ፤
፲፪፡ ተነሥሥሙ ወኢትረክቦሙ ለሰ ብእ እለ ይሣቅዩከ ፤
መከራ የሚያፀኑብህን ሰዎች ትሻቸዋለህ አታገኛቸውም ፤
ወይከውኑ ከመ ዘኢሀለዉ ፤
እንዳልነበሩ ይሆናሉ ፤
ወአልቦ እንከ ዘይፀብዐከ ፤
እንግዲህ ወዲህ የሚጣላህ የለም፤
፲፫፡ እስመ አነ አምላክከ ዘአዕናዕ ኩከ በየማንየ ፤
በሥልጣኔ ያፀናሁህ ፈጣሪህ እኔ ነኝና ፤
፲፬፡ ወእቤለከ ኢትፍራህ ያዕቆብ፤
ያዕቆብ አትፍራ አልሁህ ፤
ውጉድ አንተ እስራኤል ፤
እስራኤል አንሰህ ነበር አበዛሁህ፤ ተዋርደህ ነበር አከበርሁህ ፤
አነ ረዳእኩከ ይቤ እግዚአብሔር ዘአ ድኅነከ ቅዱሰ እስራኤል ፤
ያዳነህ ፅንዐ እስራኤል፣ ክብረ እስራኤል እግዚአብሔር እኔ ረዳሁህ አለ ፤
፲፭፡ ናሁ አነ ረሰይኩከ ከመ መንኰ ራኵረ ሠረገላ ዘየሐርስ ወይቈሥር፤
እነሆ እኔ እንደ ሠረገላ መንኰ ራኵር አደረግሁህ ፤ ያ ከበታቹ ያለውን እንዲያደቅ ፤
ወታደክም አድባረ ወተሐርዕ አው ግረ ፤
ኀጢአታቱን መኳንንቱን ታጠ ፋለህ ፤
ወትሬስዮሙ ከመ ፀበል ፤
እንደ ትቢያ ታደርጋቸዋለህ፤
፲፮፡ ወትደምቆሙ ፤
ትወጋቸዋለህ፤ አንድም ትጨ ፈልቃቸዋለህ ፤
ወይነሥአሙ ነፋስ ወይዘርዎሙ ዐውሎ፤
መዓት መቅሠፍት ያጠፋቸዋል፤
አንተሰ እስራኤል ተፈሣሕ ወተ ሠይ በቅዱሰ እስራኤል ፤
እስራኤል አንተ ግን በክብረ እስራኤል በጽንአ እስራኤል አም ነህ በውስጥ በአፍአ ደስ ይበ ልህ ፤

www.ethiopianorthodox.org

፲፮፡ ወይረክቡ ማየ እለ የጎሥሡ፣
ውሀውን የሚሹ ሰዎች በሰባ
ዘመን ዝናም ዘንሞ ውሀውን
ያገኛሉ ፤

ወእለ የብሰ ልሳኖሙ በፅምዕ ፣

ሰባ ዘመን አንደበታቸው በፅም
የተያዘ ሰዎች ውሀውን ያገኛሉ፤
በዔዋዊ ውሀ ደርቆባቸው ነበር፤
በሚጠት ውሀ ፈልቆላቸዋልና፤
አንድም ትምህርት የሚፈልጉ
አንደበታቸውም ከትምህርት
የተጠማ ሰዎች ትምህርት ያገ
ኛሉ፤ አንድም ልጅነትን የሚፈ
ልጉ አምስት ሺሕ ካምስት መቶ
ዘመን አንደበታቸው በፅምዐ ነፍስ
የተያዘ ምዕመናን ልጅነትን
ክብርን ያገኛሉ ፤

አነ ውእቱ እግዚአብሔር አምላክከ፣

ፈጣሪህ እግዚአብሔር እኔ ነኝ፤

ወአነ ሰማዕኩከ አምላከ እስራኤል ፣

የእስራኤል ፈጣሪ እኔ ሰማሁህ፤

ወኢዮነድኅሙ ፣

በረድኤት አልለያቸውም ፤

፲፯፡ አነቅዕ ሎሙ አፍላግ በውስተ
አደባር ፣

በተራራው ፈሳሹን ውሀ አፈል
ቅላቸዋለሁ፤ አንድም ከነቢያት
ከካህናት ትምህርትን ረድኤ
ትን አስገኛለሁ፤ አንድም ከጻጻ
ላት ፣ ከሊቃነ ጳጳሳት ክብርን
ልጅነትን አስጣቸዋለሁ ፤

ወአፈለፍል ማዕከለ ገዳም ፣

በምድረ በዳም ምንጮን አመነ
ጫለሁ ፤

ወአበቀሉል ያመ በውስተ በድው ፣

በምድረ በዳም ዛፍ አበቅላለሁ፤
አንድም ከሰባ ዘመን በኋላ
ትምህርት፣ ረድኤት እንዲገኝ
አደርጋለሁ ፤

ወአበቀሉል ንጉሥ እንዲነግሥ
ባት አደርጋለሁ ፤ አንድም በቀ
ራንዮ መስቀል እንዲተከል አደ
ርጋለሁ ፤ አንድም ሊቀ ጳጳስ
እሾማለሁ ፤

ወአውጎዝ ማየ በብሔረ ፅምዕ ፣

ፅምዕ ባለበት በኢየሩሳሌም ውሀ
ውን አፈሳለሁ ፤ አንድም ትም
ህርት ልጅነት እንዲሰጥ አደር
ጋለሁ ፤

፲፱፡ ወአሬስዩ ለምድረ በድው
ብሔረ አርዝ ፣

ምድረ በዳውን የዛፍ አገር አደ
ርገዋለሁ፤ አንድም ምድረ በዳ
የነበረች ኢየሩሳሌምን የዛፍ ቦታ
አደርጋታለሁ፤ አንድም የንጉሥ
የጳጳስ አገር አደርጋታለሁ ፤

ወዕባ ጳቅሶን ፣

አርዝ ያለውን ይተረትራል የሽ
ንኮር ፤

ወምርስኔን ፣

የብርስነት ፤

ወቄጽርሶን ፣

የሰኖባር ፤

ወሊውቄን ፣

ዘይት የነዚህ አገር አደርጋታ
ለሁ ፤ አንድም የአራቱ ሊቃነ
ጳጳሳት አገር አደርጋታለሁ ፤
አንድም በሐዲስ አራቱን ሊቃነ
ጳጳሳት እሾማለሁ ፤

፳፩፡ ከመ ያእምሩ ወይለብዉ ወይጠ
ይቁ ፣

ያውቁ ይረዱ ዘንድ ፤

ወይእመኑ ከመ እደ እግዚአብሔር
ገብረ ዘንተ ፣

ሥልጣነ እግዚአብሔር ይህን
ሁሉ እንዳደረገ ያምኑ ዘንድ ፤

ወቅዱሰ እስራኤል አርአየ ዘንተ ፣

ፅንዐ እስራኤል ክብረ እስራኤል
እግዚአብሔር ይህን ገለጠ፤

፳፪፡ ወአልጸቀት ኵነኔክሙ ይቤ
እግዚአብሔር አምላክ ፣

ፈጣሪ የሚሆን እግዚአብሔር
የሚፈርድባችሁ ጊዜ ደረሰ አለ፤
ዔዋዊ ነው ፤ አንድም የሚፈር
ድላችሁ ጊዜ ደረሰ አለ፤ ሚጠት
ነው ፤

ወቀርበ ምክርክሙ ይቤ ንጉሠ እስ
ራኤል ፣

የእስራኤል ንጉሥ እግዚአብሔር
ምክራችሁ ቀረበ አለ፤ ጣዖታቱን
እንዲህ ይላቸዋል ፤

፳፪፡ በጽሐክሙ ዘይረክበክሙ ፣

የሚያገኛችሁ ዔዋዊ (መከራ)
ደረሰባችሁ፤ አንድም የሚያገ
ኛችሁ ሚጠት ደረሰላችሁ ፤

ንግሩነ ዘቀዲሙ ፣

አስቀድሞ የሚሆን ዔዋዊን ንገ
ሩን ፤

ወናእምር ዘትሔልዩ ፣

የምታስቡት ሚጠትን እናውቅ
ዘንድ ፤

ወናእምር ደኃሪተክሙ ፣

ፍጻሜአችሁን እናውቅ ዘንድ፤

፳፫፡ ንግሩነ ዘይመጽእ ፣

የሚመጣውን ዔዋዊን አስቀድ
ማችሁ ንገሩን ፤

ወዘይከውን በደኃሪ ፣

በኋላ ዘመን የሚሆን ሚጠትን
ንገሩን ፤

ወናእምር ከመ አማልክት አንትሙ፣

እናንተ አማልክት እንደሆናችሁ
እናውቅ ዘንድ ንገሩን ፤ አሠንዩ
ማንሻ፤ አንድም አማልክት እንደ
ሆናችሁ እናውቅ ዘንድ ፤

አሠንዩ ወአሕስሙ ፣

ወዳጃችሁን ጥቀሙ ጠላታችሁን
ጉዱ ፤

ወናንክርክሙ ፣

እናድንቃችሁ ፤

www.ethiopianorthodox.org

፶፩፤ ወንጠይቅ ወናእምር እምአይቴ አንትሙ ፣

እናንተ ከየትም እንደሆናችሁ እንወቅ፤ እንረዳ ፤

ወእምአይቴ ገብሩክሙ ፣

ከየትም እንደ ሠሯችሁ ፤

አኮኑ እምድር ርኩስ ጎረዩክሙ ፣

ከርኩስ አገር ከፋርስ የመረጣ ችሁ አይደለምን፤ የፈረስ ምስል መመለክ የተጀመረ በፋርስ ነውና ምድር ርኩስ አለ ፤

፶፪፡ ወአነ አንሣእኩ ዘእምደቡብ፣

ከሚዶን ዳርዮስን ፤

ወዘእምሥራቀ ወሐይ ፣

ከፋርስ ቂሮስን አስነሣሁ ፤

ከሙ ይሰመይ በስምየ ፣

በስሜ ይጠራ ዘንድ ቂሮስ ማለት መሢሕ ማለት ነውና ፤

ለይምጽኡ መላእክት ፣

አለቆች ይምጡ ፤

ወከመ ለብሓዊ ዘይከይድ ዕቡሮ ፣

ሸክላ ሠሪ ጭቃውን እንዲረግጥ፤

ከማሁ ይከይድዎሙ ፣

በመከራ ይረጋግጧቸዋል ፤

፶፫፤ መኑ ዘይዜኑ ዘትካት ፣

ዔዋውያንን ዔዋዊን የሚናገር ማነው ፤

ከመ ናእምር ዘእምቅድሜሁ ፣

ከሱ አስቀድሞ የነበረ አባር ቸነ ፈርን እናውቅ ዘንድ፤ አንድም ሚጠትን የሚናገር ማነው ከሱ አስቀድሞ የሚሆን ዔዋዊን እና ውቅ ዘንድ ፤

ወንበል እሙን ውእቱ ፣

ነገሩ እውነት ነው እንል ዘንድ፤

ወአልቦኪ ዘያቀድም ነጊረ ፣

አስቀድሞ የሚናገር የለም ፤

ወአልቦ ዘይሰምዕ ነገረክሙ ፣

ነገራችሁን የሚሰማ የለም ፤

፶፬፤ ቀዳሚ አሁባ ለጽዮን ፣

ከመከራው አስቀድሞ ለጽዮን ተድላውን ደስታውን እሰጣታ ለሁ ፤

ወአገብኣ ውስተ ፍኖታ ለኢየሩሳ ሌም

ኋላ ግን ኢየሩሳሌምን ወደ መከ ራው እመልሳታለሁ፤ አንድም ዘቀዳሚሃ ቀዳሚሃ ይላል፤ ቀድሞ በግብፅ ትቀበለው የነበረውን መከራ አመጣባታለሁ ወአገብኣ አንድ ወገን ወደመከራው እመል ሳታለሁ ፤ አንድም ዘቀዳሚሃ አባቶቿ ይቀበሉት የነበረ መከ ራን እንድትቀበል አደርጋታለሁ፤ ወአገብኣ ዛሬ ግን ወደ ተድላ ወደ ደስታ እመልሳታለሁ፤ አን ድም ጽዮን ኢየሩሳሌምን አገ ብኣ፡

፶፭፤ እስመ አልቦ ለአሕዛብ እም አማልክቲሆሙ ዘይዜኑ ፣

ከአሕዛብ አማልክት አስቀድሞ የሚናገር የለምና ፤

ወእመኒ ተስእልዎሙ እምአይቴ እሙ ንቱ ኢይሠጠዉ ፣

ከየትም ከየት እንደሆኑ ቢጠ ይቋቸው አይመልሱም፤ አንድም ቢጠይቋቸውም ከየትም ከየት እንደሆኑ አይመልሱም ፤

፶፮፡ ወእለሂ ይገብርዎሙ ከንቶ ይፈ ጥርዎሙ ፣

የሚሠሯቸውም ሰዎች ላይረ ቧቸው ላይጠቅሟቸው በከንቱ ይሠሯቸዋል ::

ምዕራፍ ፶፪

ጌጣጌ

፩፤ ናሁ ቀሩልዔየ ዘአነገዝክዎ ፣

እነሆ በሥልጣኔ የያዝሁት ዘሩ ባቤል ፤

ወእስራኤልኒ ኀሩይየ ፣

የመረጥሁት ዘሩባቤል ፤

ዘተወክፈቶ ነፍስየ ፣

ልቡናዬ የወደደችው ዘሩባቤል፤

ወወሀብኩ መንፈስየ ዲቤሁ ፣

መንፈሰ ረድኤትን ያሳደርሁ በት ዘሩባቤል ፤

ወናሁ ያመጽእ ፍትሐ ለአሕዛብ ፣

እነሆ ለአሕዛብ አሪትን ያስተም ራል ፤

፪፤ ኢይኬልሕ ወኢይጠርእ ፣

አይጮኽም፤ አይገኔታም፤ (በጥ ርአ ቃል እንዲል፤ ጥበብ ፲፭፥ ፲፰) ፤

ወኢይሰምዕ ቃሎ በአፍኣ ፣

በአፍኣ ያሉ ሰዎች ቃሉን አይ ሰሙትም ፤ የቃሉን መለዘብ መናገር ነው፤ አንድም ናሁ ቀሩል ዔየ ዘአነገዝክዎ ፤

በሥልጣን አንድ የምንሆን ልጄ ክርስቶስ ፤

ወእስራኤልኒ ኀሩይየ ፣

የመረጥሁት ልጄ ክርስቶስ ፣ ልቤነቴ የወደደችው ልጄ ክር ስቶስ፤ መንፈስ ቅዱስን በአም ሳለ ርግብ በራሱ ላይ ያስቀመ ጥሁበት ልጄ ክርስቶስ፣ ለአ ሕዛብ ወንጌልን ያስተምራል፣ አይጮኽም ፣ አይገኔታም ፣ በአ ፍኣ ያሉ ሰዎች ቃሉን አይሰ ሙትም፤ ማለት የቃሉን መለ ዘብ መናገር ነው ፤ ከዚህ እንዲህ አለ ፤ ከዚያ ወአልዐለ ቃሎ በም ኵራብ ይላል፤ ዮሐ.ም፯ ቁ.፴፯ አይጣላም ቢሉ አይጣላም፤ ከዚህ እንዲህ ማለቱ በሥጋዊ ነገር አይከራከርም ሲል ነው ፤ ከዚያ ወአልዐለ ቃሎ ማለቱ መንፈሳ ዊውን አስምሮ ያስተምራል ሲል ነው ፤

www.ethiopianorthodox.org

፫፡ ብርዕ ቅጥቁጥ ኢይሰበር ፤

በዘሩባቤል የተቀጠቀጠ መቃ መስዬ አይሰበርም ፤

ወሡዕኒ ዘይጠይስ ኢይጠፍእ ፤

የሚጢያጢያስ የሚፍ ኩስታሪ አይጠፉበትም፤ አንድም ብርዐ ቅጥቁጠ ኢይሰብር ወሡዐኒ ዘይጠይስ ኢያጠፍእ ይላል ፤ የተቀጠቀጠ መቃ መስዬን አይሰብርም፤ የሚጢያጢያስ የሚፍ ኩስታሪን አያጠፋም፤ የእግሩን መጨመት መናገር ነው ፤

ዳዕሙ በጽድቅ ያገብእ ፍትሐ ፤

በእውነት በትዕግሥት በጎድአት ይፈርዳል እንጂ፤ አንድም ብርዕ ቅጥቁጥ ብለህ መልስ ፤ መቃ መስዬ አሪት አትጠፉበትም፤ የምትጢያጢያስ አሪት አትጠፉበትም፤ በእውነት ፈርዶ እንድትነገር ያደርጋታል እንጂ ፤ አሪትን መቃ መስዬ አላት ፤ መቃ መስዬ ሲወጣ ብዙ ሁኖ ይወጣል፤ ፀሐይ ሲመታው መሽከደቆ ይጠፋል ፤ አሪትም ስትሠራ ታልፍ አትመስልም ነበር፤ ኋላ ግን ጠፍታለችና፤ አንድም ብርዕ ቅጥቁጥ ኢይሰበር ብለህ መልስ ፤ በንዴት የተቀጠቀጠ ድህ አይጠፉበትም ፤ ወሡዕኒ በንዴት የሚጢያጢያስ ድህ አይጠፉበትም በውነት ፈርዶ ያድነዋል እንጂ ፤

፬፡ ወያበርህ ፤

ለትሩፋን ተድላ ደስታን ያደርጋል ፤

ወኢያጠፍእ ፤

ድህውን አያጠፋም ፤ አንድም ወያበርህ የሰው ልቡናን በትምህርት ያበራል፤ ወኢያጠፍእ አሪትን አያጠፋም ፤

እስከ ይገብእ ፍትሕ ፤

ለድህው እውነት እስኪፈረድ ድረስ፤ አንድም አሪት እስክትነገር ድረስ፤ አንድም ብርዕ ቅጥቁጥ ኢይሰበር ፤ መቃ መስዬ ወንጌል አትጠፉበትም ፤

ወሡዕኒ ዘይጠይስ ኢይጠፍእ ፤

የፍግ እሳት ወንጌል አትጠፉበትም በውነት ፈርዶ ያስተምራታል እንጂ ፤ አንድም ብርዕ ቅጥቁጥ ኢይሰበር በደቂ የተቀጠቀጠ ሕሙም አይጠፉበትም፤ እድናለሁ በማለት ተስፋ የሚጢያጢያስ ሕሙም አይጠፉበትም፤ በእውነት ፈርዶ ያድነዋል እንጂ ፤ አንድም አምስት ሺህ ካምስት መቶ ዘመን በመከራ የተቀጠቀጠ አዳም አይጠፉበትም፤ ወሡዕኒ እድናለሁ በማለት ተስፋ የሚጢያጢያስ አዳም አይጠፉበትም፤ በእውነት ፈርዶ ያድነዋል እንጂ፤ አንድም በቅናት የተቀጠቀጡ አይሁድ በቀ

ረባ አይጠፉበትም፤ በቅናት የሚጢያጢያሱ አይሁድ በቀረባ አይጠፉበትም፤ ኋላ ባርባ ዘመን በእውነት ፈርዶ ያጠፋቸዋል እንጂ ፤

ወያበርህ ፤

ለምዕመናን ለአዳም ልጅነትን ክብርን ይሰጣል ፤

እስከ ይገብዕ ፍትሕ ፤

ለአዳም ለምዕመናን እስኪፈርድ ድረስ ፤

ወይትቄከሉ አሕዛብ በስሙ ፤

አሕዛብ በስሙ ያምናሉ ፤ አንድም እስኪያምኑ ድረስ ኢያጠፍእ ብለህ እሠር ፤

፭፡ ከመዝ ይቤ እግዚአብሔር አምላክ ዘገብረ ሰማየ ፤

ሰማይን የፈጠረ እግዚአብሔር እንዲህ አለ ፤

ወተከለው ፤

ያፀናው ፤

ወአፅንዓ ለምድር ዲበ ማይ ፤

ምድርን በውሃ ላይ ያፀናት ፤

ወኮሎ ዘውስቴታ ፤

በውስጧ ያሉትን ሁሉ የፈጠረ፤

ወይሁቦሙ መንፈሰ ለአሕዛብ ዘውስቴታ ፤

በሷ ውስጥ ለሚኖሩ ሰዎች ዕውቀትን የሚሰጥ ፤

ወነፍሰ ለእለ ይነብሩ ዲቤሃ ፤

በሷ ላይ ለሚኖሩ ሰዎች ነባቢት ነፍስን የሚያዋሕድ እግዚአብሔር እንዲህ አለ ፤

፮፡ አነ ውእቱ እግዚአብሔር አምላክከ ዘጸዋዕኩከ በጽድቅ ፤

በእውነት ትሩፍ ብዬ የጠራሁህ ፈጣሪ እኔ ነኝ ፤

ወአጎዝኩከ በእዴየ ፤

በሥልጣኔ የያዝሁህ እኔ ነኝ፤

ወአፀንዐከ ፤

አፀናሃለሁ ፤

ወአሁበከ ሥርዐተ ለትውልደ ትውልድ ፤

ዘዘሩባቤልን ለልጅ ልጅ ዘመን ሥርዓት የምትሆን አሪትን እሰጥሃለሁ ይለዋል፤ አንድም አንተን ሥርዐት አድርጌ እሰጥሃለሁ፤ ንጉሡን ሥርዓት አድርጎን እንማረዋለንና ሥርዓት አለው፤

፯፡ ወትከሥት አዕይንተ ዕውራን፤

የዕውራን ልቡና የእስራኤልን ዐይነ ልቡና በትምህርት ታበራለህ ፤

ወታውዕአሙ ለሙቁሓን እማእሠር፤

የታሠሩ ትሩፋንን ከእሥራት ታወጣቸው ዘንድ ፤

ወእምቤተ ሞቅሕ ለእለ ይነብሩ ውስተ ጽልመት ፤

በዕኑ መከራ ተይዘው በባቢሎን የሚኖሩትን ከግዞት ቤት ታወ

www.ethiopianorthodox.org

ጣቸዋለህ አንድም ፤ ወእሁበከ ሥርዓተ ለትውልደ ትውልድ ጌታን ለልጅ ልጅ ዘመን ሥርዓት የምትሆን ወንጌልን እሰጥ ሃለሁ ይለዋል አብ ክርስቶስን፤ አንድም አንተን ሕግ አድርጌ እሰጥሃለሁ፤ ወንጌል እሱ ነውና፤

ወለብርሃነ አሕዛብ ፣

ወብርሃነ ለአሕዛብ ሲል ነው ፤ የአሕዛብ መምህራቸው ትሆና ለህ፤

ወትከሥት አዕይንተ ዕውራን ፣

ዕውራኑ ሥጋን በተአምራት ዕውራኑ ነፍስን በትህምርት ታበ ራለህ ፤

ወታወፅአሙ ለሙቁሓን እማእሠር፣

በፍዳ ነፍስ የተያዙትን ታድና ቸዋለህ ፤

ወእምቤተ ሞቅሕ ለእሰ ይነብሩ ውስተ ጽልመት ፣

በጨለማ የሚኖሩ ነፍሳትን ከሲ አል ከገሃነም ታወጣቸዋለህ ፤

፮፤ አነ እግዚአብሔር አምላክከ ፣

ፈጣሪህ እኔ ነኝ ፤

ከመዝ ስምየ ፣

ስሜም ፈታሒ በጽድቅ ይባላል፤

ወኢይሁብ ክብርየ ለባዕድ ፣

አምላክነቴን ለባዕድ ለጣያት አልሰጥም ፤

ወኢስብሐትየ ለግልፎ ፣

ጌትነቴንም ለተቀረፀ ጣያት አልሰጥም ግልፎ የሚለው አፍ፣ አፍንጫ ፣ ዐይን ፣ ጆሮ የተቀረ ፀለት ነው፤ አንድም የባሕርይ ክብሬን ጌትነቴን ቃል ላልተ ዋሐደው ለዘርዐ ዳዊት አልሰ ጥም፤ በኅድረት የባሕርይ አም ላክ ሆነ የሚሉ መናፍቃን አሉና፤

፱፤ ናሁ መጽአ ዘትካት ፣

እነሆ ቄዋቄ መጣ ፤

ወዘሐዲስኒ ዘእነ ነገርኩከ ፣

እኔ የነገርሁህ ሚጠት ደረሰ፤

ወናሁ ዘእንበለ ይዜንዉክሙ ነገርኩ ክሙ ፣

እነሆ ነቢያተ ሐሰት ካህናተ ጣያት ሳይነግሯችሁ አስቀድሜ እኔ ነገርኋችሁ፤ ቄዋቄን ሚጠ ትን ፤

ሰብሕዎ ለእግዚአብሔር አምላክ ስብ ሐተ ሐዲስ ፣

የክብር ባለቤት ጌታን በሐዲስ ምስጋና አመስግኑት፤ ግብሩ እየ ተለወጠ ስብሐተ ሐዲስ ይለ ዋል፤ ምሥጢሩ በየጊዜው አዲስ አዲስ ሥራ ይሠራል ማለት ነው፤

፲፤ ቀዳሚሁ ስብሐቲሁ እምአጽናፈ ምድር ፣

ግብሩ እየተለወጠ ስብሐተ ሐዲስ አልሁ እንጂ [illegible]

በረ የፈጣሪያችን ምስጋና ነው፤ አንድም ለአበው ጽንፍ ከሆነ ከአዳም ለመዓት ጽንፍ ከሆነች ከሔዋን ጀምሮ የነበረ ነው፤ ምሥ ጢሩ ተአምራት ማድረግ ነው፤

እለ ይወርዱ ውስተ ባሕር ፣

እለ ትወርዱ ሲል ነው፤ ወደ ባሕር የምትወርዱ ፤

ወይነግድዋ ፣

ወትነግድዋ ሲል ነው፤ በባሕር ላይ የምትሂዱ አመስግኑት ፤

ወደሰያትኒ ፣

ደሴት በውሀ እንዲከበብ በመ ከራ የተከበባችሁ እስራኤል ፤

ወእለ ይነብሩ ውስቴቶን ፣

ወእለ ትነብሩ ሲል ነው፤ በመ ከራ ተይዛችሁ የምትኖሩ እስ ራኤል አመስግኑት ፤

፲፩፤ ትትፈሣሕ በድው ፣

በሰባ ዘመን ምድረ በዳይቱ ደስ ይላታል፤ አንድም ሰባ ዘመን ምድረበዳ የነበረች ኢየሩሳሌም ደስ ይላታል ፤

ወአህጉሪሃ ፣

አውራጃዎቿ፤ አንድም መንደ ሮቿ ደስ ይላቸዋል ፤

ወአህጉረ ቄዳር ፣

የዘላኖች አገሮች ደስ ይላቸዋል፤ አንድም በእስማኤል ዕፃ ያሉ ሰዎች ደስ ይላቸዋል ፤

ወእለሂ ይነብርዎን ይትፌሥሑ ፣

በዚያ የሚኖሩ ሰዎች ሁሉ ደስ ይላቸዋል ፤

እለ ይነብሩ ውስተ በአታት ወውስተ አርእስተ አድባር ፣

በዋሻም በተራራም የሚኖሩ ሰዎች ሁሉ ደስ ይላቸዋል፤ ወይ ኬልሑ ማንሻ፤ አንድም በዋሻም በተራራም የሚኖሩ ሁሉ ፤

፲፪፤ ይኬልሑ ወይሴብሑ ለእግዚ አብሔር ፣

ለእግዚአብሔር በውስጥ በአፍአ ምስጋና ያቀርባሉ ፤

፲፫፤ ወይነግርዎሙ ለደሰያት ሠና ይቶ ለእግዚአብሔር አምላክ ኀያል፤ የተሰደዱት ለተማረኩት የእግ ዚአብሔርን ቸርነቱን ይነግሯ ቸዋል፤ እናንተን በፋርስ፣ በባቢ ሎን ፣ በዕርዕ በሜዶን ሳላችሁ ይጠብቃችሁ እንደነበረ ፣ እኛ ንም በባሕር ጠልቀን ፣ በገደል ወድቀን ሳለን ይጠብቀን ነበር ብለው ይነግሯቸዋል ፤

ይወጽእ ወይቀጠቅጥ ፀብዐ ፣

ፀብዐዊ ሲል ነው፤ በመዓት ይወ ጣል ዐርበኛውን ያጠፋል ፤

ወያነሥእ ቅንአተ ፣

ለአምላክነቱ የሚቀናውን ቅናት ያነሣል ፤

ወይቄውዕ ዲበ ፀሩ በኀይሉ ፣

በጠላቱ ላይ በኃይሉ ይደነፋል ማለት ጠላቱን ያጠፋል ፤

www.ethiopianorthodox.org

፲፬፡ አርመምኩ እምፍጥረተ ዓለም፣

ከሰባ ዘመን ከመጀመሪያው ጀምሮ ዝም አልሁ ፤

ቦኑ ለግሙራ እንከ አረምም ወእት ዔገሥ ፣

በውኑ አንድ ጊዜ ዝም ብል ፈጽሜ ዝም እላለሁን፤ እታገሣ ለሁን ፤

ከመ እንተ ትወልድ ግብተ እንከሰ፣

እንግዲህ ወዲህስ ያች የፀነሰች ሴት ባልጠረጠረችው ዕለት፣ ባላሰበችው ሰዓት ድንገት እንድ ትወልድ ድንገት ተነሥቼ ፤

፲፭፡ አየብስ አድባረ ወአውግረ ፣

ነገሥታቱን፣ መኳንንቱን አጠ ፋለሁ ፤

ወኮሎ ሣዕሮሙ አየብስ ኅቡረ ፣

ሠራዊቶቻቸውን ሁሉ አንድ አድርጌ አጠፋለሁ ፤

ወአውኅዝ አፍላገ ውስተ ደሰያት፣

ደሴት በውሀ እንዲከበብ፣ በመ ከራ ለተከበቡ ለትሩፋን ተድላ ደስታውን ትእምርቱን አደር ግላቸዋለሁ ፤

ወአየብስ ያመ ፣

የሺሕ አለቃውን አጠፋለሁ ፤ አንድም ዐርበኛውን አጠፋለሁ፤ [illegible]

፲፮፡ ወአመጽኦሙ ለዕውራን በፍኖት ዘኢየአምሩ ፣

ዕውራነ ልቡና እስራኤልን በማ ያውቁት ጐዳና አመጣቸዋለሁ፤ አንድም ትሩፋንን በማያውቁት ጐዳና አመጣቸዋለሁ ፤ ኢየሩሳ ሌምን አበው እንጂ ውሉድ አያ ውቋትምና ዕውራን አላቸው ፤ አንድም እንግዳና ዕውር አንድ ነውና ዕውራን አላቸው ፤

ወመጽያሕተ ዘኢርእዩ አከይዶሙ፣

ያላዩትን ጥርጊያ ጐዳና አስረ ግጣቸዋለሁ፤ ናቡከደነፆር ረዳት ፈርቶ በምድረ በዳ ማርኮ ወስዷ ቸዋልና፤ ናቡከደነፆርንስ ያህል ንጉሥ ረዳት አይፈራም ብሎ የወጡ አባቶች አልቀው የቀሩ ልጆች ናቸውና እንዲህ አለ ፤

ወእሬስዮሙ እምጽልመት ውስተ ብርሃን ፣

ከኀዘን ወደ ደስታ፣ ከመከራ ወደ ዕረፍት ፣ ከኀሣር ወደ ክብር ፣ ከድንቁርና ወደ ዕውቀት አወጣ ቸዋለሁ ፤

ወእፀይሕ ሎሙ መብእሰ ፣

ጐጻጕጹን ጐዳና እጠርግላቸዋ ለሁ ማለት አሕዛብን አጠፋላ ቸዋለሁ ፤

ወዘንተ ነገረ እገብር ሎሙ ወኢየ ኀድጎሙ ፣

ይህን ነገር አ[illegible] ድኑት አልለየቸውም ፤

፲፯፡ ወእሙንቱሰ ተመይጡ ድኅሬ ሆሙ ፣

እነሱ ግን እኔን ትተው ወደ ኃጢአት፣ ወደ ጣዖት ተመለሱ፤ አድሮ አነስ ሆኑ ፤

ተኀፈሩ ኀፍረተ እለ ትሰግዱ ለግ ልፎ ፣

ለተቀረፀ ጣዖት የምትሰግዱ ሰዎች ፈጽማችሁ እፈሩ ፤

ወእለ ትብልዎሙ ለስብኮ አንትሙ አማልክቲነ ፣

ተመትተው የተሠሩ ጣዖታቱ ንም ፈጣሪዎቻችን እናንተ ናችሁ የምትሉ ሰዎች እፈሩ ፤

፲፰፡ ስምዑ ዕሙማን ወርእዩ ዕው ራን፣

ዕሙማነ ልቡና፣ ዕውራነ ልቡና እስራኤል ስሙ ፤ እዩ ፣ ተመል ከቱ ፤

፲፱፡ መኑ ዕውር ዘእንበለ አግብር ትየ ፣

ከባሮቼ ከእስራኤል በቀር ዕውር ማነው ፤ ማን አለ ? አንድም ማነው ብትል ባሮቼ እስራኤል ናቸው ፤

ወመኑ ዕሙም ዘእንበለ መላእክቲ ሆሙ ወመኳንንቲሆሙ ፣

ከእስራኤል አለቆች ከመኳንንቱ በቀር ደንቆሮ ማን አለ? አን ድም ማነው ብትል፣ አለቆቻቸው መኳንንቶቻቸው ናቸው ፤

ወያሩ አግብርተ እግዚአብሔር ፣

አግብርተ እግዚአብሔር እስራ ኤል ዕውራነ ልቡና ሆኑ ፤

፳፡ ወትረ ትሬእዩ ወኢተዐቅቡ ፣

እያየነ ዕውራን ትለናለህን ትሉኝ እንደሆነ ማየትስ ዘወትር ታያላ ችሁ ፤ ነገር ግን ሕጉን አትጠ ብቁም ፤ አንድም ሕጉን አትጠ ብቁም እንጂ ማየትስ እናያለን ትላላችሁ ፤

ወክሡታት ዕዘኒክሙ ወኢትሰምዑ፣

እየሰማነ ዕሙማን ትለናለህን ትሉኝ እንደሆነ ጆሮአችሁ የተ ከፈተ ነው፤ ነገር ግን አትሰሙም፤ አንድም አትሰሙም እንጂ ጆሮ ዋችሁስ የተከፈተ ነው ፤

፳፩፡ እግዚአብሔር አምላክ መከረ ያጽድቅሙ ፣

ፈጣሪ የሚሆን እግዚአብሔር ያከብራችሁ ዘንድ መከረ፤ አን ድም ሚጠትን እውነት ያደርግ ዘንድ መከረ ፤

ወያዕቢ ስብሐቲሁ ፣

ጌትነቱን ይገልጥ ዘንድ መከረ፤

፳፪፡ ወርኢኩ ወናሁ ተዜወዉ ሕዝብ ወተበርበሩ ፣

እነሆ አየሁ ፤ ሕዝቡ ተማረኩ ፤ ገንዘባቸውን ተበዘበዙ ፤

www.ethiopianorthodox.org

እስመ መሥገርት ለወራዙት ውስተ
አብያት በኵለሄ ወውስተ ውሳጥያት
ጎበ ጎብዕዎሙ በርበርዎሙ ፤

ለጌልማሶች ወጥመድ የሚሆን
ጣያት በአፍአም በውስጥም አለና
ከሠወሯቸው ቦታ እየገቡ ማር
ከው ወሰዷቸው ፤

ወአልቦ ዘያድኅኖሙ ፤

ከሰዎች ጣያታቱን የሚያድና
ቸው የለም ፤ የወርቅ ናቸውና
ድሪም ፣ ዐቀመት ፣ አላድ ፣
ወቄት፣ እያሉ ለመካፈል ይበረ
ብሯቸዋልና ፤ አንድም ለወራ
ዙት ወጥመድ የሚሆን ጦር በው
ስጥም በአፍአም አለና ሚስቶቻ
ቸው ከሠወሯቸው ከዕልፍኝ ከአ
ዳራሽ እየገቡ አሕዛብ ማርከው
ወስደዋቸዋልና ፤

ወአልቦ ዘያድኅኖሙ ፤

ከጣያታቱ ሰዎችን የሚያድና
ቸው የለም ፤

ወይመሥጥዎሙ ፤

ነጥቀው ይወስዷቸዋል ፤

ወአልቦ ዘያነግፎሙ ፤

የሚያስጥላቸው የለም ፤

፳፫፤ መኑ እምኔክሙ ዘያፀምዕ ዘንተ፣

ከናንተ ወገን ይህን ቄዋቄን የሚ
ሰማ ማነው ፤

ከመ ይስማዕ ዘይመጽእ ፤

የሚመጣ ሚጠትን ይሰማ ዘንድ
አንድም ይህን አባር ቸነፈር
የሚሰማ ማነው የሚመጣ ቄዋ
ቄን ይሰማ ዘንድ ፤

፳፬፤ መኑ ረሰዮ ለያዕቆብ ከመ ይት
ማሰጥዎ ፤

ያዕቆብን እንዲነጣጠቁት ያደ
ረገ ማነው ፤

ወለእስራኤልኒ ከመ ይቄውውዎ ፤

እስራኤልንስ እንዲማርኩት ያደ
ረገ ማነው ፤

አኮኑ እግዚአብሔር ዘሎቱ አበሱ፣

እሱን የበደሉት እግዚአብሔር
አይደለምን ፤

ወዐበዩ ሐዊረ በፍኖቱ ፤

በሕጉ ፀንተው መኖርን እንቢ
አሉ ፤

ወኢሰምዑ ሕጎ ፤

ሥርዓቱን ያልሰሙት እግዚአ
ብሔር አይደለምን ፤

፳፭፤ ወአምጽአ ላዕሌሆሙ መቅሠ
ፍተ መዓቱ ፤

ተቈጥቶ ያመጣውን መቅሠፍት
በላቸው ላይ አመጣ ፤

ወአምጽአ ላዕሌሆሙ ቀትለ ፤

በላቸው ላይ ሰልፍን አመጣባ
ቸው ፤

ወአለሂ የዐወይዉ በዐውዶሙ ፤

እስራኤል መከራ መጥቶባቸው
የጮኹ የሚመክራቸው የሚያ

ስተምራቸው አጥተው አይደለም፤
ሕገ እግዚአብሔርን የሚያስተ
ምሩ ነቢያት ካህናት በዙሪያቸው
ሁነው ሳሉ ነው እንጂ አለ ፤
ባይሰሙ ነው እንጂ ፤ አንድም
እስራኤል መከራ የመጣባቸው
ነቢያት ካህናት ከበው ሲያስተ
ምሯቸው አንሰማም ብለው ነው፤
አንድም እስራኤል የተማረኩ
ገድለው ፣ ሰልበው የሚደነፋ
አሕዛብ ከበዋቸው ሳለ ነው ፤
አንድም እስራኤል የጠፉ ከቦታ
ቸው ወደ ሌላ አገር ሂደው አይ
ደለም፤ ገድለው ሰልበው የሚደ
ነፉ አሕዛብ በዙሪያቸው ሁነው
ነው እንጂ አለ፤ መጥተውባቸው
ነው እንጂ፤

ኢየአምሩ ኵሎሙ ወኢይሔልዩ
በልቦሙ፣

ሁሉም አያውቁም በልቡናቸ
ውም አያስቡም ::

ምዕራፍ ፶፫

፩፤ ወይእዜኒ ከመዝ ይቤ እግዚአ
ብሔር አምላክ ዘገብረከ ያዕቆብ
ወዘፈጠረከ እስራኤል ፣

አሁንም ያዕቆብ እስራኤል በነ
ፍስ በሥጋ የፈጠረህ እግዚአ
ብሔር እንዲህ አለ ፤

ኢትፍራህ እንከ እስመ አድኅንኩከ፣

ከመከራ አድኜሃለሁና እንግዲህ
አትፍራ አለ ፤

ወሰመይኩ ስመከ ፣

ስምህን ትሩፍ አልሁህ ፤

ወዚአየ አንተ ፣

አንተም የኔ ገንዘብ ነበርህ ፤
አንድም ከመከራ አድኜሃለሁና፣
ስምህንም ሕዝበ እግዚአብሔር
ብዬ ጠርቼሃለሁና፣ አንተም የኔ
ገንዘብ ነህና ኢትፍራህ ብለህ
እሠር ፤

፪፤ ወእመኒ ዐደውከ ማየ አነ ሀሎኩ
ምስሌከ ፣

ውሀውንም ብትሻገር እኔ ካንተ
ጋራ በረድኤት አለሁና ፤

አፍላግኒ ኢያሰጥሙከ ፣

ፈሳሾች ውሀዎች አያሰጥሙ
ህም፤

ወእመኒ ዐዶከ እሳተ ነበልባልኒ ኢያ
ውዕየከ ፣

እሳቱንም ብትሻገር ነበልባሉ
አያቃጥልህም ፤

፫፤ እስመ አነ ምስሌከ አምላክከ
ቅዱሰ እስራኤል ዘአድኅንኩከ ፣

ያዳንሁህ ፅንዐ እስራኤል ክብረ
እስራኤል የምሆን ፈጣሪህ እኔ
ካንተ ጋራ በረድኤት አለሁና፤
አንድም ማይ ያለው ከባቢሎን
ሲወጡ ሰባት ውሀ ተከፍሎላቸ
ዋል ጥቅስ (ወይሰጥቅ ሎሙ ሰብ
ዓተ አፍላጋተ ከመ ይሑርዎን
በአሳዕን ወይከውኖሙ ለሕዝብየ

www.ethiopianorthodox.org

ከመ አመ ወለዱ እም ግብፅ) እንዲል፤ ኢሳ. (ምዕ. ፲፩÷ ፲፫) እሳት ያለው የሠለስቱ ደቂቅን ነው፤ አንድም እሳትም ማይም ያለው የሠለስቱ ደቂቅ ነው ፤ እሳት አለው በቀደመ ግብሩ ፣ ማይ አለው በኋላ ግብሩ ጥቅስ (ወወረደ መልአከ እግዚአብሔር ወዘበጠ ለነበልባለ እሳት ወረሰዮ ከመ ኑፋስ ቁሪር) ቁሪረም ይላል ፤ ዳን. ምዕ. ፫ ÷ ፵፱ ፤ አንድም እሳትም ማይም ያለው ጦር ነው፤ ከባቢሎን ሲወጡ ሰባት አህጉር ወግተው ወጥተዋልና ፤

ወረሰይኩ ለከ ተውላጠከ ግብፀ ወኢት ዮጵያ ወሴዎንሃ ቤዛከ ፤

ላንተ ለውጥ አድርጌ ግብፅን፣ ኢትዮጵያን፣ ሴዎንን ለጥፋት አሳልፌ ሰጠሁ ፤

፬፡ እስመ ክቡር አንተ በቅድሚየ፡

አንተ በፊቴ ክቡር ነህና ፤

ወአክበርኩከ ፣

አከበርኩህ ፤

ወአነ አፍቀርኩከ ፣

እኔ ወደድሁህ ፤

ወአሁብ ብዙኀ ሰብአ ቤዛከ ፣

ስላንተ ለውጥ አድርጌ ብዙ ሰዎችን ለጥፋት እሰጣለሁ ፤

ወመላእክተሂ ሀየንተ ርእስከ ፣

አለቆችንም ስላንተ ፈንታ ለጥፋት እሰጣለሁ፤ አንድም ስለ አለ ቃህ ስለ ዘሩባቤል ፈንታ አለቆችህንም ለጥፋት እሰጣለሁ ፤

፭፡ ወኢትፍራህ እንከ እስመ አነ ሀለኩ ምስሌከ ፤

እኔ ካንተ ጋራ በረድኤት አለሁና ከእንግዲህ ወዲህ አትፍራ፤

አምጽሣሕ አመጽአሙ ለዘርዕከ ፣

ልጆችህን ከፋርስ አመጣቸዋለሁ ፤

ወእምዓረብ አስተጋብየሙ ፤

ከግብፅ እሰበስባቸዋለሁ ፤

፮፡ ወእብሎ ለሰሜን አምጽአሙ፣

ባቢሎንን አምጣቸው እለዋለሁ፤

ወለዓዜብ ኢትክልኦሙ ፣

ሕንድንም አትከልክላቸው እለዋለሁ ፤

ወአመጽአሙ እምብሔር ርኁቅ ፣

ከሩቅ አገር ከዕርዕ ከሚዶን አመጣቸዋለሁ ፤

ወለአዋልድየኒ እምአጽናፈ ምድር፣

ሴቶች ልጆቼን ከሞዐብ፣ ከዐሞን አመጣቸዋለሁ ፤

፯፡ ወለኵሉሙ እለ ተሰምዩ በስምየ፣

በስሜ ሕዝበ እግዚአብሔር ተብለው የተጠሩትን ሁሉ አመጣቸዋለሁ ፤

እስመ ለስብሐትየ ፈጠርክዎሙ ወገበርክዎሙ ፣

ሊያመሰግኑኝ፤ አንድም ጌትነቴን ሊናገሩ በነፍስ ፀሥጋ ፈጥሬያቸዋለሁና ፣

፰፡ ወአውፃእኩ ሕዝበ ዕውረ እለ እንዘ ቦሙ አዕይንት ኢይሬእዩ ፣

ዐይን ሳላቸው የማያዩ ዕውር ወገን እስራኤልን አወጣሁ ፤

ወእንዘ ቦሙ ዕዝን ኢይሰምዑ ፣

ጆሮ ሳላቸው የማይሰሙ ፤

፱፡ ወተጋብዑ ኵሉሙ አሕዛብ ኀቡረ፣

አሕዛብ ሁሉ አንድ ሁነው ተሰበሰቡ ፤

ወተጋብኡ ኵሉሙ መላእክቲሆሙኒ፣

አለቆቻቸውም ሁሉ አንድነት ተሰበሰቡ ፤

መኑ ዘይዜኑ ዘንተ ፣

ቄዋቄን የሚናገር ማነው ፤

ወዘትካትኒ መኑ ይነግረክሙ ፤

ከዚያ አስቀድሞ የነበረ አባር ቸነፈርንስ ማን ይነግራችኋል፤ አንድም ሚጠትን የሚናገር ማነው፤ አስቀድሞ የነበረ ቄዋቄንስ ማን ይነግራችኋል ፤

ይምጽኡ ሰማዕቶሙ ወይጽደቁ ፣

ምስክሮች ይምጡ እውነት ነገርን ይናገሩ ፤

ወይስምዑ ወይንግሩክሙ ጽድቀ ፣

ይመስክሩ፣ እውነት ነገርን ይንገሯችሁ ፤

፲፡ አንትሙኒ ኩኑኒ ሰማዕትየ ፣

እናንተ ምስክሮቼ ናችሁ፤ አንድም ምስክር ሁኑኝ ማለት አም ላክነቴን አውቃችሁ እመኑብኝ ሲል ነው ፤

ወአነሂ እከውነክሙ ሰማዕተክሙ ይቤ እግዚአብሔር አምላክ ፤

ፈጣሪ የምሆን እግዚአብሔር እኔም ምስክራችሁ ነኝ ማለት ዝናም ለዘር ጠል ለመከር እሰጣችኋለሁ ፤

ወቀኑልዓየኒ ዘኀረይኩ ፣

የመረጥሁት ወዳጄ ዘሩባቤልም ምስክር ነው ፤

ከመ ታእምሩ ወትእመኑ ወትለብዉ ከመ አነ ውእቱ ፣

ፈጣሪ እኔ እንደ ሆንሁ ታውቁ፣ ታምኑ፣ ትረዱ ዘንድ፤

ወእምቅድሚየኒ ኢኮነ ካልዕ እግዚአብሔር ፣

ከኔ አስቀድሞ ሌላ ፈጣሪ እንደ ሌለ ፤

ወእምድኅሬየኒ አልቦ አምላክ ፣

ከኔም በኋላ ሌላ ፈጣሪ እንደ ሌለ ታውቁ ዘንድ ፤

፲፩፡ አነ እግዚአብሔር ፣

ፈጣሪ እኔ ነኝ ፤

ወአልቦ ባዕድ አምላክ ዘእንበሌየ ዘያሐዩ ፣

ከኔ በቀር የሚያድን ሌላ ፈጣሪ የለም ፤

፲፪፡ ነገርኩሂ ወገሠጽኩሂ ፣

ተናገርሁ፣ በመከራ ገሠፅኋችሁ፤

www.ethiopianorthodox.org

ወአልቦ እምውስቴትክሙ ነኪር ፤
ከናንተም ባዕድ የለኝም ማለት
ዘመድ ባዳ አልልም ፤
ለሊክሙ ሰማዕትየ ከመ አነ ውእቱ
እግዚአብሔር አምላክ ፣
ፈጣሪ እኔ እንደሆንሁ እናንተ
ምስክሮቼ ናችሁ ፤
፲፫፤ ወአልቦ ባዕድ አምላክ ዘእን
በሌየ እምፍጥረተ ዓለም ፣
ከጥንት ጀምሮ ከኔ በቀር ሌላ
ፈጣሪ የለም ፤
ወአልቦ ዘያመሥጥ እምእዴየ ፣
ከሥልጣኔ የሚያመልጥ የለም፤
ወዘገበርኩ አልቦ ዘይመይጥ ፣
ያደረግሁትንም የሚለውጥ
የለም፤
፲፬፤ ከመዝ ይቤ እግዚአብሔር አም
ላክ ዘአድኅነክሙ ቅዱሰ እስራኤል፣
ያዳናችሁ ፅንዐ እስራኤል ክብረ
እስራኤል የሚሆን ፈጣሪ እግዚ
አብሔር እንዲህ አለ ፤
ጉባዔ
ናሁ በእንቲአክሙ እፈኑ ባቢሎንሃ
መራደ ፤
በናንተ የባቢሎንን ሰዎች ወራሪ
እፈታባችኋለሁ ፤
ወአነሥአሙ ለኵሎሙ ፣
ሁሉንም በናንተ ላይ አስነሣቸ
ዋለሁ፤ አንድም ስለናንተ በባቢ
ሎን ሰዎች ወራሪ እፈታባቸዋ
ለሁ፤ ሁሉንም በባቢሎን ሰዎች
አስነሣባቸዋለሁ ፤ አንድም በና
ንተ ናቡከደነፆርን አመጣለሁ፤
አንድም ስለናንተ ቂሮስ ዳርዮ
ስን ወደ ባቢሎን አመጣለሁ፤
ሁሉንም አነሣሥቼ አመጣለሁ
አለ ፤
ወፋርስኒ ይትአሠሩ በመዋቅሕት፣
የፋርስም ሰዎች በእግር ብረት
ይታሠራሉ አለ፤ በፍዳ ይጠፋሉ፤
ምነው የፋርስ ሰዎችማ አጥፊዎች
አይደሉምን ቢሉ ግብረ አበር
የሆኑት አብረው ጠፍተዋልና፤
አንድም በደበያት ይጠፋሉና ፤
አንድም እኩሌቶች ከቂሮስ፣ ከዳ
ርዮስ እኩሌቶች ከባላገር እየ
ሆኑ ይዋጋሉና ፤
፲፭፤ አነ እግዚአብሔር አምላክክሙ
ቅዱስ ፣
ፅኑ ክቡር ልዩ የምሆን ፈጣሪ
ያችሁ እኔ ነኝ ፤
ዘእርዕዮ ለእስራኤል ንጉሥክሙ ፣
ዘሩባቤልን የምጠብቀው እኔ
ነኝ ፤
፲፮፤ ከመዝ ይቤ እግዚአብሔር አም
ላክ ዘወሀበ ፍኖተ ውስተ ባሕር ፣
በባሕር ጐዳናን የሰጠ እግዚአብ
ሔር እንዲህ አለ ፤
ወመፅያሕተ ውስተ ማይ ብዙኅ ፣
ስፋሕ ሲል ነው ፤ በሰፊ ውሀ
ውስጥ ጥርጊያ ጐዳናን የሰጠ፤

አንድም በኤርትራ ጥርጊያ ጐዳ
ናን የሰጠ ፤
፲፯፤ ዘያመፅእ ሠረገላ ወአፍራሰ ወሠ
ራዊተ ፅኑዐ ፣
ፅኑዓነ ሲል ነው፤ የግብፅን ሠራ
ዊት ፈረሱን ሠረገላውን አነሣ
ሥቶ ያመጣ እግዚአብሔር እን
ዲህ አለ፤ ወይ ከከብታችን፣ ወይ
ከባሮቻችን አልሆነ ብለው ተከ
ትለው ወጥተዋልና ፤
ወባሕቱ ኖሙ ወኢነቅሑ ፣
ነገር ግን የሞት እንቅልፍ አን
ቀላፉ፣ አልተነሡም ፤
ወጠፍኡ ኵሎሙ ከመ ሐመደ ሡዕ፣
ሁሉም እንደ ሚፍ ኩስታሪ ጠፉ፤
፲፰፤ ኢትዜከሩኑ ዘትካት ፤
ቄዋቄን አታስቡምን ፤
ወዘቀዲሙ ፣
አባር ቸነፈርንስ አታስቡምን፤
አንድም ኢትዜከሩኑ ዘትካት
ሚጠትን ፤
ወዘቀዲሙ ፣
ከዚህ አስቀድሞ የነበረ ቄዋቄን
አታስቡምን ፣
ወኢትሔልዩኑ ፣
ቄዋቄን ሚጠትን አታስቡምን፤
፲፱፤ ናሁ አነ እገብር ሐዲሰ ዘይእዜ
ይሠርቅ ፣
እነሆ እኔ ዛሬ የሚደረግ ሚጠ
ትን አደርጋለሁ ፤
ከመ ታእምሩ ፣
ታውቁ ዘንድ ፤
ወእገብር ፍኖተ ውስተ በድው ፣
በምድረ በዳ ጐዳናውን እሰጣ
ለሁ ፤
ወአውጎዝ ማየ በውስተ ገዳም ፣
ሰባ ዘመን ምድረ በዳ በነበረች
በኢየሩሳሌም ውሀውን አፈሳ
ለሁ ፤
፳፤ ወይድኅሩኒ አራዊተ ገዳም ፣
የምድረ በዳ አራዊት ይመርቁ
ኛል ፤
ወዕገሎ አዕዋፈ ሰማይ ፣
በሰማይ የሚበሩ የአዕዋፍ ገላግ
ልት ፤
ወሴኔሬስ ፣
ሰገኖ (ሰጎን) እሊህ ሁሉ ያመሰ
ግኑኛል፤ አንድም በኢየሩሳሌም
ሕጉ እንዲነገር አደርገዋለሁ ፤
ወይድኅሩኒ ፣
ሕዝቡ አሕዛቡ ይመርቁኛል፤ አን
ድም ወአውጎዝ፣ ከትምህርት
ከልጅነት ምድረ በዳ በሆነች
በኢየሩሳሌም ትምህርት ልጅ
ነት እንዲሰጥ አደርጋለሁ ፤
ወይድኅሩኒ ፣
ሕዝብ አሕዛቡ ይመርቁኛል፤
ወዕገሎ አዕዋፈ ሰማይ ወሴኔሬስ፣
እነዚህ ሁሉ ያመሰግኑኛል ፤

www.ethiopianorthodox.org

እስመ ወሀብኩ ማየ በውስተ በድው፣
በምድረ በዳ ውሀውን አፍልቄ
አለሁና ፤
ወአውጎዝኩ ማየ ውስተ ገዳም
በምድረ በዳ ውሀውን አፍስሻ
ለሁና ፤
ከመ አስትዮሙ ለሕዝብየ ወለጎሩ
ያንየ ዘአጥረይኩ ፣
ገንዘብ ያደረግኋቸው ወዳጆቼን
ወገኖቼን አጠጣቸው ዘንድ ፤
ከመ ይንግሩ ስብሐትየ ፣
ምስጋናዬን ጌትነቴን ይናገሩ
ዘንድ ፤
፳፩፡ አኮ ይእዜ ዘጸዋዕኩከ ያዕቆብ፣
ያዕቆብ ዛሬ መሥዋዕት ሠዋ
ልኝ ብዬ የጠራሁህ አይደለም፤
ወኢያጽሐብኩከ እስራኤል ፣
እስራኤል መሥዋዕት አልሠዋ
ህልኝም ብዬ የዘበዘብሁህ አይ
ደለም ፤
፳፪፡ እስመ አኮ ሊተ ዘሖዕከ አባግ
ዒከ ፣
በጎችህን ለኔ የሠዋህ አይደለ
ምና ፤
ወኢሰባሕኩኒ በመሥዋዕቲከ ፣
በመሥዋዕቱም ያመሰገንሽኝ አይ
ደለምና ፤
ወኢያገበርኩከ ትሙዕ ሊተ ፣
መሥዋዕቱን ትሠዋልኝ ዘንድ
ግድ አላልሁህምና ፤
ወኢያጽሐብኩከ በስሂን ፣
ነጭ ዕጣን አላቀረብህልኝም ብዬ
አልዘበዘብሁህምና ፤
፳፫፡ ወኢተሣየጥከ ሊተ በወርቅ ዕጣነ፣
በወርቅም ዕጣኑን አልገዛህልኝ
ምና ፤
ወኢፈተውኩ መሥዋዕተከ ፣
መሥዋዕትህንም አልወደድሁ
ምና ፤
ወኢስብሐ አባግዒከ ፣
የበጎችህንም ስብ አልወደድሁ
ምና ፤
ዳዕሙ ቆምከ በኃጢአትከ ወበጌጋ
ይከ ፣
በታላላቁ በጥቃቅኑ ኃጢአትህ
ፀናህ እንጂ መሥዋዕቱን ያቀረ
ብህልኝ አይደለምና፤ አኮ ይእዜ
ዘጸዋዕኩከ ያዕቆብ ብለህ እሠር፤
አንድም በኃጢአትህ ፀንተሃልና
መሥዋዕቱን ትሠዋልኝ ዘንድ
ግድ ያልሁህ አይደለም፤ አንድም
በኃጢአትህ ፀንተሃልና በኃጢ
አትህ ተጸይፌህ ፤ አኮ ዘጸዋዕ
ኩከ ወኢያጽሐብኩከ ላለው ፤
፳፬፡ አነኪ ውእቱ ዘእደመስሶን ለኃ
ጣውኢከ ፣
ብትመለስ ኃጢአትህን የማስ
ተሠርይልህ እኔ ነኝ ፤
ወኢይዜከሮን እንከ ፣
እንግዲህ ወዲህም አላስብብህም፤

፳፭፡ ነዓ ንትዋቀስ ፤
ዕርቅ እንጂ ተዋቅሶ ነውና ተዋ
ቅሰን እንታረቅ ፤
ንግር አንተ ኃጣውኢከ ቅድመ ከመ
ትጽደቅ ፣
ትከብር ዘንድ አንተ አስቀድ
መህ ኃጢአትህን ተናገር፤ አን
ድም ጽድቅ ታገኝ ዘንድ ተና
ገር ፤
፳፮፡ ቀዳሚሁኒ አበዊክሙ ወመላ
እክቲክሙ ዐለዉኒ ፣
ጥንቱንስ አባቶቻችሁ አለቆቻ
ችሁ የወነጀሉኝ አይደለምን
የማን ልጆች ትቀደሱ ፤
ወአርኩሱ መቅደስየ ፣
ቤተ መቅደስን ያረከሱ፣ ሕጌን
ያፈረሱ አይደለምን ፤
፳፯፡ ወእምዝ አዘዝኩ ያጥፍእዎ ለያ
ዕቆብ ፣
ከዚህ በኋላ ያዕቆብን ያጠፉት
ዘንድ አዘዝሁ ፤
ወከመ ያኅሥርዎ ለእስራኤል ፣
እስራኤልንም ያዋርዱት ዘንድ
አዘዝሁ ::

ምዕራፍ ፵፬

፩፡ ወይእዜኒ ስማዕ ያዕቆብ ቍልዔየ
አሁንም ወዳጄ ያዕቆብ ስማ ፤
ወእስራኤልኒ ዘኀረይኩከ ፣
የመረጥሁህ እስራኤልም ስማ ፤
፪፡ ከመዝ ይቤ እግዚአብሔር አም
ላክ ዘፈጠረከ በውስተ ከርሥ ፣
በእናትህ ማኅፀን የፈጠረህ እግ
ዚአብሔር እንዲህ አለ ፤
ዓዲ እረድአከ ፣
ዳግመኛ የበላችው ተጭኖ፣ የጠ
ጣችው አንዝዞ እንዳይገድልህ
ረዳሃለሁ ፤
ወኢትፍራህ ያዕቆብ ቍልዔየ ፣
ወዳጄ ያዕቆብ አትፍራ ፤
ወእስራኤል ፍቁርየ ዘኀረይኩከ ፣
የመረጥሁህ ወዳጄ እስራኤል
አትፍራ ፤
፫፡ እስመ አነ እሁብ ማየ በውስተ
ዕምዕ ፣
ዕም ባለበት ቦታ ውሀን አፈል
ቃለሁና ፤
ወአውጎዝ ማየ ለእለ የሐውሩ በድወ፣
በምድረ በዳ ለሚሄዱ ሰዎች
ውሀን አፈልቃለሁ ፤ አንድም
ከትምህርት በተጠማች በኢየ
ሩሳሌም ትምህርት እንዲነገር
አደርጋለሁ ፤
ወእሠይም መንፈስየ ዲበ ዘርዕከ ወበ
ረከትየ ላዕለ ውሉድከ ፣
ረድኤቴን፣ በረከቴን በልጆችህ
በትሩፋን ላይ አሳድራለሁ ይለ
ዋል ዘሩባቤልን፤ አንድም የባሕ
ርይ ሕይወቴ መንፈስ ቅዱስን
በሐዋርያት አሳድራለሁ ይላል
ጌታ ፤

www.ethiopianorthodox.org

፩፡ ወይበቀሉ ከመ ሣዕር ማዕከለ ማይ ፣

በውሀ አጠገብ እንዳለ እንደ ፈሳ፣ እንደ ቀጤማ በረድኤት ይለመ ልማሉ ፤

፪ወከመ ኵሐ ዘጎበ ሙኃዘ ማይ ፣

በፈሳሽ ውሀ አጠገብ እንዳለ እንደ አኻያ፣ እንደ ዶቅማ በረ ድኤት ይለመልማሉ፤ በመንፈስ ቅዱስ ይታደሳሉ ፤

፫፡ ወዝኒ ይብል ዘእግዚአብሔር አነ፣

ሁለቱ ነገድ እኔ የእግዚአብሔር ወገን ነኝ ይላል ፤

ወዝክቱሂ ይኬልሕ በስመ ያዕቆብ፣

፬ሥሩ ነገድም በያዕቆብ ስም ይጠራሉ ማለት ሕዝበ እግዚ አብሔር ይባላሉ ፤

ወካልዕ ይጽሕፍ እዴሁ ዘእግዚአብ ሔር አነ ፣

አሕዛብ እኔ የእግዚአብሔር ወገን ነኝ ብሎ እጁን ይከተባል ፤ ኋላ በሐሳዊ መሢሕ ጊዜ ዘመርምያ ያስ ብለው እንዲከተቡ፤

ወበስመ እግዚአብሔር ይጼዋዕ ፣

ሕዝበ እግዚአብሔር ይባላል::

፭፡ ከመዝ ይቤ እግዚአብሔር ንጉሥ እስራኤል ወዘአድኅኖሙ አምላክ ፀባ ያት ፣

ያዳናቸው አሸናፊ የሚሆን የእ ስራኤል ንጉሥ እግዚአብሔር እንዲህ አለ ፤

አነ ቀዳማዊ ወአነ ደኃራዊ ፣

ቅድመ ዓለም የነበርሁ ዓለምን አሳልፌ የምቀር እኔ ነኝ ፤

ወአልቦ ባዕድ አምላክ ዘእንበሌየ ማሕየዊ ፣

ከኔ በቀር የሚያድን ሌላ ፈጣሪ የለም ፤

፮፡ ወመኑ መድኅን ዘከማየ ፣

እንደ እኔ ያለ የሚያድን ሌላ ፈጣሪ ማነው ? ማን አለ ፤

ይቁም ወይጸውዕ ወይንግር ፣

አለ እንደሆነ ይቁም፤ አምላክነ ቱን ይናገር ፤

ወያስተዳሉ ሊተ ዘእምአመ ፈጠር ክዎ ለሰብእ ለዓለም ፣

ሰውን ከፈጠርሁት ጀምሮ ለዘ ለዓለም የሚሆነውን አከናውኖ ይናገር ፤ አንድም ለሰው ብዬ ይህን ዓለም ከፈጠርሁት ጀምሮ ያለውን እስኪያዘጋጅልኝ ማለት እስኪ ዝርዝሩን ይወቀው ፤

ወይንግሩክሙ ዘይመጽእ ዘእንበለ ይብጻሕ ፣

የሚመጣውን ሳይሆን አስቀድ መው ይንገሯችሁ ፤

ወኢትክብቱ ፣

ከኔ አትሠውሩ ፤

፰፡ ወአዕምዑ እንግርክሙ ፣

እነግራችሁ ዘንድ ስሙ ፤

ለሊክሙ ሰማዕትየ ከመ አልቦ ባዕድ አምላክ ዘእንበሌየ ፣

ከኔ በቀር ሌላ ፈጣሪ እንደሌለ እናንተ ምስክሮቼ ናችሁ ፤

፱፡ ወኢሀለዉ አሜሃ አለ ይገብሩ ወይገልፉ ፣

ያንጊዜ ጣዖት የሚሠሩ ፣ የሚ ቀርፁ አልነበሩም ፤

ወኵሉሙ ከንቶ አለ ይገብሩ ፍት ወተ ነፍሶሙ በከ ዘኢይበቍሪሙ ፣

የማይረባቸው የማይጠቅማቸው በከንቱ ልቡናቸው የሚወደው ጣዖትን የሚሠሩ ሁሉ አልነበ ሩም፤ አንድም ወኵሉሙ ከንቱ ይላል ፤ የማይረባቸው የማይጠ ቅማቸው ልቡናቸው የሚወደው ጣዖትን የሚሠሩ ሁሉ ከንቱ ናቸው ፤

፲፡ ወይትኀፈሩ ኵሉሙ አለ ይገ ብሩ አማልክተ ፣

ጣዖት የሚሠሩ ሁሉ ያፍራሉ፤

ወይገልፉ ዘኢይበቍሪሙ ፣

የማይረባቸውን ጣዖት የሚቀር ፁም ያፍራሉ ፤

ወኵሉሙ በኀበ ተገብሩ ይየብሡ፣

ሁሉም በተሠሩበት ቦታ ይጠ ፋሉ ፤

፲፩፡ ወይትጋብዑ ኵሉሙ ሰብእ ዕሙሪሙን ፣

ዕሙሪሙን ልቡና ሰዎች ሁሉ ጣዖት ለማምለክ ይሰበሰባሉ ፤

ወይቀውሙ ኅቡረ ፣

አንድ ሁነው ይቆማሉ ፤

ይትኀፈሩ ወየኀሥሩ በአሐቲኤ ፣

አንድ ሁነው ያፍራሉ፤ ይጐሰቍ ላሉ ፤

፲፪፡ እስመ አብሊሆ ፀራቢ ሐዲነ ምሳሮ ገብሮሙ ፤

እንጨት ጠራቢ ምሳሩን ስሎ ሠርቶአቸዋልና ፤

ወበመድቅሑ ደቅሐሙ ፣

በመዶሻው ድሶአቸዋል፣ በመቀ ደሻው ቀድሷቸዋልና ፤

ወገብሮሙ በመዝራዕቱ ወበኃይሉ ፣

ክንዱን አበርትቶ ኃይሉን አፅ ንቶ ሠርቶአቸዋልና ፤

ይርኀብኒ ወይፀምዕኒ ወይደክምኒ፣

እንዲህ አድርጎ የሠራቸው ሰው ይራባል፤ ይጠማል፤ ይደክማል፤

፲፫፡ ወኀርዮ ፀራቢ ዕፀ ያቀውም በአ ምጣኑ ፣

እንጨት ጠራቢ እንጨቱን መርጦ በመጠኑ ያቆመዋል ፤

ወያስተጣግያ በኵሉ ፣

በምስማር ያያይዘዋል ፤

ወይገብሮ በአምሳለ ሰብእ ፣

በሰው አምሳል ሦስት ክንድ ከስንዝር አድርጎ ይሠራዋል፣

ወከመ ርእየተ ዕጓለ እመሕያው ፣

በሰው አምሳል እጅ እግር ያወ ጣለታል ፤

www.ethiopianorthodox.org

፲፬፡ ወያቀውሞ ውስተ ቤት ለዝኩ
ዕፅ ዘገዘሞ እምገዳም ፤

ከምድረ በዳ የቈረጠውን ይህን
እንጨት በቤቱ ውስጥ ያቆመ
ዋል ፤

ዘእግዚአብሔር አብቈለ ወበዝናም
አልሐቀ ፤

እግዚአብሔር ያበቀለውን፣ በዝ
ናም ያሳደገውን ፤

፲፭፡ ወይነሥእ እምውስቴቱ ወይስ
ሕን ፤

ከሱ ጭሮ የሞቀለትን ፤

ወያበስል ቦቱ ጎብስተ ፤

እንጀራ የሚያበስልበትን ፤

ወዘተርፈ እምኔሁ ይገብር አማል
ክተ ፤

ከዚህ የቀረውን ጣዖት አድርጎ
ይሠራዋል ፤

፲፮፡ ወይሰግድ ሎቱ ለዝኩ ዘመን
ፈቆ አንደደ በእሳት ፤

እኩሌታውን በእሳት ላነደደው
ለዚህ ይሰግድለታል ፤

ወበመንፈቁ ጠበሰ ሥጋ ፤

በእኩሌታው ሥጋ የጠበሰበትን፤

ወበልዐ ጠቢሶ ጥብሰ ወፀግበ ፤

ጠብሶ የበላበትን የጠገበበትን፤

ወተማወቀ ፤

የሞቀለትን ፤

ወይቤ ሐወዘኒ እስመ አነ ሞቁ ፤

እኔ እሳቱን በሞቅሁ ጊዜ ደስ
አለኝ ያለውን ፤

ወርኢኩ እሳቶ ፤

እሳቱን ባየሁ ጊዜ ደስ አለኝ፤

፲፯፡ ወዘተርፈ ይገብር ሎቱ አማ
ልክተ ዘግልፎ ፤

ከዚህ የቀረውን የተቀረፀ ጣዖት
አድርጎ ይሠራዋል ፤

ወያስተበርክ ወይሰግድ ሎቱ ፤

ሸብረክ ብሎ ይሰግድለታል ፤

ወይጼሊ ኀቤሁ ፤

ከሱ ዘንድ ይጸልያል ፤

ወይብሎ አድኅነኒ እስመ አምላኪየ
አንተ ፤

ፈጣሪዬ አንተ ነህና አድነኝ ይለ
ዋል ፤

፲፰፡ ወኢየአምሩ ወኢይሔልዩ ፤

አያውቁም አያስቡም ፤

ወተጸለላ አዕይንቲሆሙ ፤

ዐይነ ልቡናቸው ተሠውሯል::

፲፱፡ ኢይሬእዩ ወኢይሔልዩ በል
ቦሙ ፤

በዐይናቸው አያዩም በልቡናቸው
አያስቡም ፤

ወኢይትኤዘቡ በነፍሶሙ ፤

በሰውነታቸው አይጠራጠሩም፤

ወኢየአምሩ በምክሮሙ ፤

በምክራቸውም አያውቁም ፤

ከመ መንፈቆ አንደዱ በእሳት ፤

እኩሌታውን በእሳት እንደ አነ
ደዱት ፤

ወከመ አብሰሉ ጎብስተ በመንፈቁ፣

በእኩሌታው እንጀራ እንደጋገ
ሩበት ፤

ወበመንፈቁ ጠበሱ ሥጋ ወበልዑ ፤

በእኩሌታው ሥጋ ጠብሰው
እንደበሉበት ፤

ወዘተርፈ ገብሩ ሎሙ ርኩሰ ፤

ከዚህ የቀረውን ጣዖት አድር
ገው እንደሠሩት ፤

ወሰገዱ ሎቱ ፤

እንደ ሰገዱለትም አያውቁም፤

፳፡ አእምሩ እንከ ከመ ሐመድ
ልቦሙ፣

ልቡናቸው እንደ አመድ ዝርው
እንደሆነ፣ አንድም በአመድ ላይ
የበቀለ እህል እንዳይረባ፣ እንዳ
ይጠቅም አይረቡም ፤ አይጠቅ
ሙም፤ አንድም አመድ የፈሰሰ
በት እህል እንዳያበቅል እነሱም
ምግባር፣ ሃይማኖት የላቸውም፤

ወይጌግዩ በምግባሮሙ ፤

በሥራቸው ይበድላሉ ፤

ወአልቦ ዘይክል አድኅኖተ ነፍሱ እም
ኔሆሙ ፤

ከነዚህም ወገን ነፍሱን ማዳን
የሚቻለው የለም አለ ከሰዎቹ፤

አንድም ከጣዖታቱ የሰዎችን
ሰውነት ማዳን የሚቻለው የለም፤
አንድም ከጣዖታቱ ራሱን ከመ
ሰበር ማዳን የሚችል የለም ፤

፳፩፡ ወኢይሬኢ ፤

አያስተውልም ፤

ወኢይብል ሐሰት ዝንቱ ዘውስተ
እዴየ፣

ይህ በእጄ የሠራሁት ጣዖት
ሐሰት ነው አይልም ፤

፳፪፡ ተዘከር ዘንተ ያዕቆብ ፤

ያዕቆብ ይህን ነገር አስብ ፤

ወእስራኤልኒ ቀኖልዓየ ፤

ወዳጄ እስራኤልም ይህን ነገር
አስብ ፤

አነ ፈጠርኩከ ፤

እኔ ፈጠርሁህ ፤

ገብርየ አንተ እስራኤል ወኢትርስ
ዐኒ ፤

ወዳጄ እስራኤል በሕግ፣ በአም
ልኮት አትዘንጋኝ ፤

፳፪፡ ወናሁ ደምሰስክዎን ከመ ደመና
ለኃጣውኢከ ፤

እነሆ ኃጢአትህን ደመና ተበ
ትኖ እንዲጠፋ አጠፋሁልህ ፤

ወከመ ቆባር ለጌጋይከ ፤

በደልህንም ጭጋግ ተበትኖ እን
ዲጠፋ አጠፋሁልህ፤ ጥቅስ (ወይ
ዘርዎ ለደመና በብርሃኑ) እንዲል
ኢዮ. ፴፯÷፲፩ ፤

www.ethiopianorthodox.org

ተመየጥ ኀቤየ ወአድኀንክ ፣

በሕግ በአምልኮት ወደኔ ተመ
ለስ አድንሃለሁ ፤

ገብዔ

፳፫፤ ይትፌሥሓ ሰማያት ፣

ልዑላኑ ደስ ይላቸዋል ፤

እስመ ተሣህለሙ እግዚአብሔር ለእ
ስራኤል ፣

በሰባ ዘመን እግዚአብሔር እስ
ራኤልን ይቅር ብሏቸዋልና ፤

ወይንፍሑ ቀርነ መሠረታተ ኀምዝ፣

መሠረታተ ምድር ሲል ነው ፤
የትሑታኑ መሠረት የሚሆኑ
ነገሥታቱ ደስ ይበላቸው፤ አን
ድም በቋንቋው ምድርን ኀምዝ
አላት ፤

ወይወውዑ አድባር በፍሥሓ ወአው
ግርኒ በኀሤት ፣

ነገሥታቱ መኳንንቱ በሚጠት
ደስ ይላቸዋል ፤

ወኮሉ ዕፀወ ገዳም ዘውስቴቶሙ ፣

በነገሥታቱ፣ በመኳንንቱ ውስጥ
ያሉ እስራኤል ደስ ይላቸዋል፤

እስመ አድኀነ እግዚአብሔር ለመ
ሢሑ ለያዕቆብ ፣

እግዚአብሔር በሰባ ዘመን ቀብቶ
ያነገሠው ዘሩባቤልን አድኖታ
ልና ፤

ወበእስራኤልኒ ተሰብሐ ፣

በእስራኤልም ሚጠት ተመስግ
ኗልና፤ አንድም ይትፌሥሓ ሰማ
ያት ብለህ መልስ፤ በዕሰተ ትን
ሣኤ መላእክት ደስ ይላቸዋል፤

እስመ ተሣሃለሙ እግዚአብሔር ለእ
ስራኤል ፣

ባምስት ሺህ ካምስት መቶ
ዘመን እግዚአብሔር እስራኤል
ዘነፍስን ይቅር ብሏቸዋልና ፤

ወይንፍሑ ቀርነ መሠረታተ ኀምዝ፣

የኃጢአት መርዝ ያላቸው አጋ
ንንት ያመሰግናሉ፤ ጥቅስ (አእ
መርናከ ከመ አንተ ቅዱሱ ለእ
ግዚአብሔር) ብለዋልና ማር.
ምዕ. ፩ ቊ. ፳፭ ፤

በኢየሱስኒ ነአምን ወለጳውሎ
ስኒ ነአምሮ እንዲል ግብ. ሐዋ.
ም. ፲፱ ቊ. ፲፩ ፤

ወይወውዑ አድባር በፍሥሓ ፣

ጳጳሳት ፣ ሊቃነ ጳጳሳት በትን
ሣኤ ደስ ይላቸዋል ፤

ወአውግርኒ በኀሤት ፣

ኤጲስ ቆጳሳት ቀሳውስት ደስ
ይላቸዋል ፤

ወኮሉ ዕፀወ ገዳም ዘውስቴቶሙ፣

በሊቃነ ጳጳሳት በጳጳሳት ውስጥ
ያሉ ምዕመናን ደስ ይላቸዋል፤

እስመ አድኀኖ እግዚአብሔር ለመ
ሢሑ ለያዕቆብ ፣

ባምስት ሺህ ካምስት መቶ
ዘመን እግዚአብሔር ያዕቆብ ዘነ
ፍስን አድኖታልና ፤

ወበእስራኤልኒ ተሰብሐ ፣

በእስራኤል ዘነፍስ ድኀነትም
ተመስግኗልና ይትፌሥሓ ብለህ
እሠር ፤

፳፬፤ ከመዝ ይቤ እግዚአብሔር ዘአ
ድኀነከ ወፈጠረከ በውስተ ከርሠ
እምከ ፣

በእናትህ ማኅፀን የፈጠረህ ያዳ
ነህ እግዚአብሔር እንዲህ አለ፤

አነ እግዚአብሔር ዘገበርኩ ኵሉ ባሕ
ቲትየ ፣

ሁሉን የፈጠርሁ እኔ ብቻ ነኝ፤

አነ ሰፋሕክዎ ለሰማይ ወአዕናዕክዋ
ለምድር ፣

ሰማይን የዘረጋሁት ፣ ምድርን
ያፀናኋት እኔ ነኝ ፤

፳፭፤ መኑ ባዕድ ዘይመይጥ ምክ
ሮሙ ለእለ ያንቅሑ በፃውዕ ፣

በምትሐት ፤ አንድም በጸውያ
ይላል፤ ስመ አጋንንትን ጠርተን
ሙት እናስነሣለን የሚሉትን
ሰዎች ምክራቸውን የሚለውጥ
ማነው ፤

ወለእለ ያስግሉ እምልቦሙ ፣

ከልቡናቸው አንቅተው የሚጠ
ነቀሉትን ሰዎች ምክራቸውን
የሚለውጥ ሌላ ማነው ፤

ወያገብአሙ ድኅሬሆሙ ለጠቢባን፣

የጦር ጥበብ እናውቃለን የሚ
ሉትን አድሮ አነስ የሚያደር
ጋቸው ማነው ፤

ወያለስሕ ምክሮሙ ፣

የጦር ምክር እናውቃለን የሚሉ
ትን ምክራቸው እንዳይወደድ
የሚያደርግ ማነው ፤

፳፮፤ ወያቀውም ቃለ ገብሩ ፣

የባርያው የኢሳይያስን ቃል የሚ
ያፀና እሱ ነው ፤

ወያጸድቅ ምክረ መላእክቲሁ ፣

ያለቆችን ምክር እውነት የሚ
ያደርግ እሱ ነው

ዘይብላ ለኢየሩሳሌም ትነብሪ ፣

ኢየሩሳሌምን ፀንተሽ ትኖሪያ
ለሽ ያላት እሱ ነው ፤

ወለአህጉረ ይሁዳኒ ትትሐነፃ ፣

የይሁዳን አውራጃ ትሠሪያለሽ
ያላት እሱ ነው ፤

ወይበቍሉ አሕቃላቲሃ ፣

አውራጃዎቿ ሁሉ ይቀናሉ፤ አን
ድም አውራጃዎቿ ሁሉ ይለመ
ልማሉ ፤

፳፯፤ ወይብላ ለቀላይ ይበሲ ፣

ኤርትራን ዮርዳኖስን ደረቅ
ሁኝ ፤

ወይንጽፉ አፍላጋትኪ ፣

ፈሳሾችሽ ይድረቁ የሚላት እሱ
ነው፤ አንድም ባቢሎንን ጥፊ

www.ethiopianorthodox.org

የሚላት እሱ ነው ፤ ነገሥታቶ
ችሽም ይጥፉ ፤

፳፰፡ ዘይብሎ ለቂሮስ ጥበብ ወሐሊ ፣

ቂሮስን ብልህ ሁን ሚጠትን
አስብ ፤

ወግበር ኵሎ ፈቃድየ ፤

ፈቃዴን ሁሉ አድርግ የሚለው
እሱ ነው ፤

ዘይብላ ለኢየሩሳሌም ትትሐነፂ ፣

ኢየሩሳሌምን ትሠሪያለሽ ያላት
እሱ ነው ፤

ወእሣርራ ለቤተ መቅደስየ ፣

ቤተ መቅደስን እሠራታለሁ ::

ምዕራፍ ፵፭

፩፡ ከመዝ ይቤ እግዚአብሔር አም
ላክ ፣

ፈጣሪ የሚሆን እግዚአብሔር
እንዲህ አለ ፤

ለመሢሕየ ቂሮስ ዘአኀዝክዎ በእዴየ
ከመ አስምዖሙ ለአሕዛብ በቅድ
ሜሁ ፣

አግርሮሙ ሲል ነው ፤ ቀብቼ ያነ
ገሥሁት ቂሮስን በሥልጣኔ የያ
ዝሁት አሕዛብን በፊቱ አስገዛ
ለት ዘንድ ነው አለ ፤

ወእነጽሕ ኃይለ ነገሥት ፣

የነገሥታቱን ኃይል የነገሥታ
ቱን ሠራዊት አጠፋለሁ አለ ፤

ወአርኁ አናቅጸ በቅድሜሁ ወኢይ
ትዐፀዋ አህጉር ፣

በፊቱ በሩን እከፍታለሁ፤ አንድም
ዐርበኛውን አጠፋለሁ፤ አምባዎ
ቹም አይዘጉም አለ ፤

፪፡ አነ አሐውር ፍጽመ ቅድሜከ ፣

እኔ በፊትህ ፊታውራሪ ሁኜ እሄ
ዳለሁ ፤

ወአቴሕቶሙ ለአድባር ፣

ነገሥታቱን አዋርዳቸዋለሁ ፤

ወእሰብር አናቅጸ ብርት ፣

የብርቱን ደጅ እሰብራለሁ ፣
ማለት ኀያላኑን አጠፋለሁ ፤

ወእቀጠቅጥ መናሥግተ ዘሐፂን ፣

የብረቱን ቍልፍ እቀጠቅጣለሁ
ማለት ዐርበኛውን አጠፋለሁ ፤

፫፡ ወእሁበከ መዛግብተ ኅቡዐ ፣

የተሠወረውን ገንዘብ እሰጥሃ
ለሁ ፤

ወክሡተ ዘኢያስተርኢ እከሥት ለከ፣

በማጀት የተቀበረውን ፣ በቆጥ
የተሰቀለውን እገልጥልሃለሁ፤ ለወ
ታደር የሰጠው ቃል ኪዳን ይህ
ነው ፤

ከመ ታእምር ከመ አነ ውእቱ እግ
ዚአብሔር ዘሰመይኩ ስመከ አምላከ
እስራኤል ፤

ስምህን ቂሮስ ብዬ የጠራሁህ
የእስራኤል ፈጣሪ እግዚአብሔር
እኔ እንደ ሆንሁ ታውቅ ዘንድ፤

፬፡ በእንተ ቍልዔየ ያዕቆብ ወእስ
ራኤልኒ ኅሩይየ አነ እጼውዐከ በስ
ምየ ፣

ስለ ወዳጄ ስለ ያዕቆብ ፣ ስለ
መረጥሁት ስለ እስራኤል በስሜ
ቂሮስ ብዬ እጠራሃለሁ አለ ፤
ቂሮስ ማለት መሢሕ ማለት
ነውና ፤

ወእትዌከፈከ ፣

በረድኤት እቀበልሃለሁ ፤

፭፡ ወአንተሰ ኢያእመርከኒ ከመ አነ
ውእቱ እግዚአብሔር አምላክከ ወአ
ልቦ ባዕድ አምላክ ዘእንበሌየ ፣

አንተ ግን ፈጣሪህ እኔ እንደ
ሆንሁ ከኔ በቀር ሌላ ፈጣሪ እንደ
ሌለ በሕግ በአምልኮት አላወቅ
ኸኝም አለ ፤

አፅናዕኩከሂ ወኢያእመርከኒ ፣

በረድኤት አፀናሁህ አንተ ግን
አላወቅኸኝም ፤

፮፡ ከመ ያእምሩ እለ እምሥራቀ
ፀሐይ ወእለሂ እምዕራብ ከመ አልቦ
ባዕድ አምላክ ዘእንበሌየ ፣

ከኔ በቀር ሌላ ፈጣሪ እንደሌለ
በምሥራቅም በምዕራብም ያሉ
ሰዎች ያውቁ ዘንድ አፀናሁህ
አንተ ግን አላወቅኸኝም ፤

፯፡ አነ ፈጠርኩ ብርሃነ ወገበርኩ
ጽልመተ ፣

በምሥራቅም በምዕራብም ያሉ
ሰዎች ከኔ በቀር ያለኔ ሌላ
ፈጣሪ እንደሌለ ያውቁ ዘንድ
ብርሃንን ጨለማን የፈጠርሁ
እኔ ነኝ፤ አንድም ማካፈል ነው፤
በምሥራቅ ያሉ ሰዎች ያውቁ
ዘንድ አፀናሁህ፤ አንተ ግን አላ
ወቅኸኝም ፤ በምዕራብም ያሉ
ሰዎች ከኔ በቀር ያለኔ ሌላ
ፈጣሪ እንደሌለ ያውቁ ዘንድ
እኔ ጨለማን ፣ ብርሃንን ፈጠ
ርሁ ፤

አነ እፈጥር ሰላመ ወአመጽእ እኪተ፣

ፍቅር አንድነትን የማደርግ ፣
መከራን የማመጣ እኔ ነኝ፤ አን
ድም ተድላ ደስታን የማደርግ፣
መከራን የማመጣ እኔ ነኝ፤ አን
ድም ሚጠትን የማደርግ ዔዋ
ዌን የማመጣ እኔ ነኝ ፤

አነ እግዚአብሔር አምላክ ዘእገብር
ዘንተ ኵሎ ፣

ይህን ሁሉ የማደርግ ፈጣሪ እግ
ዚአብሔር እኔ ነኝ ፤

፰፡ ትትፌሣሕ ሰማይ በላዕሉ ፣

ሰማይና በላዕሉ አንድ ወገን
ከምድር በላይ ያለች ሰማይ ደስ
ይላታል ማለት ዝናም ለዘር፣
ጠል ለመከር ትሰጣለች ፤

ወይነሰንሳ ጽድቀ ደመናት ፣

ደመናትም ዝናም ያዘንማሉ፣

ወታበቍል ምድር ርትዐ ኅቡረ ፣

ምድርም የዘሩባትን ታበቅላለች፤
የተከሉባትን ታጸድቃለች፤

www.ethiopianorthodox.org

አንድም ትተፈሣሕ ሰማይ ብለህ መልስ፤ ልዑላኑ ደስ ይላቸዋል፤ ነቢያት ካህናትም ትምህርትን ያስተምራሉ፤ ቤተ እስራኤልም ትምህርቱን ትቀበላለች ፤ (ምግባር ሃይማኖት ትይዛለች ብት ልም ይሆናል) ፤

አነ እግዚአብሔር አምላክከ፡ ዘፈጠርኩከ ፣

የፈጠርሁህ ፈጣሪ እግዚኦብሔር እኔ ነኝ ፤

፱፡ ወዘአኅየስኩከ ፣

በደማዊት ነፍስ ከአዝርዕት ከአትክልት ከዕፀው ከአዕባን ፣ በነባቢት ነፍስ ከእንስሳት ከአራዊት፣ በምግባር በሃይማኖት ከአሕዛብ ያሻልሁህ እኔ ነኝ ፤

ወገባርኩከ ከመ ዕቡረ ለብሐዊ ዘየሐርስ ምድረ ፣

ዘይከሪ ምድረ ሲል ነው፤ ምድርን እንደሚቆፍር እንደ ሸክላ ሠሪ ጭቃ አደረግሁህ ፤

ቦኑ ይብሎ ዕቡር ለለብሐዊ ምንተ ገበርከኒ ፣

ጭቃ ሠሪውን ለምን እንዲህ አድርገህ ሠራኸኝ ይለዋልን ፤

አስመ ኢትክል ገቢረ ፣

እኔን መሥራት አይቻልህምና፤

ወአልብከ እደው ፣

እኔን የምትሠራበት እጅ የለህ ምና ለምን እንዲህ አድርገህ ሠራኸኝ ይለዋልን፣ እንደዚህስ ሁሉ እንደ ወደድሁ የማደርጋ ችሁ አይደለም ፤ የለዘበውን ብርሌ ብርጭቆ ቢያደርገው ፣ ኩስኩስት ድስት አድርገኝ ያለ ዘበውን ኩስኩስት ድስት ቢያ ደርገው ብርሌ ብርጭቆ አታ ደርገኝም ነበር ይለዋልን፤ እንደ ዚህስ ሁሉ እንደ ወደድሁ የማ ደርጋችሁ አይደለምን፤ በጎ በጎ ምችን ባድን ክፉ ክፉዎችን ባጠፋ ለምን እንዲህ አደረግህ የሚለኝ አለን ፤

፲፡ አሌ ሎቱ ለዘይብሎ ለአቡሁ ምንተ ወለድከኒ ፣

ማእዜ ወለድከኒ ሲል ነው፣ ርዳኝ አጥባኝ ባለው ጊዜ አባቱን መች ወለድኸኝ ለሚለው ወዮለት ፤

ወለእሙኒ በዓይ ማሕምምኪ ፣

እናቱንም መቼ አምጠሽ ወለ ድሽኝ ለሚላት ወዮለት ፤ አን ድም ለምንት ወለድከኒ፤ መከራ በመጣበት ጊዜ አባቱን ለምን ወለድኸኝ ለሚለው ወዮለት ፤ እናቱንም ለምን አምጠሽ ወለ ድሽኝ ለሚላት ወዮለት ፤ አን ድም እግዚአብሔርን ለምን ፈጠ ርኸኝ ለሚለው ወዮለት ፤ ሕግ ንም ለምን ተሠራችልኝ ለሚላት ወዮለት ፤ አንድም አባቱ እግዚ አብሔርን መቼ ሕግ ሠራህልኝ ለሚለው ወዮለት ፤

፲፩፡ እስመ ከመዝ ይቤ እግዚአብሔር አምላክ ቅዱሰ እስራኤል ዘገብረ ዘይመጽእ ፤

የሚመጣ ሚጠትን ያደረገ ፅንዐ እስራኤል ክብረ እስራኤል እግዚአብሔር እንዲህ ብሏልና ፤

ተሰአሉኒ በእንተ ደቂቅየ ወአዋልድየ ፣

ስለወንዶች ልጆቼ ፣ ስለሴቶች ልጆቼ ጠይቁኝ ብሏልና ፤

ወበእንተ ግብረ እደውየ አዝዙኒ ፣

የእጄ ፣ የቃሌ ፍጥረት ስለሚሆኑ እዘዙኝ ብሏልና ለምነውት ማድረጉን መታዘዝ ብሎት አዝዙኒ አለ ፤ አንድም አዝዙ ብየ ይላል ፣ አዘዙብኝ አለ ነቢያት ካህናት የለመኑትን ያደርግላቸ ዋልና አዝዙብኝ አለ ፣

፲፪፡ አነ ፈጠርክዋ ለምድር ፣

ምድርን የፈጠርኋት እኔ ነኝ ፤

ወሰብአ ዲቤሃ ፣

በሷ ላይ ሰውን የፈጠርሁ እኔ ነኝ ፤

አነ በእዴየ አዕናዕክዎ ለሰማይ ፣

ሰማይን በሥልጣኔ ያፀናሁት እኔ ነኝ ፤

ወአነ አዘዝክዎሙ ለኮሎሙ ከዋክብት ፣

ከዋክብትን ሁሉ የማዝዛቸው እኔ ነኝ ፤

፲፫፡ ወአነ አንሣእክዎ ለጻድቅ ፣

ጻድቅ ዘሩባቤልን፤ አንድም ሕዝ ቅያስን፣ ቂሮስን ያስነሣሁት እኔ ነኝ ፤

ወሠራሕኩ ኵሎ ፍኖቶ ፣

ከባቢሎን ወደ ኢየሩሳሌም ለመ ሄድ የዘሩባቤልን ጐዳናውን አቀ ናሁለት ፤ አንድም ሕገ አሪትን ሠራሁለት ፤

ወውእቱ የሐንፅ ሀገርየ ፣

ዘሩባቤል ቤተ መቅደስን ይሠ ራል ፤

ወይመይጥ ፄዋ ሕዝብየ ፤

የወገኖቼ የእስራኤልንም ምርኮ ይመልሳል ፤

አኮ በቤዛ ወአኮ በሕልያን ይቤ እግዚአብሔር ፀባዖት ፣

ይኸውም ገንዘብ ሰጥቶ ፣ ሚሣ ለኛ ሰጥቶ አይደለም በቸርነቱ ነው እንጂ አለ አሸናፊ እግዚ አብሔር ፤ አንድም ወአነ አንሣ እክዎ ለጻድቅ ብለህ መልስ ፤ ጻድቁ ባሕርይ ክርስቶስን ያስነ ሣሁት እኔ ነኝ ፤

ትንሣኤውን አከናወንሁለት ፤ አንድም ወደ ገነት፣ ወደ መንግ ሥተ ሰማያት ለመሄድ የምዕ መንን ጐዳናውን አቀናሁለት ፤ አንድም ወንጌልን ሠራሁለት፤ ጌታ ገነት መንግሥተ ሰማይን

www.ethiopianorthodox.org

ያቀናል፤ የወገኖቼ የምዕመናንን ምርኮ ይመልሳል፤ እጅ መንሻ ማግለጃ ተቀብሎ አይደለም ፤ ሰው ሁኖ ሥጋ ለብሶ በሥጋው በደሙ ነው እንጂ ፤ ጥቅስ (አኮ በወርቅ ኃላፊ ዘተሣየጠነ አላ በደሙ ክቡር ቤዘወነ እንዲል ፩ኛ ጴጥ. ምዕ. ፩ ፥ ፲፰ ፥ ፲፱ ፤)

፲፩፤ ከመዝ ይቤ እግዚአብሔር ፀባያት ፣

አሸናፊ እግዚአብሔር እንዲህ አለ ፤

ሠርሑ ግብዕ ወመስተገብራነ ኢትዮጵያ ፣

የግብዕ ሰዎች በኢትዮጵያ ያሉ ነጋድያን በሚጠት ለዘሩባቤል ግብር በማመላለስ ደከሙ ፤

ወሰብአ ሳባ ፣

የሩስቆሉ ሰዎች

ወሰብአ ርኁቃን ይመጽኡ ኀቤከ ፣

በሩቅ ያሉ አሕዛብ በሚጠት አምነው ወዳንተ ይመጣሉ ይለ ዋል ዘሩባቤልን ፤

ወይትቀነዩ ለከ ፣

ይገዙልሃል ፣

ወይተልዉ ድኅሬከ እንዘ ሙቁሓን እደዊሆሙ ፣

እጃቸውን በሰንሰለት ታሥረው ይከተሉሃል ፤

ወይሰግዱ ለከ ወይጼልዩ ኀቤከ ፣

ላንተ ይሰግዳሉ ፤ ካንተ ዘንድ ይለምናሉ ፤

እስመ እግዚአብሔር ምስሌከ ፣

እግዚአብሔር ካንተ ጋራ በረድኤት አለና ፤

ወአልቦ እግዚአብሔር ዘእንበሌከ ባዕድ ፤

እግዚአብሔር ያደረበት ካንተ በቀር ሌላ ፈጣሪ የለምና፤ አንድም ባንተ አድሮ ካለ እግዚአብሔር በቀር ሌላ አምላክ የለምና፤ አንድም ሠርሑ ግብዕ ብለህ መልስ ፤ የግብፅ ፣ የኢትዮጵያ ፣ የሩስቆሉ ምዕመናን ምግባር ትሩፋት በመሥራት ዐሥራት፣ በኵራት በማውጣት ደከሙ፤

ወሰብእ ርኁቃን ይመጽኡ ኀቤከ ፣

ከምግባር ከሃይማኖት የራቁ አሕዛብ በዘመነ ሐዲስ ወዳንተ ይመጣሉ ፤

ወይትቀነዩ ለከ ፣

ይገዙልሃል ፤

ወይተልዉ ድኅሬከ እንዘ ሙቁሓን እደዊሆሙ ፣

እደ ልቡናቸውን በፍቅር ሰንሰለት ታሥረው ይከተሉሃል ፤

ወይሰግዱ ለከ ወይጼልዩ ኀቤከ ፣

ላንተ ይሰግዳሉ ፤ ካንተ ዘንድ ይጸልያሉ ፤ አንድም ብከ ይላል ፤

ባንተ ይጸልያሉ ፤ በዋሕድ ወልድከ ፣ በሥግው ወልድከ ፣ በስቁል ወልድከ፣ በቅንው ወልድከ እያሉ ፤

እስመ እግዚአብሔር ምስሌከ ፣

እግዚአብሔር አብ በህልውናህ አለና ፤

ወአልቦ እግዚአብሔር ዘእንበሌከ ባዕድ ፣

እግዚአብሔር አብ በህልውናው ያለ ካንተ በቀር ሌላ የለምና ፤ አንድም እግዚአብሔርነትህ ካንተ ጋራ አለና እግዚአብሔርነት ያለው ካንተ በቀር ሌላ የለምና፤

፲፭፤ አንተ እግዚአብሔር ፣

ፈጣሪ አንተ ብቻ ነህ ፤

ወኢያእመርናከ አምላከ እስራኤል ማሕየዊ ፣

ማሕየዊ የምትሆን የእስራኤልን ፈጣሪ እኛ ግን በሕግ በአምልኮት አላወቅንህም ፤

፲፮፤ ለይትኀፈሩ ወይኅሠሩ ኵሎሙ እለ ይትቃወሙከ ፣

አንተን የሚቃወሙ ሰዎች ሁሉ ይፈሩ፣ ይጐስቀሉ ፤

ወይሑሩ ተኀፈሮሙ ፣

አፍረው ይመለሱ ፣

፲፯፤ ተመየጡ መንገሌየ ደሰያት ፣

ደሴት በውሀ፣ ውሀ በደሴት እንዲከበብ በመከራ የተከበባችሁ እስራኤል በሕግ በአምልኮት ወደኔ ተመለሱ ፤

እስመ አድኀንክሙ ይቤ እግዚአብሔር አምላከ እስራኤል መድኃኒተ ዘለዓለም ፣

የእስራኤል ፈጣሪ እግዚአብሔር ለዘለዓለም የምትሆን ሚጠትን አድርጌ አድናችኋለሁ ብሏልና፤

ኢትትኀፈሩ ወኢተኀሥሩ እስከ ለዓለም ፣

ለዘለዓለሙ አታፍሩም አትዋረዱም ብሏልና ፣

፲፰፤ ከመዝ ይቤ እግዚአብሔር ዘገብረ ሰማየ ፣

ሰማይን የፈጠረ እግዚአብሔር እንዲህ አለ ፤

ወውእቱ እግዚአብሔር ዘአርአያ ለምድር ፣

በፍጥረት ጊዜ ምድርን የገለጣት እሱ እግዚአብሔር ነው፤ በውሀ ተሸፍና ነበርና ፤

ወገብራ ወሰጠቃ ፣

የፈጠራት፣ ከሰባት የከፈላት እሱ ነው ፤ ጥቅስ (ወጎተምኩኪ በሰባቱ ማኅተም እንዲል)

ወአኮ ለከንቱ ዘገብራ ፣

የፈጠራትም ለከንቱ አይደለም፤

ዳዕሙ ከመ ይንበሩ ውስቴታ ፈጠራ፣

ደቂቀ አዳም በውስጧ ይኖሩባት ዘንድ ፈጠራት እንጂ ፤

www.ethiopianorthodox.org

አንድም ወውእቱ እግዚአብሔር ዘአርአያ ለምድር ብለህ መልስ፤ በኖኅ ጊዜ ምድርን የገለጣት እሱ ነው ፤

ወገብራ ወሰጠቃ ፣

የብስ ያደረጋት፤ ከሦስት የከፈላት እሱ ነው ፤ የመልአክ ዳኛ አውርዶ ቀኝ ቀኙን ለያፌት ፣ ግራ ግራውን ለካም መካከሉን ለሴም አካፍሏቸዋልና ፤

ወአኮ ለከንቱ ዘገብራ ፣

የብስ ያደረጋት ለከንቱ አይደለም፤ ደቂቀ ኖኅ በውስጧ ይኖሩባት ዘንድ ነው እንጂ ፤ አንድም ኤርትራን የገለጣት እሱ ነው፤ ምድር አላት እንደ ምድር ፀንታ ነበርና ፤

ወገብራ ወሰጠቃ ፣

የብስ ያደረጋት ከሦስት ከፀራት የከፈላት እሱ ነው ፤

ወአኮ ለከንቱ ዘገብራ ፣

የብስ ያደረጋት ለከንቱ አይደለም ፣

ዳዕሙ ከመ ይንበሩ ውስቴታ ፈጠራ፤

ይኅልፉ ውስቴታ ሲል ነው፤ እስራኤል ይሄዱባት ዘንድ ነው እንጂ ፤

አነ ውእቱ አምላክ ፣

ፈጣሪ እኔ ነኝ ፤

ወአልቦ ባዕድ አምላክ ዘእንበሌየ ፣

ከኔ በቀር ሌላ ፈጣሪ የለም ፤

፲፱፤ ወአኮ ጽሚተ ዘተናገርኩ ወአኮ በብሔረ ጽልመት ዘነበብኩ ፣

አምላክነቴን ሠውሬ ቀስ ብዬ የተናገርሁ አይደለም፤ አንድም በቆይታ በቀስታ የተናገርሁ አይደለም ፤ አንድም ከጸፈቀ ዱር ከጕደጕደ ምድር የተናገርሁ አይደለም ፤

ወኢይቤሎ ለዘርዐ ያዕቆብ ከመ ይኅሥሥ ከንቶ ፣

የያዕቆብን ልጅ ከንቱ ጣዖትን ይሻ ዘንድ ሻ ያልሁት አይደለም፤

አነ ውእቱ እግዚአብሔር ዘእነግር ጽድቀ ወአየድዕ ጥበበ ፣

እውነት ነገርን የምናገር ፣ ጥበብን የምገልጥ ፈጣሪ እኔ ነኝ ፤

፳፤ ተጋብዑ ወንዑ ፣

ተሰብሰባችሁ ኑ ፤

ወተማከሩ ኀቡረ እለ ድኅንከሙ እም አሕዛብ ፣

ከአሕዛብ የዳናችሁ እስራኤል አንድ ሁናችሁ ተማከሩ ፤

ኢያእመሩ መላእክት እለ ይገልፍዎ ለዕፅ ፣

እንጨቱን የሚቀርፁ አለቆች አላወቁም ፤

ወይጸልዩ ኀቤሁ ከመ ዘኀበ አማልክት እለ ኢያድኅኑ ፣

ከማያድኑ ከፀሐይ ፣ ከጨረቃ እንዲለምኑ ከወርቁ ፣ ከብሩ ፣

ከእንጨቱ ምስል የሚለምኑ አላወቁም ፣ አንድም ራሳቸውን ከሞት የማያድኑ ሰዎች ከፀሐይ፣ ከጨረቃ ከዕፀው ከአዕባን እንዲለምኑ ፣ አንድም እለ ያድኅኑ ይላል ፣ ሰዎች ከሚያድኑ ከሥላሴ እንዲለምኑ ከእንጨቱ ከደንጊያው የሚለምኑ አለቆች አላወቁም ፤

፳፩፤ ወእመሰ ይነግሩ ይቅረቡ ወያእምሩ ኀቡረ መኑ ዘገብረ ዘንተ ስምዐ እምትካት ፣

የሚናገሩስ ከሆኑ ከጥንት ጀምሮ ይህን ምስክር ያደረገ ማነው ፣ አንድ ሁነው ቀርበው ይወቁ ፤

ቦኑ አመ ነገሩክሙ ከመ አነ እግዚአብሔር ፣

ፈጣሪ እኔ እንደሆንሁ የነገርኋችሁ ጊዜ አለ ፤ አንድም በውኑ የነገርኋችሁ መንገር አለን ፤ ቦኑ ባለው ቦሁ ይላል ፤ ቦኑ ማለት ነው ፤

ወአልቦ ባዕድ አምላክ ዘእንበሌየ ጻድቅ ወማሕየዊ ፣

ማሕየዊ ቸር ከምሆን ከኔ በቀር ሌላ ፈጣሪ የለም ፤ አንድም ያለ እኔ ጻድቅ ማሕየዊ ፈጣሪ የለም፤

ወአልቦ እንተ ከማየ ፣

እንደ እኔ ያለ ፈጣሪ የለም ፤ አይኑር ፤

፳፪፤ ተመየጡ ወተሐይዉ እለ እም አጽናፈ ምድር ፣

በጽንፈ ምድር ያላችሁ አሕዛብ ከኃጢአት ወደ ሥርየት ፣ ከአምልኮተ ጣዖት ወደ አምልኮተ እግዚአብሔር ተመለሱ ፤ ትድናላችሁ ፤

አነ ውእቱ እግዚአብሔር ወአልቦ ባዕድ አምላክ ዘእንበሌየ ፣

ፈጣሪ እኔ ነኝ ከእኔ በቀር ሌላ ፈጣሪ የለም ፤

፳፫፤ መሐልኩ በርእስየ ከመ ኢይመይጥ ቃልየ ዘወፅአ እምአፉየ ፣

ካፌ የወጣውን ነገር እንዳልሰውጥ ሕያው አነ አማንየ በርእስየ ብዬ ማልሁ ፤

አስመ ሊተ ይሰግድ ኵሉ ብርክ ፣

በሚጠት የሰው ሁሉ ብርክ ልቡና ይሰግድልኛልና ፤

ወኵሉ ልሳን ይገኒ ለእግዚአብሔር፣

የሰው ሁሉ አንደበት ለእግዚአብሔር ይገዛልና መሐልኩ ብለህ እሠር፤ አንድም በሐሙስ ዕለት ያልሁትን ቃሌን እንዳልለውጥ አማንየ በርእስየ ሕያው አነ ለዓለም ብዬ ማልሁ ፤ የሰው ሁሉ ብርክ ልቡና ይሰግድልኛልና ፤

እንዘ ይብል ስብሐት ወጽድቅ ኀቤሁ ይመጽኡ ፣

ጌትነት ክብር ወደ እርሱ ይመጣሉ ማለት ከሱ ይገኛሉ እያለ፣

www.ethiopianorthodox.org

አንድም ኋላ በምጽአት ቃሌን እንዳልለውጥ አማንየ በርእስየ ሕያው አነ ብዬ ማልሁ ፤ የሰው ሁሉ ብርከ ልቡና ይሰግድልኛ ልና ፣ የሰው ሁሉ አንደበት ለእ ግዚአብሔርነቴ ይገዛልና ፣ ክብር ቸርነት ከሱ ይገኛል እያለ ይገ ዛልና መሐልኩ ብለህ እሠር ፤

፳፬፡ ወይትኀፈሩ ኵሎሙ እለ ይር ኅቁ እምእግዚአብሔር ፣

ኃጢአት ሠርተው ከእግዚአብ ሔር የሚርቁ ሰዎች ሁሉ መከራ መጥቶባቸው ያፍራሉ ፤

፳፭፡ ወይሴባሕ ወይጸድቅ ኵሉ ዘርዐ ደቂቀ እስራኤል በእግዚአብ ሔር ፤

የእስራኤል የልጅ ልጅ ሁሉ በእግዚአብሔር አምኖ ይከብ ራል ፤ ይመሰገናል ::

ምዕራፍ ፵፮

ጉባዔ

፩፡ ወድቀ ቤል ወተቀጥቀጠ ዳጎን ፣

ቤል የፈረስ ምስል ነው ፤ ዳጎን የሰው ምስል ነው ፤ ጠፋ ፤

ወኮነ ግልፎሙ ከመ መሬት ፣

ጣዖታቸው እንደ መሬት የተ ናቀ ሆነ ፤

ወይከይድዎ አራዊት ወእንስሳ ፣

እንስሳት አራዊት ይረጋግጡ ታል ፤

ወኢያነሥእዎሙ ፣

አያነሡዋቸውም ፤

እስመ ኀሡራን እሙንቱ ከመ ፆረ ኵስሕ ፤

እንደ ውሻ ፋንድያ ጐስቋሎች ናቸውና ፤

፪፡ ወድኩማን እሙንቱ ወአልቦሙ ኀይል ፣

ድኩማን ናቸውና ኀይል የላቸ ውም ፤

ወኢይክሉ አድኅኖ ርእሶሙ እምቀ ትል ፣

እምተሰብሮ ሲል ነው ፤ ጣዖታቱ ራሳቸውን ከመሰበር አያድኑም ፤

ወለርእሶሙኒ ዓዲ ይዜውውዎሙ ፣

ዳግመኛ ይማርኳቸዋል ፤ አን ድም ወድቀ ቤል ብለህ መልስ ፤

ንስጥሮስ ተረታ ፤ ዮሐንስ ዘአን ጾኪያም ለማውገዝ ቀረበ ፤

ወኮነ ግልፎሙ ከመ መሬት ፣

የነንስጥሮስ ክርክራቸው እንደ ትቢያ ሆነ ፤

ወይከይድዎ አራዊት ወእንስሳ ፣

ምዕመናነ አሕዛብ ፣ ምዕመናነ እስራኤል ይሠለጥኑበታል ፤

ወኢያነሥእዎሙ ፣

እነንስጥሮስን አያከብሯቸውም ፤

እስመ ኀሡራን እሙንቱ ከመ ፆረ ኵስሕ ፣

እንደ ውሻ ፋንድያ ጐስቋሎች ናቸውና ፣

ወድኩማን እሙንቱ ወአልቦሙ ኀይል ፣

ድኩማነ አእምሮ ናቸውና ፣ ዕው ቀትም የላቸውምና ፤

ወኢይክሉ አድኅኖ ርእሶሙ እምቀ ትል ፣

ራሳቸውን ከመረታት አያድ ኑም ፤

ወለርእሶሙኒ ዓዲ ይዜውውዎሙ ፣

ዳግመኛ ይረቷቸዋል ፤

፫፡ ስምዑኒ ቤተ ያዕቆብ ፣

የያዕቆብ ወገኖች ስሙኝ ፤

ወኵልክሙ እለ ተረፍክሙ እምእስ ራኤል ፣

ከእስራኤል የቀራችሁ ሁላችሁ ስሙኝ ፤

እለ ትዜኅሩ እምንዕስክሙ ፣

ከሕፃንነታችሁ ጀምሮ የምትታ በዩ ስሙ ፤

፬፡ ወኢተገሠጽክሙ እምከርሠ እም ክሙ እስከ ትረስዑ ፣

ከናታችሁ ማኅፀን ከወጣችሁ ጀምሮ እስክታረጁ ድረስ አል ተሠራችሁም ፤ አልተቀጣችሁም አነ ውእቱ ማንሻ ፤ አንድም አእ ምሮ እስክታጡ ድረስ ፤

አነ ውእቱ አምላክክሙ ፣

ፈጣሪያችሁ እኔ ነኝ ፤

እስከ ትልሕቁ እትዔገሠክሙ እም ንዕስክሙ ፣

እስከ ትልሕቁ ሲል ነው ፤ ከሕ ፃንነታችሁ ጀምሮ እስክታረጁ ድረስ እታገሣችኋለሁ ፤

አነ ገበርኩ ወአነ ተሣሃልኩ ፣

እኔ ዔዋዌን ሚጠትን አደረግሁ ፤

ወአነ እትዌከፈክሙ ወአድኅነክሙ ፣

እኔ በረድኤት ተቀብዬ አድና ችኋለሁ ፤

፭፡ በመኑ እንከ ታስተማስሉኒ ይቤ እግዚአብሔር ፣

እንዲህ የምሆን እኔን በምን ትመስሉኛላችሁ አለ እግዚአ ብሔር ፤

ርእዩ ወተኬነዉ ኵልክሙ እለ ታስ ተሐቅሩኒ ፣

የምትንቁኝ ፣ የምታቃልሉኝ ሰዎች ሁሉ አስተውሉ ፣ ተራ ቀቁ ፤

፮፡ ወእለ ታወፅኡ ወርቀ ወብሩረ እምውስተ ቁናማቲክሙ ፣

ወርቁን ፣ ብሩን ከዕቃ አቁማዳ ችሁ የምታወጡ ፤

ወትደልውዎ በመዳልው ፣

በሚዛን የምትመዝኑት ፤

www.ethiopianorthodox.org

ወተዐስብዎ ለነህቢ ፣

ጣዖት አድርገህ ሥራልን ብላ
ችሁ ለጃን ሸላሚ የምትሰጡት፤
አንድም ለጃን ሸላሚ ዋጋ አድ
ርጋችሁ የምትሰጡት ፤

ወይገብሮ ለክሙ ግብረ እደ ሰብእ፣

ሰው ሠራሽ ጣዖት አድርጎ የሚ
ሠራላችሁ ፤

ወታደንኑ ወትሰግዱ ሎቱ ፣

አንገታችሁን ስብር አድርጋችሁ
የምትሰግዱለት ሁሉ አስተውሉ፤

፯፡ ወይሰክምዎ ዲበ መትክፍቶሙ
ወየሐውሩ ፣

በትከሻቸው ተሸክመውት ይሄ
ዳሉ ፤

ወእምከመ አንበርዎ ኢይትሐወስ እንከ
እምንባሩ ፣

ካስቀመጡትም በኋላ ካለበት
አይንቀሳቀስም ፤

ወእመኒ ዐውየዉ ኀቤሁ ኢይሰምዕ፣

ወደሱ ቢጮሁ አይሰማም ፤

ወኢያድኅን ርእሶ እምእኩይ ፣

እምተሰብሮ ሲል ነው ፤ ራሱን
ከመሰበር አያድንም ፤

፰፡ ተዘከሩ ዘንተ ወብክዩ ወነስሑ
እለ ስሕትክሙ ፣

ይህን አስቡ፤ የበደላችሁ እናንተ
ንስሐ ገብታችሁ እዘኑ ፣ አል
ቅሱ ፤

ተመየጡ ወሚጡ ልበክሙ ፣

በሕግ በአምልኮት ተመለሱ ፤
ልቡናችሁን ወደሱ መልሱ፤ አን
ድም ከኃጢአት ወደ ሥርየት
ተመለሱ ፤ ልቡናችሁንም ከአም
ልኮተ ጣዖት ወደ አምልኮተ
እግዚአብሔር መልሱ ፤

፱፡ ተዘከሩ ዘእምትካት ፣

ዔዋዌን አስቡ ፤

ወዘእምፍጥረተ ዓለም ፣

ከጥንት ጀምሮ የሆነ አባር ቸነ
ፈርን አስቡ፤ አንድም ሚጠትን
ዔዋዌን አስቡ ፤ አንድም ተዘከሩ
ዘትካት በዳዊት የተደረገውን ፤

ወዘእምፍጥረተ ዓለም ፣

በሙሴ ፣ በአሮን የተደረገውን
አስቡ ፤

እስመ አነ ውእቱ እግዚአብሔር ፣

ፈጣሪ እኔ ነኝና ፣

ወአልቦ ባዕድ አምላክ ዘእንበሌየ ፣

ከኔ በቀር ሌላ ፈጣሪ የለምና ፤

፲፡ እዜኑ ዘትካት ፣

ዔዋዌን እናገራለሁ ፣

ወዘሂ ይከውን በደኃሪ ዘእንበለ ይኩን፣

በኋላ ዘመን የሚሆን ሚጠትን
ሳይሆን እናገራለሁ ፤

ወይከውን ሶቤሃ ፣

ያንጊዜ ይሆናል ፤

ወዘነበብኩሂ ኵሉ ይከውን ፣

የተናገርሁት ሁሉ ይሆናል ፤

ወእገብር ኵሎ ዘመከርኩ

የመከርሁትን ሁሉ አደርጋለሁ ፤

፲፩፡ እጼውዖ ለዖፍ እምጽባሕ ፣

ቂሮስን ከፋርስ እጠራዋለሁ ፤

ወእምርኁቅ ብሔር በእንተ ዘመከ
ርኩ ወነበብኩ ፣

ሚጠትን ስለመከርሁ ፣ ስለተና
ገርሁ ቂሮስን ከፋርስ እጠራዋ
ለሁ ፤ ስለ ፍጥነቱ ዖፍ አለው ፤

ወአምጻእክዎ ወሠራሕኩ ፍኖቶ ፣

ከፋርስ አመጣሁት ፤ መንገዱ
ንም አቀናሁለት ፤

፲፪፡ ስምዑኒ እለ ኀጐልክሙ ልበ
ክሙ ፣

አእምሮዋችሁን ያጣችሁ ስሙኝ፤

ወእለ ርኅቅሙ እምነጽድቅ ፣

ከእውነተኛ ሕግ የራቃችሁ
ስሙኝ ፤

፲፫፡ አምጻእክዋ ለጽድቅየ ወኢያር
ኅቃ ፣

ሚጠትን አመጣኋት ፤ አላርቃ
ትም ፤

ወኢያጐነዲ እንከ መድኃኒተ ዘእ
ምኀቤየ ይቤ እግዚአብሔር ፣

ከኔ ዘንድ የምትሆን ሚጠትን
እንግዲህ ወዲህ አላዘገያትም
አለ እግዚአብሔር ፤ ምነው ሰባ
ዘመን ቆይቶ የለም ቢሉ አይ
ቀርም ሲል ነው ፤

ወወሀብኩ መድኃኒተ ለእስራኤል
በጽዮን ለክብር ፣

በጽዮን ክብር ሊሆናቸው ለእ
ስራኤል መድኃኒት ሚጠትን
ሰጠሁ ::

ምዕራፍ ፵፯

፩፡ ረዲ ወንበሪ ውስተ ምድር አንቲ
ድንግል ወለተ ባቢሎን ወንበሪ ውስተ
መሬት ፣

ውስተ ምድርና ውስተ መሬት
አንድ ወገን ነው ፤ ድልድል ፣
ቅምጥል የምትሆኝ የባቢሎን
ልጅ ከዙፋንሽ ወርደሽ በመሬት
ተቀመጪ ፤ ተዋርዶዋን መናገር
ነው ፤

ወአልብኪ ምንባር ወለተ ከላውዴ
ዎን ፣

የከላውዴዎን ልጅ ዙፋን የለ
ሽም ፤ ከላውዴዎን መላው ባቢ
ሎን ከተማይቱ ናት ፤

ወኢትሰመዪ እንከ ልህደ ወስብሕተ፣

እንግዲህ ወዲህ ድልድል ፣ ቅም
ጥልና ደንዳና አትባይም ፣

፪፡ ንሥኢ ማኅረፀ ወኅርፂ ኀሪፀ ፣

መጁን ይዘሽ ዱቄቱን ፍጪ ፤
ከሆነ በኋላ ኅርፂ ኀሪፀ አለ ፤ አን
ድም እየገረደፉ ይሰልቁታልና ፤

www.ethiopianorthodox.org

ወከሥቲ ግልባቤኪ ወያስተርኢ ሲበ ትኪ ፣

ክንብንብሽን ግለጪ ፤ ሽበት ሽም ይታይ ፤ ሴቶች ሽበታችሁ ሲሏቸው ያፍራሉና ፤ (ሽበታቸውን ሲያዩባቸውም ብትል ይሆናል) ፤

ሰሐቢ አቀ፦ያጸኪ ወዕድዊ አፍላገ ፣

ጭንሽን ጐትቺ ወንዙን ተሻገሪ ማለት መንገድ ልመጂ ፤

፫፤ ወይትቀፈጽ ኀፍረትኪ ወያስተርኢ ኀሣርኪ ፣

ኀፍረትሽ ተዋርዶሽ ይገለጣል፤

እስመ ይነሥእዋ ለበቀል እምኔኪ ፣

ቂሮስ ዳርዮስ ፤ አንድም ሥላሴ በቀልን ካንቺ ይከፈላሉና ፤

ወኢይሁብ እንከ ሰብአ ህየንቴኪ ፣

ወረሰይኩ ለከ ተውላጠከ ግብፀ ወኢትዮጵያ ወሴዎንሃ ቤዛከ

ብሎ ነበርና ስለ አንቺ ሰውን ለውጥ አድርጌ ለጥፋት አልሰጥም፤ አንድም ለእስራኤል ለውጥ ግብፃውያንን እንዳጠፋ ላንተም ለውጥ እስራኤልን አላጠፋም፤

፬፤ ይቤ እግዚአብሔር ፀባኦት ስመ ዘአማሰነኪ ቅዱሰ እስራኤል ፣

ስሙ አሸናፊ የሚባል ያጠፋሽ ፅንዐ እስራኤል ክብረ እስራኤል እግዚአብሔር እንዲህ አለ ፤

፭፤ ንበሪ ድንግዕተኪ ፣

የደነገጥሽ ሁነሽ ኑሪ አለ ፤

ወባኢ ውስተ ጽልመት ወለተ ከላው ዴዎን ፣

የከላውዴዎን ልጅ ወደጪለ ማው ግቢ ማለት መከራውን ተቀበዪ ፤

ወኢትሰመዪ እንከ እቢተ መንግሥት ፣

እንግዲህ ወዲህ ክብርተ መንግሥት አትባዪም ፤

፮፤ እስመ ተዝኅርኪ ላዕለ ሕዝብየ ፣

በወገኖቼ ላይ ታብየሻልና ፤

ወአርኰስኪ ርስትየ ፣

ኢየሩሳሌምን አጐስቍለሻልና ፤ አንድም ማደሪያዎቼ እስራኤልን አዋርደሻልና ፣

ወመጠውኩኪ ውስተ እዴኪ ወኢመሐኪ ለአዕሩጊሆሙ ፣

ግጐሮቸው ብዬ ብሰጥሽ ለሽማግሎች አልራራሽምና ፤

ወአክበድኪ ፈድፋደ አርዑቶሙ ፣

አገዛዝ እጅግ አፀናሽባቸው ፤

፯፤ ወትቤሊ እኴንኖሙ ለዓለም ፣

ለዘለዓለሙ እገዛቸዋለሁ ብለሽ ነበር ፤

ወኢሐለይኪዮ ለዝንቱ በልብኪ ፣

ይህንን በልቡናሽ አላሰብሽውም፤

ወኢተዘከርኪ ደኃሪተኪ ፣

የኋላውን ጥፋትሽን አላሰብሽውም ፤

፰፤ ወይእዜኒ ስምዒ ዘንተ አንቲ ልህድ ፣

ድልድል ፣ ቅምጥል የምትሆኚ አንቺ ይህን ስሚ ፤

እንተ ትነብሪ ተአሚነኪ ፣

ጠላት ጠፍቶልሽ ተዘልለሽ የምትኖሪ ፤

እንዘ ትብሊ በልብኪ አነ ይእቲ ወአልቦ እንተ ከማየ ፣

በልብሽ እመቤት እኔ ብቻ ነኝ፤ እንደ እኔ ያለች ሌላ እመቤት የለችም እያልሽ ፤

ወኢይከውን መበለተ ፣

ድህ አልሆንም ፣

ወኢይመውቱ ውሉድየ ፣

ልጆቼም አይሞቱም እያልሽ ፤

፱፤ ወይእዜኒ ይመጽኡ እሉ ክልኤ ሙሱ ኀቡረ ላዕሌኪ በአሐቲ ዕለት፣

አሁንም እነዚህ ሁለቱ ባንዲት ቀን አንድ ሁነው ይመጡብሻል፤

ወትከውኒ መበለተ ፣

ወኢይከውን መበለተ ብላ ነበርና ድህ ትሆኛለሽ ፤

ወይመውቱ ውሉድኪ ፣

ወኢይመውቱ ውሉድየ ብላ ነበርና ልጆችሽ ይሞታሉ ፤

ቁሚ እስኑ በሥርያትኪ ፣

እስኑ ዐውደ[illegible]ሽ ፤

ወበኀይለ ሰገልኪ ዝኩ ብዙኅ ዘቦቱ ተአመንኪ በዝሙትኪ ፣

በኃጢአትሽ ብዙ መታመንን የታመንሽ በዚህ በጥንቈላሽ ብዛት ፅኚ ፤

፲፤ አንቲሰ ትብሊ አነ ዳዕሙ ይእቲ ወአልቦ እንተ ከማየ ፣

አንቺ ግን እመቤት እኔ ብቻ ነኝ ፤ እንደ እኔ ያለች እመቤት የለችም ትያለሽ ፤

አእምሪ ዘሐለይኪ በልብኪ ወበኀሣረ ዝሙትኪ ፣

በዝሙትሽ ብዛት በልብሽ ያሰብሽውን ዕወቂ ፤

እስመ ትቤሊ በልብኪ አልቦ እንተ ከማየ ካልዕት ፣

በልብሽ እንደ እኔ ያለች ሌላ እመቤት የለችም ብለሻልና ፤

፲፩፤ ወይመጽእ ኀርትምና ላዕሌኪ፣

ተዋርዶ ይመጣብሻል ፤

ወተአምሪ ዕመቂሁ ፣

ረቂቅ ፍርዱን ታውቂያለሽ ፤

ወትወድቂ ውስቴቱ ፣

በመከራው ትያዣለሽ ፤ አንድም በረቂቅ ፍርዱ ትጠፊያለሽ ፤

ወይመጽአኪ ኀሣር ፣

ተዋርዶ ይመጣብሻል ፣

ወኢትክሊ አምሥጦ ፣

ከመከራው ማምለጥ አይቻልሽም ፤

www.ethiopianorthodox.org

ወይመጽአኪ ግብተ ሞት ወኢተአ
ምሪ ፣

የድንገት ሞት ይመጣብሻል አታ
ውቂውም ፤

፲፪፡ ቁሚኬ ይእዜ በሰገልኪ ፣

እስኪ በጥንቈላሽ ዕኚ ፣

ወበብዝኀ ሥርያትኪ ዘተምህርኪ እም
ንዕስኪ ዘኢይበቍዐኪ ፣

ከሕፃንነትሽ ጀምሮ በተማርሽው
በማይረባሽ፣ በማይጠቅምሽ በሚ
ርትሽ ዕኚ ፤

እመቦ ዘይክል አድኀኖተኪ ፣

አንቺን ማዳን የሚቻለው አለ
እንደሆነ ፤

፲፫፡ ሠራሕኪ በምክርኪ እኩይ ፣

በክፉ ምክርሽ ደክምሽ ፣

እስኩ ይቁሙ ወያድኅኑኪ እለ ያሰ
ግሉ ለኪ ፣

የሚያስጠነቀሉሽ ነቢያተ
ሐሰት ፣ ካህናተ ጣዖት እስኪ
ይቁሙ ያድኑሽ ፤

ወይነጽሩ ሰማየ ወይርአዩ ኮከበ
ሰማይ ፣

ሰማዩን አይተው ከከቡን ይቀኑ
ጠሩልሽ ፤

ወይንግሩኪ ምንተ አመጽአ ላዕሌኪ፣

ባንቺ ላይ የማመጣው ምን እን
ደሆነ ይንገሩሽ ፤

፲፬፡ ናሁ ይውዕዮ ኵሉሙ ከመ
ሐሠር ውስተ እሳት ፣

እነዚያስ ስንኳን ላንቺ ይነግ
ሩሽ ገለባ በእሳት እንዲቃጠል
ይጠፋሉ ፤

ወኢያድኅኑ ነፍሶሙ እምነበልባል፣

ሰውነታቸውን ከመከራ አያድ
ኑም ፤

ወይከውኑኪ ከመ አፍሐመ እሳት ፣

አጥፊ ይሆኑብሻል ፤ ፍሕም ቢቆ
ሙበት እንዲጐዳ ነቢያቶችሽ፣
ካህናቶችሽ ይጐዳሉ ፤

ወትነብሪ ውስቴቶሙ ፣

ከነዚያ ጋራ በመከራ ትኖሪያ
ለሽ ፤

ወእሙንቱሰ ይከውኑኪ ረድኤተ ፣

እነሱ ግን ለመከራው አጋዥ
ይሆኑብሻል ፤

፲፭፡ ወይትራድኡ ላዕሌኪ ፣

ባንቺ ላይ ይራዱብሻል ፤

ሠራሕኪ እምንዕስኪ ፣

ከሕፃንነትሽ ጀምሮ በመከራ ደክ
ምሽ ፤

ሰብእኒ ዘስሕተ ለርእሱ ፣

ይረክብ መድኃኒተ ያለበት ነው፤
በድሎ ንስሐ የገባ ሰው ለራሱ ድኅ
ነትን ያገኛል ፤ አንድም ራሱን
ለመገዳት ከሕገ እግዚአብሔር
የሳተ እስራኤል ሚጠትን ያገ
ኛል ፤

ወአንቲሰ አልብኪ መድኃኒት ፣

አንቺ ግን ድኅነት የለሽም ::

ምዕራፍ ፶፰

፩፡ ስምዑ ዘንተ ቤተ ያዕቆብ አለ
ተሰመይክሙ በስመ እስራኤል ፣

ሕዝበ እግዚአብሔር የተባላችሁ
የያዕቆብ ወገኖች ስሙ ፤

ወእለ ወፃእክሙ እምይሁዳ ፣

ከይሁዳም ተማርካችሁ የሄዳ
ችሁ ፤ አንድም ከይሁዳ ወገን
የተወለዳችሁ ስሙ ፤

ወእለ ትምሕሉ በስመ እግዚአብሔር
አምላክ እስራኤል ፣

በእስራኤል ፈጣሪ በእግዚአብ
ሔር ስም የምትምሉ የያዕቆብ
ወገኖች ይህን ነገር ስሙ ፤

ወተዘከርኩክሙ በጽድቅ ወበርትዕ ፣

በእውነት ነገር በቀና ነገር አሰ
ብኋችሁ ፤

፪፡ ወትሰመዩ በስመ ሀገር ቅድስት፣

ሰብአ ኢየሩሳሌም ትባላላችሁ፤

ወታሰምኩ በአምላክ እስራኤል እግ
ዚአብሔር ፀባዖት ስሙ ፣

ስሙ አሸናፊ በሚባል በእስራ
ኤል ፈጣሪ በእግዚአብሔር ታም
ናላችሁ ፣

፫፡ ዘቀዲሙኒ ነገርኩ ፣

የቀደመ ዜዋዜን ተናገርሁ ፤

ወወፅአ እምአፉየ ፣

ከአንደበቴም ወጣ ፤

ወስምዐ ኮነ ዘገበርኩ ግብተ ወበጽ
ሐኒ ፣

ድንገት ያደረግሁት ነገር ምስ
ክር ሆነ፣ ደረሰ ፤

፬፡ ወባሕቱ አነ አእመርኩ ከመ እኩይ
አንተ ፣

ነገር ግን እኔ አንተ ክፉ እንደ
ሆንህ አወቅሁ ፤

ወዘሐሚን ሥርወ ክሣድከ ፣

ክሣደ ልቡናህ ዕኑ እንደሆነ አወ
ቅሁ ፣

ወፍጽምከኒ ዘብርት ፣

ፍጽመ ልቡናህም የብርት እንደ
ሆነ አወቅሁ ማለት ዕኑ እንደ
ሆነ አወቅሁ ፤

፭፡ ወነገርኩከ ዘይመጽእ ዘእንበለ
ይኩን ፣

የሚመጣውን ሳይሆን ነገርሁህ፣

ወአስማዕኩከ ከመ ኢትበል አማል
ክትየ ወግልፎየ ገብሩ ላዕሌየ ወስ
ብኮየ ዘአዘዙኒ ፣

ተመትተው ተቀርፀው የተሠሩ
ጣዖቶቼ ያዘዙኝን ባላደርግ እን
ዲህ ያለ መከራ አመጡብኝ እን
ዳትል አስቀድሜ ነገርሁህ ፤ አን
ድም መሥዋዕት ሠዋልን ብለው
አዘዙኝ፤ ባልሠዋ ይህን ሁሉ አመ
ጡብኝ እንዳትል አስቀድሜ ነገ
ርሁህ ፤

www.ethiopianorthodox.org

፮፡ ወሰሚዐከኒ ኮሎ ወኢያእመርከ፣
ይህን ሁሉ ሰምተህ ይደረጋል
አላልህም ፤
ወአስማዕኩከ ሐዲሰኒ ዘእምይእዜ ይከ
ውን ፣
ከዛሬ ጀምሮ የሚሆን ሚጠትን
ነገርሁህ ፤
፯፡ ወአኮ ዘትካት ፣
ዜዋዜን ፤
ወአኮ ዘቀዲሙ መዋዕል ፣
አባር ቸነፈር ይደረጋል አላል
ህም ፤
ወሰሚዐከኒ ኢትቤ እወ አእመርክ
ዎን ፣
ሰምተህም አዎን ይደረጋል አላ
ልህም ፤
፰፡ ወኢያእመርካሁ ወኢለበውካሁ፣
አላወቅኽውም፣ ልብ አላደረግኽ
ውም ፤
አኮኑ ነግርኩከ ዘቀዲሙ ፣
ዜዋዜን ፤
ወዘይመጽእ ፣
ሚጠትን የነገርሁህ አይደለምን፤
ወከሠትኩ ዕዘኒከ ፣
ዕዝነ ልቡናህን የገለጥሁልህ አይ
ደለምን ፤
ወአእመርኩከ ከመ ክሂደ ትክሀደኒ
ሀለወከ ፣
ትክደኝ ዘንድ እንዳለህ ዐወቅሁ፤
እስመ ዐማፂ አንተ ፣
አንተ ዐመፀኛ ነህና ፤
ወእምከርሠ እምከ ተሰመይከ ፣
፱፡ ዐማፂ ያለበት ነው ከእናትህ
ማኅፀን ጀምሮ አዕቃፊ ተብለ
ሃልና ፤
፱፡ ወበእንተ ስምየ አርአይኩከ መዓ
ትየ ፣
በስሜ ስላላመንህ መዓቴን አሳ
የሁህ ፤
ወአመጽአ ግርማየ ላዕሌከ ከመ አጥ
ፍእከ ፣
አጠፋህ ዘንድ ግርማ መዓቴን
በአንተ ላይ አመጣለሁ ፤
፲፡ ናሁ ሜጥኩከ ፣
እነሆ ከባቢሎን ወደ ኢየሩሳሌም
መለስሁህ ፤
አኮኑ ከመ ብሩር ፈተንኩከ ፣
ብርን በእሳት እንዲፈትኑት
በመከራ የፈተንሁህ አይደለም፤
ወአውፃእኩከ እምእቶነ እሳት ዘይነ
ድድ ፣
ከዕኑ መከራ ያወጣሁህ አይደ
ለም ፤
፲፩፡ በእንቲአየ ረሰይኩከ ፣
በኔ ስላላመንህ እኔን ስላላመ
ለክህ ለዜዋዜ አደረግሁህ ፤
እስመ አርኩስኩ አንተ ስምየ ቅድመ፣
አንተ ስሜን አስነቅፈሃልና ፤
አንድም እንቲአየ ረሰይኩከ የኔ

ገንዘብ አደረግሁህ፤ አንተ ስሜን
አስነቅፈሃልና ምንም ብታስነቅፍ
የኔ ገንዘብ አደረግሁህ፤ አንድም
ሕጌን ስለጠበቅህ ለሚጠት አደ
ረግሁህ ፤
እስመ አርኩስኩ አንተ ስምየ ቅድመ፣
ከዚህ አስቀድሞ አንተ ስሜን
አስነቅፈህ ነበርና ዛሬ ግን ተመ
ልሰህ ንስሐ ገብተሃልና ስለተ
መለስህ ለሚጠት አደረግሁህ፤
ይእዜሰ ኢይሁብ ስብሐትየ ለባዕድ፣
ዛሬ ግን ክብሬን፣ ጌትነቴን ለጣ
ዖት አልሰጥም ፤
፲፪፡ ስምዐኒ ያዕቆብ ፣
ያዕቆብ ስማኝ
ወእስራኤልኒ ዘአነ ጸዋዕኩከ ፣
እኔ የጠራሁህ እስራኤልም ስማኝ፤
አንድም እስራኤል ብዬ የጠራ
ሁህ ያዕቆብ ስማኝ ፤
አነ ቀዳማዊ ወአነ ደኃራዊ ለዓለም፣
ቅድመ ዓለም የነበርሁ፣ ዓለምን
አሳልፌ የምኖር እኔ ነኝ ፤
፲፫፡ እዴየ ሣረረታ ለምድር ፣
ምድርን የፈጠረቻት ሥልጣኔ
ናት ፤
ወየማንየ አዕንዐቶ ለሰማይ ፣
ሰማይንም ያፀናችው ሥልጣኔ
ናት ፤
እጼውዖሙ ወይመጽኡ ኀቤየ ኀቡረ
ሰማይን፣ ምድርን፣ እለፉ፤ ጥፉ
እላቸዋለሁ ፤
፲፬፡ ወይትጋብኡ ኵሎሙ ወይሰ
ምዑ ፣
ሁሉም አንድ ሁነው ያልፋሉ፤
ይጠፋሉ ፤
መኑ ነገረከ ዘንተ ፣
ይህን ማን ነገረህ ፤
አኮኑ በአፍቅሮ ዚአከ ገበርኩ ፈቃ
ደከ ላዕለ ባቢሎን ፣
አንተን በመውደድ ፈቃድህን
በባቢሎን ሰዎች ላይ ያደረግሁ
አይደለምን ፤
ከመ አዕትት ዘርዖሙ ለከላውዴዎን፣
የከላውዴዎንን ልጆች አጠፋ
ዘንድ ፤
፲፭፡ አነ ነበብኩ ወአነ ጸዋዕኩ ፣
እኔ በነቢያት በካህናት አድሬ
አስተማርሁ ፤
ወአምጻእኩከሙ ወረዳእኩከሙ ፣
ከባቢሎን አምጥቼ ረዳኋችሁ ፤
እንዘ እብል ንዑ ኀቤየ ወስምዑኒ
ዘንተ ፣
ወደኔ ኑ ይህን ስሙኝ ብዬ ፤
፲፮፡ አኮኑ እምትካት ኢተናገርኩ
ጽሚተ ፣
ከጥንት ጀምሮ ሠውሬ የተናገ
ርሁ አይደለምና ፤

www.ethiopianorthodox.org

ወእመኒ ኮነ ህየ ከመ ሀለውኩ ፣

አእምሩ ያለበት ነው፤ መከራም በዚያ ቢመጣ በመከራው እኔ እንዳለሁ ዕወቁ፤ ጥቅስ ወእመኒ ኮነ ምንዳቤ ወተፄውዎ አእምሩ ከመ ዘህሎኩ አነ እንዲል ፤

ጉባዔ

ወይእዜኒ እግዚአብሔር እግዚእ ፈነወኒ ፣

አሁንም ገዢ ፈጣሪ የሚሆን እግዚአብሔር በመምህርነት ላከኝ፤

ወመንፈሱ ፣

መንፈስ ቅዱስም በመምህርነት ላከኝ፤ አንድም እግዚአብሔር አብ ውረድ ተወለድ ብሎ ላከኝ፤

ወመንፈሱ ፣

አስተጋብዐኒ ብሎ አንክሮጦስ የሚባል ሊቅ ጨምሮበታል ፣ መንፈስ ቅዱስም አዋሐደኝ ፤

፲፯፤ ከመዝ ይቤ እግዚአብሔር ዘአድኅነከ ወባልሐከ ቅዱሰ እስራኤል፣

ያዳነህ የተቤገርህ ዕንዐ እስራኤል ክብረ እስራኤል እግዚአብሔር እንዲህ አለ ፤

አነኪ ውእቱ አምላክከ ፣

ፈጣሪህ እኔ ነኝ ፤

ወአርአይኩከ ፍኖተ ኀበ ትረክብ እንተ ባቲ ተሐውር ፣

ወአርአይኩከ ፍኖተ እንተ ባቲ ተሐውር ኀበ ትረክብ ሲል ነው፤

ድኅነት ወደምታገኝባት ወደ ኢየሩሳሌም የምትሄድባትን ጉዳ ናን አሳየሁህ ፤ አንድም ተድላ ደስታ ወደምታደርግባት ወደ ገነት፣ ወደ መንግሥተ ሰማያት የምትሄድባትን ሕግ ሠራሁልህ፤

፲፰፤ ወሶበ ሰማዕከ ትእዛዝየ እም ኮነ ከመ ውኂዝ ሰላምከ ፣

ትእዛዜንስ ብትሰማ ተድላህ ደስታህ እንደ ፈሳሽ ውሀ በበዛልህ ነበር፤ በዚህ ዓለም የሚያገኘው የዐረቦኑ ክብር ነው ፤

ወጽድቅከኒ ከመ ማዕበለ ባሕር ፣

ክብርህ፤ ረድኤትህ እንደ ማዕበለ ባሕር በበዛ ነበር ፤ በወዲያ ዓለም የሚያገኘው ደግኛው ክብር ነው ፤

፲፱፤ ወእምኮነ ከመ ሖፃ ባሕር ዘርዕከ ፣

ልጅህ እንደ ባሕር አሸዋ በበዛ ነበር ፤

ወከመ ፀበለ ምድር ትውልደ ከርሥከ ፣

የልጅ ልጅህ እንደ ትቢያ በበዛ ነበር ፣

፳፤ ወይእዜኒ ከመ ኢትጥፍኡ ወከመ ኢትትኀጐሉ ፃኡ እምባቢሎን እንዘ ትጐይዩ እምከላውዴዎን ፣

አሁንም ከከላውዴዎን እየሸሻችሁ ፈጽማችሁ እንዳትጠፉ ከባቢሎን ውጡ፤ ከዚያ አኮ በጕያ

ዘትወፅኡ አለ ፤ ከዚህ ፃኡ እምባቢሎን እንዘ ትጐይዩ እምከላውዴዎን አለ ፤ አይጣላም ቢሉ አይጣላም፤ ከዚያ አኮ በጕያ ዘትወፅኡ ማለቱ እንደ ወጓችሁ ወግ ታችሁ ፣ እንደ ዘረፏችሁ ዘርፋችሁ ትሄዳላችሁ ሲል ነው ፤ ከዚህ ግን እንዲህ ማለቱ ፈጽማችሁ ከግብራቸው ተለዩ ሲል ነው ፤

ወዜንዉ ቃለ ትፍሥሕት ፣

የሚጠትን ነገር ተናገሩ ፤

፳፩፤ ወይሰማዕ ዝንቱ ነገር ፣

ይህ የሚጠት ነገር ይሰማ ፤

ወንግሩ እስከ አጽናፈ ምድር ፣

የሚጠትን ነገር ጽንፍ እሰከ ጽንፍ ንገሩ ፤

ወበሉ አድኅኖ እግዚአብሔር ለያዕቆብ ገብሩ ፣

ባርያው ያዕቆብን እግዚአብሔር አዳነው በሉ ፤

፳፪፤ ወእመኒ ፀምዑ ማየ በበድው ያወፅእ ሎሙ ማየ እምኲኵሕ ፣

በምድረ በዳ ውሀ አጥተው ቢጠሙ ከደንጊያ ውሀ ያፈል ቅላቸዋል ፤

ወትነቅዕ ሎሙ ኲኵሕ ፣

ደንጊያይቱ ውሀ ታፈልቅላቸዋ ለች እንደ ሙሴ ጊዜ ፤

ወይውኅዝ ማይ ፣

ውሀ ይፈልቅላቸዋል ፤

ወይሰትዩ ሕዝብየ ፣

ወገኖቼ ውሀውን ይጠጣሉ ፤

፳፫፤ ወይትፌሥሑ እንከ ነዳያን ይቤ እግዚአብሔር ፣

ነዳያን እስራኤል እንግዲህ ወዲህ ደስ ይላቸዋል አለ እግዚአብሔር ፤ አንድም ወእመኒ ፀምዑ ማየ በበድው ብለህ መልስ ፤ ምዕመናን በዚህ ዓለም ዕምዐ ነፍስ ቢያገኟቸው ከጌታ ጐን ትኩስ ደም ፣ ጥሩ ውሀ ይፈስላቸዋል ፣

ወትነቅዕ ሎሙ ኲኵሕ ፣

ሥግው ቃል በኵናተ ሐራ ይወጋላቸዋል ፤

ወይውኅዝ ማይ ፣

ከጐኑ ትኩስ ደም ጥሩ ውሀ ይፈስላቸዋል ፤

ወይሰትዩ ሕዝብየ

ወገኖቼ ምዕመናን ይጠመቃሉ፤

ወይትፌሥሑ ፣

እንግዲህ ወዲህ ምዕመናን ደስ ይላቸዋል አለ እግዚአብሔር::

ምዕራፍ ፶፱

፩፤ ስምዑኒ ደሰያት ፣

ደሴት በውሀ፣ ውሀ በደሴት እንዲከበብ ሰባ ዘመን በመከራ የተከበባችሁ እስራኤል ስሙኝ፤

www.ethiopianorthodox.org

ወአፅምዑኒ አሕዛብ ፣

አሕዛብ አድምጡኝ ፤

በጕንዱይ መዋዕል ይቀውም ይቤ እግዚአብሔር ፣

እኔ እግዚአብሔር የተናገርሁት ነገር በሰባ ዘመን ይፀናል አለ፤ አንድም እግዚአብሔር የተናገረው ነገር ባምስት ሺህ ካምስት መቶ ዘመን ይፀናል አለ ፤ አንድም ባምስት ሺህ ካምስት መቶ ዘመን ጌታ ይነሣል አለ ፣ አንድም ባምስት ሺህ ካምስት መቶ ዘመን ሰው ይሆናል ፤ ሥጋ ይለ ብሳል ፤

ወእምዝርሠ እምየ ሰመየኒ ስምየ፣

በእናቴ ማኅፀን ስሜን ኢሳይያስ አለኝ፤ አንድም ከእናቴ ማኅፀን ከተወለድሁ በኋላ ኢሳይያስ ብሎ ስም አወጣልኝ ፤

፪፡ ወረሰዮ ለአፉየ ከመ መላጢ በሊህ፣

አንደበቴን እንደ ተሳለ ምላጭ አደረገው ማለት አሪትን እንዳስተምር አደረገኝ ፤

ወከደነኒ ታሕተ ጽላሎተ እዴሁ ፣

በሥልጣኑ በሚያደርገው በጽላሎተ ረድኤቱ ሠወረኝ ፤

ወረሰየኒ ከመ ሐፅ ኀሩይ ፣

እንደ ተወለወለ ፍላፃ አደረገኝ ማለት አሪትን እንዳስተምር አደረገኝ ፤

ወነብዐኒ ውስተ ምጕንጻሁ ፣

በረድኤቱ ሠወረኝ፤ አንድም ወእምከርሠ እምየ ሰመየኒ ስምየ ብለህ መልስ ፤ በእናቴ ማኅፀን ሳለሁ ስሜን ክርስቶስ አለኝ ፤

ወረሰዮ ለአፉየ ከመ መላጢ በሊህ፣

ወንጌልን እንዳስተምር አደረገኝ፤

ወከደነኒ ታሕተ ጽላሎተ እዴሁ ፣

በሥልጣኑ በፈጠረው በሥጋ ሠወረኝ ፤

ወረሰየኒ ከመ ሐፅ ኀሩይ ፣

እንደ ተወለወለ ፍላፃ አደረገኝ ማለት ሥጋን አዋሐደኝ ፤

ወነብዐኒ ውስተ ምጕንጻሁ ፣

በሥጋ ሠወረኝ ፤

፫፡ ወይቤለኒ ገብርየ አንተ እስራኤል፣

ብሉዩን ይዞ ይሄዳል፤ እስራኤል አንተ የኔ ባርያ ነህ አለኝ፤ አንድም ባርያዬ ተገዝዬ አንተ ነህ አለኝ ይላል ኢሳይያስ ፤

ወብከ እሴባሕ ፣

ባንተ እመሰገናለሁ ፤ አንድም ባንተ ምክንያት እመሰገናለሁ አለኝ ይላል ኢሳይያስ ፤

፬፡ ወአነሰ እቤ ከንቶ ኀመውኩ ፣

እኔስ በከንቱ ደከምሁ አልሁ፤

ወለዘአልቦ ባቍዕ ወኢምንትኒ ወሀብኩ ኃይልየ

ምንም ምን ረብሕ ጥቅም ለሌለው ነገር አስተምሬ ላልመልሳ

ቸው ኃይሌን አደከምሁ ፤ ምነው እሱማ የድካሙ ዋጋ ይቀርበታልን ቢሉ ስላልተመለሱለት እንዲህ አለ ፤ ጥቅስ (በቋዕኩ ወኢበቍዑኒ እንዲል) ኤር. ፲፭ ÷ ፲ አንድም ጥቅስ (አኮኑ ሐምሰ መካልየ ወሀብከኒ ወናሁ ሐምስ ካልአት እለ ረባሕኩ) ፤ ማቴ. ምዕ. ፳፭ ቍ. ፳ ብሎ ማበርከት ይቀርበታልና ፤

ወበእንተ ዝንቱ ይፈትሕ ሊተ እግዚአብሔር ፣

ስለዚህ ነገር እግዚአብሔር ይፈርድልኛል ፤

ወሕግምየኒ ቅድመ አምላኪየ ፣

መከራዬም በፈጣሪዬ ፊት ነው ማለት መከራዬን አይቶ ዋጋዬን ይሰጠኛል ፤

፭፡ ወይእዜኒ ከመዝ ይቤ እግዚአብሔር ዘፈጠረኒ በውስተ ከርሠ እምየ ከመ እኩን ገብሮ ፣

አገልጋዩ እሆን ዘንድ በእናቴ ማኅፀን የፈጠረኝ እግዚአብሔር እንዲህ አለ ፤

ከመ አስተጋብየ ለያዕቆብ ኀቤሁ ፣

ያዕቆብን መክሬ አስተምሬ ወደሱ እመልሰው ዘንድ ፤

ወለእስራኤልኒ ፣

እስራኤልንም መክሬ አስተምሬ እመልሰው ዘንድ ፤

ይቤ እትጋባዕ ምስሌሆሙ ፣

መክረህ አስተምረህ ብትመልሳቸው አድርባቸዋለሁ አለ ፤

ወእሴባሕ በቅድመ እግዚአብሔር፣

እስራኤልን መክሬ አስተምሬ በእግዚአብሔር ፊት በባለሟልነት እገለጣለሁ አለ ፤

ወይከውነኒ አምላኪየ ኀይልየ ፣

ፈጣሪዬ ኃይል ይሆንልኛል ፤

፮፡ ወይቤለኒ ዐቢይ ውእቱ ለከ ዝንቱ ከመ ትሰመይ ቍልዔየ ፣

ዘሩባቤልን ወዳጄ ትባል ዘንድ ይህ ላንተ ደግ ነው ፤

ከመ ታቅም ሕዝበ ያዕቆብ ፣

የያዕቆብን ወገን መክረህ አስተምረህ ታፀና ዘንድ ፤

ወዝርወተ እስራኤል ከመ ትሚጠሙ፣

ወዝርዋኒሆሙ ለእስራኤል ሲል ነው ፤ ከእስራኤል የተበተኑትን መክረህ ፣ አስተምረህ ትመልሳቸው ዘንድ ፤ አንድም በፋርስ፣ በባቢሎን ፣ በዕርዕ በሜዶን የተበተኑ እስራኤልን ትመልሳቸው ዘንድ ፤

ናሁ ረሰይኩከ ብርሃነ ለአሕዛብ፣

ዘሩባቤልን እነሆ የአሕዛብ ንጉሥ አደረግሁህ ይለዋል ፤

www.ethiopianorthodox.org

ከመ ትኩን መድኀነ እስከ አጽናፈ ምድር ።

ጽንፍ እስከ ጽንፍ ያሉትን ታድ ናቸው ዘንድ፤ አንድም መምህረ አሕዛብ አደረግሁህ፤ እስከ ጽንፈ ምድር ድረስ መምህረ ዓለም ትባል ዘንድ፤ አንድም ወይቤ ለኒ ዐቢይ ውእቱ ለከ ዝንቱ፣ የባሕርይ አባትህ መሆኔ ይህ ላንተ ድንቅ ነው ፤

ከመ ትሰመይ ቍልዔየ ።

ወልድየ ብሎ ሊቁ ወስዶታል የባሕርይ ልጄ ትባል ዘንድ ፤

ከመ ታቅም ሕዝበ ያዕቆብ ።

የያዕቆብ ዘነፍስን ወገኖች መክ ረህ አስተምረህ ታፀና ዘንድ ፤

ወዝርወተ እስራኤል ከመ ትሚጠሙ፣

እስራኤል ዘነፍስን ከክህደት ወደ ሃይማኖት ፣ ከገሃነም ወደ መን ግሥተ ሰማያት ትመልሳቸው ዘንድ ፤

ናሁ ረሰይኩከ ብርሃኖሙ ለአሕዛብ፣

ጌታን እነሆ የአሕዛብ ዕውቀት፤ አንድም የአሕዛብ መምህር አደ ረግሁህ ይለዋል፤ እስከ ጽንፈ ምድር ድረስ መድኀነ ዓለም ትባል ዘንድ ፤

፮፤ ከመዝ ይቤ እግዚአብሔር ዘአ ድነነከ ቅዱሰ እስራኤል ፣

ያዳነህ ፅንዐ እስራኤል ክብረ እስ ራኤል እግዚአብሔር እንዲህ አለ ፤ (ያዳነህ ዕኑዐ እስራኤል ክቡረ እስራኤል እግዚአብሔር ብትልም ይሆናል) ፤

ቀድስዎ ለዘየሐምማ ለነፍሱ ፣

ደረቅ ሐዲስ ነው ፤ በሰውነቱ በፈቃዱ መከራ የሚያመጣባት እሱን አመስግኑት ፤

ዘያስተራኵስዎ አይሁድ ለግብረ መለኮቱ ፣

አይሁድ ተአምራቱ ምትሐት ነው ፤ ትምህርቱ ሐሰት ነው እያሉ የመለኮቱን ሥራ የሚን ቁት፣ የሚያቃልሉት እሱን አመ ስግኑት ፤ አንድም ለግብረ መላ እክት ይላል፤ የመላእክት ሥራ የሚሆን እሱን አመስግኑት ፤ የመላእክት ሥራቸው ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ እያሉ እሱን ማመ ሰገን ነውና ግብረ መላእክት አለው ፤

ነገሥትሰ ይሬእይዎ ፣

ቀድስዎን ቢያይ ነገሥትሰ ዘያ ስተራኵስዎን ቢያይ ነገሥትኒ ይላል ፤ እለ ሄሮድስ እለ ጲላጦ ስም ንቀው ያዩታል ፤

ወይትነሥኡ መላእክትኒ ፣

አለቆችም ተነሥተው ፣

ወይሰግዱ ሎቱ በእንተ እግዚአብ ሔር እግዚእ ፣

ስለ እግዚአብሔርነቱ ፈንታ ፣ ስለ እግዚአብሔርነቱ ለውጥ የተ

ሳልቆ ስግደት ይሰግዱለታል ፤ አንድም እንዘ እግዚአብሔር ፣ እግዚአብሔር ሲሆን የተሣልቆ ስግደት ይሰግዱለታል፣

እስመ ቅዱስ ውእቱ ስቡሐ እስራ ኤል ዘነገረይከዎ ፣

የመረጥሁት ፅንዐ እስራኤል ክብረ እስራኤል እግዚአብሔር ክቡር ምስጉን ነውና ምንም ክቡር ቢሆን የተሣልቆ ስግደት ይሰግዱለታል፤ አንድም ቀድስዎ ለዘየሐምማ ብለህ መልስ ትርጓ ሜው አይለወጥም ፤

ዘያስተራኵስዎ አይሁድ ለግብረ መለ ኮቱ ፣

አይለወጥም ፣

ነገሥትሰ ይሬእይዎ ፣

ቀድስዎን ቢያይ ነገሥትኒ፣ ዘያ ስተራኵስዎን ቢያይ ነገሥትሰ እለ ዘይኑን፣ እለ አርቃድዮስ፣ እለ አኖሬዎስ፣ እለ ቄስጠንጢ ኖስ ግን በዐይነ ምሕረት ያዩ ታል ፤

ወይትነሥኡ መላእክትኒ ወይሰግዱ ሎቱ በእንተ እግዚአብሔር እግዚእ፣

የእነርሳቸውም አለቆች ስለ እግ ዚአብሔርነቱ ፈንታ ያምላክነት ስግደት ይሰግዱለታል ፤

እስመ ቅዱስ ውእቱ ስቡሐ እስራ ኤል ዘነገረይከዎ ፣

የመረጥሁት ፅንዐ እስራኤል ክብረ እስራኤል እግዚአብሔር ክቡር ምስጉን ነውና የአምላክ ነት ስግደት ይሰግዱለታል ፤

፯፤ ከመዝ ይቤ እግዚአብሔር ፣

እግዚአብሔር እንዲህ አለ ፤

በዕለት ኀሪት ሰማዕኩከ ፣

ዕለት ኀሪት ያላት ከግብፅ የወ ጡባት ቀን ናት፣ ከግብፅ በወጣ ህባት ቀን ሰማሁህ ፤

ወበዕለተ መድኀኒት ረዳእኩከ ፣

ዕለተ መድኀኒትም ያላት ከግ ብፅ የወጡባት ቀን ናት፤ በጉን ሠውተው ከቸነፈር ድነውባታ ልና፤ አንድም ዕለት ኀሪት ያላት ኤርትራን የተሻገሩባት ቀን ናት፤ ዕለተ መድኀኒትም ያላት እሷ ናት ፤ ከስጦመት ድነውባታልና አንድም ዕለት ኀሪት ያላት በደ ብረ ሲና ሕግ የተሠራባት ቀን ናት፣ ዕለተ መድኀኒትም ያላት እሷ ናት ከአምልኮ ጣዖት ድነው ባታልና፤ አንድም ዕለት ኀሪት ያላት ከባቢሎን የወጡባት ቀን ናት፤ ዕለተ መድኀኒትም ያላት እሷ ናት፤ ከመገዛት ድነውባታ ልና፤ አንድም ዕለት ኀሪት ከባቢ ሎን የወጡባት ቀን ናት፤ ዕለተ መድኀኒትም ያላት እሷ ናት ፤ ሰባት ወንዝ ተከፍሎላቸው ሰባት አህጉር ወግተው ወጥተዋልና፤ አንድም ዕለት ኀሪት ዕለተ ዕንስ፣ ዕለተ መድኀኒት ዕለተ ልደት፤

www.ethiopianorthodox.org

አንድም ዕለት ጎሪት ዕለተ ልደት፣ ዕለተ መድኀኒት፣ ዕለተ ስቅለት፤ አንድም ዕለት ጎሪት፣ ዕለተ ስቅለት ፣ ዕለተ መድኀኒት፣ ዕለተ ትንሣኤ ጥቅስ (ወይ ዴመሙ በእንተ መንክር ዳኅናሁ) ጥበብ ፱÷፭ እስመ አኮ ዘድኀነ ባሕቲቶ አላ አድኀነ ካል አኒሁ እንዲል፤ አንድም ከዕለተ ዐርብ ጀምሮ እስከ ዕለተ ምጽአት ያለው ነው፤ አንድም ዕለት ጎሪት፣ ዕለተ መድኀኒት ያላት ዕለተ ንስሐ ናት ፤ በዚህ ዓለም ንስሐ ገብቶ በወዲያኛው ዓለም የሚድኑባት ስለሆነ ይህንንም ዮም ዕለት ጎሪት፣ ዮም ዕለተ አድኅኖ ብሎ ጳውሎስ ወስዶ ታል ፤

ወወሀብኩከ ሥርዐተ ለአሕዛብ ፣

ለአሕዛብ ሥርዐት የምትሆን አሪትን ሰጠሁህ ፣ አንድም አንተን ሥርዐት አድርጌ ሰጠሁህ ይለዋል ዘሩባቤልን ፤

ከመ ታስተራትዓ ለምድር ፣

ኢየሩሳሌምን ታቀናት ዘንድ ፤

ወትረስ ርስተ ገዳም ፣

አሕዛብ ወርሰዋት የነበረ ኢየሩሳሌምን ትወርስ ዘንድ ፤

፱፡ ከመ ትበሥሙ ለሙቁሓን ፃኡ ፣

በመከራ የተያዙ እስራኤልን ከባቢሎን ውጡ ብለህ ታዝዛቸው ዘንድ ፤

ወታብርህ ሎሙ ለእለ ውስተ ጽልመት ፣

በመከራ የተያዙትን ደስ ታሰኛቸው ዘንድ ፤

ወይትረዐዩ በኵሉ ፍኖት ወበኵሉ መዕያሕት ፣

በጌዳናው በጥርጊያው ጌዳና ሁሉ ይሰማራሉ ማለት ብዛታቸውን መናገር ነው ፤

ጎዝዐቶሙ ውእቱ ፣

ኢየሩሳሌም ለእስራኤል ርስታቸው ጒልታቸው ናት፤ ጥንቱን የሴም ዕፃ ናትና፣ ኋላም በኢያሱ ወርሰዋታልና ፣ አንድም ወወሀ ብኩከ ሥርዐተ ለአሕዛብ ብለህ መልስ፣ ለአሕዛብ ሥርዐት የምትሆን ወንጌልን ሠራሁልህ ይለዋል ጌታን ፤ አንድም አንተን ሥርዐት አድርጌ ሰጠሁህ ፤

ከመ ታስተራትዓ ለምድር ፣

ገነት መንግሥተ ሰማይን ታቀና ዘንድ ፣

ወትረስ ርስተ ገዳም ፣

ምዕመናንን መክረህ አስተምረህ ገንዘብ ታደርግ ዘንድ ፤

ከመ ትበሥሙ ለሙቁሓን ፃኡ ፣

በፍዳ የተያዙ ነፍሳትን፣ እለ ውስተ ሲኦል ፃኡ ወእለ ውስተ ጽልመት ተከሠቱ ብለህ ታዝዛቸው ዘንድ ፤

ወታብርህ ሎሙ ለእለ ውስተ ጽልመት ፣

በጽልመተ ነፍስ ለሚኖሩ ብርሃነ ነፍስን ታበራላቸው ዘንድ ፤

ወይትረዐዩ ፣

ምዕመናን በገነት፣ በመንግሥተ ሰማይ ይኖራሉ ፤

ጎዝዐቶሙ ውእቱ ፣

ለምዕመናን ገነት፤ መንግሥተ ሰማያት ርስታቸው፣ ጒልታቸው ናት፣ ጥንቱንም መፈጠሯ ለሰው ነውና ፤ ጥቅስ (ወበእንቲ አክሙ ፈጠርክዎ ለዓለም እንዲል ፣)

፲፡ ኢይርኀቡ ወኢይፀምዑ ፣

እስራኤል አይራቡም ፤ አይጠሙም ፤ አንድም ነፍሳት ረኃበ ነፍስ ፣ ዕምዐ ነፍስ አያገኛቸውም፤ አንድም ኢይርኀብ ወኢይፀምዕ ይላል ፣ ጌታ በባሕርዩ አይራብም አይጠማም ፤

ወኢየሐምሞሙ ላህበ ፀሐይ ፣

እስራኤልን መከራ አያገኛቸውም፤ አንድም ነፍሳትን ሥቃየ ገሃነም አያገኛቸውም ፤ አበው አምስት ሺህ ካምስት መቶ ዘመን ምግባራቸው እንደ አጐበር፣ እንደ ድንኳን ሁኖላቸው በእደ እግዚአብሔር ተጠብቀው ይኖሩ ነበርና ፤ ጥቅስ (ነፍሰ ሙሉ

ለጻድቃን ውስተ እደ እግዚአብሔር ወኢለከፎሙ ሥቃይ ለግሙራ እንዲል፤ ጥበብ ፫ ÷ ፩)፡

ዳዕሙ ዘይመርሆሙ ይሣሃለሙሙ ፣

ከባቢሎን ወደ ኢየሩሳሌም መርቶ የሚያወጣቸው ዘሩባቤል ይቅር ይላቸዋል እንጂ፤ አንድም ከገሃነም መርቶ የሚያወጣቸው ጌታ ይቅር ይላቸዋል እንጂ ፤

ወያመጽኦሙ እንተ ኀበ አንቅዕተ ማያት ፣

ረድኤት፣ ትምህርት ወዳለባት ወደ ኢየሩሳሌም ያመጣቸዋል፤ አንድም ተድላ ደስታ ወደ አለባት ወደ ገነት፣ ወደ መንግሥተ ሰማያት ያመጣቸዋል ፤

፲፩፡ ወይፀይሕ ሎሙ አድባረ መብእሰ ፣

በሰባ ዘመን ጌጻጌጹን ጌጣና ይጠርግላቸዋል ማለት አሕዛብን ያጠፋላቸዋል፤ አንድም መናፍቃንን ፣ አጋንንትን ያጠፋላቸዋል ፤

ወይከውኖሙ መራዕየ ኵሉ ፍኖት፣

ጌጣናው ሁሉ መሰማርያ ይሆናቸዋል ፤

፲፪፡ ወናሁ እለሂ ይመጽኡ እምርኁቅ ፣

ከዕርዕ ከሜዶን የሚመጡ አሉ፤

ወእለሂ እምደቡብ ፣

ከባቢሎን የሚመጡ አሉ ፤

www.ethiopianorthodox.org

ወቦ አልቦ እምአድባረ ፋርስ ፤

ከፋርስም አውራጃ የሚመጡ አሉ ፤

፲፫፡ ይትፈሥሓ ሰማያት ወትትሃነ ሠይ ምድር ፤

ሰማይ ዝናም ለዘር ፤ ጠል ለመ ከር ይሰጣል ፤ ምድርም የዘሩባ ትን ታበቅላለች ፤ የተከሉባትን ታጸድቃለች፤ አንድም በሚጠት ልዑሳኑ ትሑታኑ ደስ ይላቸ ዋል ፤ አንድም በሥጋዌ ደስ ይላ ቸዋል፤ አንድም መላእክት ደቂቀ አዳም ደስ ይላቸዋል ፤

ወይፈለፍል ትፍሥሕት እምድር ወእ ምአድባር ዘለዓለም ፤

በኢየሩሳሌም አውራጃ ለዘለዓ ለሙ ተድላ ደስታ ይደረጋል ፤ አንድም ከነባሥታቱ ከመኳን ንቱ ተድላ ደስታ ይገኛል ፤ አን ድም ከጳጳሳት ከሊቃነ ጳጳሳት ልጅነት ይገኛል ፤

እስመ ተሣህሎሙ እግዚአብሔር ለሕ ዝቡ ፤

እግዚአብሔር ወገኖቹን ይቅር ብሏቸዋልና ፤

፲፬፡ ወትቤ ጽዮን ጎደገኒኑ እግዚ አብሔር ፤

ከዚህ አስቀድሞ ጽዮን እግዚአ ብሔር በረድኤት ተለየኝን ትላ ወረስዐኒኑ እግዚአብሔር ፤

እግዚአብሔር ዘነጋኝን ትላለች፤

፲፭፡ ትረስዕኑ ብእሲት ዕንላ ፤

አንቺንማ እዘነጋሽ ዘንድ ሴት ልጇን ትዘነጋለችን ይላል እግ ዚአብሔር ፤

ወኢትምሕርኑ ዘወለደት እምከርሣ፤

ከማኅፀኗ ለወለደችው ለልጇ አትራራምን ፤

ወእመኒ ረስዐት ብእሲት ዘንተ ፤

አንዳንድ አትታጣምና እን ጎቶልያ ያች ልጇን ብትዘነጋ፤

አንሰ ኢይረስዐኪ ፤

እኔ ግን አልዘነጋሽም ፤

፲፮፡ ናሁ በእዴየ ሣረርኩ ዐረፋተኪ፤

እነሆ እኔ አምስቱን ቊመ ብእሲ፤ ስድስቱን ቊመ ብእሲ፤ ሰባቱን ቊመ ብእሲ በሥልጣኔ ሠራሁ ፤ አንድም ሠዐልኩ ዐረፋተኪ ይላል ሱሳን ወርድ ይቀረዕባታ ልና ፤

ወቅድሜየ አንቲ ዘልፋ ፤

አንቺ በፊቴ ዘወትር ፀንተሽ ትኖሪያለሽ ፤

፲፯፡ ወፍጡነ ትትሐነፂ እምዘነሰ ቱኪ ፤

ድኅረ ነሰቱኪ ሲል ነው ፤ ጥቅስ እምዘበዝኑ ... ወመአኩ ... ሰሙየ ኤ ዮ

ቡር እንዲል (አሪት ዘልደት ምዕ. ፷፬÷ ፷፪)፤ አንድም አሕ ዛብ ካፈረሱሽ መፍረስ የተነሣ ትሠሪያለሽ ፤ አንድም ወትቤ ጽዮን ብለህ መልስ ፤ ምዕመን እግዚአብሔር ተለየኝን ትላለች፤

ወረስዐኒኑ እግዚአብሔር ፤

እግዚአብሔር እኔን ዘነጋኝን ትላ ለች ፤

፲፰፡ ትረስዕኑ ብእሲት ዕንላ ፤

አንቺንማ እዘነጋሽ ዘንድ ሴት ልጇን ትዘነጋለችን ፤ ከማኅፀኗ ለወለደችው ለልጇ አትራራምን አንዳንድ አትታጣምና እንደ ጎቶልያ ያች ልጇን ብትዘነጋ እኔ ግን አልዘነጋሽም፤ እነሆ እኔ ሕዋ ሳቶችሽን በልጅነት በጸጋ በክ ብር አደስሁ ፤ አንቺ ዘወትር በፊቴ በባለሟልነት ፀንተሽ ትኖ ሪአለሽ፤ አጋንንት ካሳቱሽ በኋላ ፈጥነሽ በልጅነት ትታደሻለሽ ፤

ወይወፅኡ እምኔኪ አለ አማሰኑኪ፤

ያጠፉሽ አሕዛብ ካንቺ ይርቃሉ፤ አንድም ያሳቱሽ አጋንንት ካንቺ ይርቃሉ ፤

፲፱፡ አንሥኢ አዕይንተኪ ወነጽሪ ወውደኪ ፤

መ[illegible] አንባትሽን አቅ ንተሽ ዙሪያሽን ተመልከቺ፤

ናሁ ተጋብዑ ወመጽኡ ኀቤኪ ፤

እነሆ ልጆችሽ ተሰብስበው ወደ አንቺ መጡ ፤

ሕያው አነ ይቤ እግዚአብሔር ፤

እግዚአብሔር እኔ ሕያው ነኝ አለ ፤

ከመ ትሠረገዊዮሙ ወትትረሰዪ ዮሙ ከመ መርዓት ፤

አሕዛብን እንደ ሙሽራ ጌጥ እን ድታደርጊአቸው እግዚአብሔር እኔ ሕያው ነኝ አለ፤ የሀገር ጌጡ ሰው ነውና ፤ አንድም ከመ ትሠ ረግዪዮሙ ሠርጅተሽ እንድት ጥያቸው ሠርጊ እንዲል ትግሬ፤

ወትረሰዪዮሙ ከመ መሬት ፤

እንደ ትቢያም እንድታደርጊያ ቸው እኔ ሕያው ነኝ አለ ፤ አን ድም አንሥኢ አዕይንተኪ ብለህ መልስ ፤ ምዕመን ምን ያጸክም ሻል ፣ አንገትሽን አቅንተሽ ዙሪ ያሽን ተመልከች፤ እነሆ ልጆችሽ ተሰብስበው ወደ አንቺ መጡ ፤

ሕያው አነ ይቤ እግዚአብሔር ከመ ትሠረገዊዮሙ ወትትረሰዪዮሙ ከመ መርዓት ፤

አጋንንትን እንደ ሙሽራ ጌጥ እንድታደርጊያቸው እግዚአብ ሔር እኔ ሕያው ነኝ አለ ፤ አን ድም ከመ ትሠረግዪዮሙ ሠር ጅተሽ እንድትጥያቸው ወትረ ስዪዮሙ ከመ መሬት እንደ

www.ethiopianorthodox.org

ትቢያም እንድታደርጊያቸው ሕያው ነኝ አለ ፤

፲፱፡ እስመ ተመዝበርኪ ወወደቂ ወግሰንኪ ፣

ከዚህ ቀድሞ ፈርሰሻልና በመ ከራም ወድቀሽ ጠፍተሻልና ፤

ወትፀብቢዮሙ ለእለ ይነብሩ ውስ ቴትኪ ፣

ባንቺ ለሚኖሩ ሰዎች ትጠቢያ ቸዋለሽ፤ አንድም ትፀብጺዮሙ ቢል አሕዛብን ትወጊያቸዋለሽ፤

ወይትረኀቱ እለ ኬዱኪ ፣

መከራ ያፀኑብሽ አሕዛብ ካንቺ ይርቃሉ ፤

፳፡ ወይብሉኪ ደቂቅኪ ውስተ ዕዝ ንኪ ይፀብበነ ብሔር ፣

ልጆችሽ በጆሮሽ ስትሰሚ አገር ጠቦናል ፤

ግበሪ ለነ ብሔረ ኀበ ንነብር ፣

የምኖርበት አገር አቅኚልን ይሉ ሻል ፤

፳፩፡ ወአንቲኒ ትብሊ በልብኪ መኑ ወለደ ሊተ እሎንተ ፣

አንቺም በልብሽ እኒህን ሁሉ ማን ወለደልኝ ትያለሽ፤ አንድም ወትፀብቢዮሙ ብለህ መልስ ፣ ቤተ ክርስቲያን ለምዕመናን ትጠ ቢያቸዋለሽ ትፀብጺዮሙ ቢል አጋንንትን ድል ትነሻቸዋለሽ፤

ወይትረኀቱ እለ ኬዱኪ ፣

አጋንንት ካንቺ ይርቃሉ፤ ልጆ ችሽ በጆሮሽ ስትሰሚ ሀገረ ስብ ከት ጠቦናል ፤ ሀገረ ስብከት አስ ፈልጊ ይሉሻል ፤ አንቺም በልብሽ እኒህን ሁሉ ማን ወለደልኝ ትያ ለሽ ፤

ናሁ አንሰ መካን ፣

እኔ መካን ነበርሁ ፤

ወመበለት መኑ አልሐቆሙ ለእሉ ፣

እኔ ድሀ ነበርሁ እነዚህን ማን አሳደጋቸው ትያለሽ ፤

ናሁ አነ ባሕቲትየ እምአይቴ መጽኡ እሉ ፣

እነሆ እኔ ብቻዬን ነበርሁ፣ እነ ዚህ ከወዴት መጡ ትያለሽ ፤

፳፪፡ ከመዝ ይቤ እግዚአብሔር ፣

እግዚአብሔር እንዲህ አለ ፤

ናሁ አነ አነሥእ እዴየ መንገለ አሕ ዛብ ፣

እነሆ እጄን ወደ አሕዛብ አነሣ ለሁ እጅ ለነገር ያግዛልና፣ አን ድም እደ መዐቴን በአሕዛብ ላይ አነሣለሁ ፣ አንድም ነቢያትን ወደ አሕዛብ እሰዳለሁ፣ አንድም ሐዋርያትን ወደ አሕዛብ እሰዳ ለሁ ፤ አንድም እጄን ዘርግቼ እሰቀላለሁ ::

ወእገብር ተአምረ ውስተ ደሰያት ፣

ደሴት በውሀ፣ ውሀ በደሴት እን ዲከበብ በመከራ ለተከበቡ እስ

ራኤል ሞተ ብልጣሶርን አደር ጋለሁ ፤ አንድም ደሴት በውሀ፣ ውሀ በደሴት እንዲከበብ ሰባ ዘመን በጦር ስተከበቡ ለትሩፋን ተአምራት አደርጋለሁ ፤

ወያመጽእዎሙ ለደቂቅኪ በሕዕኖሙ፣

ወንዶች ልጆችሽን የቀላጥም፤

ወይፀውርዎን ለአዋልድኪ በመታክ ፍቲሆሙ ፣

ሴቶች ልጆችሽን እሽኮኮ እየተ ሸከሙ ያመጣቸዋል ፤ አንድም በዘመነ ሐዲስ እናት አባቶቻ ቸው፣ አንድም አንሽዎች አጥም ቁልን አሞርቡልን እያሉ ያመ ጣቸዋል ፤

፳፫፡ ነገሥት አማሑትኪ ፣

ይህ ቢደረግልሽ ድንቅ ነውን ዳዊት ሰሎሞን አያቶችሽ ናቸው፤

ወነጋሥያት ሐፃንያትኪ ፣

ሚስቶቻቸው እነ ቤርሳቤህም ሞግዚቶችሽ ናቸው ፤ አንድም ቂሮስ ዳርዮስ አያቶችሽ ናቸው፤ የቂሮስ የዳርዮስ ሚስቶቻቸው ሞግዚቶችሽ ናቸው ፤ አንድም ዮሴፅ ዘሩባቤል ሞግዚቶችሽ ናቸው ፤

ወይሰግዱ ለኪ ውስተ ገጸ ምድር ፣

ከምድር ወድቀው ይሰግዱልሻል፤

ወይልሕሱ ፀበለ እግርኪ ፣

የእግርሽን ትቢያ ይልሳሉ ማለት ተዋርደው ይገዙልሻል፤ አንድም

ነገሥት አማሑትኪ ፣ ምዕመን ይህ ቢደረግልሽ ድንቅ ነውን ሐዋ ርያት አባቶችሽ ናቸው፤ ሰባ አር ድእትም ሞግዚቶችሽ ናቸው፤ አንድም ሠላሳ ስድስቱ ቅዱሳት አንስት ሞግዚቶችሽ ናቸው ፤ ምዕመናን አሕዛብ ከምድር ወድ ቀው ይሰግዱልሻል በቁሙ የእግ ርሽን ትቢያ ይልሳሉ፤ እንደ አስ ከናፍር ይህስ እንደ ምነው ቢሉ አስከናፍር የሚባል ደግ ሰው ነበር ፣ ዐሥራ ሦስት ወንበዴዎች እሱን ገድለን ገንዘቡን ዘርፈን ቤቱን ተኩሰን እንሂዳለን ብለው መጡ ፣ ሲደርሱ እግራቸውን አጥቦ ባልጋ ቀራኛ በደጁ ዳኛ ተይዞ የሚኖር ልጅ ነበረው የእ ግራቸውን ዕጣቢ ቢያጠጣው ከደ ጁው ዳነ፤ ምን ብለህ ነው አሉት፤ በዚያ ወራት የጌታን የሐዋርያ ትን ዜና ይሰማ ነበርና ዐሥራ ሁለቱ ሐዋርያት ናችሁ ዐሥራ ሦስተኛው ጌታዬ ኢየሱስ ክርስ ቶስ ነው ብዬ ነው አላቸው፤ እኛስ አንተን ገድለን ገንዘብህን ዘርፈን ቤትህን ተኩሰን እንሂዳለን ብለን ነበር ብለው ሰይፋቸውን ቢመ ዙት ደም ጐርሶ ተገኝቷል ይላሉ፤ በዚህ ምክንያት በዚያው መንነው ቀርተዋል ፣ ሰላም ለአስከናፍር ድደ ሃይማኖቱ ሥሩር፣ በኩሉ ሐ ወንጌል ሥሙር ፣ ያዋኪ ወትረ እምእግረ አሜር መፃጉዕ ደዌ

www.ethiopianorthodox.org

አሕየወ በፀበለ ፈያት ነኪር ፣ ወሃይማኖቱ ዔነወ ለኵሉ ብሔር እንዳለ ደራሲ ፤

ወተአምሪ ከመ አነ ውእቱ እግዚአብሔር ወኢትትኀፈሪ እንከ ፣

ፈጣሪሽ እኔ እንደ ሆንሁ ታውቂአለሽ እንግዲህ ወዲህም መከራ መጥቶብሽ አታፍሪም ፤

፳፬፡ ቦኑ ዘየሐይድ ንዋዮ ለኀያል ይድኅንኑ ፣

በውኑ የኀይለኛውን ገንዘብ የቀማ ይድናልን ?

ወዘዜወዎ ለያርብሓዊ ኢይመውትኑ፣

ዐርበኛውንስ የማረከ አይሞት ምን ፤

፳፭፡ ከመዝ ይቤ እግዚአብሔር ጸባያት ፣

አሸናፊ እግዚአብሔር እንዲህ አለ ፤

እመኒ ዘሃዶ ለኀያል ይድኅን ፣

ኀይለኛውን የቀማው ሰው ምንም የሚድን ቢሆን ወዘዜወዎ ለያር ብሐዊ ኢይመውትኑ ያለበት ነው ፤

አንሰኬ እፈትሕ ፍትሐኪ ፣

እኔ ግን እንደዚያ አይደለሁም፤ ፈርጄ አድንሻለሁ ፤

ወዓዲ አድኅኖሙ ለደቂቅኪ ፣

ዳግመኛ ልጆችሽን አድናቸዋለሁ ፤

፳፮፡ ወይበልዑ ሥጋሆሙ ለእለ ይግ ቅዩኪ ፣

መከራ የሚያፀኑብሽን ሰዎች ገን ዘብ ይበላሉ ፤

ወይሰትዩ ደሞሙ ከመ ጸዕፍ ወይሰ ክሩ ፣

ገንዘባቸውን እንደ መጠጥ አብዝ ተው ይሰበስባሉ ፤ በኃጢአት አረቂ ይሰክራሉ ፤

ወየአምሩ ኵሉ ዘሥፍስ ከመ አነ ውእቱ እግዚአብሔር ዘአድኅንኩኪ ፣

ሥጋዊ ደማዊ ሰዎች ሁሉ ያዳን ሁሽ ፈጣሪ እኔ እግዚአብሔር እንደ ሆንሁ ያውቃሉ ፤

ወዘተወከፍኩ ኀይለ ያዕቆብ ፣

ነገደ ያዕቆብ ሲል ነው ፤ የያዕቆ ብን ወገን በረድኤት የተቀበልሁ እኔ እንደ ሆንሁ ያውቃሉ፤ አን ድም የያዕቆብን ሠራዊት፤ አን ድም የያዕቆብን ብዕል የተቀበ ልሁ እኔ እግዚአብሔር እንደ ሆንሁ አእምሮ ያላቸው ሰዎች ሁሉ ያውቃሉ ::

ምዕራፍ ፶

፩፡ ከመዝ ይቤ እግዚአብሔር ዐይኑ ዝንቱ መጽሐፈ ኀዳጋቲሃ ለእምክሙ ዘፈነውኩ ላቲ ፣

እግዚአብሔር ነገሥታቱን ካህና ቱን እንዲህ ይላቸዋል፤ ፄዋዌን ያመጣሁባት እናታችሁ የምት

ፈታበት፣ ነውሯን የሚነግር ደብ ዳቤ ወዴት ነው ? አንድም የና ታችሁ የንጉሥ የሊቀ ካህናቱ የኃጢአቷ ፍዳ ወዴት ነው አል ጠፋም ፤

ወለመኑ እፈዲ ዕዳ ዘሚጥኩክሙ ፣

እናንተን ለአሕዛብ አሳልፌ የሰ ጠኋችሁ የማን ዕዳ ኑሮብኝ ልከ ፍል ነው ፤

አኮኑ በኃጢአትክሙ ሜጥኩክሙ ፣

በኃጢአታችሁ አሳልፌ የሰጠኋ ችሁ አይደለምን ፤

ወበጌጋይክሙ ፈነውክዋ ለእምክሙ፣

በኃጢአታችሁ ነገሥታቱን ካህ ናቱን አስማርኬ የሰደድኋቸው አይደለምን ፤

፪፡ ወናሁ መጻእኩ ወአልቦ ሰብእ ፣

እነሆ እኔ በነቢያት ፣ በካህናት አድራ በረድኤት መጣሁ ባለ አእምሮ ሰው የለም ፤

ወጸዋዕኩ ወአልቦ ዘተሰምዎኒ ፣

በነቢያት በካህናት አድራ ተናገ ርሁ፣ የመለስልኝ የለም፤ አንድም በነቢያት በካህናት አድራ አስተ ማርሁ፣ የሰማኝ የለም ፤

ኢትክልኑ አድኅኖ እዴየ ፣

አያድንም ትሉኝ ዘንድ ሥልጣኔ ማዳን አይቻላትምን ፤

ወኢይክልኑ ባልሖ ፣

እኣስ ማዳን አይቻለኝምን ፤

ናሁ በተግሣጸየ አነጽፋ ለባሕር ፣

እነሆ ፈርጄ ኤርትራን ዮርዳኖ ስን እከፍላታለሁ፤ አንድም ባቢ ሎንን አጠፋታለሁ ፤

ወአየብሰሙ ለአፍላግ ፣

ነገሥታቱን አጠፋቸዋለሁ ፤

ወይመውቱ ዓሣቲሆሙ ቡኀኒአ ማይ፣

ሠራዊቱ ተድላ ደስታ በማጣት ይጠፋሉ ፤

ወየኀልቁ በዕምዕ ፣

በፅም ያልቃሉ ፤

፫፡ ወእገለብባ ለሰማይ በጽልመት ፣

በባቢሎን መከራ አመጣባታለሁ፤

ወአለብሳ ሠቀ ፣

አዋርዳታለሁ ፤

ጌባኤ

፬፡ እግዚአብሔር እግዚእ ይሁበኒ ልሳነ ጥበብ ከመ አእምር ቃለ ዘእነ ብብ ፣

የማስተምራት አሪትን ዐውቄ አስተምር ዘንድ ገባር የሚሆን እግዚአብሔር ጥበብ ያለበትን አንደበት ይሰጠኛል ይላል ነቢዩ፤

አንቅሐኒ በጽባሕ ፣

ፈጥኖ ከንዋመ ሐኬት አስነሣኝ ይላል ነቢዩ ፤

ወመሰከኒ ዕዝነ በዘአፀምዕ ፣

አሪትን በማስተምር ገንዘብ አስተ ምር ዘንድ በአእምር ጠባይዕ ላይ

www.ethiopianorthodox.org

አእምሮ መንፈሳዊን ጨመረ
ልኝ ፤

፭፡ ወተግሣጸ እግዚአብሔር ይክሥ
ተኒ ዕዝንየ ፣

ሥልጣኑ እግዚአብሔር ዕዝነ ልቡ
ናዬን ይገልጥልኛል ፤

አንሰ ኢይክሀድ ፤

ፈጣሪዬን አልክድም ፤

ወኢይትዋሣእ ፣

በሐሰት ነገር አልከራከርም፤ አን
ድም እግዚአብሔር እግዚእ ይሁ
በኒ ልሳነ ጥበብ ከመ አእምር
ቃለ ዘእነብብ ብለህ መልስ ፣
የማስተምራት ወንጌልን ዐውቄ
አስተምር ዘንድ ጥበብ ያለው
አንደበት ይሰጠኛል ፤

አንቅሐኒ በጽባሕ ፣

ምዕመናንን ከንዋመ ሐኬት አስ
ነሣልኝ ይላል ጌታ ፤

ወመሰከኒ ዕዝነ በዘሖየምዕ ፣

በዕዝነ ሰማዕያን ላይ ዕዝነ ሰማዕ
ያንን ጨመረልኝ ወንጌልን በማ
ስተምር ገንዘብ፤ አንድም በዕዝነ
መስኮት ላይ ዕዝነ ሥጋን ጨመ
ረልኝ ጽርፈተ አይሁድን በምሰማ
ገንዘብ ፤

ወተግሣጸ እግዚአብሔር ይክሥተኒ
ዕዝንየ ፣

ተግሣጸ እግዚአብሔርም የምዕ
መናንን ዕዝነ ልቡና ይገልጥል
ኛል ፤

አንሰ ኢይክሀድ ወኢይትዋሣእ ፣

አምላክነቴን አልክድም በሥጋዊ
ነገር አልከራከርም ፤

፮፡ መጠውኩ ዘባንየ ለቅሥፈት ፣

ደረቅ ሐዲስ ነው ጀርባዬን ለግ
ርፋት ሰጠሁ ፤

ወመልታሕቴየ ለጽፍዐት ፣

ፊቴንም ለጽፍዐት ሰጠሁ ፤

ወኢሜጥኩ ገጽየ እምነፍረተ ምራቅ፣

ከነፍረተ ምራቅ የተነሣ ፊቴን
አልመለስሁም፣ አንድም ምራቀ
ርኩሳንን ከመቀበል ፊቴን አል
መለስሁም ፤

፯፡ ወእግዚአብሔር እግዚእ ረዳኤ
ኮነኒ ፣

እግዚአብሔር ረዳት ሆነኝ ፤

ወበእንተ ዝንቱ ኢተኀፈርኩ ፣

ስለዚህ ነገር አላፈርሁም ማለት
ተነሣሁ ፤

ወረሰይኩ ገጽየ ከመ ኰኮሕ ዕኑዕ፣

ፊቴን እንደ ዐለት ደንጊያ ዕኑ
አደረግሁ ማለት መከራውን አል
ተሰቀቅሁም ፤

ወአአመርኩ ከመ ኢይትኀፈር ፣

እንድነሣ አወቅሁ ፤

እስመ አልጸቀ ዘያጸድቀኒ ፣

የሚያስነሣኝ ሥልጣኔ ከእኔ ጋራ
አለና ፤

፰፡ መኑ ውእቱ ዘይትዋቀሰኒ ይም
ጻእ ኀቡረ ፣

ከዐቀብተ መቃብር የሚቃወመኝ
ማነው? አለ እንደሆነ ይምጣ ፤

ወመኑ ዘይሳነነኒ ወዘይቀርበኒ ፣

ከዐቀብተ መቃብር የሚጣላኝ
ወደኔ የሚቀርብ ማነው ፤

፱፡ ናሁ እግዚአብሔር ይረድአኒ ወመኑ
ይነስሶ ላዕሌየ ፣

እነሆ እግዚአብሔር ይረዳኛል
በእኔ ላይ ክፉ ነገር ማድረግ የሚ
ቻለው ማነው ?

ናሁ ኵልክሙ ከመ ልብስ ትበልዩ፣

ብሉዩን ይዞ ይሄዳል፣ እነሆ ሁላ
ችሁ እንደ ልብስ ትጠፋላችሁ ፤

ወከመ ዓፄ ዘይበልዕ ዕፀ ፣

ወከመ ዕዕ ዘይበልዖ ዓፄ ሲል ነው፤
ነቀዝ እንደ በላው እንጨት ትሆ
ናላችሁ ፤ አንድም እንጨት እን
ደሚበላ ነቀዝ ትሆናላችሁ ፤

፲፡ መኑ እምኔክሙ ዘይፈርህ ይስማዕ
ቃለ ገብሩ ፤

ከእናንተ ወገን የባርያው የኢሳ
ይያስን ቃል ይሰማ ዘንድ ከእና
ንተ የሚፈራ ማነው ፤

እለ ትነብሩ ውስተ ጽልመት ወአል
ብክሙ ብርሃን ፣

በድንቁርና ፀንታችሁ የምትኖሩ
ናችሁ፣ ዕውቀት የላችሁም፤ አን
ድም በመከራ ፀንታችሁ የምት
ኖሩ ናችሁ ተድላ ደስታ የላች
ሁም፤ አንድም በኃጢአት ፀንታ
ችሁ የምትኖሩ ናችሁ፣ ንስሓ የላ
ችሁም ፤ አንድም አምልኮተ እግ
ዚአብሔር የሌላችሁ በአምል
ኮተ ጣዖት ፀንታችሁ የምትኖሩ
ናችሁ ፤

ተወከሉ በስመ እግዚአብሔር ፣

በእግዚአብሔር ስም እመኑ ፤

ወአስምኩ በስመ እግዚአብሔር ፣

በእግዚአብሔር ስም ዕኑ ፤

፲፩፡ ናሁ ኵልክሙ ትውዕዩ በእሳት፣

አናምንም ግን ብትሉ ሁላችሁም
በመከራው ትጠፋላችሁ ፤

ወአዕበይክሙ ነበልባለ ፣

ኃጢአቱን አብዝታችሁ ሠራ
ችሁ ፤

ሑሩኬ እንከ በብርሃነ እሳትክሙ፣

እንግዲህ ወዲህስ በሠራችሁት
ኃጢአት ተማርካችሁ ወደምት
ጠፉበት አገር ሂዱ ፤

ወበነበልባል ዘአንደድክሙ ፣

በሠራችሁት ኃጢአት ትጠፋላ
ችሁ ፣

በእንቲአየ ረከበክሙ ዝንቱ ፣

እኔን ባታመልኩ ይህ ሁሉ መከራ
አገኛችሁ ፤

ወኵልክሙ ትሰክቡ በሕማምክሙ፣

ሁላችሁም በመከራ ተይዛችሁ
ትኖራላችሁ ::

www.ethiopianorthodox.org

ምዕራፍ ፶፭

፩፤ ስምዑ ዘንተ ኵልክሙ፡ አለ ትደ
ግንዋ ለጽድቅ ፣

ሕግን የምትከተሏት እናንተ ሁሉ
ይህን ስሙ ፤

ወአለ ተነሥሥዎ ለእግዚአብሔር ፣

እግዚአብሔርን በሕግ በአምል
ኮት የምትሹት ስሙ፤ አንድም
ጽድቅን ሳትከተሏት እንከተላታ
ለን የምትሉ እግዚአብሔርንም
ሳትፈልጉ እንፈልገዋለን የምትሉ
ስሙ ፤

ርእይዋ ለኵሉ ሕ ፅንዕት እንተ ወቀ
ርክሙ ፣

ያለዘባችኋትን ፅንዕት ደንጊያ
እዩአት ፤

ወዐዘቅተ ዕምቅተ እንተ ከረይክሙ፣

የቈፈራችኋትን ጥልቅ ዐዘቅት
እዩአት የኩሬውን የጥ ድጓዱን
ማለት ነው ፣ አንድም ርእይዋ
ለኵሉ ሕ ፅንዕት እንተ ወቀር
ክሙ እንተ ተወለድክሙ ሲል
ነው የተወለዳችሁለት አብርሃ
ምን እዩት ፤

ወዐዘቅተ ዕምቅተ እንተ ከረይክሙ፣

እንተ ተወለድክሙ ሲል ነው፤ የተ
ወለዳችሁላት ሣራንም እዩአት፤

፪፤ ርእይዎ ለአብርሃም አቡክሙ

ኵሉ ሕ ያለውን ገለጠው አባታ
ችሁ አብርሃምን እዩት አስቡት፤

ወለሣራሂ እንተ ሐመት ብክሙ ፣

ዐዘቅት ያለውን ገለጠው፤ ስለ እና
ንተ መከራ የተቀበለች ሣራንም
እዩአት አስቧት ፤

እስመ አሐዱ ውእቱ ፣

አብርሃም አንድ ነበርና አለ ፣
ጥቂት ነበርና ፤

ወጸዋዕክዎ ፣

ከከላውዴዎን ወደ ካራን፣ ከካራን
ወደ ከነዓን ጠርቼዋለሁና ፤

ወባረክዎ ፣

አክብሬዋለሁና ፤

ወአፍቀርክዎ ፣

ወድጂዋለሁና

ወአብዛኅክዎ ፣

አብዝቼዋለሁና እንደ እሱ ትበዙ
ዘንድ የዛሬውን ብዛታችሁን
አትዩ ፣ የቀድሞውን ማነሳችሁን
እዩ ፣ በጥቂትነት ሳላችሁ አሕ
ዛብ ይቀሟችሁ እንደነበረ፤ አን
ድም ርእይዋ ለኵሉ ሕ ፅንዕት
እንተ ወቀርክሙ እንተ ሰተይ
ክሙ እንተ ረወይክሙ ሲል ነው፣
የጠላችሁባትን ፅንዕት ደንጊያ
እዩአት፤ ወዐዘቅተ ዕምቅተ እንተ
ከረይክሙ ፣ እንተ ሰተይክሙ
እንተ ረወይክሙ ሲል ነው ፣ የጠ
ላችሁባትን ዐዘቅት እዩአት ፤

ርእይዎ ለአብርሃም አቡክሙ

አባታችሁ አብርሃምን እዩት፤

ወለሣራሂ እንተ ሐመት ብክሙ ፣

ስለ እናንተ መከራ የተቀበለች
ሣራንም እዩአት ፤

እስመ አሐዱ ውእቱ ፣

አብርሃም አንድ ነበርና ማለት
ጥቂት ነበርና ፤

ወጸዋዕክዎ ፤

ከከላውዴዎን ወደ ካራን፣ ከካራን
ወደ ከነዓን ጠርቼዋለሁና ፤

ወባረክዎ ፣

አክብሬዋለሁና ፤

ወአፍቀርክዎ ፣

ወድጂዋለሁና ፤

ወአብዛኅክዎ ፣

አብዝቼዋለሁና የዛሬውን መቀ
ማታችሁን አትዩ፣ በአብርሃም
ጊዜ ትቀሙት የነበረውን አስቡ፤
አንድም ርእይዋ ለኵሉ ሕ ፅን
ዕት እንተ ወቀርክሙ እንተ ዘበ
ጥክሙ ወእንተ ከፈልክሙ ሲል
ነው ፣ በብትር መትታችሁ የከ
ፈላችኋትን ኤርትራን ፣ ወዐዘ
ቅተ ዕምቅተ እንተ ከረይክሙ፤
እንተ ዐደውክሙ ወእንተ ኀለፍ
ክሙ ውስቴታ ሲል ነው ፤ በው
ስጣ ያለፋችሁባት ኤርትራን እዩ
አት ፤

ርእይዎ ለአብርሃም አቡክሙ ፤

አባታችሁ አብርሃምን በሃይማ
ኖት ምሰሉት ፤

ወለሣራሂ እንተ ሐመት ብክሙ ፣

ስለ እናንተ መከራ የተቀበለች
ሣራንም በሃይማኖት ምሰሏት፣
የቀረው አይለወጥም፤ አንድም
ርእይዋ ለኵሉ ሕ ፅንዕት እንተ
ወቀርክሙ ፤

እንተ ዘበጥክሙ ወእንተ አንቃ
ዕክሙ ማየ ሲል ነው፤ ከኤርትራ
ከወጣችሁ በኋላ በምድረ በዳ
በብትር መትታችሁ ከደንጊያ
ያወጣችሁትን ውሀ ፤

ወዐዘቅተ ዕምቅተ እንተ ከረይክሙ፣

እንተ ሰተይክሙ ማየ እምኔሃ
ሲል ነው፤ ከእሷ የጠጣችሁትን
ውሀ አስቡ ፤

ርእይዎ ለአብርሃም አቡክሙ ፣

አባታችሁ አብርሃምን በሃይማ
ኖት ምሰሉት ፤

ወለሣራሂ እንተ ሐመት ብክሙ ፣

ስለ እናንተ መከራ የተቀበለች
ሣራንም በሃይማኖት ምሰሏት፣
የቀረው አይለወጥም፤ እንደ ቀደ
መው ነው፤ እንተ ወቀርክሙ
እንተ ከረይክሙ ማለቱ በኮሬ
ብና በቃዴስ የተደረገውን መና
ገር ነው ፤ አንድም ርእይዋ ለኵ
ኵሉ ሕ ፅንዕት እንተ ወቀርክሙ
እንተ ሰቀልክሙ ወእንተ ቀተል
ክሙ ሲል ነው ፤ ሰቅላችሁ የገደ
ላችሁት ክርስቶስን እዩ ፤ ወዐዘ
ቅተ ዕምቅተ እንተ ከረይክሙ

www.ethiopianorthodox.org

እንተ ረገዝክሙ ወእንተ አውፅአ
ለክሙ ማየ ሲል ነው፣ በኮናተ
ሐራ የወጋችሁት ውሀ ከጉኑ ያነ
ቃላችሁን ያፈሰሰላችሁን ክርስ
ቶስን እዩት ፤

ርእይዎ ለአብርሃም አቡክሙ ፣

አባታችሁ አብርሃምን በሃይማ
ኖት ምሰሉት ፤

ወለሣራሂ እንተ ሐመት ብክሙ ፣

ስለ እናንተ መከራ የተቀበለች
ሣራንም በሃይማኖት ምሰሏት፤

እስመ አሐዱ ውኢቱ ፣

አብርሃም አንድ ነበርና ማለት
ጥቂት ነበርና ፤

ወጸዋዕክዎ ፣

ከከላውዴዎን ወደ ካራን፣ ከካ
ራን ወደ ከነዓን ጠርቼዋለሁና፤

ወባረክዎ ፤

አክብሬዋለሁና ፤

ወአፍቀርክዎ ፣

ወድጄዋለሁና ፤

ወአብዛኅክዎ ፣

አብዝቼዋለሁና እናንተም እን
ድትወደዱ እንድትበዙ አብርሃ
ምን በሃይማኖት ምሰሉት፤ አን
ድም ወጸዋዕክዎ ጠርቼዋለሁና፤

ወባረክዎ ፣

ባረክዎን አስጠብቅ ፤

ወአፍቀርክዎ ፣

ወድጄዋለሁና ፤

ወአብዛኅክዎ ፣

አብዝቼዋለሁና ወባረክዎ ብለህ
ግጠም አክብሬዋለሁና እናን
ተም እንደ እሱ ትከብሩ ዘንድ
በሃይማኖት ምሰሉት ፤

፫፤ ወይእዜኒ አስተፋሥሐኪ ለኪ ኢየ
ሩሳሌም ፣

አሁንም ኢየሩሳሌም ከዚህ አስ
ቀድሞ አባቶችሽን ደስ እንዳሰ
ኘሁ አንቺንም ደስ አሰኝሻለሁ፤

ወአስተፋሥሕ ኦሎ አኀቃላተኪ ፣

አውራጃዎችሽን ሁሉ ደስ አሰኛ
ለሁ፣

ወእሬስያ ለበድው ከመ ገነት ፣

ምድረ በዳይቱን የተክል ቦታ
አደርጋታለሁ ማለት ሰባ ዘመን
ምድረ በዳ የነበረች ኢየሩሳሌ
ምን ገነት ለምለም እንደ ሆነች
እንድትለመልም አደርጋታለሁ፤

ወለአኀቃላቲሃ ከመ ገነተ እግዚአብ
ሔር ፣

አውራጃዎቿን እግዚአብሔር እን
ደፈጠራት እንደ ገነት አደርጋቸ
ዋለሁ ፤

ወይትረከብ በውስቴታ ትፍሥሕት
ወነሢት ፣

ፍጹም ተድላ ደስታ በእሷ ይገ
ኛል ፤

አሚን ወቃለ ስብሐት ፣

ምግባር ሃይማኖት የጌትነት ነገር
በእሷ ይገኛል፤ አንድም አሚን
ሃይማኖት ወቃለ ስብሐት የምስ
ጋና ቃል እንዲሰማባት አደርጋ
ለሁ ፤

፬፤ ስምዑኒ ስምዑኒ ሕዝብየ ፣

ወግኖቼ ስሙኝ ስሙኝ ፤

ወአፅምዑኒ ነገሥት ተግሣጽየ ፣

ነገሥታቱ ምክሬን ስሙኝ ፤

እስመ ሕግ ይወፅእ እምኔየ ፣

ሕግ ከእኔ ይገኛልና ፣

እስመ ፍትሕየኒ ብርሃነ አሕዛብ ፣

ፍርዴም የአሕዛብ ተድላ ደስታ
ነውና ፣

፭፤ ትመጽእ ፍጡነ ጽድቅየ ወትበ
ጽሕ መድኀኒትየ ፤

ሚጠት ፈጥና ትደረጋለች፣ ትደ
ርሳለች ፤ አንድም ባምስት ሺህ
ካምስት መቶ ዘመን ረድኤቴ
ቸርነቴ ትመጣለች ፣

ወይትዌከሉ አሕዛብ በመዝራዕትየ፣

አሕዛብ በሥልጣኔ ያምናሉ ፣

ኪያየ ይሴፈዉ አሕዛብ ፣

አሕዛብ በእኔ ያምናሉ ፣

ወደሰያትኒ ይትዌከሉ በመዝራዕትየ፣

ደሴት በውሀ፣ ውሀ በደሴት እን
ዲከበብ ሰባ ዘመን በመከራ ሥጋ
የተከበቡ ትሩፋን በሥልጣኔ ያም
ናሉ ፤ አንድም ደሴት በውሀ ፣
ውሀ በደሴት እንዲከበብ አም
ስት ሺህ ካምስት መቶ ዘመን
በመከራ ነፍስ የተከበቡ ምዕመ
ናን በልጄ ያምናሉ ፣

፮፤ አንሥኡ አዕይንቲክሙ ወነጽሩ
ሰማየ ፣

አንገታችሁን አቅንታችሁ ሰማ
ይን እዩ ፣

ወምድረሂ በታሕቱ ፣

ከሰማይ በታች ያለች ምድር
ንም እዩ ፤ አንድም ከተማውን
ገጠሩን እዩ፣ ሁለቱም አርእስት
ነው ለሁለቱም ያመጣል፣

እስመ ሰማይኒ ከመ ጢስ ፀነት ፣

ትፀንን ሲል ነው፣ ሰማይ በአድ
ማስ ላይ አዘንብላለችና ነጽሩ
ሰማየ ላለው ፣

ወምድርኒ ከመ ልብስ ትበሊ ፣

ምድርም ልብስ ተለብሶ እንዲ
ያረጅ አርጅታለችና፣ ወምድረሂ
በታሕቱ ላለው፤ አንድም ነጽሩ
ሰማየ ልቡላኑን፣ ወምድረሂ በታ
ሕቱ ትሑታኑን እዩ ፤

እስመ ሰማይኒ ፣

ባቢሉን ጠፍታለችና ነጽሩ ሰማየ
ላለው ፣

ወምድርኒ ፣

ትሑታኑ ይጠፋሉና ወምድረሂ
በታሕቱ ላለው፤ አንድም

www.ethiopianorthodox.org

አንሥኡ አዕይንቲክሙ ወነጽሩ ሰማየ፣
አንገታችሁን አቅንታችሁ ሰማ
ይን እዩ ፤
ወምድረሂ በታሕቱ ፣
ምድርንም እዩ ፤
እስመ ሰማይኒ ከመ ጢስ ፀነት ፣
ትፀንን ሲል ነው ሰማይ ታልፋ
ለችና ወነጽሩ ሰማየ ላለው ፤
ወምድርኒ ከመ ልብስ ትበሊ ፣
ምድርም እንደ ልብስ ታልፋለ
ችና ወምድረሂ በታሕቱ ላለው ፤
ወእለሂ ይነብርዋ ከመ ዘይመውቱ፣
በእሷም የሚኖሩ ሰዎች የሚሞቱ
ናቸው፤ አንድም ከመ ዘሞቱ ሲል
ነው፤ በውስጧ ያሉ አሕዛብ እንደ
ሞቱ ሰዎች ያሉ ናቸው ፤ አን
ድም በዚህ ዓለም ያሉ ሰዎች
እስኪያልፉ ድረስ እንደሚሞት
ሰው ያጣጥራሉ፣ ሊሞት የቀረበ
ሰው እንዲያጥር ይጣጣራሉ ፤
ወመድኀኒትየሰ ለዓለም ይእቲ ፣
ሚጠት ግን ፈጽማ ትደረጋለች፤
ወጽድቅየኒ ኢተኀልቅ ፣
ቸርነቴም አትፈጸምም ፤
፯፡ ስምዑኒ እለ ተአምሩ ፍትሐ ሕዝ
ብየ እለ ውስተ ልብክሙ ሕግየ ፣
ሕጌም በልቡናችሁ ያለ የድሆ
ችን ፍርድ የምታውቁ፤ አንድም
ሳይናበብ የሆነ እንደሆነ ሕጌ
በልባችሁ የተጻፈ ፍርድን የም
ታውቁ ወገኖቼ ስሙ ፤
ኢትፍርሁ ጽእለተ ሰብእ ፣
የሰውን ስድብ አትፍሩ ፤
ወትግርምቶሙ ፣
የባቢሎንን ሰዎች መገረማቸውን
አትፍሩ ፤
ወኢትትመውዑ ፣
ድል አትነሡም ፤
፰፡ እስመ ከመ ልብስ ይበልዩ ፍጡነ፣
እንደ ልብስ ፈጥነው ይጠፋሉና፤
ወኢይጐነድዩ ፣
አይዘገዩምና ምነው ሰባ ዘመን
ኑረው የለም ቢሉ አይቀሩም ሲል
ነው ፤
ወከመ ብላዐ ቍንቍኔ ይከውኑ ፣
ብል እንደ በላው ልብስ ይሆናሉ፤
ጽድቅየሰ ለዓለም ትቀውም ፣
ሚጠት ግን ለዘለዓለም ፀንታ
ትኖራለች ፤
ወመድኀኒትየኒ ለትውልደ ትውልድ፣
መድኀኒቴ ሚጠት ለልጅ ልጅ
ዘመን ፀንታ ትኖራለች ፤
፱፡ ተንሥኢ ተንሥኢ ኢየሩሳሌም ፣
ነገሥታቱን ካህናቱን እንዲህ
ይላቸዋል ፣ ኢየሩሳሌም ተነሽ
ተነሽ ፤

ልበሲ ኀይለ መዝራዕትኪ ፣
የሥልጣንሽን ኀይል ግለጭ ፤
ተንሥኢ ከመ መዋዕለ ትካት ፣
እንደ ዳዊት እንደ ሰሎሞን ጊዜ
ተነሽ ፤
ወዘእምፍጥረተ ዓለም ፣
እንደ ሙሴ እንደ አሮን ዘመን፤
፲፡ አኮኑ አንቲ እንተ አንጸፍኪያ
ለባሕር ፣
ምን ያዳክምሻል ደግ እንደ ሆንሽ
ይታወቅ ዘንድ ኤርትራን ከሦ
ስት ከአራት እንድትከፈል ያደ
ረግሻት አንቺ አይደለሽምን?
ወአይበስኪ ማየ ቀላይ ብዙኀ ፣
ዮርዳኖስን የብስ ያደረግሽው
አንቺ አይደለሽምን ፤
ወረሰይኪያ ለቀላየ ማይ ፍኖተ መፅ
ያሕት ፣
የኤርትራን የዮርዳኖስን ውሀ
ጥርጊያ ጐዳና ያደረግሻት አንቺ
አይደለሽምን ፤ አንድም አኮኑ
አንቲ እንተ አንጸፍኪያ ለባሕር
ታነጽፊያ እንደ ማለት ባቢሎንን
የምታጠፊያት አንቺ አይደለሽ
ምን ፤
ወአይበስኪ ማየ ቀላይ ብዙኀ ፣
ታየብሲ ሲል ነው ፤ ሠራዊቱን
የምታጠፊ አንቺ አይደለሽምን፤
ወረሰይኪያ ለቀላየ ማይ ፍኖተ መፅ
ያሕት ፣
ትሬስዪያ እንደ ማለት ባቢሎ
ንን ጥርጊያ ጐዳና የምታደርጊ
ያት አንቺ አይደለሽምን ፤
፲፩፡ ለእለ ድኅኑ ወተባልሑ ሜጦሙ
እግዚአብሔር ፤
ከሞት የዳኑ ትሩፋንን እግዚአ
ብሔር ከባቢሎን ወደ ኢየሩሳ
ሌም መለሳቸው ፤
ወአተዉ ጽዮንሃ በትፍሥሕት ወበኀ
ሤት ዘለዓለም ፣
ዘለዓለም ፀንቶ በሚኖር ተድላ
ደስታ ወደ ኢየሩሳሌም ገቡ ፤
እንዘ ውስተ ርእሶሙ ስብሐት ፣
ዘሩባቤል ዘውድ ደፍቶላቸው ፤
ወይረክቦሙ ትፍሥሕት ወኀሤት ፣
ተድላ ደስታ ያገኛቸዋል ማለት
ተድላውን ደስታውን ያገኛሉ ፤
ኀልቀ እንከ ሕማም ወትካዝ ፣
እንግዲህ ወዲህ የሰባው ዘመን
መከራ ትካዝ ተፈጸመ፤ አንድም
ለእለ ድኅኑ ወተባልሑ ሜጦሙ
እግዚአብሔር ፣ ከኃጢአት የዳኑ
ትን እግዚአብሔር ከሲኦል ወደ
ገነት ወደ መንግሥተ ሰማያት
መለሳቸው ፤
ወአተዉ ጽዮንሃ በትፍሥሕት ወበኀ
ሤት ዘለዓለም ፣
ምዕመናን ለዘለዓለም ፀንቶ በሚ
ኖር ተድላ ደስታ ወደ ገነት ወደ
መንግሥተ ሰማይ ገቡ ፤

www.ethiopianorthodox.org

እንዘ ውስተ ርእሶሙ ስብሐት ፣

ክርስቶስ አክሊለ ሦክ ደፍቶላ ቸው ፤

ወይረክቦሙ ትፍሥሕት ወኀሤት ፣

ተድላውን ደስታውን ያገኛሉ ፤

ኀልቀ እንከ ሕማም ወትካዝ ፣

ያምስቱ ሺህ ካምስት መቶ ዘመን መከራ ነፍስ ኀዘነ ነፍስ ተፈጸመ ፤

፲፪፡ አነ ውእቱ ዘአስተፌሥሐኪ ፣

ደስ የማሰኝሽ እኔ ነኝ ፤

ወአእምሪ እንከ ፣

እንግዲህ ወዲህ ዕወቂ ፤

አንቲሂ መነሃ ፈራህኪ ፣

ከባቢሎን አልወጣም ያልሽ አንቺ ማንን ፈራሽ ፤

ሰብአኑ መዋቴ ፣

ፈራሽ በስባሽ ሰውን ፈራሽን ፤

ወዕጓለ እመሕያውኑ ዘይየብስ ከመ ሣዕር ፣

እንደ ሣር የሚደርቅ ማለት ፈጥኖ የሚጠፋ ሰውን ፈራሽን ፤

፲፫፡ ወአንቲሰ ረሳዕኪዮ ለእግዚአብ ሔር ዘፈጠረኪ ፣

አንቺ ግን የፈጠረሽ እግዚአብ ሔርን ዘነጋሽው ፤

ወዘገብረ ሰማየ ወዘሣረራ ለምድር ፣

ሰማይንና ምድርን የፈጠረ ብሎ ለእግዚአብሔር ቀጠለ ፣ እግዚአ ብሔርን በሕግ በአምልኮት ዘነ ጋሽው ፤

ወፈራህኪ በኵሉ ልብኪ ፣

በፍጹም ልቡናሽ ፈራሽ ፤

ወበኵሉ መዋዕልኪ እምገጸ መዓቱ ለዘሣቀየኪ ፣

መከራ የሚያፀናብሽ የእግዚአ ብሔር ገጸ መዓቱ ከመገለጡ የተ ነሣ ባለ በዘመንሽ ሁሉ ፈራሽ ፤

፲፬፡ እስመ እምከመ ድኅንኪ ኢይሄሉ እንከ ወኢይጐነዲ ፣

አንቺ ከዳንሽ በኋላ መከራው እንግዲህ ወዲህ ካንቺ ጋር አይኖ ርም አይዘገይምና ፤

፲፭፡ እስመ አነ እግዚአብሔር አም ላክኪ ዘአከውሳ ለባሕር ፣

ባቢሎንን እንድትጠፋ የማደር ጋት እኔ ነኝና ፤

ወአደምፆ ለማዕበላ ፣

ዜና ጥፋቷ እንዲሰማ የማደ ርግ ፤ አንድም ኀያላኑን የማጠፋ ፈጣሪሽ እኔ ነኝና ፤

ወስምየኒ እግዚአብሔር ፀባዖት ፣

ስሜም አሸናፊ እግዚአብሔር ይባላልና ፤

፲፮፡ ወእወዲ ቃልየ ውስተ አፉከ ፣

ዘሩባቤልን ኦሪትን እንድታስ ተምር አደርግሃለሁ ይለዋል ፤

ወእከድነከ ታሕተ ጽላሎተ እዴየ ፣

በጽላሎተ ረድኤቴ እሠውርሃ ለሁ ፤

እንተ ባቲ ሰፋሕክዎ ለሰማይ ወሣረ ርክዋ ለምድር ፣

ሰማይን ምድርን የፈጠርሁበት ብሎ ለሥልጣን ቀጠለ ፤ አንድም ወእወዲ ቃልየ ውስተ አፉከ ኢሳ ይያስን ኦሪትን እንድታስተምር አደርግሃለሁ ይለዋል ፤

ወእከድነከ ታሕተ ጽላሎተ እዴየ እንተ ባቲ ሰፋሕክዎ ለሰማይ ወሣረርክዋ ለምድር ፣

ሰማይን ባረጋሁበት ምድርን በዘረጋሁበት በሥልጣኔ በሚደ ረግ ረድኤቴ እሠውርሃለሁ ፤ አንድም ወእወዲ ቃልየ ውስተ አፉከ ጌታን ወንጌልን እንድታ ስተምር አደርግሃለሁ ይለዋል ወንጌል የሦስቱም ሕግ ናትና ፣ ቃልየ አለ ፣ በሥልጣኔ በፈጠር ሁት በሥጋ እሠውርሃለሁ ማለት ሥጋን አዋሕድሃለሁ ፤

ወእብላ ለጽዮን ሕዝብየ አንቲ ፣

ጽዮንን ወገኔ አንቺ ነሽ እላታ ለሁ ፤

፲፯፡ ተንሥኢ ተንሥኢ ኢየሩሳሌም ፣

ነገሥታቱን ካህናቱን እንዲህ ይላቸዋል ፣ ኢየሩሳሌም ተነሽ ተነሽ ፤

ወቁሚ እንተ ሰተይኪ እምእደ እግዚአ ብሔር ጽዋዐ መዓቱ ዘያወድቀኪ ፣

የሚያጠፋሽ ጽዋዐ መዓቱን ከእ ግዚአብሔር እጅ ተቀብለሽ የጠ ጣሽ ፅኚ ፤

ወሦጥኪዮ ፣

ጭልጥ አድርገሽ የጠጣሽው ማለት ፈጽመሽ የተቀበልሽው ፤

፲፰፡ ወኀጣእኪ ዘይናዝዘኪ እምኵሉ ደቂቅኪ ዘወለድኪ ፣

ከወለድሻቸው ከልጆችሽ የሚያ ረጋጋሽ ያጣሽ አንቺ ፅኚ ፤

ወአልቦ ዘይሜጥወኪ እዴሁ እምኵሉ ደቂቅኪ ዘአልሐቂ ፣

ካሳደግሻቸው ከልጆችሽ እጁን ሰጥቶ የሚያወጣሽ የለም ፤

፲፱፡ ወይእዜኒ እሉ አርባዕቱ ይጸን ሑኪ ፣

አሁንም እሊህ አራቱ መከራት ደጅ ይጠኑሻል ፤ አርባዕቱ ያለውን ይተረትራል ፤

ኀሣር ፣

ጕስቍልና ፤

ወድቀት ፣

መከራ ፤

ረኀብ ፣

ቀጠና ፤

ወመጥባሕት ፣

ጦር ይመጣብሻል አርባዕቱ ያላ ቸው እሊህ ናቸው ፤ አንድም

www.ethiopianorthodox.org

ወአኮ በወርቅ ዘእትቤዘወክሙ ።

ዛሬም ወርቅ ሰጥቼ ከባቢሎን ያወጣኋችሁ አይደለም፤ በቸርነቴ ነው እንጂ፤ አንድም በከንቱ ተማ የጥኩክሙ ምግባር ሳይኖራችሁ ከሲኦል ከገሃነም አወጣኋችሁ፣

ወአኮ በወርቅ ዘእትቤዘወክሙ ።

ወርቅ ተቀብዬ ከሲኦል ከገሃነም ያወጣኋችሁ አይደለም ፣ ሰው ሁኜ ሥጋ ለብሼ ነው እንጂ ፣

፬፡ ከመዝ ይቤ እግዚአብሔር እግዚእ፣

እግዚአብሔር እንዲህ አለ ፣

ግብፅአ ወረዱ ሕዝብየ ቀዲሙ፣

ወገኖቼ እስራኤል በአብርሃም ጊዜ አንድም በያዕቆብ ጊዜ ወደ ግብፅ ወረዱ ፣

ወነበሩ ህየ ፣

ከግብፅ ወጥተው በከነዓን ተቀመጡ ፤

ወእምዝ ወሰድክዎሙ ብሔረ ፋርስ በግብር ፣

ከግብፅ ወጥተው በኢየሩሳሌም ከኖሩ በኋላ በግድ አስማርኬ ወደ ፋርስ ወሰድኋቸው ፤ አንድም ግብፅአ ወረዱ ሕዝብየ ቀዲሙ ወገኖቼ እስራኤል ቀድሞ በኤር ምያስ ጊዜ ወደ ግብፅ ወረዱ ፤

ወነበሩ ህየ ፣

በግብፅ ኖሩ ፤

ወእምዝ ወሰድክዎሙ ብሔረ ፋርስ በግብር ፣

ወእምህየ ሲል ነው ፤ ከግብፅም በግድ አስማርኬ ወደፋርስ ወሰድኋቸው፣ (ታሪክ) ናቡከደነፆር ሁለቱንም ነገድ ማርኮ በዴብ ላታ ሰፍሮ ሳለ ናቡዛርዳንን ሂደህ ቤተ መቅደስን አቃጥለህ ንዋየ ቅድሳቱን ይዘህ ና፣ ኤርምያስን እመጣለሁ ያለ እንደሆነ ይዘኸው ና፣ በአገሬ እቀበራለሁ ያለ እን ደሆነ ትተኸው ና አለው፤ ለናቡ ከደነፆር የተገዛ የሕይወት መገኛ ይሆናል፣ ለናቡከደነፆር ያልተገዛ ይማረካል እያለ ያስተምር ነበ ርና ለእኔ የተናገረልኝ መስሎት ናቡዛርዳንም ሂዶ ቤተ መቅደ ስን አቃጥሎ ንዋየ ቅድሳቱን ይዞ ለከርሚ ወለሄሬሚ ይላል፣ ዕደው ነዳያን ማለት ነው፤ ወይን ለሚያርሙ ለሚኮተኩቱ ጎዶል ያንን ሹሞላቸው ሲሄድ ኤርም ያስን ትሄድ ትቀር አለው፣ እኔስ ከዚህ ከሀገሬ እቀበራለሁ አለው ትቶት ሄደ እስማኤል ወልደ ናታንዩ ዘእም ዘመደ መንግሥት ይለዋል፣ ጎዶልያንን ገድሎ ሕዝ ቡን ማርኮ ሲሄድ ዮሐናን ወልደ ቃርሔ መጥቶ እስማኤል ወልደ ናታንዩን ገደለው፣ ወደ ኢየሩሳ ሌም እንዳይመለሱ ንጉሥ የሾመ ውን ገድለን ብንገኝ ይጣላን የለም ብለው በቢሮት ዘቅርብት

ለግብፅ ይላታል በግብፅ አፋፍ ያለች አገር ናት፣ በዚያ ሰፍረው ሳለ ኤርምያስን ወደ ኢየሩሳሌም ተመለሱ ወደ ግብፅም ሂዱ ይለን እንደሆነ ቃለ እግዚአብሔር ጠይ ቅልን አሉት ፣ እስከ ዐሥር ቀን ድረስ ቢጠይቅ ዝም አለው፣ እግ ዚአብሔር በተጣላበት ወራት ፈጥኖ አይሰማምና ባሥረኛው ቀን ወደ ኢየሩሳሌም የተመለ ሳችሁ እንደሆነ ያ የፈራችሁት መከራ ያገኛችኋልና ወደ ግብፅ ሂዱ በላቸው አለው፣ ይህን ቢነ ግራቸው ኢተናገረከ እግዚአብ ሔር አላ ባሮክ ወልደ ኔርዩ ያስ ሕተከ፣ የኔርዩ ልጅ ባሮክ ያስ ትሐል እንጂ እግዚአብሔር አል ተናገረህም ብለው ወደ ግብፅ ሂዱ፣ እኔሳ ልሂድ ልቅር አለው አብረሃቸው ሂድ አለው ሂዶ ከፈርያን አደባባይ አራት ደንጊያ ተክሎ ናቡከደነፆር መጥቶ ከዚህ ዙፋኑን ይዘረጋል እያለ ያስተም ራቸው ጀመር ፣ ኋላ ናቡከደነ ፆር ግብፅ ወረደ ኤርምያስን ከዚያ አገኘው ቀድሞ ና ብለው ከሀገሬ እቀበራለሁ አለ፣ ይህን ቀጣፊ ነቢይ ከዚህ ደግሞ ምን አመጣው ብሎ ነድዕዎ እንዘ ያቴ ክልዎ ይላል እያዳፉ ባቢሎን ይዘውት ወርደዋልና፣ ግብፅአ ወረዱ ሕዝብየ ቀዲሙ ውነደሩ ህየ ወእምዝ ወሰድክዎሙ ብሔረ ፋርስ ያሰኘው ይህ ነው ፣

፭፡ ይእዜኒ ምንት አቀመክሙ ዝየ፣

አሁንስ ከዚህ ምን አቁማችኋል፤

ከመዝ ይቤ እግዚአብሔር ፣

እግዚአብሔር እንዲህ አለ ፤

እስመ ነሥእዎሙ ለሕዝብየ በከንቱ፣

ባለ ጸጎች እስራኤል ድሆች እስ ራኤልን በከንቱ ሳይበድሏቸው ገንዘባቸውን ቀምተዋቸዋልና ፤

ወአንከርክሙ ወከላህክሙ በእንተ ዝንቱ ፣

እንዲህ ስላደረጋችሁ ነቢያት ካህናትን እያደነቃችሁ ጮኻ ችሁ ፤

፮፡ ከመዝ ይቤ እግዚአብሔር በእን ቲአክሙ ይጸርፉ አሕዛብ ላዕለ ስምየ፣

በናንተ ምክንያት አሕዛብ ስሜን ይነቅፋሉ ሕዝበ እግዚአብሔር ነን ይላሉ ይበድላሉ መበደላቸ ውን አያውቅ ይሆን እንጂ ይወድ ይሆን እንጂ እያሉ፤ አንድም እስመ ነሥእዎሙ ለሕዝብየ በከ ንቱ ፣ አሕዛብ እስራኤልን ሳይ በድሏቸው ገንዘባቸውን በከንቱ ቀምተዋቸዋልና ፤

ወአንከርክሙ ወከላህክሙ በእንተ ዝንቱ ፣

ነቢያት ካህናት ስለዚህ ነገር አደ ነቃችሁ ፤

ከመዝ ይቤ እግዚአብሔር በእንቲአ ክሙ ይጸርፉ አሕዛብ ላዕለ ስምየ ፣

በናንተ ምክንያት አሕዛብ ስሜን ይነቅፋሉ አለ እግዚአብሔር፣

www.ethiopianorthodox.org

ሕዝበ እግዚአብሔር ነን ይላሉ ይበድላሉ፣ መበደላቸውን አያ
ውቅ ይሆን እንጂ ይወድ ይሆን እንጂ ይሉታልና፤ አንድም እስመ
ነሥእዎሙ፣ አሕዛብ እስራኤልን ማርከው ወስደዋቸዋልና ፤

ወአንከርክሙ ፣

እስራኤል አደነቃችሁ ፣

ከመዝ ይቤ እግዚአብሔር በእንቲአ
ክሙ ይጸርፉ አሕዛብ ላዕለ ስምየ፣

በእናንተ ምክንያት አሕዛብ
ስሜን ይነቅፋሉ አለ፣ አሕዛብ
እስራኤል ሲማረኩ መከራ ሲቀ
በሉ አይተው እስራኤል የእግ
ዚአብሔር ወዳጆች ከሆኑ ለምን
መከራ ይቀበላሉ ይለዋል፣ ኃጢ
አት ቢሠሩ ጣዖት ቢያመልኩ
ነዋ ይለዋል፣ ኃጢአት እንዳይ
ሠሩ ጣዖት እንዳያመልኩ አያደ
ርጋቸውም ይለዋል ፣ አያውቅ
ይሆን እንጂ አይችል ይሆን
እንጂ ይወድ ይሆን እንጂ ይሉ
ታልና ፤

፭፤ በእንተ ዝንቱ የአምሩ ሕዝብየ
ስምየ ፣

ስለዚህ ነገር እንዲህ የሚሉ
አሕዛብን አጥፍቼላቸው ወገኖቼ
ስሜን ያውቃሉ ፣

ይእተ አሚረ በከመ አነ ዘነበብኩ
ወሀሎኩ ፣

መከራውን የተናገርሁ በመከ
ራው እኔ እንዳለሁ ዕወቁ ፣

፮፤ ከመ ሠናይ በውስተ አድባር ዘይ
ዜኑ ዜና ሰላም ወከመ ዘይዜኑ ዜና
ሠናየ ፣

ዘይዜኑ ዜና ሰላምና ወከመ ዘይ
ዜኑ ዜና ሠናየ አንድ ወገን በተ
ራራ ላይ ሁኖ በጎ ወሬ የሚያ
ወራ ደስ እንዲያሰኝ ደስ እንዲ
ላችሁ አደርጋለሁ፤ አንድም በተ
ራራ ላይ ሁኖ በጎ ወሬ የሚያወራ
ሰው ያማረ የተወደደ እንደሆነ
እኔም የተናገርሁት ያማረ የተወ
ደደ ነው ፤

እስመ ነገረ እገብራ ለመድኃኒትየ፣

መድኃኒት ሚጠትን ቁምነገር
አደርጋታለሁና ፤

ወእብላ ለጽዮን ይነግሥ ለኪ እግዚአ
ብሔር ለዓለም ፣

ጽዮንንም እግዚአብሔር ለዘለ
ዓለም ነግሦልሽ ይኖራል እላታ
ለሁ ፤

፱፤ እስመ ተለዐለ ቃሉሙ ለእለ የዐ
ቅቡኪ ፣

የሚጠብቁሽ የነቢያት የካህናት
ልመናቸው ተሰምቷልና ነግሦ
ልሽ ይኖራል እላታለሁ፤ ወኅቡረ
ይትፌሥሑ ብሎ ማንሻ ፤ አን
ድም የሚጠብቁሽ የነቢያት የካ
ህናት ቃላቸው ከፍ ከፍ ብሏልና፤

ወኅቡረ ይትፌሥሑ በቃሉሙ ፣

በልመናቸው አንድ ሁነው ደስ
ይላቸዋል፤ አንድም በቃላቸው
አንድነት ደስ ይላቸዋል ፤

እስመ ዐይነ በዐይን ይትረአዩ አመ
ተሠሀላ እግዚአብሔር ለጽዮን ፣

እግዚአብሔር በሚጠት ጽዮንን
ይቅር ባላት ጊዜ ዐይን ለዐይን
ይተያያሉና ወኅቡረ ይትፌሥሑ
በቃሉሙ ላለው ፣ ወይፈለፍል
ኀሜት ማንሻ፤ አንድም እግዚአ
ብሔር ጽዮንን ይቅር ባላት ጊዜ
ዐይን ለዐይን የሚተያዩ ስለሆነ
አንድነት ደስ ይላቸዋልና ፤

፲፤ ወይፈለፍል ኀሜት ኅቡረ በድዋ
ለኢየሩሳሌም ፣

በኢየሩሳሌም አውራጃ ተድላ
ደስታ ይደረጋል ፤

እስመ ተሠሃላ ወአድነና እግዚአብ
ሔር ፣

እግዚአብሔር ኢየሩሳሌምን
ይቅር ስላላት ስላዳናት ይፈለ
ፍል ኀሜት፤ አንድም ይቅር ብሏ
ታል አድኗታልና ፤

፲፩፤ ወይከሥት እግዚአብሔር መዝ
ራዕቶ ቅዱሰ በቅድመ ኵሉ አሕዛብ፤

እግዚአብሔር ዕኑዕ ክቡር የሚ
ሆን ሥልጣኑን በአሕዛብ ፊት
ይገልጣል ፤

ወይሬእዩ ኵሉ አሕዛብ መድኃኒተ
እግዚአብሔር ፣

አሕዛብ ሁሉ መድኃኒተ እግዚ
አብሔር ሚጠትን ያያሉ ፤ አን
ድም ያያሉና ክቡር ሥልጣኑን
ይገልጥላቸዋል ፤

፲፪፤ ርኁቀ ረኀቁ ፣

ይህ ሊደረግላችሁ ፈጽማችሁ
ራቁ ፤

ወፃኡ እምህየ ፣

ከባቢሎን ውጡ፤ አንድም እስመ
ተሠሃላ ወአድነናን ወደላይ ጨር
ሰህ ፤

ወይከሥት እግዚአብሔር መዝራዕቶ
ቅዱሰ በቅድመ ኵሉ አሕዛብ ፣

እግዚአብሔር ልጁን በሥጋ ይገ
ልጠዋል ፤

ወይሬእዩ ኵሉ አሕዛብ መድኃኒተ
እግዚአብሔር ፣

ምዕመናነ አሕዛብ ሥጋዌውን
ያያሉ ፤

ርኁቀ ረኀቁ ወፃኡ እምህየ ፤

ፈጽማችሁ ከሲኦል ከገሃነም ራቁ፤

ወኢትግሥሡ ርኩሰ ፣

ከባቢሎን ገንዘብ አትንኩ፤ አን
ድም የባቢሎንን ጣዖት አትንኩ
ማለት አታምልኩ ፤

ወፃኡ እምነ ማዕከላ ፣

ከመካከሏ ውጡ ፤

ወተፈለጡ ንዋያተ እግዚአብሔር ፣

የእግዚአብሔር ገንዘቦች እስራ
ኤል ከባቢሎን ሰዎች ተለዩ ፤

፲፫፤ እስመ አኮ በሁከት ዘትወፅኡ፣

በሽብር የምትወጡ አይደለምና፤

www.ethiopianorthodox.org

ወአኮ በጥያ ዘተሐውሩ ፣

ሸሽታችሁ የምትሔዱ አይደለ ምና ፤

ዳዕሙ የሐውር እግዚአብሔር ፍጽመ ቅድሜክሙ ፣

እግዚአብሔር ፊታውራሪ ሁኖ በፊት በፊታችሁ ይሄዳል እንጂ፣

ወያስተጋብዐክሙ እግዚአብሔር አም ላከ እስራኤል ፣

የእስራኤል ፈጣሪ እግዚአብሔር ይሰበስባችኋል እንጂ ሸሽታችሁ የምትወጡ አይደለምና፣ ወኢት ግሥሡ ላለው ከዚህ አኮ በጥያ ዘተሐውሩ አለ፣ ካለፈው ፃኡ እም ባቢሎን እንዘ ትጐይዩ አለ፣ አይ ጣላም ቢሉ አይጣላም ፣ ከዚያ እንዘ ትጐይዩ ማለቱ ፈጥናችሁ ከግብራቸው ተለይታችሁ ውጡ ሲል ነው ፣ ከዚህ ግን አኮ በጥያ ዘተሐውሩ ማለቱ እንደ ወጓችሁ ወግታችሁ እንደ ዘረፏችሁ ዘር ፋችሁ ውጡ ሲል ነው ፤

ጉባዔ

፲፬፡ ናሁ ይሌቡ ቊልዔየ ፣

እነሆ ወዳጄ ዘሩባቤል የጠላት መጥፊያ መጥፊያውን ያውቃል፤ አንድም አሪትን ዐውቆ ያስተምራል ፤

ወይትሌዐል ፣

ከፋርስ ከባቢሎን ወጥቶ በመን ግሥት ከፍ ከፍ ይላል ፤

ወይከብር ፣

በመንግሥት ይከብራል ፤

ወይትፌሣሕ ፈድፋደ ፣

ፈጽሞ ደስ ይለዋል፤ አንድም በአ ሕዛብ ጥፋት በእስራኤል ሚጠት ደስ ይለዋል ፤

፲፭፤ ወያነክሩ በእንቲአሁ ብዙኃን ከመ ዘነኪር ራእዩ እምሰብእ ፣

የዘሩባቤል መልክዐ ፍትሑ ከሰው ሁሉ ልዩ እንደሆነ አይተው ብዙ ሰዎች የእሱን ነገር ያደንቃሉ፤

ወክቡር እምዕጓለ እመሕያው ፣

ከሰው ይልቅ ከሰው ተለይቶ ውድ እንደሆነ አይተው ያደንቃሉ፣ እህል ልብስ ከብሮ ዋለ እንዲሉ ተወዶ ዋለ ሲሉ ፤

፲፮፤ ወኪያሁ ያነክሩ አሕዛብ ብዙኃን፣

ብዙ አሕዛብ እሱን ያደንቃሉ፤

ወይፈትሑ ወይከሥቱ አፉሆሙ ነገ ሥት ፣

ቂሮስ ዳርዮስ ያመሰግኑታል፤

እስመ እለ ኢዜነውዎሙ በእንቲአሁ ያእምርዎ ሀለዎሙ ፣

ነቢያት ካህናት የእሱን ነገር ነግ ረዋቸው ያላወቁ ትሩፋን ነግሦ ያዩት ዘንድ አላቸውና፤

ወእለሂ ኢሰምዕዎ ሀለዎሙ ይለብ ውዎ ፣

ነቢያት ካህናት ነግረዋቸው ያል ሰሙት የእሱ [illegible]

ዘንድ አላቸውና፤ አንድም ናሁ ይሌቡ ቊልዔየ ብለህ መልስ፣ ወልድየ ብሎ ሊቁ ተርጕሞታል ልጄ ክርስቶስ መጥፊያ መጥፊያውን ያውቃል፣ አውቆ ያስተምራል፣ በሕማሙ ሕማመ ሥጋ በሞቱ ሞተ ነፍስ እንዲጠፋ፤ አንድም በመለኮቱ የሚያውቀውን በሰውነቱ ያውቃል ፤

ወይትሌዐል ፣

በሰባት ክንድ ከስንዝር መስቀል ከፍ ከፍ ብሎ ይሰቀላል ፤

ወይከብር ፣

በባሕርይ ክብር ይከብራል ፤

ወይትፌሣሕ ፈድፋደ ፣

በአጋንንት ጥፋት በምዕመናን ድኅነት ደስ ይለዋል፤ (ጥቅስ) በእንተ ፍሥሓሁ ዘጽኑሕ ሎቱ፤ (ዕብ. ፲፪፥፪)

፲፯፤ ወያነክሩ በእንቲአሁ ብዙኃን ከመ ዘነኪር ራእዩ እምሰብእ ፣

የጌታ መልኩ ከሰው ሁሉ ልዩ እንደሆነ አይተው ብዙ ሰዎች የሱን ነገር ያደንቃሉ፤ (ጥቅስ) ይሜኒ ላህዩ እምውሉደ ዕጓለ እመሕያው እንዲል ፤ መዝ. ፵፬፥፪፣ ካምስቱ ገበያ የአንዱን ገበያ ያህል መልኩን ለማየት ይከተሉት ነበርና፤ አንድም መልክዐ ትምህርቱ መልክዐ ተአምራቱ ከነቢያት ከሐዋርያት ልዩ እንደሆነ አይተው የእሱን ነገር ያደንቃሉ፣ ነቢያት ሲያስተምሩ ከመዝ ይቤ እግዚአብሔር ከመዝ ይቤ እግዚአብሔር እያሉ ነው፣ ተአምራትም ሲያደርጉ ከመዝ ይቤ እግዚአብሔር ፈወስክዎ ለዝንቱ ማይ እንዲል፣ (፪ኛ፡ ነገ. ፪÷ ፳፩)፣ ሐዋርያትም ሲያስተምሩ ወረደ ተወለደ እያሉ ነው፣ ተአምራትም ሲያደርጉ ፃእ መን ፈስ ርኩስ በስሙ ለኢየሱስ ክር ስቶስ እያሉ ነው ፤ ግብ. ሐዋ. ምዕ. ፲፮ ቊ. ፲፰፣ እሱ ግን ሲያስተምር አንሰ እብለክሙ አንሰ እብለክሙ እያለ ነው ፣ ማቴ. ምዕ. ፭ ቊ. ፳፪፤ ተአምራትም ሲያደርግ ተነድገ ለክ ኃጢአ ትከ እንዲል፤ (ማር. ምዕ. ፪ ቊ. ፭) ተነድገ ለኪ ኃጢአትኪ እንዲል ፤ (ሉቃ. ምዕ. ፯ ቊ. ፵፰)፤ ፈቀድኩ ንጻሕ እያለ ነው፣ ማቴ. ምዕ. ፰ ቊ. ፬ ፤

ወክቡር እምዕጓለ እመሕያው ፣

ከሰው ይልቅ ውድ እንደሆነ አይተው ያደንቃሉ ፤

ወኪያሁ ያነክሩ አሕዛብ ብዙኃን ፣

ምዕመናን አሕዛብ እሱን ያደንቃሉ ፤

ወይፈትሑ ወይከሥቱ አፉሆሙ ነገ ሥት ፣

ሄሮድስ ጲላጦስ አፋቸውን ከፍተው ይፈርዱበታል ፤

www.ethiopianorthodox.org

እስመ እለ ኢዜነውዎሙ በእንቲአሁ ያእምርዎ ሀለዎሙ ፤

ነቢያት ካህናት የእሱን ነገር ነግረዋቸው ያላወቁ አሕዛብ ፣ ሐዋርያት ነግረዋቸው ያውቁ ዘንድ አላቸውና፤ ምንም ቢነግሯቸው ይፈትሑ፤ አንድም ወይ ፈትሑ ወይከሥቱ አፉሆሙ ነገሥት ፤ እለ ዘይኑን እለ አርቃድዮስ እለ አኖሬዎስ እለ ቈስጠንጢኖስ ያመሰግኑታል ፤

እስመ እለ ኢዜነውዎሙ በእንቲአሁ ያእምርዎ ሀለዎሙ ፤

ነቢያት ካህናት የእሱን ነገር ነግረዋቸው ያላወቁ፣ አሕዛብ ሐዋርያት ነግረዋቸው ያውቁ ዘንድ አላቸውና ፤

ወእለሂ ኢሰምዕዎ ሀለዎሙ ይለብውዎ፤

ነቢያት ካህናት የእሱን ነገር ነግረዋቸው ያልሰሙ አሕዛብ፣ ሐዋርያት ነግረዋቸው ልብ ያደርጉ ዘንድ አላቸውና ::

ምዕራፍ ፶፫

፩፡ እግዚኦ መኑ የአምነነ ቃለነ ወነገረነ ፣

ቃለነ ነገረነ አንድ ወገን ነው፤ አቤቱ አስተምሩ ትለናለህ እንጂ ዐባር ቸነፈር ይመጣባችኋል ዔዋዌ ይደረግባችኋል ብለን ብናስተምር ነገራችንን ማን ያምነናል ፤

ወለመኑ ተከሥተ መዝራዕቱ ለእግዚአብሔር ፣

የእግዚአብሔር ሥልጣን ለማን ተገለጠ ፤

፪፡ ወነገርነኒ ከመ ሕፃን በቅድሜሁ፣

በቅድሜሁ ለነገሮሙ ነው፤ ነገራችን በነገራቸው ፊት በቅድሜሆሙ ቢል በእሳቸው ፊት ሕፃን እንዲናቅ የተናቀ ሁኗል፤ ትች ብናስተምርስ ማን ይሰማናል ፤ አንድም እግዚኦ መኑ የአምነነ ቃለነ ፣ አቤቱ አስተምሩ ትለናለህ እንጂ ይወርዳል ይወለዳል ብለን ብናስተምር ነገራችንን ማን ይሰማናል ፤

ወለመኑ ተከሥተ መዝራዕቱ ለእግዚአብሔር ፣

ሚጠት ለማን ተገለጠ ፤

ወነገርነኒ ከመ ሕፃን በቅድሜሁ ፣

ነገራችን በነገራቸው ፊት በቅድሜሆሙ ቢል በሳቸው ፊት ሕፃን እንዲናቅ የተናቀ ሁኗል፤ ትች አስተምሩ ትለናለህ እንጂ ብናስተምርስ ማን ይሰማናል ፤

ወከመ ሥርው ዘውስተ ምድር ዕምዕት ፣

በተጠማች ምድር ያለ ሥር እንዲናቅ ነገራችን የተናቀ ሁኗል ትች፣ አስተምሩ ትለናለህ እንጂ ይወርዳል ይወለዳል ብለን ብናስ

ተምር ማን ይሰማናል፤ አንድም እግዚኦ መኑ የአምነነ ቃለነ ወነገረነ ፣ አቤቱ ሐዋርያት ወረደ ተወለደ ብለን ብናስተምር ነገራችንን ማን ይሰማናል ይላሉ ፤

ወለመኑ ተከሥተ መዝራዕተ እግዚአብሔር ፣

ልጁ ክርስቶስ ሰው ሁኖ ሥጋ ለብሶ ለማን ተገለጠ፣ መገለጥስ ለሁሉ ነው ፤ ስላላመኑበት እንዲህ አለ ፣

ወነገርነኒ ከመ ሕፃን በቅድሜሁ ፣

ነገራችን በነገራቸው ፊት በቅድሜሆሙ ቢል በሳቸው ፊት ሕፃን እንዲናቅ የተናቀ ሁኗል፤ አስተምሩ ትለናለህ እንጂ ብናስተምርስ ማን ይሰማናል ፤

ወከመ ሥርው ዘውስተ ምድር ዕምዕት ፣

በተጠማች ምድር ያለ ሥር እንዲናቅ ነገራችን የተናቀ ሁኗል፣ ትች፤ አስተምሩ ትለናለህ እንጂ ይወርዳል ይወለዳል ብለን ብናስተምር ማን ይሰማናል፤ አንድም ሕፃን እንዲናቅ በተጠማች ምድር ያለ ሥርም እንዲናቅ ነገራችን በእነሱ ፊት የተናቀ የሆነ ጌታ ቢያስተምራቸው ያልሰሙ እኛ ብናስተምራቸው ይሰሙናልን፤ አንድም አይሰሙንም እንጂ ቢሰሙንስ የምናስተምረው ከመ ሕፃን ዘውስተ ምድር ዕምዕት ከዘር ከሩካቤ ከተጠማች ከድንግል ማርያም እንደ መወለዱ ነው ፤

ወከመ ሥርው በቅድሜሁ ፣

ከአብም ቅድመ ዓለም እንበለ እም እንደ መወለዱ ነው ፤

አልቦ ራእይ ፣

መልክ የለውም ማለት አይመካበትም ፤ አንድም በአይሁድ ዘንድ መልክ የለውም ፤

ወኢትርሢት ፣

አፍአዊ ጌጥ የለውም ፤

ወርኢናሁ ወአልቦ ራእይ ፣

አየነው በአይሁድ ዘንድ መልክ የለውም፤ አንድም መልከ መልካም ነው ይባላል፤ አሁን መልኩ ከማን ያምራል ይሉታልና፤ አንድም ተኵሎ ተቀብቶ የሚያወጡት መልክ የለውም ፤

ወአልቦ ላህይ ፣

በአይሁድ ዘንድ መልክ ደምግባት የለውም ፤

www.ethiopianorthodox.org

፫፡ ወራእዩኒ ምኑን ወትሑት እም ኵሉ ሰብእ ፤

መልኩም በአይሁድ ዘንድ ከሰው ሁሉ የተናቀ የተዋረደ ነው ፤

ብእሲ ቅሡፍ ውእቱ ወሕሙም ፤

በመከራ የተገረፈ የታመመ ነው አንድም በዕለተ ዐርብ የተገረፈ ነው ፤

እስመ ሜጠ ገጸ ወአስተሐቀርዎ ፤

ምራቅ ርኩሳንን ለመቀበል ፊቱን ወደ እነሱ መልሶ ቁሟልና ናቁት አቃለሉት ፤

ወኢሰብሕዎ ፤

አላከበሩትም ፤

፬፡ ውእቱሰ ነሥአ ደዌነ ወፃረ ሕማመነ ፤

እሱ ግን ደዌያችንን ሕማማችንን ገንዘብ አደረገ፤ ነሥአ ማለቱ ለካሳ ነውና፤ አንድም ለኛ የሚገባውን መከራ ተቀበለ፣ (ጥቅስ) እስመ እምደለዎ ለአዳም ይመ·ት ስቁለ ዘበ·ነሣር እንዲል (መቅ. ወን)

በእንቲአነ ሐመ ፤

በእኛ ምክንያት መከራ ተቀበለ፤

ወንሕነ ርኢናሁ ሕሙመ ወቅሡፈ በሕማም ፤

እኛም በዕለተ ዐርብ የታመመ የተገረፈ ሁኖ አየነው ፤

፭፡ ወውእቱሰ ቈሰለ በእንተ ኃጢአትነ፣

እሱ ግን በኛ ስለኛ ኃጢአት ተቸነከረ ፤

ወሐመ በእንተ ጊጋይነ ፤

ስለ ኃጢአታችን መከራ ተቀበለ፤

ትእምርተ ሰላምነ ፤

የፍቅራችን ምልክት እሱ ነው (ጥቅስ) ወውእቱ ትእምርተ ሰላም ክሙ· ዘረሰ ዮሙ· አሐደ ለ፪ሆሙ· እንዲል (ኤፌ. ፪ ÷ ፲፭)

አንድም ትምህርተ ሰላምነ ይላል የወንጌላችን መምህር እሱ ነው (ጥቅስ) ተስዒነክሙ· ኃይለ ወን ጌል ዘበሰላም እንዲል፤ (ኤፌ. ፮ ÷ ፲፭) ፤

ወበቍሰለ ዚአሁ ሐዮነ ቍሰለነ ፤

በሱ መገረፍ በሱ መሰቀል በሱ መቸንከር ከቍሰለ ነፍሳችን ዳንን፤ አንድም ቍሰለ ነፍሳችንን አራቀልን፣ የሱ ቍሰል በቀኖት በጦር የኛ ቍሰል በኃጢአት በፍዳ ነው ፤

፮፡ ኵልነ ከመ አባግዕ ተገዲፈነ ፤

ከዚህ አስቀድሞ አምስት ሺህ ካምስት መቶ ዘመን ቃባ እንደ ያዘው በግ ሁላችን በመከራ ተጥለን ነበር ፤

ብእሲኒ ዘዘዚአሁ ሐረ በፍኖቱ ፤

ሰው ሁሉ በሠራው ሥራ ተይዞ ይኖር ነበር፣ አንድም አንዱም አንዱም በኃጢአቱ ፀንቶ ኖረ፤

ወስሕተ ፤

ስቶ በመራው ፤

ወመጠዎ እግዚአብሔር በእንተ ኃጢአትነ ፤

ከዚህ የተነሣ እግዚአብሔር አብ እግዚአብሔር ወልድን ለሕማም ለሞት አሳልፎ ሰጠው ፤

፯፡ ወውእቱሰ ኢከሠተ አፉሁ በሕማሙ ፤

እሱ ግን በመከራው ጊዜ ለምን ትገርፉኛላችሁ፣ ለምን ትሰቅሉኛላችሁ ብሎ አልተናገረም ፤

ወመጽአ ይጠባሕ ከመ በግዕ ፤

እንደ በግ ይሠዋ ዘንድ መጣ፣ አንድም እንደ በግ ሊሠዋ መጥቷልና ምንም ቢመጣ አልተናገረም ፤

ወከመ በግዕ ዘኢይነብብ በቅድመ ዘይቀርፆ ፤

በግ በሚሸልቱት ሰዎች ፊት ከቀን ሐሩር ከሊሊት ቍር የሚያድነኝን ጠጕሬን ለምን ትሸል ቱኛላችሁ እንዳይል ፤ አንድም እንዳለ ይሆናል፣ በግ በሚሸል ተው ሰው ፊት ለሌሊት ቍር ለመዓልት ሐሩር እንዳይሆነኝ ለምን ትሸልተኛለህ ብሎ እንዳ ይናገር፤

ከማሁ ኢከሠተ አፉሁ በሕማሙ ፤

እንደዚህም ሁሉ እሱም በሕማሙ· ጊዜ ለምን ትገፉኛላችሁ፣ ለምን ትገርፉኛላችሁ ለምን ትሰቅሉኛላችሁ ብሎ አልተናገረም ፤

፰፡ እስመ ይነሥእዋ ለነፍሱ ፤

ሰውነቱን በሞት ይወስዷታልና፤

ወኢየአምርዋ ለልደቱ ፤

ከአባት ያለ እናት፣ ከእናት ያለ አባት መወለዱን ባያውቁ ፤

ወይነሥእዋ ለሕይወቱ በኃጢአተ ሕዝብየ በጽሐ ለሞት ፤

ሰውነቱን ወደሞት ይወስዷታልና በወገኖቼ ኃጢአት ለሞት ደረሰ፤ አንድም እስመ ይነሥእዋ ለነፍሱ እምድረ ሕያዋን ይላል፤ ሰውነቱን ከአብርሃም ከይስሐቅ ከያዕቆብ አገር በሞት ይወስዷታልና በወገኖቼ ኃጢአት ለሞት ደረሰ፤ አንድም እስመ ይነሥእዎ እም·ነበ ዐፀውዎ ወእምኮ·ናን መ· ይነግር ልደቶ ይላል፣ ከሊቶስጥራ ወደ ቀራንዮ፣ ከቀራንዮ ወደ ሊቶስጥራ፣ ወእምኮ·ናን ከሐና ወደቀያፋ፣ ከቀያፋ ወደ ሐና ፣ ከወሰዱት በኋላ ከአባት ያለ እናት ፣ ከእናት ያለ አባት መወለዱን ማን ያውቃል ብለው በሞት ይወስዱታልና በወገኖቼ ኃጢአት ለሞት ደረሰ፤ አንድም እስመ እምከመ ተዐተተ መ· ይነግር ልደቶ ይላል፤ እሱ ከሞተ ወዲያ ከአባት ያለ እናት ፣ ከእናት ያለ አባት መወለዱን ማን

www.ethiopianorthodox.org

ይናገራል ብለው ሰውነቱን በሞት ይወስዷታልና በወገኖቼ ኃጢአት ለሞት ደረሰ ፤ እንድም እስመ ተዐተተ እምድር ሕይወቱ ፣ ሕይወቱ መንፈስ ቅዱስ ከሰው ልቡና ርቋልና ከአባት ያለ እናት ፣ ከእናት ያለ አባት መወለዱን ማን ይናገራል ብሎ ነቢዩ ያደንቃል ፣ እንድም እስመ ይነ ሥእዎ እምነበ ዐፀውዎ ወእም ኮናን ፣ ዐሥረው ካጋዙበት ከሃሪሮድስ ከጲላጦስ አደባባይም ወደ ሞት ይወስዱታልና ፤

መኑ ይነግር ልደቶ ፣

ቅድመ ዓለም ከአብ ፣ ድኅረ ዓለም ከእመቤታችን መወለዱን ማን ይናገራል ቢነግሩትስ ማን ይሰማል ፤

፱፤ ወእሁብ አዅያነ ሀየንተ ሞቱ ፣

ሊገድሉት አራቱ ቤት ሮማው ያንን እሰጣለሁ ፤

ወአብዕልተ ሀየንተ መቅበርቱ ፣

ሊቀብሩት አይሁድን እሰጣለሁ ለመቀበሩ ምክንያት ስለሆኑ ፤

እስመ ኢገብረ ኃጢአተ ፣

እመኒ ሲል ነው ፤ ምንም ኃጢአት ባይሠራ ፤

ወኢተረክበ ሐሰት ውስተ አፉሁ ፣

ምንም በአንደበቱ ሐሰት ባይገኝ ያንን ፣ ሊቀብሩት አይሁድን እሰጣለሁ፤ አንድም ወእሁብ እኩያን ሀየንተ ሞቱ፣ ሕዝቡ እንዲገድሉት አደርጋለሁ ፣ ገድለውት አይደለም ለሞት ስለ አበቁት ነው እንጂ ፤

ወአብዕልተ ሀየንተ መቅበርቱ ፣

ሊቀብሩት በብዕለ ኃጢአት የከበሩ አሕዛብን እሰጣለሁ፤ ቀብረውት ኢይደለም ለመቃብር ስለ አበቁት ነው እንጂ፤ አንድም ወእሁብ እኩያን ሀየንተ ሞቱ ሊገድሉት ሕዝቡን አሕዛቡን እሰጣለሁ ፤

ወአብዕልተ ሀየንተ መቅበርቱ ፣

ሊቀብሩት በብዕለ አሪት የከበሩ ዮሴፍ ኒቆዲሞስን እሰጣለሁ፤ አንድም በድርብ በፍታ ገንዘው ቀብረውታልና አብዕልት አላቸው እስመ ኢገብረ ኃጢአተ እመኒ ሲል ነው ምንም ኃጢአት ባይሠራ ፤

ወኢተረክበ ሐሰት ውስተ አፉሁ ፣

ምንም በአንደበቱ ሐሰት ባይገኝ፣ አንድም ወእሁብ እኩያን ሀየንተ ሞቱ፣ እሱ ስለሞተ ዝሕቡን አጠፋለሁ ፤

ወአብዕልተ ሀየንተ መቅበርቱ ፣

እሱ ስለ ተቀበረ አሕዛብን አጠፋለሁ፤ አንድም እሱ ስለ ሞተ ሕዝቡን አሕዛቡን አጠፋለሁ ፤

ወአብዕልተ ሀየንተ መቅበርቱ ፣

አጋንንትን አጠፋለሁ ኃጢአት አልሠራምና ስላልሠራ እሁብ ላለው፤ አንድም ወእሁብ እኩያን ሀየንተ ሞቱ፣ እሱ ስለሞተ ፈንታ ሕዝቡን አድናለሁ ፤

ወአብዕልተ ሀየንተ መቅበርቱ ፣

እሱ ስለ ተቀበረ ፈንታ አሕዛብን አድናለሁ ፤ አንድም ወእሁብ እሱ ስለሞተ ፈንታ ኃጥአንን አድናለሁ ፤

ወአብዕልተ ፣

እሱ ስለ ተቀበረ ፈንታ ጻድቃንን አድናለሁ፣ ኃጢአት አልሠራምና ስላልሠራ ባንደበቱም ሐሰት አልተገኘምና ንጹሐ ባሕርይ ስለሆነ ወእሁብ እኩያን ላለው ፤

፲፤ ወፈቀደ እግዚአብሔር ያንጽሖ አምነ መቅሠፍቱ ፣

ጲላጦስ ከገረፈው ግርፋት የተነሣ አዳምን ከኃጢአቱ ነፃ ያወጣው ዘንድ ወደደ፤ አንድም ወፈቀደ እግዚአብሔር ይሕምም ወይኅሥር ይላል ፣ እግዚአብሔር አብ ፣ እግዚአብሔር ወልድ መከራን ይቀበል ዘንድ ወደደ፤ አንድም እግዚአብሔር ወልድ መከራ ይቀበል ዘንድ ወደደ፤

ወእመኒ ወሀብክሙ በእንተ ኃጢአት ክሙ ትሬኢ ነፍስክሙ ዘርዐ ዘነዋኅ የሐዩ ፣

ኃጢአት ስለሠራችሁ ምጽዋት[illegible] ዘመን የሚኖር ማለት አርባ ዘጠኝ ዘመን የሚገዛ ዘሩባቤልን ታያላችሁ፤ ዘመነ መንግሥቱ አርባ ዘጠኝ ነውና፤ አንድም በኃጢአታችሁ ምክንያት ሰውነታችሁን ለመከራ አሳልፋችሁ ብትሰጡ ማለት ለሰማዕትነት ብትሰጡ ሰውነታችሁ ለዘለዓለም ሕያው ሁኖ፤ አንድም በሕያውነት የሚኖር ክርስቶስን ታያለች ፤

፲፩፤ ወፈቀደ እግዚአብሔር ያዕትት ሕማመ እምነፍሱ ፣

እግዚአብሔር ከአዳም ሰውነት መከራውን ሊያርቅ ወደደ፤ አንድም እግዚአብሔር አብ ከእግዚአብሔር ወልድ ሰውነት መከራን ያርቅ ዘንድ ወደደ፤ እግዚአብሔር ወልድ ከሰውነቱ መከራን ያርቅ ዘንድ ወደደ ፤

ወያርእዮ ብርሃነ ፣

ለዘሩባቤል ብርሃነ ረድኤቱን ያሳየዋል፤ አንድም ለአዳም ተድላውን ደስታውን ያሳየዋል፣ አንድም ብርሃነ ትንሣኤውን ይገልጥለታል ፤

ወይፈልጥ በጥበቡ ፣

በባሕርይ ጥበቡ ከክፉ በጎውን፣ ከበጎ ክፉውን ይለያል፤ አንድም በባሕርይ ጥበቡ ጻድቃንን ከኃጥአን ይለያል ፤

ወያጸድቆ ለጻድቅ ፣

ደጉን ሰው ያከብረዋል ፤

www.ethiopianorthodox.org

ለዘይትቀነይ ለጽድቅ ወለሠናይ ፣

ለና ለ አንድ ወገን እውነት ነገር በኅ ነገር የሚያደርገውን ደጉን ሰው ያከብረዋል፤ አንድም በም ግባር በሃይማኖት ፀንቶ የሚገዛ ለትን ያከብረዋል ፤

ወለብዙኃን ኃጢአቶሙ ውእቱ ይደ መስለ ፣

የብዙዎችን ሰዎች ኃጢአት ያስ ተሠርያል ፤

፲፪፤ በእንተዝ ውእቱ ይወርሶሙ ለእ ስራኤል ፣

ኃጢአት የሚያስተሠርይ ስለ ሆነ እስራኤልን ገንዘብ ያደር ጋቸዋል ፤

ወይመጎርኮሙ ለዕኑዓን ፣

አሕዛብንም ገንዘብ ያደርጋቸ ዋል፤ አንድም ይወርሶሙ ጻድ ቃንን፣ ወይመጎርኮሙ ኃጥአንን ገንዘብ ያደርጋቸዋል፤ አንድም ይወርሶሙ መናፍቃንን ወይ መጎርኮሙ ከሃድያንን ይማርካ ቸዋል ሁሉም ወጡ ለማለት፤

እስመ ተውህበት ነፍሱ ለሞት ፣

ሰውነቱ ለሞት ተሰጥታለችና፤ ወተጐለቈ ምስለ ኃጥአን፣ ከመ ይደምረነ ምስለ ነፍሰ ጻድቃን ብሎ ሊቁ ወስዶታል ፣ ቅዳ. ዮሐ. ወል. ነጐ፣ ከጻድቃን ጋራ አንድ ያደርገን ዘንድ ኃጥአ ተባለ፤

ወውእቱ የዐርግ ኃጢአቶሙ ለብዙ ኃን ፣

የብዙ ሰዎችን ኃጢአት ይዞ ወደ መስቀል ይወጣል ማለት በኃጢ አታቸው ምክንያት ይሰቀላል፤ አንድም ያዐርግ ኃጢአታቸውን ወደ መስቀል ያወጣል ማለት ኃጢአታቸውን በመስቀል ያስተ ሠርይላቸዋል ፤

ወበእንተ ኃጢአቶሙ ተውህበ ውእቱ፣

ስለ ኃጢአታቸው ለሕማም ለሞት ተሰጠ ::

ምዕራፍ ፶፫

፩፤ ትትፈሣሕ መካን እንተ ኢትወ ልድ ወትኬልሕ ወተዐወዩ እንተ ኢሐ መት ፣

እንተ ኢትወልድና እንተ ኢሐ መት አንድ ወገን ነው፣ ሰባ ዘመን ያላማጠች ማለት ልጅ ያላስገ ኘች መካን ቤተ እስራኤል ደስ ይላታል ፤ አንድም ትትፈሣሕ መካን እንተ ኢትወልድ እንተ ኢወለደት ሲል ነው፣ ሰባ ዘመን ልጅ ያልወለደች ፣

ወትኬልሕ ወተዐወዩ ፣

ኋላ ከባቢሎን ወጥታ የምታመ ሰግን ፣

እንተ ኢሐመት ፣

እንተ ሐመት ሲል ነው፣ መከራ የተቀበለች፤ አንድም እንተ ኢተ

ሐምም ፣ እንግዲህ መከራ የማ ትቀበል ቤተ እስራኤል ደስ ይላ ታል ፤

እስመ ብዙኅ ውሉዳ ለመዐስብ እም እንተ ባቲ ምት ፣

ባል ካላት ከባቢሎን ይልቅ የፈት የኢየሩሳሌም ልጆቿ ብዙ ናቸ ውና ማለት ከናምሩድ ጀምሮ ንጉሥ ካልጠፋባት ከባቢሎን ይልቅ ሰባ ዘመን ንጉሥ የጠፋ ባት የኢየሩሳሌም ልጆቿ ብዙ ናቸውና ትትፈሣሕ ላለው እም እንተ ባቲ ምት አላት፣ ባቢሎንን ከናምሩድ ጀምሮ ንጉሥ ጠፍቶ ባት አያውቅምና፤ አንድም ትት ፈሣሕ መካን እንተ ኢትወልድ ወትኬልሕ ወተዐወዩ እንተ ኢሐ መት፣ አምስት ሺህ ካምስት መቶ ዘመን ልጅ ያላስገኘች መካን ወን ጌል ደስ ይላታል፣ መካን አላት በመልከ ጼዴቅ ጊዜ ታይታ ጠፍ ታለችና ፤ አንድም እንተ ኢሐ መት ፣ ሕማመ ነፍስ የሌለባት ወንጌል ደስ ይላታል፤ ወትኬ ልሕ ወተዐወዩ ይላል ፣ ጽንፍ እስከ ጽንፍ ትነገራለች፤

እስመ ብዙኅ ውሉዳ ለመዐስብ እም እንተ ባቲ ምት ፣

ብዙ ነቢያት ካህናት ከነበሯት ከአሪት ይልቅ የወንጌል ልጆቿ ብዙ ናቸውና ትትፈሣሕ ላለው እምእንተ ባቲ ምት አላት፣ አሪ ትን ከአሮን ጀምሮ ሊቀ ካህናት ጠፍቶባት አያውቅምና ፤

፪፤ እስመ ከመዝ ይቤ እግዚአብሔር አርኃቢ መታክለ ደብተራኪ ፣

የድንኳንሽን ካስማ አስፊው ማለት ባለ ድንኳን አይጠፋብ ሽም ብሏልና፤ አንድም ሀገረ ስብ ከትሽን አስፊ ብሏልና ፤

ወትክለ ዐፀደኪ ወኢትምሐኪ ፣

ድንኳንሽን ትከዪው አትሸልጊ ማለት ባለ ድንኳን አይጠፋብ ሽም፤ አንድም ሀገረ ስብከትሽን አጽኚ ፣

አንኒ አኅባለኪ ወአንሥኢ ሠርቄኪ፣

አውታሩን አርዝሚ ተራዳውን አንሺ ማለት ባለ ድንኳን አይጠ ፋብሽም፤ አንድም ሀገረ ስብከት ሽን አስፊ ፤

ወአዕንዲ መታክለኪ ፣

ካስማሽን አዕኚ ማለት ባለ ድን ኳን አይጠፋብሽም፤ አንድም ልቡ ናሽን አዕኚ ፣

፫፤ ወዓዲ ለየማን ወለፀጋም አንጐ ልዲ ፣

ዳግመኛም ወደ ቀኝ ወደ ግራም ሁኖ ትከዪው መጋረጃውን ጋር ጂው ማለት ባለድንኳን አይጠ ፋብሽም ፤ አንድም ወደቀኝም ወደግራም ብለሽ ወንጌልን አስ ተምሪ ሀገረ ስብከትሽን አስፊ ፤

www.ethiopianorthodox.org

እስመ ዘርዕኪ ይወርሱ አሕዛበ ፣

ልጆችሽ አሕዛብን ይወርሳሉና፤

ዘነበርኪ አህጉረ መዝበረ ፣

ትትሐነፂ ያለበት ነው ፣ ሰባ ዘመን የነበርሽ ኢየሩሳሌም ትሠ ሪያለሽ ፤ አንድም አምስት ሺህ ካምስት መቶ ዘመን ከክብር ከል ጅነት ተለይተሽ የነበረ ቤተ ክር ስቲያን ልጆችሽ ሐዋርያት አሕ ዛብን ይወርሳሉና ሀገረ ስብከት ሽን አስፊ ፤

፬፡ ወኢትፍርሂ እስመ ተኀፈርኪ ፣

ከዚህ ቀድሞ በመከራው አፍረ ሻልና አትፍሪ ፣

ወኢተኀፍሪ እስመ ጸአሉኪ ፣

ሰድበውሻልና ምንም ቢሰድቡሽ አታፍሪም ፤

ወትረስዒ ኀፍረተኪ ዘለዓለም ፣

ለዘለዓለም የሚሆን ኀፍረትሽን ትዘነጊዋለሽ ማለት የሰባውን ዘመን መከራ ትዘነጊዋለሽ፤ አን ድም አምስት ሺህ ካምስት መቶ ዘመን ትሰደቢው የነበረውን ኀፍ ረተ ነፍስ ትዘነጊአለሽ ፤

ወኢትዜከሪዮ ለጽእለትኪ ዘአመ ምዕ ስብናኪ ፣

በጋለሞትነትሽ ጊዜ የተሰደብ ሽውን አታስቢውም ፤

፭፡ እስመ እግዚአብሔር ዘገብረ ለኪ እግዚአብሔር ፀባዖት ስሙ ፣

ይህን ያደረገልሽ እግዚአብሔር ስሙ መዋዒ አሸናፊ እግዚአብ ሔር ይባላልና ፤

ወውእቱ አምላከ እስራኤል ዘአድኅ ነኪ ዘይሰመይ በኵሉ ምድር ፣

ይኸውም ያዳነሽ በዓለሙ ሁሉ የሚመሰገን፤ አንድም በዓለሙ ሁሉ ስሙ የሚጠራ የእስራኤል ፈጣሪ ነውና ፣

፮፡ አኮ ከመ ብእሲት ኅድግት ወዕን ብዝት ዘጸውዐኪ እግዚአብሔር ፣

በመከራ እንደተጣለች አእምሮ ዋን እንደ አጣች እንደ ባቢሎን እግዚአብሔር የጠራሽ አይደ ለም ፤

ወአኮ ከመ ብእሲት ጽእልት እምን ዕሳ ፣

ከሕፃንነቷ ጀምሮ እንደ ተሰደ በች ሴት አይደለሽም ማለት ከጥንት ጀምሮ እንደ ተሰደበች እንደ ባቢሎን የጠራሽ አይደለም፣ ባቢሎን ማለት ዝሩት ማለት ነውና ፤ አንድም አኮ ከመ ብእ ሲት ኅድግት ወዕንብዝት ዘጸው ዐኪ እግዘብሔር፣ እንደ ተፈታች (ጥቅስ) ወኵሉ ዘይድኅር ብእ ሲቶ ይጽሐፍ ላቲ መጽሐፈ ኅዳጋቲሃ ዕንብዝት እንዲል ፤ (ማቴ. ፭ ÷ ፴፩) አእምሮዋን እንደ አጣች እንደ ባቢሎን ወይ

መከራ እግዚአብሔር የጠራሽ አይደለም ፤

ወአኮ ከመ ብእሲት ጽእልት እምን ዕሳ ፣

ከናምሩድ ጀምሮ ትሰደብ እንደ ነበረች እንደ ባቢሎን የጠራሽ አይደለም ፤ አንድም መገዛት እንዳለባት እንደ ባቢሎን የጠ ራሽ አይደለም ፤

፯፡ ይቤ አምላክኪ ኅዳጠ መዋዕለ ኀደጉኪ ፣

ኢየሩሳሌም ፈጣሪሽ እግዚአብ ሔር ሰባ ዘመን በመከራ ጣልሁሽ አለ ፣ የሰባውን ዘመን መከራ ኅዳጥ አለው፤ ከፋርስ ከባቢሎን ወጥተው ኢየሩሳሌም ገብተው የሚያደርጉት የኋላው ተድላ ደስታ በዝቶላቸዋልና ፤ አንድም አኮ ከመ ብእሲት ኅድግት ወዕ ንብዝት ዘጸውዐኪ እግዚአብ ሔር ግዕዛነ ነፍስ እንደማይገኝ ባት እንደ ኦሪት የጠራሽ አይደ ለም፤

ወአኮ ከመ ብእሲት ጽእልት እምን ዕሳ ፣

ከጥንት ጀምሮ እንደተሰደበች እንደ ኦሪት የጠራሽ አይደለም፤ ኦሪትን ነዋሪት ሕግ ብለው አል ያዟትምና ፤ አንድም ጳውሎስ ጣዖተ ዝ ዓለም ብሎ ሰድቧታ ልና፤ አንድም አኮ ከመ ብእሲት [illegible] ወዕንብዝት ዘጸውዐኪ

እግዚአብሔር እንዳለፈች ዕንብ ዝት አእምሮን እንደምታጣ እንደ ኦሪት የጠራሽ አይደለም ፤

ወአኮ ከመ ብእሲት ጽእልት እም ንዕሳ ፣

ከጥንት ጀምሮ አምሳል መር ገፍ ሁና እንደተሠራች እንደ ኦሪት የጠራሽ አይደለም ፤

ይቤ አምላክኪ ኅዳጠ መዋዕለ ኀደ ጉኪ ፤

ወንጌል ፈጣሪሽ እግዚአብሔር አምስት ሺህ ካምስት መቶ ዘመን ተውሁሽ አለ ፤ የተሠራች ከሥ ጋዌ በኋላ ነውና ፤

ወበዐቢይ ምሕረት እሠሃለኪ ፣

ኋላ ግን በብዙ ይቅርታ ይቅር እልሻለሁ ፣

፰፡ ይቤ እግዚአብሔር በኅዳጥ መዓት ሜጥኩ ገጽየ እምኔኪ ፣

በጥቂት ኃጢአት ሰባ ዘመን ገጸ ረድኤቴን ካንቺ መለስሁ፤ ኅዳጥ አለው ፤ በሱ ዘንድ ጥቂት ነውና በዐባይ ጽዋዐ ኮሶ፣ በጣና ጭብጥ አፈር ቢበትኑበት ከባሕርዩ እን ዳይለወጥ፤ አንድም በጥቂት ኃጢ አት አምስት ሺህ ካምስት መቶ ዘመን ፊቴን ካንቺ መለስሁ ፣

ወበምሕረት ዘለዓለም እሠሃለኪ ፣

ለዘለዓለም በሚሆን ይቅርታ ይቅር እልሻለሁ ፣

www.ethiopianorthodox.org

ይቤ እግዚአብሔር ዘአድኅነኪ እምነ ማየ አይኅ ዘአመ ኖኅ ፣

በኖኅ ጊዜ ከማየ አይኅ ያዳንሽ እግዚአብሔር እንዲህ አለ፤ ቤተ እስራኤል በኖኅነት ነበረችና ፤

፱፡ ወዝንቱ ውእቱ ስምየ ፣

ስሜም ይህ ነው ማለት አሸናፊ መባል ነው ፤

በከመ ቀዲሙ መሐልኩ ላቲ ለም ድር ፣

እምዝ ዳግመ ኢያማስና ለም ድር ብዬ ከዚህ ቀድሞ እንደ ማልሁ ፤ (ዘፍ. ምዕ. ፱፡፩) ፤

ወከመ ኢይትመዐዕ እንከ ፣

እንግዲህም ወዲህ እንዳልፈርድ፤

፲፡ ወከመ ኢይቅሥፎሙ ለአድባር፣

ኢይቀሥፎሙ ሲል ነው ፤ ነገሥ ታቱን በመከራ እንዳልጥላቸው

ወኢያፍለሶሙ ፣

ኢያፈልሶሙ ሲል ነው ፤ እንዳሳ ስግርካቸው ፤

ወከመ ኢይትሐወሱ አውግርኪ ፣

ኢይትሐወሱ ሲል ነው፤ መኳን ንቱም እንዳይነዋወጡ እንደ ማልሁ ፤

ከማሁ ማህልኪሃ ኢየኀልቅ ለዓለም ዘእምኀቤየ ፣

ከማሁ ኢየኀልቅ ለዓለም ማህልኪ ዘእምኀቤየ ሲል ነው ፤ እንደዚ

ህም ሁሉ ከኔ ዘንድ የሚሆን ይቅርታሽ ለዘለዓለም አይፈጸ ምም ፤

ወኢይጠፍእ ሰላምኪ ፣

ተድላሽ ደስታሽ አይጠፋም፤

እስመ ትቤሊ ሐሰ ለከ እግዚኦ ፣

አቤቱ ታጠፋን ዘንድ አገባብህ አይደለም ብለሻልና ፤

፲፩፡ ወትነብብ በእንተ ሕምምት ወትሕት ፤

ትንብብ ሲል ነው ፤ ያዘንሁ የተ ዋረድሁ የኔን ተስፋ ትናገር ዘንድ አገባብህ አይደለም ብለሻልና ፣ ማለት ራስሽን አዋርደሻልና ተድ ላሽ ደስታሽ አይጠፋም ፤ አን ድም እስከ ትቤሊ ሐሰ ለከ እግ ዚኦ ፣

አቤቱ እንግዲህስ ወዲህ ታጠ ፋን ዘንድ አገባብህ አይደለም እስከ ማለት ድረስ ደርሰሽ ራስ ሽን አዋርደሻልና ተድላሽ ደስ ታሽ አይጠፋም ፤

አንድም እስመ ትቤሊ ሐሰ ለከ እግዚኦ ወትነብብ በእንተ ሕም ምት ወትሕት ፣

ሰባ ዘመን ስለተዋረደች ፣ መከራ ስለተቀበለች ስለ ኢየሩሳሌም ፤

ኀዳጠ መዋዕለ ኀደጉኪ ወበዐቢይ ምሕ ረት እሠሃለኪ፣

በጎዳጥ መዓት ሜጥኩ ገጽየ እም ኔኪ ወበምሕረት ዘለዓለም እሠሃ

ለኪ ብለህ ትናገራለህ ፤ ትች ነው ፤ ለመምለኬ ጣዖት ለኔ ይህን ሁሉ ታደርግልኝ ዘንድ አገባብህ አይደለም ትያለሽና፤ ከ፫ሁ ማህልኪሃ ኢየኀልቅ ላለው፤ አንድም እስመ ትቤሊ ሐሰ ለከ እግዚኦ ወትነብብ በእን ተ ሕምምት ወትሕት ፣ ትን ብብ ሲል ነው፤ ሰባ ዘመን መከራ ስለተቀ በልሁ ስለተዋረድሁ ፤ ኀዳጠ መዋዕለ ኀደጉኪ ወበዐቢይ ምሕረት እሠሃለኪ ፣ ወበኀዳጥ መዓት ሜጥኩ ገጽየ እምኔኪ ብለህ ትናገር ዘንድ ለኔ ለመም ለኬ ጣዖት ይህን ሁሉ ታደርግ ልኝ ዘንድ አገባብህ አይደለም ትያለሽና ኢየኀልቅ ላለው ፤

ናሁ አነ እሬስዮ ለመሠረትኪ ዘዕ ንቍሩ ፣

እነሆ መሠረትሽን የዕንቍሩ አደ ርገዋለሁ ፤

ወዘመረግድ ዘየሐቱ ፣

የሚያበራ መረግድ የሚባል ዕንቍሩ አደርገዋለሁ ፤

፲፪፡ ወዐረፋተኪ ዘከርከዴን ፣

ቅጽርሽን ከርከዴን የሚባል ዕንቍሩ አደርገዋለሁ ፤

ወአናቅጸኪ ዘቢረሌ ፣

በርሽን ቢረሌ የሚባል ዕንቍሩ አደርገዋለሁ ፤

ወአልባስኪኒ ዘወርቅ ፣

ልብስሽን የወርቅ አደርገዋለሁ፤ አንድም ናሁ አነ እሬስዮ ለመ ሠረትኪ ዘዕንቍሩ ፤ ምዕመን መሠረትሽን የዕንቍሩ አደርገ ዋለሁ ማለት መሠረትሽ ክርስ ቶስ ጽሩየ ባሕርይ ነው፤ ዕንቍሩ መክብበ ንዋያት እንደሆነ ክር ስቶስም በሉሪ ምዕመናን ነውና ዕንቍሩ አለው ፤

ወዘመረግድ ዘየሐቱ ፣

የጴጥሮስ አደርገዋለሁ የሰውን ልቡና በትምህርቱ ያበራልና ዘየ ሐቱ ብሎ ቀጠለለት ፤

ወዐረፋተኪ ዘከርከዴን ፣

ቅጽርሽን የአሥራ ሁለቱ ሐዋ ርያት አደርገዋለሁ ፤

ወአናቅጸኪ ዘቢረሌ ፣

በርሽን የሰባ አርድእት አደር ገዋለሁ ፤

ወአልባስኪኒ ዘወርቅ ፣

ልብስሽን የሊቃውንት የሰማዕ ታት አደርገዋለሁ፤ አንድም ጴጥ ሮስን መረግድ የሚባል ዕንቍሩ አደርገዋለሁ ፤ ክቡር አደርገዋ ለሁ ፤ ዐሥራ አንዱን ሐዋርያት የከርከዴን አደርጋቸዋለሁ፤ ሰባ አርድእትን ቢረሌ የሚባል ዕንቍሩ አደርጋቸዋለሁ ፤ ሊቃውንትን፣ ሰማዕታትን የወርቅ አደርጋቸዋ

www.ethiopianorthodox.org

ለሁ ማለት እነዚህን ሁሉ ጽሩያነ ምግባር ወሃይማኖት አደርጋቸ ዋለሁ ፤

፲፫፡ ወኵሎሙ ደቂቅኪ ምሁራን በኀበ እግዚአብሔር ፣

ልጆችሽ ሁሉ ከእግዚአብሔር ዘንድ ተገልጦላቸው የተማሩ ይሆናሉ ፤

ወውስተ ብዙኅ ሰላም ይነብሩ ደቂ ቅኪ ፣

ልጆችሽ በብዙ ተድላ ደስታ ይኖ ራሉ ፤

፲፬፡ ወናሁ ትትሐነፂ በጽድቅ ፣

እነሆ በውነት ትሠሪያለሽ ፤

ረኀቂ እምዐመፃ ወኢትፍርሂ ፣

ይህ ሊደረግልሽ ከዐመፅ ራቂ፤ መከራውን አትፍሪ ፤

ወኢይቀርበኪ ረዐድ ፣

ፍርሀት ረዐድ አያገኝሽም ፤

፲፭፡ እስመ ናሁ ፈላስያን ይመጽኡ እንተ ኀቤየ ፣

በሚጠት ያመኑ አሕዛብ ወደኔ ይመጣሉና ፤

ወይትመኀፀኑ ብኪ ፣

ካንቺ ተጠግተው ይኖራሉ ፤

፲፮፡ ወናሁ አነ ፈጠርኩኪ ፣

እኔን ልታመልኪ እኔን ልታመ ሰግኚ ፈጠርሁሽ ፤

ወአኮ ከመ ነሀቢ ዘይበቀኦ አፍሐመ በምንሃብ ፣

ጃን ሸላሚ በአጎዶ በወናፍ ፍሙን እንዲጭር ፤

ወያወፅእ ንዋየ ለምግባሩ ፣

ለተግባሩ ከዕቃ አቁማዳው ወር ቁን ብሩን እንዲያወጣ ሠርቶ ለኀሣር እንዲያደርገው ፤

ወአንሰ ፈጠርኩኪ ለሠናይ ፣

እንደዚያ አይደለም፤ እኔ ለበጎ ነገር ፈጠርሁሽ፤ አንድም ያ እን ዲህ አድርጎ ሠርቶ ለኀሣር ያደ ርገዋል፤ እኔ ግን ለበጎ ነገር ፈጠ ርሁሽ ፤

ወአኮ ለኀርትምና ፣

ለተዋርዶ የፈጠርሁሽ አይደ ለም ፤

፲፯፡ ወይትነሣእ ኵሉ ቃል ይትዋ ቀሰኪ ፣

ሰው ሁሉ ሊከራከርሽ ይነሣል፤

ወባሕቱ ትመውዒዮሙ ለኵሎሙ፣

ነገር ግን አንቺ ሁሉንም ድል ትነሻቸዋለሽ ፤

ወይወርስዎሙ ሰብእኪ ፣

ሰዎችሽ ይወርሷቸዋል ፤

ወይከውኑኒ ጻድቃንየ ይቤ እግዚአ ብሔር ፤

እግዚአብሔር ወዳጆቼ ይሆናሉ አለ ፤

ምዕራፍ ፶፭

ጉባዔ

፩፡ ወይቤ ኵሎሙ እለ ፀምዑ ይሑሩ ኀበ ማይ ፣

ከውሀ የተጠሙ ሰዎች ሁሉ ወደ ውሀ ይሂዱ አለ ፤

ወእለሂ አልቦሙ ወርቅ ይሣየጡ ሎሙ ይሑሩ ወይስተዩ ዘእንበለ ወርቅ ፣

ውሀውን ይገዙ ዘንድ ገንዘብ የሌላቸው ሰዎች ያለዋጋ ይጠጡ ዘንድ ወደ ውሀው ይሂዱ ፤

፪፡ ለምንት ትሠይጡ በወርቅ ፣

ባለዐዘቅቶችን እንዲህ ይላቸዋል ውሀውን በወርቅ ለምን ትሸጣላ ችሁ ?

ኢይከውነክሙኑ ለጽጋብ ፃማክሙ፣

ጥራችሁ ግራችሁ ያወጣችሁትን ውሀ ያለዋጋ ብትሰጡ ለጽጋበ ነፍስ አይሆናችሁምን፤ አንድም ጥራችሁ ግራችሁ ደክማችሁ ያጠራቀማችሁት ገንዘባችሁ ለጽጋበ ሥጋ አይሆናችሁምን፤ አንድም ኵሎሙ እለ ፀምዑ ይሑሩ ኀበ ማይ፣ ከውሀ የተ ጠሙ ሰዎች ወደ ውሀ ይሂዱ ፤

ወእለሂ አልቦሙ ወርቅ ይሣየጡ ሎሙ ፣

ውሀ የሚገዙበት ወርቅ ለሌላቸው ሰዎች ወርቅ ያላቸው ሰዎች ይግ ዙላቸው ፤

ወይስተዩ ፣

ድሆች ያለ ወርቅ፣ ወርቅ ሳይ ሰጡ ይጠጡ፤ ኢይከውነክሙኑ አይለወጥም፤ አንድም እለ ፀምዑ ይሑሩ ኀበ ማይ ከትምህርት የተጠሙ ሰዎች ወደ ትምህርቱ ይሂዱ ፤

ወእለሂ አልቦሙ ወርቅ ፣

ገንዘብ የሌላቸው ሰዎች ያለ ዋጋ ይማሩ ዘንድ ወደ ትም ህርቱ ይሂዱ፤ አንድም መምህር የሚገዙበት ወርቅ ለሌላቸው ሰዎች ወርቅ ያላቸው ሰዎች መምህር ይግዙላቸው ፤

ለምንት ትሠይጡ በወርቅ ፣

መምህራኑን እንዲህ ይላቸዋል፤ ገንዘብ ተቀብላችሁ ለምን ታስ ተምራላችሁ ፤

ኢይከውነክሙኑ ፣

ጥራችሁ ግራችሁ የተማራችሁ ትን ትምህርት ያለ ዋጋ ብታስ ተምሩ ለጽጋበ ነፍስ አይሆናች ሁምን፤ አንድም የጣራችሁበት የጋራችሁበት ገንዘብ ለፅጋበ ሥጋ አይሆናችሁምን ፤ ከዚህ እንዲህ አለ በኦሪት፣ ኢትፍጽሞ አፉሁ ለላህም ሶበ ታከይድ እክ ለከ አለ ፤ (ዘዳ.፣ ፳፭ ÷ ፬) ዘካርያ ስም እመ አሥመርኩክሙ ቅድ ሜክሙ ድልዉ ሊተ ዐስብየ ፴ ብሩረ አለ፤ ዘካ. ምዕ.፲፩፡ ቍ.፲፪፡

www.ethiopianorthodox.org

ጌታም በወንጌል ይደልዎ ዐስቡ ለዘይትቀነይ አለ፤ ማቴ. ምዕ. ፲ ቍ. ፲፤ አይጣላም ቢሉ አይጣላም ፤ ያመት ልብስ ፣ የዕለት ጉርስ የሌለው ሰው ገንዘብ ተቀብሎ ማስተማር ይገባዋልና ፤ ከዚያ ኢትፍጽሞ አፉሁ ለላህም ሶበ ታከይድ እክለከ፣ እመ አሥመርኩክሙ ቅድሜክሙ ድልዉ ሊተ ዐስብየ ፴ ብሩረ፣ ይደልዎ ዐስቡ ለዘይትቀነይ አለ፤ ያመት ልብስ የዕለት ጉርስ ያለው ሰው ግን ያለ ዋጋ ማስተማር ይገባልና ፣ ከዚህ እንዲህ አለ ፤ አንድም ኵሎሙ እለ ፀምዑ ይሑሩ ኀበ ማይ ከልጅነት የተጠሙ ሰዎች ወደ ልጅነት ይሂዱ ፣

ወእለሂ አልቦሙ ወርቅ ፣

ገንዘብ የሌላቸው ሰዎች ያለ ዋጋ ልጅነቱን መዐርጉን ይቀበሉ ዘንድ ይሂዱ፤ አንድም ይሣየጡ ሎሙ ልጅነት የሚገዙበት ወርቅ ለሌላቸው ሰዎች ባለጸጐች ይግዙላቸው ፤

ወይስተዩ ፣

ድሆች ያለ ዋጋ ልጅነትን ይቀበሉ ፤

ለምንት ትሠይጡ ፤

ቀሳውስቱን እንዲህ ይላቸዋል ገንዘብ ተቀብላችሁ ልጅነትን ለምን ትሰጣላችሁ ፤

ኢይከውነክሙኑ ፣

ጥራችሁ ግራችሁ ያገኛችሁትን ልጅነት ያለ ዋጋ ብትሰጡ ለጽጋበ ነፍስ አይሆናችሁምን፤ አንድም የጣራችሁበት የጋራችሁበት ገንዘብ ለጽጋበ ሥጋ አይሆናችሁም፤ አንድም እለ ፀምዑ ይሑሩ ከማዕርግ የተጠሙ ሰዎች ወደ ማዕረጉ ይሂዱ ፤

ወእለሂ አልቦሙ ወርቅ ፤

ገንዘብ የሌላቸው ሰዎች ያለ ዋጋ ማዕረጉን ይቀበሉ ዘንድ ይሂዱ፤

ለምንት ትሠይጡ ፣

ጳጳሳቱን እንዲህ ይላቸዋል፤ ገንዘብ ተቀብላችሁ መዐርጉን ለምን ትሰጣላችሁ? ጥራችሁ ግራችሁ ያገኛችሁትን ማዕርግ ያለ ዋጋ ብትሰጡ ለጽጋበ ነፍስ አይሆናችሁምን ፤

ስምዑኒ ወትበልዑ በረከተ ፤

ነገሬን ስሙኝ፤ ብትሰሙኝ የኢየሩሳሌምን ድልብ ትበላላችሁ፤ አንድም በረከተ ሥጋ፣ በረከተ ነፍስን ታገኛላችሁ ፤

ወትትፌሣሕ በበረከት ነፍስክሙ ፣

ሰውነታችሁ በበረከት ደስ ይላታል፤ አንድም በፍሬ ምድር ሰውነታችሁ ደስ ይላታል፤ አንድም በረከተ ሥጋ በረከተ ነፍስን አግኝታ ሰውነታችሁ ደስ ይላታል ፤

ወትልዉ ፍኖትየ ፤

ሕጌን ያዙ ፤

ወስምዑኒ ወተሐዩ በበረከት ነፍስክሙ ፤

ነገሬን ስሙኝ፤ ሰውነታችሁ በበረከተ ሥጋ፣ በበረከተ ነፍስ ፀንታ ትኖራለች ፤

፫፤ ወእሠርዕ ለቤተ ዳዊት ሥርዐተ ጽድቅ ዘለዓለም ፤

ለዘሩባቤል ለዘለዓለም የምትኖር ኦሪትን እሠራለሁ ፤

እስመ ናሁ ምዕመነ ረሰይክዎ ፣

እነሆ ዘሩባቤልን የታመነ አድርጌዋለሁና ፤

ወስምዐ ለአሕዛብ ፣

ለአሕዛብም ንጉሥ አድርጌዋለሁና ፤

፬፤ ወሕዝብ እለ ኢየአምሩከ ይጼውዑከ ፤

የማያውቁህ አሕዛብ በሚጠት ባንተ ያምናሉ ፤

ወሕዝብ እለ ኢይሌብዉከ ይትመኀፀኑ ኀቤከ ፣

አንተን ልብ የማያደርጉህ ወገኖች ካንተ ይጠጋሉ ፤

በእንተ እግዚአብሔር አምላክከ ቅዱሰ እስራኤል ፣

ፅንዐ እስራኤል ክብረ እስራኤል ይመጥን ረሰረሀ እግዚአብሔር

በረድኤት ስላደረብህ፤ አንድም ወእሠርዕ ለቤተ ዳዊት ሥርዐተ ጽድቅ ዘለዓለም ብለህ መልስ፤ ለጌታ ለዘለዓለም ፀንታ የምትኖር ወንጌልን እሠራለሁ ፤ አንድም እሱን ሥርዐት አድርጌ እሰጠዋለሁ ጌታን የታመነ አድርጌዋለሁና፣ ለአሕዛብም መምህር አድርጌዋለሁና በሕግ በአምልኮት የማያውቁህ ወገኖች ያምኑ ብሃል ፤

አንተን ልብ የማያደርጉህ ወገኖች አምነው ካንተ ይጠጋሉ፤ በአምልኮት ልብ የማያደርጉህ ወገኖች ስለ እግዚአብሔርነትህ ባንተ ያምናሉ፤ አንድም እግዚአብሔር አብ ባንተ ህልው ስለ ሆነ ፤

እስመ ውእቱ አክበረከ ፣

እሱ አክብሮሃልና ፤

፭፤ ኅሥዎ ለእግዚአብሔር

እግዚአብሔርን በሕግ በአምልኮት ሹት ፤

ወእምከመ ረከብክምዎ ጸውዕዎ ፣

ብታገኙት ለምኑት ፤

ወእምከመ ቀረብክሙ ኀቤሁ ፣

ወደሱ በባለሟልነት ከቀረባችሁ በኋላ ፤

ይኅድግ ኃጥእ ፍኖቶ ፣

ኃጥእ ሰው ክፉ ሥራውን ይተው፤

www.ethiopianorthodox.org

ወብእሲ ዐማፂ ምክሮ ፣

ዐመፀኛ ሰውም ክፉ ምክሩን ይተው ፤

፮፡ ወይትመየጥ ኀበ እግዚአብሔር፣

በሕግ፣ በአምልኮት ወደ እግዚ አብሔር ይመለስ ፤

ወይሠሃሎ እግዚአብሔር ፣

እግዚአብሔር ይቅር ይለዋል፤

እስመ ብዙኀ የኀድግ ለክሙ ኃጢ አተክሙ ፣

ኃጢአታችሁን ብዙ ጊዜ ይቅር ይላችኋልና፤ አንድም ብዙ ኃጢ አታችሁን ይቅር ይላችኋልና፤

፯፡ እስመ ኢኮነ ምክርየ ከመ ምክ ርክሙ ፤

እግዚአብሔር ምክሬ እንደ ምክራችሁ አይደለምና፣ ወኢ ኮነ ፍኖትየ ከመ ፍኖትክሙ ይቤ እግዚአብሔር ፣ ሥራዬም እንደ ሥራችሁ አይደለምና አለ፤ አንድም ምክሬ እንደ ምክራችሁ አይደለምና ወብእሲ ዐማፂ ምክሮ ላለው ይህ ለምሥጢር ነው ፤ አንድም ለተራ ያሉ እንደ ሆነ ምክሬ እንደ ምክራችሁ አይ ደለምና ይኀድግ ኃጥእ ፍኖቶ ላለው ሥራዬም እንደ ሥራችሁ አይደለምና ወብእሲ ዐማፂ ምክሮ [illegible]

፰፡ በከመ ይርኀቅ ሰማይ እምድር፣

ፅኑ ነገር ይናገራቸዋል፤ ሰማይ ከምድር እንዲርቅ ፤

ከማሁ ይርኀቅ ፍኖትየ እምፍኖት ክሙ ፣

አሁን እንደተናገርሁት ሥራዬ ከሥራችሁ ይርቃልና ፣

ይኀድግ ኃጥእ ፍኖቶ ወሕሊናየ እም ሕሊናክሙ ፣

አሳቤም ካሳባችሁ የራቀ ነውና ወብእሲ ዐማፂ ምክሮ ላለው ፤

፱፡ ከመ ሶበ ይወርድ ዝናም እምሰ ማይ ወበረድ ዐቢይ ፣

ፅኑ በረድ ዝናም ከሰማይ በወ ረደ ጊዜ ፤

ወኢየኀድግ እስከ ሶበ ያረውያ ለም ድር ፣

ምድርን ሳያረካት ፤ አንድም ምድርን እስኪያረካት ድረስ መውረዱን እንዳይተው ፤

ወያበቀሎል ወያሠምር ፣

ዘሩን እንዲያበቅል የበጀ እንዲ ያደርግ ፤

ወይሁብ ዘርዐ ለዘራዒ ፣

ለሚዘራ ሰው ጫኑን ፤

ወእክለ ለሲሳይ ፣

ምግብ ሊሆ[illegible] ፤

፲፡ ከማሁ ውእቱ ቃልየ ዘይወፅእ እምአፉየ ፣

ካፌም የሚወጣ ነገር እንደዚህ ነው ፤

ወኢይትመየጥ እስከ እገብር ዘፈቀ ድኩ ፣

የወደድሁትን እስካደርግ ድረስ አይመለስም፤ አንድም የወደድ ሁትን ሳላደርግ አልመለስም፤ ወይሁብ ዘርዐ ያለው እንደ ምነው ቢሉ፣ በግንቦት በሰኔ ጫን ይዘራል ፤ በኀዳር በታኅሣሥ ዐሥር ጫን ያገባል፤ አንዱ ጫን ዘሩ፣ ዘጠኙ ምግቡ ነው፤ እንደ ዘሩ በዐረቦኑ የሚያገኙት ክብር ነው፤ እንደ መከሩ በወዲያው የሚያገኙት ክብር ነው ፤

ወእሤርሕ ፍኖትየ ወትእዛዝየ ፣

ሕጌን ትእዛዜን እስካፀና ድረስ አይመለስም ፤

፲፩፡ እስመ በፍሥሓ ትወፅኡ ወበ ኀሤት ትትነሥኡ ፣

በፍጹም ደስታ ተነሥታችሁ ከባ ቢሎን ትወጣላቸሁና ፤

ያንፈርዕፁ አድባር ወአውግር ፣

ነገሥታቱ መኳንንቱ ደስ ይላቸ ዋል ፤ አንድም በተድላ በደስታ ከባቢሎን ትወጣላችሁና፣ አድባር ዐበይት ነቢያት ፣ ወአውግር ደቂቀ ነቢያት ደስ ይላቸዋል፤ አንድም በፍጹም ደስታ ተነሥታ [illegible] ትወጣላች

ሁና፣ አድባር ሐዋርያት፣ ወአው ግር ሰብዓ አርድእት ደስ ይላቸ ዋል፣

ወይጸንሑክሙ በኀሤት ፣

በደስታ ይጠብቃችኋል ፤

ወይጠፍሑ እደዊሆሙ ኵሉ ዕፀወ ገዳም በበአዕፁቂሆሙ ፣

በበነገዶሙ ሲል ነው፤ እስራኤል ሁሉ በየነገዳቸው በእጃቸው ያጨ በጭባሉ ፤

፲፪፡ ወይሴብሑ ስመ እግዚአብሔር በትእምርት ዘለዓለም ወኢየኀልቅ ስብሐቲሁ ፣

ዘኢየኀልቅ ስብሐቲሁ ሲል ነው፤ ጌትነቱ የማይፈጸም እግዚአብ ሔር ሞተ ብልጣሶርን አድርጎ ላቸው. የእግዚአብሔርን ስም ያመሰግናሉ ፤ አንድም ክብሩ ፣ ጌትነቱ የማይፈጸም ጌታ ለዘለ ዓለም ባደረገው ድኅነት ስመ እግ ዚአብሔርን ያመሰግናሉ ፤ በብ ልጣሶር ሞት፣ በዲያብሎስ ድል መነሣት ፤

ምዕራፍ ፶፮

፩፡ ከመዝ ይቤ እግዚአብሔር ዕቀቡ ጽድቀ ወርትዐ ፣

እግዚአብሔር እውነተኛ ሕግን፣ የቀና ፍርድን ጠብቁ አለ ፤

እስመ አልጸቀት ሕይወትየ ወበጽሐት መድኀኒትየ ፣

ለናንተ የማደርጋት ድኅነቴ ሚጠት ደርሳለችና ፤

www.ethiopianorthodox.org

ወተከሥተት ምሕረትየ ፤

ቸርነቴም ተገልጣለችና ፤

፪፤ ብፁዕ ብእሲ ዘይገብሮ ለዝንቱ፤

ይህን የሚያደርገው ሰው ንዑድ ነው ክቡር ነው ፤

ወይትዔገሥ ቦቱ ፤

ለፈተና ብዬ መከራ ባመጣበት መከራውን ታግሦ የሚቀበል ሰው ንዑድ ነው ክቡር ነው ፤

ወየዐቅብ ሰንበታትየ ወኢያረኵስ፤

ኢይሥዕር ሲል ነው፤ ሰንበትን የሚጠብቅ ፤ የማይሽር ንዑድ ነው ክቡር ነው፤ የዓመቱን ቅዳሜ ቄጥሮ ሰንበታት ብሎ አበዛ፤ አንድም እሑድን በትንቢት ጨምሮ ቄጥሮ ፤ አንድም እሑድን በተስፋ የሚያከብር፤ ወኢያረኵስ ፤ የማይሽር ሰው ብፁዕ ነው ፤

ወኢይገብር ዐመፃ ፤

ኃጢኣት የማይሠራ ጣዖት የማያመልክ ሰው ንዑድ ነው፤ ክቡር ነው ፤

፫፤ ኢይበል ፈላሲ ዘገብአ ኀበ እግዚአብሔር ይፈልጠኒ እንጋ እግዚአብሔር እምሕዝቡ ፤

በሚጠት ወደ እግዚአብሔር የተመለሰ መጻተኛ እግዚአብሔር ከወገኖቹ ከእስራኤል ይለየኝ ይሆን እንጂ አይበል ፤

ወኢይበል ሕፅው አንሰ ከመ ዕፅ ይቡስ ፤

ጃንደረባም እኔ እንደ ደረቅ እንጨት ነኝ አይበል ፤

፬፤ ከመዝ ይቤ እግዚአብሔር ለሕፅዋን ፤

እንዲህስ እንዳይል ጃንደረቦቹን እግዚአብሔር እንዲህ ብሏቸዋል፤

እመ ዐቀቡ ሰንበታትየ ፤

ሰንበትን ቢጠብቁ ፤

ወአብደሩ ዘአነ አፈቅድ ፤

እኔ የምወደውን ቢወዱ

ወተዐገሡ በሥርዐትየ ፤

በሥርዐቴ ፀንተው መከራውን ቢታገሡ ፤

አሁበሙ በቤትየ ወበዕረፍትየ መካነ ዘያሰሚ ፤

ለእስራኤል ዕረፍት በማደርግባት በቤቴ በኢየሩሳሌም ስም የሚያስጠራ ቦታ እሰጣቸዋለሁ፤

፭፤ ወዘይኄይስ እምደቂቅ ወአዋልድ ፤

ከሴት ልጅ ፣ ከወንድ ልጅ የሚበልጥ ቦታ እሰጣቸዋለሁ ፤

ወእሁቦሙ ስመ ዘለዓለም ዘኢየኀልቅ፤

ለዘለዓለሙ የማይጠፋ ስም እሰጣቸዋለሁ ፤

፮፤ ወለእለ ገብኡ ኀበ እግዚአብሔር እምካልዕ ሕዝብ ፤

ከአሕዛብ ወገን ተለይተው ወደ እግዚአብሔር የተመለሱትን ፤

ወተቀንዩ ሎቱ ፤

የተገዙለትን ፤

ወአፍቀሩ ስመ እግዚአብሔር ፤

የእግዚአብሔርን ስም የሚወዱትን ፤

ወለእለ ኮንዎ አግብርቲሁ ወአዕማቲሁ ፤

ወንድ ባርያ ሴት፣ ባርያ የሆኑትን ፤

ወለኵሎሙ እለ የዐቅቡ ሰንበታትየ ፤

ሰንበትን የሚያከብሩትን፣ የማይሽሩትን ፤

ወይትዔገሡ በሥርዐትየ ፤

በሥርዐቴ የፀኑትን ፤

አበውአሙ ውስተ ደብረ መቅደስየ፣

ቤተ መቅደስ ወደአለችባት ወደ ኢየሩሳሌም አገባቸዋለሁ፤

፯፤ ወአስተፈሥሖሙ በቤተ ጸሎትየ፣

ጸሎት በሚደረግባት በቤተ መቅደስ ደስ አሰኛቸዋለሁ፤ አንድም ኢይበል ፈላሲ ዘገብአ ኀበ እግዚአብሔር ብለህ መልስ ፤

በንስሓ ወደ እግዚአብሔር የተመለሰ እግዚአብሔር ከወ

ገኖቹ ከጻድቃን ይለየኝ ይሆን እንጂ ፣ አይበል ፤

ወኢይበል ሕፅው ፤

ንጹሕ መነኩሴም እኔ እንደ ደረቅ እንጨት ነኝ አይበል ፤

፭፤ ከመዝ ይቤ እግዚአብሔር ለሕፅዋን፣

እንዲህስ እንዳይል መነኮሳትን እንዲህ ብሏቸዋል ፤

እመ ዐቀቡ ፤

ሰንበትን ቢጠብቁ ፤

ወአብደሩ ፤

እኔ የምወደውን ቢወዱ ፤

ወተዐገሡ ፤

በሕጌ፣ በሥርዐቴ ቢፀኑ፤ አንድም በሕጌ በሥርዐቴ ፀንተው መከራውን ቢታገሡ ፤

አሁበሙ ፤

ለጻድቃን ዕረፍት በማደርግባት በመንግሥተ ሰማይ ስም የሚያስጠራ ቦታ እሰጣቸዋለሁ፤ አንድም በዚህ ዓለም ስም የሚያስጠራ ቦታ እሰጣቸዋለሁ፤ እንደ ዋልድባ፣ እንደ መጦና፣ ሳሙኤል ዘዋልድባ፣ ጊዮርጊስ ዘልዳ እንዲሉ ፤

ወዘይኄይስ ፤

ከሴት ልጅ ፣ ከወንድ ልጅ የሚበልጥ ቦታ እሰጣቸዋለሁ ፤

www.ethiopianorthodox.org

ወእሁበሙ ፣

ለዘለዓለም የማያልፍ ስም እሰ
ጣቸዋለሁ ፤

ወለእለ ገብኡ ፣

ከኃጢአት ተለይተው በንስሐ
ወደ እግዚአብሔር የተመለሱ
ትን፤ አንድም ከዓለም ወደ ገዳም
የተመለሱትን ፤

ወተቀንዩ ሎቱ ፣

የተገዙለትን ፤

ወአፍቀሩ ፣

የእግዚአብሔርን ስም የሚወዱ
ትን ፤

ወለእለ ኮንዎ ፣

ሴት ባርያ፣ ወንድ ባርያ የሆኑ
ትን ሰንበትን የሚያከብሩትን
የማይሽሩትን

ወይትዔገሡ ፣

በሕጌ፣ በሥርዐቴ የፀኑትን፤ አን
ድም በሕጌ በሥርዐቴ ፀንተው
መከራውን የሚታገሡትን ፤

አበውአሙ ፣

ወደ ገነት ወደ መንግሥተ ሰማ
ያት አገባቸዋለሁ ፤

ወአስተፈሥሐሙ ፣

በጸሎት በምትገኝ በገነት በመ
ንግሥተ ሰማያት ደስ አሰኛቸ
ዋለሁ ፤

ወይከውን መሥዋዕቶሙ ወቀሩርባ
ኖሙ ኅሩየ ፣

መሥዋዕታቸው ቀሩርባናቸው
የተመረጠ ይሆናል ማለት ይቀ
በለዋል፤ አንድም ዕሩየ ይላል፤
የአሕዛብ መሥዋዕታቸው ቀሩር
ባናቸው ከእስራኤል ጋራ የተ
ካከለ ይሆናል ፤ አንድም የኃጥ
አን መሥዋዕታቸው፣ ቀሩርባና
ቸው የተወደደ ይሆናል ፤ አን
ድም ዕሩየ ይላል፤ የኃጥአን መሥ
ዋዕታቸው ቀሩርባናቸው ከጻድ
ቃን ጋራ የተካከለ ይሆናል ፤

ወቤትየኒ ቤተ ጸሎት ይሰመይ ፣

ቤቴ ቤተ መቅደስ ጸሎት የሚ
ደረግበት ቤት ይባላል፤ አንድም
ቤቴ ገነት መንግሥተ ሰማይ
በጸሎት የሚገኝ ቤት ይባላል ፤

ይቤ እግዚአብሔር ለኵሉሙ አሕ
ዛብ ፣

እግዚአብሔር ለአሕዛብ ሁሉ
ተናገረ ፤

፰፤ ወውእቱ ዘያስተጋብዖሙ ለእለ
ተዘርዉ እስራኤል ፣

በፋርስ ፣ በባቢሎን የተበተኑ
እስራኤልን የሚሰበስባቸው እሱ
ነው ፤

ወያስተጋብዕ ላዕሌሆሙ ኵሎ አራ
ዊተ ፤

ከዚህ አስቀድሞ አሕዛብን በላ
ቸው ላይ ይሰበስባል ፤

፱፤ ወይቤሎሙ ንዑ ብልዑ ኵል
ክሙ አራዊተ ገዳም ፣

አሕዛብ የእስራኤልን ገንዘብ
ትበሉ ዘንድ ኑ አላቸው፤ አን
ድም አሕዛብ ሥጋዬን ደሜን
ትቀበሉ ዘንድ ኑ አላቸው ፤

፲፤ ንዑ ትርአዩ ከመ ያሩ ኵሎሙ፤
ሁሉም ዕውራን ልቡና እንደሆኑ
ታዩ ዘንድ ኑ ፤

ወኢሐለዩ ዘይመክሩ ፣

የሚመክሩትን አያስቡትም ፤

፲፩፤ ኵሎሙ አክልብት እሙንቱ
አለ ኢይጸግቡ ፣

ሁሉም የማይጠግቡ ውሾች
ናቸው፤ ውሻ ምን ቢጠግብ መል
ከፍከፉን አይተውም ፤ እስራኤ
ልም ምን ተመለስን ቢሉ አንድ
ጊዜ ወደ ጣዖት፣ አንድ ጊዜ ወደ
አምልኮተ እግዚአብሔር ማለታ
ቸውን አይተዉምና ፤

ወአልቦሙ ልብ ፣

አእምሮ የላቸውም ፤

ወኵሉሙ እለ ተለዉ ለግዕዘሙ ፣

ሁሉም ፈቃደ ሥጋቸውን የሚ
ያደርጉ ናቸው ፤

ምዕራፍ ፶፯

፩፤ ርኢክሙኑ ከመ ተነጉለት ጽድቅ፣
ሕግ እንደ ጠፋች አያችሁን፤

ወኢሐለይክሙ በልብክሙ ፣

ሕግን በልቡናችሁ አላሰባችሁ
ትም ፤

ወአዕተትክሙ ዕደወ ጻድቃነ ፣

ነቢያት ካህናትን ገደላችሁ ፤

፪፤ ወኢያእመርክሙ እስመ እም
ገጸ ዐመፃ ዘተዐተተ ይከውን መቅ
በርቱ በሰላም ፣

ከኃጢአት፣ ከጣዖት የተለየ ሰው
ሞቱ በተድላ በደስታ እንዲሆን
አላወቃችሁም ?

ወይነሥእዎ እማዕከል ፣

ከማዕከለ ዘመኑ ይወስዱታል
በሕይወት ቢሉ እንደ ኤልያስ፤
በሞት ቢሉ እንደ ኢዮስያስ ፤
አንድም ሥላሴ በሕይወት እንደ
ኤልያስ፣ በሞት እንደ ኢዮስያስ
ከኃጥአን መካከል እንዲወስዱት
አላወቃችሁም ፤

፫፤ ወአንትሙሰ አምጻእክሙ ዝየ
ደቂቀ ኃጥአን ወዘርዐ ዘማውያን ወዘ
ማት በእንተ ፍግዕክሙ ፣

እናንተ ግን ተድላ ደስታ ስላደረ
ጋችሁ ከሞዐብ ከዐሞን ካህናተ
ጣዖትን አመጣችሁ፤ አንድም በእ
ንተ ግፍዕክሙ ግፍ ስለሠራ
ችሁ ዛሬም ነቢያተ ሐሰት ካህ
ናተ ጣዖት የሚሆኑ የዘማውያን
ልጆች ናቸውና ፤

፬፤ ወላዕለ መኑ አብቀውክሙ አፋ
ክሙ ፣

አፋችሁን በማን ላይ አላቀቃ
ችሁ ? በእኔ አይደለምን ፤

አኮኑ አንትሙ ትውልደ ኀርቱማን፣
የወራዶች ልጆች አይደላችሁ
ምን ፤

www.ethiopianorthodox.org

፭፡ ወዘርዐ ዐማፅያን እለ ትትፌ
ሥሑ በጣዖት ፣

በጣዖት ደስ የሚላችሁ የዐማ
ፅያን ልጆች አይደላችሁምን፤

ወትሠውዑ ታሕተ ዖም ወቈጽል ፣

በቅጠሉ፣ በዛፉ ሥር ትሠዋላ
ችሁ ፤ ዛፉ ልዑል እንደሆነ
ልዑላን አድርገን፤ ቅጠሉ ብዙ
እንደሆነ ገንዘባችንን አብዛልን፤
ፍሬው ንብብር እንደሆነ ልጆ
ቻችንን አብዛልን ስትሉ ፤

ወትዘብሑ ውሉደክሙ በውስተ
ቈላት ማዕከለ ዖላዕት ፣

ልጆቻችሁን በቈላ በዋሻ መካ
ከል ትሠዋላችሁ ፤

፮፡ ዝንቱ ውእቱ መክፈልትኪ ወዝ
ንቱ ርስትኪ እለ ሎሙ አውፃሕኪ
ሞፃሕተኪ ወእለ ሎሙ አዕረጊ መሥ
ዋዕተኪ ፣

መሥዋዕቱን የሠዋሽላቸው ፣
ወይኑን ያፈሰስሽላቸው ቤተ እስ
ራኤል ዕድል ፈንታሽ ጽዋ ተር
ታሽ ይህ ነው ፤

ኢይትመዐዕኑ እንከ እንበይነ ዝንቱ፣

ስለዚህ ነገር አልቈጣምን፤ አን
ድም አልቈጣ ፤

፯፡ ውስተ ደብር ዐቢይ ወነዋኅ ህየ
ነጸፍኪ ምስካበኪ ፤

በረጅሙ ተራራ ላይ መኝታሽን
አደረግሽ ፤

ወበህየ አዕረጊ መሥዋዕተኪ ፣

በዚያም መሥዋዕቱን ሠዋሽ ፤
ስለምን በተራራ ላይ ይሠዋሉ
ቢሉ ተራራውን ያመልካሉና ፤
አንድም ፀሐይ ጨረቃን ከዋ
ክብትን ያመልካሉና፣ እንዲቀ
ርበን ብለው ፤ አንድም ፈቃዳ
ቸውን ለመፈጸም ከተራራ ላይ
ሠውተው ተረፉን፤ በልተው ጠጥ
ተው መብራቱን አጥፍተው
ደይ እዴከ ኀበ ዘፈቀድከ ወዘ
ኀረይክ ይላል (ሲራ. ፲፭ ÷ ፲፯)፤
ይህን ጊዜ አባት ከልጁ ልጅ
ከእናቱ ይደርሳል ፤ ምነው ያሏ
ቸው እንደሆነ ባለማወቅ ተደረ
ገብን ለማለት ፤

፰፡ ወሠራዕኪ ድኅረ ማዕዖ ፅብዓ
ተኪ ፣

ሰልፍሽን ከመዝጊያ በኋላ አደ
ረግሽው ማለት ፈራሽ፤ አንድም
ጸባኢተኪ ይላል ዐርበኞችሽን
ከመዝጊያ በኋላ አደረግሽ ማለት
ዘግተሽ ተዋጋሽ ፤ አንድም ጸባ
ሕተኪ ግብርሽን ገበርሽ ፤ አን
ድም ጸብሐኪ ይላል ፤ ወጥሽን
ከመዝጊያ በኋላ አደረግሽ ማለት
ለጣዖት አደረግሽ ፤ አንድም
ድኅረ ማዕዖ ይላል ፤ ኢታምልክ
ባዕደ አምላከ ዘእንበሌየ ኢበሰ
ማይ በላዕሉ ወኢበምድር በታ
ሕቱ ብሎ ቃሉን በደብረ ሲና
ከዘጋ በኋላ፤

www.ethiopianorthodox.org

ወመሰለኪኑ ለእመ ኪያየ ኀደግኒ
በዘቦቱ ይረብሐኪ ፣

እኔን በሕግ በአምልኮት ብት
ተዪኝ የሚረባሽ የሚጠቅምሽ
መሰለሽን ፤

ወአብደርኪ መሐዛነኪ እለ ይሰክቡ
ምስሌኪ ፣

ከእኔ ይልቅ ኃጢአት የሚያ
ሠሩሽ ጣዖታቱን ወደድሽ ፤

፱፡ ወአብዛኀኪ ምስሌሆሙ ዝሙ
ተኪ ፣

ከነዚያ ጋራ ኃጢአትሽን አበ
ዛሽ ፤

ወተመሐዝኪ ብዙኃነ እለ ርኁቃን
እምኔኪ ፣

ካንቺ በልደት ከራቁ አሕዛብ
ጋራ መዳራትን አበዛሽ ማለት
ካንቺ በረድኤት የራቁ ጣዖታ
ትን አመለክሽ ፤

ወፈነውኪ ተናብልተ ፣

መልክተኞችሽን ሰደድሽ፣ ጣዖ
ቱን ከሞዐብ ከዐሞን እየገዙ ያመ
ጣሉና ፤

ወአስተጓኅለውክኒ ምስሌሆሙ ፣

ከጣዖታቱ ጋራ አከዳዳሽኝ ፤
አንድም ወአስተጓኅለውኪዮሙ
እርስ በርሳቸው አከዳዳሻቸው
እንጨቱን ደንጊያውን አምል
ከው ወርቁን ብሩን ያመልካሉ፤
ወርቁን ብሩን አምልከው ፀሐይ
[illegible]

ወተኀሥሪ በሞት እስከ ሲኦል ፣

በሞት እስከ መቃብር ድረስ
ትሄጃለሽ ፤

፲፡ ወሠራኀኪ በዐዊድ ፣

ጀዋት ፣ እንጅሞንን ለመፈለግ
በመዞር ደከምሽ፤ አንድም ጣዖ
ትን ለመፈለግ በመዞር ደከምሽ፤
አንድም ተማርከሽ ስትሄጂ
በመንገድ ደከምሽ ፤

ወዓዲ ኢትቤሊ አኀድግ እንከሰ ዘንተ
ፍኖተ እንዘ ብየ ኃይል ፣

ዳግመኛም እንግዲህስ ወዲህ
አእምሮ ሳለኝ ይህን ሥራን እተ
ዋለሁ አላልሽም ፣

እስመ ዘንተ ገበርኪ ፣

ይህን አድርገሻልና ፤

ወኢፈራህኪ ፣

አልፈራሽም ፤

፲፩፡ መነ ተሐዘብኪ ዘኢፈራህክኒ፣

እኔን ያልፈራሽኝ ማን ያድነኛል
ብለሽ ተጠራጠርሽ ፣

ወሐሰውክኒ ፣

ከዳሽኝ ፤

ወኢተዘከርክኒ ወኢሐለይክኒ በል
ብኪ ፣

በልቡናሽም ፈጽመሽ አላሰብሽ
ኝም ፤

ወአነሂ ተኀየይኩኪ እስመ ኢፈራህ
ክኒ ፣

አልፈራሽኝምና እኔም ቸል አል
ሁሽ ፤

፲፪፤ እንከሰ እወቅስ ዘዚአየሂ ጽድ
ቅየ ፣

እንግዲህስ ወዲህ የኔን ቸርነት
እናገራለሁ ፤

ወዘዚአኪሂ ጌጋየኪ ዘኢይበቍዐኪ፣

የማይረባሽ፣ የማይጠቅምሽ ያን
ቺንም ኃጢአት እናገራለሁ ፤

፲፫፤ እስኩኬ ያድኅኑኪ እምከመ ዐው
የውኪ አመ ተመንደብኪ ፣

በመከራው በተጨነቅሽ ጊዜ
ከጮህሽ በኋላ እስኪ ያድኑሽ፤

ናሁ ይነሥኦሙ ዐውሎ ለኵሎሙ
ወየሐፍሶሙ ነፋስ ፣

ስንኳን አንቺን ሊያድኑሽ እነ
ሱን መዓት መቅሠፍት ያጠፋ
ቸዋል ፤

ወእለሰ ይትዔገሡኒ እሙንቱ ይወ
ርስዋ ለምድር ፣

ለፈተና ብዬ መከራ ባመጣባ
ቸው መከራውን ታግሠው የሚ
ቀበሉ ሰዎች ግን ኢየሩሳሌምን
ይወርሳሉ ፤

ወይወርሱ ደብረ መቅደስየ ፣

ቤተ መቅደስን ይወርሳሉ ፤

፲፬፤ ወእብል ጺሑ ፍኖቶ ቅድመ
ገጹ ፣

የዘሩባቤልን ጐዳናውን ጥረጉ፤
አንድም ከፊቱ ጣዖቱን አርቁ፤

ወአዕትቱ ዕብነ እምፍኖተ ሕዝብየ፣

ከወገኖቼ ጐዳና ደንጊያውን
አንሡ፤ አንድም ጣዖቱን አርቁ፤

፲፭፤ ከመዝ ይቤ ልዑል ዘየኀድር
ውስተ አርያም ለዓለም ቅዱሰ ቅዱ
ሳን ስሙ ፣

በልዕልና የሚኖር ልዑል እግ
ዚአብሔር እንዲህ አለ ፤ አን
ድም በልዕልና የሚኖር ስሙ
ከከበሩ የከበረ፣ በወዳጆቹም በረ
ድኤት አድሮ የሚኖር እግዚአ
ብሔር እንዲህ አለ ፤

እግዚአብሔር ዘየዐርፍ በውስተ ቅዱ
ሳን ፣

በቅዱሳን አድሮ የሚኖር እግ
ዚአብሔር ነው ፤

ወይሁቦሙ ትዕግሥተ ለዕንቡዛን ፣

አእምሮዋቸውን ላጡ ሰዎች
ታግሦ የሚያደርጋት ሚጠትን
ይሰጣቸዋል ፤

ወያስተፌሥሖሙ ለቀኑሱላነ ልብ፣

በኀዘን የተያዙትን ደስ ያሰኛ
ቸዋል ፤

፲፮፤ ወአኮ ለዓለም ዘእቀሥፈክሙ፣

ሁል ጊዜ በመከራ የምገርፋችሁ
አይደለም ፤

ወአኮ ዘልፈ ዘእትመዐዐክሙ ፣

አንድ ጊዜ መከራ ባመጣ ሁል
ጊዜ የማመጣባችሁ አይደለም፤

እስመ እምኀቤየ ይወፅእ መንፈስ፣

መንፈሰ ረድኤት ከእኔ ዘንድ
ይገኛልና ፤

ወአነ ፈጠርኩ መንፈሰ ኵሉ ፣

ለሰው ሁሉ ዕውቀትን የሰጠሁ
እኔ ነኝ ፤

፲፯፤ ወበእንተ ኀዳጥ ኃጢአት አሕ
መምክዎ ወቀሠፍክዎ ፣

ስለጥቂት ኃጢአት ሰባ ዘመን
በመከራ ገረፍሁት፤ አስጨነቅ
ሁት፤ ኀዳጥ አለው፤ በዓባይ ጽዋ
ኮሶ፣ በጣና ጭብጥ አፈር ቢበ
ትኑበት ከባሕርዩ እንዳይለወጥ፤

ወሜጥኩ ገጽየ እምኔሁ ፣

ሰባ ዘመን ገጸ ረድኤቴን ከሱ
መለስሁ ፣

ወተከዘ ወሖረ ትኩዙ ፣

አዘነ፣ እያዘነ ተማርኮ ሄደ ፤

፲፰፤ ወእምዝ ርኢኩ ፍናዊሁ ወፈ
ወስክዎ ወአስተፍሣሕክዎ ፣

ከዚህ በኋላ ወደ እኔ መመለ
ሱን አይቼ በሰባ ዘመን አዳን
ሁት፤ ደስ አሰኘሁት፤ አንድም
ወበእንተ ኀዳጥ ኃጢአት አሕ
መምክዎ ብለህ መልስ፣ ስለ
ጥቂት ኃጢአት አዳምን አም
ስት ሺህ ካምስት መቶ ዘመን
በመከራ ገረፍሁት ፤ አስጨነቅ
ሁት ፤ ኀዳጥ አለው ፤ ሐተታ
እንዳለፈው ወሜጥኩ ገጽየ፤ አም
ስት ሺህ ካምስት መቶ ዘመን
ከአዳም ፊቴን መለስሁ ፤

ወተከዘ ፣

አዘነ፣ እያዘነ ወደ ደብር ቅዱስ
ሄደ ፤

ወእምዝ ርኢኩ ፣

ከዚህ በኋላ የአዳምን ንስሓ
ውን አይቼ ባምስት ሺህ ካም
ስት መቶ ዘመን አዳንሁት፤ ደስ
አሰኘሁት ፤

ወወሀብክዎ ፍሥሓ ወጽድቀ ፣

ቸርነትን ደስታውን ሰጠሁት

ወሰላመ በዲበ ሰላም ፣

በፍቅር አንድነት ላይ ፍቅር አን
ድነትን ሰጠሁት ፤

፲፱፤ ለቅሩባን ወለርኁቃን ፣

ለዐሥሩ ነገድ ለሁለቱ ነገድ ፤
አንድም በኃጢአት ለራቁ ለአ
ሕዛብ፣ በኦሪት ለቀረቡ ለእስ
ራኤል ፍቅር አንድነትን ሰጠ
ኋቸው ፤ አንድም ለጻድቃን ለኃ
ጥአን ክብርን ልጅነትን ሰጠ
ኋቸው ፤

ይቤ እግዚአብሔር እሠሃሎሙ ፣

እግዚአብሔር ይቅር እላቸዋለሁ
አለ ፤

፳፤ ኃጥአንሰ ከመዝ ይትገፈትዑ ፣

ኃጥአን ግን አሁን እንደ ተናገ
ርሁት ይጠፋሉ ፤

www.ethiopianorthodox.org

ወኢይረክቡ ዕረፍተ ፣

ዕረፍተ ሥጋ ዕረፍተ ነፍስን አያገኙም ፤

፳፩፤ ወአልቦሙ ፍሥሐ ለኃጥአን ይቤ እግዚአብሔር ፣

ለኃጥአን ተድላ ደስታ የላቸውም አለ እግዚአብሔር ::

ምዕራፍ ፶፰
ጉባዔ

፩፤ ክላሕ በኃይልከ ወኢትምሐክ ፣

ጩኸህ አሰምተህ አስተምር ፤ አትሸልግ ማለት ማስተማሩን ቸል አትበል ፤

ወአዕቢ ቃለከ ከመ ቀርን ፣

ቃልህን እንደ ነጋሪት ድምፅ ከፍ ከፍ አድርግ ፤ ልዑለ ቃል ይጸርሕ ከመ ቃለ ቀርን የሚያሰኘው ይህ ነው ፤ (ቴዎዶ. ሃይ. አበ.) ፤

ወንግሮሙ ለሕዝብየ ኃጢአቶሙ ፣

ለወገኖቼ ኃጢአታቸውን ንገራቸው ፤

ወለቤተ ያዕቆብ ጌጋዮሙ ፣

ለያዕቆብ ወገኖችም በደላቸውን ንገራቸው ፤

፪ እንዘ ትብል ኪያየኑ ተኀሥሡ እም ዕለት ዕለተ ፣

ከዛሬ ነገ ከነገ ማግስት እያላችሁ እኔን በአምልኮት በጸሎት ትሹኛላችሁ ፤

ወትፈቅዱ ታእምሩ ፍኖትየ ከመ ሕዝብ ዘይገብር ጽድቀ ፣

በጎ ሥራ እንደሚሠራ ሰው ሁሉ እኔን ልታውቁ ትወዳላችሁ ፤

ወከመ ዘኢኀደገ ፍትሐ አምላኩ ፣

ሕግ አምላኩ ሲል ነው ፤ የፈጣሪውን ሕግ እንዳልተወ ሰው እኔን ልታውቁ ትወዳላችሁ ፤

፪፤ ወይእዜሰ ኢያእመርክሙኒ ፣

ዛሬ ግን አላወቃችሁኝም ፣

ትስእሉኒ ፍትሐ ወጽድቀ ፣

ይቅርታን፣ ቸርነትን አደርግላችሁ ዘንድ ትለምኑኛላችሁ ፤

ወኢፈተውክሙ ታእምሩኒ ይቤ እግዚአብሔር ፣

በሕግ በአምልኮት ታውቁኝ ዘንድ አልወደዳችሁም አለ እግዚአብሔር ፤

፫፤ ሕዝብኒ ይብሉ እፎ ጾምነሂ ወኢርኢከነ ፤

ሕዝቡም ካላየኸን ለምን ጾምን ይላሉ ፤

ወአሕመምነ ነፍሰነ ወኢያእመርከነ፣

ካላወቅኸን ሰውነታችንን በመከራ ለምን አሳዘነ ፤

፬፤ እስመ ይቤ አመ ትጸውሙ ትግብሩ ፈቃደክሙ ፣

ጌታ እንዲህ አለ ፤ ጾም በጾማችሁ ጊዜ ፈቃዳችሁን ታደርጋላችሁና ፤

ወትትፈደዩ ዕዳክሙ ፣

ዕዳችሁን ትከፈላላችሁና ፤

፭፤ ትሰክዩ ወትትዋቀሱ ወትትላኰዩ ወትትገዓዙ ፣

ትካሰላላችሁ ፣ ትጣላላችሁ ፣ ትከራከራላችሁና ፤

ወትጸውሙ ወትዘብጡ ወትትዔገሉ ነዳየ ፣

እንዲህ እያደረጋችሁ ትጾማላችሁና፣ ድሀውን እየቀማችሁ እየደበደባችሁ ፤

ለምንትኬ እንከሰ ትጸውሙ ሊተ ከመ ዮም ፣

ዛሬ እንደምትጾሙት ያለ ጾም ለምኔ ነው ፤

እንዘ ታግዕሩ ወታዐወይዉ ነዳየ ፣

ድሀውን እያስጮኻችሁ እየደበደባችሁ ፤

፭፤ አኮኬ ዘንተ ጾመ ዘኀረይኩ ፣

እንዲህ ያለውን ጾም የምወድ አይደለም ፤

ወአኮ ከመ ዛቲ ዕለት ዘየሐምም ነፍሶ ሰብእ ፣

ወአኮ ከመ ዛቲ ዕለት ዘየሐምም ነፍሶ ሰብእ ፣

ዛሬ እንደምትጾሚት ባለች ጾም ሰውነቱን የሚያሳዝን ባለ አእምሮ አይደለም ፤

ወኢእመ አቀሥጠጠ ክሣዶ ከመ ጎል ቀት ፣

አንገቱን እንደ ቀለበት ቢያቀ

ወሰከበ ውስተ ሐመድ ወሠቅ ፣

ምንጣፍ ለብሶ ፣ ትቢያ ነስንሶ ቢተኛ ፤

ኢኮነ ጎፍየ ዝንቱ ጾም በጎበ እግዚአብሔር ፣

እንዲህ ያለው ጾም በእግዚአብሔር ዘንድ የተወደደ አይደለም ፣

፮፤ ወአኮ ዘንተ ጾመ ዘኀረይኩ አነ ይቤ እግዚአብሔር ፣

እግዚአብሔርም እኔ ይህንን ጾም የመረጥሁ አይደለም አለ፣

ዳዕሙ ፍታሕ ኵሉ ማዕሠረ ዐመፃ፣

ፍታሕ ማዕሠረ ግሥ ነው ፤ እውነት ፍርድ ፍረድ እንጂ ፤ አንድም በግፍ የታሠረውን ፍታ እንጂ ፤

ወዕርቅ ወአርትዕ ኵሉ ጠዋየ ፣

የተጣላውን አስታርቅ ጠዋየ ልቡናን መክረህ አስተምረህ አቅና እንጂ ፤

ወባልሕ ኵሉ ምንዱበ ፣

በመከራ የተጨነቀውን እውነት ፈርደህ አድነው ፤

ወጎድግ ኵሉ መጽሐፈ ዐመፃ ፣

ጎድግ መጽሐፈ ዐመፃ ግሥ ነው ኃጢአት አትሥራ፤ አንድም መጽሐፈ ሥራይ መጽሐፈ ሟርት መጽሐፈ ጥንቈላን ተው ፤

www.ethiopianorthodox.org

፰፡ ወአጽግቦ ለርኁብ እምእክልከ፣
የተራበውን ከእህልህ አጥግበው፤
ወአብእ ነዳየ ወአኅድሮ ውስተ ጽላሎተ ቤትከ ፣
ድሀውን አስገብተህ ከቤትህ አሳድረው ፤
ወእመኒ ርኢከ ዕሩቀ አልብሶ ፣
የታረዘም ብታይ አልብሰው፤
ወኢትትዐወር እምዘርዐ ቤትከ ፣
ቤተሰቦችህን ቸል አትበል ፤
፱፡ ወይገውህ ሶቤሃ ብርሃንከ ፣
ያንጊዜ ክብርህ ረድኤትህ ይበዛልሃል ፤ በዚህ ዓለም የምታገኘው ፤
ወይሠርቅ ፍጡነ አልባሲከ ፣
ልብስህ ፈጥኖ ነጭ ይሆናል ፤ ማለት በወዲያኛው ዓለም የምታገኘው ክብርህ ፣ ረድኤትህ ይበዛልሃል ፤
ወተሐውር ጽድቅከ ቅድመ ገጽከ ፣
በጐነትህ (ደግነትህ) በፊትህ ትሄዳለች፤ ማለት በጌታ ዘንድ ዋጋህን ታሰጥሃለች ፤
ወስብሐተ እግዚአብሔር ይከድነከ፣
ረድኤተ እግዚአብሔር ከመከራ ይሠውርሃል ፤
፲፡ ሶቤሃኬ ይሰምዐከ እግዚአብሔር በጊዜ ዐውየውከ ፣
በለመንኸው ጊዜ እግዚአብሔር ይሰማሃል ፤

ወእንዘ ትነብብ ነየ ሀለውኩ ይብለከ፣
በተናገርህም ጊዜ እነሆ አለሁ ይልሃል ማለት በለመንኸው ጊዜ ፈጥኖ ልመናህን ይሰማሃል ፤
ለእመ አዕተትከ እምላዕሌከ ኵሎ ማዕሠረ ዐመፃ ወነጐርጓር ፣
ማዕሠረ ዐመፃ ግሥ ነው፤ ኃጢአቱን መበጣበጡን ካንተ ካራቅህ ፤
፲፩፡ ወለእመ ኢዘበጥከ ወአንከይከ እምሲሳየ አፉከ ፣
ድሀውን ካልበደልህ፣ አንተ ከምትመገበው ከሰጠኸው ፤
ወለእመ አፍዐምኮ ለነዳይ ፣
ድሀውን ካበላኸው፣ ካጐረስከው
ወለእመ አጽገብከ ከርሠ ርኅብተ፣
የተራበችውን ሰውነት ካጠገብህ ፤
ሶቤሃኬ ይሠርቅ ማዕከለ ጽልመት ብርሃንከ ፣
ያንጊዜ በመከራ ተይዘህ ሳለ ተድላ ደስታ ይደረግልሃል ፤
ወይከውን ጽልመትከ ከመ ብርሃነ መዓልት ፣
ኀዘንህ በደስታ ይለወጣል ፤
፲፪፡ ወይሄሉ እግዚአብሔር ወትረ ምስሌከ ፣
እግዚአብሔር ሁልጊዜ ካንተ ጋራ በረድኤ[illegible]

ወያጸግበከ ፍትወተ ነፍስከ ፣
ልቡናህ የወደደችውን ያጠግብሃል ማለት የልቡናህን ፈቃድ ይሰጥሃል ፣
ወያጠልለከ አዕፅምቲከ ፣
ሰውነትህን በረድኤት ያለመልመዋል ፤
ወትከውን ከመ ገነት ርውይት ፣
እንደ ለመለመች ተክል ትሆናለህ፤ ውሀ ያልተለያት ተክል ከፍሬ ከልምላሜ እንዳትለይ፣ ከተድላ ከደስታ አትለይም ፤
ወከመ ዐዘቅት ዘኢይነጽፍ ማያ ፣
ውሀዋ እንደማይገታ ምንጭ ትሆናለህ፣ ውሀዋ እንዳይጐድል፤ ቤትህ ከብትህ አይጐድልም ፤
፲፫፡ ወይትሐነፅ መዝበርከ ለዓለም፣
ግዳጅህ ለዘለዓለሙ ይፈጸምልሃል ፤
ወይከውን መሠረትከ ለትውልደ ትውልድ ለዓለመ ዓለም ፣
አባትነትህ ለዘለዓለሙ ለልጅ ልጅ ፀንቶ ይኖራል ፤
ወትሰመይ ሕንፃ ወጥቅመ ፣
ሕንፃ እግዚአብሔር ጥቅመ እግዚአብሔር ትባላለህ ፤
፲፬፡ ለእመ ሜጥከ እግረከ በሰንበት ከመ ኢትግበር ኵሎ ፈቃደከ በዕለተ ሰንበት ቅድስት ፣
በከበረች ዕለት ፈቃድህን እንዳታደርግ በሰንበት ከመሄድ እግ[illegible]

ወትሬስዮን ትፍሥሕተ ለሰንበታት፣
ሰንበታትን ተድላ ደስታ ብታደርጋቸው ፤
ወቀደስኮን ለእግዚአብሔር ፣
ለእግዚአብሔር ብለህ ብታከብራቸው ፤
ወኢታንሥእ እግረከ ለገቢረ እከይ፣
ክፉ ነገር ለማድረግ እግርህን አታንሣ ፤
ወኢታውሥእ ቃለ ኅሡመ በአፉከ፣
በአንደበትህ ክፉ ነገር አትናገር፤
፲፭፡ ወተወከል በእግዚአብሔር ወየዐርገከ ዲበ በረከታ ለምድር ፤
በእግዚአብሔር እመን፤ ወደ ኢየሩሳሌም ድልብ ያወጣሃል፤
ወይሴስየከ ርስተ ያዕቆብ አቡከ ፣
ያባትህ የያዕቆብን ርስት ያወርስሃል፤ አንድም ባባትህ በያዕቆብ ርስት የበቀለውን እህል ይመግብሃል፤ አንድም ካባትህ ከያዕቆብ ርስት የተገኘውን እህል ይመግብሃል ፤ አንድም የያዕቆብን በረከት ይሰጥሃል ፤ አንድም ሕጉን ይሰጥሃል፤ ወትሁቦ ኪያሃ ርስቶ እንዲል ፤
እስመ አፉሁ ለእግዚአብሔር ነበበ ከመዝ ፣
የእግዚአብሔር አንደበቱ እንዲህ በሎ ተናግሯልና ማለት

www.ethiopianorthodox.org

ባራት መቶ ሠላሳ ዘመን ለልጆ
ችህ የማወርሳት አገር ይች ና
ት ብሎ ለአብርሃም ነግሮታል ፤

ምዕራፍ ፶፱

፩፡ ቦኑ ኢትክል አድኅኖ እዴየ ፣
በውኑ ሥልጣኔ ማዳን አይቻላ
ትምን ፤
ወቦኑ ኢይሰምዕ በዕዝንየ ፣
በውኑ በጆሮዬስ አልሰማምን ፤
፪፡ አኮኑ ኃጢአትክሙ ይቀውም ማዕ
ከሌክሙ ወማዕከለ እግዚአብሔር ፣
ኃጢአታችህ በእናንተና በእግ
ዚአብሔር መካከል ፀንቶ የሚ
ኖር አይደለምን ፤ አንድም በእ
ኔና በእናንተ መካከል ኃጢአ
ታችህ ቁሟልና ስለዚህ ነው
እንጂ ፤ አንድም ኃጢአታችህ
በእኔና በእናንተ መካከል ተራራ
ሁኖ ቁሟልና ፣ ስለዚህ ነው
እንጂ በውኑ ሥልጣኔ ማዳን
አይቻላትምን ፤
፫፡ ወበእንተ ኃጢአትክሙ ሜጥኩ
ገጽየ እምኔክሙ ‘ከመ ኢይሠ
ክሙ ፣
ስለ ኃጢአታችህ ይቅር እንዳ
ልላችህ ገጸ ረድኤቴን ከእናንተ
መለስሁ ፤
እስመ ደም ምሉዕ ውስተ እደዊክሙ፡፣
በእጃችህ ደም መልቷልና፤ አን
ድም እስመ ደመ ይላል ፤ እጃ
ችህ ደምን ተሞልቷልና ፤

ወአፃብዒክሙ በኃጢአት ፣
ተሜረይ ያለበት ነው፤ ጣታችህ
በኃጢአት ታልሷልና፤ አንድም
አፃብዐ ልቡናችህ በኃጢአት
ታልሷልና ፤
ወከናፍሪክሙ ነበባ ዐመፃ ፣
ከንፈሮቻችህ ሐሰት ነገርን ተና
ግረዋልና ፤
ወኃጢአተ ተናገረ ልሳንክሙ ፣
አንደበታችህም ኃጢአት የሚ
ሆን ነገርን ተናግሯልና ፤
፬፡ ወአልቦ ዘይነብብ ጽድቀ ፣
እውነትን ነገር የሚናገር የለ
ምና ፤
ወኢትፈትሑ ጽድቀ ፣
እውነትን ፍርድ አትፈርዱምና
ስለ ኃጢአታችህ ገጸ ረድኤቴን
ከናንተ መለስሁ ፤
ወተወከልክሙ በከንቱ ፣
በከንቱ ነገር ታመናችህ ፤
ወነበብክሙ ዘኢይበቍዕክሙ ፣
የማይረባችህን የማይጠቅማች
ሁን ነገር ተናገራችህ ፤
ወፀነስክሙ ኃጢአተ ፣
ኃጢአት የሚሆን ነገርን አሰባ
ችህ ፤

ወወለድክሙ ሕማመ ፣
አስባችህም አልቀራችህ ሠራች
ሁት ፤
፭፡ አንቄቅሆ አርዌ ምድር ታነቅው፣
የእባብ ዕንቁላል ትቀፈቅፋላ
ችሁ ማለት ጣዖት ታመልካላ
ችሁ፤ ተረፈ መሥዋዕተ ጣዖቱን
ትበላላችሁ ፤
ወፈትለ ሣሬት ተአንሙ ፣
የሸረሪት ድር ወተር ትሠራላ
ችሁ ማለት ጣዖት ታመልካላ
ችሁ፤ ተረፈ መሥዋተ ጣዖቱን
ትበላላችሁ፤ ለጣዖት የሚቀርበ
ውን መሥዋዕት ለማጸየፍ የእ
ባብ ዕንቁላል መቀፍቀፍ፣ የሸ
ረሪት ድር ወተር መሥራት
አለው፤ አንድም ሲጸሙ ውለው
የሚበሉትን ሥጋውን ቅቤውን
የእባብ ዕንቁላል መቀፍቀፍ
አለው ፤
እስመ ዘበልዖ ለአንቄቅሆ አርዌ
ምድር ፍጡነ ይመውት ፣
የእባብ ዕንቁላል የበላ ሰው ፈጥኖ
የሚሞት ሲሆን አንቄቅሆ አርዌ
ምድር ታነቅው ላለው፤
፮፡ ወፈትለ ሣሬት ኢይበቍዕ ለተ
አፅፎ ፣
የሸረሪት ድር ወተር መጐናጸ
ፊያ ሊሆን የማይበቃ ሲሆን
ወፈትለ ሣሬት ተአንሙ ላለው፤
፯፡ እስመ ግብረ ዐመፃ ምግባሪክሙ፣
ሥራችህ የዐመፅ ሥራ ነውና፤
ወለኃጢአት ይረውፃ እገሪክሙ ወያ
ፈጥና ለክዒወ ደም ፣
እግሮቻችህም ኃጢአት ለመሥ
ራት ፣ ደም ለማፍሰስ ይፋጠና
ሉና ፤
ወትመክሩ ለቀቲለ ነፍስ ፣
ነፍስ ለመግደል ትመክራላች
ሁና ፤
ጎሣር ወቅጥቃጤ ውስተ ፍኖትክሙ፡፣
በጐዳናችህ በሬ ማረድ፣ ሞፈር
ቀንበር መማገድ ፣ አባት ማሳ
ነስ፣ ጨርቅ ማልበስ አለና ፤
፰፡ ወኢተአምርዋ ለፍኖተ ሰላም፣
የፍቅርን ጐዳና አታውቋትምና፤
እስመ ጠዋይ ፍኖትክሙ ዘተሐውሩ
ቦቱ ፣
እስመን ቢርቀው ደገመው፤ ፀን
ታችህ የምትኖሩበት ሥራ
ጠማማ ነውና ፤
፱፡ በእንተ ዝንቱ ርኅቀ ጽድቅ እም
ኔክሙ ፣
ስለዚህ ነገር በሳ ሥራ ከናንተ
ራቀ ፤
ወኢትረክበክሙ ርትዕ ፣
የቀና ሥራ አትሠሩም፤ አንድም
ወኢተረከብክሙ በርትዕ፣ በቅ
ንነት አልተገኛችህም ፤

www.ethiopianorthodox.org

ወከነክሙ ጽልመተ ብርሃንክሙ ፤
ተድላችሁ ደስታችሁ ኀዘን ሆነ ባችሁ ፤
፲፭፡ ወታረመስሱ ውስተ ዐረፍት ከመ ዕውር ዘአልቦ ዐይን ፤
ዐይን የሌለው ዕውር ባደባባይ በቀን እንዲዳብስ ትዳብሳላችሁ፤
ወትወድቁ መሳልተ ከመ ዘመንፈቀ ሌሊት ፤
ደኅንኛው በመንፈቀ ሌሊት እን ዲዳብስ ትዳብሳላችሁ፤ እንዲወ ድቅ ትወድቃላችሁ ፤
ወትትመነደቡ ከመ ዘይመውት ፤
እንደሚሞት ሰው ትጨነቃላ ችሁ ፤
፲፮፡ እስመ ተሐውሩ ኀቡረ ለቀቲል ከመ ርግብ ፤
ርግብ አደምድማ እንድትሄድ፤ ነፍስ ለመግደል አደምድማችሁ ትሄዳላችሁና ፤
ወከመ ድብ ጸናሕያነ ፍኖት ፤
በጐዳና እንደሚጠብቅ እንደ ጅብ፤ እንደ ግሥላ ፤
በእንተ ዝንቱ አልቦ ዘያድኅነክሙ፤
ስለዚህ ነገር የሚያድናችሁ የለም ፤
፲፱፡ ወሕዝብኒ ይብሉ ርኁቀ ቆምነ እንበይነ ኃጢአትነ በቅድሜከ ፤
ተአምኖ ኃጣውኢ ነው፤ ሕዝቡም ስለ ኃጢአታችን ከፊትህ ርቀን ቆምን ይላሉ ፤
ወጊኃይነ ተቃወመነ ፤
በደላችን ተቃወመን ፤
እስመ ኃጢአትነ ላዕሌነ ፤
ኃጢአታችን በኛ ላይ ፀንቷልና፤
ወጽድቀኒ ኢያእመርነ ፤
በኅ ሥራንም አላወቅንምና
፳፡ አበስነ ወሐሰውናከ ፤
በደልነ፤ ከዳንህ ፤
ውነደግነ ተለዎቶ ለአምላክነ ፤
ፈጣሪያችንን በሕግ በአምልኮት መከተል ተውን ፤
ወነበብነ ዐመፃ ወክህድናከ ፤
ሐሰት ተናገርን፤ ካድንህ፤
ወፀነስነ ወሐለይነ በልብነ ነገረ ኃጢ አት ፤
በልቡናችን ኃጢአት የሚሆን ነገርን አሰብን ፤
፳፩፡ ወርኅቀነ እምጽድቅ ፤
ከበኅ ሥራ ራቅን ፤
ውነደግነ ርትዐ ፤
የቀና ሕግን ተውን ፤
ወተንሥአት ጽድቅ እምፍኖትነ ፤
ከሥራችን በኅ ነገር ታጣች ፤
ወስእነ ሐዊረ በመዕያሕት ፤
በቀና ሕግ ፀንቶ መኖር ተሳነን፤
፳፪፡ ወተዐተትነ እምርትዕ ፤
ከቀና ሕግ ራቅን ፤

ወዐለወ ልብነ ከመ ኢነሐሊ ፤
ሕግ እግዚአብሔርን እንዳናስብ ልቡናችን ወነጀለ ፤ አንድም ፤ ዐለወነ ልብነ ፤ ልቡናችን ወነጀ ለን፤ አንድም፤ አዕለውነ ልበነ ፤ ልቡናችንን አስ ካድነ ፤
ወሶበ ርእየ እግዚአብሔር ከመ ኢያ ሥመሮ ሰብእ ፤
ሰባ ዘመን እግዚአብሔር ሰው ደስ እንዳላሰኘው ባየ ጊዜ ፤ አን ድም አምስት ሺህ ካምስት መቶ ዘመን ሰው ደስ እንዳላሰኘው ባየ ጊዜ ፤
እስመ አልቦ ጽድቅ ፤
ጽድቅ ስለሌለ ፤
፲፭፡ ወርእየ ከመ አልቦ ሰብእ ፤
ባለ አእምሮ ሰው እንደሌለ ባየ ጊዜ ፤
ወጠየቀ ከመ አልቦ ዘይሠጠም ፤
ሰባ ዘመን ፤ አንድም አምስት ሺህ ካምስት መቶ ዘመን የሚ መልስለት ሰው እንደሌለ በተ ረዳ ጊዜ ፤
ኰነኖሙ በመዝራዕቲ ፤
ሰባ ዘመን ፤ አንድም አምስት ሺህ ካምስት መቶ ዘመን በሥ ልጣኑ ፈረደባቸው ፤
ወፀንዖሙ በምሕረቱ ፤
በቸርነቱ ጠበቃቸው ፤
ወለብሰ ጽድቀ ከመ ልብሰ ጎሚን ፤
ወለብሰ ጽድቀ ግሥ ነው፤ እው ነተኛ ቀጠሮ ፣ ውኃሊቆ ሰብዓ ዓመት እትቤቀሎ ለንጉሠ ባቢ ሎን ወለኮሉ ሰብኡ፣ ኤር. ምዕ. ፳፭ ቁ. ፲፪፤ ያለውን አደረገ፤ አንድም እውነተኛ ቀጠሮ በሐ ሙስ ዕለት ወበመንፈቃ ለዕ ለት እትወለድ እምወለተ ወለ ትከ. ቀሌ. ም. ያለውን አደረገ፤
ወወደየ ጌራ መድኃኒት ዲበ ርእሱ፤
ወወደየ ጌራ ግሥ ነው ፤ በራሱ ላይ ቦርቦርቴ ደፋ ማለት በሰባ ዘመን ሚጠትን አደረገ ፤ አን ድም ባምስት ሺህ ካምስት መቶ ዘመን ድኅነተ ነፍስን አደረገ፤ አንድም እንዳለ ይሆናል ፤ አክ ሊለ ሦክን ደፋ ፤
፲፯፡ ወለብሰ ልብሰ በቀል ፤
ለብሰ ልብሰ በቀል ግሥ ነው ፤ በሰባ ዘመን ከባቢሎን ሰዎች በቀልን አደረገ ፤ አንድም ባም ስት ሺህ ካምስት መቶ ዘመን ከአጋንንት በቀልን ተከፈለ ፤
፲፰፡ ወተሞጥሐ ሞጣሕተ በቀል ወፍዳ በዘየኀሥሮሙ ለፀሩ ፤
ተሞጥሐ ሞጣሕተ በቀል ግሥ ነው፤ ጠላቶቹ፤ የባቢሎንን ሰዎች በሚያጐሰቁላቸው ገንዘብ ሽያ የሚባል የጦር ልብስ ለበሰ ማለት በቀልን አደረገ ፤ አንድም ጠላ

www.ethiopianorthodox.org

ቶቹ አጋንንትን በሚያዋርዳቸው ገንዘብ አጋንንትን የሚበቀልበትን ከለሜዳ ለበሰ ፤

፲፱፤ ወይፈርሁ ስመ እግዚአብሔር ኣለ እምዐረብ ወእምሥራቀ ፀሐይ ፣ ገምሥራቅ ፣ በምዕራብ ያሉ ነዎች የእግዚአብሔርን ስም ይፈራሉ ፤ ለስሙ ክቡር ብሉ ሣንሻ ነው ፤ አንድም በምሥራቅ ፣ በምዕራብ ያሉ ሰዎች ፤

ነስሙ ክቡር ፣

ገቡር ለሆነ ለስሙ ክብር ምስጋና ያቀርባሉ ፤ አንድም ማካፈል ነው ፤

ወይፈርሁ ስመ እግዚአብሔር እለ ነምዐረብ ፣

ገምዕራብ ያሉ ሰዎች ስመ እግዚአብሔርን ይፈራሉ ፤

ወእለ እምሥራቀ ፀሐይ ለስሙ ክቡር ፣

ገምሥራቅም ያሉ ሰዎች ለክቡር ስሙ ምስጋና ያቀርባሉ ፤

ወይመጽእ ከመ ውኂዝ ኀያል መቅሠፍት እምነበ እግዚአብሔር በመት ፣

መዓት መቅሠፍት ከእግዚአብሔር ዘንድ ታዝዞ እንደ ፈሳሽ ውሀ በዝቶ ይመጣል ፤

፡ ወይወፅእ እምጽዮን መድኀን ወየትት ኃጢአተ እምያዕቆብ ፣

ገጽዮን ሰዎች ዘሩባቤል ይወለዳል ፤ ከያዕቆብ ወገኖችም ኃጢአትን ያርቃል ፤

፳፩፤ ወዛቲ ይእቲ ኪዳኖሙ እንተ እምነቤየ ይቤ እግዚአብሔር ፣

ውነሊቆ ሰብዓ ዓመት ብዬ ለእስራኤል የማልሁላቸው መሐላ ይች ናት ፤

መንፈሰ ዚአየ ውእቱ ዘዲቤከ ፣

ባንተ ያደረ መንፈሰ ረድኤት የኔ ገንዘብ ነው ፤

ወወደይኩ ቃልየ ውስተ አፉከ ፣

አሪትን እንድታስተምር አደረ ግሁህ ፤

ወኢየኀልቅ እምአፉከ ወእምአፈ ዘር ዕከ ይቤ እግዚአብሔር እምይእዜ ወእስከ ለዓለም ፣

እግዚአብሔር እንግዲህ ከዛሬ ጀምሮ እስከ ዘለዓለሙ ድረስ አሪት ካንተ አንደበት፣ ከልጆችህም ከትሩፋን አንደበት አይጠፋም አለ፤ አንድም ወይወዕእ እምጽዮን መድኀን ብለህ መልስ፤ መድኀኔ ዓለም ክርስቶስ ከእመቤታችን ይወለዳል ፣ ከያዕቆብ ዘነፍስም ተሰቅሎ ኃጢአትን ያርቃል ፤

ወዛቲ ይእቲ ኪዳኖሙ ፣

በሐሙስ ዕለት ወበመንፈቃ ለዕለት እትወለድ እምወለተ ወለትከ ብዬ የማልሁላቸው መሐላ ይች ናት ፤

ይቤ እግዚአብሔር መንፈሰ ዚአየ ውእቱ ዘዲቤከ ፣

እግዚአብሔር አብ ባንተ ህልውና ያለ መንፈስ ቅዱስ የኔ ገንዘብ ነው አለ ፤

ወወደይኩ ቃልየ ፣

ወንጌልን እንድታስተምር አደረግሁህ ፤ ወንጌል የሦስቱ ሕግ ናትና ቃልየ አለ ፤

ወኢየኀልቅ ፣

እንግዲህ ከዛሬ ጀምሮ እስከ ዘለዓለሙ ድረስ ወንጌል ከአንተ አንደበት፣ ከልጆችህም፣ ከሐዋርያት ከምዕመናን አንደበት አይጠፋም አለ እግዚአብሔር ። ።

ምዕራፍ ፷

ጉባዔ

፩፤ አብርሂ አብርሂ ኢየሩሳሌም ፣

ብርሂ ብርሂ ተፈሥሒ ተፈሥሒ ሲል ነው ፤ ኢየሩሳሌም ደስ ይበልሽ ፤ ደስ ይበልሽ ፤

በጽሐ ብርሃንኪ ፣

ሚጠት ደርሶልሻልና ፤ አንድም ተድላ ደስታሽ ደርሷልና ፤

ወስብሐተ እግዚአብሔር ሠረቀ ላዕሌኪ ፣

ረድኤቱ ተገልጦልሻልና አብርሂ ፤

፪፤ ናሁ ጽልመት ደፈና ለምድር ፣

እነሆ ባቢሎንን መከራ ሸፈናት ፤

ወቆባር ላዕለ አሕዛብ ፣

በአሕዛብ መከራ መጣባቸው ፤

ወለኪሰ ብርሃነ አሕዛብ ፣

ላንቺ ግን ሚጠት ተደረገልሽ ፤

ወስብሐቲሁ ነዋ አስተርአየ ላዕሌኪ ፣

እነሆ ረድኤቱ ተገለጠልሽ ፤

ወየሐውሩ ነገሥት በብርሃንኪ ፣

ነገሥታቱ ቂሮስ ፣ ዳርዮስ በብርሃነ ረድኤትሽ ፀንተው ይኖራሉ ፤

ወአሕዛብኒ በፀዳልኪ ፣

ሠራዊቶቻቸውም በፀዳለ ረድኤትሽ ፀንተው ይኖራሉ ፤ አንድም አብርሂ አብርሂ ኢየሩሳሌም ብርሂ ብርሂ ሲል ነው ፤ ምዕመን ደስ ይበልሽ ፤ ደስ ይበልሽ ፤ ልጅነት የምትቀበይበት ደርሷልና ፤ ወስብሐተ እግዚአብሔር ሠረቀ ላዕሌኪ ፣ ወልድ ተወልዶልሻልና ፤

ናሁ ጽልመት ደፈና ለምድር ፣

እነሆ ልበ መናፍቃንን ድንቁርና ሸፈናት ፤

ወቆባር ላዕለ አሕዛብ ፣

በአጋንንት መከራ መጣባቸው ፤

ወለኪሰ ብርሃነ አሕዛብ ፣

ላንቺ ግን ልጅነት ተሰጠሽ ፤

www.ethiopianorthodox.org

ወስብሐቲሁ ነዋ አስተርአየ ላዕሌኪ፣

ወልድ ተወለደልሽ ፤

፫፡ ወየሐውሩ ነገሥት በብርሃንኪ፣

ሐዋርያት በብርሃንሽ በወልድ ፀንተው ይኖራሉ፣ ነገሥት አላቸው ነገሥታት እደ ሥጋ ዐይነ ሥጋ እንዲነሡ ፣ ሐዋርያትም እደ ነፍስ ዐይነ ነፍስ ይነሣሉ፣ በሌጌዎን ይነጻሉ በነፋስ ይሰቅላሉና ፤

ወአሕዛብኒ በፀዳልኪ ፣

ሰባ አርድእትም በፀዳልሽ በወልድ ፀንተው ይኖራሉ ፤

፬፡ አንሥኢ አዕይንተኪ ወነጽሪ ዐውደኪ ፣

ምን ያዳክምሻል አንገትሽን አቅንተሽ ዙሪያሽን እዪ ፤

ወርእዪ ከመ ተጋብዑ ደቂቅኪ ወአዋልድኪ ፣

ሴቶች ልጆችሽ ፣ ወንዶች ልጆችሽ በብሉይ በሐዲስ እንደተሰበሰቡ እዪ ፤

ወይመጽኡ ኵሎሙ ደቂቅኪ እምርኁቅ ብሔር ፣

ልጆችሽ ሁሉ ከሩቅ አገር ይመጣሉ ፤

ወለአዋልድኪኒ እንዘ ይፀውርዎን በመታክፍቲሆሙ ፣

ሴቶች ልጆችሽን እሽኮኮ የቀላጥም እየተሸከሙ ያመጧቸዋል፤

አንድም በዘመነ ሐዲስ አቀኑር ቡልን አቅሱልን እያሉ ያመጧቸዋል ፤

፭፡ ወትሬእዪ ሶቤሃ ወትፈርሂ ፤

ያንጊዜ አይተሽ ትፈሪአለሽ ፤

ወይደነግፀኪ ልብኪ ፤

ልብሽ የደስታ ድንጋጤ ይደነግጥብሻል ፤

እስመ ይትመየጥ ኀቤኪ ብዕለ ባሕር ዘአሕዛብ ፣

ብዕለ አሕዛብ ወደ አንቺ ይመለሳልና ፤

ወበሐውርት ፣

አገሩ ሁሉ ወደ አንቺ ይመለሳልና ፤

፮፡ ወያመጽኡ መራዕየ አግማል ፣

የግመሉን መንጋ ግብር አድርገው ያመጣሉ፤ ይመጽኡ ቢል ግመሎች ግብር ሁነው ይመጣሉ ፤

ወይከድኑ አናቅጸኪ አግማለ ምድያም ፣

የምድያም ግመሎች በርሽን ይመሉታል ፤ ግብር ተጭነው መጥተው፤ አንድም ግብር ሁነው መጥተው ፤

ወያመጽኡ እምሳባ ወርቀ ወስኂነ፣

ከፋስቆሎ ወርቁን፣ ዕጣኑን ያመጣሉ ፤

ወይዜንዉ መድኃኒተ ዘእምኀበ እግዚአብሔር

ከእግዚአብሔር የሚገኝ መድኃኒት ሚጠትን ይናገራሉ ፤

፯፡ ወይትጋብዑ አባግዐ ቄዳር ፣

የዘላኖች በጎች ይሰበሰባሉ ፤

ወያመጽኡ ሐራጊተ ዘናቤዎን ፣

ዘናቡአት ሲል ነው ፤ ለመሥዋዕት የናቡአትን ጊደሮች ያመጣሉ ፤

ወየዐርጉ መሥዋዕተ ኀሩየ ውስተ ምሥዋዕየ ፣

በምሥዋዑ ያማረ ፤ የተወደደ መሥዋዕት ይሠዋሉ ፤

ወይሴባሕ ቤተ ጸሎትየ ፣

ጸሎት የሚደረግበት ቤተ መቅደስ ይከብራል ፤

፰፡ መኑ እሉ እለ ይረውፁ ከመ ደመና ፤

እንደ ደመና ከባቢሎን ፈጥነው የሚወጡ እሊህ እነማን ናቸው?

ወከመ ርግብ እንተ ትበውእ ውስተ መስኮታ ፣

ርግብ አደምድማ (በተርታ) ወደ መስኮቷ እንድትገባ አደምድመው ከባቢሎን የሚወጡ እሊህ እነማን ናቸው ?

፱፡ ኪያየ ይሴፈዋ ደሰያት ፣

ደሴት በውሀ፣ ውሀ በደሴት እንዲከበብ በመከራ የተከበቡ እስራኤል በእኔ ያምናሉ ፤

ይቀድማ ወይመጽኣ አሕማረ ተርሴስ፣

በደሴት የሚኖሩ ነገሥታት አስቀድመው ይመጣሉ ፤

ወአሕዛብኒ ይመጽኡ እምርኁቅ ብሔር ፣

አሕዛብም ከሩቅ ሀገር ይመጣሉ፤

ወምስሌሆሙ ወርቆሙ ወብሩሮሙ በእንተ ስመ እግዚአብሔር ቅዱሰ እስራኤል ክቡር ፤

ዕንዐ እስራኤል ፣ ክብረ እስራኤል በሚሆን በእግዚአብሔር ስም ስላመኑ ወርቁን ብሩን ይዘው ይመጣሉ ፤

፲፡ ወአሕዛብኒ የሐንፁ ዐረፋተኪ ፣

አሕዛብ ቅጽርሽን ይሠራሉ ፤

ወይቀውሙ ቅድሜኪ ነገሥቶሙ፣

ነገሥታቱም በፊትሽ ይቆማሉ፤

እስመ በመዓትየ ቀሠፍኩኪ ፣

ከዚህ አስቀድሞ በመከራ ገርፌሻለሁና ፤

ወበምሕረትየ አቅረብኩኪ ፣

በቸርነቴ አቀረብሁሽ ፤

፲፩፡ ወበኵሉ ጊዜ ይትረኀዋ አናቅጽኪ መዓልተ ወሌሊተ ወኢይትዐፀዋ ፤

በመዓልትም በሌሊትም በየጊዜው ሁሉ በሮችሽ ይከፈታሉ፤ አይዘጉም፣ እንደ ናርጋ ፤

www.ethiopianorthodox.org

ወይበውእ ኀቤኪ ብዕለ አሕዛብ ፣

የአሕዛብ ባለጸግነት ወደ አንቺ ይመጣል ፤

፲፪፡ ወነገሥት እለ ኢይትቀነዩ ለኪ ይመውቱ ፣

ላንቺ የማይገዙልሽ ነገሥታት ይሞታሉ ፤

ወአሕዛብኒ ጠፊአ ይጠፍኡ ፣

ሠራዊቶቻቸውም ፈጽመው ይጠፋሉ ፤

፲፫፡ ወይመጽእ ኀቤኪ ኀይለ ሊባኖስ ፣

የንጉሡ ገንዘብ ወደ አንቺ ይመጣል ፤

ወይሴባሕ ቤተ መቅደስየ ፣

ቤተ መቅደሴ ይከብራል ፤

፲፬፡ ወይመጽኡ ኀቤኪ ፣

ወደ አንቺ ይመጣሉ ፤

ወያመጽኡ አምኃ ደቂቆሙ እልኩ አለ አምዕፁኒ ፣

እሊህ ያሳዘኑሽ አሕዛብ ልጆቻቸውን እጅ መንሻ አድርገው ያመጣሉ ፤

ወትሰመዪ ሀገረ እግዚአብሔር ቅዱሰ እስራኤል ጽዮን ፣

ጽዮን የፅንዐ እስራኤል የክብረ እስራኤል የእግዚአብሔር አገር ትባያለሽ ፤

፲፭፡ እስመ ኀድግተ ወጽእልተ ኮንኪ ፣

ከዚህ አስቀድሞ በመከራ ተጥለ ሻል ፣ ተሰድበሻልና ፤

ውኀጣእኪ ዘይረድኦኪ ፤

የሚረዳሽ አጥተሻልና ፤

ወእሁበኪ ትፍሥሕተ ውኀሴተ ዘለ ዓለም ወለትውልደ ትውልድ ፣

ለዘለዓለም የሚሆን ተድላውን ደስታውን ለልጅ ልጅ ዘመን እሰጥሻለሁ ፤

፲፮፡ ወትትሐፀኒ በሀሊበ አሕዛብ ፣

በብዕለ አሕዛብ ትከብሪያለሽ ፣ አንድም ወንጌልን ትማሪያለሽ፤

ወትበልዒ ብዕለ አሕዛብ ወነገሥት፣

የአሕዛብን፣ የነገሥታትን ገንዘብ ትበያለሽ ፤ አንድም ብዕለ አሕዛብ ወንጌልን ትማሪያለሽ ፤

ወተአምሪ ከመ አነ ውእቱ እግዚአ ብሔር ዘአድኀንኪ ወዘአነግፈኪ አም ላከ እስራኤል ፣

ከመከራ የማድንሽ የእስራኤል ፈጣሪ እኔ እግዚአብሔር እንደ ሆንሁ ታውቂያለሽ ፤

፲፯፡ ወናሁ እሁበኪ ሀየንተ ዕንቍሩ ወርቀ ፣

ስለ ዕንቍሩ ፈንታ ወርቅ እሰጥሻለሁ ፤

ወሀየንተ ወርቅ ብሩረ ፣

ስለ ወርቅ ፈንታ ብር ፤

ወሀየንተ ብሩር ብርተ ፣

ስለ ብር ፈንታ ብርት ፤

ወሀየንተ ብርት ኀጺነ ፣

ስለ ብረቱ ፈንታ ብረት ፤

ወሀየንተ ኀጺን ዕብነ ፣

ስለ ብረቱ ፈንታ ደንጊያ ፤

ወሀየንተ ዕብን ዕፀ ፣

ስለ ደንጊያው ፈንታ እንጨት እሰጥሻለሁ ፣ የቤተ መቅደስን ሥራዋን መናገር ነው ፤ አንድም ሀየንተ ዕፅ ዕብነ፣ ወሀየንተ ዕብን ኀጺነ ፣ ወሀየንተ ኀጺን ብርተ፣ ወሀየንተ ብርት ብሩረ ፣ ወሀየንተ ብሩር ወርቀ ፣ ወሀየንተ ወርቅ ዕንቈ ብሎም ይጽፋል ፤ እንዲህ ማለት በዔዋዊ ጥቂት ገንዘብ ስለሃደብሽ በሚጠት ብዙ ገንዘብ ታገኛለሽ፤ አንድም ስለ ዐበይት ነቢያት ስለ ደቂቅ ነቢያት ስለ ካህናት ስለ መዘምራን ፈንታ ሐዋርያትን፣ ሰባ አርድእትን፣ ቅዱሳት አንስትን ሰጠሁሽ፤ አንድም ዐበይት ነቢያትን ደቂቅ ነቢያትን፣ ካህናትን መዘምራንን ስለአጣሽ ፈንታ ሐዋርያትን፤ ሰባ አርድእትን ሊቃውንትን ፣ ሊቃነ ጳጳሳትን አስነሣልሻለሁ ፤

ወእሁብ ሰላመ ለመላእክትኪ ፣

ለአለቆችሽ ፍቅር አንድነትን እሰጣለሁ ፤

ወጽድቀ ለመኳንንትኪ ፣

ለመኳንንቱም እውነተኛ ፍርድን እገልጥላቸዋለሁ ፤

፲፰፡ ወኢይሰማዕ እንከ ዐመፃ ውስተ ምድርኪ ፣

በሀገርሽ ዐመፅ አይሰማም ማለት ሐሰት ፍርድ አይፈረድም ፤

ኢንሣር ወኢተቀጥቅጦ በውስተ ብሔርኪ ፣

በሀገርሽ እንግዲህ በመከራ መቀጥቀጥ ተዋርዶ የለም ፤

ወይሰመዩ አዕዋንኪ መድኃኒተ ፣

አምባዎችሽ መድኃኒት ይባላሉ ማለት ያድናሉ ፤

ወይትገለፉ አናቅጽኪ ፣

በሮችሽ ሱሳንወርድ ይቀረፃሉ፤ አንድም ሐዋሳቶችሽ በልጅነት ይታደሳሉ ፤

፲፱፡ ወአኮ እንከ ዐሐይ ዘያበርህ ለኪ መዓልተ ፣

በመዓልት ዐሐይ የሚያበራልሽ አይደለም ማለት ዐሐይን የም ታመልኪ አይደለም ፤

ወአኮ እንከ ወርኀ ዘይሠርቅ ለኪ ሌሊተ ፣

ሌሊትም ጨረቃን የምታመልኪ አይደለም ፤

ዳዕሙ ውእቱ እግዚአብሔር ብርሃንኪ ለዓለም ፣

ለዘለዓለሙ እግዚአብሔርን ታመልኪያለሽ እንጂ፣ አንድም ወአኮ

www.ethiopianorthodox.org

እንከ ፀሐይ ዘያበርህ ለኪ መዓ
ልተ ብለህ መልስ፣ ቀን ፀሐይ
የሚያበራልሽ አይደለም ወአኮ
እንከ ወርኀ ዘይሠርቅ ለኪ
ሌሊተ፣ ሌሊትም ጨረቃ የሚ
ያበራልሽ አይደለም፣ ዳዕሙ
ውእቱ እግዚአብሔር ብርሃንኪ
ለዓለም፣ ለዘለዓለሙ የሚያበራ
ልሽ እግዚአብሔር ነው እንጂ፤
እንደ ሁለት አኃው ፣ አንዱ
አንዱን ወደ ምዕራብ ሲሰግድ
አየው ፤ ዛሬስ ፀሐይ የምትወጣ
በምዕራብ ሆነን አለው ፤ ለፀሐ
ይከኒ ኢየአምራ ኢ በሠሪቆታ
ወኢ በዐሪቦታ ብሎታል ፤ ሁሉ
ብርሃን ሁኖበት ፤

ወአምላክኪ ክብርኪ ፣

ክብርሽ ፈጣሪሽ ነው ፤ ፈጣሪሽ
ክብርሽ ነው ፤

፳፡ እስመ ኢየዐርብ ፀሐይኪ ፣

ዐሐይሽ አይገባም ማለት አያል
ፍምና ፤

ወኢየሐልቅ ወርኀኪ ፣

ጨረቃሽም አይፈጸምም ፤

እስመ እግዚአብሔር ብርሃንኪ ለዓ
ለም ፣

ለዘለዓለም ብርሃንሽ እግዚአብ
ሔር ስለሆነ ፤

ወየኀልፍ መዋዕለ ኀዘንኪ ፣

የኃዘንሽም ወራት ያልፋል ፤

፳፩፡ ወይጸድቁ ኵሎሙ ሕዝብኪ
ወይወርሱ ለዓለም ምድረ ፣

ወገኖችሽ ሁሉ ይከብራሉ፤ ኢየ
ሩሳሌምን ለዘለዓለሙ ይወርሳሉ፤
አንድም ገነት መንግሥተ ሰማ
ያትን ይወርሳሉ ፤

ወየዐቅቡ ተግባረ እደዊሁ ለስብሐ
ቲሁ ፣

በጌትነቱ የፈጠራቸው ዐሥርቱ
ቃላትን፣ ስነ ፍጥረትን ይመለ
ከታሉ፤ አንድም እሱን ለማመ
ስገን ሕጉን ይጠብቃሉ፤ አንድም
ጌትነቱን ለማመስገን በእጹ ጽፎ
በቃሉ ተናግሮ የሠራውን ሕግ
ይጠብቃሉ ፤

፳፪፡ ወእለሂ ይውኅዱ የአክሉ ዕልፈ፣

አንሰው የነበሩ ይበዛሉ ፤

ወእለሂ ይቴሐቱ ይከውኑ ሕዝበ ዕኡ፣

ተዋርደው የነበሩ ዕኑ ወገን ይሆ
ናሉ ፤

ወአነ እግዚአብሔር አስተጋብያመ
በዕድሜሆሙ ፣

እኔ እግዚአብሔር በሰባ ዘመን
አሰበስባቸዋለሁ ::

ምዕራፍ ፷፩

ጌባኤ

፩፡ መንፈሰ እግዚአብሔር ላዕሌየ
ዘቀብዐኒ ዘበእንቲአሁ አስተፍሥሐመ
ለነዳያን ፈነወኒ ፣

ስለሱ ነዳያን ትሩፋንን ደስ አሰ
ኛቸው ዘንድ በእኔ ያደረ

መንፈሰ ረድኤት ላከኝ ይላል
ኢሳይያስ ፤

ወእፈውሶሙ ለቀኑሳነ ልብ ፣

በቀኑስለ መከራ የተያዙትን አድ
ናቸው ዘንድ ፤

ወእስብክ ሎሙ ግዕዛነ ለሚውዋን ፣

ለተማረኩት ነፃነትን አስተምራ
ቸው ዘንድ ማለት ሚጠትን አስ
ተምራቸው ዘንድ ላከኝ ፤

ወይርአዩ ዕውራን ፣

ዕውራነ ልቡና እስራኤል ያዩ
ዘንድ ላከኝ ፤

፪፡ ወእስምዮ ለዓመተ እግዚአብሔር
ኀሩየ ፣

ዕለተ ሚጠትን የተመረጠ እለው
ዘንድ ፤

ወለዕለተ ፍዳ ኀሪተ ፣

ዕለተ ፍዳም ያላት ዕለተ ሚጠት
ናት ፤ የባቢሎን ሰዎች ፍዳን ስለ
ተቀበሉባት ዕለተ ፍዳ አላት ፤

ወአስተፍሥሖሙ ለልህዋን ፣

ሰባ ዘመን ያዘኑትን ደስ አሰኛ
ቸው ዘንድ ፤

፫፡ ወእሁቦሙ ክብረ ለእለ ይላህውዋ
ለጽዮን ፣

ኢየሩሳሌምን አጥተው ላዘኑ
ሰዎች ክብረ ሥጋን እሰጣቸው
ዘንድ ፤

ወህየንተ ሐመድ ዕፍረተ ትፍሥሕት
ለእለ ይላህዉ ፣

ትቢያ ይበንባቸው ስለነበረ
ፈንታ ላዘኑ ሰዎች ደስ የሚያ
ሰኝ ሽቱን እሰጣቸው ዘንድ ፤

ወልብሰ ክብር ህየንተ መንፈስ ትኩዝ፣

ሰባ ዘመን ስለአዘነ ልብ ፈንታ
ደስ አሰኘው ዘንድ ፈነወኒ ፣
ላከኝ ፤ አንድም መንፈሰ እግዚ
አብሔር ላዕሌየ ዘቀብዐኒ ዘበእ
ንቲሁ አስተፍሥሐመ ለነዳያን
ፈነወኒ ፣ ያዋሐደኝ በህልውናዬ
ያለ የእግዚአብሔር የባሕርይ
ሕይወቱ መንፈስ ቅዱስ ፤ አን
ድም ሳይናበብ መንፈሰ እግዚ
አብሔር ላዕሌየ፤ በእኔ ህልውና
ባለ መንፈስ ቅዱስ ያዋሐደኝ
እግዚአብሔር አብ ምዕመናንን
አስተምር ዘንድ ላከኝ ፤ አንድም
መንፈሰ ዘዚአየ በህላዌ ለሊሁ
ኀደረ ላዕሌየ ብሎ ሳዊሮስ ዘአን
ጾኪያ ተርጉሞታልና ብሎ የእግ
ዚአብሔር አብ የባሕርይ ሕይ
ወቱ መንፈስ ቅዱስ ላዕሌየ በእኔ
ህልው ነው ፤

ወዘበእንቲአሁ ቀብዐኒ ፣

ስለ ማስተማርም ያዋሐደኝ
መንፈስ ቅዱስ ምዕመናንን አስተ
ምራቸው ዘንድ ላከኝ ፤

ወእፈውሶሙ ፣

ቀኑሳነ ሥጋን በተአምራት
ቀኑሳነ ነፍስን በትምህርት አድ
ናቸው ዘንድ ፤

www.ethiopianorthodox.org

ኢታርምሙ ሎቱ እስከ ይሠርፅ ወእ
ስከ ይሬሲ ትፍሥሕተ ለኢየሩሳሌም
በዲበ ምድር ፤

ኢየሩሳሌምን እስኪያፀናት፣ በም
ድርም ደስ እስኪያሰኛት ድረስ
እረፍት አትስጡት ፤

፯፡ መሐለ እግዚአብሔር በስብሐቲሁ
ወበኀይለ መንግሥቱ ፣

እግዚአብሔር በጌትነቱ ፣ በከሀ
ሊነቱ ፣ ሕያው አነ አማንየ በር
እስየ ብሎ ማለ ፤

ከመ ኢይሁብ እክለኪ ወሥርናየኪ
ለፀር ፣

ሥንዴሽን እህልሽን ለጠላት እን
ዳይሰጥ ማለ ፤

ወኢይሰትይዎ ፀር ለወይንኪ ለዓለም
ዘተገበርኪ ፣

የደከምሽበትን ወይንሽን ጠላ
ቶች እንዳይጠጡት ማለ ፤

ዳዕሙ ዘአስተጋብዖ ይበልዖ ፣

የሰበሰበው ይበላዋል እንጂ ፤ አን
ድም መሐለ እግዚአብሔር ፣
እግዚአብሔር በጌትነቱ ፣ በከሀ
ሊነቱ ፣ ሕያው አነ አማንየ በር
እስየ ብሎ ማለ ፤

ከመ ኢይሁብ ፣

ጸጋሽን ክብርሽን ለአጋንንት
እንዳይሰጥ ፤

ወኢይሰትይዎ ፣

የደከምሽበት ጸጋሽን ክብርሽን
አጋንንት እንዳይወስዱት ማለ፤

እነዚያም የሚወስዱት ሁነው
አይደለም፤ አስቀርተውብሽ ደስ
እንዳይላቸው ሲል ነው ፤

፰፡ ዳዕሙ ዘአስተጋብዖ ፣

ጸጋውን ክብሩን የደከመበት
ያገኘዋል እንጂ ፤

ወይሴብሕዎ ለእግዚአብሔር ፣

እግዚአብሔርን ያመሰግኑታል፤

ወእለ አስተጋብዕዎ ይሰትይዎ በአ
ህጉርየ ቅዱሳት ፣

የሰበሰቡት ሰዎች በከበሩ አገሮች
ይጠጡታል ፤ አንድም ወኢይሰ
ትይዎ ፀር የምግባር የትሩፋት
ሽን ዋጋ አጋንንት አያስቀሩ
ትም ፤

ዳዕሙ ዘአስተጋብዖ ፣

የትሩፋቱን ዋጋ ባለቤቱ ይቀ
በለዋል እንጂ ፤

ወይሴብሕዎ ፣

እግዚአብሔርን ያመሰግኑታል፤

ወእለ አስተጋብዕዎ ይሰትይዎ ፣

የደከሙበት ሰዎች ጸጋውን ክብ
ሩን በገነት በመንግሥተ ሰማይ
ይቀበሉታል ፤

፱፡ ሑሩ ባኡ እንተ አንቀጽየ ፣

ሂዳችሁ ወደ ኢየሩሳሌም ግቡ ፤

ወፂሑ ፍኖተ ለሕዝብየ ፣

ለወገኖቼ ጐዳናውን ጥረጉ፤ አን
ድም ጣዖቱን አርቁ ፤

ወአዕትቱ ዕብነ እምፍኖት ፣

ደንጊያውን ከጐዳና አንሡ፤ አን
ድም ጣዖቱን አርቁ ፤

ወንሥኡ ትእምርተ ለአሕዛብ ፣

ለአሕዛብ ሞተ ብልጣሶርን ንገ
ሯቸው ፤

፲፡ ናሁ እግዚአብሔር ይገብር መን
ክረ እስከ አጽናፈ ምድር ፣

እነሆ እግዚአብሔር ጽንፍ እስከ
ጽንፍ ድረስ ድንቅ ተአምራት
ያደርጋል ፤ አንድም እግዚአብ
ሔር ጽንፍ እስከ ጽንፍ ድረስ
ድንቅ ተአምራት ያደርጋልና ፤
በአሕዛብ ሰንደቅ አላማ ያዙ
ማለት ትከሉ ፤

ወበልዋ ለወለተ ጽዮን ነዋ ንጉሥኪ
በጽሐ ፣

የጽዮንን ልጅ እነሆ ንጉሥሽ ዘሩ
ባቤል ደረሰ በሏት ፤

ወምስሌሁ ዕሤቱ ፣

የሃይማኖቱ ዋጋ መንግሥት የም
ግባሩ ዋጋ ሚጠት ከሱ ጋራ አለ፤

ወምግባሩ ቅድመ ገጹ ፣

በፊቱ ትእምርተ መንግሥት
አለ፤ ሳንቲ ዛጉፍ ይነፋል፤ ድብ
አንበሳ ይሳባል ፤ ነጋሪት ይመ
ታል፤ አላማ ይዘረጋል፣ ሰንደቅ
ይተከላል፤ አንድም የጽዮን ልጅ
ምዕመንን እነሆ ንጉሥሽ ወልደ
[illegible] መጣ በሏት ፤

የሥጋው፣ የደሙ ዋጋ አዳም ከሱ
ጋራ አለ፤ ሦስት ዓመት ከሦስት
ወር በፊቱ ተአምራት ይደረጋል፤

፲፩፡ ወትሰመዩ ሕዝበ ቅዱሰ ዘአድ
ኀነ እግዚአብሔር ፣

እግዚአብሔር ያዳናችሁ ክቡራን
ወገኖች ትባላላችሁ ፤

ወአንቲኒ ትሰመዪ ሀገረ ቅድስተ ፣

አንቺም ክብርት አገር ትባያ
ለሽ ፤

እንተ ይፈቅድዋ ወአኮ እንተ የኀድ
ግዋ ፣

የሚጠሏት ያይደለ የሚወዷት
አገር ትባያለሽ ::

ምዕራፍ ፷፫

ጉባዔ

፩፡ ተስእሎ እምነቢይ ወተሠጥዎ እመ
ልአክ ፣

ከነቢይ የተገኘ ጥየቃ ከመል
አክ የተገኘ መልስ ይህ ነው ፤
ሁለቱም አርእስት ነው ፤ ለሁለ
ቱም ያመጣል ፤

እንዘ ይብል መኑ ዝንቱ ዘወፅአ እም
ዔዶም ቀይሐ አልባስ እምባሶር ፣

ዔዶም ባሶር አንድ ወገን ቀይ
ግምጃ ለብሶ ከኤዶምያስ የወጣ
ይህ ማነው ሲል ከነቢይ የተገኘ
ጥየቃ ይህ ነው ፤ መልአኩ በአ
ምሳለ ሕርቃሎስ ኤዶምያስን
ወግቶ ሲወጣ ያየዋል ፤

www.ethiopianorthodox.org

መካህ ብእሲ ኃያል ወግሩም በልብ
ሰቱ ፣

ቀይ ግምጃ በመልበሱ ኀያል
ግሩም መካህ የሚሆን ይህ ማነው
ሲል ከነቢይ የተገኘ ጥየቃ ይህ
ነው ፤

አነ ዘእትዋቀስ በእንተ ጽድቅ ወእ
ፈትሕ ለአድኅኖ ፣

ተሠጥዎ ላለው አመጣ ስለእው
ነት ነገር የምከራከር ሰውን ለማ
ዳን የምፈርድ እኔ ነኝ ሲል ከመ
ልአክ የተገኘ መልስ ይህ ነው ፤

፪፤ ለምንት ቄሐ አልባሲከ ፣

ተስእሎ ላለው ቀይ ግምጃ ለምን
ለበስህ ፤

ወክዳንከኒ ከመ ዘወፅአ እምክያድ ፣

ቀሚስህስ ከወይን አውድማ
እንደ ወጣ ሰው ለምን ሆነ፣ በሀገ
ራቸው ልማድ ተናግሮታል ብለህ
እንዳለፈው ተርክ ፤

ወይቤለኒ ሶበ ርኢኩ ከመ አልቦ ዘይ
ረድእ ወአልቦ ዘያድኅን ፣

ተሠጥዎ ላለው አመጣ ፤ የሚያ
ድን የሚረዳ እንደሌለ ባየሁ ጊዜ ፤

ቀጥቀጥክዎሙ ለአሕዛብ በመዓትየ፣

የኤዶምያስን ሰዎች ተቈጥቼ
አጠፋኋቸው ፤

ወኬድክዎሙ ከመ ጽንጉነ መርኅብ፣

እንደ አደባባይ ጭቃ ረጋገጥ
ኋቸው ፤

በእንተዝ ተነዝኀ ደሞሙ ውስተ
አልባስየ ፣

ስለዚህ ነገር ደማቸው በልብሴ
ተረጨ ፤

ወኵሉ ክዳንየ ተሴረየ በደም ፣

ቀሚሴም በደም ታለለ አለኝ ፤
አንድም ቀይ ግምጃ የለበስሁ፣
መጐናጸፊያዬም በደም የታለለ
መሆኑ ከወይን አውድማ እንደ
ወጣ ሰው የማጠፋቸው ስለሆነ
ነው ፤ አንድም ተስእሎ እምነቢይ
ወተሠጥዎ እመልአክ አይለወ
ጥም ፤

እንዘ ይብል መኑ ዝንቱ ዘወፅአ እም
ኤዶም ቀይሐ አልባስ እምባሶር ፣

ተስእሎ ላለው ቀይ ግምጃ ለብሶ
ከባቢሎን የወጣ ይህ ማነው ሲል
ከነቢይ የተገኘ ጥየቃ ይህ ነው ፤
የኤዶምያስ ሰዎች የጠላታችንን
ደም እናፈሳለን ሲሉ ቀይ ግምጃ
ይለብሱ ነበርና፣ መልአኩ ቀይ
ግምጃ ለብሶ በአምሳለ ቂሮስ
ባቢሎንን ወግቶ ሲወጣ ያየዋል ፤

መካህ ብእሲ ኃያል ወግሩም በልብ
ሰቱ ፣

ቀይ ግምጃ በመልበሱ ኀያል
ግሩም መካህ የሚሆን ይህ ማነው
ሲል ከነቢይ የተገኘ ጥየቃ ይህ
ነው ፤

አነ ዘእትዋቀስ በእንተ ጽድቅ ወእ
ፈትሕ ለአድኅኖ ፣

ተሠጥዎ ላለው አመጣ፣ ስለእው
ነት ነገር የምከራከር፣ ሰውን ለማ

ዳን የምፈርድ እኔ ነኝ ሲል ፤ አን
ድም ወኀሊቆ ሰብዓ ዓመት ያል
ሁትን ለመፈጸም የምከራከር ፣
ትሩፋንን ለማዳን የምፈርድ እኔ
ነኝ ሲል ከመልአክ የተገኘ መልስ
ይህ ነው ፤

ለምንት ቄሐ አልባሲከ ፣

ተስእሎ ላለው አመጣ ፣ ለምን
ቀይ ግምጃ ለበስህ ፣

ወክዳንከኒ ከመ ዘወፅአ እምክያድ፣

ቀሚስህስ ከወይን አውድማ እንደ
ወጣ ሰው ሆነ ሲል ከነቢይ የተገኘ
ጥየቃ ይህ ነው ፤

፫፤ ወይቤለኒ ሶበ ርኢኩ ከመ አልቦ
ዘይረድእ ወአልቦ ዘያድኅን ፣

ተሠጥዎ ላለው ሰባ ዘመን የሚ
ያድን የሚረዳ እንደሌለ ባየሁ
ጊዜ ፤

ቀጥቀጥክዎሙ ለአሕዛብ በመዓትየ፣

የባቢሎንን ሰዎች ተቈጥቼ አጠ
ፋኋቸው ፤

ወኬድክዎሙ ከመ ጽንጉነ መርኅብ፣

እንደ አደባባይ ጭቃ ረጋገጥኋ
ቸው ፤

በእንተዝ ተነዝኀ ደሞሙ ውስተ አል
ባስየ ፣

ስለዚህ ነገር ደማቸው በልብሴ
ተረጨ ፤

ወኵሉ ክዳንየ ተሴረየ ፣

ቀሚሴም በደም ታለለ አለኝ ፤
አንድም ከወይን አውድማ እንደ
ወጣ ሰው ቀይ ግምጃ የለበስሁ፣
መጐናጸፊያዬም በደም የታለለ
መሆኑ የባቢሎንን ሰዎች የማ
ጠፋ ስለሆነ ነው ፤ አንድም ተስ
እሎ እምነቢይ ወተሠጥዎ እመ
ልአክ ከነቢይ የተገኘ ጥየቃ ከመ
ልአክ የተገኘ መልስ ይህ ነው ፤

እንዘ ይብል መኑ ዝንቱ ዘወፅአ እም
ኤዶም ቀይሐ አልባስ እምባሶር ፣

ሥጋ ለብሶ ከማርያም የተወለደ
ይህ ማነው ሲል ከነቢይ የተገኘ
ጥየቃ ይህ ነው ፤ ባሶር ያለው
ሥጋ ነው ፤ (ጥቅስ) እስመ ብሂለ
ባሶር ይተረጐም ሥጋ እንዲል ፤
(ሃይ. አበ.)፤ አንድም ሰው ሁኖ፣
ሥጋ ለብሶ ከገሊላ የወጣ ይህ
ማነው ሲል ከነቢይ የተገኘ ጥየቃ
ይህ ነው ፤ (ጥቅስ) እስመ ኤዶም
ያስ እምአድያመ ገሊላ ይእቲ
እንዲል ፤ (አፈ ወርቅ ድርሳን)፤

መካህ ብእሲ ኃያል ወግሩም በልብ
ሰቱ ፣

ሥጋ በመልበሱ ኀያል ግሩም
መካህ የሚሆን ይህ ማነው ሲል
ከነቢይ የተገኘ ጥየቃ ይህ ነው ፤

አነ ዘእትዋቀስ በእንተ ጽድቅ ወእ
ፈትሕ ለአድኅኖ ፣

ተሠጥዎ ላለው ስለእውነት ነገር
የምከራከር ምዕመናንን ለማዳን
የምፈርድ እኔ ነኝ ሲል ከመል
አክ የተገኘ መልስ ይህ ነው ፤

www.ethiopianorthodox.org

ለምንት ቈሐ አልባሲከ ፣

ተስእሎ ላለው ለምን ሥጋ ለበ
ስህ ፤

ወክዳንከኒ ከመ ዘወዕአ እምክያድ ፣

ቀሚስህስ ከወይን አውድማ እንደ
ወጣ ሰው ለምን ሆነ ሲል ከነቢይ
የተገኘ ጥየቃ ይህ ነው ፤

ወይቤለኒ ሶበ ርኢኩ ከመ አልቦ ዘይ
ረድእ ወአልቦ ዘያድኅን ፣

አምስት ሺህ ካምስት መቶ ዘመን
የሚያድን የሚረዳ እንደሌለ
ባየሁ ጊዜ ፤

ቀጥቀጥክዎሙ ለአሕዛብ በመዓትየ፣

አጋንንትን ፈርጄ አጠፋኋቸው፤

በእንተዝ ተነዝኀ ደሞሙ ውስተ አል
ባስየ ፣

ለአጋንንት ደም ኑሯቸው አይ
ደለም ፤ ጐስቋልናቸውን መና
ገር ነው፤ አንድም ተስእሎ እም
ነቢይ ወተሠጥዎ እመልአክ አይ
ለወጥም ፤

እንዘ ይብል መኑ ዝንቱ ዘወዕአ እም
ኤዶም ቀይሐ አልባስ እምባሶር ፣

ከለሜዳ ለብሶ ከሲኦል የወጣ
ይህ ማነው ሲል ከነቢይ የተገኘ
ጥየቃ ይህ ነው ፤

መካህ ብእሲ ኃያል ወግሩም በልብ
ሰቱ ፣

ከለሜዳ በመልበሱ ኀያል ግሩም
መካህ የሚሆን ይህ ማነው ሲል
ከነቢይ የተገኘ ጥየቃ ይህ ነው ፤
መልአኩ በአምሳለ ክርስቶስ ከለ
ሜዳ ለብሶ ፣ ገሃነም ወርዶ ነፍ
ሳትን ሲያወጣ ያየዋል ፤

አነ ዘእትዋቀስ በእንተ ጽድቅ ወእ
ፈትሕ ለአድኅኖ ፣

በሐሙስ ዕለት ያልሁትን ለመ
ፈጸም የምከራከር ነፍሳትን ለማ
ዳን የምፈርድ እኔ ነኝ ሲል ከመ
ልአክ የተገኘ መልስ ይህ ነው፤

ለምንት ቈሐ አልባሲከ ፣

ለምን ከለሜዳ ለበስህ ?

ወክዳንከኒ ከመ ዘወዕአ እምክያድ፣

ቀሚስህስ ከወይን አውድማ
እንደ ወጣ ሰው ለምን ሆነ ?
ማለት ለምን ከለሜዳ ለበስህ
ሲል ከነቢይ የተገኘ ጥየቃ ይህ
ነው ፤

ወይቤለኒ ሶበ ርኢኩ ከመ አልቦ ዘይ
ረድእ ወአልቦ ዘያድኅን ፣

አምስት ሺህ ካምስት መቶ ዘመን
የሚያድን የሚረዳ እንደሌለ
ባየሁ ጊዜ ፤

ቀጥቀጥክዎሙ ለአሕዛብ በመዓትየ፣

አይሁድን ተቈጥቼ አጠፋኋ
ቸው ፤

ወኬድክዎሙ ከመ ጽንጉን መርኅብ፣

እንደ አደባባይ ጭቃ ረጋገጥኋ
ቸው ፤

በእንተዝ ተነዝኀ ደሞሙ ውስተ አል
ባስየ ፣

ስለዚህ የአይሁድ ደማቸው ፈሰሰ፡
ቀሚሳቸውም በደም ታለለ፤

፬፡ እስመ በጽሐት ዕለተ ፍዳሆሙ
ወመጽአት ዕለተ ቤዛ ፣

ብድራቸውን የምመልስበት ቀን
ደርሳለችና ፤ እኔም እርሳቸውን
የምበዥበት ቀን መጥታለችና ፤

፭፡ ወርኢኩ ከመ አልቦ ዘይረድእ
ወአእመርኩ ከመ አልቦ ዘይትዌከፍ
ወአድኅኖሙ በመዝራዕትየ ፣

የሚረዳ እንደሌለ አይቼ ፣ የሚ
ቀበልም እንደሌለ አውቄ ፣ በሥ
ልጣኔ አድናቸዋለሁ፤

ወመጽአት መዐትየ ፣

ቊጣዬም መጣች ፤

፮፡ ወኬደቶሙ መቅሠፍትየ ወከሀውኩ
ደሞሙ ውስተ ምድር ፣

መቅሠፍቴም አጠፋቻቸው፤ ደማ
ቸውንም በምድር ላይ አፈሰስሁ፤

፯፡ ወተዘከርኩ ሣህሎ ለእግዚአብሔር
በኵሉ ዕሜቱ ለእግዚአብሔር ፣

እግዚአብሔር ለእስራኤል በሚ
ሰጠው ዋጋ ሁሉ ይቅርታውን
አሰብሁ ፤ ጻድቅ ውኔር ማንሻ ፣
አንድም እስራኤል ባደረገው ቸር
ነቱ ሁሉ የእግዚአብሔር ይቅር
ታውን አሰብሁ ብሎ ወደላይ ፤

ጻድቅ ውኔር እግዚአብሔር ለቤተ
እስራኤል ፣

እግዚአብሔር ለቤተ እስራኤል
ቸር እውነተኛ ነው ፤ አንድም
እስራኤል በሚሰጠው ዋጋ ሁሉ
ጻድቅ ቸር የሚሆን የእግዚአብ
ሔርን ይቅርታ አሰብሁ ፤

ወያመጽእ ለነ ሣህሎ በከመ ብዝኀ
ጽድቁ ፤

እንደ ቸርነቱ ብዛት መጠን በሰባ
ዘመን ይቅርታውን ያመጣል
ናል፤

፰፡ ወይቤ አኮኑ ሕዝብየ ወውሉድየ፡

ወገኖቼ እስራኤል ልጆቼ ናቸ
ውና ፤

እመሰ ኢክህዱኒ አድኅኖሙ ፤

ካልካዱኝ አድናቸዋለሁ፤ አንድም
ኢኮኑ ሕዝብየ አላ ውሉድየ ፤
ወገኖቼ አይደሉም ልጆቼ ናቸው
እንጂ ፤ አንድም አኮኑ አግብር
ትየ አዕርክትየ ፤ ባሮቼ እስራኤል
ወገኖቼ ናቸውና፣ ካልካዱኝ አድ
ናቸዋለሁ ፤ አንድም ኢኮኑ አግ
ብርትየ አላ አዕርክትየ ፤ ባሮቼ
አይደሉም ወዳጆቼ ናቸው እንጂ ፤
አንድም አኮኑ ሕዝብየ ወውሉ
ድየ ወገኖቼ ምዕመናን ልጆቼ
ናቸውና ፣ ካልካዱኝ አድናቸዋ
ለሁ፤ አንድም ኢኮኑ ሕዝብየ አላ
ውሉድየ ፤ ወገኖቼ አይደሉም
ልጆቼ ናቸው እንጂ ፤ አንድም

www.ethiopianorthodox.org

ወመርሆሙ ፣

ከገሃነም መርቶ አወጣቸው ፤

ወከመዝ አውሣእከ ሕዝበከ ፣

እንዲህ አድርገህ ወገኖችህ ምዕመናንን ከገሃነም አወጣሃቸው ፤

ወረሰይከ ለከ ስመ በስብሐቲከ ፣

ገሃነምን አጥፍተህ ነፍሳትን አውጥተህ ጌትነትህን ለመግለጥ ስምህ እንዲነገር አደረግህ ፤ እንዲህ እንዲህ አድርጌ ከገሃነም ባወጣቸው ጎዱር፣ ፍጡር፣ ዕሩቅ ብእሲ፣ ወልደ ዮሴፍ አሉኝ ብሎ፣ ተዘከረ መዋዕለ ዓለም ብለህ እሠር ፤

፲፮፤ ወተመየጥ እምሰማይ ወርኢ ቤተ መቅደስከ ወስብሐቲከ ፤

ከሰማይ በረድኤት ተመልሰህ የምስጋናህን ማደሪያ ቤተ መቅደስን አይ ፤ ምስጋናህንም አይ ፤

አይቴ ውእቱ ቅንዓትከ ወኃይልከ፤

ለአምልኮትህ የምትቀናው ቅናት ኃይልህ ወዴት ነው ፤

ወአይቴ ውእቱ ብዝኀ ምሕረትከ ወሣህልከ ፣

የቸርነትህ ብዛት ይቅርታህ ወዴት ነው ፤

አስመ ተዐገሥከነ ፤

ቸል ብለኸናልና ፤

፲፯፤ አንተ ውእቱ አቡነ ፣

አባታችን አንተ ነህ ፤

አብርሃምሰ ኢያእመረነ ፣

አብርሃም ግን አላወቀንም ፤

ወእስራኤልኒ ኢጠየቀነ ፣

እስራኤልም አልተረዳንም ፤

አንተሰ ዳዕሙ አቡነ አድኀነነ ፣

አባታችን አንተ ግን አድነን እንጂ ፤

እምትካት ተሰምየ ስምከ በላዕሌነ ፣

ከጥንት ጀምሮ ስምህ በኛ ላይ ተጠራ ፤

፲፰፤ ወበእንተ ምንት አስሐትከነ እግዚኦ እምፍኖትከ ፣

አቤቱ ከሕግህ ስለምን አራቅኸን ፣ ረድኤት መንግሥቱን መናገር ነው ፤

ወአዕናዕከ ልበነ ከመ ኢንፍራኅከ ፣

እንዳንፈራህ ልቡናችንን ለምን አበናህ ፤

ተመየጠሙ ለአግብርቲከ ወለሕዝበ ርስትከ ፣

ለባሮችህ ለማደሪያምችህ ለአብርሃም ለይስሐቅ ለያዕቆብ ልጆች ከመዓት ወደ ምሕረት ተመለስላቸው ፤

፲፱፤ ከመ ንርከብ ጎዳጠ መክፈልተ ውስተ ደብረ መቅደስከ ፣

በመመስገኛህ ቦታ በኢየሩሳሌም ጥቂት ዕድል ፈንታ አናገኝ ዘንድ ፤

፲፱፤ አስመ ኮነ ከመ ትካት ፣

እንደ ሙሴ እንደ አሮን ጊዜ ሁነናልና ፤

ወከመ አመ ኮንከነ ፣

ገዢ እንደሆንኸን ጊዜ ፤

ወከመ አመ ተሰምየ ስምከ በላዕሌነ፣

ስምህ በኛ ላይ እንደ ተጠራ ጊዜ ሁነናልና ፤ አንድም አስመ ኢኮነ ከመ ትካት ፣ እንደ ሙሴ እንደ አሮን ጊዜ አልሆንምና ፤

ወከመ አመ ኮንከነ ፣

ገዢ እንደ ሆንኸን ጊዜ ፤

ወከመ አመ ተሰምየ ስምከ በላዕሌነ፣

ስምህ በኛ ላይ እንደ ተጠራ ጊዜ አልሆነምና ፤ አንድም አስመ ኢኮነ ከመ ትካት ፤ እንደ ኤግሎም እንደ ኮሳድስትኤም ጊዜ አልሆንምና ፤

ወከመ አመ ኢኮንከነ ፣

ገዢ እንዳልሆንኸን ጊዜ ሁነናልና ፤

ወከመ አመ ኢተሰምየ ስምከ በላዕሌነ፣

ስምህም በኛ ላይ እንዳልተጠራ ጊዜ አልሆንምና ከመዓት ወደ ምሕረት ተመለስልን ::

ምዕራፍ ፷፬

፩፤ ወእመሰ አርኀውከ ሰማየ ይርዕዱ አድባር እምኔከ ፤

ከሰማይ መዓት መቅሠፍትስ ብታዝዝ ከአንተ የተነሣ ነገሥታቱ ይርዳሉ፣ ይንቀጠቀጣሉ፤

፪፤ ወከመ ይትመሰው መዓረ ግራ እምገጸ እሳት ከማሁ ትበልየሙ እሳት ለፀርከ ፣

ከእሳት ፊት የተነሣ ሰም አደሮ ማር ቀልጦ እንዲጠፋ፣ እንደ ዚህም ሁሉ ጠላቶችህን መዓት መቅሠፍት ታጠፋቸዋለች ፤

ወይትዐወቅ ስምከ በጎቤሆሙ ፣

ስምህ በነዚያ ዘንድ ይታወቃል፤

ወይደነግፁ አሕዛብ እምቅድመ ገጽከ፣

ከገጸ መዓትህ የተነሣ አሕዛብ ይደነግጣሉ ፤

፫፤ ወሶበሂ ገበርከ ስብሐቲከ ይርዕዱ አድባር እለ እምፍጥረተ ዓለም ፣

ጌትነትህን፤ አንድም ተአምራትህን በገለጥህ ጊዜ ከጥንት ጀምሮ የነበሩ ነገሥታቱ ይርዳሉ፣ ይንቀጠቀጣሉ ፤

፬፤ ኢርኢነ ወኢሰማዕነ ባዕደ አምላከ ዘእንበሌከ ፣

ካንተ በቀር ያላንተ ሌላ ፈጣሪ አላየንም ፣ አልሰማንም ፤

ወትገብር ምሕረተከ ለእለ ይሴፈዉ ሣህለከ ፣

ይቅርታህን ተስፋ ለሚያደርጉ ሰዎች ቸርነትህን ታደርጋለህ፤

፭፤ ወይረክቡከ እለ ይትዔገሡ በጽድቅከ ፣

ለፈተና ብለህ መከራ ብታመጣባቸው በቸርነትህ ፀንተው መከ

www.ethiopianorthodox.org

ራውን የሚታገሡ ሰዎች ስትራዳቸው ያገኙሃል ፤

፮ እለ ይዜከሩ ፍኖተከ ፣

ሕግህን የሚያስቡ ሰዎች ስትራዳቸው ያገኙሃል ፤

፯ ናሁ አንተሂ ትትመዐዕ ፣

እነሆ አንተ ትፈርዳለህ ፤

ወንሕነሂ አበስነ ፣

እኛም በደልን ፤

፰ ወበይነ ዝንቱ ስሕትነ ፣

ስለዚህ ነገር ሳትነ ፤

፱ ወኮነ ርኩሳነ ኵልነ ፣

ሁላችንም የምናጸይፍ ሆንነ ፤

ወከመ ፀርቀ ትክቶ ኵሉ ጽድቅነ፣

ሥራችን ሁሉ እንደ ግዳጅ ጨርቅ የሚያጸይፍ ሆነ፤ አንድም ወኮነ ርኩሳነ ርኩሳን ሆንነ ፤

፲ ወከመ ፀርቀ ትክቶ ኵሉ ጽድቅነ፣

ሥራችን ሁሉ እንደ ግዳጅ ጨርቅ ሆነ ይላሉ እስራኤል ፤ አንድም ነቢያት ካህናት አምስት ሺህ አምስት መቶ ዘመን የጸለይ ነው ጸሎት ፣ የሠዋነው መሥዋዕት እንደ ግዳጅ ጨርቅ ሆነ ይላሉ ፤ የጸለዩት ጸሎት የሠዉት መሥዋዕት በእደ እግዚአብሔር ለመያዝ አበቃቸው እንጂ ለክብር ፣ ለልጅነት ፣ ለገነት ለመንግሥተ ሰማያት አላበቃቸውምና፤

፲፩ ወተነገፍነ ከመ ቈጽል በእንተ ኃጢአትነ ፣

ስለ ኃጢአታችን እንደ ቅጠል ረገፍን ፤

፲፪ ወከማሁ ነፋስ ሐፈሰነ ፣

አሁን እንደ ተናገርሁት መዓት መቅሠፍት አጠፋን ፤

፲፫ ወአልቦ ዘፀውዐ ስመከ ወኢተዘከርናከ ፣

ስምህን የጠራ የለም ፣ አላሰብን ህም ፤

እስመ ሜጥከ ገጸከ እምኔነ ፣

ገጸ ረድኤትህን ከኛ መልሰሃልና፤

ወመጠውከነ ለኃጢአትነ ፣

ለኃጢአታችን አሳልፈህ ሰጥተኸናልና አለ፤ ኃጢአት እንድን ሠራ አድርገኸናልና፣ ረድኤት መንሣቱን መናገር ነው ፤ አንድም በኃጢአታችን ለመጣ ፍዳ አሳልፈህ ሰጥተኸናልና እንደ ቅጠል ረገፍን ፤

፲፬ ወይእዜኒ አንተሰ እግዚእነ ወአቡነ ፣

አሁንም አንተ ጌታችን አባታችን ነህ ፤

ወንሕነ ጽቡር ፣

እኛ ፈራሾች ፣ በስባሾች ነን ፤

ወአንተ ፈጠርከነ ፣

የፈጠርኸን አንተ ነህ ፤

ወተግባረ እደዊከ ኵልነ ፣

ሁላችን የእጅህ የቃልህ ፍጥረቶች ነን ፤

፲፭ ወፈድፋደሰ ኢትትመዐዓነ እግዚኦ ፣

አቤቱ ፈጽመህ አትፍረድብን፤

ወኢትዝክር ለነ አበሳነ ፣

ኃጢአታችንን አታስብብን ፤

ወይእዜኒ ነጽረነ ፣

አሁንም በዓይነ ምሕረትህ ተመልከተን ፤

እስመ ሕዝብከ ንሕነ ኵልነ ፣

እኛ ሁላችን ወገኖችህ ነንና ፤

፲፮ እስመ ንጎለ ሀገረ መቅደስከ ኢየሩሳሌም ፣

ቤተ መቅደስህ ያለችበት ሀገርህ ኢየሩሳሌም ፈርሷልና ፤

ወተመዝበረ ቤተ መቅደስከ ፣

ቤተ መቅደስህም ፈርሷልና ፤

፲፯ ወውዕየ በእሳት ክብርነ ዘባረኩ አበዊነ ፣

አባቶቻችን ያከበሩት ንዋየ ቅድሳት በእሳት ተቃጥሏልና ፤

ወወድቀ ኵሉ ትርሢትነ ፣

ሽልማታችን ሁሉ ጠፍቷልና ፤ አንድም ንዋየ ቅድሳታችን ጠፍቷልና ፤

፲፰ ወበዝንቱ ኵሉ ተዐገሥከነ እግዚኦ፣

አቤቱ በዚህ ሁሉ ቸል ብለኸናልና፤

ወአርመምከ ፣

ዝም ብለሃልና ፤

ወአጎሠርከነ ፈድፋደ ፣

ፈጽመህ አዋረድኸን ፤ አንድም ፈጽመህ አዋርደኸናልና በዐይነ ምሕረት ተመልከተን ፤

ምዕራፍ ፷፭

ጉባኤ

፩ ረከቡኒ እለ ኢጎሠሡኒ ፣

በሕግ በአምልኮት ያልሹኝ (ያልፈለጉኝ) በሰባ ዘመን በረድኤት አገኙኝ ፤

ወአስተርአይክዎሙ ለእለ ኢተስአሉኒ ፣

ሰባ ዘመን ላልጠየቁኝ ለእስራኤል በረድኤት ተገለጥሁላቸው፤ አንድም ሰባ ዘመን አድነን ብለው ያልፈለጉኝ ትሩፋን በሰባ ዘመን ስረዳቸው አገኙኝ ፤

ወአስተርአይክዎሙ ፣

እኔም በነቢያት በካህናት አድነን ብለው ላልጠየቁኝ ለትሩፋን በሰባ ዘመን እገለጥላቸዋለሁ፤ አንድም አምስት ሺህ ካምስት መቶ ዘመን ያልሹኝ ምዕመናን ባምስት ሺህ ካምስት መቶ ዘመን ሰው ሁኜ አገኙኝ፤ አምስት ሺህ ካምስት መቶ ዘመን በምሥሃል በአዕናቀኑ ላልጠየቁኝ ምዕመናን ሰው ሁኜ ሥጋ ለብሼ ተገለጥሁላቸው ፤

www.ethiopianorthodox.org

ወሶበ ይጸርሑ እሰጠምሙ ፣

ጩኸው በተናገሩ ጊዜ እመል ስላቸዋለሁ ፤

ወእብሎሙ ነየ አነ ለሕዝብየ እለ ፀውዑ ስምየ ፣

ስሜን ለጠሩ ወገኖች እነሆ እኔ አለሁ እላቸዋለሁ ፤

፪፡ ወኮሉ አሚረ እሰፍሕ እደውየ ለሕዝብ ዐላውያን ወከሃድያን እለ ኢሖሩ በፍኖተ ጽድቅ ፣

ወንጀለኞች ለሆኑ በውነተኛ ሕማ ፀንተው ለማይኖሩ ለከሃድያን እጄን እዘረጋለሁ፤ እጅ ለነገር ያግዛልና፤ አንድም ለዐላውያን ለከሃድያን እጄን ዘርግቼ እሰቀ ላለሁ፣ ምነው ኮሎ አሚረ አለ፤ (ጥቅስ) ምዕረ ሦዐ ርእሶ እንዲል ዕብ. ፱ ÷ ፳፮፤ የተሰቀለ አንድ ቀን በዕለተ ዓርብ አይደለምን፣ ስለምን እንዲህ አለ ቢሉ፣ አንድ ቀን በዕለተ ዓርብ የተሰቀለው የዘለዓለም ዋጋ የሚያሰጥ ስለሆነ እንዲህ አለ ፤

ወተለዉ ኃጢአቶሙ ፣

ኃጢአታቸውን ተከተሉ ማለት ኃጢአት ሠሩ ፤

፫፡ ዝንቱ ሕዝብ ዘአምዕዑኒ ፣

እሉ ሕዝብ ሲል ነው፤ ያሳዘኑኝ እሊህ ወገኖች ፤

ወሦዑ ወዐጠኑ ለአጋንንት ፣

ለጣዖት የሠዉ፣ ለአጋንንት ያጠኑ ሰዎች ፤

፬፡ ወውስተ መቃብር ይትኤወሙ፣

በመቃብር ይጋደማሉ፣ አንድ ጊ በመቃብር የሚጋደሙ ፤

ወውስተ በዓታት ሀላምያን ፣

በዋሻ አለምን አለምን የሚሉ ናቸው ፤

ወይበልዑ ሥጋ ሐራውያ ፣

የእሪያውን ሥጋ ይበላሉ፤ አንድም የእሪያ ሥጋ የሚበሉ ናቸው፤

ወያረኵሱ ስመ መሥዋዕቶሙ ፣

የመሥዋዕታቸውን ስም ያረክሳሉ ማለት መሥዋዕታቸውን መሥዋዕተ ጣዖት ያሰኙታል፤ አንድም መሥዋዕተ ሳህም መሥዋዕተ በግዕ መባሉ ቀርቶ መሥዋዕተ እሪያ ያሰኙታል፤ አንድም የእሪያ ሥጋ በልተው መሥዋዕታቸውን ሰውነታቸውን ያጐሰቁላሉ ፤

ወንዋዮሙ

ንዋየ ቅድሳቱን ያረክሳሉ ፤

፭፡ እለ ይብሉ ረኀቁ እምኔነ ፣

ከእኛ ራቁ የሚሉ ናቸው ፤ አንድም ከእኛ ራቁ የሚሏቸው ናቸው፤

ወኢትቅረቡነ እስመ ንጹሓን ንሕነ፣

እኛ ንጹሓን ነንና ወደእኛ አትቅረቡ የሚሉ ናቸው ፤ አንድም

ወደእኛ አትቅረቡ የሚሏቸው ናቸው ፤

በእንተ ዝንቱ ጢሰ መዓትየ ይነድድ ከመ እሳት በላዕሌሆሙ በኵሉ መዋዕል ፣

ይነድድ ጢስ ግሥ ነው፤ ስለዚህ ነገር ተቈጥቼ ያመጣሁት መዓት መቅሠፍት ባለ በዘመኑ ሁሉ በላያቸው ላይ ይነዳል፤ አንድም መዓቴን አብዝቼ አመጣባቸዋለሁ ፤

፮፡ ናሁ ጽሑፍ ቅድሜየ ፣

እነሆ በፊቴ ተጽፏል ፤ አንድም ኃጢአታቸው በፊቴ ነው ፤

ወኢያረምም እስከ እፈዲ ወእትቤ ቀል ፣

ኃጢአት በሠሩ ሰዎች ፍዳውን እስካመጣ፣ እስክበቀል ድረስ ዝም አልልም

ወአገብእ ሎሙ ውስተ ሕዕኖሙ ኃጢአቶሙ ፣

በኃጢአታቸው የመጣባቸውን ፍዳ አስበብታቸዋለሁ፣ አስጐረጕሳቸዋለሁ ፤

ወዘአበዊሆሙ

ባባቶቻቸው ኃጢአት የመጣውን ፍዳ አስጐረጕሳቸዋለሁ ፤

፯፡ ይቤ እግዚአብሔር ለእለ የዐጥኑ ውስተ አድባር ወውስተ አውግር ፣

እግዚአብሔር እንዲህ አለ፤ በተራራ በኰረብታ የሚያጥኑትን፤

ወዘንጐጉኒ ፣

የሚያሸሟጥጡኝን ፤

እፈድዮሙ በከመ ምግባሮሙ ውስተ ሕዕኖሙ ፣

እንደ ሥራቸው መጠን ፍዳውን አመጣባቸዋለሁ ፤

፰፡ ከመዝ ይቤ እግዚአብሔር ፣

እግዚአብሔር እንዲህ አለ ፤

በከመ ይትረከብ ሕንባበ ወይን ውስተ አስካል ፣ ወይብሉ ኢታጥፍኦ እስመ በረከተ እግዚአብሔር ላዕሌሁ ፣

ወይን በዘለላው እንደሚገኝ የእግዚአብሔር በረከት በሱ ላይ አለና አታጥፋው እንደሚሉ ፤

ከመዝ እገብር በእንተ ዘተቀንየ ሊተ በበይነ ዝንቱ ከመ ኢያጥፍእ ፣

ስለዚህ ነገር እንዳላጠፋ ስለተገዛልኝ እንዲህ አደርጋለሁ ፤

፱፡ ወአመጽአ ዘርዐ ያዕቆብ ወዘርዐ ይሁዳ እለ ይወርሱ ደብረ መቅደስየ ፣

የመመስገኛዬ ቦታ ኢየሩሳሌምን የሚወርሱ የይሁዳን፣ የያዕቆብን ልጆች አመጣለሁ ፤

ወይወርሱ ኅሩያንየ ወአግብርትየ ፣

ወዳጆቼ ባሮቼ ኢየሩሳሌምን ይወርሳሉ ፤

፲፡ ወየኀድሩ ወይነብሩ ማዕከለ ያም፣

ጠላት ጠፍቶላቸው ተዘልለው ይኖራሉ ፤

www.ethiopianorthodox.org

ወአዕፃዳተ መራዕይ ፣

በመንጋው መሰማሪያ ፤

ወውስተ ቈላት ፣

በቈላ ፤

ወአዕፃዳተ ወፍር ዘሕዝብየ እለ ኀሠሡኒ ፣

በሕግ፣ በአምልኮት በሚሹኝ በወገኖቼ መሰማሪያ ቦታ ይኖራሉ፤ አንድም በሕግ፣ በአምልኮት የፈለጉኝ ወገኖቼ በሚሰማሩበት በኢየሩሳሌም አውራጃ በረድኤት ተጠብቀው ይኖራሉ ፤

፲፩፡ ወአንትሙሰ እለ ኀደግሙኒ ፣

በሕግ በአምልኮት የተዋችሁኝ እናንተን ግን ፤

ወረሳዕክሙ ደብረ መቅደስየ ፣

ኢየሩሳሌምን የዘነጋችሁ ፤

ወሠራዕክሙ ማዕደ ለአጋንንት ፣

ለአጋንንት ማዕድ የሠራችሁ፤

ወትቀድሑ ወይነ ለእለ በፃውዕ ወትመልዑ ፣

በምትሓት ፤ አንድም በጸውዖ ይላል ፤ ስመ አጋንንትን በመጥራት፣ ሙት እናስነሣለን ለሚሉ ሰዎች ወይኑን ቀድታችሁ ለምትመሉ እናንተን ግን ፤

፲፪፡ አነ እሜጥወክሙ ለኵናት ፣

እኔ ለጦር አሳልፌ እሰጣችኋለሁ ፤

ወትመውቱ ኵልክሙ በመጥባሕት፣

ሁላችሁም በጦር ትሞታላችሁ፣ ትጠፋላችሁ ፤

እስመ ጸዋዕኵክሙ ወኢያውሣእክሙኒ ፤

በነቢያት በካህናት አድሬ ብጠራችሁ አልመለሳችሁልኝምና ፤

ወነበብኩክሙ ወተጸመምክሙኒ ፣

በነቢያት በካህናት አድሬ ባስተምራችሁ ቸል ብላችሁኛልና ፤

ወገበርክሙ እኩየ ቅድሜየ ፣

በፊቴ ክፉ ነገር አድርጋችኋልና፤

ወኢፈቀድክሙ አድኅንክሙ ፣

አድናችሁ ዘንድ አልወደዳችሁምና ፤

፲፫፡ በእንተ ዝንቱ ከመዝ ይቤ እግዚአብሔር ፣

ስለዚህ ነገር እግዚአብሔር እንዲህ አለ ፤

እለ ይትቀነዩ ሊተ ይበልዑ ወአንትሙሰ ትርኅቡ ፣

ለኔ የሚገዙልኝ ሰዎች ይበላሉ፤ እናንተ ግን ትራባላችሁ ፤

እለ ይትቀነዩ ሊተ ይሰትዩ ወአንትሙሰ ትፀምዑ ፣

ለኔ የሚገዙልኝ ሰዎች ይጠጣሉ፣ እናንተ ግን ትጠማላችሁ ፤

፲፬፡ እለ ይትቀነዩ ሊተ ይትፌሥሑ ወአንትሙሰ ተኀሥሩ ፣

ለኔ የሚገዙልኝ ሰዎች ደስ ይላቸዋል ፤ እናንተ ግን ትዋረዳላችሁ ፤

እለ ይትቀነዩ ሊተ ይትፌሥሑ በኀሤት ወአንትሙሰ ትግዕሩ በመንሱት፣

ለኔ የሚገዙልኝ ሰዎች ፈጽሞ ደስ ይላቸዋል፤ እናንተ ግን በመከራ ተይዛችሁ ታዝናላችሁ ፤

ወበሕማመ ልብክሙ ወበቅጥቃጤ ነፍስክሙ ተዐወይዉ ፣

በልቡናችሁ ኀዘን ሰውነታችሁ በመከራ በመቀጥቀጡ ትጮሃላችሁ ፤

፲፭፡ ወኀደግሙ ስመክሙ ፣

ሕዝበ እግዚአብሔር መባልን ተዋችሁ ፤

ወተፀገብክምዎሙ ለኅሩያንየ ፣

ወዳጆቼ ነቢያት ካህናትን ሰለቻችኋቸው፣ ጥልቅልቅ አላችኋቸው ፤

ወለክሙሰ ያጠፍአክሙ እግዚአብሔር፣

እናንተን ግን እግዚአብሔር ያጠፋችኋል ፤

ወይሰሚ ስመ ሐዲሰ ለእለ ይትቀነዩ ሎቱ ፣

ለሚገዙለት ሰዎች አዲስ ስም ያወጣላቸዋል ማለት ትሩፋን ይሰጣቸዋል ፤

፲፮፡ ወይትባረኩ ዲበ ምድር ፣

በኢየሩሳሌም ይከብራሉ ፤

እስመ ይባርክዎ ለአምላከ ጽድቅ ፣

የክብር ባለቤት እግዚአብሔርን ያመሰግኑታልና ፤

ወይረስዑ ሕማሞሙ ዘትካት ፣

የሰባውን ዘመን መከራ ይዘነጋሉ፤ አንድም ያምስቱን ሺህ ካምስት መቶ ዘመን መከራ ይዘነጋሉ ፤

ወኢይሔልይዎ በልቦሙ ፣

በልቡናቸውም አያስቡትም ፤

፲፯፡ አመ ይከውን ሰማይ ሐዲሰ ወምድርኒ ሐዳሰ ፣

ሰማይ ፣ ምድር በታደሱ ጊዜ ማለት ሰማይ ዝናም ለዘር፣ ጠል ለመከር በሰጠ ጊዜ ፣ ምድርም የዘሩባትን ባበቀለች ፣ የተከሉባትን ባጸደቀች ጊዜ ፤ ማብቀላቸውን ተሐድሶ፣ አለማብቀላቸውን ብሌት ብሎ ተናገረ ፤ አንድም ፀሐይ ጨረቃ ከዋክብት መመለካቸውን በተዉ ጊዜ ፣ ወምድርኒ፣ ዕፀው አዕባንም መመለካቸውን በተዉ ጊዜ፣ መመለካቸውን ብሌት፣ አለመመለካቸውን ተሐድሶ ፣ ብሎ ተናገረ ፤ አንድም አዲስ ሊቀ ካህናት በተሾመ ጊዜ፣ አዲስ ንጉሥ በነገሠ ጊዜ፤ አንድም ልዑላኑ ትሑታኑ በሚጠት በታደሱ ጊዜ ፤ አንድም መለኮት ሥጋን በተዋሃደ ጊዜ ፣ ሥጋም

www.ethiopianorthodox.org

(ትስብእትም) መለኮትን በተዋ
ሃደ ጊዜ ፤ አንድም ሰማይ ምድር
በታደሱ ጊዜ ፣ ነቢያተ ሐሰት ፣
ካህናተ ጣዖት ለጣዖት ሲሠዉ
ምድርን በደሙ ፣ ሰማይን በጢሱ
አስተራኵሰውት ነበር ፤ ምድርን
ሠላሳ ሦስት ዓመት በኪደተ
እግር ቀድሳታል ፣ ሰማይንም
በሰባት ክንድ ከስንዝር መስቀል
ከፍ ብሎ ተሰቅሎ ቀድሶታልና ፤
አንድም ልዑላኑ ፣ ትሑታኑ በል
ጅነት በታደሱ ጊዜ ይረስዑ
ላለው ፣ ወኢይዜከሩ ብሎ ማንሻ ፤
አንድም እንዲህ ነውና ፤

ወኢይዜከሩ እንከ ዘቀዲሙ ፣

እንግዲህ ወዲህ የሰባውን ዘመን
መከራ አያስቡትም ፤ አንድም
ያምስቱን ሺህ ካምስት መቶ
ዘመን መከራ አያስቡትም ፤

ወኢይመጽአሙ በልቦሙ ፣

በልቡናቸው አይታሰባቸውም ፤

ዳዕሙ ትፍሥሕተ ወሐሤተ ይረክቡ
ውስቴታ ፣

በርሷ ፈጽሞ ተድላ ደስታ ያገ
ኛሉ እንጂ ፤

፲፰፤ ወአነሂ እገብር ለኢየሩሳሌም
ትፍሥሕተ ወሐሤተ ፣

እኔም ለኢየሩሳሌም ተድላ ደስ
ታን አደርጋለሁ ፤

ወእትፌሣሕ በሕዝብየ ፣

በወገኖቼ ደስ ይለኛል ፤

፲፱፤ ወኢይሰማዕ እንከ በውስቴታ
ቃለ ብካይ ወቃለ ዐውያት ፣

እንግዲህ ወዲህ በውስጧ የጩ
ኸት ፣ የልቅሶ ድምፅ አይሰማም ፤

፳፤ የሐንፁ አብያተ ወይነብሩ ውስ
ቴቶን ፣

ተሐንፁ ቤተ ወኢትነብሩ ብሎ
ነበርና ፣ ቤት ይሠራሉ በውስጡ
ይኖራሉ ፤

ወይተክሉ ወይነ ወይበልዑ ቀምሐ ፣

ትተክሉ ወይነ ወኢትበልዑ ብሎ
ነበርና ፣ ወይን ይተክላሉ ፍሬ
ውን ይበላሉ ፤

፳፪፤ ወይከውን መዋዕሊሆሙ ለሕ
ዝብየ ከመ መዋዕለ ዕፀ ሕይወት ፣

የወገኖቼ ዘመናቸው እንደ ዕፀ
ሕይወት ዘመን ይሆናል ፤ ዕፀ ሕይ
ወት እየታደሰ እንዲኖር ታድ
ሰው ይኖራሉ ፤ አንድም ከመ
መዋዕለ ፀሐይ ፤

ፀሐይ እንዲኖር ይኖራሉ ፤ አን
ድም ፣ ከመ መዋዕለ ሰማይ ፣
ጠፈር በአድማስ ላይ ፀንቶ እንዲ
ኖር እንደዚያ ፀንተው ይኖራሉ ፤
አንድም የምዕመናን ዘመናቸው
ፀሐየ ጽድቅ ክርስቶስ የኖረውን
ያህል ይኖራል ፤

ወይረስዑ ኀሩያንየ ተግባረ ዕደዊሆሙ ፣

የመረጥኋቸው እስራኤል የእጃ
ቸውን ሥ[illegible]

፳፫፤ ወኢይፃምዉ እንከ ለከንቱ ፣

እንግዲህ ወዲህ ጣዖት ለመሥ
ራት አይደክሙም ፤

ወኢይወልዱ ለመርገም ፣

ለመርገም ሊሆን ልጅ አይወል
ዱም

እስመ ዘርዕ ቡሩክ ዘእምኀበ እግዚ
አብሔር እሙንቱ ፣

ከእግዚአብሔር የተገኙ ዘር ቡሩክ
ናቸውና ፤

፳፫፤ ወዘእንበለ ይክልሑ እሠጠዎሙ
አነ ፣

ሳይጮኹ እኔ እመልስላቸዋለሁ ፤

ወሶበ ይነቡ እብሎሙ ነዮ ሀሎኩ ፣

በተናገሩ ጊዜ እነሆ እኔ አለሁ
እላቸዋለሁ ፤

፳፬፤ ወውእተ አሚረ ተኮላት ወአ
ባግዕ ይትረዐዩ ኀቡረ ፣

ያንጊዜ ተኵላዎችና በጐች ባን
ድነት ይሰማራሉ ማለት ፣ አሕዛ
ብና እስራኤል በሚጠት አንድ
ይሆናሉ ፤

ወአንበሳሂ ከመ ላህም ኀሠረ ይቀምሕ ፣

አንበሳም እንደ ላም ገለባን ይቅ
ማል ማለት አሕዛብ እንደ እስራ
ኤል ሕገ ትሕትና አሪትን ይማ
ራሉ ፤ ደግ መጽሐፍ በጀመረበት
መጨረስ ልማድ ነውና በጀመ
ረበት ጨረሰ ፤

ወአልቦ ዘየሐስም በደብረ መቅደስየ
ይቤ እግዚአብሔር ፣

በመመስገኛዬ ቦታ በኢየሩሳሌም
ክፉ ነገር የሚያደርግ የለም አለ
እግዚአብሔር ::

ምዕራፍ ፷፮

፩፤ ከመዝ ይቤ እግዚአብሔር ሰማ
ይኒ መንበርየ ወምድርኒ መከየደ
እገርየ ፣

እግዚአብሔር እንዲህ አለ ፤ ሰማይ
ዙፋኔ ነው ፤ ምድርም የእግሬ
መመላለሻ ናት ፤ እስራኤል በባ
ቢሎን ሳሉ ቤተ መቅደስን ሳን
ሠራ ቤታችንን አንሠራም ብለው
ተሳሉ ፤ ከወጡ በኋላ ቤታቸውን
እየሠሩ ኢኮነ ጊዜሁ ለሐኒፀ ቤተ
እግዚአብሔር እያሉ ቤተ መቅደ
ስን የማይሠሩ ሁነዋል ፤ ዳዊት
እመ እግዚአብሔር ኢሐነፀ ቤተ
ከንቶ ይፃምዉ እለ የሐንፁ ብሎ
ዘልፏቸዋል ፤ መዝሙር ፻፳፮ ÷
፩ ፤ ሐጌም ለምንት ትብሉ ኢኮነ
ጊዜሁ ለሐኒፀ ቤተ እግዚአብሔር
ብሎ ዘልፏቸዋል ፤ ሐጌ ም. ፩÷፪
ከዚህም ኢሳይያስ እንዲህ አለ ፤

አየኑ ቤተ ተሐንፁ ሊተ ፣

እንሥራልህስ ብትሉ ቤተ መቅ
ደስን ወዴት ትሠሩልኛላችሁ ፤

ወአየኑ ማኀደር ለምዕራፍየ ፣

ማደሪያዬ ሊሆን የምትሠሩልኝ
ቤተ መቅደስ ወዴት ነው ፤

www.ethiopianorthodox.org

፪፡ ዝንቱሰ ኵሉ ግብረ እደውየ ፣
ይህ ሁሉ የእጄ፣ የቃሌ ፍጥረት ነው ፤
ወዝንቱ ኵሉ ዘዚአየ ውእቱ ፣
ይህ ሁሉ የኔ ገንዘብ ነው ፤
ይቤ እግዚአብሔር ኀበ መኑ እንከ እኔጽር ፣
እኔስ በዓይነ ምሕረት ወደማን እመለከታለሁ ፤
ዘእንበለ ኀበ የዋህ ወፅምው ፣
የዋህ ዕጉሥ ወደሆነው ነው እንጂ፤
ውነበ ዘይርዕድ እምቃልየ ፣
ከቃሌ የተነሣ ወደሚርድ፣ ወደ ሚንቀጠቀጥ ነው እንጂ ወደ ማን እመለከታለሁ ፤
፫፡ ወኃጥአሰ ዘይሠውዕ ሊተ ላህመ ከመ ዘይጠብሕ ሊተ ከልበ ፣
ላም የሚሠዋልኝ ኃጥእ ሰው ግን ውሻ እንደሚሠዋልኝ ሰው ነው፤
አልቀበለውም ፤
ወዘሂ ያበውአ ሊተ ስንዳሌ ከመ ሐራ ውያ ፣
በኃጢአት ሳለ ልጠ ጕርዶ የወጣ ስንዴ የሚያቀርብልኝ ሰው እሪያ እንደሚሠዋልኝ ሰው ነው አልቀበለውም ፤
ወዘሂ ይሁብ ስኒነ ለተዝካርየ ፣
ለስሜ መታሰቢያ ሊሆን ነጭ ዕጣን የሚያቀርብ ሰው የውሻ

ፋንድያ እንደሚሠዋ ነው አልቀበለውም ፤
እሙንቱሰ አብደሩ ፍኖቶሙ ወርኵሶሙ ዘአፍቀረት ነፍሶሙ ፣
እነሱም ልቡናቸው የወደደችው ጣዖቱን ኃጢአቱን ወደዱ ፤
፬፡ ወአነሂ እፈቅድ አኀሥሮሙ ፣
እኔም ላዋርዳቸው እወዳለሁ፤
ወእትበቀሎሙ በእንተ ኃጢአቶሙ፣
ስለ ኃጢአታቸው ተበቅዬ ላጠ ፋቸው እወዳለሁ ፤
እስመ ጸዋዕክዎሙ ወኢያውሥኡኒ፣
በነቢያት፣ በካህናት አድሬ ብጠ ራቸው አልመለሱልኝምና ማለት በነቢያት በካህናት አድሬ ባስተ ምራቸው አልሰሙኝምና ፤
ወነበብክዎሙ ወኢሰምዑኒ ፣
በነቢያት፣ በካህናት አድሬ ብና ገራቸው አልሰሙኝም ፤
ወገብሩ እኩየ በቅድሜየ ፣
በፊቴ ክፉ ነገር አደረጉ ፤
ወአፍቀሩ ዘጸላእኩ አነ ፣
እኔ የጠላሁትን ወደዱ ፤
፭፡ ስምዑ ቃለ እግዚአብሔር እለ ትርዕዱ እምቃሉ ፣
ከቃሉ የተነሣ የምትርዱ፣ የም ትንቀጠቀጡ የእግዚአብሔርን ነገር ስሙ ፤

በልዎሙ አኀዊነ ለጸላእትክሙ ፣
ጠላቶቻችሁን ወንድሞቻችን በሏ ቸው ፤
ከመ ይሰባሕ ስመ እግዚአብሔር ፣
የእግዚአብሔር ስም ይመሰገን ዘንድ እኛ እንጂ ስንጠላቸው የሚ ወዱን ፈጣሪያቸው ደግ ቢሆን ነው ብለው ፤
፮፡ ቃለ እግዚአብሔር ይቤ ፣
የእግዚአብሔር ቃል እንዲህ አለ ፤
መኑ ርእየ ከመዝ ፣
እንዲህ ያለ ነገር ያየ ማነው፤
፯፡ ከመ ይእኀዝ ማሕምም ለአሐቲ ብእሲት ፣
አንዲቱን ሴት ምጥ እንዲይዛት፤
ወከመ ወለደት ብዙኀ ሕዝበ በአሐቲ ሰዓት ፣
ባንዲት ሰዓት ብዙ ወገኖችን እንደ ወለደች ያየ ማነው ፣
፰፡ ወመኑ ሰምዐ ከመዝ፣
እንዲህ ያለ ነገር የሰማ ማነው፤
ይትወለዱኑ ሕዝብ በምዕር ፣
ብዙ ወገኖች ባንድ ጊዜ ይወለ ዳሉን ፤
እስመ ወለደት ጽዮን ደቂቃ ወአዋ ልደ ፣
ጽዮን ወንድ ልጅ ሴት ልጅ ወል ዳለችና ማለት መቃብር ጥም ቀት ፤
፱፡ አነ ወሀብኩኪ ትፍሥሕተ ወኀ ሤተ ፣
እኔ ተድላ ደስታውን ሰጠሁሽ፤
ወአንቲኒ ኢተዘከርክኒ ፣
አንቺም በሕግ በአምልኮት አላ ሰብሽኝም ፤
ይቤ እግዚአብሔር አኮኑ አነ ዘአ ወልድ ወእፈጥር መካነ ፣
እግዚአብሔር እንዲወልዱ የማ ደርግ፣ መካንንም የፈጠርሁ እኔ አይደለሁምን አለ፤ ሂኖክ ምክ ንትሰ ኢተውህባ ለብእሲት አላ በግብረ እደዊሃ ትመውት ዘእ ንበለ ውሉድ አለ፤ ከዚህ እንዲህ አለ፣ አይጣላም ቢሉ አይጣላም፤ ነገር እንደ ሂኖክ ነው፣ ምክንት መሰጠቱ በደዌ፣ በኃጢአት ምክ ንያት ነው ፤ ከዚህ ግን እንዲህ ማለቱ እስክትወልድ ድረስ ያለ ውን ዘመን ነው፣ (ጥቅስ) ሣህሉ ለእግዚአብሔር በጊዜሁ እንዲል (መዝ. ፷፮ ÷ ፬) ያለጊዜው አይ ደረግምና፤ አንድም ጽዮንን በሚ ጠት ልጅ እንድትወልድ በዔዋዌ መካን የማደርጋት እኔ ነኝ፤ አን ድም ዘአወልድ መካነ በመቃብር ወእፈጥር በትንሣኤ ፤
፲፡ ይቤ እግዚአብሔር አምላክኪ ተፈ ሥሒ ኢየሩሳሌም ፣
ኢየሩሳሌም ፈጣሪሽ እግዚአብ ሔር ደስ ይበልሽ አለ ፤

www.ethiopianorthodox.org

ወተነሥዩ ኮልክሙ እለ ታፈቅርዋ፣
የምትወጺት ሁሉ ደስ ይበላችሁ፤
ተፈሥሑ ተፍሥሕተ ኮልክሙ እለ ለሀውክምዋ ፣
የምታዝኑላት ሁሉ ፈጽሞ ደስ ይበላችሁ ፤
፲፩፤ ከመ ትልሐቁ ወትዕገቡ እም አጥባተ ትፍሥሕታ ፣
ከደስታዋ ጡት ትጠግቡ ዘንድ ማለት በሁለቱ ጽላት የተጻፉ ሕግጋትን ከመጠበቃችሁ የተነሣ ደስ ይላችሁ ዘንድ ፤
ወከመ ትትሐፀኑ ፣
በረድኤት ትፀኑ ዘንድ ፤
ወትትፈሥሑ በክብራ ፤
በክብሯ ደስ ይላችሁ ዘንድ ፤
፲፪፤ ከመዝ ይቤ እግዚአብሔር ናሁ አነ አመጽእ ሎሙ ሰላመ ከመ ውኂዝ፣
እነሆ እግዚአብሔር እንዲህ አለ፤ ፍቅር አንድነትን እንደ ፈሳሽ ውሀ አብዝቼ አመጣላቸዋለሁ፤
ወከመ ማዕበለ ባሕር ክብረ አሕዛብ፣
የአሕዛብን ባለጸግነት እንደ ማዕበለ ባሕር አብዝቼ አመጣላቸዋለሁ ፤
ወይፀውርዎሙ ለደቂቆሙ በመትከፍቶሙ ፣
ትሩፋን ልጆቻቸውን እሸከክ የቀላጥም እየተሸከሙ ያመጧቸዋል፤ አንድም ምዕመናን ልጆቻቸውን አጥምቁልን ፣ አቀሩቡልን እያሉ ያመጧቸዋል ፤
፲፫፤ ወአነ አስተፌሥሐክሙ በኢየሩሳሌም ፣
እኔ በኢየሩሳሌም ደስ አሰኛች ኋለሁ ፤
ወትሬእዩ ወይትፌሥሐክሙ ልብ ክሙ ፣
ተድላውን ፣ ደስታውን ታያላችሁ፤ ልቡናችሁንም ደስ ይለዋል፤
፲፬፤ ወታስተርኢ እደ እግዚአብሔር ለእለ ይፈርህዎ ፣
ለሚፈሩት፣ ለሚያመልኩት ለትሩፋን ሥልጣነ እግዚአብሔር ትገለጣለች ፤
ወያጠፍአሙ ለዐላውያን ፣
የባቢሎንን ሰዎች ያጠፋቸዋል፤ አንድም እነ ሰናክሬምን፣ ዕርዓውያንን ያጠፋቸዋል፣ አንድም እለ ሐሳዊ መሢሕን ያጠፋቸዋል ፤
፲፭፤ ናሁ እግዚአብሔር ይመጽእ ከመ እሳት ፣
እነሆ እግዚአብሔር እንደ እሳት በማስፈራት ይመጣል ፤
ወከመ ዐውሎ ሠረገላሁ ፣
ሠረገላ መዓቱም እንደ ዐውሎ ፈጥኖ ይመጣል ፤

ከመ ይትበቀሎሙ በመዓቱ ለብዙኃን አሕዛብ ፣
ብዙ አሕዛብን በመዓቱ ተበቅሎ ያጠፋቸው ዘንድ ፤
፲፮፤ እስመ በእሳተ እግዚአብሔር ይትኴነኑ ወበኲናቱ ኵሉ ዘነፍስ ፣
ሥጋዊ ደማዊ ሁሉ በእሳተ መዓቱ በጦር ይጠፋሉና ፤
እስመ ብዙኃን ቅቱላን እምኀበ እግዚአብሔር ፣
ከእግዚአብሔር ዘንድ ታዝዘው የሞቱ ብዙ ናቸውና ፤ አንድም እስመ በእሳተ እግዚአብሔር ይትኴነኑ ፣ በእሳተ መዓቱ ይጠፋሉና ፣
ወበኲናት ኵሉ ዘነፍስ ፣
ሥጋዊ ደማዊም ሁሉ በጦር ይቀጣሉና ፤
እስመ ብዙኃን ቅቱላን እምኀበ እግዚአብሔር ፣
ከእግዚአብሔር ዘንድ ታዝዘው የሞቱ ብዙ ስለሆኑ በመቅሠፍተ እግዚአብሔር ይቀጣሉና፣ ናሁ አነ አመጽእ ሎሙ ሰላመ ከመ ውኂዝ ብለህ እሠር ፤ የሥጋው መከራ ከነፍሱ ፍዳ ያደርሰዋልና፣ በእሳተ እግዚአብሔር አለ ፤ አንድም ይህ ለዕርዓውያን አያሳትትም፤ አንጥያኮስ ቀኖስለ ሥጋ ወጥቶበት ምላሱ ሽቶ ተልቶ እንደ እሳት እያቃጠለው ሞቷል፤ አንድም እነ ሐሳዊ መሢሕ ሐተታ እንደ ባቢሎን ሰዎች ፤
፲፯፤ ወናሁ አነ አመጽእ ወአስተጋብዕ ኵሎ አሕዛበ ፣
እነሆ እኔ አሕዛብን ሁሉ ሰብስቤ አመጣለሁ ፤
ወይመጽኡ ወይሬእዩ ስብሐትየ ፣
መጥተውም ጌትነቴን፤ አንድም ተአምራቴን ያያሉ ፤
፲፰፤ ወእገብር ሎሙ ትእምርተ ፣
ሞተ ብልጣሶርን አደርግላቸዋለሁ ፤
ወእፈንዎሙ ውስተ አሕዛብ ለእለ ድኅኑ እምውስተ ሞት ውሉድ ፣
ከሞት የቀሩትን ልጆች ወደ አሕዛብ አስማርኬ እሰዳቸዋለሁ፤ አንድም ከሞት ለቀሩ ልጆች በብሔረ አሕዛብ ተአምራት አደርግላቸዋለሁ፤ አንድም ከሞት ለቀሩ ለትሩፋን ክብርን ረድኤትን እሰድላቸዋለሁ ፤ አንድም ውሉድ ይላል በሉድም ላሉ ሰዎች ፤
ውስተ ተርሴስ ወፋዩድ ወሞሳሕ ወቶቤል ወዔላድ ፣
ወደነዚህ ሁሉ አገሮች እሰዳቸዋለሁ ፤
ወውስተ ደሰያት ዘርኁቅ ፣
በሩቅ ወደ አሉ ደሴቶች እሰዳቸዋለሁ ፤

www.ethiopianorthodox.org

እለ ኢሰምዑ ምግባርየ ወኢርእዩ ስብ
ሐትየ ፣

ሥራዬን ወዳልሰሙ፣ ጌትነቴን
ወዳላዩ ወደነዚህ እሰዳቸዋለሁ፤

ወይነግሩ ስብሐትየ ለአሕዛብ ፣

እስራኤል በሰባ ዘመን ጌትነቴን
ለአሕዛብ ይናገራሉ ፤

፲፱፡ ወያመጽእዎሙ ለደቂቅኪ ወለ
አዋልድኪ ኅቡረ ፣

ወንዶች ልጆችሽን፣ ሴቶች ልጆ
ችሽን ባንድነት ያመጧቸዋል፤

ወያመጽኡ አምኃየ ውስተ ሀገር ቅድ
ስት ፣

እጅ መንሻውን ወደ ከበረች አገር
ወደ ኢየሩሳሌም ያመጣሉ ፤

ወበከመ የዐርጉ ሊተ ደቂቀ እስራኤል
መሥዋዕተ ወቍርባነ ፣

የእስራኤል ልጆች መሥዋዕቱን
ቍርባኑን እንዲያቀርቡልኝ ፤

ከማሁ የዐርጉ ሊተ ኵሎሙ አሕዛብ
ይቤ እግዚአብሔር ፣

አሕዛቡ ሁሉ መሥዋዕቱን፣ ቍር
ባኑን ያቀርቡልኛል አለ እግዚ
አብሔር ፤

፳፡ ወአነሥእ እምውስቴቶሙ ካህናተ
ወሌዋውያነ ይቤ እግዚአብሔር ፣

ካህናትን ፣ ሌዋውያንን ከነዚያ
ወገን አስነሣለሁ አለ እግዚአብ
ሔር ፤

፳፩፡ በከመ እገብር ሰማየ ሐዲሰ ወም
ድረ ሐዲሰ ዘይነብር ቅድሜየ ፣

በፊቴ ፀንቶ የሚኖር ሰማይ
ምድር እንዲታደስ አደርጋለሁ፣
ማለት ሰማይ ዝናም ለዘር ጠል
ለመከር ይሰጣል፣ ምድርም የዘ
ሩባትን ታበቅላለች፤ የተከሉባ
ትን ታጸድቃለች ብዬ የተናገ
ርሁት፤ አንድም ፀሐይ ጨረቃ
መመለካቸውን ይተዋሉ ብዬ
የተናገርሁት፤ አንድም ልዑላኑ
ትሑታኑ በሚጠት ይታደሳሉ
ብዬ የተናገርሁት ፀንቶ እንዲ
ኖር ፤

ይቤ እግዚአብሔር ከማሁ ይከውን
ዘርዕክሙ ወስምክሙ ፣

ልጆቻችሁ ስማችሁ በሚጠት
ፀንተው ይኖራሉ ፤

ወሥርውክሙ ፣

አባትነታችሁም ፀንቶ ይኖራል
አለ እግዚአብሔር ፣

ወይመጽኡ ኵሉ ዘነፍስ ቅድሜየ
ወይሰግዱ ሊተ በኢየሩሳሌም ይቤ
እግዚአብሔር ፣

ሥጋዊ ደማዊ ሁሉ በፊቴ ይመ
ጣሉ፤ በኢየሩሳሌምም ይሰግዱ
ልኛል ይላል እግዚአብሔር ፤

፳፪፡ ወይመጽኡ ወይሬእዩ አብድን
ቲሆሙ ለእለ ዐለዉኒ ፣

መጥተው የወነጀሉኝ የነሰናክ
ሬምን ሬሳ ያ[illegible]

ንጥያኮስን ሬሳ ያያሉ፤ አንድም
የእለ ሐሳዊ መሢሕን ሬሳ ያያሉ፤

፳፫፡ ወዕፄሆሙኒ ዘኢይነውም ወእ
ሳቶሙ ዘኢይጠፍእ ፣

የባቢሎን ሰዎች ፍዳቸው የማ
ያንቀላፋ እሳቱ የማይጠፋ ነው፤
የሥጋው መከራ ከነፍሱ ያደር
ሰዋልና ፤ አንድም የፅርዓውያን
ፍዳቸው ትሉ የማያንቀላፋ ፣
እሳቱ የማይጠፋ ነው ፣ አንጥያ
ኮስ ቍስለ ሥጋ ወጥቶበት ምላሱ
ተልቶ ሸቶ እንደ እሳት እያቃ
ጠለው ሙቷልና እንዲህ አለ ፤
አንድም የእለሐሳዊ መሢህ ፍዳ
ቸው ትሉ የማያንቀላፋ፣ እሳቱ
የማይጠፋ ነው፤ የሥጋው መከራ
ከነፍሱ ፍዳ ያደርሳልና ፤

፳፬፡ ወይከውኑ አርአያ ለኵሉ ዘሥጋ፣

ለሥጋዊ ለደማዊ ሁሉ አብነት
ይሆናሉ፤ አብነት ይሆናሉስ ብሎ
አያጠፋቸውም ብሎ፣ ከሆነ በኋላ
እንዲህ አለ ፤ አንድም የባቢሎን
ሰዎች ለሥጋዊ ለደማዊ ሁሉ
አምሳል መርገፍ ይሆናሉ ፤ አን
ድም ፅርዓውያን ለሥጋዊ ለደ
ማዊ ሁሉ አምሳል መርገፍ ይሆ
ናሉ ፤ አንድም እለ ሐሳዊ መሢህ
ለሥጋዊ ለደማዊ ሁሉ አምሳል
መርገፍ ይሆናሉ፤ የባቢሎናው
ያን የፅርዓውያንስ ይሁን፣ አሁን
እየተነገረ ለሌላው አብነት እየ
ሆነ ይኖራል ፤ እለ ሐሳዊ መሢ
ሕማ ኋላ አይደሉም ቢሉ ዛሬ
እየተነገረ አብነት ሲሆን የሚ
ኖር ስለሆነ እንዲህ አለ ::

ተፈጸመ መጽሐፈ ኢሳይያስ
ነቢይ በረከቱ ወበረከተ አምላኩ
የሀሉ ምስሌነ ለዓለመ ዓለም
ወስብሐት ለእግዚአብሔር ::

አሜን ::

www.ethiopianorthodox.org